# ገድለ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ

## የቅደስት ወለተ ጴጥሮስ ገድል
## በግዕዝና በአማርኛ

**መታሰቢያነቱ ለሬማ መድኃኔዓለም**
**ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ አንድነት ገዳም**

## የቅድስት ወለተ ጴጥሮስ አጭር ታሪክ

እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ኢትዮጵያዊት ናት የተወለደችበት ቦታ ደዋሮና ፈጠጋር ይባላል። የአባቷ ስም ባሕር ሰገድ የእናቷም ስም ክርስቶስ ዕበያ ይባላል የንጉሥ ሱስንዮስ የአማካሪዎቹ አለቃ የሚሆን መልክአ ክርስቶስ የሚባል ታላቅና ባለ ጸጋ የሆነ ሰውን አግብታ ሦስት ልጆች ወለደችለትና አቤቱ ፈጣሪየ ሆይ እነዚህ ልጆቼ አንተን የማያስደስቱ ከሆነ በሞት ውሰዳቸው ብላ ሦስቱም ልጆቿ ሞቱ ባለቤቷም እጅግ እየወደዳት እርሷ ይህ ዓለም እንደ ሣር ያልፋል ብላ ከሞላ ሀብቷ ተለይታ መንና ወደ ባሕር ዳር ገዳማትና ወደ ዋልድባ ገዳም ሄዳ ብዙ ተጋድሎን ተጋደለች በሃይማኖትም ምክንያት ወደ ጉምዝ አገር ተሰዳ በነደደ እሳት ውስጥ ተጨምራ እሳቱ ሳያቃጥላት ወጥታለች ከዚያ በኋላ ሰባት ገዳማትን አቅንታለች ለብዙ ጊዜ ከሰባት መቶ ካላነሱ ወንዶች መነኮሳትና ሴቶች መነኮሳይያት ላይ እመ ምኔት ሁና ተሹማ አስተዳድራለች ምግቧ የመረረ ቅጠልና ኮሶ አመድ ነበር በምታርፍበትም ጊዜ የብርሃን ምሰሶ ከምድር እስከ ሰማይ ተተክሎ በመላ ዓለም ተገልጦአል። ሰባት አክሊል ወርዶላታል ዝክሯን የሚዘክር በዓሏን የሚያከብር ስሟን የሚጠራ እንደሚማርና እንደሚድን ቃል ኪዳን ተቀብላለች የሬማ መድኃኔ ዓለምን ቤተ ክርስቲያን አሠርታ ኅዳር ዓሥራ ሰባት ቀን አርፋ በሬማ ተቀብራለች። የሬማም ገዳም የኢየሩሳሌም አምሳል ናት ።

እሳታሚ የሬማ ገዳም

፩ በስመ እግዚአብሔር ዘሀሎ እምቅድመ ዓለም ወይሄሉ እስከለዓለም ዘአልቦ ጥንት ወኢታፍጻሜት አምላክነ በመለኮቱ ወአቡነ በሂሩቱ ስብሔቲሁ ዘእምንቤሁ ወውዳሴሁ እምዚአሁ ዘይክል ኵሉ ወአልቦ ዘይስአኖ ንዌጥን ዘንተ መጽሐፈ ለዓለመ ዓለም አሜን ::

፪ ንጽሕፍ እንከ ንስቲተ እምዜና ስደታ ወእምብዙኅ ገድላቲሃ ወትሩፋቲሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እመ አዕናቍ አዕላፍ ቅድስተ ከናፍር ወአፍ ዘወጽአ ስሙዓቲሃ ውስተ ኵሉ ዓለም ወተሰብከ እምጽንፍ እስከ ጽንፍ እስመ ዜናሃ ረብሕ ለዘይሰምዖ ወበቁዔት ለዘያጸምኦ ወፍኖተ መድኃኒት ለዘይዴግኖ ወይተልዎ አኮ በተሃብሎ ወበትእቢት ወበኃሢሰ ስብሐት ብጡል ወውዳሴ ከንቱ ዘገበርኩ ዘንተ አላ እስመ አገበረተኒ ቅድስተ ክርስቶስ እንተ ነደ ልባ በፍቅረ ዚአሃ ወትቤለኒ ጸሐፍ ከመ ይኩን ክሡተ ለሰብእ ኅበ ዘኢበጽሐ ይብጻሕ ወይስማዕ ዘኢሰምዓ ወይትነበብ ዝክራ ለትውልደ ትውልድ እለይመጽኡ እምድኅሬነ እስከ ለዓለም።

፫ በከመ ይቤ በወንጌል ዘነገርኩክሙ በውስተ ጽልመት ንግርዎሙ በብርሃን ወዘአልኖስስኩ ለክሙ ውስተ እዝንክሙ ስብክዎ በዲበ አንስሕስት ሀገር እንተ ተሀንጸት መልእተ ደብር ኢትክል ተከብቶ ማኅቶት ከመ ይክድንዋ ታሕተ ከፊር አላ ያንብርዋ ዲበ ተቅዋማ ወታበርህ ለኵሎሙ እለ ውስተ ቤት ወበእንተዝ አነሂ ጽሑቁ እትልዎ እምጥንቱ እስከ ተፍጻሜቱ እንዘ አኮ ድልወት ሊተ እዝክር ስማ በአፉየ ርኩስ ወእጽሐፍ ዜናሃ በእዴየ።

፬ እስመ አእመርኩ ከመ ኢይረኩስ በርኩስተ ዚአየ ዜናሃ ንጹሕ ወቅዱስ ዳዕሙ ወይቀድስኒ ኢያንክዮ ምንተኒ ለሰማዒ ወኢይቶስ ሕ ቦቱ እበደ ዚአየ ለእመ ሰምዐ ወተወክፈ እምኔየ ዘንተ ዜና ንጹሐ ወቅዱሰ ወጥዑመ ዘወጽአ እምአፉየ እንዘ ርኩስ አነ በኵሉ ምግባርየ ወእኩየ ግዕዝ እንተ ውስጥየ ወዘአፍአየ ተገበርኩ ግብረ ሠናየ በከመ ይትጌበሩ ፫ቱ:መስተግብራን፡ እለሀለዉ ውስተዓለም ::

፭ ቦ አሐቲ እምነ ንጹሐን ወ፪ እምነ ርኩሳን ወያሠምሩ ሰብአ በተግባሮሙ ሠናይ እንዘ ኅሩማን ወእኩያን ወርኩሳን





፩ ቅድመ ዓለም በነበረ ዓለምን አሳልፎ እስከ ዘለዓለም በሚኖር መጀመሪያና መጨረሻ በሌለው በመለኮቱ ፈጣሪያችን በቸርነቱ አባታችን ምስጋና ከእሱ ዘንድ የሆነ ምስጋናም የሱ የሆነ ሁሉን በሚችል የሚሳነው ነገር በሌለው በእግዚአብሔር ስም አምነን ይህን መጽሐፍ እንጀምራለን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን።

፪ እንግዲህ አእናቁ የተባሉ የአእላፍ ቅዱ.ት ደናግል እናት አንደበቷ ፈጽሞ ልዩ የሆነ ስም አጠራሯ በዓለም ሁሉ የታወቀ ከዳርቻ እስከ ዳርቻ የተባረከች የተቀደሰች የእናታችን የወለተ ጴጥሮስ ዜና ስደቷንና ገድሏን ፈጽሞ ለሚሰማና ለሚያደምጥ ረብ ጥቅም ነው ለሚከተል የድኅነት ጐዳና ነው ይህን የጻፍኩት በትዕቢትና ብላሽ የሚሆን ውዳሴ ከንቱን በመፈለግ አይደለም በእሷ ፍቅር የተነሳ ልቧ የነደደ ቅድስተ ክርስቶስ ወደ አልደረሰበት ይድረስ ያልሰማ ይስማ ከእኛ በኋላ ለሚነሱ እስከ ዘለዓለም ለልጅ ልጅ ዘመን መታሰቢያዋ ሆኖ ይነበብ ዘንድ ጻፍ ብላ አስገደደችኝ።

፫ ጌታችን በወንጌል በጨለማ የነገርኳችሁን በብርሃን ተናገሩ በጆሮ የነገርኳችሁን በአደባባይ ስበኩ በተራራ ላይ የተሰራች ቤት መሸሸግ አትችልም መብራትን ከእንቅብ በታች እንደማያኖሩ ከፍ ካለ መቅረዝ ላይ እንደሚያኖሩና በቤት ውስጥ ላሉት ሁሉ እንደምታበራ እንደአለ እኔም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ተከታትየ ሳይገባኝ በረከሰች አንደበቴ ስሟን እጠራ ዘንድ ደነዝ በሆነ እጄም ዜናዋን እጽፍ ዘንድ ተጨነቅሁ።

፬ ንጹህና ቅዱስ የሆነ ዜና ገድሏ እኔን ይቀድሰኛል እንጂ በእኔ ርክስና እደማይረክስ አውቄያለሁና ለሚሰማም ምንም የኔ ርክስና ወደ እሱ አይሄድም ከአንደበቴ የወጣ ይህ የጣፈጠና የተቀደሰ የሷን ዜና የሰማውን ሁሉ ይቀድሳል ውስጤም ሆነ አንደበቴ የከፋ ነው በዓለም እንዳሉ እንደ ፫ቱ ሠራተኞች እኔም መልካም ሥራን ጀመርኩ።

፭ አንዷ ከንጹሐን ወገን ናት ሁለቱ ግን ከርኩሳን ወገን ናቸው በፍጥረታቸው ርኩሳን በፀባያቸው ክፉዎች ሁነው ሥራቸው

እሙንቱ እምግዕዘ ፍጥረቶሙ ዘውእቶሙ ንሕብ ወአድግ ወከልብ እምነ ንጹሐንስ ንህብ እኪት ይእቲ ወመሪር ህምዘ ወትነድፍ ሰብአ ወታሐምም ፈድፋደ ባሕቱ እንበይነ ተቀንዮታ ለሰብእ ትወፍር ገዳመ ወትተግህ ወታስተጋብእ አቅማኃ ጽጌያት ወትወርድ ካዕበ ኀበማይ ወትቀድሕ ወትበጽሕ ኀበ ኵሉ ዘይሤኒ ለተግባራ ወኢትትሃከይ ምንተኒ አላ ትተግህ ወትነሥእ እምኔሁ ወትገብሮ ውስተ መዝገብ አው ውስተ ጸላእተ ኰኵሕ ወንቅዓተ ኦም ዘተኃድር ቦቱ ወሶበ ይወርድ ላእሌሁ በረከት እምአርያም ይከውን ፀቃውዐ መዓር ጥዑመ ወለእመ ቀርበ ኀቤሃ ሰብእ እመሂ በዓለ ቤት አው እንግዳ ትነድፍ ወኢትምህክ ለመኑሂ ወኢተኃፍር እለሰ የአምሩ ግብራ ያጠይሱ ላዕሌሃ ወይነፍሑ መንገሌሃ ወትጉይይ እምፍርሀተ ጢስ ወትትገሐስ ወተኃድግ መዓረ ::

፮ ወይእተ ጊዜ ይነሥኡ እምኔሃ ወይጥዕም ሶበ ይበልዕዎ ወይምእዝ ሶበ ያዔንውዎ ወያሠተፌሥሕ ልበ ነገሥት ወመኳንንት ሶበ ይገብርዎ ሜሰ ወሰምዑሂ ይከውን ማኅቶተ ለቤተ ክርስቲያን ወለቤተ መግሥት ወኢየኃድግዎ ለመዓር በእንተ ሕማመ ኀምዛ ለንህብ ይእቲኒ ኢተኃዝን ወኢትትቀየም እመነሥእዋ ወኢትኃድግ ተግባሮ አላ ትወፍር ጌሠመ ከመልማዳ እስመ እዝዝት ይእቲ ለሰብእ ከማሃ አነሂ እንዘ እኩይ በምግባር ወእነድፍ ሰብአ በልሣንየ ወአሐምም ጥቀ በእንተ ተአዝዞትየ ለክሙ አስታጋብእ ናሁ እመጻሕፍት ቅዱሳት ወእምቃለ አበው ማእምራን ወእጽሕፍ ዜናሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘይጥዕም እምጸቃውዓ መዓር ወያስተፌሥሕ ልበ ሰብእ::

፯ አድግኒ ርኩስ ውእቱ ወባሕቱ ይጸውር ንዋየ ቅዱስ ዘቤተ እግዚአብሔር ወሲሳየ ለሰብእ ወኢየኃድግዎ ለንዋይ በእንተ ርኵሰቱ ለአድግ አላ ይነሥእዎ ዘይከውን ለቤተ እግዚአብሔር ወዘይትፈቀድ ለሲሳዮሙ ከማሁ አነሂ እጸውር ንዋየ ኅሩየ ወሲሳየ መንፈሳዌ ዘውእቱ ገድል ወትሩፋት ዘእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከልብኒ ርኩስ ውእቱ ወባሕቱ





ሰውን ያስደስታል እነሱም ንብ ውሻ አህያ ናቸው ከንፁሐን ወገን ንብ ክፉ ናት ሰውንም ትነድፋለች መርዟም የመረረ ነው እጅግም ታሳምማለች ነገር ግን ለሰው ስለምትገዛ ወደ ዱር ሄዳ አበባን ትቀስማለች ዳግመኛ ወደ ውሀ ወርዳ ውሀ ቀድታ ታርከፈክፍበታለች ምንም አትሰንፍም ተግታ በቀፎ ውስጥና የጉደጉደ እንጨት ወይም በዋሻ ውስጥ ማር ትሠራለች ከሰማይ በረከት በሱ ላይ በወረደ ጊዜ የጣፈጠ የማር ወለላ ይሆናል ባለቤቷም ሆነ እንግዳ ሰው ወደ እርሷ ቢቀርብ ትነድፈዋለች እንጅ አትራራለትም አታፍረውም ፀባይዋን የሚያውቅ እሳት አያይዞ ጢስ አጢሶ ወደ እሷ እፍ ሲል ማሩን ጥላ ትሸሻለች ::

፮ በዚያን ጊዜ ማሩን ይቆርጣል ሲበሉትና ሲያሸቱት ደስ የሚያሰኝ ጣዕም አለው ጠጅ በጠመቁ ጊዜ የነገሥታትና የመኳኳንንትን ልቡና ታስደስታለች እጩ ለቤተ ክርስቲያንና ለቤተ መንግሥት ጧፍ ሆኖ ያበራል ስለንቡ መርዝ ስላላት ቀረጠብኝ ብላ ሥራዋን አትተውም በማግስቱ ትሠማራለች ለሰው ታዛዥ ናትና እኔም እንደሷ ሰውን በምላሴ የምነድፍ ክፉ ስሆን ስለምታዘዝላችሁ እጅግ ተጨንቄ ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከአባቶች መምህራን ቃል አስማምቸ ጠቅሼ ከማዓር ወለላ ይልቅ የሰውን ልብ የሚያስደስት የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ዜና ገድሏን እጽፋለሁ::

፯ አህያም ርኩስ ሆኖ ሳለ የቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳትና ሰው የሚመገበውን እህል ይሸከማል ለቤተክርስቲያን የሚያስፈልገውን ለቤተክርስቲያን ለሰው የሚያስፈልገውን ለሰው ይወስዱታል እንጅ አህያው ርኩስ ስለሆነ እቃውን አይተውትም እንደዚሁ እኔም መንፈሳዊ ሲሣይ የሚሆን የእናታች ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ገድልና ትሩፋት እሸከማለሁ ውሻም ርኩስ ነው ነገር ግን ከባለቤቱ ጋር ወደ ዱር ተሰማርቶ ያድንና

የሐውር ገዳመ ምስለ እግዚኡ ኀበ ንዒው ወለእመ ርእየ ምዳቄ አው፡ካልአ፡እንስሳ፡ገዳም፡እመኒ፡ቆቅሐ፡አው፡ካልአነ፡አዕዋፈ፡እለ፡ይት በልዑ፡ ይረውፅ በትጋህ ወይእኅዝ ውእተ ጊዜ ይዘብጦ እግዚኡ ወያኃድግ፡ሎቱ ወይነሥእ ውእተ ዘተእኀዘ በአፈ ከልብ ወይበልእ ወኢየኃድጎ በእንተ ርኩሰቱ ለከልብ ፡፡

፰ ከማሁ፡አነሂ፡እኑዕ፡እመጻሕፍት፡ቅዱሳት፡ዜናሃ፡ወቅድስናሃ ለኀሪት፡ወብጽዕት፡እም ነወለተ፡ጴጥሮስ፡ወእጽሕፍ፡ለክሙ፡አንትሙ ኒ፡ተወከፍዎ፡በአሚን፡ከመ፡መሥዋዕት፡ንጹሕ፡ዘውእቱ፡ሥጋሁ፡ወደ ሙ፡ለመድኀን እንዘ ትብሉ አሜን በአሜን ወኢትመንንዎ በእንተ ርኩሰተ ዚአየ እኮኑ ትቤ አሪት ረከበ ሶምሳን መዓረ እምአፈ አንበሳ ምውት ዘቀተሎ ለሊሁ ወበልዐ በከመ መሰለ ወይቤ እምአፈ በላዒ ወጽአ መብልዕ ወእምነ ጽኑዕ ጣዕም ወካዕበ ሶበ ጸምአ ወቀርበ ለመዊት፡ሰአሎ ለእግዚአብሐር ወአውሐዘ ሎቱ እመንስከ አድግ ማየ ጥዑመ ወሰትየ ወገብአት ነፍሱ በከመ መሰለ ለሊሁ ወይቤ ስቴ ለጊዜ ጽምዕ ወንዋየ ሐቅል ለፀብዕ፡፡

፱፡ወለኤልያስኒ፡ነቢይ፡ኮነ፡ያመጽእ፡ሎቱ፡ሲሳዮ፡፡ቋዕ፡ኵሎ፡አ ሚረ፡ወይነሥእ፡ወይበልዕ፡ወኢያረኩሶ፡እመሰ፡ለእሉ፡ቅዱሳን፡ኢያር ኩስዎሙ፡እሙንቱ፡ርኩሳን፡አንትሙኒ፡ኢታረኵስዎ፡ለዝንቱ፡ዜና፡ዘ ወጽአ፡እምአፉየ፡ርኩስ፡ሊተስ፡እኮ፡ድልወት፡ሊተ፡እግበር፡ዘንተ፡እንዘ፡ኃ ጥእ፡ወአባሲ፡አነ፡ገላውዴዎስ፡እስመ፡ቅድስት፡ለቅዱሳን፡ወንጹሕት፡ለ ንጹሐን፡አላባሕቱ፡አገበረኒ፡ፍቅረ፡ዚአሃ፡ከመ፡እጽሐፍ፡ለክሙ፡ኀዳጠ ኣምብዙኅ፡አምጣነ፡ሕጸተ፡አእምሮትየ፡ወውሕደተ፡ሕሊናየ፡በአምጣነ፡ ትክለ፡ሰሚዓ፡ከመአፍ፡ድምቢጽ፡ዘትወርድ፡ኀበ፡ቀላየ፡ባሕር፡ወትሰቲ፡ መጠነ፡የአክላ፡ከመ፡ጽበተ፡ከርሣ፡ወይእዜኒ፡ኦ፡ሰብእ፡መፍቀርያነ፡እግዚ አብሔር፡እለ፡መጻእክሙ፡እምርሑቅ፡ብሔር፡ወእለ፡ተኃድሩ፡ውስተ፡ዛ ቲ፡ደሴት፡መነኮሳት፡ወመነኮሳይያት፡አዕሩግ፡ወሕፃናት፡አርጎዉ፡መሳክ ወ፡አእዘኒክሙ፡ወአንቅሁ ልበ ከመ ታጽምኡ፡ዘንተ፡ ዜና፡ ጥዑመ ዘጸሐፍኩ ለክሙ፡፡





ሚዳቋ ወይም ሌላ የዱር አውሬ ወይም ቆቅ ካየ ሌሎችንም ከአእዋፍ ወገን ካየ በትጋት እየሮጠ ይይዛል ያን ጊዜ ባለቤቱ ይመታዋል እሱም ይተውለታል ያም ሰው ወስዶ ይበለዋል እንጅ ውሻ በአፉ ሰለነካ አይተወውም፡፡

፰ እኔም እንደዚሁ ከቅዱሳን መጻሕፍት የተመረጠችና ብፅዕት የሆነች የናታችን ወለተ ጴጥሮስ ዜና ገድል ጽፌ አቆያችኋለሁ እናንተም የክርስቶስን ሥጋና ደም ይጠቅመናል ብላችሁ አምናችሁ እንደምትቀበሉ ቃል ኪዳኗ ያድነናል ብላችሁ ተቀበሉ ስለኔ በደል አታቃሉት ኦሪትም ሶምሶን እሱ ራሱ ከገደለው አንበሳ አፍ ማር አግኝቶ በላ ከነይለኛ ጣፋጭ ከሚባላ መብል ተገኘ እንደአለ ዳግመኛም በጣም ውሀ ጠምቶት ለሞት በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔርን ለመነውና ከአህያ መንጋጋ የጣፈጠ ውሀ አፈሰሰለትና ጠጥቶ ነፍሱ ከሞት ዳነች በፀብ ጊዜ የበረሃ ፀብት በጥም ጊዜ መጠጥ ብሎ እንደመሰለ፡፡

፱ ለነቢዩ ኤልያስም ሁልጊዜ አሞራ ምግቡን ያመጣለት እንደነበርና ከእሱ ተቀብሎ ቢበላ እንዳላረከሰው እነዚህን ቅዱሳን እነዚህ የረከሱት ካላረከሱዋቸው ከአንደበቴ የወጣ ይህን ዜና አታቃሉት እኔ ገላውዴዎስ ይህን መጽሐፍ እጽፍ ዘንድ የበቃሁ አልነበርኩም ከብዙ ገድሏ ጥቂቱን እንደ እውቀቴ ትንሽነት መጠን መስማት የምትችሉትን ጻፍኩላችሁ ድምቢጥ የምትባል ወፍ ወደ ባሕር ወርዳ የምትችለውን የሆዷን ያህል ጠጥታ እንደምትመለስ አሁንም ከሩቅ አገር መጥታችሁ በዚች የመነኰሳት ደሴት ያላችሁ ወንድሞች መነኰሳትና እኅቶች መነኰሳይያት ምዕመናንም ሽማግሌዎችና ሕፃናት የልባችሁን ጆሮ ከፍታችሁ የጻፍኩላችሁን የሚጥም የእናታችንን ገድል ስሙ፡፡

፩ በከመ ይቤ ዳዊት ስምዑ ዘንተ ኵልክሙ አሕዛብ ወአጽምዑ ኵልክሙ እለ ትነብሩ ውስተ ዓለም በበሐውርቲክሙ ደቂቀ እጓለ እመሕያው አብዕልትኒ ወነዳይኒ አፉየ ይነግር ጥበበ ወሕሊና ልብየ ምክረ አጸምዕ ምሳሌ በእዘንየ ወእከሥት በመዝሙር ነገርየ ወካዕበ ይቤ አጽምዑ ሕዝብየ ሕግየ ወጽልዉ እዝነክሙ ኀበ ቃለ አፉየ እከሥት በምሳሌ አፉየ ወእነግር አምሳለ ዘእምትካት ኵሎ ዘሰማዕነ ወዘርኢነ ወዘነገሩነ አበዊነ መቅድመ ኵሉ አአኵቶ ለእግዚአብሔር ዘረሰየኒ ድልወ ለጽሒፈ ዝንቱ መጽሐፍ ዘኢድልዎትየ ወኢመጠንየ ሊተ በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል አአምነከ አ አብ ወእሴብሐከ እግዚአ ሰማያት ወምድር ዘሰወርኮ ለዝንቱ እምጠቢባን ወእማእምራን ወከሠትኮ ለሕፃናት እወ አባ እስመ ከማሁ ሥምረትከ፡፡

፪ ወካዕበ:እስእል:ወአስተበቍዕ:ኀቤሁ:ከመ:ይርድአኒ:ወይከሥት ሊተ:ኃይለ:ቃል:ዘእነብብ:እምጥንቱ:እስከ:ተፍጻሜቱ:ከመ:ኢይሳለቁ ኒ:ሰብእ:ወኢይበሉኒ:ዝንቱ:ብእሲ:አኃዘ:ይሕንጽ:ወስዐነ:ፈጽሞ:እስ መ:ድኩመ:ልብ:አነ:ወብዙኃን:እሙንቱ:እለ:ፈቀዱ:ይጽሐፉ:ዘንተ:ወ ባሕቱ:ኢጸሐፉ:እስመ:ኢበጽሐ:ጊዜ:ወዕለት: ዘሠምረ ቦቱ እግዚአብሔር ወእንበይነዝ ንሕነኒ ነበርነ እንዘ ነኃዝን ፈድፋደ እስመ ኢተጽሕፈ ለነ ዜናሃ ወምግባረ ትሩፋት ወተአምራት ዘገብረት በሕይወታ ወእምድኅረ ዕረፍታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ፡፡

፫ ወእምዝ በ፻ ዓመት እምዘአዕረፈት በ፸፻ወ፩፻ ፷ ወ፭ ዓመተ ምሕረት በ፲ወ፭ አበቅቴ ወበ፲ወ፱ መጥቅዕ ወበ፳ ዓመተ መንግሥቱ ለንጉሥነ ዮሐንስ መፍቀሬ እግዚአብሔር ፡ በዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ ጸሐፍነ ዘንተ፡መጽሐፈ ገድል እስመ ሆከነ ቅንዓት መንፈሳዊ በእንተ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወይትነበብ አመ፲ ወ፯ ለወርኃ ኅዳር በረከተ ጸሎታ ወሞገሰ ረድኤታ የሀሉ ምስለ ፍቁራ አግናጥዮስ ለዓለመ ዓለም አሜን ፡፡





፩ ነቢዩ ዳዊት አሕዛብ ሁላችሁም ስሙ በዓለም ያላችሁ የሰው ልጆች ባለጸጎችም ነዳያንም ሁላችሁ ልቤ የሚያጕላውን ምክር እዝናትና አንደበቴ የሚናገረውን ጥበብ አድምጡ ጆሮን በብርሌ ነገር በምሳሌ እንዲሉ ነገሬን በምሳሌና በመዝሙር እናገራለሁ አለ ዳግመኛም ወገኖቼ ሕጌን ስሙ ጆሮዋችሁን አዘንብላችሁ ቃሌን አድምጡ ነገሬን በምሳሌ እናገራለሁ አስቀድሞ እንደተደረገ ያለውን የሰማነውንና ያየነውን አባቶቻችን የነገሩንን እናገራለሁ እንዳለ ከሁሉ አስቀድሞ ይህን መጽሐፍ ሳይገባኝ እንድጽፍ ያደለኝ እግዚአብሔርን ከሁሉ አስቀድሜ አመሰግናለሁ ወንጌል የሰማያትና የምድር ጌታ አባቴ ፈጽሜ አመሰግንሃለሁ ይህን ከአዋቂዎችና ከጥበበኞች ሰውረህ ለሕፃናት የገለጥክ አባቴ ፈቃድህ እንደዚህ ነው እንደአለ፡፡

፪ ዳግመኛም ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ የምናገረውን ቃል ይገልፅልኝ ዘንድ ፈጽሜ ወደ እሱ እለምናለሁ እኔ የልብ ደካማ ስለሆንኩ ይህ ሰው መሥራት ጀመረ መፈጸም ግን አልቻለም በማለት ሰው እንዳይሣለቅብኝ ይህን ገድል ለመጽሐፍ የፈለጉ ብዙዎች ነበሩ እግዚአብሔር የፈቀደበት ጊዜ ስለ አልደረሰ ይጽፉ ዘንድ አልቻሉም ስለዚህ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በሕይወቷ ዘመንና ከአረፈች በኋላ ያደረገችው ዜና ትሩፋት ስለ አልተጻፈ እኛ ስናዝን ቆየን

፫ ከዚህ በኋላ በአረፈች በ፻ ዓመት በሰባት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ አምስት ዓመተ ዓለም አበቅቴ ፲፭ መጥቅ ፲፱ በነበረበት እግዚአብሔርን በሚወድ በንጉሥ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በወንጌላዊ ማቴዎስ ዘመን ይህን የገድል መጽሐፍ ጻፍን ስለ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መንፈሳዊ ቅናት ይዞን ነበርና ይህም መጽሐፍ ኅዳር ፲፯ ቀን የሚነበብ ነው ጸሎቷና የረዳትነቷ ኀይል ከሁላችን ጋር ይሆን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይሁን ይደረግልን፡፡

## ምዕራፍ ፩

፩ ንዌጥን በረድኤተ እግዚአብሔር ወንጽሕፍ ዜና ጽንሰታ ወልደታ ለእምነ ቅድስት ልዕልተ ዝክር ወለተ ጴጥሮስ እምዘመደ ኄራን ወእምነገደ ክቡራን እምቤተ ደዋሮ ወፈጠጋር ስሙ ለአቡሃ ባሕር ሰገድ ወስማ ለእማ ክርስቶስ ዕበያ ወክልኤሆሙ ጻድቃን ወፈራህያነ እግዚአብሔር እሙንቱ ወብዑላን ጥቀ በንዋየ ዝንቱ ዓለም ወይንዕድዎሙ ሰብእ በኵሉ ምግባረ ሠናይ በጾም ወበጸሎት ወበምሒረ ነዳያን።

፪ ወአኃዊሃኒ መኳንንት እሙንቱ እለ አስማቲሆሙ ጳውሎስ ዘመንፈስ ቅዱስ ልሣነ ክርስቶስ ዘድንግል ዮሐንስ ወአቡሃሰ ባሕር ሰገድ ነበረ ኵሎ አሚረ ለለይከውን ጾመ ነሐሴ ይበውእ ደሴተ ሬማ ወይጸውም በንጹሕ ልብ ወበጽሩይ ሕሊና በእንተ ፍቅራ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ እንዘ ይቀውም ሌሊተ ውስተ ባሕር ለቢሶ ልብሰ ሐጺን ይጼሊ ወያስተበቍዕ በእንተ መድኀኒተ ነፍሱ።

፫ ወሶበ ይትፌጸም ጾም ወይበጽሕ በዓል ይገብር በዓለ ዐቢየ ወያስተፌሥሕ ነደያነ ወምስኪናነ ወአሐተ ዕለተ ሶበ ኃጥአ መፍቅዶ ለገቢረ በዓል ተከዘ ፈድፋደ ወእንዘ ይጼሊ ውስተ ባሕር በከመ ልማዱ ረከበ ዓሣ ወሶበ ሰጠጠ ከርሶ ተረክበ ውስቴቱ ወርቅ ዘድልወቱ ኀልቀት ወአንከረ ጥቀ ወተፈሥሐ ወአእኰታ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወፈጸመ ቦቱ ፈቃዶ።

፬ ወዓዲ እንዘ ሀሎ በቤተክርስቲያን በጊዜ ቅዳሴ ርእየ ምሥጢረ ቍርባን እንዘ ይትዌለጥ እምከዊነ ኅብስት ኀበ ከዊነ በግዕ ጸዓዳ ወርእየ:ካዕበ:እንዘ:ይትመየጥ:ኀበ:ሕላዌሁ:ዘቀዳሚ: ወእንዘ:ሀሎ:በዘከመዝ:ግብር:ይቤሎ:፩:መነኮስ:ጻድቅ:ርኢከ:ራእየ:ዐ ቢየ:እንዘ:ተኃድር:ፀሐይ:ብርኀት:ውስተ:ከርሣ:ለብእሲትከ ክርስቶስ ዕበያ ።

፭:ወይቤሎ:ኦ:አባ:ፈክር:ሊተ:ምንት:ፍካሬሁ:ለራዕይከ:ወፈከ ረ:ሎቱ:ትትወለድ:ለከ:ወለት:ሠናይት:ዘታበርህ:ከመ:ፀሐይ:ውስተ: አጽናፈዓለም





## ምዕራፍ ፩

፩ በእግዚአብሔር ረዳትነት በደዋሮና በፈጠጋር ከአሉ ከደጋጐችና ከከበሩ ሰዎች ወገን የምትሆን ስም አጠራሯ ከፍ ያለ ቅድስትና ክብርት የምትሆን የእናታችን የወለተ ጴጥሮስን የፅንሰቷንና የልደቷን ዜና እንጽፋለን የአባቷ ስም ባሕር ሰገድ የእናቷ ስም ክርስቶስ ዕበያ ይባላል ሁለቱ ኦግዚአብሔርን የሚፈሩ ጻድቃን ነበሩ በዚህ ዓለም ገንዘብም እጅግ የከበሩ ነበሩ በመጾምና በመጸለይ ለነዳያን በመራራት ሰው ሁሉ ያደንቃቸው ነበር።

፪ ስማቸው ጳውሎስ ዘመንፈስ ቅዱስና ልሳነ ክርስቶስ ዘድንግል ዮሐንስ የሚባሉ ወንድሞቿ መኳንንት ናቸው አባቷ ባሕር ሰገድ ግን የነሐሴ ጾመ ፍልሰታ በመጣች ጊዜ ወደ ሬማ ደሴት ሄዶ በንጹሕ ልቡናና በጠራ ኅሊና ይጾማል የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል እመቤታችንንም በመውደድ ሌሊት በባሕር ውስጥ ቆሞ የብረት ልብስ ለብሶ እየጸለየ ስለ ነፍሱ ድኅነት ይለምናል።

፫ ጾም በተፈጸመና በዐሏ በደረሰ ጊዜ ነዳያንንና ምስኪናንን በማስደሰት ታላቅ በዐል ያደርጋል ከዕለታት በአንድ ቀን በዓሏን የሚዘክርበት ገንዘብ አጥቶ እጅግ አዝኖ ከባሕር ውስጥ እንደልማዱ ቁሞ ሲጸልይ ዓሣ አገኘ ሆዱን በቀደደ ጊዜ ከዓሣ ሆድ ሚዛኑ ቀለበት የሚያክል ወርቅ ተገኘለት እሱም እጅግ አድንቆና ተደስቶ አምላክን የወለደች ቅድስትና ድንግል የምትሆን እመቤታችንን አመስገናትና ፈልጐ የነበረ ዝክሩን ዘከረበት።

፬ ዳግመኛም በቤተክርስቲያን በቅዳሴ ጊዜ ኅብስቱ ተለውጦ ነጭ በግ ሆኖ አየ ዳግመኛም ወደቀድሞ ኅብስትነቱ መልክ ሲመለስ አየ በዚህ በመልካም ሥራ ሳለ አንድ ደግ የበቃ መነኩሴ በባለቤትህ በክርስቶስ ዕበያ ማህፀን ብርሀት ፀሐይ ስታድር አየሁ አለው።

፭ እሱም አባቴ የህልምህ ፍች ምንድነው ተርጉምልኝ አለው በመላው ዓለም እንደ ፀሐይ የምታበራ ለእውራነ ልብ መርህ የምትሆን ደግ ልጅ ትወለድልሃለች

ወትከውን:መርሐ:ለዕውራን:ልብ:ወላቲ:ይገንዩ:ነገሥተ:ምድርወጳጳሳትወይትጋብኡ:ኀቤሃ:ሰብእ:ብዙኃን:እም፬ቱ:መዓዝነዓለም:ወይከውኑ:፩ማኅበረ:ወመሥመርያነ:ለእግዚአብሔር:ወባቲ:ይጼዋዕ:ስምከሙ:እስከ ኀልፈተ ዓለም::

፯ወርእየ:ካዕበ:ውእቱኒ ከማሁ:ወነገራለብእሲቱዘከመ:ይቤሎ:መነኮስ ጻድቅ:ወዘከመ ርእየ ለሊሁ ወይቤላ ንዒ ንትጋህ ወንጸሊ በዓቢይ ቀኖና:እስከ:ሰቡዕ:ዕለት:ከመ:ይክሥት:ለነ:ወያጠይቀነ:እግዚአብሔር:እመአማን:ውእቱ:ዝንቱ:ነገር:ወትቤሎ:አሆ:ወገብሩ:ከማሁ:ወፈጺሞሙ:አሐተ:ሱባዔ:ይቤላ:ንድግም:ካዕበ:ካልእተ:ሱባዔ:እስመ:ኢተከሰተ:ሊተ:ምንትኒ:ወትቤሎ:ዳግመ:አሆ:ወገብሩ:ከማሁ:ወሶበ:ፈጸሙ:፪ተ:ሱባዔ:ርእዩ:እሙንቱሂ:በከመ:ርእየ:መነኮስ:ጻድቅ:ወአቀብዎ:በልቦሙ:ለዝንቱነገር:እስከ ጊዜሁ::

፰ ወበኀዳጥ:መዋዕል:ጸንሰት:ክርስቶስ:ዕበያ:በፈቃደ:እግዚአብሔር ወሶበ:በጽሐ:ጊዜ:ወሊዶታ:አኃዛ:ማሕምም:ወዘንተ:ሰሚዖ:ባህር:ሰገድ:ተግሕሠ:ውስተ: ቤተ: ጸሎት: ወጸለየ :ከመ: ትለድ እንበለ ጻዕር ወሕማም ወለለጊዜሁ ይፌኑ ልዑካነ እንዘ ያስተባሪ ለለ ፩ ፩::

፱:ከመወለደት:በጊዜሃ:ወመጽአ:ላእክ:ዘተፈነወ:እንዘ:ይጸውር:ብስራተ:ወዜነዎ:ከመ:ወለደት:ወተስእለ:ወይቤ:ምንትኑ:ሕፃን:ዘተወልደ ተባዕትኑ:አው:አንስት:ወይቤሎ:ብእሲት:ይእቲ:ወሶቤሃ:አንከረ:ወሰብሐ:ለእግዚአብሔር:በእንተ:ዘኮነ::ሎቱ:እሙነ::ዘይቤሎ:መነኮስ:ጻድቅ ወዘርእየ ለሊሁ::

፲ ወሖረ እንዘ ይትፌሣሕ ወያንፈርዕጽ ወቦአ ውስተ ቤተሐሪስ እንዘ ዐቢይ መኮንን ውእቱ ወኢይደልዎ ይባእ ውስተቤተሐሪስ ወይቤልዎ እፎ ትበውእ ውስተ ቤተ ሐሪስ ዘእንበለ ይብጻሕ ጊዜ በዊእ ወይቤሎሙ ኀድጉኒ እባእ ዘአነ አአምር አንትሙ ኢተአምሩ

ይእዜ ዘይከውን ምስጢረ እምዛቲ ሕፃን ወቦአ ወነበረ ወይቤላ ለመወልዲት እስኩ አርእይኒ ሕፃነ ወወሀብኒ እሕቅፋ ወእስአማ





የምድር ነገሥታትና ጳጳሳት ይገዙላታል ከአራቱ መአዝነ ዓለም ያሉ ሰዎች ወደ እሷ ይሰበሰባሉ እግዚአብሔርን የሚያስደስቱ አንድ ማኅበር ይሆናሉ እስከ ዓለም ፍጻሜ ስማችሁ በሷ ምክንያት ይጠራል አለው::

፯ እንደገና እሱም እንደዚሁ አይቶ የበቃ መነኩሴ እንደነገረውና እሱም እራሱ እንዳየ ለባለ ቤቱ ነገራትና እስከ ሰባት ቀን በሱባኤ እግዚአብሔር እንዲገልፅልን ይህ ነገር እውነት መሆኑን እንረዳ አላት እሷም እሺ ብላው አንድ ሱባኤ አደረጉ አንዱን ሱባኤ ከፈጸሙ በኋላ ስለአልገለጠልኝ ሁለተኛ ሱባኤ እንድገም አላትና እሷም እሽ ብላው ሁለተኛ ሱባኤ አደረጉ ሁለተኛ ሱባኤ በፈጸሙ ጊዜ የበቃ መነኩሴ እንደአየ እነሱም:አይተው እስከጊዜው ድረስ ይህን ነገር በልባቸው ያዙ::

፰ ከጥቂት ወራት በኋላ ክርስቶስ ዕበያ በእግዚአብሔር ፈቃድ ፀነሰች መውለጃዋ በደረሰ ጊዜ ምጥ ያዛት ባሕር ሰገድም ይህን ሰምቶ ወደ ጸሎት ቤት ሄዶ ያለ ፃዕርና ያለ ሕማም ትወልድ ዘንድ ጸለየ በየጊዜው መልእክተኞችን እያንዳንዳቸው እያፈራረቀ ይልካቸው ነበረ::

፱ በዚያን ጊዜውኑ ወለደችና መልእክተኛው የምስራች ይዞ መጣና እንደወለደች ነገረው እሱም መልሶ የተወለደ ሕፃን ወንድ ነው ወይም ሴት ብሎ ጠየቀ መልክተኛውም ሴት ናት ብሎ ነገረው ያን ጊዜም የበቃ መነኩሴ የነገረውና እራሱ ያየው እውነት መሆኑን ተረድቶ እጅግ አድንቆ እግዚአብሔርን አመሰገነ::

፲ እየተደሰተና እየፈጠነ ሄዶ ወደ አራስ ቤት መግባት የማይገባው ታላቅ መኰንን ሆኖ ሳለ ወደ አራስ ቤት ገባ የሚገቡበት ጊዜ ሳይደርስ ወደ አራስ ቤት እንዴት ትገባለህ አሉት እሱም ዛሬ ከዚህች ሕፃን የተደረገውን እኔ የማውቀው ምሥጢር እናንተ የማታውቁት ምሥጢር አለና እገባ ዘንድ ተውኝ አላቸውና ገብቶ ተቀምጦ አዋላጅቷን እስኪ እቅፍ አድርጌ ልሣማት ስጪኝ አላት::

፲ ወትቤሎ እፎ ተሐቅፍ ወትስዕም ሕፃነ ዘዕለተ ተወልደት ዘኵለንተሃ ደም ወይቤላ ሀብኒ እስመ ኢሀሎ ደም ርኩስ ወኢርስሐት በላዕለ ዛቲ ወለትየ ወጠብለለታ በልብሰ ሰንዱን ወወሀበቶ ወተወከፉ ውእቱኒ ወጾራ በመዝራዕቱ ንስቲተ ወነጸረ ገጻ ወሰዓመ ርእሳ ወአንከረ እምስነ አርአያሃ ወይቤላ ቡርክት አንቲ ሕፃን ዘኃረየኪ እግዚአብሔር ወቀደሰኪ እምከርሠ እምኪ ከመትኩኒዮ አመተ ወዘንተ ብሂሎ ወጽአ ወሖረ።

፲፩ ወበእንተዝ ናስተበፅዖሙ ለአቡሃ ወለእማ ዘወለዱ ለነ ዛተ እመ ቡርክተ ወቅድስተ ዘበእንቲአሃ ረከብነ መድኃኒተ ወኮነተነ መርሐ ጽድቅ ወተስፋ ወከሠተት ለነ ፍኖተ ምናኔ ወምንኩስና ወመሠረተ ሥርዓተ ፍቅር ወትሕትና እመሰ ኢወለዱ ለነ ኪያሃ እምኮነት ሕይወትነ ለሐጕል።

፲፪ በከመ ይቤ ኢሳይያስ ነቢይ ሶበ አኮ እግዚአብሔር ጸባዖት ዘአትረፈ ለነ ዘርአ ከመ ሰዶም እምኮነ ወከመ ገሞራ እመሰልነ ወናሁ ተዓወቀ ትእምርተ ጽድቆሙ በላእሌሃ እስመ ዕፅ ሠናይ ፍሬ ሠናየ ይፈሪ ወእኩይሰ ዕፅ ፍሬ እኩየ ይፈሪ በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል አልቦ ዕፅ ሠናይ ዘይፈሪ ፍሬ እኩየ ወአልቦ ዕፅ እኩይ ዘይፈሪ ፍሬ ሠናየ ኵሉ ዕፅ እምፍሬሁ ይትዐወቅ ።

፲፫ ወጳውሎስኒ ይብል ለእመ ኮነት ቀዳሚሃ ቅድስት ወብሑአኒ ከማሁ ቅዱስ ውእቱ ወለእመ ኮነ ሥርዌ ቅዱስ ከማሁ አዕጹቂሃኒ ቅዱስ ወለይእቲሰ ሕፃን ሶበ ኮና ፹ ዕለተ በከመ ሥርዓተ መጽሐፍ አጥመቅዋ ጥምቀተ ክርስትና ወሰመይዋ ስማ ወለተ ጴጥሮስ አማንኬ ወለቱ ይእቲ ለጴጥሮስ እስመ ግብረ አብ ይገብር በዘተወልደ እምኔሁ በከመ ይቤሎ ሎቱ እግዚእነ ዲቤከ አሐንፃ ለቤተክርስቲያንየ።

፲፬ ወላቲኒ ሐነጸ ዲቤሃ ማኅበረ ወረሰዮሙ ቤተ በከመ ይቤ ጳውሎስ ወሰብእ ቤቱሰ ለእግዚአብሔር አንትሙ ወበከመ ወሀቦ ሎቱ መራኁተ ዘመንግሥተ ሰማያት ወላቲ ወሀባ ከማሁ እለ ተለዉ ኪያሃ ይባኡ መንግሥተ፡ሰማያት ወበከመ ይቤሎ





፲ እሷም መልሳ በተወለደችበት ዕለት ሁለንተናዋ ደም ሆኖ ሳለ እንደምን ትስማታለህ አለችው እሱም በዚች በልጄ ላይ የረከሰ ደምና ርስሐት የለምና ስጪኝ አላት በልብስ ጠቅልላ ሰጠችው እሱም ተቀብሎ ጥቂት በክንዱ ተሸክሞ ፊቷን እያየ እራሷን ሳመ ከመልኳ ደምግባት የተነሣ አድንቆ እግዚአብሔር አገልጋዩ ትሆኚ ዘንድ በእናትሽ ማህፀን ሳለሽ የመረጠሽና የቀደሰሽ አንቺ ሕፃን፡የተባረክሽና፡የተቀደስሽ ነሽ አላትና ይህን ብሎ ወጥቶ ሄደ።

፲፩ ስለዚህ ቅድስትና ቡርክት የምትሆን ይህችን እናት የወለዱትን አባቷንና እናቷን እናድንቃቸው ስለ እሷ መድኃኒት አግኝተናልና የተስፋና የጽድቅ መርሀ ሆና የምናኔንና የምንኩስናን ጐዳና ገልጣ የፍቅርና የትሕትናን ሥርዓት አስተማረችን እሷን ባይወልዱልን ኖሮ ሕይወታችን ለጥፋት በተደረገች ነበር።

፲፪ ነቢዩ ኢሳይያስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ጸባዖት ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደሰዶም በሆን ገሞራንም በመሰልን ነበረ እነሆ የጽድቃቸውም ምልክት በእኛ ላይ ታወቀ መልካም ዛፍ መልካም ፍሬን ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬን ያፈራልና ጌታችንም በወንጌል መልካም እንጨት ክፉ ፍሬን አያፈራም ክፉ እንጨትም መልካም ፍሬን አያፈራም እንጨት ሁሉ ከፍሬው የተነሣ ይታወቃል እንደአለ።

፲፫ ቅዱስ ጳውሎስም መጀመሪያዋ ንጹሕ ከሆነ እርሾዋም ንጹሕ ይሆናል ሥሩ ቅዱስ ከሆነ ጫፏም ቅዱስ ይሆናል አለ ሕፃኗንም ሰማንያ ቀን በሆናት ጊዜ በመጽሐፉ ሕግና ሥርዓት የክርስትናን ጥምቀት አጠመቋት ስሟንም ወለተ ጴጥሮስ ብለው ሰየሟት በውነት የጴጥሮስ ልጅ ናት ከእሱ ስለተወለደ ልጅ የአባቱን ሥራ ይሠራልና ጌታችን በአንተ ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ እንደአለ።

፲፬ በእሷም ላይ የአንድነት ማኅበር መሥርቶ እነሱንም ማኅበርተኞች ማደሪያ አደረጋቸው ቅዱስ ጳውሎስ እናንተ የእግዚአብሔር ማደሪያ ናችሁ እንደአለ የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ ለጴጥሮስ እንደ ሰጠ በግብር እሷን የተከተሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገቡ ዘንድ ቃል ኪዳን ሰጣት ሦስት ጊዜ

ሎቱ ሥልሰ ጊዜያተ ረዓይኬ አባግዕየ ላቲኒ ወሀባ ከማሁ ትርአይ አባግዒሁ ውስተ ጽሑተ ገድል ሠናይ::

፲፩ በአማን ደለዋ ዝንቱ ስም እስመ ወልደ ንጉሥ ይነግሥ ወወልደ ካህን ይትከሃን ወበከመ ውእቱ ኮነ ርእሰ ሐዋርያት ይእቲኒ ኮነት ከማሁ ርእሰ ኲሎሙ መምህራን ወበከመ ውእቱ ይ ቀትል ወያነሥእ በስልጣኑ ይእቲኒ ትቀትል ወታነሥእ ከማሁ ወኮነት አምላከ በጸጋ በከመ ይቤ መጽሐፍ አማልክት አንትሙ ወደቂቀ ልዑል ኲልክሙ::

፲፪ ኦ ክብር ዘመጠነዝ ክብር ኦ ልዕልና ዘመጠነዝ ልዕልና እንዘ ሰብእ ይእቲ ከማነ ተውሕባ ላቲ ከዊነ አምላክ ንግባእኬ ኀበ ነገርነ ወ ኮነት ይእቲ ሕፃን መአድምተስን ወመልክዕ ወሠናይተ አባል ወይመስል ጥቀ ንጻሬ አዕይንቲሃ ከመ ኮከብ ወአስናኒሃ ፀዓዳ ከመ ሀሊብ በከመ ይቤ ሰሎሞን በመኃልየ መኃልይ ኲለንታኪ ሠናይት አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ::

፲፫ እምስነ አርአያሃሰ ዘእፍአ ይኄይስ ሥነ ሕሊናሃ ዘውሥጥ ስምዑ ኦ ፍቁራንየ ምንትኑ ያኄብረነ ንትመካሕ በሥነ መልክዕ ወቦኑ ይትኃጐልኑ በእንተ ኀሰመ ራእዩ ወእንበይነዝ ትቤ ኦሪት ራሔል ሠናይ አርአያሃ ወሠናይ አዕይንቲሃ ወአፍቀራ ያዕቆብ ጥቀ ወተቀንየ ለአቡሃ በእንቲአሃ ፯ ዓመተ ወኢወሀቦ ኪያሃሰ አላ ወሀቦ ልያሃ በኀቡዕ ወልያሰ ጸምላጥ አዕይንቲሃ ወኢያፍቀራ ያዕቆብ ወሶበ ርእያ ሐዘነ ጥቀ::

፲፬ ወይቤሎ ላባ ኢትኀዝን ኢኮነ ከመዝ በብሔርነሰ ኢያቀድሙ ውሂበ እንተ ትንዕስ እንዘ እንተ ትልህቅ ሀለወት ወፈጽም ካዕበ ፯ ዓመተ ወእሁበከ ኪያሃኒ ወተቀንየ ሎቱ ካዕበ ፯ ዓመተ ወወሀቦ ኪያሃኒ ወእግዚአብሔርሰ አፍቀራ ለእንተ ትጸላእ ልያ ዘኀሱም ራእያ ወጸምላጥ አዕይንቲሃ ወፈትሐ ማኅጸና ወወለደት ይሁዳሃ ወእምዘርዐ ዚአሁ ተወልደ ክርስቶስ በከመ ይቤ ያዕቆብ ኢይጠፍዕ ምልክና እምይሁዳ ወምስፍና እምአባሉ::





በጉቼን ጠብቅ እንደአለው እሷም በመልካም ገድል ጥርጊያ በጉቼን ትጠብቃለች::

፲፩ ይህም ስም በውነት ይገባታል የንጉሥ ልጅ ንጉሥ የካህን ልጅ ካህን ነውና እሱ የሐዋርያት አለቃ እንደ ሆነ እሷም የመምህራን ሁሉ አለቃ ናትና እሱም በተሰጠ ሥልጣኑ እንደሚገድልና እንደሚያስነሳ እንደዚሁ እሷም ትገድላለች ታሥነሣለች የጸጋ አምላክ ሆናለችና መጽሐፍ እናንተ አማልክት ናችሁ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ እንደ አለ::

፲፪ እንደዚህ ያለውን ክብር አከበራት እንደዚህ ያለውን ከፍታ ከፍ አደረጋት እንደ እኛ ሰው ስትሆን የጸጋ አምላክነት ተሰጥቷታልና ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስና ይህችም ሕፃን መልኳና ደምግባቷ ያማረ መላ ሰውነቷ ያማረ ዓይኖቿ እንደኮከብ ጥርሶቿ እንደ ወተት ያማረ ነበር ሰሎሞን በመኃልይሁ ጉለንተናሽ ውብ ነው ነውር የለብሽም እንደ አለ::

፲፫ ከውጪ የደምግባቷ ማማር ይልቅ የውስጣዊ ህሊናዋ ማማር ይበልጣል ወዳጆቼ ሆይ እስቲ ስሙ በሚጠፋና በሚለወጥ መልክ ምን አስመካን በውኑ ሰው በመልክ መልካምነቱ ይጸድቃልን መልከ መልካም ባለመሆኑ ይኰነናልን ስለዚህ ኦሪት ራሔል መልኳ ያማረ ዓይኖቿ የቀኑ ናቸው ያዕቆብ እጅግ ወደዳትና ስለሷ ሰባት ዓመት ተገዛ አባቷ በድብቅ ልያን ሰጠው እንጂ እሷን አልሰጠም ልያ ዓይነ ሞጭሟጫ ነበረችና ያዕቆብ አልወደዳትም ሲያያት እጅግ አዘነ እንጂ::

፲፬ ላባም ያዕቆብን በአገራችን ልማድ ታላቂቱ ሳለች ታናሽቱን መስጠት ሥርዓት አይደለም አሁንም ሰባት ዓመት ተገዛልኝና ራሔልን እሰጠሃለሁ አለው ዳግመኛ ያዕቆብ ሰባት ዓመት ተገዝቶ ራሔልን ሰጠው እግዚአብሔር ግን መልከ መልካም ያይደለች ዓይነ ሞጭሟጫ ተጠልታ የነበረች ልያን ወደዳትና ማህፀኗን ከፍቶ ይሁዳን ወልዳ ከየሁዳ ዘር ክርስቶስ ተወለደ ግዛትና ሥልጣን ከየሁዳ ወገን አይጠፋም እንደአለ::

፲፱ ወለራሔልሰ ዘሠናይ አዕይንቲሃ ዘአፍቀራ ያዕቆብ ኢያፍቀራ እግዚአብሔር ወኢወሀባ ወልደ እስከትቀንዕ ላዕለ እኅታ ወትቤሎ ለያዕቆብ ሀበኒ ወልደ ወእመ አኮ እመውት ወእምዕጹብ ወለደት ዮሴፍሃ ወብንያምሃ ወእምዘርአ እሉሰ ኢተወልደ ክርስቶስ እግዚአብሔርሰ ኢይሬኢ ስነ ዘአፍአ አላ ይሬኢ ሥነ ዘውስጥ።

፳ ወካዕበ ትቤ ኦሪት ኤሳው ሠናይ ራእዩ ወያፈቅሮ ይስሐቅ ወያዕቆብ ኅሱም ራእዩ ወአፍቀሮ እግዚአብሔር ወይቤ ያዕቆብሃ አፍቀርኩ ወኢሳውሃ ጸላእኩ ወልደተ ክርስቶስኒ ኢኮነ እምዘርአ ዔሳው አላ እምዘርአ ያዕቆብ ወዳዊትኒ ይቤ ወነሥአኒ እምአባግዓ አቡየ ወቀብአኒ ቅብአ ቅዱሰ አኀውየሰ ሠናያን ወልሂቃን ወኢሠምረ ቦሙ እግዚአብሔር።

፳፩ በእንተ ዝንቱ ኢንትመካሕ በእንተ፡ስነ፡መልክዓ ወኢነሀፍር በእንተ ኅሰመ ራእያ እስመ ሀለዎ ለዝንቱ ዘይማስን ይልበስ ዘኢይማስን ስምዑ ካዕበ ንነግረክሙ ዜናሁ ለባሕር ሰገድ ዘውእቱ አበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በከመ ኮነ ያፈቅራ እምኵሉሙ ወራዙት ደቂቁ በኵሉ ልቡ ወበኵሉ ሕሊናሁ ወይትሜካህ ባቲ ።

፳፪ ወእንዘ ሕፃን ይእቲ ወንዑስ መዋዕሊሃ ዘኢተአምር ሰምየ አቡሃ ወእማ ያነብራ ላዕለ መንበር ወላዕለ ዓራት ወይእኅዝ ሰይፎ ወይትዋነይ ቅድሜሃ ወያነሥእ እገሪሁ ወይደብል ላቲ በከመ ይደብሉ ሐራ ቅድመ ንጉሥ ወይዜምር በስማ ወይቤላ እመውት ለኪ አነ አቡኪ ኦ ቡርክት ሕፃን ዘኃረየኪ እግዚአብሔር ወባረከኪ ወቀደሰኪ ወከመዝ ይገብር ኵሉ ዕለተ አኮ በጽጋብ ወበስካር አላ እንዘ ርኁብ ወእንዘ ፅሙዕ ውእቱ እስመ ሰክረ በፍቅረ ዚአሃ።

፳፫ ወአእመረ ዘይከውን ምሥጢረ እምኔሃ ወባሕቱ ውእቱሰ ፍጡነ ሞተ ወኢተፈጸመ ሎቱ ፍሥሓሁ ፈተወ ወኢርእየ ኃሠሠ ወኢረከበ በከመ ይቤ ወንጌል እስመ ብዙኃን ነቢያት ወጻድቃን ፈተዉ ይርአዩ አንትሙ ዘትሬእዩ ወኢርእዩ።





፲፱ መልኳና አይኗ ያማረ ያዕቆብ የሚወዳት ራሔልን እግዚአብሔር አልወደዳትም በጎቷ ላይ ቀንታ ያዕቆብ አለዚያ እሞታለሁ ልጅ ስጠኝ እስክትለው ድረስ ኋላ በጭንቅ ዮሴፍንና ብንያምን ወለደች ከእነሱም ወገን ክርስቶስ አልተወለደም እግዚአብሔር የአፍአ መልክን አያይም የውስጥ ቅን ህሊናን ያያል እንጂ።

፳ ዳግመኛም ኦሪት መልከ መልካም ኤሳውን ይስሐቅ ይወደዋል መልከ መልካም ያይደለ ያዕቆብን እግዚአብሔር ይወደዋልና ልቡ የቀና ያዕቆብን ወደድኩ ልቡ ያልቀና ኤሳውን ጠላሁ አለ የክርስቶስ ልደትም ከኤሳው ወገን አይደለም ከያዕቆብ ወገን ነው እንጂ ዳዊትም የአባቴን በጐች ከምጠብቅበት ከእረኝነት መርጦ ቅዱስ ቅባትን ቀባኝ ወንድሞቼ ትላልቆችና መልከ መልካሞች ነበሩ እግዚአብሔር አልመረጣቸውም አለ።

፳፩ ስለዚህ ስለመልክ አንመካ ይህም የሚጠፋ እንስሳዊ ባሕርይ ያለውን አካል የማይጠፋ መልአካዊ ባሕርይ ይለብሰዋልና ዳግመኛም የቅድስትና የቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አባት የባሕር ሰገድን ዜና ከወንዶች ልጆቹ ይልቅ በፍፁም ልቡና በፍጹም ሐሳቡ እንዲወዳትና እንደሚመካባት ስሙ ልንገራችሁ።

፳፪ ገና ትንሽ ሕፃን ሳለች አባቷንና እናቷን መጥራት ሳትችል በዙፋንና በአልጋ ላይ ያስቀምጣትና ሰይፍ ይዞ ከፊቷ እየተጫወተ ወታደሮች ንጉሣቸውን እጅ እንደሚነሱ እግሮቹን አስተካክሎ እጅ ይነሣት ነበር እግዚአብሔር የመረጠሽና የባረከሽ የቀደሰሽ የተባረክሽ ሕፃን ሆይ እኔ አባትሽ ስለአንች እሞትልሻለሁ እያለ በስሟ ይዘምር ነበር ዘወትር እንደዚህ የሚያደርገው በስካርና በጥጋብ አይደለም ተርቦም ተጠምቶም ሳለ ነው እንጂ በእሷ ፍቅር ሰክሮዋልና።

፳፫ ከእሷ ዘንድ የሚደረገውን ምሥጢር አውቋዋልና ነገር ግን ወደደ እንጂ አልአየም ፈለገ እንጂ አላገኘም ፍጻሜው ሳይደርስ ፈጥኖ ሞተ ወንጌል ብዙ ነቢያትና ጻድቃን ያዩ ዘንድ ወደዱ እናንተ ያያችሁትን አልአዩም እንደአለ።

## ምዕራፍ ፪

፩ ወእምዝ ሐጸንዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አሜሃ እማ ወአኃዊሃ በጥበብ ወበፈሪሃ እግዚአብሔር ወመሃርዋ መጻሕፍተ ቤተክርስቲያን ወሶበ ልህቀት ወበጽሐት ለሕገ ሰብሳብ ወሀብዎ ኪያሃ ለ፩ዱ ብእሲ እመኳንንተ ምድር ዘስሙ መልክአ ክርስቶስ ወውእቱኬ ሊቀ መማክርቱ ለንጉሥ ሱስንዮስ ዘነግሠ በሃይማኖተ አፍርንጅ ከመ ትኩኖ ብእሲተ በሥርዓተ ከብካብ ከመ አዋልደ መኳንንት ለዓቅሞተ ዘርእ እስመ ይቤ መጽሐፍ ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልእዋ ለምድር ወሶበ አእተዋ አፍቀራ ፈድፋደ ወአእመራ ወጸንሰት ወእምዝ ጸለየት ኀበ እግዚአብሔር ከመ ማርታ እንዘ ትብል ከመዝ ለእመ:ከነ ዝንቱ ፅንስ ዘውስተ ከርሥየ ይትወለድ ወያሠምረከ ይሕየው ወእመ አኮሰ:ይሙት:ፍጡነ:ወሶበ:ተፈጸመ:መዋዕለ:ጽንሳ:ወለደት:ወአብአቶ ክርስትና:ወሞተ:በጊዜሃ:ወሰምዓ:እግዚአብሔር:ስእለታ:ወእንዘ:ትብል ከመዝ:ወለደት:፫ተ:ውሉደ ወሞቱ ኵሎሙ በፈቃደ እግዚአብሔር።

፪ ወብእሲሃሰ መልክዓ ክርስቶስ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ባዕል ውእቱ ጥቀ ወያፈቅራ ፈድፋደ ወይእቲሰ ኢትፈቅድ ትንበር ምስሌሁ እስመ ተዘከረት ኀልፈቶ ለዓለም በከመ ይቤ ጴጥሮስ ሐዋርያ እስመ ኵሉ ዘሥጋ ከመ ሣዕር ወኵሉ ክብሩ ለሰብእ ከመ ፍሬ ሣዕር።

፫ ወዮሐንስኒ ይቤ ኢታፍቅርዎ ለዓለም ወኢዘሀሎ ውስተዓለም ፍትወቱ ለሥጋ ወፍትወቱ ለዓይን ወሥራሁ ለመንበርት ኢኮነ ዝንቱ እምኀበ አብ አላ እምዓለም ውእቱ ዓለሙኒ የኃልፍ ወፍትወቱኒ የኃልፍ ወጳውሎስኒ ይቤ ከመዝ ይረትዕ አኃዊነ ይኩን እስመ አልጸቀ ይኀልፍ ኵሉ ንብረተዝ ዓለም እለኒ አውሰቡ ይከውኑ ከመ ዘኢያውሰቡ ወእለኒ ይዴለዉ ከመ ዘኢይዴለዉ ወእለ ይበክዩ ከመ ዘኢይበክዩ ወእለኒ ይትፌሥሑ ከመ ዘኢተፈሥሑ ወእለኒ ይሣየጡ ከመ ዘኢተሣየጡ ወእለኒ ይመልኩ ከመ ዘኢመለኩ ወእለኒ ይበልዑ ከመ ዘኢይበልዑ ወእለኒ ይሰትዩ ከመ ዘኢይሰትዩ እስመ ኵሉ ተድላዝ ዓለም የኃልፍ ወያኃልቅ ወእግዚእነኒ ይቤ በወንጌል ምንተ ይበቁዖ ለሰብእ ለእመ ኵሎ ዓለመ ረብኃ ወነፍሶ ሐጕለ ወምንተ እምወሀበ ሰብእ ቤዛሃ ለነፍሱ።





## ምዕራፍ ፪

፩ ከዚህ በኋላ ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን እናቷና ወንድሞቿ በጥበብና እግዚአብሔርን በመፍራት አሳደጓት የቤተ ክርስቲያንንም መጻሕፍት አስተማሯት አድጋ ለጋብቻ በደረሰች ጊዜ ከዓለም መኳንንት ስሙ መልክዓ ክርስቶስ ለሚባል ይህውም ለጊዜ ካቶሊክ እምነት ተከታይ የነበረው የንጉሥ ሱስንዮስ የአማካሪዎቹ አለቃ ለሚሆን ለአንድ ሰው እንደ መኳንንት ልጆች ዘር ለመተካት የሕግ ሚስት ትሆነው ዘንድ አጋቡት መጽሐፍ የብዙኅ ብዙ ሁኑ ምድርንም ሙሉዋት እንደአለ በአገባትም ጊዜ እጅግ ወደዳት እሷ በፀነሰች ጊዜ እንደማርታ እራሷን ዘንበል አድርጋ ይህ በማህፀኔ ያለው ፅንስ የሚያስደስትህ ከሆነ ይዳን አንተን የማያስደስትህ ከሆነ ፈጥኖ ይሙት እያለች ወደ እግዚአብሔር ጸለየች የፅንሷ ወራት በተፈጸመ ጊዜ ወልዳ ክርስትና አስነስታ ወዲያውኑ ሞተ እግዚአብሔር ልመናዋን ሰምቷታልና እንደዚህ እየጸለየች ሦስት ልጆች ወልዳ ሁሉም በእግዚአብሔር ፈቃድ ሞቱ።

፪ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ባለቤት መልክአ ክርስቶስ እጅግ ባለፀጋ ነበር እጅግም ይወዳት ነበር እሷ ግን ከእሱ ጋር ትኖር ዘንድ አትፈልግም ጴጥሮስ ሥጋ የለበሰ ሁሉ እንደሣር ነው የሰው ሥራ ሁሉ እንደሚደርቅ ሣር ነው እንደ አለ የዚህች ዓለም ማለፏን አስባለችና ።

፫ ዮሐንስም ዓለሙንና በዓለሙ ውስጥ ያለውን የሥጋን ደስታ አትውደዱ እነዚህ ሁሉ ከዓለም እንጂ ከአብ አይደሉምና ዓለሙና የሥጋ ደስታ ፈጥኖ ያልፋልና እንደአለ ጳውሎስም ወንድሞቼ እንደዚህ ቢሆን የቀና ነው የዚህ ዓለም ንብረት ያልፍ ዘንድ ደርሷል ያገቡት እንዳላገቡት ይሆናሉ

ያከማቹ ንብረት እንዳላከማቹት ይሆናሉ ያለቀሱት እንዳልአለቀሱት ይሆናሉ የተደሰቱት እንደልተደሰቱት ይሆናሉ

የሸጡት እንዳልሸጡት የገዙት እንዳልገዙት የበሉት እንዳልበሉት የጠጡት እንዷልጠጡት ይሆናሉ የዚህ ዓለም ተድላ ደስታ ያል ፋልና እንደአለ ወንጌልም ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ ነፍሱን ከአጣ ምን ይጠቅመዋል እንደአለ ።

፩ ወበእንተዝ ነበረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ኵሎ መዋዕሊሃ በጾም ወበጸሎት ወጊዜ ምሴት ትበውዕ ኀበ ቤተክርስቲያን ወትተግህ ኵላ ሌሊተ እንበለ ፅርዓት በቀዊም ወበሰጊድ ወበ ኵሉ ግብረ ጸሎት ወትትመሰጥ ወትትኃባዕ እምእለ ተለዋሃ ወጊዜ ጽባሕ ትትከሠት ሎን ወተአቱ ቤታ ወለለ እሑድ ትገብር ምሳሐ ለካህናተ ቤተክርስቲያን ወሀለወት ምስሌሃ አሐቲ ብእሲት ዘትትጌበር ግብረ ፁቡሕ ወግብረ መባልዕት ዘዘዚአሁ ወኮነት ታንጐረጕር ወኢይሔውዛ ተገብሮተ መብልዕ ለካህናት ወሶበ አእመረት ሕሊናሃ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ነሥአታ ምስሌሃ ፩ደ ዕለተ ኀበ ቤተክርስቲያን ጊዜ ምሴት ወአርአየታ ትጋሆሙ ለካህናት ወጻማሆሙ።

፪ ወእምዝ ነስሐት ወትቤ አበስኩ ስረዪ ሊተ እስመ አነ አኀዘ–ንኩኪ እምቅድመዝሰ ኢያእምር ግብሮሙ ለካህናት ወናሁ ርኢኩ፡አንክርኩ፡እምይዜሰ፡እገብር፡ኵሉ፡ፈቃደኪ ፡ወኢይትዓደ ፡እም ትእዛዝኪ ወካዕበ ሶበ ትገብር እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ በዓለ ወምሳሐ ወታስተዳሉ ኵሉ መፍቅዳተ ሥጋ መባልዕተ ወስቴያተ ዘዘዚአሁ ወጥብሐታተኒ ወታስተጋብኦሙ ለነዳያን ወለምስኪናን ወለኵሎሙ ሰብአ ሀገር ወለካህናተቤተክርስቲያን ወታረፍቆሙ በበምርፋቃቲሆሙ ይበልዑ ወይሰትዩ ይጸግቡ ወይትፌሥሑ።

፫ ወይእቲሰ ኢትጥዕም ምንተኒ እምዝንቱ ኵሉ አላ ትበልዕ ቈጽለ ረንጭ መሪረ ዘአብሰልዎ ወትሰቲ ማየ ወትመስሎሙ ለሰብእ ከመ ዘትበልዕ ወትሰቲ ከማሆሙ ወኢየአምር ባቲ መኑሂ እምሰብእ ዘእንበለ አመት ዘትትለአክ ወነበረት እንዘ ትገብር ከመዝ ብዙኃ መዋዕለ ወኢትፈቅድ ግሙራ ትፍግዕተ ዝንቱ ዓለም ኃላፊ ወነበረት በሥርዓት ሰብሳብ ምስለ ብእሲሃ መልክዓ ክርስቶስ አላ ትጸንሕ ወተኃሥሥ ዕለተ እንተ ባቲ ሠምረ እግዚአብሔር ከመትጸእ ወታምስጥ ወትጕየይ እምኔሁ ወትኀድግ ዓለመ ወትመንኵስ ወዘልፈ ትስእል ወታስተበቍዕ ኀበ እግዚአብሔር እንዘ ትብል





፩ ስለዚህ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በጾምና በጸሎት ዘመኗን ሁሉ ፈጸመች በመሸ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብታ በመቆምና በመስገድ የጸሎትን ሥራ ሳታቋርጥ የሚከተሏትን ሰዎች ተደብቃ በተመስጦ ታድራለች ጥዋት ትገናኛቸውና ወደ ቤቷ ትሄዳለች እሁድ እሁድ በየሳምንቱ ቤተ ክርስ–ቲያንን ለሚያገለግሉ ካህናት ምግብ ታዘጋጅና ታበላለች እንጀራን የምትጋግርና ወጥ የምታፈላ አንዲት ሴት ነበረች ይህችም ሴት ስትሠራ ታንጐራጕር ካህናትንም በማብላት አትደሰትም ነበር እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሐሳቧን በአወቀች ጊዜ ከዕለታት በአንድ ቀን ቀኑ በመሸ ጊዜ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ወሰደቻትና የካህናት ትጋታቸውንና ድካማቸውን አሳየቻት።

፪ ከዚህም በኋላ ተፀፅታ ከዚህ በፊት የካህናትን ሥራ ስለማላውቅ አሳዝኜሻለሁና ይቅር በይኝ አለቻት ከዛሬ ጀምሮ ፈቃድሽን እፈጽማለሁ ትዕዛዝሽንም አልደፍፈርም አለቻት ዳግመኛም እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ምሣ በአዘጋጀች እርድ በአረደች ጊዜ ነዳያንንና ምስኪናንን የአገሩን ሰዎች ትሰበስብና የቤተክርስቲያንን ካህናትንም በየቦታቸው አስቀምጣ በልተው ጠጥተው ጠግበው ይደሰታሉ ።

፫ እሷ ግን ከዚህ ሁሉ አትቀምስም ነበር የመረረና ያበሰሉት የሬንጭ ቅጠል ትበላለች እንጂ ውሃንም ትጠጣለች ለሰው እንደ እነሱ የምትበላና የምትጠጣ ይመስላቸዋል ከሰው ወገን ማንም አያውቅባትም ከምትላክ አገልጋዩዋ በስተቀር እንደዚህ ስታደርግ ብዙ ዘመን ኖረች አላፊ የሚሆን የዚችን ዓለም ደስታንና ከባለቤቷ መልክአ ክርስቶስ ጋር በጋብቻ ሥርዓት መኖር አትፈልግም ነበር ከእሱ ተለይታ ወጥታ ይህን ዓለም ትታ መንና በምንኵስና ትኖር ዘንድ ፈቃደ እግዚአብሔር የሚሆንበትን ቀን ጸንታ ትፈልግ ነበር አቤቱ ጐዳናንን አመልክተኝ ፍለጋህን ምራኝ በቸርነትህ ምራኝ አቤቱ እኔን ባሪያህን የቀናውን ጐዳናህን አሳየኝ እያለች ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ትለምን ነበር።

ፍኖተከ እግዚኦ አምረነ ወአሰረ ዚአከ ምሕረነ. ወምርሐነ በጽድቅከ ምርሐኒ እግዚኦ ፍኖተከ ፍኖተ ርቱዓ ለዓመትከ ፡፡
፯ ወነበረት እንዘ ትጼሊ. ከመዝ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሶበ በጽሐ ጊዜ ዘሠምረ ቦቱ እግዚአብሔር ከመትጻእ እምዝንቱ ዓለም ተንሥአ ወሖረ ብእሲሃ መልክዓ ክርስቶስ ኀበ ፀብዕ ምስለ ንጉሥ ወይእቲሰ ትነብር በብሔረ ስማዳ መልዕልተ ተሰላስ ዘማኅፌድ ወኢይሬእያ መኑሂ ወአሜሃ መጽኡ በፈቃደ እግዚአብሔር ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ፪ቱ መነኰሳት አባ የማነ ክርስቶስ ዘሬማ ወአባ ተዝካረ ድንግል ዘፃና ተፈኒዎሙ እምኀበ አባ ፈትለ ሥላሴ ከመ ያውጽእዋ ጽሚተ ወይንሥእዋ ወይሰድዋ ምስሌሆሙ ኀበ ዘጌ ወሶበ ርእየቶሙ ተፈሥሐት ፈድፋደ፡፡
፰ ወእምዝ መጽወተት ኵሎ ንዋያ ለነዳያን ወለምስኪናን ወነሥአት ኵሎ ሠርጓቲሃ ፹ ሕልቀ መደልወ ወርቅ ከመትዝሩ በፍኖት ለጽኑሳን ወለአብያተ ክርስቲያንት ወተሰነአዉ ወተዓደሙ ጊዜ ይወጽኡ ወሶበ ኮነ ምሴተ እምድኅረ ኖሙ ሰብእ ጸውአቶን ለ፫ቱ አዕማቲሃ እለይብልዎን ማርያማዊት ወእስክንድራዊት ወኢዮጰራቅስያ ከመይትልዋሃ ወወጽአት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወተቀበልዋ እሉ መነኰሳት ወነሥእዋ ምስሌሆሙ ወአዕዓንዋ ዲበ በቅል ወቤ፡ቱ እንዘ የሐውሩ ኵላ ሌሊተ ወበጽሑ በይእቲ ዕለት ማኅደረ እግዝእትነ ማርያም ረቻ ወኃደሩ ህየ፡፡
፱ ወአኃዘት ትዝሩ ውእተ ወርቀ ለለኵሉ ፍኖት ዝኒ ዕፁብ ወመንክር ውእቱ ዘተሐውር በአሐቲ ዕለት መጠነዝ ኑኃ ፍኖት እንዘ ድኩም ኃይላ ወልምሉም ሥጋሃ ሰበ አኮ ኃይለ እግዚአብሔር ዘአጽንዓ መኑ እምክህለ ይሖር ከመዝ ኀድገሰ





፯ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንደዚህ እየጸለየች ብዙ ዘመን ኖረች ከዚህ ዓለም በምትለይበትና በምትመንንበት እግዚአብሔር የፈቀደበት ጊዜ ሲደርስ ባለቤቷ መልክአ ክርስቶስ ከንጉሡ ጋር ወደ ጦርነት ተነሥቶ ሔደ እሷ ግን በስማዳ አገር በ አዳራሹ ፎቅ ላይ ትኖር ነበር ማንም አያያትም ያንጊዜ በፈቃደ እግዚአብሔር ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሁለት መነኰሳት አባ የማነ ክርስቶስ ዘሬማና አባ ተዝካረ ድንግል ዘፃና ከአባ ፈትለ ሥላሴ ተልከው በድብቅ አውጥተው ከነሱ ጋር ወደዘጌ ይወስዷት ዘንድ መጡ በአየቻቸው ጊዜ እጅግ ደስ አላት፡፡
፰ ከዚህ በኋላ ገንዘቧን ሁሉ ለነዳያንና ለምስኪናን መጸወተች ለቤተ ክርስቲያንና ለተቸገሩ በጐዳና ትሰጥ ዘንድ ሰማንያ የወርቅ ሚዛን ቀለበቶችንና ጌጦቿን ከሷ ጋራ ይዛ ተነሣች በሚወጡበት ጊዜ ተቀጣጠሩ መሸቶ ሰው በተኛ ጊዜ ይከተሏት ዘንድ ሦሥት አገልጋዮቿን ማርያማዊትንና እስክንድራዊትን ኢዮጰራቅስያ የሚባሉትን ጠራቻቸውና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወጣች እነዚህም መነኰሳት ተቀበሏትና ከእነሱ ጋር ይዘዋት ሌሊቱን ሁሉ ሄደው የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ረቻ ደርሰው እዚያ አደሩ፡፡
፱ የያዘችውን ወርቅ በየመንገዱሁሉ ለነዳያን ትበትነው ጀመር ሰውነቷ የለሰለሰ ኀይሏ የደከመ ሲሆን ይህን ያህል የራቀውን መንገድ የሄደችው ድንቅ ነው የእግዚአሔር ኃይል ባያፀናት ይህን ያህል ጐዳና የሚጓዝ ማነው እንደ እሷ ያለች ሴት ቀርቶ ኀይለኛ ጎልማሳ ስንኳን ይሄድ ዘንድ ይህን ያህል አይችልም እሷ ግን ኀይሏ የደከመ ሰውነቷ የለሰለሰ በዘመኗ

ዘከማሃ ብእሲት ወሬዛ ጽኑዓ ኃይል እምኢክህለ ይሑር ከመዝ ይእቲስ ድኩም ኃይላ ወልምሉም እገሪሃ ወኢረገፀት ቦቱ ምድረ በ ኩሉ መዋዕሊሃ እመኒ ወረደት እምዓራት ወቆመት ላዕለ ዘርቤት ዘተነጽፈ ወእመረከባ ህየ ፍርፋረ ኅበስት ይቡስ ዘወድቀ ይጕድዕ እገሪሃ ወይወጽእ እምኔሁ ደም።

፲ ወባሕቱ ኃይለ እግዚአብሔር አጽንዓ ወኢተዓውቃ ድካም እስመ ኮነት ስክርተ በፍቅሩ ከመብእሲ ዘተጸውአ ውስተ ከብካብ ወከመ ያርብሐዊ ጽኑዕ ኀበ ምህርካ እማንኬ ተሐውር እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኀበ ከብካብ ሰማያዊ ወኀበ መርዓዊ ኢየሱስ ክርስቶስ እማንኬ ተሐውር እምነ ቅድስት፡ወቡርክት፡ወለተጴጥሮስ፡ኀበ፡ምህርካ፡ወትትቃተል፡ምስለዲያብሎስ፡ወትነሥእ፡እምኔሁ፡ብዙኃን፡ነፍሳተ፡እለ፡ረሰዮሙ፡ዔዋሁ ።

፲፩ ወከዕበ፡ተንሥአ እምዝየ ወበጽሁ ጨጓሪ ዘግባ ወግዕዙ እምህየ ወበጽሑ ወንጪፕ ወተሣብኡ ውስተ ቤተ አረጊት መነኩሳይት እንተ ትሰመይ አመተ ጴጥሮስ ወነበረት ህየ ኅዳጠ መዋዕለ ወእምዝ ተንሥአት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ እምነ ወንጪፕ ወሖረት ሮቢት ወበጽሐት እመብራ እንጻረ ዘጌ ወሀሎ ቢሃ በጽንፈ ባሕር ፩ዱ ብእሲ በአለ ታንኳ ዘስሙ ክፍለ ማርያም ወሠናይ ውእቱ ብእሲ ወተአንገደት ቦቱ ወተወከፋ ወአኀደራ ውስተ ቤቱ ወበሳኒታ አምጽአ ላቲ ታንኳ ወአብአ ገዳመ ዘጌ።

፲፪ ወበጺሓ ህየ ተፈሥሐት ወአእኰተቶ ለእግዚአብሔር ወተአምኃቶሙ ለቅዱሳን እለ ሀለዉ ውስተ ውእቱ ገዳም መነኩሳት ወመነኩሳይያት ወአማኀፀነቶሙ ከመ ይዘከርዋ በጸሎቶሙ ወእምዝ ነበረት ህየ እንዘ ትብል ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም ዝየ አኃድር እስመ ኃረይክዋ ወተላጸየት ሥዕርተ ርእሳ ወገብረት ቆብዓ ወአሜሃ ሰምዐ ብእሲሃ መልክዓ ክርስቶስ እንዘ ሀ ሎ ውስተ ትዕይንት ምስለ ንጉሥ ከመ ጕየት ወተኃጥአት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ወነገሮ ለንጉሥ ወተሰነአለ እምኔሁ ከመ ይሑር ወይዱግና ወይኅስሣ ወአብሖ ንጉሥ ወፈነዎ ወሶቤሃ ተንሥአ በዐቢይ መዓት ወጕኀረ ከመ አንበሳ ወጸውኦሙ ለሐራሁ ዘይሰመዩ ሥልጣን





ሁሉ በእግሯ መሬትን ያልረገጠች ከአልጋዋ ወርዳ ባዶ እግሯን ከአበባ ምንጣፍ ላይ ስትቆም የዳቦ ፍርፋሪ እግሯን በወጋ ጊዜ እግሯ ይደማ ነበር።

፲ ነገር ግን የእግዚአብሔር ኀይል አፅንቷታልና ድካምም አልታወቃትም በእሱ ፍቅር ሰክራለችና ወደ ሰርግ እንደሚሄድ ጕልማሳ ሰውና ምርኮን ለመማረክ እንደሚሄድ ወታደር ታፈጥን ነበር እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በውነት ሰማያዊ ሰርግና ወደ ሙሽራ ኢየሱስ ክርስቶስ እየሄደች ነው በውነት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከዲያብሎስ ጋር ተዋግታ እሱ የማረካቸውን ነፍሳት ትረከባለች።

፲፩ ዳግመኛም ከዚያ ተነስተው ጨጓሪ ዘግባ ደረሱ ከዚያ ተጉዘው ወንጨፕ ደርሰው አመተ ጴጥሮስ ከምትባል አንዲት አሮጊት ቤት ተሸሸጉ እዚያ ጥቂት ቀን ተቀመጡ ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከወንጭፕ ተነስታ በሮቢት አድርጋ በዘጌ አንጻር እመብራ ደረሰች ከባሕር ዳር ስሙ ክፍለ ማርያም የሚባል ታንኳ ያለው አንድ ሰው ነበር ደግ ሰው ስለ ነበረ ወደ እሱ ሄዳ ተቀበላትና በስነሥርዓት በቤቱ አሳደራትና፡በማግሥቱ፡ታንኳአምጥቶ ወደ ዘጌ ገዳም አደረሳት።

፲፪ እዚያ ደርሳ ደስ ብሏት እግዚአብሔርን አመስገነችና እዚያ ያሉ ቅዱሳን ወንዶች መነኰሳትንና ሴቶች መነኰሳይያትን እጅ ነ ሳቻቸውና በጸሎት አስቡኝ ብላ አማፀነቻቸው ከዚህ በኋላ ይህችን ቦታ መርጫታለሁ የዘለዓለም ማረፊያየ ናት ብላ እዚያ ተቀ መጠች ፀጉሯን ተላጭታ ቆብ አደረገች ያን ጊዜ ባለቤቷ መልክዓ ክርስቶስ ከንጉሡ ጋር በከተማ ሳለ እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ እንደጠፋች ሰምቶ ለንጉሡ ነግሮ ንጉሡን ተሰናብቶ ያን ጊዜ ሥልጣን መርእድ የሚባል ከአለቃቸው ቀኝ

መርዕድ ዘሠርየሙ በብሔረ ውዱ ምስለ ሊቃሙ አዝማች ወነሥአሙ ምስሌሁ ወአደ ኵላ ሀገረ እንዘ ይሴአል ወየሐትት ኀበ አይ መካን ሖረት ፡፡

፲፫ ወነገርዎ ከመ ቦአት ዘጌ ወዐገታ ለሀገረ ሮቢት ወአዘዞሙ ለሐራሁ ሥልጣን መርዕድ ከመ ያጥፍኡ ሀገረ ወይበርብሩ ንዋያተ፡ሀ'ሙ ወይብልዑ እክሎሙ እንበለ መሥፈርት ወኢይምህኩ ወሶበ ረከብዎ ለውእቱ ብእሲ በአለ ታንኳ አሰርዎ ወበርበሩ ንዋዮ ወማህረኩ እንስሳሁ ወገብሩ በከመ አዘዞሙ ወአውየዉ ሰብአ ሀገር እድ ወአንስት ወኮነ ዐቢይ ሁከት፡፡

፲፬ ወካዕበ ይቤሎ ለሊቀ፡ሐራ ግበር ማማ መልዕልተ ኦም በጽንፈ ባሕር ወዕርግ ዲቤሁ ወነጽር ታንኳ ዘየሐውር ወየአዱ እምለፌ ወእምለፌ ወለእመ ረከብካሃ አኀዝ ወገብረ በከመ አዘዞ እግዚኡ ወዓርገ ዲበ፡ማማ ወነበረ እንዘ የአቅብ መዓልተ ወሌሊተ ወሶበ ርእየ እንዘ ይመጽእ ታንኳ ይወርድ ወይሬኢ ወሶበ ኃጥአ ይፌንዎ፡፡

፲፭ ወመልክዓ ክርስቶስሰ ሖረ ወይናያት ኀበ ወለተ ጊዮርጊስ ወለተ ንጉሥ ሠርጸ ድንግል ወኀበ አባ ፈትለ ሥላሴወገሠጽዎ ለምንት ታማስን ሀገረ በከንቱ ዘኢአበሱ ወኢዓመጹ ዑቅ ርእሰከ ከመ ኢይትመዓዕ እግዚአብሔር ላዕሌከ ወወድቀ ታሕተ እገሪሆሙ ወይቤሎሙ ተማኅፀንኩ በከመ አንትሙ ፍትሑ ላዕሌየ ወግበሩ ሰላመ ማዕከሌየ ወማዕከለ ብእሲትየ ለእመቦ ዘአበስኩ ቀዲሙ ትንሣኤ ፍዳሃ እምይእዜሰ ዳግመ ኢይኤብስ ወለእመ ትቤለኒ ኅድግ ከዊነ ሐራ ዘንጉሥ አኃድግ ላቲ በከመ ኃረየት ወእንዘ ይትናገር ዘንተ ይበኪ ወያነብዕ፡፡

፲፮ ወሰሚያሙ ቃሎ ይቤልዎ ኢኮነ ዝንቱ ቃልከ እሙነ ዳእሙ ይትዌለጥ፡ጌሠመ፡ወመሐለ በቅድሜሆሙ ጽኑዓ መሐላ ወእምድኅረ ዝንቱ ሖረ አባ ፈትለ ሥላሴ ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወነገራ ጥፍአተ ሀገር ዘኮነ በምክንያተ ዚአሃ ወኵሎ ነገረ ዘተናገረ መልክዓ ክርስቶስ ወዘከመ መሐለ መሐላ ጽኑዓ፡፡





አዝማቾች ጋር በውዶ አገር የሾማቸውን ወታደሮች ይዞ ወዴት አለች ወዴት ደረሰች እያለ አገሩን ሁሉ ዞረ፡፡

፲፫ ወደበረ እንደገባች ነገሩትና የሮቢትን አገር ከቦ አገሩን ሁሉ ያጠፉና ንብረታቸውን ይዘርፉ ምግባቸውን ይበሉ ዘንድ እንዲደረጉላቸው አዘዛቸው ባለታንኳ የሆነውን ሰው በአገኙ ጊዜ አሰረው ንብረቱን ዘረፉ ከብቶችንም ማረከበት እንደአዘዛቸውም አደረጉ፡የአገሩ፡ሰዎች፡ሴቶችና፡ወንዶች፡አለቀሱ፡ታላቅ፡ረብሻም ሆነ፡፡

፲፬ ዳግመኛ የወታደሮቹ አለቃ በባሕሩ አጠገብ ግንብ ሠርተህ በባሕሩ ዳር የእንጨት ቶሞ ሠርተህ እዚያ ላይ እየወጣ ከወዲያና ከወዲህ የሚሸጋገረውን ታንኳ አይተህ ያዘው አለው ብሎ አዘዘው ጌታው እንደ አዘዘው ከዛፍ ያለው ቶሞ አዘጋጅቶ እዚያ ላይ ወጥቶ ቀንና ሌሊት እየጠበቀ ታንኳ ሲመጣ እየወረደ ይዞ ይመረምራቸውና አሷን ሲያጣ ይለቃቸዋል፡፡

፲፭ መልክአ ክርስቶስ ግን ወደ ወይናት ከንጉሥ ሠርፀ ድንግል ልጅ ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ዘንድና ከአባ ፈትለ ሥላሴ ዘንድ ሄደ እነሱም እግዚአብሔር በአንተ ላይ እንዳይቆጣ ድረስ ምንም ያልበደሉህን አገር እንዴት ታጠፋለህ ብለው ተቆጡት እሱም ከእግራቸው ላይ ወድቆ በእኔና በባለቤቴ መካከል እናንተ ፍረዱ ከበደልኳት ዳግመኛ አልበድላትም ከንጉሥ ጋር መዘመትን ተው ካለችኝ እተዋለሁ እሷ እንደፈለገች አደርግላታለሁ አለ ይህን ሲል እያለቀሰ እንባውን ያፈስ ነበር ፡፡

፲፮ እነሱም ቃሉን ሰምተው ይህ ቃል ነገ ይለወጣል እንጂ እውነት አይደለም አሉት እሱ ጽኑ መሐላን በእነሱ ፊት ማለ ከዚህ በኋላ አባ ፈትለ ሥላሴ ወደ እናታችን ቅድስትና ብርክት ወለተ ጴጥሮስ ሄዶ በእሷ ምክንያት አገር መጥፋቱንና መልክዓ ክርስቶስ የተናገረውንም የማለውን ጽኑ መሐላ ነገራት፡፡

፲፯ ወሰሚዓ እምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ ትቤ እንብየ እንብየ ኢይወጽእ እምዝንቱ ገዳም ወኢይትዓረቅዊ ምስሌሁ ወነሥአ አባ ፊትለ ሥላሴ ወይቤላ ለእመ ኃደገዮ አንቲ ወአውሰበ ካዕበ ከልእተ ይከውን ጌጋዩ ላዕሌኪ አንሰ እመክረኪ ይኄይሰኪ ተአርቆ ምስሌሁ ለእመ አበሰ ላዕሌኪ ቀዲሙ ንሥኢ ፍዳኪ ወከመኒ ኢየአብስ ዳግመ እምሐልክዎ አነ ወዓዲ ለእመበከዩ ሰብአ ሀገር በእንተ ጥፍአተቶሙ እግዚአብሔር የኃዝን ላዕሌኪ ወኢያፈቅር ምናኔኪ ወኢይትዌከፍ ጸሎተኪ ወተሰጥወቶ እምነ ቅድስት ወብርክት ወለተጴጥሮስ ለመልክዓ ክርስቶስስ አነ ለእምር ግዕዞ ከመ ኢይቀውም በጽድቅ ባሕቱ እብል አሆ ለቃልከ ኦ አቡየ ወመምህርየ ይኩን በከመ ትቤ ከመኢይኅዝኑ ላዕሌየ ሰብአ ሀገር አንተኒ መሐል ሊተ ከመ ኢታርእየኒ ገጸ ለእምየ ወይቤላ እሆ።

፲፰ ወተሰነዓዉ በዝንቱ ወቀደመ አባ ፊትለ ሥላሴ ሖረ ከመይፈኑ ላቲ በቅለ ወእምነሰ ቅድስት ወብርክት ወለተጴጥሮስ ቤተት ሆየ ርኢክሙን ኦ ፍቁራንየ ሰነ ሂሩታ ለእምነ ቅድስት ወብርክት ወለተጴጥሮስ ዘከመ አግብአት ርእሳ ለመልክዓ ክርስቶስ እንዘ ትብል ይኄይሰኒ እትሐጐል አነ እምይትሐጐሉ ኩሉ ሕዝብ በእንቲአየ፡ወዝንቱ፡ቃል፡ይመስል፡ቃለ እግዚእነ ዘይቤሎሙ ለሠገራት እለ መጽኡ የአኀዝዎ በከመ ይቤ ወንጌል ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ መነኑ ተኀሥሡ ወይቤልዎ ኢየሱስሃ ናዝራዌ ወይቤሎሙ አነ ውእቱ እመሰ ኪያየ ትፈቅዱ ኅድግዎሙ ለእሉ ይሑሩ ።

፲፱ ወእምዝኒ ቅድስት ወብርክት ወለተጴጥሮስ ከማሁ ገብረት ወትቤ ፈቃደ እግዚአብሔር ለይኩን ወውእቱ ይክል አድኅኖትየ ወአልቦ ይዘይሰእና ዘአድኃና ለሳራ እምእደ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ወእምእደ አቤሜሌክ ንጉሠ ጌራራ ውእቱ ያድኅነኒ ዘአድኃና ለሶስና እም እደ ረበናት ውእቱ ያድኅነኒ ዘአድኃና ለእግዚእ ኃረያ እምእደ ሞተሰሚ ውእቱ ያድኅነኒ ወካዕበ ትቤ ኢይፈርሆ ለእኩይ እስመ አንተ ምስሌየ እግዚአብሔር ያበርህ ሊተ ያድኅነኒ ምንትኑ ያፈርሀኒ እግዚአብሔር ምእመና ለሕይወትየ ምንትኑ ያደነግፀኒ በእግዚአብሔር ተወከልኩ ኢይፈርህ ምንተ ይሬስየኒ ሰብእ ዘንተ ወዘይመስሎ እንዘ ትጼሊ ቤተት ኩላ ሌሊተ።





፲፯ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ይህን ሰምታ ከሱ ጋር አልታረቅም ከዚህ ገዳምም አልወጣም እንቢ አለች አባ ፊትለ ሥላሴም አንቺ እንቢ ካልሽና ሁለተኛ ሌላ ሚስት ከአገባ በደሉ በአንች ይሆናል እኔ እመክርሻለሁ ከበደለሽ ይካስሽ ወደፊት እንዳይበድልሺ እኔ አስምየዋለሁ ዳግመኛም ብአንቺ ምክንያት ስለደረሰባቸው ሥቃይ የአገሩ ሰዎች ቢያለቅሱም እግዚአብሐር በአንቺ ያዝናል ምናኔሽንና ጸሎትሽን አይቀበልም አላት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም እኔ መልክዓ ክርስቶስ በመሐላው እንደማይፀና ጠባዩን አውቃለሁ፡ነገር፡ግን፡አባቴና፡መምህሬ፡ሆይ፡የአገሩም፡ሰዎች፡እንዳያዝ ኑ ፡ትእዛዝህን፡አከብራለሁ የእናቴን ፊት እንዳታሳየኝ ማልልኝ አለች እሱም እሺ አለ።።

፲፰ በዚህ ተስማምተው አባ ፊትለ ሥላሴ በቅሎ ይልክላት ዘንድ ቀድሞ ሄደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እዚያው አደረች ወዳጆቼ ሆይ ይህ ሁሉ ሕዝብ ስለኔ ከሚጐዳ እኔ ብጐዳ ይሻላል ብላ እራሷን አሳልፋ ለመልክዓ ክርስቶስ እንደ ሰጠች አስተውሉ ወንጌል እንደተናገረ ጌታችንን ለመያዝ የመጡት ወታደሮች ማንን ትፈልጋላችሁ በአላቸው ጊዜ እነሱም ናዝራዊ ኢየሱስን ነው አሉት እሱም እኔን ከፈለጋችሁኝ ሰዎችን ተውና እኔን ያዙኝ እኔ ነኝ አላቸው።።

፲፱ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም እንደዚሁ አደረገች የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን እሱ እኔን ማዳን ይችላል የሚሳነው ነገር የለም ሣራን ከፈርዖንና ከዓቤሜሌክ እጅ ያዳነ ሶስናን ከክፉዎች መምህራን እጅ ያዳነ እግዚእ ኃረያን ከሞተለሚ እጅ ያዳነ እሱ ያድነኛል አለች ዳግመኛም ክፉን አልፈራም አንተ ከእኔ ጋር ነህና እግዚአብሔር ያበራልኛል ያድነኛልም ምን ያስፈራኛል እግዚአብሔር ለሕይወቴ ጠባቂየ ነው ምን ያስደነግጠኛል በእግዚአብሔር አመንኩ ሰው ምን ያደርገኛል ብየ አልፈራም ይህንና ይህን የመሳሰለውን እየጸለየች ሌሊቱን ሁሉ አደረች።።

፳ ወባሳኒታ አውረዱ ታንኳ ሌሊተ ወአዕረግዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወለእሎን አእማቲሃ ወኮኑ ኖትያተ አባ የማነ ክርስቶስ ወአባ ተዝካረ ድንግል ወሐደፉ ፩ ፍጽመ ወ ፩ ከዋላ ወእንዘ ሀለዉ ማዕከለ ባሕር ሰምዑ ድምጾሙ እሉ ሐራ እለ ይፀንሕዎሙ መልዕልተ ማማ ወአእመርዎሙ በቃሎሙ እስመ ኮኑ እሙንቱ ይጼእልዎ ለመልክዓ ክርስቶስ ወይጸርፉ ላዕለ እሙ ወትጌስጾሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎሙ ለምንት ታበዝኁ ነቢበ ወለምንት ትጸርፉ ዐባየ ብእሲተ አልቦኑ ማዕያ ለአፉክሙ ወወሪዶሙ እምነ ማማ ተኃብእዎሙ ወ መንፈቆሙሰ ሮጹ ኀበ እግዚአሙ ከመ ያብሥርዎ ወእሙንቱሰ በጽሑ ሐይቀ እመብራ ወአርሰዩ ታንኳሆሙ ወኢይሬእይዎሙ ለሐራ እለይትኃብእዎሙ ወይጸንሕዎሙ እስመ ሌሊት ውእቱ ወኢጸብሐ ወነበሩ በሐይቀ ባሕር እስከ ይጸብሕ ወእስከ ይፌንዉ ላቲ በቅለ።

፳፩ ወሶበ ጸብሐ ወጽአ ውእቱ ሊቀ ሐራ እምእለ ተኃብኡ ወፈቀደ የአኃዞሙ ለእሉ መነኮሳት ወሶበ ዐበይዎ ተበአሶሙ ወጸረፈ ላዕሌሆሙ ወይቤሎሙ አንትሙ ዐማፅያን መኮሳት ዘትዔምጹ ብእስተ ብእሲ ዮምሰ ኃደገክሙ እግዚአብሔር ወአግብአክሙ ውስተ እዴየ ወእምዝ አግደመ ሰይፎ ምስለ ቀቀቡ ወዘበጦሙ ከመ ያፍርሆሙ ወለአባ ተዝካረ ድንግልሰ ዘበጦ እገሪሁ ወአቍሰሎ፡ወነበረ፡ትእምርተ፡ቍስል፡ውስተ፡እገሪሁ፡እስከ አመ ሞተ።

፳፪ ወሶቤሃ ተንሥአት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ በዐቢይ መዓት ወጸፍዓቶ መልታሕቶ ወትቤሎ አንተ ዕቡይ ገብር እፎ ደፈርከ ወተሣለቀ ላዕሌየ ወእሉሰ ሐራ በጽሁ ኀበ መልክዓ ክርስቶስ ወነገርዎ ወሰሚዖ ተንሥአ በትፍሥሕት ወተጽዕነ ፈረሶ ወበጽሐ እንዘ ያረውጽ ወረስዓ መሐላሁ ወፈቀደ ይምስጣ ወይንሥኣ በከሃ እንበለ ያእምሩ አባ ፌትለ ሥላሴ ወወለተ ጊዮርጊስ ወወገረ ቆብዓ እምላዕለ ርእሳ ወለከፉ ንስቲተ በእገሪሁ፡እንተ፡ድኅሬሁ፡ወይቤላ፡ተንሥኢ፡ወሶቤሃ፡ወድቀት፡እምነ፡ቅድ ስት፡ወቡርክት፡ወለተጴጥሮስ፡ወአምሰለት፡ርእሳ፡ከመ፡ምውት፡ወአርመ መት፡ወኃደገት፡አንሳሐስሖ፡በእከይ፡ወስእንዋ፡ከመ፡ያጽዕንዋ፡በበቅል፡ወእ ዘዞሙ ለሐራሁ ከመ ይጹርዋ በልብስ እኂዞሙ በዓርባዕቱ ጽነፌሁ፡





፳ በማግሥቱ ታንኳ አውርደው በሌሊት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ከእነዚያ አገልጋዮቿ ጋር ከታንኳ ላይ አስወጧት ቀዛፊዎችም አባ የማነ ክርስቶስና አባ ተዝካረ ድንግል ነበሩ እነሱም አንዱ ከፊት አንዱ ከኋላ እየቀዘፉ ሄደው ከባሕር መካከል ሲደርሱ እነዚያ እንጨት ላይ ሁነው የሚጠብቋቸው ወታደሮች በአነጋገራቸው የመልክአ ክርስቶስን እናቱን ሲረግሙ ሰምተው አወቋቸው እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለምን ንግግር ታበዛላችሁ ትልቅ ሴት ወይዘሮንስ ለምን ትሳደባላችሁ አንደበታችሁ የታረመ ይሁን አለቻቸው እነዚያም ወታደሮች ከቆጥ ላይ ወርደው ተደብቀው ይጠብቋቸው ጀመር ግማሾቹ የምሥራች ሊነግሩት ወደ ጌታቸው እየተሯሯጡ ሄዱ መነኮሳቶች ግን ተደብቀው የሚጠብቋቸውን ወታደሮች ስለአላዩ ከመብራ፡ወደብ ታንኳቸውን አስጠግተው፡ሌሊት፡ስለነበር አልነጋምና እስኪነጋና በቅሎ እስኪልኩላት ከሐይቅ ዳር ተቀመጡ ።

፳፩ በነጋ ጊዜ ያ ከተደበቁት የወታደሮች አለቃ ወጥቶ እነዚያን መነኮሳት ሊይዛቸው ፈለገ አንያዝም በአሉት ጊዜ ተቆጥቶ እናንተ አመፀኞች መነኮሳት የሰውን ሚስት የምትቀሙ ዛሬስ እግዚአብሔር በረድኤት ከእናንተ ተለይቶ በእጄ አሳልፎ እናንተን ሰጠኝ ብሎ ሰደባቸውና ሰይፉን ከነአፎቱ አጋድሞ ያስፈራራቸው ዘንድ፡መታቸው፡አባ፡ተዝካረ፡ድንግልን፡ግን፡እግሩን፡መትቶ፡አቆሰለው፡ እስከ፡ሚሞትበትም፡ጊዜ፡ድረስ፡የቁስሉ፡ምልክት፡በእግሩ፡ላይ ነበር ።

፳፪ በዚያን ጊዜ ፡እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በታላቅ ቁጣ ተነስታ አንተ ክፉ ባሪያ እንዴት ደፈርከኝ ብላ በጥፊ መታችው እነዚያ ወታደሮችም ወደመልክአ ክርስቶስ ሄደው ነገሩትና ሰምቶ በደስታ ፈረስ ላይ ተጭኖ እየጋለበ ደረሰ መሐላውንም አፍርሶ ነጥቆ በዚያው ይወስዳት ዘንድ አባ ፌትለ ሥላሴ ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ሳያውቁ ከራሷ ላይ ቆቧን ወርውሮ፡ከኋላዋ፡ተነሺ፡ብሎ፡ነካ፡አደረጋት፡ያንጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት፡ወለተ፡ጴጥሮስ፡እንደሞተ፡ሰው፡ሁና፡መንቀሳቀስ፡እምቢ፡አለ ች።

፳፫ ወስእንዋ አንቀልቅሎታ ወእምዕሡብ ጸርዋ ንስቲተ ወሀሉ በፍኖት አስዋክ እምለፌ ወእምለፌ ወዓጸበሙ ለሐዊር ወአውረድዋ ውእቱስ ይትመዐዕ ወየሐቂ ስነኒሁ ወያፈርሆሙ ወይቄጽር ገጸ ላዕሌሆሙ ወይእተ ጊዜ አኃዙ ያስተበቍዕዋ በቃለ ርኅራኄ እንዘ ይብሉ ኦ እግዝእትነ ርኅርኅት ወመስተሣህልት ተራኅርኂ:ወተሣሃሊ:ላዕሌነ ከመ ልማድኪ ወለእመ አበይክነ ወስዕነ ጸዊሮተኪ ይትመዓዓነ እግዚእነ ወይቀትለነ ኦሆ በልነ ወተሣሃልነ::

፳፬ ወሰሚዓ ቃሎሙ ተራኅርኃት ላዕሌሆሙ ወተንሥአት ከመ ያጽዕንዋ በቅለ ወእንዘ ይትባሀሉ ከመዝ በጽሑ ልዑካን እለ ተፈነዉ እምኀበ አባ ፈትለ ሥላሴ ወእምኀበ ወለተ ጊዮርጊስ ወይቤልዎ እፎ ሐሰውከነ ወሔጥከነ ወሖርከ ጽሜተ እንዘ ኢነአምር ንሕነ ትምስጣ በፍኖት ከመ ሠራቂ ወፈያቂ ወመከርከ ምክረ ደቂቅ ወኢይከውን ሠናየ ዝንቱ ምክርከ ወይእዜኒ ንብለከ ነዓ ዝየ ወይእቲኒ ትምጻእ ወንግበር ዕርቀ ማዕከሌክሙ:እመሰ:አበይከ:መጺአ:ወአስተኃቀርከነ:ለነ:ወአስተትከ ቃለነ ንትገፋዕ ንሕነ እምኔከ እግዚአብሔርኒ ይትገፋዕ ምስሌነ ወሰሚዖ:ዘንተ:መልእክተ ፈርሃ ወተመይጠ ወሖረ መንገሌሆሙ::

ምዕራፍ ፫ ዘሠሉስ

፩ ወለእምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አጽዓንዋ በቅለ ወወሰድዋ ወአብጽሕዋ ኀቤሆሙ ወናየት ወበህየ አስተዋቀሥዎሙ ወዓረቅዎሙ ወፈነውዎሙ በሰላም ወአተዉ ብሔሮሙ ስማዳ ወእምዝ ነበረት እንዘተኃሥሥ ምክንያተ ከመ ትትፈለጥ እምኔሁ ወበውእቱ መዋዕል ተወጥነ ሃይማኖተ አፍርንጅ ወቀተልዎ ለአቡነ ስምዖን ጳጳስ ምስለ ዮልዮስ ወኮኑ ሰማዕተ ወውእቱ ብእሲ ቀታሊ ጳጳስ ነሥአ ልብሰ ጳጳስ ወወሀበ ለመልክአ ክርስቶስ ወሶበ አእመረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ አንሶጠጠ ሕሊናሃ ወአስቈረረቶ ለመልክዓ ክርስቶስ ወአበየት ቀሪበ ኀቤሁ ወኃደገት ሰኪበ ምስሌሁ ወትቤሎ እፎ እነብር ምስሌከ ዘኢኮንከ ክርስቲያነ ወአቅተልከ ጳጳስ ወናሁ ሀሎ ኀቤከ ልብሰ ጳጳስ::





፳፫ በዚን ጊዜ ወታደሮች በበቅሎ ይጭኗት ዘንድ ተሳናቸውና ወታደሮቹ ዐራት ሁነው በልብስ አድርገው እንዲሸከሟት አዘዛቸውና በጭንቅ ተሸክመዋት ሲሄዱ መንገድ ላይ በወዲያና በወዲህ እሾህ ነበርና ለአራት ማለፍ ሲሳናቸው አወረዷት እሱ ግን እዴት ያቅታቸዋል እያለ ጥርሱን እየነከሰ ይቆጣቸው ፊቱን እያጠቆረ ያስፈራራቸው ነበርና ያንጊዜ ርኅሪት እመቤታችን ሆይ ባክሽን አንቺን መሸከም አቅቶናልና ራርተሽ ተነሺልን ጌታችን እየተቆጣን ነውና አሏት ::

፳፬ ቃላቸውን ሰምታ ራርታ በበቅሎ ይጭኗት ዘንድ ተነሥታ እየሄደች ሳለ አባ ፈትለ ሥላሴና ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ የላኩዋቸው መልእክተኞች ደርሰው የሕፃናት ምክር ከእኛ ጋር መክረህ እንደሸፍታና እንደሌባ ተሸሽገህ ቀምተህ እንዴት ትሄዳለህ ይህ ምክርህ መልካም አይደለም አሁንም ከእኛ ዘንድ መጥተህ በመካከላችሁ እርቅ እናድርግ ነገር ግን እኛን ንቀህ እምቢ ብትል እኛም እንጠላሃለን እግዚአብሔርም ከእኛ ጋር ይጣላሃል አሉ ይህን መልክት ሰምቶ ፈራና ከእነሱ ጋር ሄደ::

ምዕራፍ ፫ የማክሰኞ

፩ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስንም በበቅሎ ጭነው ከእነሱ ጋር ወደነያት አደረሷትና በዚያ አወቃቅሰው አስታርቀው በሰላም ሸኟቸው እነሱም ወደ አገራቸው ስማዳ ገቡ ከዚህ በኋላ ከእሱ ትለይ ዘንድ ምክንያት ትፈልግ ጀመር በዚያን ዘመን የካቶሊክ እምነት ተጀምሮ ጳጳሱ አቡነ ስምዖንን ከዮልዮስ ጋር በሰማዕትነት ገደሉት ያም ጳጳሱን የገደለ ሰው የጳጳሱን ልብስ ወስዶ ለመልክዓ ክርስቶስ ሰጠ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ይህን ባወቀች ጊዜ ልቡናዋ ተፀይፎ መልክዓ ክርስቶስን ናቀችው ወደ እሱም መቅረብና ከሱም ጋር መተኛት እምቢ አለችው ከአንተ ጋር እንዴት እኖራለሁ አንተ ክርስቲያን አይደለህም ጳጳስን አስገድለሃልና አለችው::

፪ ወእምዝ ሖረመት መብልዓ ወመስቴ ወኃደገት ተሰንዮ ከመሥርዓተ አንስት እመሂ ተጸፍሮ ሥእርት ወተቀብዖ ቅብዕ ወአፈዋት ወተዓጥኖ መዓዛ ዘዘዚአሁ ወገቢረ ጥምዓታተ ኀምር ዘአጽፋር ወተኰህሎ ዓዕይንት ወተሠርግዎ አልባስ ዘንተ፡ኵሎ ወይመስሎ ኃደገት ወነበረት ከመ መነኮሳት ወአኅሠረት -ርእሳ በኵሉ ግብር ወእምዝ ሶበ ርእየ ግብራ ወጥብዓተ ልባ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ወዓዲ ሶበ ኮነ ፈቃደ እግዚአብሔር ይቤላ ለሊሁ በፈቃዱ እንዘ አልቦ ዘያገብሮ እስከ ማእዜኑ ትነብሪ ምስሌየ በዘከመዝ ግብር ሑሪ ኀበ ፈቀድኪ ወኢይከልአኪ ወትቤሎ መሐል ሊተ ከመ ኢትወልጥ ቃልከ ወመሐለ ላቲ ውእቲኒ ይቤላ ከማሁ ወመሐለት ሎቱ::

፫ ወበሳኒታ ትቤሎ ፈንወኒ በከመ ቃልከ ወይቤላ ኦሆ ወአዘዞሙ ለሐራሁ ይርኃኑ በቅለ ወያጽእንዋ ወይሰድዋ ወለአከ ኀበ አዝማዲሃ እንዘ ይብል ንሥኡ ወለተክሙ እምከመ ተዓረቀ ምስሌሃ ኢያስተፍሥሐተኒ አላ አህዘነተኒ ወኢኮነት ምስሌየ አሐደ አባለ ከመ በሥርዓተ ብእሲ ወብእሲት እምይእዜሰ ትግበር ዘፈቀደት ወዘሐለየት ወይእተ ጊዜ አስቆቀዉ ወበከዩ ኵሉ ሰብአ ቤት እድ ወአንስት ወይቤልዎ ለእግዚአሙ ኢትኅድጋ ትሑር ወይቤሎሙ አንሰ መሐልኩ ወኢይትከሃለኒ:እኃዛ:አኮ:ውእቱ:ዘኃደጋ:አላ:ከልአ:ፈቃደ:እግዚአብሔር:ወ ይእተ:ጊዜ:ተጽእነት:በቅለ:እምነ:ቅድስት:ወቡርክት:ወለተጴጥሮስ :ወሖረት:ፍኖታ:ወአስተፋነውዋ:እድ:ወአንስት:እንዘ:ይበክዩ ወያስቆቅዉ እስመ ኃደገቶሙ ::

፬ ወተመይጡ በኃዘን ውስተቤቶሙ ወእሉሰ እለተፈነዉ ምስሌሃ አብጽሕዋ ኀበ ቤተ እኁሃ ዘድንግል ወነገርዎ መልእክቶሙ ወተመ ይጡ:ኀበ:ሀገሮሙ:ወተወከፋ:ውእቱኒ:ወአንበራ:ኀቤሁ:ወይእቲ ኒ:ተፈሥሐት:ወተሐሥየት:ፈድፋደ: ወአእኰተቶ:ለእግዚአብሔር:ወትቤ:አብደርኩ:እትገደፍ:ውስተ :ቤተ እግዚአብሔር:እምእንበር:ውስተ:ቤተ:ኃጥአን:ወሶበ:ወጽአት:እምነ:ቅድ ስት:ወቡርክት:ወለተጴጥሮስ:እምነ:ቤታ:ኢነሥአት:ምንተኒ:ኢወርቀ: ወኢብሩረ:ወስንቀ:ለፍኖት:ኢበትረ:ወኢዓሣዕነ:እንዘ:ብእሲተ:መኮንን: ወወለተ:ክቡራን:ይእቲ:በከመ:ይቤሎሙ:እግዚእነ:ለሐዋርያት:ኢታ ጥርዩ:ለክሙ:ወርቀ:ወኢብሩረ ::





፪ ከዚህ በኋላ መብልና መጠጥ ትታ እንደ ሴቶች ፀጉር መሠራትን ቅባትና ሽቶ መቀባትን ስንቡልንና ጡንጂት መታጠንን እንሶስላ መሞቅ ቅያሬ ልብስ መልበስንና የመሣሰሉትን ትታ እንደ መነኮሳት ሥርዓት እራሷን ጥላ ተቀመጠች ከዚህ በኋላ ሥራዋንና ጭካኔዋን በአየ ጊዜም በእግዚአብሔር ፈቃድ ማንም ሳያስገድደው እራሱ ፈቅዶ እስከመቼ እንደዚህ ሆነሽ ከእኔ ጋር ትኖሪያለሽ ወደ ወደድሽበት ሂጂ እኔ አልከለክልሽም አላት እሷም ቃልህን እንዳትለውጥ ማልልኝ አለችው ማለላትና እሱም ማይልኝ አላት ማለችለት::

፫ በማግስቱ እንደቃልህ ሸኘኝ አለችው እሱም እሺ ብሎ ወታደሮቹ በበቅሎ ጭነው ይወስዷት ዘንድ አዘዘ ከእሷ ጋር ከታረቅሁ ጀምሮ በባልና ሚስት ሥርዓት አንድ አካል አልሆንምና ልጃችሁን ውሰዱ ከዛሬ ወዲህ የፈለገችውን ታድርግ ብሎ ወደ ዘመዶቹ ላከ ያን ጊዜ በቤት ያሉ የወንድና የሴት አገልጋዮች እያለቀሱ ትሄድ ዘንድ አታሰናብታት አሉት እሱም መልሶ እኔ ምያለሁና ልከለክላት አልችልም አላቸው እንድትሄድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ ነው እንጂ እሱ ወዶ ያሰናበታት አይደለም በዚህን ጊዜ እናታችን ቅድስት እና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በበቅሎ ላይ ተቀምጣ ጉዳናዋን ቀጠለች ወንዶችና ሴቶች በጣም እያለቀሱ ሸኟት ተለይታቸዋለችና::

፬ በኃዘን ወደቤታቸው ተመለሱ ከሷ ጋራ የተላኩትም ከዘድንግል ወንድሟ ቤት አድርሰው መልክታቸውን ተናግረው ወደ አገራቸው ተመለሱ እሱም ተቀበላትና ከቤቱ አስገባት እሷ ግን እጅግ ተደስታ በኃጥአን ቤት ከመኖር ይልቅ በቤተ እግዚአብሔር መጣልን ወደድሁ እያለች እግዚአብሔርን አመሰገነች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የመኰንንና የከበሩ የባለ ፀጐች ልጅ ስትሆን ለመንገድ ወርቅና ብር ለእግሯ ጫማ ለመንገድ ስንቅ ምንም አልያዘችም ጌታችን ለሐዋርያት ወርቅና ብር አትያዙ እንዳላቸው::

፭ ወይእቲስ ወጽአት እራቃ እንዘ ትብል ዕራቅየ ወጻእኩ እምከርሠ እምየ ወዕራቅየ እገብእ ውስተከርሠ መቃብር በከመ ይቤ ዳዊት ይኄይሰኒ ሕገ አፉከ እምአእላፍ ወርቅ ወቡሩር በእንተዝ አፍቀርኩ ትእዛዘከ እምወርቅ ወእምጳዝዮን ምንትኑ ትእዛዙ ለእግዚአብሔር አኮኑ መንኖ ጥሪት ወጻዊረ መስቀል ውእቱ ወእግዚእነሂ ይቤ ይቀልል ገመል ይኅልፍ እንተ ስቁረተ መርፍዕ እምይባእ ባዕል መንግሥተ ሰማያት ወጳውሎስኒ ይቤ ወስርወ ለኵሉ እከይ አፍቅሮ ንዋይ እስመ በዛቲ ስሕቱ ወዓለዉ ሃይማኖቶሙ ብዙኃን ወበእንተዝ እምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ፈድፋደ ትጸልእ ወትሬስዮ ከመ ወኢምንት፡፡

፮ ወእምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል ሶበ ሐለየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ከመ ትሑር ወትመንኩስ ትቤሎ ለእኁሃ ዘድንግል አብሐኒ እሑር ኀበ መምህርየ ከመ አሐውጾ እስመ ውእቱ ይደዊ ወየሐምም ወጉንዱይ መዋዕል እምዘ ርኢክዎ አነ ወለእመ ሞተ እንዘ ኢይሬእዮ ይረግመኒ እስመ አበ መንፈስ የዓቢ እምአበ ሥጋ ወይቤላ ኦሆ ወኢያእመረ ከመ ትቤሎ በጒጣን ወበተጥባበ ነገር ወመሰሎ እሙነ ወአዘዞሙ ለወዓልቱ ይርኃኑ ላቲ በቅለ ወያጽዕንዋ ወይጸወንዋ ወይሰድዋ ኀበ መምህራ ወገብሩ ላቲ በከመ አዘዞሙ ወሖረት፡፡

፯ ወሀለዋ ምስሌሃ አእማት እለ ይተልዋሃ ወሶበ ቀርበት ለበጺሐ ኀበ ውእቱ ሀገር ትቤሎሙ አውርዱኒ ዝየ ዮምሰ አኃድር በህየ ወኢያከብድ አርዑተ ላዕለ መምህርየ እስመ ብዙኃን ንሕነ ወኢይክል ጸዊርተነ አንትሙኒ ግብኡ ፍኖተክሙ ወትትቄበሉኒ ከልእ ዕለተ እስመ አነ እጐንዲ ኀበ መምህርየ ወዘንተ ብሂላ ፈነወቶሙ ወሖሩ ወአቅደመት አእምሮ ዘንተ ምክረ በኀበ መምህራ ወተጥበበት ከመ ኢይኅዝኑ ላዕሌሁ ወኢይጽልእዎ ወተርፈት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ምስለ አእማቲሃ ፡፡





፭ እሷም ከእናቴ ማህፀን እራቁቴን ወጣሁ ዳግመኛም እራቁቴኂ ወደ መቃብር እመለሳለሁ አለች ዳዊትም ከብዙ ወርቅና ብር ሕግህ ይሻለኛልና ስለዚህ ከወርቅና ከዕንቁ ይልቅ ትዕዛዝህን ወደድኩ አለ የእግዚአብሔር ትዛዙ ወርቅና ብር መናቅን መከራ መስቀልን መሸከም አይደለም ጌታችንም ባለጸጋ መንግሥተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል አለ ጳውሎስም የክፋት መሠረቷ ገንዘብ መውደድ ነው በእሱም ብዙዎች ሃይማኖታቸውን ክደው መናፍቅ ሆነዋልና ስለዚህ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እጅግ እንደ ኢምንት ትጠላው ነበር፡፡

፮ ከጥቂት ወራት በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሄዳ ትመነኩስ ዘንድ ባሰበች ጊዜ ወንድሟ ዘድንግልን ወደ መምህሬ ሄጀ እጠይቀው ዘንድ አሰናብተኝ እሱ እጅግ ታሟል እኔም ካየሁት ብዙ ዘመን ሆኗልና ሳላየው ቢሞት ይረግመኛል ከሥጋ አባት የመንፈስ አባት ይበልጣልና አለችው እሱም እንደምታታልለው ሳያውቅ እውነት መስሎት በበቅሎ ጭነው ይወስዷት ዘንድ አገልጋዮቹን አዘዘ እንዳዘዛቸውም አደረጉለትና ወደ መምህሯ ሄደች፡፡

፯ የሚከተሏት አገልጋዮቿ ከሷ ጋራ ነበሩ ወደዚያ ሀገር ለመድረስ ጥቂት ሲቀራት እዚህ አውርዱኝ ዛሬ እዚህ አድራለሁ በመምህሬ ላይ እንግዳን በማብዛት ከባድ ሸክም አላሸክምም እኛ ብዙዎች ነንና እኛን ለማስተናገድ ይከብደዋል እናንተ ተመልሳችሁ ግቡ ሌላ ጊዜ ትቀበሉኛላችሁ እኔ ከመምህሬ ዘንድ እቆያለሁ አለቻቸውና ሸኘቻቸው እነሱም ተመልሰው ሄዱ አስቀድማ ይህን ምክር የመከረቻቸው በመምህሯ እንዳያዝኑ እና እንዳይጠሉት ነው፡፡

፰ ወቦአት እምነ ውስተ ቤተ ፩ዱ እምሰብአ ሀገር ወቤተት ወሶበ ኮነ ዕቅበተ ሌሊት እንዘ ይነውማ ኵሎን አእማት አንቀሀታ ለአሐቲ ሕፃን ከመ ትትልዋ ወወጽአት ጽሚተ ምስለ ይእቲ ሕፃን ወሖረት በእግር እንዘ ይውሕዝ ደማ ከመማይ ወእንዘ ይትለካዕ ቅንዋተ ዕብን በሊሕ ውስተ እገሪሃ እስመ ልምሉም ውእቱ ከመ እግረ ሕፃን ዘወጽአ እምከርሠ እሙ ወእለ ርእዩ ሰብእ ውእተ ደመ ይትበሀሉ በበይናቲሆሙ ምንትኑ ዝንቱ ደም ደመጠሊኑ አው ደመ በግዕ ዘመሠጠ ነምር ወእመ አኮ ዘጠብሐ ሠራቂ።

፱ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ተሐውር በበንስቲት ምስለ ይእቲ ሕፃን በጽሐት ሀገረ ሮቢት ውስተ ቤተክርስትያነ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ዘበአታ ውስተ ቤተመቅደስ ወነበረት በዴዴሆሙ ለሰብአ ይእቲ መካን ወይቤልዋ አልብነ ማኅደር ተንሥኢ ዝየሰ አላ ሑሪ ውስተ ሀገር ኀበ ትረክቢ ማኅደረ ወትቤሎሙ አንሰ ኢይሐውር ሀገረ አላ አኃድር በ ዴዴክሙ ወሶበ መስየ አብእዋ ውስተ ቤት ዘኃደገቶ መነኮሳይት ወሖረት በይእቲ ሰሙን ወኃደረት ውስቴቱ እምነ ቅድስት ወቡርክት ምስለ ይእቲ ሕፃን ወአፍቀረቶ ፈድፋደ ለውእቱ ቤት ወፈቀደት ትንበር ኀቤሁ እስከ ትትፈታሕ እምእግዚአብሔር።

፲ ወይእቲሰ ሕፃን ሆከታ ዓቢየ ሁከተ ዘይበዝኀ እምሁከተ ፪ት ሰብእ ወኃዘነት ፈድፋደ ወትቤ እመ ረከብኩ ሰብአ ዘይወስድ ሊተ እምፈነውክዋ ወእምኀየሰኒ እንበር ባሕቲትየ ከመአዕርፍ እምሁከት ወአህሉ በኀድአት ወሶበ ርእዮ እግዚአብሔር ጽንዓ ኃዘና አምጽአ ላቲ አሐተ ብእሲተ እንተ ተሐውር ኀበ ይእቲ ሀገር ወሰአለታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ለይእቲ ብእሲት ከመ ታብጽሐ ኀበ ሀገራ ወፈነወታ ምስሌሃ ወተርፈት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ባሕቲታ ወባሕቱ እግዚአብሔር ኢኃደጋ ወበይእቲ ዕለት መጽአት አሐቲ ወለት እንተ ተፈነወት እምለባሲተ ክርስቶስ ዘሀለወት በፉሬ።





፰ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከሀገሩ ሰዎች ወደ አንዱ ቤት ገብታ አረፈች ሌሊት በሆነ ጊዜ ገረዶቿ ተኝተው ሣሉ አንዷን ገረድ ጠርታ አስከትላ ደሟ እንደውሃ እየፈሰሰ እንቅፋት እየመታት ጠጠር እየወጋት በእግሯ ሄደች እግሯ እንደ ሕፃን እግር የለሰለሰ ነውና ሰው ይህን ደም ባየ ጊዜ ነብር የበላው የፍየል ደም ነው ወይስ ሌባ ሰርቆ ያረደ የበግ ደም ነው ተባባሉ።

፱ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጥቂት ጥቂት እያለች ወደ ሮቢት አገር ደርሳ ከእመቤታችን በአታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አረፈችና በዚያ አካባቢ ከአሉት ሰዎች ደጅ ሂዳ ተቀመጠች እነሱም ማደሪያ የለንምና ማደርያ ወደምታገኚበት ወደ ሌላ ቦታ ሂጂ አሏት እሷም እኔ ሌላ ቦታ አልሄድም እዚሁ ከደጃችሁ አድራለሁ አለቻቸው በመሸ ጊዜ በዚያን ሰሞን አንዲት መነኩሴ ጥላ የሄደችው ቤት አስገቧት እናታችን ወለተ ጴጥሮስም ገብታ ከእዚያች ልጅ ጋር አደረች ያችንም ጐጆ እጅግ ወደደችና እግዚአብሔር እስከ አሰናበታት ድረስ እዚያው ሰነበተች።

፲ ያችም ልጅ መቶ ሰው ከሚያስቸግር ይልቅ አስቸገረቻት እጅግ አዝና ወደሀገሯ የሚመልስልኝ ሰው ባገኝ ከጭቅጭቅ በአረፍኩና በፀጥታ በኖርኩ ነበር አለች እግዚአብሔር የሐዘኗን ጽናት በአየ ጊዜ ወደዚያች አገር የምትሄድ አንዲት ሴትን አመጣላት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ያችን ሴት ይችን ልጅ ወደ አገሯ አድርሽልኝ ብላ ጠየቀቻትና እሷም እሺ ብላ ይዛት ሄደች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ብቻዋን ቀረች ነገር ግን እግዚአብሔር በረድኤት አልተለያትምና በዚያች ቀን በፉሬ ከአለች ከለባሲተ ክርስቶስ ዘንድ አንዲት ልጅ ተልካ መጣች።

፲፩ እስመ ይእቲ ሰምዓት ዜናሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ፈነወታ ለይእቲ ወለት ከመ ተሐውጻ ወትጠይቅ ሀልዎተ ዚአሃ ወመጽአት ባሕቲታ ምስለ ኃለፍተ ፍኖት ወቀርበት ኀበ ውእቱ መካን ወሐተተት እንዘ ትብል አይቴ ተኀድር ዛቲ እንግዳ ወበጽሐት እንዘ አልቦ ዘይመርሓ ወቆመት በአንቀጽ ወጠፍሐት እደዊሃ ከመ ሥርዓተ ደብር ወአውጽአት ርእሳ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ እምኆኅት ወነጸረታ ወቀጸበታ በእደዊሃ እስመ ይእቲ ባሕቲታ ሀለወት በይእቲ ዕለት ወአልቦ ዘይትለአካ ወቀርበት ይእቲ ወለት ኀቤሃ ወትቤላ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ እምአይቴ አንቲ ወኀበ መኑ መጻእኪ ::

፲፪ ወትቤላ ፈነወተኒ ኀቤኪ እግዝእትየ ለባሲተ ክርስቶስ ወትቤለኪ እፎ ሀሎኪ ወእፎ ሀልዎትኪ ሰላም ለኪ ወሰላመ እግዚአብሔር የሀሉ ምስሌኪ ወሰሚዓ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ:ዘንተ አምኃ አንከረት ወሰብሐቶ ለእግዚአብሔር ዘኢኃደጋ ዕለተ ባሕቲታ ትኅድር ወኃደረት ምስሌሃ በይእቲ ዕለት ወበሳኒታ ትቤላ አብሕኒ እሑር ኀበ እግዝእትየ ወአግብእ ላቲ ሥጣዌ መልእክት እንተ እምኀቤኪ ወትቤላ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ንበሪ ምስሌየ ዛተ ሰሙነ እስመ ባሕቲትየ አነ ወትቤላ እሆ እስመ ሠናይተ ግዕዝ ይእቲ ወለት ወንባበ ቃላ ሥዑሩዕ ወጥዕጡዕ::

፲፫ ወትትፌቀር በኀበ ኵሉ ወነበረት ምስሌሃ ወአስተፍስሐታ ምክዕቢተ ህየንተ ኮነት ቀዳሚት ኀዘንተ በእንተ እከያቲሃ ለዛቲ ሕፃን ዘሖረት ርእክሙኑ ፍትሐ አእምሮቱ ለእግዚአብሔር ለሕፃን እንተ መጽአት ወተሰደት ምስሌሃ ሰደደ ወለዛቲሰ እንተ ኮነት ርኅቅተ ሰሀባ ወአቅረባ ወረሰያ ትንበር ምስሌሃ እስመ ከሃሊ ውእቱ በከመ ፈቀደ ይገብር ወበከመ ሐለየ ይፌጽም ወአልቦ ዘይክል ተዋሥኦቶ ያእትቶ ለልጹቅ ወያቀርቦ ለርሑቅ እስመ ውእቱ ፈታኔ ልብ ወኵልያት::





፲፩ እሷ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን መምጣት ሰምታ ነበርና መኖሯን ትጠይቃት ዘንድ ያችን ልጅ ላከቻት ያችም መልዕክተኛ ከመንገደኞች ጋር መጥታ እሷ ወደ አለችበት ቤት ቀርባ ይህን ሰሞን የመጣች እንግዳ ሴት የት ናት እያለች እየጠየቀች የሚነግራት ሰው ሳይኖር ሂዳ እሷ ካለችበት በር ላይ ቆማ እንደገዳም ሥርዓት ሌሊቱን ፀፋች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም አንገቷን አውጥታ በአየቻት ጊዜ በእጇ ጠቀሰቻት በዚያች ቀን ብቻዋን ነበረችና የሚላላካት የለምና ያችም ልጅ ወደ እሷ ቀረበች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም አንቺ የት ነሽ ከወዴት መጣሽ አለቻት ::

፲፪ እሷም እመቤቴ ለባሲተ ክርስቶስ ወደ አንቺ ላከችኝ እንዴት አለሽ እንዴት ነሽ የእግዚአብሔር ሰላም ከአንቺ ጋር ይሁን ብላሻለች አለቻት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ይህን ሰላምታ ሰምታ ብቻዋን ያልተዋት እግዚአብሔርን አመሰገነች በዚያች ቀንም ከእሷ ጋር አደረች በማግሥቱም ከአንቺ ዘንድ ያገኘሁትን ምልክትና ሰላምታ አደርስላት ዘንድ አሰናብችኝ ወደ እመቤቴ ልሂድ አለቻት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም እኔ ብቻየን ነኝ ና በዚህ ሰሞን ከኔ ጋር ሁኝ አለቻት እሷም መልካም ፀባይ ያላት ልጅ ናትና እሺ አለቻት የቃሏ አነጋገር የለሰለሰና የቀና ያማረ ነውና ::

፲፫ በሁሉም ዘንድ የምትወደድ ናትና ከእሷ ጋር ተቀምጣ ያች ስለ አሳዘነቻት ፈንታ እጥፍ አስደሰተቻት የእግዚአብሔር ድንቅ ፍርድን አያቹሁን ከእሷ ጋር የመጣችውን ልጅ እንድትሄድ አድርጐ የህችን የራቀችውን አቀረባትና ከእሷ ጋር እንድትቀመጥ አደረገ ሁሉን ቻይ ነውና የወደደውን ያደርጋል ያሰበውን ይፈጽማል ይህን ለምን አደረክ ብሎ እሱን መናገር የሚችል የለም አንድ ላይ የነበረውን ያስወግዳል የራቀውን ያቀርባል ልብ ያመላለሰውን ኩላሊት ያጤሰውን ያውቃል::

፲፬ ወእንዘ ትነብር እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ምስለ ይእቲ ወለት በውእቱ መዋዕል መጽአ አባ ጽጌ ሃይማኖት እምነ ፉሬ ከመ የሐውጻ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ሶበ ሰምዓ ዜናሃ ከመ ሀለወት በሮቢት ወበጺሖ ህየ ተራከበ ምስሌሃ ወአእመረ ከመ ሀለወት ባሕቲታ ወይቤላ አንቲ ሕፃን እፎ ትነብሪ ባሕቲተኪ ዘእንበለ ቢጽ ወኢይከውን ሠናይ ለኪ አውሥአቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎ እፎ እገብር ወእምአይቴ እረክብ ቢጸ እንተ ትነብር ምስሌየ አኮኑ አነ ፈላሲት በዛቲ ሀገር።

፲፭ ወአውሥአ ወይቤላ እመሰ ትፈቅዲ እምአምጻእኩ ለኪ አነ ሀለወት አሐቲ ብእሲት ሠናይት እንተ ትሰመይ እኅተ ክርስቶስ ዘኃደገት ከማኪ ምታ ወቤታ ወመንኮሰት ወትነብር ይእዜ ምስለ እኅታ ወዝንቱ እምኮነ ሠናየ ለክልኤክን አውሥአቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት:ወለተጴጥሮስ:ወትቤሎ:አንሰ:ኢይፈቅድ:ነቢረ:ምስለ:ብእሲት :እንተ:ኃደገት:ቤታ:አውሥአ ወይቤላ አንሰ አአምር ግዕዛ ለይእቲ ብእሲት ሠናይት ይእቲ እመሰ ርኢኪያ አንቲ እምአፍቅርኪያ።

፲፮ ወዘንተ ብሂሎ ወፅአ ወሖረ ፉሬ ወይቤላ ለእኅተ ክርስቶስ እመ ነበርኪ ምስለ እኅትኪ ባጥንቃቄ ወአግዘፍኪ ሥጋኪ በመብልእ ወመስቴ ማእዜ መነንኪ ዓለመ ወምንትኑ ሠናየ ኃደጊ በእንተ እግዚአብሔር እምንብረትኪሰ ዘይእዜ እምኃየሰኪ ትንበሪ ምስለ ምትኪ እመሰ ትሰምዒ ቃልየ ወትትዌከፊ ነገርየ አንሰ እመክረኪ ይሄይሰኪ ትንበሪ ምስለ ወለተጴጥሮስ ዘሀለወት በሮቢት እስመ:ሠናይት:ብእሲት:ይእቲ:ወከሠተ:ላቲ:ኵሎ:ግብራ:እምጥንቱ: እስከ:ተፍጻሜቱ አውሥአቶ ወትቤሎ አንሰ ኢይፈቅድ እንበር ምስለ ብእሲት:ዘነበረት:በከተማ:እመነበርኩ:ምስሌሃ:ምንተ :ትሜህረኒ:ወምንተ አርአያ እነሥእ እምኔሃ ወክልኤነ ሐዲሳት አትክልት ንሕነ።





፲፬ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከዚያች ልጅ ጋር ተቀምጣ ሳለች በዚያን ጊዜ አባ ጽጌ ሃይማኖት በሮቢት እንደአለች ዜናዋን ሰምቶ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ይጠይቃት ዘንድ ከፉሬ መጣ እሷ ከአለችበት ደርሶ ሰላምታ ሰጣትና ብቸኛ መሆኗን ተረድቶ አንቺ ልጅ ነሽ ብቻሽን እንዴት ትኖሪያለሽ ያለ ጓደኛ መኖር ለአንቺ ጥሩ አይደለም አላት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መልሳ እንደምን አድርጌ ከእኔ ጋር የምትቀመጥ ጓደኛ አገኛለሁ እኔ በዚህ አገር ስደተኛ ነኝና አለችው።

፲፭ እሱም መልሶ አሁን ከእኅቷ ጋር የምትኖር እንደ አንቺ ባለቤቷንና ንብረቷን ጥላ መንና የመነኮሰች እኅተ ክርስቶስ የምትባል አለች ከፈለግሽ ላምጣልሽ አላት እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስም እኔ ባለቤቷን ትታ ከመጣች ሴት ጋር አልኖርም አለችው መልሶ እኔ የዚያችን ሴት ፀባይ አውቃለሁ አንቺ ብታዪ በወደድሻት ነበር አላት ።

፲፮ ይህን ብሎ ከሷ ተለይቶ ፉሬ ደርሶ እኅተ ክርስቶስን እዚህ ቁጭ ብለሽ ከኅትሽ ጋር የጣመ የላመ ስትበዪ ሥጋሽን አደለብሽ እንጂ ምኑን መነንሽ ስለ እግዚአብሔር መልካሙን ነገር ምኑን ተውሽ ንብረትሽን ይዘሽ ከባለቤትሽ ጋር በኖርሽ ነበር ነገር ግን ቃሌን ብትሰሚ ነገሬን ብትቀበይ እኔ እመክርሻለሁ በሮቢት ከአለችው ከወለተ ጴጥሮስ ጋር ብትኖሪ ይሻልሻል መልካም ደግ ሴት ናትና ብሎ ሥራዋን ሁሉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ነገራት እሷም መልሳ እኔ በከተማ ከኖረችው ሴት ጋር አልኖርም ከእሷ ጋር ብቀመጥ ምን ትመክረኛለች ምን አርአያ ከእሷ አገኛለሁ ሁለታችንም አዲስ አትክልት ነንና አለችው ።

፲፯ አውሥአ ወይቤላ እስኩ ሑሪ ኀቤሃ ምዕረ ነጽሪ ግዕዛ ወፍትኒ ግብራ እመ አፍቀርኪያ ትነብሪ ምስሌሃ ወእመ ጸላእኪያ አልቦ ዘይኤዝዘኪ በአገብሮ ወትቤሎ አሆ ዘንተሰ እገብር ከመ ይኩን ፈቃድከ ወነቢረሰ ምስሌሃ ኢይፈቅድ ግሙራ ወእምዝ ሖረት ኀበ ወለተጴጥሮስ ጽሚተ በታንኳ ወኢየአምር መኑሂ እንበለ ክልኤሆሙ ወበጽሐት ኀበ ውእቱ መካን ወቆመት በአንቀጽ ወጠፍሐት:እደዊሃ:ወትቤሎ:እምነ:ቅድስት:ወቡርክት :ወለተጴጥሮስ:ለይእቲ ወለት እስኩ ጻኢ ወጠይቂ መኑ ውእቱ ዘይጠፍሕ ወሶበ ወጽአት ይእቲ ወለት አእመረታ ወተመይጠት ወነገረታ ከመይእቲ እኀተ ክርስቶስ እስመ ተአምራ ቀዲሙ እንዘ ሀለወት በፉሬ::

፲፰ ወትቤላ ንዒ በሊያ ወሖረት ወአምጽአታ ወሶበ ተናጸራ እም ርኁቅ ተሰውጠ ፍቅር ውስተልበ ፪ሆን ፍቅረ አሐቲ ኀበ አሐቲ ወተአምኃ በበይናቲሆን ወነበራ ወተዚያነዋ ነገራተ እግዚአብሔር ወአልቦ ማዕከሌሆን ፍርሃት ወኢትሕዝብት ወኮና ከመ ዘይትአመራ ቅድመ እስመ አስተዋኃዶን መንፈስ ቅዱስ ወእምዝ ተማከራ ከመ ይንበራ ኅቡረ ወትቤላ ባሕቱ እኅተ ክርስቶስ አንሰ አሐውር ይእዜ ወእፌኑ ለኪ ታንኳ ወአንቲ ትመጽኢ ኀበ ከሃ ወንትራከብ በህየ ወንትማከር ምክረ ዘከሰተ እግዚአብሔር ወሶቤሃ ሖረት እኀተ ክርስቶስ ወፈነወት ላቲ ታንኳ ወተቀበለታ::

ምዕራፍ ፬

፩ ወበጽሐት ፉሬ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወተአምኃቶ ለአባ ጽጌ ሃይማኖት ወለኲሎን አኃት እለ ሀለዋ ዝየ ወመጽአት እኀተ ክርስቶስ ወተአምኃታ ከመ እንግዳ ዘኢይትአምራ ቀዲሙ ወይቤሎን አባ ጽጌ ሃይማኖት ለክልኤሆን እንተ ባሕቲቶን አ አዋልድየ እፎ ኮንክን ተፋቀርክንኑ ወሚመ አልቦ ወይቤላሁ ፍቅረሰ ተፋቀርነ ዳዕሙ ኢነአምር ዘከመ እፎ ንጐይይ ወናመስጥ ወይቤሎን ዝሰ ምክር ሊተኒ ዐጸበኒ ::





፲፯ እሱም መልሶ እስኪ ከእሷ ዘንድ ሄዴሽ መጀመሪያ ፀባይዋን እዪ:ሥራዋን:መርምሪ:ከጠላሻት:በግድ:የሚያስቀምጥሽ: የለም:ከወደድሻት ከእሷ:ጋር ትኖሪያለሽ አላት እሷም ይህንንስ እሺህ ፈቃድህን አደርጋለሁ መቀመጥ ግን ፈጽሞ አልፈልግም አለችው ከዚህ በኋላ ያለ ሁለቱ ማንም ሳያውቅ በታንኳ ቀስ ብላ ወደ ወለተ ጴጥሮስ ዘንድ ሄዳ እዚያ ደርሳ ከደጃ ቆማ እጅ ጸፋች:እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተጴጥሮስም ያችን ልጅ እስኪ:ወተሽ:እይ እጅ የሚፀፋ:ማነው:አለቻት:ያችም:ልጅ ወጥታ በአየቻት ጊዜ እኅተክርስቶስ እንደሆነች አውቃ ነገረቻት ቀድሞ በፉሬ ታውቃታለችና ::

፲፰ ነዪ በያት አለቻትና ወጥታ አመጣቻት ገና ከሩቅ ሲተያዩ በሁለቱ ልቡና የእርስ በርስ ፍቅር አደረባቸው እርስበርሳቸው እጅ ተነሳስተው የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ተጨዋወቱ በመካከላቸውም ፍራትና መተፋፈር አልነበረም መንፈስ ቅዱስ ስለ አፋቀራቸው አስቀድመው እንደሚተዋወቁ ሆኑ ከዚህ በኋላ በአንድነት ይኖሩ ዘንድ ተማከሩ እኅተ ክርስቶስም እኔ ሄጀ ታንኳ እልክልሻለሁ አንቺም እዚያ መጥተሽ እግዚአብሔር የገለጠልንን ምክር እዚያ እንማከራለን ብላ ያን ጊዜ እኅተ ክርስቶስ ታንኳ ላከችላት ስትመጣም ተቀበለቻት ::

ምዕራፍ ፬

፩ እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስም ፉሬ ደርሳ አባ ጽጌ ሃይማኖትንና ከዚያ ያሉትን እኅቶች በሙሉ እጅ ነሣቻቸው እኅተ ክርስቶስም ቀድሞ እንደማታውቃት እንደእንግዳ እጅ ነሣቻት አባ ጽጌ ሃይማኖትም ለብቻቸው አቁሞ ልጆቼ እንዴት ናችሁ እርስበርሳችሁ ተፋቀራችሁን አላቸው እነሱም ፍቅርንስ ተፋቅረናል እንዴት አድርገን ሸሽተን እንደምናመልጥ አናውቅም አሉት እሱም ይህ ምክርስ ለኔም ቸግሮኛል አላቸው::

፪ ወእምዝ ይቤላ ለእኅተ ክርስቶስ አንቲ በሊያ ለእኅትኪ ኢይኤድመኒ ነቢር ኀቤኪ በተደልዎ ወኢይመስለኒ ጽድቀ አላ አብሕኒ በፈቃድኪ እኩን ረድእተ ለዔርስና ወእመ አኮ እጐይይ እምኔኪ ወአሐውር ኀበ ኢትሬእይኒ እምዝ ዳግመ ወይቤላሁ ሠናየ ትቤ ወባሕቱ ሑር አንተ ለሊከ ወግበር ከመዝ ወሖረ ወነገራ:ዘንተ ወትቤሎ ኦሆ ይኩን በከመ ትቤ አባሕክዋ ትሑር::

፫ ወእምዝ ወሰዳለእኅተ ክርስቶስ ኀበ ኤርስና ወከሠተ ላቲ ምሥጢሮ ወይቤላ ኢትክሥቲ ለመኑሂ ዘንተ ምሥጢረ ወእምዝ አስተዳለወ ሎን ታንኳ ወፈነዎን ሌሊተ ወይቤሎን ዮምሰ እትዋ ዘጌ ወንበራ እስከ ሠሉስ ዕለት ከመ ኢይርከቡክን እለ ይዴግኑክን ወገብራ በከመ አዘዞን ወእምድኅረ ሠሉስ ዕለት ዐርጋ በውእቱ ታን ኳ ወሖራ ኀበ ሮቢት ኀበ ነበረት ቀዲሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወነበራ ኅቡረ እንዘ ይትፋቀራ ከመ ነፍስ ወሥጋ ወእምአሜሃ ʼዕለት ኢተፈልጣ ክልኤሆን እመኒ በዘመነ መከራ ወስደት ወእመኒ በዘመነ ዕረፍት እንበለ ዳዕሙ በሞት:

፬ ወእምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል ሖራ ደብረ እንቆ ወለብሰት በህየ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አልባሰ ምንኵስና ወነበረት እንዘ ትትቀነይ ወትጸመድ ለእግዚአብሔር በጾም ወበጸሎት ወበኵሉ ምግባረ ሠናይ ወትሩፋት ወወጠነት ግብረ ትሕትና ወአኃዘት ትትለአክ ከመ አመት ወተሐርጸ በአሐቲ ሌሊት ፳ተ መስፈርተ ኢፍ ሰገመ ወእመ አኮ ሥርናየ እንዘ አእዳዊሃ ልምሉማት እማንቱ ወኢለመዳ ግብረ ማኅረጽ ወኢምንተኒ ተግባረ ወሀለዋ ምስሌሃ እኅተ ክርስቶስ ወወለተ ጳውሎስ ወለቱ ለአትናቴዎስ ወሠናየ ኮነ ተራክቦቶን ወንብረቶን ኅቡረ:በህየ:በከመ ይቤ ዳዊት ሣህል ወርትዕ ተራከባ ጽድቅ ወሰላም:ተሰዓማ:ናሁ:ሠናይ:ወናሁ:አዳም:ሶበ:ይሄልዋ:አኃት:ኅቡረ

፭ ወለእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አልቦ ዘይትማሰላ ወአልቦ ዘይትዔረያ በጾታ ኵሉ ተግባር እመኒ ትትጌበር ግብረ ጸቢሕ ይጥዕም ወይምዕዝ ላቲ ወይፈደፍድ ወይተርፍ እመሥፈርት ወእመኒ ወፈረት ገዳመ ታስተጋብእ





፪ከዚህ:በኋላ:እኅተ:ክርስቶስን:እኅትሽን:እንደልባችን:እየበላን:ከአንቺ:ጋር:መኖር:ጽድቅ:አይመስለኝም:ለኤርስና:አገልጋይ:እሆን:ዘንድ:በፈቃድሽ:አሰናብቺኝ:ያለዚያ:ከአንቺ:ተለይቼ:ዳግመኛ:ወደማታዪኝ:እሄዳለሁ:በያት:አላት:እነሱም:በአንድነት:መልካም:ብለሃል:አንተ:እንዲህ:ብለህ:ሂደህ:ንገራት:አሉትና:ሄዶ:ነገራት:እሷም:እሽ:እንዳልክ:አሰናብቻታለሁ:እንደ:ወደደች:ትኑር:አለች::

፫ ከዚህ በኋላ እኅተ ክርስቶስን ወደ ኤርስና ወሰዳትና ምሥጢሩን ነገራት ይህንንም ምሥጢር ለማንም አትንገሪ አላት ከዚህ በኋላ ታንኳ አዘጋጅቶላቸው በሌሊት ሸኝቶ የሚከታተሉዋችሁ እንዳያገኟችሁ እስከ ሦስት ቀን ከዛሬ ጀምራችሁ ዘጌ ገብታችሁ ተቀመጡ አላቸው እነሱም እንደ አዘዛቸው አደረጉና በሦስተኛው ቀን በዚያ ታንኳ አስቀድማ እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ተቀምጣ ከነበረችበት ሮቢት ሂደው እንደ ነፍስና ሥጋ ተስማምተው በፍቅር ተቀመጡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሁለቱም በመከራና በስደትም ቢሆን በደስታ ዘመን እስከ ሚሞቱ አልተለያዩም ::

፬ ከጥቂት ወራት በኋላ ወደ ደብረ አንቆ ሂደው በዚያ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የምንኵስናን ልብስ ለበሰችና እዚያ መነኮሰች በዚያ በጾምና በጸሎት መልካም ሥራን በመሥራትና በትሩፋት እግዚአብሔርን ስታገለግል ቆየች የትሕትናንም ሥራ ጀመረች እንደ አገልጋይ ሁና ትላላክ ጀመረች እጆቿ ውሀን ያዝሉና ይቆስሉ ነበር እነሱም የለሰለሱ የወፍጮ መፍጨትንና ሥራን ያለመዱ ስለሆኑ በአንድ ሌሊትም አምስት እንቅብ ገብስ ወይም ስንዴ ትፈጭ ነበረ እኅተ ክርስቶስና የአትናቴዎስ ልጅ ወለተ:ጳውሎስ ከእሷ ጋር ነበሩ ነቢዩ ዳዊት ይቅርታና ቅን ተገናኙ ፍቅርና ሰላም ተስማሙ እነሆ:ሁለት:እኅትማማች:በአንድነት:ተስማምተው:ቢኖሩ:መልካም:ነው:እንደአለ:ተገናኝተው:በዚያ:መኖራቸው:መልካም:ሆነ::

፭ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተጴጥሮስ ግን በተለያየ ሥራ ሁሉ የሚስተካከላት አልነበረም ወጥ ብታፈላ ይጣፍጥላት መአዛው ያማረ ይሆንላት ይበረክትላት ከልክ በላይ ይትረፈረፍላት ነበር ወደዱር እንጨት ለመስበር በሄደች ጊዜ

ዕፀወ ይትጋባእ ላቲ ፍጡነ ወይከውን ጸረ ዓቢየ በጊዜሃ ወበኵሉ ዘሠረአት ይሴሪ ላቲ እግዚአብሔር ወካዕበ ተሐውር ኀበ ፈለግ ርጉቅ እንዘ ትጸውር ኮራ ዓቢየ ወትቀድሕ ማየ ወትጸውር ወተዓርግ ዐቀበ ደብር ዐቢየ እንዘ ትድህክ ወበማዕከለ ፍኖት ሀሎ ዕብን ዐቢይ ወትነብር ህየ ወተዓርፍ ንስቲተ በእንተ ድካመ ሥጋሃ ወታስተነፍስ።

፮ ወይሰምይዎ ለውእቱ ዕብን ምዕራፈ ወለተጴጥሮስ ወኵሉ ዘየዐርግ ወይወርድ ይስዕሞ ወይሳለሞ እስከ ይእዜ ወኮነ ትእምርተ ለተዝካረ ስማ እስከ ኅልፈተ ዓለም ወእምዝ ትትነሣእ እምህየ ወትጸውር ውእተ ኮራ ወትበጽሕ ኀበ ማኅደሪሆን ወያነክር ኵሉ ዘርእያ ወመጠነ ርኍቀተ ፍኖቱሂ ለውእቱ ፈለግ ይከውን እምነግህ እስከ ፫ ሰዓት

፯ ወእማንቱኒ አኃት እለ ሀለዋ ምስሌሃ ይገብራ ከማሃ እስመ ኮነቶን አርአያ ወመሐረቶን ግብረ ትሕትና በከመይቤ እግዚእ ዘፈቀደ ይኩን ሊቀ እምኔክሙ ይኩንክሙ ገብረ ወጴጥሮስኒ ይቤ አርአያ ኩንዎሙ ለመርዔቱ ከመአመ ያስተርኢ እግዚአ ኖሎት ትንሥኡ አክሊለ ስብሐት ወሀለዋ ውስተውእቱ ደብር መነኮሣይያት ፅሩዓት ወሀካያት ወኢይትጌበራ ምንትኒ ተግባረ ወይነብራ በሀኬት።

፰ ወያነውኃ አጽፋረ እደዊሆን ወኢይገብራ ግብረ ጻማ ወሶበ ርእያ ትሕትናሃ ወግብረ ፃማሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ አሃዛ ይገሥፃ ወይዝልፋ ርእሶን እንዘ ይብላ ወይ ለነ አሌ ለነ ዘአኅለፍነ መዋዕሊነ በከንቱ ወበሃኬት ወበፅርዓት እንዘ አዋልደ ነደያን ንሕነ አንስት አግብርቲሃ ወወዓልያኒሃ ።

፱ ወልማድነ ማኅረጽ ወቀዲሐ ማይ ኢተዘከርነ ዕለተ ሞት ወ ኢያእመርነ ከመ ቦ ፍዳ ለሀካያን ይእቲሰ አግዓዚት ወለተ ክቡራን ወብእሲተ መኰንን አንደየት ርእሳ ወቦአት ውስተ ጸባብ አንቀጽ እንተ ትወስድ ውስተ ሕይወት ዘለዓለም ወንሕነሰ ሀለውነ ውስተ ርሒብ አንቀጽ እንተ ትወስድ ውስተ ሐጕል ወዘንተ ብሂሎን ነስሓ በቀዳሚ ግብሮን ወተመሰላ ኪያሃ ወአኃዛ ይትገበራ ከማሃ።





ፈጥኖ ይሰበስብና ይበዛላት ትልቅ ሸክም ይሆንላት ነበር የምትሠራውን ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር ያከናወንላት ነበር ዳግመኛ ወደራቀ ወንዝ ወርዳ በትልቅ እንስራ ውሃ ቀድታ ተሸክማ ትልቅ የሆነ የተራራውን አቀበት እየቧጠጠችና እየዳኸች ትወጣ ነበረ በጉዳና መካከል ታላቅ ድንጋይ ነበርና ከዚያ ጥቂት ስለሥጋዋ ድካም አረፍ ብላ ተሸክማ ትሔዳለች ።

፮ ዛሬም ያ ድንጊያ የወለተ ጴጥሮስ ማረፊያ ድንጋይ እየተባለ በስሟ መታሰቢያ ሆኖ ይጠራል እስከ ዛሬም የሚወጣና የሚወርድ ሰው ሁሉ ሳይስምና ሳይሳለም አያልፍም እስከ ዓለም ፍጻሜም፡የስሟ፡መጠሪያ፡ሆነ፡ተሸክማ፡ስትሄድ፡ያያት፡ሁሉ፡ያደንቅ፡ነበረ፡የጉዳናውም፡ርቀት፡መጠን፡ከጧት፡እስከ፡ሦስት፡ያስኬዳል ።

፯ ከእሷ ጋር ያሉ እነዚያ ሴቶችም እንደ እሷ ይሠሩ ነበር አርአያ ሁና የትሕትናን ሥራ ታስተምራቸው ነበርና ጌታችን ከሁሉ በላይ መሆን የፈለገ የሁሉ አገልጋይ ይሁን እንዳለ ጴጥሮስም ጌታችን በመጣ ጊዜ የምስክርነት አክሊል ታገኙ ዘንድ ለመንጋዎቻችሁ አርአያ ሁኑ እንደአለ በዚያ ደብር ምንም ሥራ የማይሠሩ ሰነፎች ሥራ መፍታት የሚወዱ መበለታት ነበሩ።

፰ ጥፍሮቻቸውንም እያሳደጉ የኩክ ማውጫ አድርገውት ነበር እነሱም የእናታችን የቅድስትና የቡርክት የወለተ ጴጥሮስን ትሕትናዋንና ድካሟን በአዩ ጊዜ እነዚያ ሰነፎች መበለታት ምንም ሥራ ሳንሠራ ዘመናችንን በከንቱ በስንፍና በዋዛ በፈዛዛ ስለ አሳለፍን ወዮልን ወዮታ አለብን እያሉ እራሳቸውን ዘለፉ ገሥፁ እኛ የድሆች ልጆች ስንሆን አገልጋዮቿ ተላላኪዎቿ በሆን እያሉ ያዝኑ ጀመሩ።

፱ መፍጨት ውሀ መቅዳት ሲገባን እለተሞታችንን አላሰብንም ለሰነፎች ፍዳ እንደሚቆያቸው አላሰብንም እሷ ግን የክቡራን ሰዎች ልጅና የመኰንን ባለቤት ታላቅ እመቤት ስትሆን እራሷን ድሀ አድርጋ ወደ ዘለዓለም ሕይወት በምትወስድ በጠባብ በር ገባች እኛ ግን ወደጥፋት በምትወስድ በሰፊ በር ነው ያለነው ይህን ብለው በአለፈ ስንፍናቸው ተፀፅተው እሷን ተከትለው እንደ እሷ ይሠሩ ጀመር ።

፲ እስፍንተ ንዜኑ ትሩፋቲሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ እስመ ብዙኅ ውእቱ ጸሎትሰ ወሰጊድ ወምግባረ ትሩፋት ዘትገብር በኅቡእ ኢይትአመር እስመ ኅቡእ ውእቱ ግብሮሙ ለጻድቃን::

፲፩ ወእምድኅረዝ ሶበ ወጠነ ንጉሥ ሱስንዮስ ይወልጥ ወያቅም ሃይማኖተ አፍርንጅ ርኩስተ እንተ ትብል ፪ኤ ባሕርይ ውእቱ ክርስቶስ እምድኅረ ተወሐደ ወኮነ ሰብአ ፍጹመ ወያሰስል ሃይማኖተ እስክንድርያ ቅድስተ እንተ ትብል ከመዝ ኮነ ሰብአ ፍጹመ ኢተበዓደ ወኢተፈልጠ በኵሉ ግብሩ ወልድ ዋሕድ አላ ፩ ራእይ ወ፩ ሕላዌ ወ፩ መለኮት ዘእግዚአብሔር ቃል ወሰሚዓ ዘንተ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ሶበ ስእነት ተዓግሦ ተግኅሠት ወጐየት እምሀገር ለሀገር ወተሰደት ወበጽሐት ሀገረ ጽያት ምስለ እማንቱ አብያጺሃ እለ ቀደምነ ዘክሮቶን በከመ ይቤ ወንጌል ብፁዓን እለ ይሰደዱ በእንተ ጽድቅ እስመ ሎሙ ይእቲ መንግሥተ ሰማያት

፲፪ ወካዕበ ይቤ ተገሐሡ እምሐሳውያነ ነቢያት እለይመጽኡ ኀቤክሙ በአልባሰ አባግዕ ወእንተ ውስጦሙሰ ተኩላት ወመሠጥ ወእምፍሬሆሙ ተአምርዎሙ ወጳውሎስኒ ይብል አስተበቁዓክሙ አኃዊነ ተዓቀብዎሙ ለእለ ይገብሩ ሀከከ ወያመጽኡ ካህደ ላዕለ ትምህርትክሙ ትግበሩ እስመ ለከርሶሙ ይትቀነዩ ወአኮ ለእግዚአብሔር ወበሒጣነ ነገር ወበተየውሆ ያስሕትዎሙ ለብዙኃን የዋሃን ወኢትኩኑ ንፉቃነ ወኢትሑሩ ውስተ ዓርዑተ ቅኔ እለ ኢየአምኑ ወበእንተዝ ጻኡ እማዕከሎሙ ወተፈለጡ እምኔሆሙ ይቤ እግዚአብሔር ወኢትቅረቡ ኀበ ርኩሳን ወአነ እትዌከፈክሙ ወእከውነክሙ አባክሙ ወአንትሙኒ ትከውኑኒ:ደቂቅየ ወአዋልድየ ይቤ እግዚአብሔር ዘኵሎ ይመልክ::

፲፫ ወሕንፃ:መነኮሳትኒ:ይብል:ኢትጸልዩ:ምስል:አርሲሳን ዘውእቶሙ መናፍቃን ወበእንተዝ ርኅቀት ወጐየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሖረት ርኁቀ ብሔረ ከመኢትስማዕ ጽርፈተ አፍርንጅ ወኢትሳተፍ መነሂ ዘኃብረ በዝንቱ ሃይማኖት ወበህየኒ ነበረት እንዘ ትትቀነይ ወትጸመድ





፲ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ዜና ትሩፋት ስንቱን እንናገራለን ጸሎቷና ስግደቷም በድብቅ የምትሠራ ትሩፋቷ ተቆጥሮ አይዘለቅም የጻድቃን ሥራቸው በስውር ነውና::

፲፩ ከዚህ በኋላ ንጉሥ ሱስንዮስ የቀናች ሃይማኖት ኦርቶደክስ ተዋህዶን ክዶ ሁለት ባሕርይ የምትል የረከሰች የካቶሊክ ሃይማኖትን አስፋፋ ሥጋን ከተዋሀደ በኋላ ቃለ እግዚአብሔር በሥራ ሁሉ ሳይለይ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆነ አንድ መልክ አንድ አኗኗር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ የምትል የእስክንድርያ ሃይማኖት ተዋህዶን ያስክድ ጀመር እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ይህን በሰማች ጊዜ አላስችል ብሏት ከአንዱ አገር ወደ አንዱ አገር እየተሰደደች አስቀድመው ከተጠሩ ከእነዚያ ጓደኞቿ ጋር ጽያት ከምትባል አገር:ደርሳ:ማስተማር:ጀመረች:ወንጌል:ስለጽድቅ:የሚሰደዱ:ንዑዳ ን:ክቡራን:ናቸው:መንግሥተ:ሰማያት:የነርሱ:ናትና:እንደ:አለ::

፲፪ ዳግመኛም የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡ ውስጣቸው ነጣቂ ተኩላ ከሚሆኑ ሐሳውያን ነቢያት ተጠበቁ ከፍሬያቸው ታውቋቸኋላችሁና እንደአለ ጳውሎስም ወንድሞቼ እለምናቸዋለሁ በትምህርታችሁ ላይ ክህደት በመካከላችው ፀብ ክርክር ከሚያመጡ መናፋቃን ተጠበቁ እነሱ ለእግዚአብሔር ያይደለ ለሆዳቸው ይገዛሉና በማታለልና በሽንገላ ብዙ የዋሆችን ያስቱዋቸኋል ተጠራጣሪዎች አትሁኑ ከማያምኑ ሰዎች ጋርም አትሂዱ እንዳለ ስለዚህ ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ከመካከላቸው ውጡ ከእነሱም ተለዩ ወደርኩሳን ሰዎች አትቅረቡ እኔ አባት ሁኜ እቀበላቸኋለሁ እናንተም ልጆች ትሆኑኛላችሁ አለ::

፲፫ ሕንፃ መነኮሳትም ከመናፋቃን ጋር አትጸልዩ ይላል ስለዚህ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የካቶሊክ ተከታዮች የሚሳደቡትን እንዳትሰማ ከእነሱም ጋር እንዳትሳተፍ እሩቅ አገር ሄደች በዚያም በጾምና በጸሎት እግዚአብሔር ስታገለግል እንደቀድሞ በመፍጨትና ውሃን በመቅዳት እግሮቿ በእሾህ በስንጥር እንጨት በሻፎ ድንጋይ ደሟ እስኪፈስ ድረስ

ለእግዚአብሔር በጾም ወበጸሎት ወእንዘ ትትለአክ ከመ ቀዳሚ ግብራ በግብረ ማኅረጽ ወበቀዲሐ ማይ ወበአስተጋብአ እፀው እምነሐቅል እንዘ ይትጐዳ እገሪሃ በውግዓተ ሦክ ወበስጻረ ዕፅ በሊሕ ወበአዕባን ደቃቅ እስከ ይውሕዝ እምኔሃ ደም ብዙኅ ወእለ ርእዩ ውእተ ደመ ውስተ ፍኖት:ይትበሃሉ በበይናቲሆሙ ዝንቱ ደም ዘወለተጴጥሮስ ውእቱ::

፲፬:ወካዕበ:የሐውራ:ውስተገራህት:ዘተዓፅደ:ለተቅራመ:እክል:ያስተጋብኣ ለሲሳዮን ወሶበ አኃዘት ትትቀረም ኀዳጠ ምዕረ ይመልዕ ላቲ ፍጡነ ሙዳየ ዚአሃ እመኒ አስተጋብአት ውስተ ጽፍነት አው ወደየት ውስተ ካልእ ሙዳያ ኢይውሕድ ወኢይሐፅፅ ባቲ እስመ በረከተ እግዚአብሔር ሀሎ ውስተ እዴሃ ወእማንቱኒ አኃት ንስቲተ ይትቃረማ ወሶበ:ይመጽእ በዓለ ገራህት ወይሬኢ ዘዚአሃ ቀሪመ ወዘዚአሆን ወይጸርፍ ላዕሌሃ ወይቤላ ይእቲሰ ሰረቀት እምከላስስትየ ወመልአት ፍጡነ ወይዘሩ ባቲ ውስተ ምድር ኵሎ ዘአስተጋብአት ይእቲሰ ኢተኃዝን ወኢታንጐረጕር ግሙራ ሶበ ይጸርፍ ላዕሌሃ ወይክዑ ባቲ አላ ትትዔገሥ ወትትዌከፍ ኵሎ ዘይረክባ በአኰቴት::

፲፭ ወእንዘ ከመዝ ሀለወት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ በውእቱ ሀገር ቀንዓት ቅንዓተ ሃይማኖት ወስዕነት ተዐግሦ ወገሠጸቶሙ ለሰብአ ሀገር ከመ ኢይትወከፉ ሃይማኖተ ልዮን ርኵስተ ወኢይዝክሩ ስሞ ለንጉሥ ከሐዲ በጊዜ ቅዳሴ እስመ:ውእቱ:ውጉዝ:ወርጉም:በከመ:ይቤ:ጳውሎስ:መልአክ:እምሰማይ:ለእመ:መሀረክሙ:ካልአ:እምዘመሀርናክሙ:ውጉዘ:ለይኩን::

፲፮ ወሶበ ሰምዓ ዘንተ ነገረ ንጉሥ ሱስንዮስ ተምዓ ፈድፋደ ወተቈጥዓ ጥቀ ወጥኅረ ከመ አንበሳ ወገረሞሙ ለአዝማዲሃ ወለአኃዊሃ ወአስምዓ ላዕሌሆሙ እንዘ ይብል አሰምዕ ለክሙ ሰማየ ወምድረ ወእምሕል በመንግሥትየ እዚዝየ ከመ እነ እትቤቀ ለክሙ ወትመውቱ ሞተ እኩየ ወእሥዕር እምድር ዝክረክሙ ለእመ ኢያምጻእክዋ ፍጡነ ለወለተ ጴጥሮስ ወነዋ ሠዓረተኒ እመንግሥትየ ወዓመዓተኒ ወዓለወተኒ ወጸረፈት ላዕሌየ ወላዕለ ሃይማኖትየ ወገፍትዓት ልቦሙ ለሰብአ ሀገር ከመ ኢይትወከፉ ሃይማኖትየ ወኢይዝክሩ :ስምየ:በቅዳሴ አልቦ ጽልእ ማዕከሌየ ወማዕከሌክሙ እምቅድመዝ እምይእዜሰ እገብር ጽልአ ምስሌክሙ::





እየተወጉ ከበርሃ እንጨት በመልቀም ኖረች ያን ደም ያየ ሁሉ ይህ ደም የወለተ ጴጥሮስ ደም ነው ይባባሉ ነበር::

፲፬ ዳግመኛ ቃርሚያ ለመልቀም ወደ አጨዳ እህል እየሄዱ ምግባቸውን ይሰበስባሉ ቃርሚያ መልቀም በጀመረች ጊዜ ፈጥኖ የያዘችውን ቁና ይሞላ ነበር በአቁፋዳም በአደረገች ጊዜ ይሞላል በሌላ አቁፋዳም ብታደርግ ፈጥኖ ይሞላል እንጅ ምንም አይጐ:ድልባትም የእግዚአብሔር በረከት ‹ ኘጇ ውስጥ አለና እነዚያ እኅቶቿ ጥቂት ይለቅማሉ ባለ እርሻው መጥቶ የነሱንና የሷን በአየ ጊዜ ይሰድባትና ይህች ነዶየን ሰርቃ ፈጥና ሞልታለች ብሎ የሰበሰበችውን በመሬት ላይ ያፈስባት ነበር በሚሰድባትና በሚበትንባት ጊዜ አታዝንም አታንጐራጉርም የሚደርስባትን ፈተና ታግሣ በትእግሥትና በምስጋና ትቀበል ነበር እንጂ ::

፲፭ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንደዚህ በዚያ አገር ስትኖር የሃይማኖት ቅናት ቀንታ መታገሥ ተስኗት የአገሩን ሰዎች የልዮንን ክደት እንዳይከተሉ የተወገዘና የተረገመ ስለሆነ የዚያን ከሐዲ ንጉሥ ስም በቅዳሴ ጊዜ እንዳይጠሩ እየገሠጸች አስተማረቻቸው ቅዱስ ጳውሎስ እኛ ካስተማርናቸው ሃይማኖት በስተቀር ሌላ ሃይማኖት መልአክ ከሰማይ ወርዶ ቢያስተምራችሁ የተወገዘ ይሁን እንደአለ::

፲፮ ንጉሥ ሱስንዮስም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እጅግ ተቆጥቶ እንደ አንበሳ ደነፋ ወንድሞቿንና ዘመዶቿን እኔ በሥልጣኔ አዝዤ ሰማይንና ምድርን አስመስክሬባችሁ ተበቅየ ስም አጠራራችሁን ከምድር አጠፋለሁ በክፉ አሟሟት ትሞታላችሁ ከዚህ በፊት በእኔና በእናንተ መካከል ፀብ ክርክር አልነበረም ስሜን በቅዳሴ ጊዜ እንዳይጠሩ ከመንግሥቴ አዋርዳ አመፀኛ ወንጀለኛ አድርጋኝ ለኔ እንዳይገዙ በሃይማኖቴ እንዳያምኑ የአገሩን ሰዎች ልቡና አጽንታብኛለችና ፈጥናችሁ ወለተ ጴጥሮስን ከላመጣችሁልኝ ከዛሬ ጀምሮ ፀቤ ከእናንተ ጋር ነው አላቸው::

## ምዕራፍ ፰

፩ ወሶበ ሰምዑ አዝማዲሃ ትግርምተ ንጉሥ ዘይቤሎሙ ፈርሁ ፈድፋደ ወተሃውኩ እስመ ድሩክ ውእቱ ንጉሥ ወኢይምሕክ ለመኑሂ በከመ ነበበ ይገብር ወይእተ ጊዜ ለአኩ ኀቤሃ እንዘ ይብሉ ከመዝ ናሁ ንትሐጐልአ ኵልነአ በእንቲአኪአ ወኢይትርፍአ ፩ዱ እምኔነአ ኢንኡስአ ወኢዓቢይአ እስመ ናሁ ተምዐ ንጉሥ ወአስምዓ ላዕሌነ ወአሰፈወነ ተስፋ ሞት ወይቤለነ ናሁ ሠዓረትኒ ወለተ ጴጥሮስ እመንግሥትየ ወዓመዓተኒ ወለእመ ኢያምጻእክምዋ ፍጡነ ትመውቱ ሞተ እኩየ ወይእዜኒ ንብለኪ ንዒ ፍጡነ ወኢትጐንድዪ ወኢታጥብዒ በሞተ ዚአነ እስመ ዘአንቲ ሥጋ እምሥጋነ ወአፅመ ዚአኪ እምዓፅምነ ወንህነ እምኪ ወአኃዊኪ።

፪ ወሰሚዓ ዘንተ መልእክተ እምነ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ፡ተከዘት ፈድፋደ ወተማከረት ምስለ አኃት እለሀለዋ ምስሌሃ ወይቤላ ኵሎን ኀቡረ በ፩ ቃል ይኄይሰነ ንሑር ንሕነ ወከመ ንሙት በእንተ ሃይማኖትነ እምይሙቱ አዝማዲነ በምክንያተ ዚአነ አኮኑ ዘንተ ንሴፎ ወንፀንሕ ወሃይማኖትነ ምስሌነ ውስተ ልብነ አልቦ ዘየሐይደነ በከመ ይቤ ማርያምሰ ኃርየት መክፈልተ ሠናየ ዘአልቦ ዘየሐይዳ ወዘንተ ብሂሎን ተንሥአ እምህየ ወገብአ ወተመይጣ ወተራከበት እምነ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ምስለ እማ ወአሃዊሃ አስተብቊዕዋ ወይቤልዋ ኢትትዓደዊ እምቃለ ንጉሥ ከመ ኢይቅትልኪ ወኢይቅትል ኪያነ በዓሊወ ዚአኪ።

፫ ወአንሥአት እማ አጥባቲሃ ወትቤላ አኮኑ አነ እምኪ ዘሐጸንኩኪ በእሎን አጥባትየ ኢትምህኪኑ ኪያየ፡ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ኢሰምዓት ነገሮሙ ወኢያጽነነት ኀሊናሃ ውስተ ምክሮሙ በከመ ይቤሉ ሐዋርያት ይረትዕኑ ኪያክሙ ንስማዕ ወአኮ እግዚአብሔር ይሄይሰነ ናድሎ ለእግዚአብሔር እምነ አድልዎ ለሰብእ ወሶቤሃ ሀለወ ንጉሥ ውስተ ታዕካሁ ወአዘዘ ያምጽእዋ ኀቤሁ ወወሰድዋ ወሖረት እንዘ ትሴፎ መዊተ በእንተ ሃይማኖት ርትዕት ወሖሩ ምስሌሃ እማ ወአኃዊሃ ወተለውዋ እንዘ ይበክዩ ከመ ያስተፋንውዋ ለሞት በአምሳለ በድን ዘይወስድዎ ይቀብርዎ።





## ምዕራፍ ፰

፩ ዘመዶቿም የንጉሥን ቁጣ በሰሙ ጊዜ እጅግ ፈሩ ተጨነቁ እሱ ለማንም የማይራራ የተናገረውን ፈጥኖ የሚያደርግ ክፉ ነውና ያን ጊዜ ፈጥነው ወደእሷ በአንቺ ምክንያት ሁላችንም ትልቁም ትንሹም ሳይቀር ልናልቅ ነው ንጉሡ ተቆጥቶ የሞት ተስፋ አስምቶናልና ወለተ ጴጥሮስ አዋርዳኛለች፡ሥልጣኔንም፡አቃላለችና፡ፈጥናችሁ፡እሷን፡ ካላመጣች ሁልኝ፡ክፉ፡አሟሟት ትሞታላችሁ ብሎናልና አሁንም በእኛ ሞት ሳትጨክኝ፡አንቺ፡ከሥጋችን፡ሥጋ፡ከአጽማችን፡አፅም፡ነሽና፡ፈጥነሽ፡ ወደኛ፡ነይ፡አሏት።

፪ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ይህን ሰምታ እጅግ አዝና ከእሷ ጋር ከነበሩት ጓደኞቿ ጋር ተማከረች እነሱም ሁላቸውም በአንድ ቃል በእኛ ምክንያት ዘመዶቻችን ከሚሞቱ እኛ ስለሃይማኖታችን ሂደን እንሙት ተስፋ የምናደርገው ይህ አይደለምን ሃይማኖታችን ከእኛ ጋር ነው ወንጌል ማርያምስ የማ ይቀሟትን እድል መረጠች እንዳአለ ሃይማኖታችን ማን ይቀማናል አሉ ይህን ብለው ከዚያ ተነስተው ተመልሰው፡ገቡ፡እናታችን፡ወለተ፡ጴጥሮስም፡ከእናቷና፡ከወንድሞቿ ጋር፡ተገናኘች፡ወንድሞቿም፡ከንጉሥ፡ትዕዛዝ፡እንዳትተላለፊ እንዳይገልሽ እኛንም ጭምር ይገለናልና ብለው ለመኗት ።

፫ እናቷም ጡቶቿን አውጥታ አጥብቼ በአሳደኩሽ በጡቶቼ ብለሽ አትራሪልኝም አለቻት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ነገራቸውን ፈጽማ አልተቀበለቻቸውም ኅሊናዋንም ወደ ምክራቸው አላዘነበለችም ሐዋርያት የእግዚአብሔርን ትተን የናንተን እንሰማ ዘንድ ይገባልን ለሰው ከምናዳላ ለእግዚአብሔር ማድላት ይሻላል እንዳሉ ያን ጊዜ ንጉሥ ከአዳራሹ ሳለ ያመጧት ዘንድ መልክተኛ አዘዘና ወሰዷት እሷ በቀናች ሃይማኖቷ ትሞት ዘንድ ቆርጣ ሄደች እናቷና ወንድሞቿ ሊቀብሩ ሬሣን ይዘው እንደምሄዱ እያለቀሱ ተከተሏት ።

፩ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ኢያንሥአት ገጻ ወኢርእየቶሙ አላ ትቤሎሙ ለምንት ትበክዩ ወትሰብሩኒ ልብየ ወታነብሩ ዕቅፍተ ውስተ ፍኖትየ ሊተሰ ኢትብክዩኒ አላ ብክዩ ላዕለ ርእስክሙ እምይእዜሰ አልቦ ዘያነጥየኒ አንሰ ሕማም ለክርስቶስ እጸውር በሥጋየ መኑ ያኀድገኒ ፍቅሮ ለክርስቶስ ሕማምኑ ምንዳቤኑ ተሰዶኑ:ረኃብኑ:ዕርቃንኑ መጥባሕትኑ:ጻዕርኑ:

፪ ወካዕበ በከመ ይቤ መጽሐፍ በእንቲአከ ይቀትሉነ ኵሎ ዕለተ ወኮነ ከመ አባግዕ ዘይጠብሑ አ ፍቁራንየ ወኢትአመን ባሕቱ ከመ አልቦ ዘያኀድገኒ ፍቅሮ ለክርስቶስ ኢሞት ወኢሕይወት ኢመላእክት ወኢቀደምት ኢዘሀሎ ወኢዘይመጽእ ኢዘኃይል ወኢዘልዑል ኢጸድፍ ወኢዳግም ልደት ዘመትሕት አልቦ ዘይክል አኀድኆትየ ፍቅሮ ለክርስቶስ አንሰ እትአመን ዘልፈ ወኢይክህድ ግሙራ ወኢይክል መኑሂ ያሥምር ልብየ ከመ እክሀድ ሃይማኖትየ እመኒ አፍርሁኒ በስደት ውስተ መካናት ርኁቃት ወእመኒ ወደዩኒ ውስተ እሳት ወእመኒ ገደፉኒ ለአናብስት ወእመኒ አስጠሙኒ ውስተ ባሕር ወእመኒ መተሩ ዐባልየ እመለያልይየ ወእመኒ ኰነኑኒ በዘዚአሁ ኵነኔ አንሰ ኢይክህድ ግሙራ ሃይማኖትየ አላ ጽንዕተ ልብ አነ በቃለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘይቤ ኢትፍርህዎሙ ለእለ ይቀትሉ ሥጋክሙ ወለነፍስክሙሰ መኑሂ ኢይክል ቀቲሎታ ፍርህዎሰ ለዘእምድኅረ ቀተለ ብውሕ ሎቱ ይደይ ነፍሰኒ ወሥጋ ህቡረ ውስተ እሳተ ገሐነም ::

፫ ወእምዝ እንዘ ተሐውር እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ በጽሐት ውስተ ታዕካ ንጉሥ ወአዘዘ ንጉሥ ይትጋብኡ ኵሎሙ መኳንንት ወመሳፍንት ሊቃውንት ወመናብርት ወገብሩ በከመ አዘዘ ንጉሥ ወተጋብኡ ኵሎሙ ተረሲዮሙ በግርማ ዐቢይ ወነበሩ ዓውደ በበመናብርቲሆሙ ወበበሥርዓቶሙ ወአዘዘ ያምጽእዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ወመጽአት ወቆመት በቅድሜሆሙ በጥቡዕ ወበጽኑዕ ሃይማኖት ወኢገገጸት እምግርማሆሙ ወእምብዝኃ ጉባኤሆሙ ወንባቦሙ ከንቱ በከመ ይቤ ዳዊት ለምንት አንገለጉ አሕዛብ ወሕዝብኒ ነበቡ ከንቶ ወተንሥኡ ነገሥተ ምድር ወመላእክትኒ ተጋብኡ ምስሌሆሙ ኅቡረ ላዕለ እግዚአብሔር ወላዕለ መሲሑ::





፩ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ግን ቀና ብላ አላየቻቸውም ለምን ታለቅሳላችሁ ልቦናየንስ ለምን ትሰብሩኛላችሁ በጐዳናየ ላይ እንቅፋት ለምን ታኖሩብኛላችሁ ለኔ አታልቅሱ ለራሳችሁ አልቅሱ ከዛሬ ጀምሮ እኔ በሥጋየ የክርስቶስን መከራ እቀበላለሁ የሚያስጥለኝ የለም ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማነው ሕማም ነውን መቸገር ነውን መሰደድ ነውን መራብ ነውን መጠማት ነውን መራቆት ነውን ሰይፍ ነውን ጭ ኔነቅ ነውን እንደአለ ጳውሎስ::

፪ ዳግመኛም መጽሐፍ ስለአንተ ዘወትር ይገሉናል እንደሚታረዱ በጐች ሆን እንደአለ ወዳጆቼ ሆይ ነገር ግን ሞትም ቢሆን ሕይወትም መላእክትም የቀደሙትም ቢሆኑ ያለውም የሚመጣም ኃይለኛም ቢሆን ከፍታም ቢሆን ገደልም ቢሆን ዳግመኛ ወደታች መውረድም ቢሆን ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ የለም እሱ እንደሚያፀናኝ አምናለሁና ሃይማኖቴን የምያስክደኝ የለም ወደራቀ ቦታ አስፈራርተው ቢያሳድዱኝ ወደእሳት ቢጥሉኝ ለአንበሳ ቢሰጡኝ ከባሕር ቢጥሉኝ ቢያሰጥሙኝ ሰውነቴን በብልት በብልት ቢቆራርጡኝ በተለያየ ሥቃይ ቢያሰቃዩኝ እኔ ፈጽሞ ሃይማኖቴን አልክድም በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ሁሉን እችላለሁ ሥጋችሁን የሚገሉዋችሁን አትፍሩ ነፍሳችሁን መግደል የሚቻለው የለምና መፍራትስ የሚገባ ከገደለ በኋላ ነፍስንም ሥጋንም ወደገሐነም መክተት የሚችለውን እግዚአብሔርን ነው እንጂ በአለው ቃል ጸንቻለሁና አልፈራም አለች::

፫ ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እየሄደች ከንጉሡ አዳራሽ ደረሰች ንጉሡም መኳንንትና መሳፍንት አለቆች ሹማምንት ይሰበሰቡና ይዘጋጁ ዘንድ አዘዘ እነሱ ንጉሡ እንደአዘዛቸው በሚያስፈራ ግርማ ተዘጋጅተው መጥተው በዙፋናቸው ላይ ተቀመጡ ንጉሡም እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ያመጧት ዘንድ አዘዘ እሷም መጥታ በጨከነ ልቡናና በጸና ሃይማኖት ከመፈራታቸውና ከበዛ ጉባኤያቸው በከንቱ ከሚቆጡ ከቁጣቸው የተነሣ ሳትፈራ ሳትጨነቅ በፊታቸው ቆመች ነቢዩ ዳዊት አሕዛብ ለምን ተሰበሰቡ ሕዝብ ከንቱ ነገርን ለምን ተናገሩ የምድር ነገሥታትም ለምን በእግዚአብሔር እና በወዳጁ ላይ በከንቱ ተነሱ አለቆችም ከእነሱ ጋር በከንቱ ተሰበሰቡ እንደአለ::

፯ ይእቲሰ ትቀውም ባሕቲታ ከመሥርዓተ ዓላዌ ንጉሥ ወእምዝ ይቤልዋ ዐቃቢያነ ነቢብ ዘንጉሥ ዓለውኪዮ ለንጉሥ ዓለውኪዮ ለእግዚአብሔር ወተቃረንኪ ትእዛዞ ወተዓደውኪ ቃሎ ወጸረፍኪ ሃይማኖተ ዚአሁ ወገፍታዕኪ አልባበ ሰብአ ሀገር ከመ ኢይትዌከፉ ሃይማኖቶ ወኢይዝክሩ ስሞ በቅዳሴ ይእቲሰ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኢታወሥእ ወኢትሰጠው ምንተኒ አላ ትሰምዕ እንዘ ድኍን ገጻ ወትስሕቅ በአክሞስሶ ወባሕቱ ትቤ በትሑት ቃል አንሰ ኢይጸርፍ ንጉሠ ወሃይማኖትየኒ ኢይክህድ ግሙራ ወንጉሥሰ ይፌኑ ላእካነ በበጊዜሁ ወየሐትት ወይሴአል እንዘ ይብል ምንተ ትብል ወምንተ ታወሥእ ወይቤልዎ ይእቲሰ ኢታወሥእ ወኢትሰጠው ምንተኒ ዳዕሙ ታረምም ወትስሕቅ።

፰:ወይእተ:ጊዜ:ተምዓ:ወይቤ:ሶበ:ታስተሐቅረኒ:ትስሕቅ:ላዕሌየ:ወ ትሣለቅኒ ወአዘዘ ይቅትልዋ ወእም አኮ ይምትሩ አጥባቲሃ ወአሜሃ ሀለወ:ይቀውም ቅድመ ንጉሥ ብእሲሃ መልክዓ ክርስቶስ ወይቤሎ ለንጉሥ:እንዘ:ያየውሆ:ኢትትመዓዕ:ኦእግዚእየ አኮ በአስተሐቅሮትከ ዘትስሕቅ አላ ያስሕቃ ጋኔን ዘላዕሌሃ ዘኃደረ ባቲ እምንእሣ ወዘንተ ብሄሎ አህድአ መዓቶ እስመ ውእቱ ያፈቅራ ጥቀ።

፱ ይእቲሰ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኢትፈርህ ሞተ ወኢትደነግጽ እምግርማሁ በከመ ይቤ ጴጥሮስ ሐዋርያ ወዘሰ ይጌርመክሙ ኢትፍርሁ ወኢትደንግፁ አላ ቀድስዎ ለእግዚአብሔር በኵሉ ልብክሙ ዳዕሙ ትብል ኦ ዘአጽናዕኮሙ ለነቢያት አጽንዓኒ ኦ ዘአጽናዕኮሙ ለሐዋርያት አጽንዓኒ ኦ ዘአጽናዕኮሙ ለሰማዕታት አጽንዓኒ ከመ እሙት በእንተ ስምከ ወእንሣእ አክሊለ ስምዕ።

፲ ወእምዝ አምከርዎ መማክርቲሁ ለንጉሥ ወይቤልዎ ስምዓነ ኦ ንጉሥ ይኄይሰከ ትኅድግ ቀቲሎተ አሐቲ ብእሲት እምይኩኑከ አጽራረ ኵሎሙ አዝማዲሃ ደዋሮ ወፈጠጋር ወይቤ ንጉሥ ይእቲሰ እመ ተኃድገኒ ወተዓርፍ ኅድግዋ ዝኒ ኮነ በፈቃደ እግዚአብሔር እስመ ኢሠምረ ላቲ እግዚአብሔር ከመ ትሑር በዛቲ ፍኖት አላ አስተዳለወ ላቲ ፍኖተ ካልአ ዘውእቱ ፍኖተ እንጦንስ ወመቃርስ በከመ ይቤ መነኮስ እምቅድመ ጽንሰታ ከመ ትእቀብ መራዕይሁ እስመ ይቤ እግዚእነ ለአቡየ ብዙኅ ማኅደር ቦቱ።





፯ እሷም እንደ ወንጀለኛ ሥርዓት ብቻዋን ትቆም ነበር የንጉሥ ነገር ጠባቂዎችም ንጉሥን ወነጀልሽው እግዚአብሔርንም አሳዘንሽው ቃሉን ተደፋፍረሽ የትዕዛዙ ተቃራኒ ሆንሽ የሱን ሃይማኖት ተሳድበሽ ሃይማኖቱን እንዳይቀበሉ በቅዳሴ ጊዜ ስሙን እንዳይጠሩ የአገሩ ሰዎች ልቡናን አስተምረሽ አጨከንሽ አሏት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ግን ምንም መልስ አትሰጣቸውም ቀስ ብላ እራሷን ዘንበል አድርጋ ፈገግ እያለች ትስቃለች እንጂ ኋላ ግን እኔ ንጉሡንም አልሰድብም ሃይማኖቴንም ፈጽሞ አልክድም አለቻቸው ንጉሡም መልክተኞችን እየላከ ምን አለች ምን መለሰች ይል ነበር መልክተኞችም እሷስ ምንም መልስ አትመልስም ዝም ብላ ትስቃለች እንጂ አሉት።

፰ በዚህ ጊዜ ንጉሡ ተቆጥቶ እያቃለለችኝ ትስቅብኛለች አለና ይገሏት ዘንድ ወይም ጡቷን ይቆርጡ ዘንድ አዘዘ ያን ጊዜ ባለቤቷ መልክዓ ክርስቶስ ከንጉሡ ፊት ቆሞ ነበርና ንጉሡን:ጌታየ:ሆይ:አትቆጣ:የምትስቀው:አንተን:በማቃለል:አይደለም: የሚያስቃት:ጋኔን:በልጅነቷ:ጀምሮ:አድሮባታል:ብሎ:አታለለው:ይህን :ብሎ:ቁጣውን:አስታገሰው:እሱ:እጅግ:ይወዳት ነበርና።

፱ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ግን ሞትን አትፈራም ከቁጣውም የተነሣ አትደነግጥም ነበር የሚያስደነግጣችሁ ቢኖር አትደንግጡ በፍጹም ልባችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑት እንጂ እንደአለ እሷም ነቢያትን ሐዋርያትን ሰማዕታትን ያጸናህ ፈጣሪ እንደ እነሱ እኔንም አጽናኝ እያለች ትጸልይ ነበር ስለ ስምህ ሙቼ የምስክርነትን አክሊል እቀዳጅ ዘንድ አድለኝም ትል ነበር።

፲ ከዚህ በኋላ የንጉሥ አማካሪዎችም ንጉሥን በፈጠጋርና በድዋሮ ያሉ ወገኖቿ ጠላት ከሚሆኑህ አንዲት ሴትን መግደል ብትተው ይሻላል ብለው መከሩት ንጉሡም እሷ ካልሰደበችኝ ከእኔ ላይ ብታርፍ አትግደሏት ተዋት አለ ይህም የሆነ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው በዚህ በሰማዕታት ጐዳና እንድትሄድ አልወደደላትም ሌላ የእንጦንስንና የመቃርስን ጐዳና አዘጋጅቶላታልና ያ የበቃ መነኩሴ ከመፀነሷ በፊት መንጋዎቹን ትጠብቅ ዘንድ መርጧታል እንደአለ ጌታችን ለአባቴ ብዙ ማደሪያ አለ እንደአለ።

፲፩ ወእምዝ ኀደግዋ ወይቤልዋ ኢትሑሪ ርኁቀ ብሔረ ወኢትድግሚ ምሂረ አላ ንበሪ ኀበ አዝማድኪ ወሶቤሃ ነሥእዋ አዝማዲሃ ወአንበርዋ ኀቤሆሙ ወበህየኒ ይመጽኡ ብዙኃን መምሕራን እለ ሀለዉ በርትዕት ሃይማኖት ወይትናዘዙ ምስሌሃ ወይትጸንዑ በበይናቲሆሙ ፩ ለካልኡ ወእምድኅሬሁ ጕየት ወፀአት ገዳመ ዘጌ ወምስሌሃ ሀለዋ ወለተ ጳውሎስ ወእኅተ ክርስቶስ ወካልአትሂ ብዙኃት ወአእማቲሃኒ ኢዮጳራቅስያ ወማርያማዊት ወእስክንድራዊት ወአባ ጽጌ ሃይማኖትኒ ሀለወ ህየ ምስሌሆን ወኮነ ይናዝዞን ወያጸንዖን።

፲፪ ወእንዘ ይነብሩ ኅቡረ በሰላም ወእምድኅሬሁ መጽአ ፩ ብእሲ መስተመይን በጕሕሉት በአምሳለ ፍቁር ዘይሔውጾሙ በከመ ሐወጸ ለአባ በብኑዳ ውእቶሙሰ ኢያእመርዎ ከመ በትምይንት መጽአ ወአቅረቡ ሎቱ መባልዕተ ሠናያተ ወበልዓ ወነሥአ ኅዳጠ እምውእቱ መብልዕ ወቈጸረ በልብሱ ከመ ይሰድ ውስተቤቱ ወያርኢ ለሰብእ ወሶቤሃ ወጽአ ወሖረ ወበጺሖ ቤቱ አውጽአ እምአልባሲሁ ውእተ መብልዓ ከመ ያርኢ ለብእሲቱ ወእንዘ ሀሎ ውስተ እዴሁ መሰጦ መልአከ እግዚአብሔር ለውእቱ መብልዕ ወደንገጸ ወአንከረ ወነገራ ለብእሲቱ ዘከመ ገብረ።

፲፫ ወተቀጥዓቶ ወትቤሎ ለምንት ከመዝ ገበርከ ወኃሠሥከ መቅሠፍተ ለርእስከ ወካዕበ ፈነወ ራስ ሥዕለ ክርስቶስ ፩ደ እምሐራሁ ሰብአ ዓይን ከመይሕትት ወይጠይቅ ሀልዎተ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተጴጥሮስ ወበጽሐ ወተራከበ ምስሌሆሙ ወሎቱኒ ወሀብዎ መብልዓ ወበልዓ ውእቱሰ ሐራ ወልደ ብእሲሃ ለእኅተ ክርስቶስ ውእቱ ወሖረ ወነገሮ ለሥዕለ ክርስቶስ ዘከመ ርእየ ወዘከመ በልዓ መብልዓ ሠናየ ወጥዑመ ወምዑዘ ወይቤሎ ኦ እግዚእየ አንተሰ ትጻሙ ከንቶ እምሀልዎተ ዚአከሰ ይኄይስ ሀልዎተ ዚአሃ ለወለተ ጴጥሮስ።

፲፬ ወሰሚያ ዘንተ ሐቀየ ስነኒሁ ወፈቀደ ይድብዮሙ ወሀሎ አሜሃ በደብረ እንጦንዮስ ወሰሚዓ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወጽአት ወጕየት ወሖረት መንገለ አባቢት በታንኳ ወበውእቱ ባሕር ሀለዉ ጕማሬ ዐቢያን ወተፈልጠ፡፩ዱ እምኔሆሙ





፲፩ ከዚህ በኋላ ከሩቅ አገር አትሂጂ ዳግመኛ አታስተምሪ አርፈሽ ከዘመዶችሽ ጋር ተቀመጭ አሏትና ለቀቋት በዚያን ጊዜ ዘመዶቿ ተቀበሏትና ከእነሱ ጋር አስቀመጧት እዚያው ሳለች በቀናች ተዋህዶ ሃይማኖት ያሉ መምህራንም ወደ እሷ እየመጡ የእግዚአብሔርን ቸርነት እየተጨዋወቱ አንዱ ከአንዱ ጋር ይረጋጉ ጀመር ከዚህ በኋላ ጠፍታ ወደ ዘጌ ገዳም ሄደች ወለተ ጳውሎስና እኅተ ክርስቶስ አገልጋዮቿ ኢዮጳራቅስያና ማርያማዊት እስክንድራዊትም አባ ጽጌ ሃይማኖትም በዘጌ ሳሉ አባ ጽጌ ሃይማኖት ወደነሱ እየመጣ ያስተምራቸው ያፅናናቸው ነበር።

፲፪ በአንድነት በሰላም ተቀምጠው ሣሉ በሽንገላ አባ በብኑዳን ይጕበኘው እንደ ነበረው ያለህ አንድ ወዳጅ መሳይ ዘወትር የሚጕበኛቸው ፈታኝና አታላይ ሰው ነበር እነሱ ግን ለመፈተንና ለማታለል እንደሚመጣ አላወቁትም ነበርና ጥሩ ምግብ ሰጡት እሱም በልቶ ከእዚያ ምግብ ጥቂት በልብሱ ቋጥሮ ወደቤቱ ሄዶ ከልብሱ ውስጥ ያን ምግብ አውጥቶ ለሚስቱ አሳያለሁ ብሎ በእጁ እንደያዘ የእግዚአብሔር መልአክ ድንገት ከእጁ ነጥቆ ሄደ እሱም ደነገጠና እሱ አድንቆ ለሚስቱ ነገራት።

፲፫ እሷም አንተስ ለምን እንደዚህ አደረግህ ለራስህም መቅሠፍትን ለምን ፈለክ አለችው ዳግመኛ ራስ ሥዕለ ክርስቶስ ከወታደሮቹ መካከል አንዱን ለስለላ ወደ እነሱ ላከ የእናታችን የወለተ ጴጥሮስን ኑሮ ይጠይቅና ይረዳ ዘንድ እሱም ደርሶ ከእነሱ ጋር ሰላም ተባባሉና አስቀምጠው ለእሱም ምግብ ሰጡትና በላ ያም ለስለላ የመጣ ወታደር የእኅተ ክርስቶስ የባሏ ልጅ ነበር ተመልሶ ሄዶ እንደአየና መዓዛው የጣፈጠ ምግብ እንደበላ ነገረውና ጌታየ ሆይ አንተ በከንቱ ትደክማለህ ካንተ ኑሮ የወለተ ጴጥሮስ ኑሮ ይሻላል አለው።

፲፬ ይህን ሰምቶ ጥርሱን አፋጨና ይደበድባቸው ዘንድ አሰበ ያን ጊዜ በእንጦንስ ደብር ነበርና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሰምታ ወደአባቢት በታንኳ ስትሄድ በዚያ ባሕር ሶስት ጕማሬዎች ነበሩ አንዱ ከእነሱ ተለይቶ ይገለብጣቸውና ያስጥማቸው ዘንድ እየጮኸ መጣባቸው

:ወመጽአ:እንዘ:ይጥኀር:ከመ:ይገፍትያሙ:ወያስጥሞሙ:ወፈርሁ:ኖትያት:ወአኃትኒ:እለ:ሀለዋ:ምስሌሃ ወይቤሉ ንትወረው ለሊነ በፈቃድነ ከመ ኢያስጥመነ ዝንቱ ጉማሬ ወገሠጸቶሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎሙ ኢትፍርሁ ኦ ህፁፃነ ሃይማኖት ምንትኑ ያፈርሃክሙ ይመስለክሙኑ ዘኢትመውቱ ግመራ እመኒ ተወረውክሙ ለሊክሙ ወእመኒ ገፍትዓክሙ ውእቱ ጉማሬ ፩ደ ሞተ ትመውቱ ጽንዑ:ወኢትፍርሁ:ወሶበ:ጸንዓ:ላዕሌሆሙ:ፍርሃት:ከደነቶሙ:በዓፅፋ:ወይእቲሰ:ትጼሊ:በልባ ሰላመ መልአክ::

፲፫ ወቀርበ ውእቱ ጉማሬ ወወደየ እገሪሁ መልዕልተ ታንኳ ወአብቀወ አፉሁ ወእምነሰ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ኢትፈርሀ ግሙራ አላ ኈለቄት አስናኒሁ ወኮነ ኈላቁሆን ፱ ወእምድኅረ ጐንደየ አውረደ እገሪሁ ወገብአ ድኅሬሁ ወጐየ ወሮጸ ከመቦ ዘይተልዎ ወይሰድዶ እንተድኅር እስከ ተሠወረ እምዓይን ወኢተደመረ ምስለ አብያጺሁ ወኢተዐውቀ ኀበ ሖረ ርኢክሙኑ ፍቁራንየ ዘገብረ ላቲ እግዚአብሔር መንክራተ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በእንተ ጽንዓ ሃይማኖታ በከመ ይቤ መጽሐፍ መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅድሳኒሁ ወብፁዕ ብእሲ ዘስመ እግዚአብሔር ትውክልቱ ወይእተ ጊዜ ወጽአት እምባሕር በዳኅና ወበጽሐት ኀበ መካን ዘፈቀደት ወነበረት ኀዳጠ መዋዕለ ::

ምዕራፍ ፯ ዘረቡዕ

፩ ወእምድኅሬሁ ተመይጠት ወአተወት ዘጌ ወዓዲ ሶበ በዝኁ እለ ያስተኃይጽዋ ወይንዕውዋ ነዓውያን ሠራዊተ አፍርንጅ ተግኅሠት ወጐየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እምነ ዘጌ ምስለ እሊአሃ አኃት ሶበ ፈቀደት ትሑር ዋልድባ ወኃደገቶ ለአባ ጽጌ ሃይማኖት በህየ ወንብአቶ ወኢከሠተት ሎቱ ምሥጢራ ከመ ኢይኩን ባቲ ዕቅፍተ ወኢይከልኣ ሐዊረ ወሶበ አእመረ ተለዋ ወዴገና እንዘ ይሴአል ወየሐትት ኀበ አይቴ ሖረት ወረከባ በፍኖት ወተቃወማ ከመ ይክልኣ ሐዊረይእቲሰ አበየቶ ወኢተወክፈት ቃሎ አላ አርትዓት ፍናዊሃ ውእቱኒ ኢኃደገ ተሊዎታ ወሶቤሃ ትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በቃለ ተግሣጽ ኢትገብእኑ ብሔረከ ምንትኑ ከመ ገደፍከ ምስሌየ ወምንተ ተኃሥሥ እምኔየ ኢሰማዕከኑ ዘይቤ መጽሐፍ መቅድመ ኵሉ ይርኃቁ ጻድቃን ወመነኮሳት እምነአንስት::





የሚዋኙና ከእሷ ጋር እዚያ ታንኳ የሚቀዝፉ ወንዶችና እኅቶችም እጅግ ፈሩና:ይህ ጉማሬ ሳያስጥመን እኛ በፈቃዳችን ከውሀው ውስጥ ተወርውረን እንሙት አሏት እናታችን ወለተ ጴጥሮስም እናንተ ሃይማኖት የጐደላችው አትፍሩ እራሳችሁ እናንተ ብትወረወሩ ቶሎ የምትሞቱ ይመስላችኋልን ወይም እራስን መግደል ጽድቅ ይመስላችኋል ይህ ጉማሬ ቢወረውራችሁ ግን አንድ ሞት ነው የምትሞቱት አይዟችሁ አትፍሩ ጽኑ አለቻቸው በእነሱ ላይ ፍርሃት በጸና ጊዜ በልብሷ ሸፈነቻቸውና እሷ በልቧ የመልአኩን ሰላምታ ትጸልይ ጀመረ::

፲፫ ያም ጉማሬ ቀርቦ እግሩን ከታንኳ ላይ አድርጐ አፉን ከፈተ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ፈጽማ አልፈራችም አንድ ሁለት እያለች ጥርሶቹን ትቆጥር ነበር እንጂ የጥርሶቹም ቁጥራቸው ዘጠኝ ሆነ ጥቂት ከቆየ በኋላ ከታንኳ ላይ እግሩን አውርዶ ወደኋላ ተመልሶ ከኋላ የሚያባርረው እንደአለው ሸሸ ከዓይን እስኪሰወር ድረስ ከጓደኞቹ ተለይቶ ሸሸ ወደደረሰበትም አልታወቀም ወዳጆቼ እግዚአብሔር ስለ ሃይማኖቷ ጽናት ለወለተ ጴጥሮስ ያደረገላትን ድንቅ ሥራ አያችሁን መጽሐፍ እግዚአብሔር በቅዱሳን አድሮ ድንቅ ሥራ ያደርጋል እምነቱ በእግዚአብሔር የሆነ ሰው ንዑድ ክቡር ነው እንደአለ ያን ጊዜ በደኅና ከባሕር ወጥታ ከፈለገችበት ቦታ ደርሳ ጥቂት ቀን ተቀመጠች::

ምዕራፍ ፯ የረቡዕ

፩ ከዚህ በኋላ ተመልሳ ዘጌ ገባች እንደገና የሚፈልጓት የካቶሊክ ሠራዊት በበዙ ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከእነዚያ እኅቶች ጋር ወደዋልድባ ለመሄድ በአሰበች ጊዜ አባ ጽጌ ሃይማኖትን ትታ ከእሱ ተሸሽጋ አትሂጂ እንዳይላት ምሥጢሯን ደብቃ ተነሣች እሱም ወዴት ሄደች ብሎ ጠይቆ ተከትሎ በመንገድ አገኛትና እንዳትሄድ ከለከላት እሷም ዝም ብላ ሄደች እሱ ግን እየተከታተለ ተይ ተመለሽ ይላት ጀመር በዚያን ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በቁጣ ቃል ከኔ ምን ጥለሃል ወደ አገርህ አትገባም መጽሐፍ ከሁሉ አስቀድሞ ማችሁ: ደጋጐች ሰዎች ከሴቶች ራቁ ሲል አልሰማህምን አለችው::

፱ ወሶበ ትቤሎ ዘንተ ሐመ ልቡ ተምዓ ወኃደጋ ወገብአ ብሔሮ ወእምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ተሐውር በበንስቲት በእጋሪሃ ልምሉማት እንተ ተዓርግ ዐቀበ:ወትትቈለቈል ቍልቍሊተ ወትድህክ ከመ ሕፃናት ወይውሕዝ ደም እምነ እእገሪሃ ልምሉማት እስመ ቈቍዓ በሐዊረ ፍኖት መብዕሳት ወጕጻጕጻት ወሶበ ትስዕን ሐዊረ ትጠበልሎ በግማደ ጸርቅ ወእንዘ ትገብር ከመዝ በጽሐት ኀበ መካን ዘአልቦቱ ማይ በጊዜ ፺ ሰዓት ወአዕረፈት ታሕተ ጽላሎተ ዕፅ ወፈቀደት ትኅድር በህየ ወእለ ሀለዉ:ምስሌሃ:አርድዕት:ኃሠሡ:ማየ:ወኢረከቡ:ወእንበይነዝ:ተሀውኩ: ወቀብፁ:ተስፋ:ወይቤልዋ:ለእምነቅድስት:ወቡርክት:ወለተ:ጴጥሮስ:ንፍ ልስ:እምዝንቱ:መካን:ከመ ኢንኅልቅ በጽምዕ::

፲:ወይእቲኒ:ትቤሎሙ:ኦ:ኀፁፃነ:ሃይማኖት:ለምንት:ትትሀወኩ: ወትቀብፁ:ተስፋ:ወእምዝ:ሜጠት:ገጻ:ድኅሬሃ:አንጸረት:በአፃብዒሃ:እብለ ክሙ:ሑሩ:ኀሡ:ኀበ:ከሀ:ወኢይትኃጣእ:ማይ:ወሐዊሮሙ:ኀበ:መካን:ቅ ሩብ:ዘአመረቶሙ:ረከቡ:ማየ:ጽሩየ:እንዘ:የዓውዶ:ቍልቋል:እምለፌ:ወ እምለፌ:ወሰትዩ:እምኔሁ:ወተፈሥሑ:ወነቅዓ:ውእቱ:ማይ:በጸሎተእም ነ:ቅድስት:ወቡርክት:ወለተ:ጴጥሮስ:ኀበ:መካን:ዘተኃጥአ:ቀዲሙ::

፲፩ ወእምድሬሁ ቦአት ዋልድባ ወነበረት ህየ እንዘ ትጸመድ ወትትቀነይ ለእግዚአብሔር በጾም ወበጸሎት ወእንዘ ትትጋደል በኵሉ ገድል ጽኑዕ ወበምግባረ ትሩፋት ብዙኀ በፃማ ወበስራኀ በከመ ይቤ መጽሐፍ ዘፃመወ በዓለም የሐዩ ለዝሉፉ እስመ ኢይሬኢ ሙስና ወሀለወት ትንበር በህየ አሐቲ አረጊት መዓትምት ፈድፋደ ወዘልፈ ትትመዓዕ ወአልቦ ዘይክል ጽዊሮተ እከይ ግዕዛ ወኢታመዘግን ሶበ ይትለአካሃ ወኢትባርክ ግሙራ ሶበ ይትጌበራ ወያሠምራሃ አላ ትረግም ወትጸርፍ ወበእንተዝ ይርኅቃ እምኔሃ ኵሎን አኃት እለ በገዳም ወትነብር ባሕቲታ ወትትመነደብ ዓቢየ ምንዳቤ ወአልቦ ዘይሬእያ መኑሂ እምአኃት::

፲፪ ወእምዝ ሶበ ርእየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኵሎ ግዕዛ ወኵሎ ምንዳቤ ዘላዕሌሃ ቀነተት ቅናተ ሃይማኖት ወአጠቀት መክፌ ትሕትና ወአኃዘት ትትለአክ ላቲ ከመ አመት በጥቡዕ ልብ ወኮነታ ረድእተ ወገደፈት ነፍሳ





፱ ይህን ባለች ጊዜ በልቡ አዝኖ ተቆጥቶ ትቷት ወደ አገሩ ተመለሰ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም በለሰለሰ እግሯ አቀበቱን:ቁልቁለቱን ቀስ ቀስ እያለች እንደ ሕፃናት እየዳኸች ትሔድ ጀመረ ከእግሮቿም ደም ይፈስ ጀመር ጉጻጉጽና አስቸጋሪ በሆነ ጐዳና እግሮቿ ሻክሮዋልና መሄድ በአቃታት ጊዜ በተቀደደ ጨርቅ ትጠቀልል ነበር እንደዚህ እያደረገች ስትሄድ በ፺ ሰዓት ውሀ ከሌለበት ቦታ ደረሰችና ከዕንጨት ጥላ ስር አረፈች እዚያው ማደር በፈለገች ጊዜ ከእሷ ጋር ያሉ ውሀ ፈልገው ስለአልአገኙ ተስፋ ቆርጠው እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስን በውሀ ጥም እንዳናልቅ ከዚህ ቦታ እንሂድ አሏት::

፲ እሷም እናንተ ሃይማኖት የጐደላችሁ ለምን ትጨነቃላችሁ ተስፋስ ለምን ትቆርጣላችሁ አለቻቸው ከዚህ በኋላ ፊቷን ወደኋላ መልሳ በእጇ እያመለከተች ወደዚያ ሄዳችሁ ፈልጉ እዚያ አይጠፋም አለቻቸው እነሱም ወደአመለከተቻቸው ቦታ በሄዱ ጊዜ በወዲህና በወዲያ ቁልቋል የከበበው የጠራ ንጹሕ ውሀ አገኙ እነሱም ደስ ብሏቸው ጠጡ አስቀድሞ ተፈልጐ ከጠፋበት ቦታ በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎት ያ ውሀ መንጭቷልና::

፲፩ ከዚህ በኋላ ወልድባ ገብታ በጾምና በጸሎት ጽኑ በሆነ ተጋድሎና በብዙ ሥቃይ እግዚአብሐርን ታገለግል ጀመር መጽሐፍ በዓለም የደከመ ለዘለዓለም ይኖራል ጥፋትን አያይም እንደአለ በዚያ እጅግ የምትቆጣ መጥፎ ባሕርይ ያላት ማንም ፀባይዋን መታገስ የማይችል ምንም ቢላኩላትና ቢያገለግሏት መራገምና መሳደብ እንጂ መመረቅና ማመስገን የማታውቅ አንዲት አሮጊት ነበረች ስለፀባይዋ በገዳም ያሉ እኅቶች ይርቋት ነበር ብቻዋን ተቀምጣ እጅግ ትቸገር ነበር በገዳም ከአሉት እኅቶች የሚጐበኛት ማንም የለም ::

፲፪ ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ፀባይዋንና ችግሯን በአየች ጊዜ የሃይማኖትና የትሕትና መታጠቂያን ትዕግሥትን ታጥቃ የሷ ረድ ሁና እንደአገልጋይ ታገለግላት ሰውነቷን ከእግሯ በታች አድርጋ ወፍጮ እየፈጨች

ታሕተ እገሪሃ ወትትጌበር ግብረ ማኅረፅ ወተሀብዝ ኅብስተ ወትቀድሕ ማየ ወሶበ ኃጥአት እክለ ተሐውር ኀበ ቀሪም ወታመጽእ ወትሴስያ ወትፌጽም ላቲ ኲሎ ፈቃደ ዚአሃ ወይእቲሰ አረጊት ኢታመዘግን ተግባራ አላ ትትመዓዕ ወትጸርፍ ላዕሌሃ ወትረግማ ወትቤላ አንቲ ሰራቂት ወትትሜሰሊ ጻድቅተ በአፍአ ወእንተ ወሥጥኪ አርዌ ምድር እኪት አንቲ።

፯ ወሶበ ተሐብዝ ኅብስተ ትእኅዝ እዴሃ ወታውዕያ በእቶነ እሳት ዘረስነ እስከ ይትመለጥ እዴሃ ወትቤላ እፎ ሐፀነተኪ እምኪ ወእፎ መሀረተኪ ወአልመደተኪ በዝንቱ ልማድ እኩይ ዕምስለ ዝኒ ብዙኅ ውእቱ ንባበ ጽርፈት ወቃለ ትዕይርት ዘትነብብ ላዕሌሃ ኲሎ ዕለተ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኢተኃዝን ወኢታንጐረጕር፡በዝንቱ፡ኲሉ፡አላ፡ትትፌሣሕ፡ወትትዔገሥ፡ወትትሜሰል፡ከመ፡ዮሐንስ፡ሐፂር።

፰ ወአሐተ ዕለተ ሶበ ሰምዓት እኅተ ክርስቶስ እንዘ ትጸርፍ ላዕሌሃ በከየት ፈድፋደ ወትቤላ ምንት ብኪ ምስለ ዛቲ አረጊት ዘትትለአኪያ እንዘ ትጴእለኪ ወትረግመኪ አልቦኑ ካልእ ግብር ዘእንበለ ዝንቱ ዘያሠምሮ ለእግዚአብሔር አውሥአታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤላ ኢትብክዪ በእንቲአየ ዝንቱ ጽርፈት አኮ ዘዚአሃ አላ ዘሰይጣን ውእቱ ሊተሰ ኢየኃዝነኒ አላ እኄልቄ ከመ በቀኈዔት ወበረከት እስመ ይቤ ወንጌል አሌ ለክሙ እስመ ሠናየ ይብል ሰብእ ላዕሌክሙ ወይዌድሱክሙ።

፱ ወእምዝ ሶበ ፈጸመት ፩ ዓመተ እንዘ ትትለአካ አዕረፈት ይእቲ አረጊት ወገነዘታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮሰ በእዴሃ ወቀበረታ ርእዩኬ ፍቁራንየ ዘመጠነዝ ሀብት ዘተውህባ ላቲ ኦ ትሕትና ዘመጠነዝ ትሕትና ኦ ኂሩት ዘመጠነዝ ኂሩት ኦ ትዕግሥት ዘመጠነዝ ትዕግሥት እንዘ አግዓዚት ይእቲ አቅነየት ርእሳ በፈቃዳ ለእንተ ትንዕሷ እምኔሃ ወለእንተ ትጸርፍ ላዕሌሃ ከመ ትርክብ እምኔሃ አክሊለ ዕጉሳን ሰማዕታት እስመ ዘያፈቅራ ለንህብ ይጥዕም መዐረ ወዘሰ ኢያፈቅራ ወይጕይይ እምኔሃ ኢይጥዕም መዐረ ወከማሁ እምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አፍቀረታ ለዛቲ አረጊት ወአግረረት ላቲ ርእሳ እስመ በእዴሃ ሀሎ ጣዕመ መንግሥተ ሰማያት ።





እንጀራ እየጋገረች ውሃ እየቀዳች እህል ስታጣ ቃርሚያ እየቃረመች አምጥታ ትመግባት ፈቃዷን ሁሉ ትፈጽምላት ጀመረች ይህች አሮጊትም አታመሰግናትም ትቆጣ ትጮኽባት ትሰድባትና ትረግማት ላይሽን ሲያዩሽ ጻድቅ ትመሲያለሽ ውስጥሽ ግን እንደ እባብ ክፋትን የተሞላ ነው ትላታለች ።

፯ እንጀራንም በምትጋግርላት ጊዜ እጇን ትይዝና እጇ እስኪመለጥ ድረስ በጋለ ምጣድ ታቃጥላታለች እናትሽ እንዴት አሳደገችሽ ይህን ክፉ ልማድ እንዴት አስለመደችሽ እያለቻት ታሰቃያት ከዚህም የበለጠ ብዙ ስድብ ትሰድባት ነበር እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም እንደ ዮሐንስ ሐፂር ታግሣ በደስታ ትቀበላለች እንጂ በዚህ ሁሉ ስድብ አዝና አታንጐራጕርም ነበር።

፰ ከዕለታት በአንድ ቀን ስትሰድባት እኅተ ክርስቶስ ሰምታ በጣም አለቀሰችና ይች አሮጊት እየሰደበችሽ ትላኪያት ዘንድ ከእዚህች አሮጊት ጋር ምን ጥለሻል እግዚአብሔርን የሚያስደስት ያለዚህ ሌላ ሥራ የለምን አለቻት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም መልሳ እኅቴ ይህ ስድብ የሷ አይደለም የሰይጣን ነው እንጂ ለኔ አታልቅሺ እኔን አያሳዝነኝም እኔስ ጥቅም እንደአለው እንደበረከት እቆጥረዋለሁ ወንጌል ሰው በከንቱ ቢያመሰግኑዋችሁ መልካም ቢሉዋችሁ ወዮላችሁ ብሏልና አለቻት ።

፱ ከዚህ በኋላ አንድ ዓመት አገልግላ ያቺ አሮጊት አረፈችና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በእጅዋ ገንዛ ቀበረቻት ወዳጆቼ እስኪ የተሰጣትን ሀብተ ትሕትና ተመልከቱ እንደዚህ ያለ ትሕትና እንደምን ያለ ትሕትና ነው እንደዚህ ያለ ትዕግሥትስ እንደምን ያለ ትዕግሥት ነው እመቤት ስትሆን በፈቃዷ እራሷን አዋርዳ ለምትሰድባት ከእሷ ለምታንስ ተገዛች ታጋሾች የሆኑ የሰማዕታት አክሊልን ከእሷ ታገኝ ዘንድ ንሁብን የሚወዳት ከእሷ መዓርን ይበላል የማይወዳት ከእሷ የሚሸሽ ግን መዐርን አይበላም እንደዚሁ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጰጥሮስ ያችን አሮጊት ወደደቻት እራሷንም አስገዛችላት የመንግሥተ ሰማያት ጣዕም በእጇ አለና ።

፱ ካዕበኒ እመ ኢያግረረት ርእሳ ለአረጊት እምኢገረሩ ላቲ ነገሥት ወመኳንንት ወእምኢተመውኡ ላቲ ሰይጣናት በከመ ይቤ አረጋዊ መንፈሳዊ ሶበሰ ኢያግረረ ዮሴፍ ርእሶ ቀዲሙ ለሕገ ግብርናት እምኢኮነ እግዚአ ላዕለ ምድረ ግብጽ ወጳውሎስኒ ይብል እስመ ግረትሰ በሥጋ ለኅዳጥ ዘመን ትበቍዕ ወጽድቅሰ ታሠልጥ በኵሉ ወባቲ ተስፋ ሕይወት በዝ ዓለም ወበዘይመጽእ ::

፲ ወይ ለነ አሌ ለነ ለእለ ኢንገብር ከመዝ ወኢናገርር ርእሰነ ኀድጉሰ ለእለ ይጼእሉነ ወይረግሙነ ወለእለሂ ይዌድሱነ ወይባርኩነ ኢንትለአክ በርትዕ እንዘ ጥዑያን ንሕነ ሕሙማን ንሕነ ንብል ወእንዘ ብነ ኃይል ድኩማን ንሕነ ንብል ወናመክኒ ብዙኃ ምክንያተ ስምዑ ዓዲ ንንግርክሙ ዜናሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘከመ ነበረት ፯ አውራኀ በውእቱ ገዳም እንዘ ትሴሰይ ቈጽለ ሐምል ምስለ እኅተ ክርስቶስ ወምስለ:ኵሎን:እለ:ሀለዋ:ምስሌሃ:እስከ:ተወለጣ:አስናኒሆን:እምፅዕዳዌ ሁ:ወተመሰላ ውእተ ሐምለ::

፲፩ ወአሐተ ዕለተ ሶበ ርእየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አስናኒሃ ለእኅተ ክርስቶስ ትቤላ ኦ እኅትየ ምንተ ኮነ ስነንኪ ወይእቲኒ ትቤላ ዘለኪኒ ኮነ ከማየ በከመ ይቤ መጽሐፍ ተጸነሱ ወተመንደቡ ወሐሙ ዘኢይደልዎ ለዓለም ረከቡ ወዔሉ ውስተ አድባር ወውስተ ገዳም ወበዓታት ወግበበ ምድር ፡ ዕብ ፲፩ ወእምድኅሬሁ ፈነወት እማ ክርስቶስ ዕበያ አዕዱገ ብዙኃነ እለ ፅዑናን ሐሪፀ እክል ወኵሎ መፍቅዳተ ሥጋ ዘዘዚአሁ ወእለ ተፈነዉ ልኡካን በጽሑ ህየ ወተፈሥሐ ኵሎን አኃት ሶበ ርእያ ዘንተ እስመ ርኅባት እማንቱ መጠነ ፯ አወራኀ ::

፲፪ ወመሰሎን ዘይበልዓ ውእተ ጊዜ ወነገራሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሰሚዓ ኃዘነት ፈድፋደ ወትቤ በምንትኑ አምዓዕክዎ ለእግዚአብሔር ወአምጽአ ብየ ዘጕየይኩ እምኔሁ ወይቤላሃ እማንቱ አኃት ንሕነሰ ንትፌሣሕ ወንጓጕዕ ለበሊዕ እንበይነ ምንትኑ ተኃዝኒ አንቲ ወትቤሎን አሐዝን አንሰ እስመ:ይመስለኒ:ዘአምጸአ:ብነ:ሰይጣን:ከመ ያመክረነ እስመ ውእቱ ያመክኒ ወለእግዚአብሔርኒ አመክሮ ከመዝ በከመ ይቤ ወንጌል ወጸመ ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ ወእምድኅረዝ ርኅበ ወቀርበ::





፱ ዳግመኛም እራሷን ለዚያች አሮጊት ባታስገዛ ኖሮ ነገሥታትና መኳንንት ባልተገዙላት ሰይጣናትም ባልተገዙላት ነበር አረጋዊ መንፈሳዊ አስቀድሞ ዮሴፍ እንደ ባሮች ልማድ እራሱን ባያስገዛ ኖሮ በግብፃውያን ላይ አለቃ ባልሆነም ነበር እንደአለ ጳውሎስም በሥጋ መግዛት ለጥቂት ጊዜ ነው እውነት ግን በሁሉ ዘንድ ሥልጣን አላት የዘለዓለም ሕይ ኑ የማውረስ ተስፋ አላት አለ::

፲ እንደዚህ ለማናደርግና እራሳችንን ለማናስገዛ ለኛ ወዮልን ወዮታ አለብን እኛ ግን ክፉዎች ስለሆን እንኳን ለሚጠሉንና ለሚረግሙን ለሚያመሰግኑንና ለሚመርቁን ያመናል ይደክመናል እንላለን እንጂ በቅን አንላክም አንታዘዝም ጉልበት እያለን ደካሞች ነን እንላለን ብዙ ምክንያትን እናመካኛለን ዳግመኛ ም የእናታችን የቅድስት ወለተ ጴጥሮስን ዜና ገድሏን ስሙ በዚያ ገዳም ከእኅተ ክርስቶስና ከእሷ ጋር ከአሉት እኅቶች ጋር ጥርሶቻቸው እስኪ ለወጡና የሚበሉትን ቅጠል እስኪመስል ድረስ የጐመን ቅጠል እየበላች ኖረች

፲፩ ከእለታት በአንዲት ቀን እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አይታ እኅተ ክርስቶስን እኅቴ ሆይ ጥርስሽ ምን ሆነ አለቻት እሷም መልሳ ያንቺም እንደኔው ሆኗል እኮ አለቻት መጽሐፍ ተሰቃዩ ተቸገሩ ታመሙ ዓለም አልተገባቸውምና በየተራራውና በየዱሩ በየዋሻውና በየፍርኩታው ዞሩ እንደአለ ዕብ ፲፩ ከዚህ በኋላ እናቷ ክርስቶስ ዕበያ ዱቄትና የተለያዩ ለሥጋ የሚያስፈልጉ ምግቦችን በብዙ አህዮች አስጭና ላከች የተላኩትም መልእክተኞች ጭነው እዚያ ደረሱ እነዚያም እኅቶች ይህን በአዩ ጊዜ ደስ አላቸው ሰባት ወር እህል ሳይቀምሱ በረሀብ ቆይተዋልና

፲፪ ያን ጊዜ የሚበሉ መስለዋቸው ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ነገሯት እሷም ሰምታ እግዚአብሔርን በምን አሳዝኜ ነው ሸሽቼ የመጣሁትን እህል ያመጣብኝ ብላ አዘነች እነዚያም እኅቶች እኛስ ለመብላት እየጓጓን ተደስተናል አንቺ ለምን አዘንሽ አሉዋት እሷም እኔስ አዝናለሁ ሰይጣን በመብል ይፈትነን ዘንድ ያመጣብን ይመስለኛል እሱ ለማሳት ምክንያት ያደርጋልና ወንጌል ዓርባ መዓልትና ዓርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ተራበ ከተራበ በኋላ ፈታኙ ለመፈተን ወደ እሱ ቀረበ እግዚአብሔርንም እንደዚህ አድርጐ ፈተነ እንደአለ አለቻቸው ::

፲፫ ዘያሜክሮ ወለነኒ ፈቀደ ያመክረነ በዝንቱ መከራ ወይቤላሃ ይምጽኡኑ ልኡካን ወይንግሩኪ መልዕክተ ዘእምኀቤሆሙ ወትቤሎ ን እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዮምሰ ይቢቱ አፍአ ወይጼሪሩ እምነ ሐሪጽ ዘአምጽኡ ኢይሰምዕ መልዕክቶሙ ወኢይትዌከፍ እምኔሆሙ ወቤቱ በአፍአ ወነበሩ እንዘ ይጸንሑ እስከ ሠሉስ ዕለት ወይእቲኒ አፀወት ቤታ ወነበረት እንዘ ትጼሊ ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይክሥት ላቲ ምክንያተ ምጽአቶሙ ወከሠተ ላቲ ወአእመረት ከመ ኮነ ፈቃደ እግዚአበሔር እስመ ውእቱ ርኅሩኅ ላዕለ ምንዱባን ወርኁባን በከመ አቅደምነ ወንቤ አመ ርኅበ ሶምሶን ጸለየ ኀበ እግዚአብሔር ወረከበ መዐረ እምአፈ አንበሳ ወበልዓ ወለኤልያስኒ ሴሰዮ በአፈቋዕ ወለዳንኤልኒ ፈነወ ሎቱ ዕንባቆምሃ እንዘ ምስሌሁ ኀብስት አመ ወደይዎ ውስተ ግብ እስመ ምንዱብ ውእቱ በረኃብ ::

፲፬ ወበሣልስት ዕለት ትቤላ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸውኢ ልዑካነ ወተወከፊ እክለ ዘአምጽኡ ወሐረት ወፀውአቶሙ ወቦኡ ወነገርዋ መልእክተ እሚ ወዘከመ ትቤላ ንዒ ምዕረ እስመ እፈቱ እረአይኪ ወብየ ነገር ዘእትናገር ምስሌኪ አፈ በአፍ ምንትኑ ያጸንአኪ አኮኑ አነ እምኪ ዘጾርኩኪ በከርሥየ ወሐፀንኩኪ በአጥባትየ ቦኑ ሀለወተኒ ካልእት ወለት ዘእንበሌኪ ኢእምቅድሜኪ ወኢ እምድኅሬኪ ወሰላመ እግዚአብሔር የሃሉ ምስሌኪ አሜን ::

፲፭ ወሰሚዓ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አርመመት ወኢተሰጥወቶሙ ወይቤላሃ እልኩ አንተ አግብኢ ሎሙ ስጣዌ መልዕክት ይግብኡ ሐገሮሙ አውሥአቶሙ ለልዑካን ወትቤሎሙ በልዋ ለእምየ ከመዝ አኮ ድልወት ሊተ እጻእ እምገዳም ወእባእ ውስተዓለም ዘወጻእኩ እምኔሁ ድልወትሰ ለኪ ትትልዊ አንቲ ኀበ ሖረት ወለትኪ ወዘንተ ብሂላ ፈነወቶሙ ለልዑካን ወገብኡ ሐገሮሙ ወእምዝ ተስዕለታ እኅተ ክርስቶስ ወትቤላ ምንትኑ ዘአበይኪ ቀዲሙ ወእንበይነ ምንትኑ ተወከፍኪ ድኅረ ወትቤላ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ቅድመኒ አበይኩ እስመ መሰለኒ ዘእምሰይጣን ውእቱ ወድኅረኒ ተወከፍኩ እስመ አእመርኩ ከመ በፈቃደ እግዚአብሔር መጽኡ::





፲፫ ይዘው የመጡትን መልክተኞች ከወዴት እንደመጡ ይንገሩሽ አሏት ዛሬስ ከእዚያው ከደጅ አድረው ይዘው ከአመ ጡት ዱቄት ይመገቡ መልዕክታቸውንም አልሰማም እህሉንም አልቀበልም አለች እነሱም እዚያው ከደጅ እያደሩ እስከ ሶስት ቀን ሰነበቱ እሷም ቤቷን ዘግታ የመጡበትን ምክንያት ይገልጥላት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ታመለክት ጀመር እሱም ገለጠላት የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ አወቀች እሱ ለተራቡትና ለተቸገሩት ርኅሩኅ ነውና አስቀድሞ ሶምሶን በተራብ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጸለየና ከአንበሳ አፍ መዐር አግኝቶ እንደ በላ ኤልያስንም ቁራ እንዲመግበው እንደ አደረገ ዳንኤልንም በአንበሳ ጉድጓድ በወረወሩትና በተራብ ጊዜ ለአጫጆች ምሳ እንደያዘ እንባቆምን ልኮለት እንደ መገበው::

፲፬ በሦስተኛ ቀንም እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እኅተ ክርስቶስን እነዚያን መልእክተኞች ጠርተሽ ያመጡትን እህል ተቀበያቸው አለቻትና ሄዳ ጠራቻቸው እነሱም ገብተው አንድ ጊዜ ነይ አንቺን ለማየት ናፍቄያለሁና ለአንቺ የምነግርሽም ነገር አለና ከአንቺም በፊት ከአንቺም በኋላ የወለድኋት ያለ አንቺ ሌላ ሴት ልጅ አለችኝን እኔ በማህፀኔ የተሸከምኩሽና በጡቴ ያሳደኩሽ እናትሽ አይደለሁምን ምን ያስጨክንሻል ልጄ የእግዚአብሔር ሰላም ካንች ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ይደረግልን የሚል የእናቷን መልዕክት ነገሯት::

፲፭ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ሰምታ መልስ ሳትሰጣቸው ዝም አለች ያን ጊዜ እነዚያ ሴቶች የመልእክቱን መልስ መልሺላቸው እንጂ ወደ አገራቸው መልእክቱን ይዘው እንዲመለሱ አሏት እሷም ሂዳችሁ ለእናቴ ዓለምን ጥየ ከመጣሁ በኋላ ከገዳም ወደ ዓለም እመለስ ዘንድ ለኔ አገባብ አይደለም የሚገባስ አንቺ ልጅሽን ተከትለሽ ትመንኚ ዘንድ ይገባሻል በሏት አለቻቸው ይህን ብላ እነዚያን:መልእክተኞች:ላከቻቸው:ከዚህ:በኋላ:እኅተ:ክርስቶስ:አስቀድሽ:ለ ምን:እንቢ:አልሽ:ኋላስ:ስለምን:ተቀበልሽ:ብላ:ጠየቀቻት:እናታችን:
ቡርክት:ወለተ:ጴጥሮስምአስቀሞ:እንቢ:ያልኩት:ከሰይጣን:እንደ ሆነ: ብየ ነው ኋላ የተቀበልኩት በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደመ ጡ አውቄ ነው አለቻት::

፲፮ እስኩ አእምሩ ወለብዉ ኦ ፍቁራንየ ለመኑ ይትከሃሎ ይትዓገሥ ከመዝ እንዘ ርኁብ ውእቱ ዘኢጥዕመ እክለ መጠነ ፯ አውራኅ መኑ ሰብእ ዘርኅበ ሶበ ርእየ እክለ ዘኢይጔጕዕ ለበሊዕ ኀድግሰ ዘፈነወት ሎቱ እሙ ኀበ ባዕዳንሂ እምሐረ ይስእል አው ከመ ይሰርቅ ይመስለኒ ወይእቲሰ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ክህለት በኀይለ እግዚአብሔር በከመ ይቤ ጳውሎስ ከሃሊ አንሰ ተጽናሰኒ ወተደልምኒ በኵሉ ወውስተ ኵሉ ለመድኩ ርኂበኒ ወጸጊበኒ ሐሚመኒ ወተፈሥሖኒ ኵሎ እክል በዘውእቱ አክህለኒ እግዚአብሔር::

ምዕራፍ ፯

፩ ወሀሎ ፩ዱ መነኮስ ጻድቅ ዘስሙ መልክዓ ክርስቶስ በውእቱ ገዳም ወሶበ አእመረ ከመ ቀርበ ጊዜ ዕረፍቱ መጽአ ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ይንግራ ዕለተ ሞቱ ወይሰነአል እምኔሃ እስመ ውእቱ ማእምረ ኅቡአት ወየአምር ዘይከውን እምቅድመ ይኩን ወሶበ ዜነዋ ዕለተ ሞቱ ተከዘት ፈድፋደ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤ በልባ ያሙተኒ ሊተ እምቅድሜሁ እፎ ይመውት ዝንቱ ጻድቅ ወዝንቱሰ ሕሊና ኢኮነ ሠናየ በቅድመ እግዚአብሔር ወሶቤሃ ሐመት ሕማመ ውግዓት ወአልፀቀት ለሞት በከመ ሐመ ሕዝቅያስ ወይቤ ከመ ዐድገ መረብ ዘገዳም ከማሁ እነቁ ወከመ ርግብ እነብብ::

፪ ወአእመረ ሕሊናሃ ውእቱ መነኩስ ወገሠጻ ወይቤላ እፎ ተመነይኪ ሞተ ወተቃረንኪ ፍትሐ እግዚአብሔር እስመ ውእቱ ያበዝኅ ወያውኅድ ዕድሜሁ ለሰብእ ይቀትል በፈቃዱ ወያሐዩ በፈቃዱ ወኢኮነ በፈቃደ ሰብእ ወበእንተዝ መጽአ ላዕሌኪ ዝንቱ ሕማም ጽኑዕ ከመ ያመክርኪ ሞተሰ ኢትመውቲ እምዝ ዳግመ ኢተሐልዪ ዘንተ ሕሊና ስምዒ እነግረኪ ዘወደየ እግዚአብሔር ቃለ ውስተ አፉየ ሀለወ ይከውን በዕብሬትኪ ማኅበር ፯ ጊዜ ኀበ ፯ መካናት ወይድኅኑ በእዴኪ ብዙኃት ነፍሳት::

፫ ፩ዱ ማኅበር ዘዢበይ ወካልእ ዘጫንቋ ወሣልስ ዘምጽሌ ወራብዕ ዘዘጌ እለ ቀተሎሙ ብድብድ ወሐምስ ዘደምበዛ ወሳድስ ዘአፈርፈረስ ወሳብዕ ዘዘምቦል ወእምድኅሬሁ ይከውን ሞትኪ ወካዕበ እብለኪ አንብቢ ወትረ ወንጌለ ዮሐንስ እስመ አነ ርኢኩ እሙነ ራእየ እንዘ ያከብርዎ ክብረ ዓቢየ ለዘያነብብ ኪያሁ ወትረ ወይገብሩ ሎቱ መልዕልቲሁ ተድባበ ብርሃን ወያነብሩ





፲፮ ወዳጆቼ ሆይ ሰባት ወር እህል ሳይቀምስ ተርቦ ሳለ እህል እያየ ይመልስ ዘንድ ለማን ይቻለዋል እህልንም አይቶ ለመብላት የማይጓጓ ማነው እናቷ የላከችላት ቀርቶ ሌላ ሰው ከተራበ ወደሌላ ሄዶ ይለምናል የሚሠርቅም አለ እናታችን ቅድስት እና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ግን በእግዚአብሔር ኃይል ረሀብና ችግሩን ችላለች ሁሉን ቻይ ጳውሎስ እኔ ረሀቡንም ጥጋቡንም በፈጣሪየ ኃይል ሕማሙንም ደስታንም እግዚአብሔር እንዳስቻለኝ ሁሉንም እችላለሁ እንዳለ::

ምዕራፍ ፯

፩ በዚያ ገዳም ስሙ መልክአ ክርስቶስ የሚባል በጣም የበቃ መነኩሴ ነበር ዕለተ ሞቱ መድረሱን ባወቀ ጊዜ ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ይነግራትና ይሰናበታት ዘንድ መጣ እሱ የተሠወረውንና ወደፊት የሚሆነውን ከመሆኑ አስቀድሞ ያውቃልና በነገራት ጊዜም እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እጅግ አዝና በልቡናዋ ከሱ አስቀድሞ እኔን ይግደለኝ ይህ ጻድቅ ሰው እንዴት ይሞታል አለች ይህ ሀሳቧ በእግዚአብሔር ፊት መልካም አልነበረምና በዚያን ጊዜ ውጋት ያዛትና ታመመች ሕዝቅያስ በታመመ ጊዜ እንደበርሃ /አህያ እጮኻለሁ እንደርግብም እጮኻለሁ እንዳለ::

፪ ከዚህ በኋላ ያ የበቃ መነኩሴ ሞትን ለምን ተመኘሽ የእግዚአብሔር ፍርድንስ ለምን ተቃረንሽ እሱ የሰውን እድሜ ቢፈልግ ያበዛል ቢፈልግ ያሳንሳል የፈለገውን ይገላል የፈለገውን ያድናል በሰው ፈቃድ የሚሆን ነገር የለም ስለዚህ ነገር ይህ ጽኑ ደዌ ይቀጣሽ ዘንድ ባንቺ ላይ ታዘዘ ሞትንስ አትሞችም እንዲህ:ያለውን:ነገር:ሁለተኛ:አታስቢ:አላት:እንደገናም እግዚአብሔር ያቀበለኝን ነገር ልንገርሽ ስሚኝ ሰባት ጊዜ ሰባት ቦታ ባንቺ መሪነት ገዳም ይመሠረታል ብዙ ነፍሳት ባንቺ ጸሎት ይድናሉ ::

፫ አንዱ ማኅበር የዢበይ ሁለተኛው የጫንቋ ሶስተኛው የምጽሌ አራተኛ ተስቦ የሚገላቸው የዘጌ አምስተኛ የደምበዛ ስድስተኛው የአፈር ፈረስ ሰባተኛው የዘምቦል ማኅበር ናቸው ሞትሽ እነዚህን ከመሠረትሽ በኋላ ነው አላት ዳግመኛ የዮሐንስን ወንጌል ዘወትር አንብቢ ዘወትር የዮሐንስን ወንጌል የሚያነበውን ታላቅ ክብር ሲያከብሩት መላእክት ከላይ የብርሃን

ሎቱ መትሕቴሁ ዓራተ ዘወርቅ ንጹፈ ወርሱየ ወሥርግወ በእንተ ዝንቱ እብለኪ ዘንተ አንብቢ ኵሎ መዋዕለ ሕይወትኪ ወእምድኅረ ነገራ ዘንተ ወኵሎ ወዘይመስሎ እምሥጢረ እግዚአብሔር ተሰነዓለ እምኔሃ ተመይጠ ወአተወ ውስተ በዓቱ ወፈለሰ እምዝንቱ ዓለም ኀለፈ ወሖረ ኀበ እግዚአብሔር ዘአፍቀሮ ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስለ ፍቁሩ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፬ ወኮነ ልማዶሙ ለመነኮሳት ዘዋልድባ ይገብሩ ምህላ ወይ ትመሀለሉ እምሠኑዩ ለወርኃ ሐምሌ እስከ ሰሙኑ ለወርኃ ሐምሌ ወእምዝ ይትባረኩ እምአዕሩግ ወይሰነዓሉ ወይትፋነዉ ወየሐውሩ ኀበ መፍቅዶሙ ያስተጋብኡ ሲሳዮሙ ወበውእቱ መዋዕል ተግኅሠት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወተፈልጠት እምነ አኃት እለ ሀለዋ ምስሌሃ ወነበረት ጥቃ መካን ዘመነኮሳት ከመ ትስማዕ ድምፀ ምህላሆሙ እንበለ ትግበር ምጽላለ እመሂ በዝናም ወእመሂ በፀሐይ እስከ ይትፌጸማ እሎን አውራኅ እንዘ ትተግህ ኵላ ሌሊተ ወመዓልተ እንተ ባሕቲታ።

፭ ወሀሎ ፩ ረድእ ዘስሙ ተክለ ማርያም ዘይሔውጻ ወይትለአካ ወያመጽእ ላቲ ሲሳያ ቋርፈ ውእቱኬ ዘተብሀለ በእንቲአሁ ከመ ረከበ ተመነ ዐቢየ ውስተ ማኅደሩ ዘይሰክብ ባቲ ወሶበ ርእዮ ደንገፀ ወፈርሃ ወሖረ እንዘ ይርዕድ ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሶበ ርእየቶ አእመረት ኅሊናሁ ወትቤሎ ምንትኑ ያፈርሃከ ሑር ስክብ ላዕሌሁ ለእመ ኮነ ትእዛዘ እግዚአብሔር ይትበዋህ ላዕሌከ ወኢታመስጥ እምኔሁ ወለእመ ኢኮነ ትእዛዘ እግዚአብሔር አልቦ ዘይነክየከ ወተአዚዞ ሖረ ወነጸፈ ላዕሌሁ ሣዕረ ወሰከበ ቦቱ ወይእተ ጊዜ ኮነ ምትሐተ ወኢተረክበ።

፮ ወእንዘ ሀለወት ህየ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በተግኅሦ ኮኑ የአቅብዋ ፪ እንስሳተ ገዳም በበዘመዶሙ ዘውእቶሙ ደስከኖ ወአጋዘን ፩ዱ ትርአሰ ወ፩ዱ ትርጋፀ ወለለጽባሑ የሐውር ውእቱ ረድእ ወይረክብ አሰረ ትእምርት ኀበ ይሰክቡ በበምስካቢሆሙ።

፯ ወአሐተ ዕለተ በውእቱ መዋዕል እንዘ ትጼሊ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በሰፌሐ እድ መጽአ ኀቤሃ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት ወይቤላ ሰላም ለኪ





ድባብ ሲይዙለት ከታች የተነጠፈና የተዘጋጀ የተሸለመ የወርቅ አልጋ ሲያደርጉለት ስለአየሁ ዘወትር የዮሐንስን ወንጌል አንብቢ አልኩሽ አላት ከዚህ በኋላ ይህንንና ይህን የመሰለውን የእግዚአብሔርን ምሥጢር ከነገራት በኋላ ከሷ ተሠናብቶ ወደባአቱ ተመልሶ ገብቶ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ወደ ወዳጁ እግዚአብሔር ሄደ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋራ ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ።

፬ የዋልድባ መነኰሳት ከሐምሌ ሁለት እስከ ሐምሌ ስምንት ምህላ ማድረግ ልማዳቸው ነበርና ምህላ አድርገው ከአባቶች ተሰናብተው ምግባቸውን ያዘጋጁ ዘንድ ይሄዱ ነበር በዚያን ወራት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከእኅቶቿ ተለይታ ምህላቸውን ሰምታ ከበረከታቸው ትካፈል ዘንድ ዋሻ ወይም መጠለያ ሳታዘጋጅ የምህላ ወራት እስኪፈጸም ድረስ በጸሎትና በስግደት ተግታ ምህላ ከያዙት መነኩሳት አጠገብ ሰነበተች ።

፭ ስሙ ተክለ ማርያም የሚባል ዘወትር የሚጐበኛትና ዘወትር የሚላላካት ረድዕ ነበረ እሱም ከዕለታት በአንድ ቀን የሚተኛበት ቦታ ትልቅ ዘንዶ አይቶ እጅግ ፈርቶ እየተንቀጠቀጠ ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሄደ ገና ሲመጣ አ ይታው ምን ያስፈራሀል ዝምብለህ በላዩ ላይ ተኛ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ከሆነ ሸሽተህ አታመልጥም አሳዶ ይበላሀል የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ካልሆነ ግን ምንም አይነካህም አለችው እሱም እሺ ብሎ ሄዶ ከዘንዶ ላይ ሣር ጐዝጉዞ አንጥፎ ተኛ በዚያን ጊዜም በምታት ዘንዶ የመሰለው ሰይጣን አፍሮ ጠፋ ከዚያ ቦታ አልተገኘም ።

፮ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም በዋልድባ በፍልሰቸ በረሃ ወድቃ ሳለች በየወገናቸው የዱር እንስሳት አንዱ ከእግሯ አንዱ ከራስጌዋ ሆነው ይጠብቋታል እነዚህ የዱር እንስሳት ስማቸው አጋዘን ጐሽ እነዚህን የመሳሰሉት ናቸው ዘወትር ሲነጋ ያ ደቀመዝሙር በሚሄድበት ጊዜ እነዚያ እንስሳት የተኙበት ቦታንና የእግራቸውን ፍለጋ ምልክት ያገኝ ነበር።

፯ ከዕለታት በአንድ ቀን እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እጇን ዘርግታ ስትጸልይ ክብር ይግባውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደሷ መጥቶ ሰላምታ ይገባሻል እንደምን አለሽ አላትና የተዘረጉ እጆቿን በከበሩ እጆቹ ሰብስቦ በዚህ ገዳም ለብቻሽ ትኖሪ ዘንድ እድል ፈንታሽ አይደለም

ወአስተጋብአ እደዊሃ በእደዊሁ ወይቤላ አልብኪ ክፍል ውስተ ዛ ገዳም ከመ ትንበሪ ባሕቲተኪ አላ ትወጽኢ ወይትጋብኡ ኀቤኪ ብዙኃን ሰብእ እምሥራቅ ወእምዕራብ ወይከውኑ ዓርጋበ ንጹሐነ ወይረብሑ መድኃኒተ ነፍሶሙ ወኢትትሐጐል አሐቲሂ ነፍስ እምኔሆሙ አውሥአቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎ እፎ ይከውነኒ ዝንቱ ወእፎ ይትከሀለኒ አድኅኖ ካልአነ ዘኢይክል አድኅኖ ርእስየ አኮኑ አነ ፅቡር ወዓዘቅተ ዓምዓም ጽይእት::

፳፰ አውሥአ እግዚእነ ወይቤላ ፅቡርኒ ኀ ሶበ ተደመረ ምስለ ኃሠር ይጸንዕ ወይቀውም ወይጸውር እክለ ለኪኒ አነ አጸንዓኪ ከማሁ ይእቲሰ ኢተወክፈት ቃሎ ወኢአምነት ነገሮ ወይእተ ጊዜ አምጽአ ኀቤሃ አርጋበ ንጹሐነ ወፅዕድዋነ ወፈነዎሙ ላዕሌሃ ወአገትዋ ኵለንታሃ እምርእሳ እስከ እገሪሃ ቦ እለ ይበውኡ ውስተ ቀሚሳ ወቦ እለ ይፈቅዱ ይስርሩ ወትመይጦሙ በእዴሃ ወታስተጋብኦሙ ውስተ ህፅና ወይቤላ እሉ እሙንቱ ዘአማኅፀንኩኪ ትዕቀቢዮሙ አውሥአቶ ወትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አንሰ ኢይክል ዐቂቦቶሙ ይሰርሩ ወያመስጡ እምኔየ ወሶበ አበየቶ ሖረ እምኀቤሃ ወአርገ ሰማየ ወካዕበ መጽአ በሳኒታ ወይቤላ ከማሁ ይእቲኒ ትቤሎ ከመ ቀዳሚ ወአምጽአ በመሶብ ዘወርቅ ማኅዋተ ወብረሌያተ ፅዕድዋተ ወይቤላ እሉ እሙንቱ ንዋያት ኅሩያን ዘወሀብኩኪ ማኅፀንተ ትዕቀቢዮሙ:ሊተ:እስከ:አኀሥሦሙ እምኀቤኪ ወእንሥኦሙ ኀቤየ::

፳፱ ወትቤሎ ኢይክል ዓቂቦቶሙ ይሰበሩ ብየ ወይቤላ አልቦ ዘይትሐጐል አሐዱሂ እምኔሆሙ እስመ አነ እሄሉ ማዕከሌኪ ወማዕከሌሆሙ ወከመዝ ምዕረ ወካዕበ ይቤላ ሠልሰ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኢትትዌከፍ ቃሎ ወኢተአምን ነገሮ እስመ ፈርሃት ከመ ኢይርከባ ዘረከባ ለሔዋን::

፴ ወእምዝ ወሀባ ኪዳነ ወይቤላ ሰማይ ወምድር የኃልፍ ወቃልየሰ ኢየኃልፍ ኀድጊሰ ዘውሥጥ እለ ሀለዉ ውስተ ህጽንከ ወዘአፍአኒ እለ ሀለዉ እምሥራቅ ወእምዕራብ እለ ይጼውዑ ስመኪ ይድኅኑ ወኢይትሐጐሉ ወለእመኒ ኢአመንኪ ነገርየ ናሁ አነ እፌኑ አንበሳ ወይቀትል አሐደ እምአርድእትኪ ወዘንተ ብሂሎ እግዚእነ ሖረ እምኀቤሃ ወኮነ በከመ ይቤ መጽአ አንበሳ ወአደንገፆሙ ወዘረዎሙ ወቀተለ አሐደ እምኔሆሙ ወእንዘ ይረውፁ ወይትባደሩ ተጋብኡ ኀቤሃ ወወድቁ ላዕሌሃ ወአፅዓቅዋ እስከ አልፀቀት ለመዊት ::





ትወጫለሽ ከምሥራቅና ከምዕራብ ብዙ ሰዎች ወደ አንች ተሰብስበው ይመጣሉ ከኃጢአት የነጹ እንደ ርግቦች የዋሆች ሁነው የነፍሳቸውን መድኃኒት ያገኛሉ ከነሱም መካከል አንዲቷም አትጠፋም አላት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መልሳ ይህ ነገር እንደምን ይሆንልኛል እኔ እራሴን ማዳን ሳልችል ሌላውን ማዳን እንደምን ይሆንልኛል እኔ የሸተተ ፣ረግረግ ጭቃ ነኝና አለችው ::

፳፰ ጌታችንም መልሶ የቦካ ጭቃ ከጭድ ጋራ ፣ተላወሰ ጊዜ ፀንቶ ጉታ /ድብኝት / ሁኖ ቁሞ እህልን ይሸከማል እኔም እንደሱ አፀናሻለሁ አላት እሷ ግን ቃሉን አምና አልተቀበለችም በዚያን ጊዜ ነጫጮች ርግቦችን ወደሷ አመጣና ከእግሯ እስከ ራስዋ ድረስ ከበቧት ወደ ቀሚሷ የሚጠጉ ነበሩ ወደላይም ሊበሩ ፈልገው በእጇ እየሰበሰበች ወደብብቷ ትመልሣቸው ጀመር እሱም ትጠብቂ ዘንድ አደራ የሰጠሁሽ እነዚህ ናቸው አላት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መልሳ እየበረሩ ያመልጡኛል መጠበቅ አይሆንልኝም አለችው ይህን ባለችው ጊዜ ከእሷ ተለይቶ ወደ ሰማይ አረገ ዳግመኛ በማግስቱ መጥቶ እንደዚያው አላት እሷም መልሳ እንደ ቀድሞው አለችው እሱም በወርቅ መሶብ ነጫጭ የእንቁ ብርሌወችንና ዋንጫዎችን አምጥቶ እነዚህን የተመረጡ እቃዎችን ትጠብቂያችው ዘንድ ፈልጌ ካንች እስክረከብ ድረስ ካንች ዘንድ ይሁኑ አደራ ሰጥቼሻለሁ አላት ::

፳፱ እሷም መልሳ ይሠበሩብኛል እኔ መጠበቅ አይሆንልኝም አለችው እሱም መልሶ ከነሱ መካከል የሚሠበር የሚጠፋ የለም አላት እኔም በአንቺና በእነሱ መካከል ሆኜ በረድኤት ፈጽሜ እጠብቃችኋለሁ አላት ሦስተኛም እንደዚሁ ነገራትና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተጴጥሮስ ሔዋንን በውዳሴ ከንቱ ያሳታት እንዳያስታት ፈርታለችና በደስተኝነት ቃሉን ሰምታ ነገሩን አልተቀበለችውም ::

፴ ከዚህ በኋላ ክብር ምስጋና ይግባውና ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም ብሎ ቃልኪዳን ሰጣትና አንቺ ካለሽበት ከገዳምሽ ውስጥ ያሉት ቀርቶ በምሥራቅና በምዕራብ በሰሜንና በደቡብ ያሉ ዝክርሽን ዘክረው ስምሽን የሚጠሩ ይድናሉ እንጂ ምንም አይጠፉም ይህን የነገርኩሽን ቃሌን ካላመንሽ ግን እነሆ አንበሳ ልኬ ከልጆችሽ መካከል አንዱን እገልብሻለሁ አላትና ጌታችን ከሷ ተለይቶ ሄደ ጌታችን እንዳላት አንበሳ መጥቶ ልጆቿን አስደንግጦ በታተናቸው ከነሱም መካከል አንዱን ገደለ እየተሸቀዳደሙ ሩጠው እሷ ካለችበት ደርሰው እግሯ ላይ እየወደቁ አስጨነቋት ::

፲፩ ወእምዝ ገሠጸቶሙ ወትቤሎሙ ምንትኑ ያፈርሃክሙ ቦኑ ይመስለክሙ ዘኢትመውቱ ወይእተ ጊዜ ተንሥአት ወጸለየት ኀበ እግዚአብሔር ኀቡረ ምስሌሆሙ ወሶቤሃ አርመመ አንበሳ ወገብአ ኀበ ኀዘአቱ ወተመይጣ እማንቱኒ ወሖሩ ኀበ ማኅደሪሆን ወተርፈት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ባሕቲታ ወእምዝ ካዕበ መጽአ ኀቤሃ ወይቤላ አኮኑ እቤለኪ ፃዒ እምዝንቱ ገዳም ከመ ታርብሒ ነፍሳተ ወኢይበቍዓኪ አድኅኖ ርእስኪ ባሕቲተኪ ወወሀብኩኪ ኪዳነ ከመ አነ እሄሉ ምስሌኪ ወአዓቅብ ለኪ፡፡

፲፪ በከመ እቤ ለልየ በወንጌል እስመ ኀበ ሀለዉ ፪ ወ፫ ጉቡአን በስምየ፣ ህየ ሀለውኩ አነ ማዕከሌሆሙ ወለእመ ሰአልከኒ ወፈቀድኪ ይሙት በዕለት ዘቦአ እገበር ለኪ ወእፌጽም ፈቃደኪ ወካዕበ አምጽአ ኀቤሃ ከመ ቀዳሚ እሎንተ አርጋበ ፅዕድዋነ ወእሎንተ ማኀዋተ ወቢረሌያተ ወይቤላ ዕቀቢ ሊተ እስመ እማንቱ ንዋያት ኀሩያት እለ አልቦን ነውር ነፍሳተ ደቂቅኪ ወአዋልድኪ እማንቱ ወኢይትሐጐል መኑሂ ዘይበውእ ውስተ ቤትኪ ወዘይትሐጐልሂ ኢይበውእ ውስተ ቤትኪ ወቤትኪሂ ኢይፈልስ እስከ ኀልፈተ ዓለም ወዝንቱ ውእቱ ትእምርተ ኪዳን ዘማዕከሌየ ወማዕከሌኪ

፲፫ ወእምዝ ትቤሎ ይኩን ፈቃድከ ኦ እግዚእየ ወከመዝ ውእቱ ግብሮሙ ለጠቢባን ኢየአምኑ ፍጡነ ሶበ ይነግርዎሙ ነገረ ዘሀለዎ ይኩን በከመ ይቤ ሉቃስ ወንጌላዊ ወይቤሎ መልአክ ኢትፍራህ ዘካርያስ እስመ ናሁ ተሰምዐ ጸሎትከ ወብእሲትከኒ ኤልሳቤጥ ትፀንስ ወትወልድ ለከ ወልደ ወትሰምዮ ስሞ ዮሐንስ ወይከውነከ ትፍሥሕተ ወሐሤተ ዐቢየ ወብዙኃን ይትፌሥሑ በልደቱ እስመ ዐቢየ ይከውን ውእቱ በቅድመ እግዚአብሔር ወይቤሎ ዘካርያስ ለመልአክ በምንት አአምር ከመ ይከውን ዝንቱ ኵሉ አነሂ ልሂቅ ወብእሲትየኒ ኃለፈ መዋዕሊሃ ወተሠጥዎ መልአክ ለዘካርያስ ወይቤሎ አነ ውእቱ ገብርኤል ዘእቀውም ቅድመ እግዚአብሔር ተፈኖኩ ኀቤከ እንግርከ ወእዜኑከ ዘንተ ወናሁ ትከውን በሐመ ወትስዕን ነቢበ እስመ ኢአመንከኒ ነገርየ ዘይከውን በዕድሜሁ ወኮነ ከማሁ፡፡





፲፩ ከዚህ በኋላ በውኑ የማትሞቱ እንደዚህ የምትኖሩ ይመስላችኋል ምን ያስፈራችኋል ብላ ገሠፀቻቸው በዚያን ጊዜ ተነስታ ከነሱ ጋራ በአንድነት ወደ እግዚአብሔር ጸለየች በዚህን ጊዜ አንበሳው ተመልሶ ወደ ነበረበት ሄደ እነዚያም ልጆቿ ተመልሰው ወደ ቤታቸው ገቡ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ብቻዋን ስትጸልይ ዳግመኛ ጌታችን ወደእሷ መጥቶ ከዚህ ገዳም ውጪ ነፍሳትን አድኝ አንችን ብቻ ማዳን አይጠቅምሽም አላልኩሽም ነበር እኔ ካንቺ ጋራ ሁኜ ልጆችሽን እንድጠብቅ አልነገርኩሽም አላት ፡፡

፲፪ በወንጌል ሁለትም ሦስትም ሁነው ከተሠበሰቡበት እኔ በመካከላቸው እገኛለሁ እንዳልኹ ከፈለግሽ ዕለቱን ወዳንቺ መጥቶ ከገዳምሽ ከገባ በኋላ ወደ ዓለም እሄዳለሁ ቢል ዓለም ገብቶ በኃጢአት እንዳይሰነካከል ወዲያውኑ እዚያው ሳለ በሞት ውሰድልኝ ካልሽ ፈጥኜ እወስደዋለሁ ፈቃድሽን እፈጽማለሁ አላት ዳግመኛ እንደቀድሞ እነዚያን ነጫጮች ርግቦችንና እንቀሎዎችን ብርሌዎችን ጠብቂልኝ አላት እነዚህ የተመረጡ ነውር ነቀፋ የሌለባቸው እቃዎች የልጆችሽ ነፍሳት ናቸው ወደ ገዳምሽ የሚገባ ሁሉ አይጠፋም የሚጠፋ ወደ ገዳምሽ አይገባም ቤተ መቅደስሽ እስከ ዓለም ፍጻሜ አይፈርስም በአንቺና በእኔ መካከል የሚደረገው የቃልኪዳኔ ምልክት ይኸ ነው አላት፡፡

፲፫ ከዚህ በኋላ ፈጣሪየ ሆይ የአንተ ፈቃድ ይሁን አለችው አዋቂዎች ሰዎች የሚደረገውን ነገር በነገሯቸው ጊዜ ፈጥነው አይቀበሉም ምን እንደሆነ መጀመሪያ መርምረው ተረድተው ነው እንጂ ወንጌላዊ ሉቃስ መልአኩ ዘካርያስን ጸሎትህ ተሰምቷል ባለቤትህ ኤልሳቤጥ ፀንሳ ወንድ ልጅ ትወልድልሀለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታም ይሆንልሃል ብዙዎችም በመወለዱ ይደሰታሉ እሱም በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ነውና አለው ዘካርያስም መልአኩን እኔ አርጅቻለሁ ባለቤቴም የመውለጃዋ ወራት አልፏል ይህ ይሆን ዘንድ በምን አውቀዋለሁ አለ እነሆ በጊዜው የሚሆን ነገሬን አምነህ አልተቀበልከኝምና ድዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም አለው እንደዚያው ሆነ፡፡

፲፬ ወካዕበ ይቤ በእንተ እግዝእትነ ማርያም እመ ዜነዋ ውእቱ መልአክ ወይቤላ ኢትፍርሂ እ ማርያም እስመ ረከብኪ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር ወናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ወትሰምዩዮ ስሞ ኢየሱስ ውእቱ ዐቢይ ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል ወትቤሎ ማርያም ለመልአክ እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ አውሥአ መልአክ ወይቤላ መንፈሰ እግዚአብሔር ቅዱስ ይመጽእ፡ላዕሌኪ፡ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ ዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል ወናሁ ኤልሳቤጥኒ እንተ እምአዝማድኪ ይእቲኒ ፀንሰት ወረከበት ወልደ በልህቃቲሃ ወበርስዓቲሃ ወናሁ ሳድስ ዝንቱ ወርኀ ለእንተ ይብልዋ መካን እስመ አልቦ ነገር ዘይስአኖ ለእግዚአብሔር።

፲፭ ወትቤሎ ማርያም ለመልአክ ነየ አመተ እግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ ወኮነ ከማሁ ወእምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ቅድመ ተቃወሞቶ እስመ አምሰለቶ ሰይጣነ በከመ ይቤ ጳውሎስ እስመ ለሊሁ ይትሜሰል ሰይጣን ከመ መልአከ ብርሃን ወድኅረኒ ተወክፈቶ ሶበ ርእየት በኀቤሁ ትእምርተ ጽዱቀ ሔዋንሰ ሶበ አምነት ፍጡነ ቃለ ከይሲ ዘአሰፈዋ ከዊነ አምላክ በበሊዓ ዕፅ እንተ ታሌቡ ሠናየ ወእኩየ ኮነት መስተቃርንተ እግዚአብሔር ወወፅአት እምገነት ወኃደረት ውስተ ምድረ ሦክ ወአሜከላ።

፲፮ ወአምጽአት ሞተ ላዕለ ርእሳ እስመ አቅደመ ወይቤሎሙ ኢትብልዑ እምዕፅ ዘማዕከለ ገነት እስመ በዕለተ ትበልዑ እምኔሃ ሞተ ትመውቱ ወኢረከበት ዘፈተወት ወዝንቱ ኵሉ ተጽሐፈ ከመይኩን ለነ ዕቅበተ ወበቍዔተ።

፲፯ ወነገራ ካዕበ ዘከመ ተሐውር ምድረ ገርበይ ወትትሞቃሕ ወትትዓቀብ በእደ ሽንቅላ ወትነብር ፫ ዓመተ ወዘከመ ተሐምም ሕማመ ማቄ ወዘከመ እምድኅሬሁ ትወጽእ ርእዩኬ እ ፍቁራንየ ዘከመ ያየድዖሙ እግዚአብሔር ቅድመ ለቅዱሳን ከመይረክቦሙ ሙቃሔ ወስደት ወኵሉ መከራ ዘዘዚአሁ እምነ ዓላውያን ነገሥት በእንተ ሃይማኖት ርትዕት በከመ ይቤ ወንጌል ናሁ አነ እፌንወክሙ ከመ አባግዕ ማዕከለ ተኵላት ።





፲፬ ዳግመኛም ስለ እመቤታችን ይናገራል ይህ መልአክ በነገራት ጊዜ ማርያም ሆይ ከእግዚአብሔር ጸጋን አግኝተሻልና አትፍሪ እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እሱም ታላቅ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል እመቤታችንም ለመልአኩ መልሳ ወንድ ሳላውቅ ይህ ነገር እንደምን ይሆንልኛል አለችው መልአኩም መልሶ መንፈስ ቅዱስ ወደ አንቺ ይመጣል የልዑል ኃይልም ይጋርድሻል እነሆ ከአንቺ የሚወለድ ልዩ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል እነሆ ኤልሳቤጥ ስንኳን ከአረጀችና ከአፈጀች በኋላ ወንድ ልጅ ፀነሰች እነሆ መካን ሲሏት ከፀነሰች ስድስተኛ ወር ሆኗታል ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና አላት ።

፲፭ እመቤታችንም ለመልአኩ መልሳ እንደአልከኝ ይሁን አለችው እንደዚያው ሆነ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም የሰይጣን ስለመሰላት አስቀድማ አልቀበልም አለችው ቅዱስ ጳውሎስ ሰይጣን እንደ መልአከ እግዚአብሔር እራሱን ሊለውጥ ይችላል እንደአለ ኋላ ግን የእውነት ምልክት ከእሱ ዘንድ ስለአገኘች፡ተቀብላለች፡ሔዋንም፡በእባብ አድሮ የመከራት የሰይጣንን ምክር ዕፀ በልስን በመብላት አምላክ የምትሆን መስሏት ፈጥና ስለተቀበለች የእግዚአብሔር ተቃራኒ ሁና ከገነት ወጥታለች እሾህና አሜካላ ወደምታበቅል የፍዳ ቦታ ምድር ወረደች ።

፲፮ በእራሷ ላይም ሞትን አመጣች ጌታችን አስቀድሞ ከእዚች ዕፅ አትብሉ ከዚች በበላችሁ ቀን ሞትን ትሞታላችሁ ብሏቸዋልና አምላክን እሆናለሁ ብላ የተመኘችውንም አላገኘችም ይህ ሁሉ የተጻፈ እኛ እንድንጠበቅበትና እንድንጠቀምበት ነው።

፲፯ ዳግመኛም ወደ ምድረ ገርበይ ሂዳ ታስራ በሻንቅላዎች እጅ እንድትጠበቅና ሦስት ዓመት እንድትቀመጥ እንደምትታመምና ከዚያ በኋላ እንደምትወጣ ነገራት ወደጆቼ ሆይ ስለ ቀናች ሃይማኖት ከአላውያን ነገሥታት መታሰርና መሰደድ መከራ ሁሉ እንደሚያገኛቸው እግዚአብሔር ለቅዱሳን አስቀድሞ እንደሚነግራቸው ተመልከቱ ወንጌል እነሆ እኔ እንደበጎች በተኩላት መካከል እልካችኋለሁ እንደአለ።

፲፰ ወካዕበ ይቤ እምቅድመ ዝንቱ ኵሉ ይእኅዙክሙ ወይወስዱክ ኀበ አዕዋዳት ወኀበ ነገሥት ወመኳንንት ወዝ ይረክበክሙ በእንተ ስምየ ወጳውሎስኒ ይቤ በመጽሐፈ አበርክሲስ ወባሕቱ አስምዓ ሊተ መንፈስ ቅዱስ በበአህጉር እንዘ ይብል ሕማም ወመዋቅሕት ይፀንሐከ ወጴጥሮስኒ ሐዋርያ ይቤ በመልእክቱ ወባሕቱ ኅዳጠ ይእዜ ሀለወክሙ ትተክዙ በዘይመጽአክሙ መከራ ዘዘዚአሁ ከመ መከራሃ ለሃይማኖትክሙ አኮ ግብተ ዘይረክቦሙ መከራ ለቅዱሳን አላ ያቀድም ነጊሮቶሙ ከመይጽንዑ ጽንዓተ ተስፋ ወልባዌ ወይትወልተው ወልታ ሃይማኖት:ወይልበሱ:ልብሰ:ሐፂን:ዘጽድቅ:ወይሠዓኑ:አሣዕነ:ወንጌል::

፲፱ ወለእምነ ሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከማሁ አቅደመ ወዜነዋ ዘይከውን እም ቅድመ ይኩን ወለኃጥአንሰ ግብተ ይረክቦሙ መከራ በከመ ይቤ ጳውሎስ ተአምሩ ጥዩቀ ከመ ዕለተ እግዚእነ ትመጽእ ከመ ምጽአተ ሠራቂ አመ ይብሉ እለ ይክሕዱ ኪያሁ ከመ ኄውስተ ዳህን ወሰላም እሙንቱ ወህየ ግብተ ይመጽአሙ ተሰርዎ ከመ ፅንስት እንተ ይመጽአ:ማሕምም:ወኢይክሉ:አምሥጦ:ወእምድኅረ:ተፈጸመ:ሥርዓተ:ምህላ:ዘዋልድባ:ተመይጠት:እምነ:ቅድስት: ወቡርክት :ወለተ: ጴጥሮስ:እም: ተግኅሦ: ወተደመረት :ምስለ: እሊአሃ::

፳ ወተስእላሃ እኅተ ክርስቶስ ወግርማና ወይቤላሃ ምንተ ረከብኪ ወምንተ ርኢኪ እምነ ራእያት እምአመ ተፈለጥኪ ወተግኅሥኪ እምኔነ በእሉን አውራኅ ወኃብአቶን ወትቤሎን አንበ ኢረከብኩ ወኢርኢኩ ምንተኒ እስመ ከደነኒ ግላ ኃጢአተ ወሰወረኒ መንጦላዕተ ጌጋይ ወተስእላሃ ዳግመ ለለአሐቲ አሐቲ ወተቈጥዓቶን ወኢነገረቶን እስመ ፈርሃት ውዳሴ ከንቱ ወኢኃደጋ እማንቱኒ ተስእሎቶን ወአምሐላሃ ወአገበራሃ ወእምዝ አልዓለተ ሕሊናሃ ኀበ እግዚአብሔር ወኈንደየት ነዋኃ ሰዓተ በአርምሞ ወተበውሐት እምኔሁ ወሶቤሃ ነገረቶን ዘከመ መጽአ ኀቤሃ:እግዚእነ:ወአኃዘ:እዴሃ:ወዘከመ:ነገራ:ኵሎ:ዘይከውን:እምጥንቱ :እስከ:ተፍጻሜቱ:ወዘከመ:ትቤሎ:አነ:ጽቡር:እፎ:እክል:ዘንተ:ወዘከመ :ወሀባ:ኪዳነ::

፳፩ ወኮና ስምዓ እማንቱ ወነገራነ ለነ ወከማሁ ረድእኒ ተክለ ማርያም ስምዓ ኮነ ላቲ ወኀብረ ቃለ ስምዕ ዘሠለስቲሆሙ ወነአምር ከመ ርትዕት ይእቲ ስምዖሙ ወአኮ ዘጸሐፍነ ሐሰተ ወአመርናክሙ ቦቱ ዜና ዕበያ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አላ አእመርነ ወጠየቅነ ከመ ስምዓ ፪ቱ ወ ፫ቱ ሰብአ እሙን ውእቱ ወንሕነኒ በከመ ሰማዕነ ከማሁ ርኢነ ወነበረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ትሜህሮሙ ለሰብአ ዋልድባ ሃይማኖተ ርትዕተ ወትጌሥጾሙ ከመ ኢይትወከፉ ሃይማኖተ አፍርንጅ ::





፲፰ ዳግመኛም:ከዚህ:ሁሉ:በኋላ:ይይዟችኋል:ከአላውያን ነገሥታትና ከአላውያን መኳንንት: አደባባይ ያቀርቧችኋል ይህ መከራ:ስለ:ስሜ:ያገኛኋል:ቅዱስ:ጳውሎስ:በግብረ:ሐዋርያት:መጽሐፍ: ነገር:ግን:መንፈስ:ቅዱስ:በየአገሩ:ትሰቃያለህ:መታሰር:ያገኝሃል:ብሎ:ለ እኔ:አሰማኝ አለ ቅዱስ ጴጥሮስም በመልክቱ ነገር ግን ዛሬ እንደየ ሃይማኖታችሁ በሚመጣባችሁ የወንጌል ጫማ እንዲያደርጉ የብረትና የጽድቅ ልብስ እንዲለብሱ የሃይማኖት ጋሻ እንዲይዙ የልበኝነትና የተስፋ ፅናት ይፀኑ ዘንድ አስቀድሞ ይነግራቸዋል እንጂ መከራ ቅዱሳንን ድንገት አያገኛቸውም እንደአለ::

፲፱ ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም አስቀድሞ የሚሆነውን ሁሉ ነገራት ኃጥአንን ግን መከራ ድንገት ያገኛቸዋል ቅዱስ ጳውሎስም የጌታችን ቀን እንደሌባ ድንገት ትመጣለች እሱን የሚክዱ ድኅና ነን ሲሉ እንደ ፀነሰች ሴት ድንገት ምጥ እንደሚመጣባት ወድያው ድንገት ጥፋት ይመጣባቸዋል እንደአለ የዋልድባ የምህላ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከፍልሰት ተመልሳ ወደ ጓደኞቿ ተመለሰች::

፳ እኅተ ክርስቶስና ግርማና የሚባሉ እኅቶቿ ከእኛ ተለይተሽ ከፈለስሽ በኋላ በእነዚህ ወራት ምን አየሽ ምንስ አገኘሽ ንገሪን ብለው ጠየቋት የኃጢአቴ ጥላና የበደሌ መጋረጃ ሸፍኖኛልና ምንም አላየሁም አለቻቸው ሌላ ጊዜ ለየራሳቸው ጠየቋት ውዳሴ ከንቱን ስለፈራች ምንም አላየሁም አልአልኳችሁም ብላ ተቆጣቻቸው እነሱም ሳይታክቱ በየጊዜው የአየሽውን ንገሪን ካልአየሽ አልአየሁም ብለሽ ማይልን ብለው ስለ አስገደዷት እጇን ወደሰማይ ዘርግታ ሀሳቧን ወደ እግዚአብሔር አቅርባ ጥቂት ቆየች ከእግዚአብሔር ፈቃድ አግኝታ ጌታችን ወደ እሷ እንደመጣ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሚሆነውን እሷም:እኔ:ጭቃ:ነኝ:እንደአለችው:ቃል:ኪዳንንም:እንደሰጣት:ነገረቻቸው:

፳፩ እነሱም ለኛ ምስክር ሆኑን እንደዚሁ አገልጋይዋ ተክለ ማርያም ምስክር ሆነላት የሦስታቸውም ምስክርነት አንድ ሆነ ይችም ምስክርነታቸው እውነት እንደሆነች አውቀናል እውነት እንጂ ሐሰት አይደለም የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የገድሏን ዜና ነገርናችሁ የሦስትና የሁለት ሰዎች ምስ ክርነት እውነት እንደሆነ ተረድተን ጻፍንላችሁ እኛም እንደሰማነው እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለዋልድባ መናንያን እንደምታስተምራቸው የካቶሊክ ሃይማኖት እንዳይከተሉ እንደምትገስፃቸው አይተናል::

## ምዕራፍ ፰

፩ ወሶበ ሰምዓ ንጉሥ ሱስንዮስ ዜናሃ ፈነወ ጽሚተ ሰብአ ዓይን እለ ያስተኃይፅዋ ወነገርዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ መጽኡ ኀቤሃ ሰብአ ዓይን እለ ተፈነዉ እምኀበ ንጉሥ ተግኅሠት ምስለ እሊአሃ እምውእቱ መካን ዘሀለወት ቦቱ ቅድመ ወኃደረት ውስተ ፈለግ ይቡስ እስመ መዋዕለ ሐጋይ ውእቱ ወሀለዉ ምስሌሃ መጽሐፈ ሃይማኖተ አበው ወካልአንሂ መጻሕፍት ወዘንመ በውእቱ ዕለት ዐቢይ ዝናም እስከ መልአ ግብተ ፈልግ ወውሕዘ ወኃለፈ ላዕለ ሰብእ:ወላዕለ:መጻሕፍት:ወኢነከዮ:ምንትኒ:ወኢተደምሰሰ:፩:ፊደል: እምኔሁ:ወድኅነ:በኃይለ:ረድኤታ:ለእምነ:ቅድስት:ወቡርክት:ወለተ: ጴጥሮስ:ወኢተወለጠ:ግሙራ:

፪ ወእምድኅሬሁ ተመይጠት ወአተወት ውስተ ቤታ ዘቀዳሚ ስምዑ ካዕበ ንነግረክሙ ስነ ጊሩታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወዘከመ ገብረ ላቲ እግዚአብሔር ተአምራተ ወመንክራተ ወሶበ ተፈጥረ በውስተ ከርሣ ዕፄ ዘሀለወ ውስቴትነ አስተዳለዋ ላቲ ፈውሰ ከመ ትስተይ ወታውፅአ ለውእቱ ዕፄ ወእንዘ ያሜንያ ላቲ መጽአ ፩ዱ ብእሲ ዘተመንደበ በውእቱ ዕፄ ወነበረ ጉንዱየ መዋዕለ እስመ ኃጥአ ፈውሰ ዘይስቲ ወሰአለ ከመ የሀብዎ ወነገሮን ዘከመ ተመንደበ በውእቱ ዕፄ ወሰሚዓ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተራኅርኃት ላዕሌሁ ወኃደገት ሰትየ ወወሀበቶ ወሰትየ ወተፈወሰ ይእቲኒ ቅድሜሁ ተፈወሰት እንበለ ትስተይ ወኢያስተርአያ ውእቱ ዕፄ እምድኅሬሁ ርኢክሙኑ ዘከመዝ አፍቅሮተ ቢጽ ወመጥዎተ ቤዛ ነፍስ በከመ ይቤ ወንጌል ብፁዕ ዘይሜጡ ነፍሶ ቤዛ ቢጹ ዐቢይ ምጽዋት ውእቱ ወየዐቢ እምኩሉ ምጽዋት::

፫ ወእምድኅሬሁ ፈነወ እግዚአብሔር መቅሠፈተ በዋልድባ:አርዌ:ዘስሙ:ሸልጐልጐት:ወይመጽእ:ሌሊተ:ኀበ:ይሰክቡ ·:ይሰቀውር:ርእሶሙ:ወይበልዕ:ናላሆሙ:ወበዝንቱ:ግርማ:ኮነ:ድንጋጼ ::ወሁከት:ዐቢይ:ላዕለ:ኵሎን:አኃት:ወይቤላሃ:ለእምነ:ቅድስት:ወቡ ርክት:ወለተጴጥሮስ ኢይትከሃለነ ንንበር ዝየ እም ግርማ ውእቱ አርዌ ዘአልቦቱ ድምፅ ወኢይከልአ ማዕፆ ለበዊእ ወይበውእ እንተ ጠፈረ ቤት ከማሁሰ አንበሳኒ ወተመንኒ ኢያፈርሁነ ንፃእ ወንሑር ኀበ ካልእ መካን ወለእመ ዓበይኪ አንተ ንዘረው ንሕነ ወነኃድገኪ ባሕቲትኪ ::





## ምዕራፍ ፰

፩ ንጉሥ ሱስንዮስም የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ዝና በሰማ ጊዜ ለማስያዝ ሰላዮች ላከ ከንጉሥ ዘንድ እሷን ለመያዝ ሰላዮች እንደመጡ ነገሯትና ቀድሞ ከነበረችበት ሄዳ ወራቱ በጋ ነበርና ከደረቅ ወንዝ ውስጥ ተቀምጣ ሣለች ከእሷ ጋር ሃይማኖተ አበውና ሌሎች መጻሕፍት ነበሩ በዚያች ዕለት ወንዙ ሞልቶ በተኙ ሰዎችና በመጻሕፍት ላይ እስኪፈስ ድረስ ታላቅ ዝናም ዘነመ መጻሕፍቱ ውሀ ውስጥ/ሳሉ ምንም ሳይሆኑ አንድም ቀለም ሳይደመሰስ ምንም ሳይበሰብሱ በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የጸሎት ኃይል ዳኑ::

፪ ከዚህ በኋላ ወደቀደመ ቦታ ተመለሰች ዳግመኛም እግዚአብሔር ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ድንቅ ታአምራት እንደአደረገ ዜናዋን ልንገራችሁ ስሙ እኛ ንም እንደሚያስቸግረን ያለ ኮሶ ታያትና የኮሶ መድኃኒት ተዘጋጅቶላት ሳለ አንድ በየጊዜው ኮሶ ያስቸገረ ኮሶ የሚያጠ ጣው ያጣ አንድ ሰው ነበር ድንገት መጥቶ ኮሶ እንደ አስቸገረው ነገራቸው እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሰምታ ራርታ ለራሷ መጠጣት ትታ ለእሱ ሰጠችውና ጠጣ እሷ ግን ሳትጠጣ አስቀድማ ዳነች ከዚያ በኋላ ኮሶ አልታያትም እንደዚህ ያለውን ወንድም መውደድና እራስን ለሰው አሳልፎ መስጠት አያችውን እራስን ለወንድም አሳልፎ የሚሰጥ ንዑድ ክቡር ነው ከምጽዋት ሁሉ የሚበልጥ ምጽዋት ነው ብሎ ወንጌል እንደተናገረ::

፫ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ስሙ ሸልጉልጉት የሚባል ሌሊት ከተኙበት እየመጣ ጭንቅላትን እየበሳ የሰውን አንጎል የሚበላ መቅሠፍት በዋልድባ ገዳም ላከ ከዚህ ከሚያስፈራ አውሬ የተነሳ በእኅቶች መካከል ታላቅ ሁከትና ድንጋጤ ሆነ እነሱም ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እዚህ እንኖር ዘንድ ከዚህ ድምፅ ከሌለውና በር ከማይከለክለው አውሬ የተነሣ መቀመጥ አልተቻለንም ተኝተን ሳለን እሱ በጣሪያ ይገባልና እንደሱ አንበሳም ሆነ ዘንዶ አላስፈራንም ወጥተን ወደሌላ ቦታ እንሂድ አይሆንም ካልሽ እኛ አንቺን ትተን እንበተናለን አሏት::

፬ ወሶበ ይቤላሃ ከመዝ ወጽአት እምህየ ወሖረት ምድረ ጸለምት ወነበረት በህየኒ እንዘ ትሜህሮሙ ለሰብእ ሃይማኖተ ርትዕተ ወትጌሥጾሙ ከመ ኢይትወከፉ ሃይማኖተ አፍርንጅ ርኩስተ ወእምዝ ሶበ ሰምዓ ንጉሥ ሱስንዮስ ከመ ሀለወት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በሀገረ ጸለምት ወከመ ትሜህሮሙ:ሃይማኖተ:ተምዓ:ጥቀ:ወተቈጥዓ:ወጥኅረ:ከመ:ሕንበሳ :ወይቤ:ለእመኃደግዋ:ኢተኃድገኒ:ወለእመመሐርክዋ:ኢትምሕረኒ: እምይእዜሰ:እንሰ እመክር ዘእገብር ወጸውዖ ለ፩ እምሐራሁ ዘስሙ አምባራስ ፊላታዎስ:ዘተሰይመ ላዕለ:ዛቲ:ሀገር ወይቤሎ ሑር አምጽእ ሊተ ፍጡነ ወለተ:ጴጥሮስሃ:ወሖረ በከመ ይቤሎ ወበጽሐ ኀቤሃ ወይቤላ አዘዘኒ ኀቤኪ ንጉሥ ወይቤለኪ ንዒ:ፍጡነ ወኢትበሊ ጌሠመ::

፭ ወትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ነየ አነ ውስተ እዴከ ወግበር በከመ አዘዘከ ንጉሥ ላዕሌየ አንሰ ድልወት ለዝንቱ ወጥብዕት ለመዊት ወኢይፈርህ ምንተኒ ወሶቤሃ ተንሥአት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እምህየ ወ ሖረት ምስሌሁ ወሀለዋ ምስሌሃ እኅተ ክርስቶስ ወክርስቶስ ስና ማርያማዊት ወእስክንድራዊት ወእምዝ በጽሐት ወቦአት ኀበ ታዕካ ንጉሥ በወርኃ ግንቦት ወአንበርዋ ኀበ ቤተ ደጅ አዝማች ብዕለ ክርስቶስ ወአኃዙ ይጌጥዋ በብዙኅ ጊጠት ከመ ያውፅእዋ እምሃይማኖተ ዲዮስቆሮስ ርትዕት ወያብእዋ ውስተ ሃይማኖተ ልዮን ርኩስት

፮ ወመጽኡ ኀቤሃ ፫ መምሕራነ ሐሰት ወዐበይተ አፍርንጅ ወተዋሥእዋ በሃይማኖቶሙ ርኩስት እንተ ትብል ፪ኤ ባሕርይ ውእቱ ክርስቶስ እምድኅረ ተዋሕዶ ዘኢይትነገር ወተዋቀሰት ምስሌሆሙ ወሞአቶሙ ወአስተኃፈረቶሙ ወለለጽባሑ ይመጽኡ ኀቤሃ ካልአን አፍርንጅ ወያነብቡ ወይተረጕሙ:ላቲ:መጽሐፎሙ ርኩስተ:ወእምነሰ:ቅድስት:ወቡርክት:ወለተጴጥሮስ:ኢትሰምዖነገሮ ሙ:ወኢትትዌከፍ:ሃይማኖቶሙ አላ ትስሕቅ ወትሳለቅ ላዕሌሆሙ::

፯ በከመ ይቤ ወንጌል እንትሙሰኬ ኢትሰመዩ ለክሙ መምህረ በዲበ ምድር እስመ ፩ዱ ውእቱ መምህርክሙ ክርስቶስ ወዮሐንስኒ ሐዋርያ ይቤ በመልእክቱ አኃዊነ ለኵሉ መንፈስ ኢትእመኑ አላ አመክርዋ ለመንፈስ ለእመ እምኀበ እግዚአብሐር እስመ ብዙኃን ሐሳውያን ነቢያት መጽኡ ውስተ ዓለም እለ ኢየአምኑ በኢየሱስ





፬ ይህን በአሏት ጊዜ ወጥታ ወደ ጸለምት አገር ሄደችና በዚያ ለአሉት ሰዎች የካቶሊክ እምነት እንዳይከተሉ በቀናች በተዋህዶ ሃይማኖት እንዲጸኑ ታስተመራቸውና ትገሥፃቸው ጀመር ከዚህ በኋላ ንጉሥ ሱስንዮስ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በዚያ ተቀምጣ ሃይማኖትን እንደምታስተምር በሰማ ጊዜ ተቆጥቶ እንደ አንበሳ ደንፍቶ ብታገሣት አትተወኝም ብምራትስ አትምረኝም ከእንግዲህ ወዲህስ የማደርገውን እመክራለሁ አለና ከወታደሮቹ መካከል ስሙ አምባራስ ፊላታዎስ የሚባለው በዚያች አገር ላይ የተሾመውን ጠርቶ ሄደህ በፍጥነት ወለተ ጴጥሮስን አምጣልኝ አለው እሱም እንደ አለው ሄዶ እሷ ከአለችበት ደርሶ ንጉሡ ዛሬ ነገ ሳትይ ፈጥነሽ ነይ በላት ብሎ አዞኛልና እንሂድ አላት::

፭ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም እነሆ እኔ በእጅህ ነው ያለሁት ንጉሡ በኔ ላይ አድርግ ያለውን ማድረግ ትችላለህ ለዚህ መከራ የተዘጋጀሁና ለሞት የጨከንኩ የማልፈራ ነኝ አለችውና ያን ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከዚያ ተነሥታ ከእሱ ጋር ሄደች ከእሷ ጋር እኅተ ክርስቶስ ክርስቶስስና ማርያማዊት እስክንድራዊት ነበሩ በግንቦት ወር ከንጉሡ አዳራሽ ደረሰችና ብእለ ክርስቶስ ከሚባል ደጅ አዝማች ቤት አስቀመጧትና ከቀናች ከነዲዮስቆሮስ ሃይማኖት ያወጧትና ወደ ልዮን ክህደት ያስገቧት ዘንድ ይመክሯት ጀመር::

፮ ሦስት የሐሰት መምህራን የካቶሊክ መሪዎች ወደ እሷ መጥተው ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ ነው ብለው በረከሰች ሃይማኖታው ተዋህዶን ሳይናገሩ ይከራከሯት ጀመር እሷም መልስ እየሰጠቻቸው ታሸንፋቸውና ታሳፍራቸው ነበር በየቀኑ የካቶሊክ መምህራን ወደእሷ እየመጡ የረከሰች መጽሐፋቸውን ያነቡላት ነበር እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ነገራቸውን አትሰማም ሃይማኖታቸውንም አትቀበልም ትስቅና ትሳለቅባቸው ነበር እንጂ::

፯ ወንጌል እናንተ በዚህ መመህር ነኝ አትበሉ መምህራችሁ ክርስቶስ ነው እንደአለ ሐዋርያ ዮሐንስም በመልእክቱ ወንድሞቼ ሆይ መንፈስን ሁሉ አትእመኑ ከእግዚአብሔር መሆኑንና አለመሆኑን መጀመሪያ መርምሩ እንጂ የሰውን ሥጋ ተዋህዶ ወደዚህ ዓለም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመጣ የማያምኑ

ክርስቶስ ከመ መጽአ በሥጋ ሰብእ ወበዝንቱ ተአምርዎ ለመንፈሰ እግዚአብሔር ወኵሉ መንፈስ እንተ ተአምን በኢየሱስ ክርስቶስ ከመ መጽአ በሥጋ ሰብእ እምነ እግዚአብሔር ወኵሉ መንፈስ እንተ ኢተአምን በኢየሱስ ክርስቶስ ከመ መጽአ በሥጋ ኢኮነት እምእግዚአብሔር አላ ባሕቱ እምሐሳዊ መሲሕ ዘሰማዕክሙ ከመ ይመጽእ ፡፡

፰ ወካዕበ ይቤ ወኵሉ ዘይናፍቅ ወኢይነብር በትምህርቱ ለክርስቶስ ኢሀሎ ምስለ እግዚአብሔር ወዘሰ ይነብር በትምህርቱ ለክርስቶስ በአብ ወበወልድ ሀሎ ወዘኒ ይመጽእ ኀቤክሙ ወዘንተ ትምህርተ ኢያመጽእ ኢታብእዎ ቤተክሙ ወበሀዊ ጥቀ ኢትበልዎ እስመ ዘይቤሎ በሀ ይሳተፎ በምግባሩ እኩይ ወእንበይነዝ ይእቲሂ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አስተሐቀረቶሙ ወመነነቶሙ ለእሉ፡መምህራነ፡ሐሰት ዘአፍርንጅ፡፡

፱ ወሐተተ ንጉሥ እንዘ ይብል ምንተ ትብል ወምንተ ታወሥእ አውሥእዎ ወይቤልዎ እሉ አፍርንጅ ይእቲሰ ኢትሰምዕ ወኢትትዌከፍ ቃለነ አላ ትጸርፍ ላዕሌነ ቦኑ ይበውእ ማይ ውስተ ልበ ዕብን ወበእንተዝ ተምዓ ንጉሥ ወፈቀደ ይቅትላ ወከልእዎ መማክርቲሁ እንዘ ይብሉ ከመዝሰ ኢትግበር ወለእመ ቀተልካ በዝየ ኵሉ ዓለም ይተሉ ድኅሬሃ ወየኃብር ምስሌሃ መዊተ ወለእመ ኀልቀ ሰብእ ላዕለ መኑ ትነግሥ አላ አዝዝ ትንበር ሞቅሕታ ወሶቤሃ አዘዘ ንጉሥ ይሰድዋ ምድረ ዠበይ ወየሀብዋ ለሻንቅላ ትንበር ሞቅሕታ፡፡

፲ ወእምዝ ቦአ መልክዓ ክርስቶስ ውስተ ጽርሐ ንጉሥ ወቆመ ቅድሜሁ ወሰአሎ እንዘ ይብል እስእለከ ኦ እግዚእየ ንጉሥ እመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ ሀበንያ ሊተ ለወለተ ጴጥሮስ እስከ የኃልፍ ወርኃ ክረምት ወአነ እምዕዳ ወእመክራ መምህረ አፍርንጅሂ አፎንሱ ያንብብ ላቲ መጽሐፎ ወያስምዓ ኵሎ ዕለተ ወለእመ ዓበየት ተመይጠ ይእተ ጊዜ ንፌንዋ ወይቤ ንጉሥ አሆ ለቃልከ ወእምዝ ተመጠዋ መልክዓ ክርስቶስ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወወሰዳ አዚዞ ወአንበራ ውስተቤቱ ወወሀባ ሲሳያ ወሀለዋ ምስሌሃ እኅተ ክርስቶስ ወወለተ ክርስቶስ ወኮና በኵሉ መዋዕለ ሕይወቶን ለወለተ ጴጥሮስ ወእኅተ ክርስቶስ ከመ እግዝእትነ ማርያም ወከመሰሎሜ፡፡





ብዙ ሐሳውያን ነቢያት ወደ ዓለም መጥተዋልና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ሥጋ መዋሀዱን የምታምን መንፈስ ከእግዚአብሔር የተገኘች ናት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ መዋሀዱን የማታምን መንፈስ ግን ከእግዚአብሔር አይደለችም ይመጣ ዘንድ ከሰማችሁት ከሐሰዊ መሲሕ ናት እንጂ የእግዚአብሔር መንፈስ መሆኑን በዚህ ታውቁታላችሁ እንደአለ፡፡

፰ ዳግመኛም የክርስቶስን ትምህርት የሚጠራጠር ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር አይደለም በክርስቶስ ትምህርትም የሚያምን እሱ ከአብና ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ነውና ወደእናንተ መጥቶ ትክክለኛውን ይህን ትምህርት የማይናገር እሱን ሰላምም አትበሉት ከቤታችሁ አታስገቡት ሰላምም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ተባባሪ ይሆናልና ስለዚህ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እነዚህን የሐሰት መምህራን የሚሆኑ የካቶሊክ እምነት የሚከተሉትን አቃለለቻቸው ፡፡

፱ ንጉሡም ስለ እሷ ምን አለች ምንስ ተናገረች እያለ ጠየቀ እነዚያ ካቶሊካውያንም እሷስ ምንም ቃላችንን አትቀበልም ትሰድበናለች እንጂ ውሀ በድንጊያ ልብ ውስጥ ይገባልን ብለው ነገሩት ንጉሡም ተቆጥቶ ያስገድላት ዘንድ አዘዘ አማካሪዎቹም እሷን ከገደልካት ሰው ሁሉ እሷን ተከትሎ ይሞታል ሁሉ ከሞተ በማን ላይ ትነግሣለህ ባይሆን እንድትታሰር እዘዝ እንጂ ብለው መከሩት በዚህን ጊዜ ወደ ዠበይ ምድር ወስደው ለሻንቅላ ይሰጧትና እዚያ ታስራ ትቀመጥ ዘንድ አዘዘ ፡፡

፲ ከዚህ በኋላ መልክዓ ክርስቶስ ከንጉሡ አዳራሽ ገብቶ ከፊቱ ቆሞ በአንተ ፊት ባለሟልነትን ካገኘሁ የክረምት ወራት እስኪያልፍ ድረስ ወለተ ጴጥሮስን ስጠኝ እኔ እመክራታለሁ የካቶሊክ መምህር አፎንሱም በየቀኑ መጽሐፍ እያነበበላት ያስተምራት አይሆንም እልመለስም ካለች በዚያን ጊዜ እንልካታለን አለ ንጉሡም እንደ ቃልህ ይሁን እሺ አለውና መልክዓ ክርስቶስ እዞ ወደቤቱ አስወሰዳትና ከቤቱ አስቀምጦ የምትመገበውን ምግብ ሰጣት እኅተ ክርስቶስና ወለተ ክርስቶስም ከእሷ ጋር ነበሩ ወለተ ጴጥሮስና እኅተ ክርስቶስ የሕይወታቸውን ዘመን እንደእመቤታችንና እንደ ሰሎሜ አንድ ላይ ሁነው ኑሮ ያሳለፉት፡፡

፲፩ ወየሐውር ኀቤሃ አፎንሱ ለለቅዳሚት ሰንበት ነግሀ እንዘ ኢትመስሕ ከመ ያጹማ በጥበብ ከማሁ ወያነብብ ላቲ መጽሐፎ ወይገብእ ተኃፊሮ እስመ አስተኃቀረቶ ወመነነቶ ወኢሰምዓት ትምህርቶ ወንጉሥኒ ይሴአል ኵሎ ጊዜ እንዘ ይብል ተመይጠትኑ ወለተ ጴጥሮስ ወተወክፈትኑ ሃይማኖትነ ወይቤልዎ አልባ ወእምድረዝ ሶበ ኃለፈ ወርኃ ክረምት ወሠረቀ ወርኃ ኅዳር ወሶበ አልፀቀ ጊዜ ዘይቤላ እግዚእነ ትወርዲ ዝበይ ጸውዖ ንጉሥ ለ፩ዱ እምነ ሐራ ወይቤሎ ሑር ወስዳ ለወለተ ጴጥሮስ ብሔረ ዝበይ እንተ ባሕቲታ ወኢታትሉ ላቲ ሰብአ ኢእደ ወኢ አንስተ፡፡

፲፪ ወተአዚዞ እምኀበ ንጉሥ ሖረ ውእቱ ሐራ ወበጽሐ ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወይቤላ አዘዘኒ ንጉሥ ከመእሰድ, ኪያኪ ብሔረ ዝበይ አውሥአቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎ ነየ ኣነ ውስተ እዴከ ግበር በከመ አዘዘከ ንጉሥ ወይእተ ጊዜ ፈርሃት ወለተ ክርስቶስ ወጐየት እንዘ ትጸውር ቀሡተ ወትለብስ ልብሰ አመት ከመ ዘትቀድሕ ማየ ወእኅተ ክርስቶስኒ ተርፈት በውእቱ መካን ወእምነስ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሖረት ባሕቲታ ከመ ሖረ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ባሕቲቱ መካነ ቀራንዮ እንዘ ይጸውር መስቀለ ይእቲኒ ተመሰለት ኪያሁ በከመ ይቤ ጳውሎስ ንትመሰል በአርአያ ዚአሁ ከመ ንባእ እምክብር ውስተ ክብር፡፡

፲፫ ወውእቱሰ ሐራዊ ግዙፈ ክሳድ ወእከየ ግዕዝ ውእቱ ወአልቦ ምሕረት ወኢፍርሃተ እግዚአብሔር ወነሥአ ወአፅዓና ዲበ በቅል እኩይ ወኢይእኅዝ ላቲ ልጓመ አላ ይነድኦ እንተ ድኅር ወይደጕጸ በበትር መንገለ ምኵሳሑ ከመ ይትመዓዕ ወያወድቃ ወትሙት ወኢየኃዝን ላቲ ግሙራ እስመ አጽንአ ሰይጣን ወእንዘ ይገብር ከመዝ አብጽሓ ኀበ ፍኖት መብዕስ ወጕጸጕጽ ወዘበጠ ለውእቱ በቅል ዐቢየ ዝብጠተ ወወድቀ ወወረደ መትሕተ ጸድፍ ፡፡





፲፩ ቅዳሜ ጥዋት አፎንሱ በጥበብ ያጾማት ዘንድ ሳትበላ እየሄደ መጽሐፍ ያነብላትና እያፈረ እየተዋረደ ይመለስ ነበር ንቃው አቃላው ትምህርቱን አትቀበለውም ነበር ንጉሡም በየጊዜው ወለተ ጴጥሮስ ተመልሳ የኛን ሃይማኖት ተቀብላለችን እያለ ይጠይቅ ነበር አልተቀበለችም እያሉ ይመልሱለታል የክረምት ወራት አልፎ ኅዳር በገባ ጊዜ ጌታችን ወደ ዝበይ ትወርጃለሽ ያላት ጊዜ ሲደርስ ንጉሡ ከወታደሮቹ አንዱን ጠርቶ ወለተ ጴጥሮስን ወደ ዝበይ አገር ብቻዋን ውሰዳት ወንድም ሴትም ቢሆን እዳታአስከት ልላት አለው፡፡

፲፪ ያም ወታደር ከንጉሡ ታዞ ወደ እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ደርሶ ንጉሡ አንቺን ወደዝበይ አገር እወስድሽ ዘንድ አዞኛል አላት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም እነሆ እኔ አለሁ ንጉሥ እንደ አዘዘ አድርግ አለችው በዚህን ጊዜ ወለተ ክርስቶስ ፈርታ የገረድ ልብስ ለብሳ ውሀ የምትቀዳ ሰራተኛ መስላ እንስራ ተሸክማ ሸሸች እኅተ ክርስቶስም በዚያች ቦታ ቀረች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻውን መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ እንደ ሄደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ብቻዋን ሄደች ቅዱስ ጳውሎስ ከክብር ወደ ክብር እንድንገባ እሱን በመከራ እንምሰል እንደአለ እሱን በመከራ መሰለችው፡፡

፲፫ ያም ወታደር አንገተ ደንዳና መጥፎ ጸባይ ያለው ርህራሄና እግዚአብሔርን መፍራት የሌለው ነበርና ወስዶ በክፉ በቅሎ ላይ ጫናት ልጓምንም አይዝላትም ከኋላ በቅሎውን በበትሩ እየመታና እየወጋው ወድቃ እንድትሞት ይፈልግ ነበር ፈጽሞ አያዝንላትም ሰይጣን ልቦናውን አስጨክኖታልና እንደዚህ እያደረገ ከጕጸጕጽ ጉዳና አደረሳትና ድንገት ያንን በቅሎ በኀይል መታው በቅሎው ወደቀና ከገደል በታች አረፈ፡፡

## ምዕራፍ ፱ ዘሐሙስ

፩ ወለእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሶቤሃ ተመጠዋ መልአክ ወአንበራ ውስተ ምድር ሠናይ መልዕልተ ሣዕር ልምሉም ወተንሥአት ሕያውታ እንበለ ሙስና በከመ ይቤ መጽሐፍ ፫ተ አስማተ ንሢእየ እትመረጐዝ እመኒ ወደቁ እትነሣእ ወዳዊትኒ ይቤ ብዙኀ ሕማሞሙ ለጻድቃን ወእምኵሉ ያድኅኖሙ እግዚአብሔር እግዚአብሔር የዓቅብ ኵሎ አዕፅምቲሆሙ ወኢይትቀጠቀጥ ፩ዱ እምውስቴቶሙ ወካዕበ ይቤ እስመ ለመላእክቲሁ ይኤዝዞሙ በእንቲአከ ከመ ይዕቀቡከ በኵሉ ፍናዊከ ወበእደዊሆሙ ያነሥኡከ ከመ ኢትትዓቀፍ በዕብን እግርከ::

፪ ወጳውሎስኒ ይብል ውብነ መዝገብ ውስተ ንዋየ ልሕኵት ከመ ይኩን ዕበየ ኃይል ዘእምኀበ እግዚአብሔር ወአኮ ዘእምኀቤነ እንዘ በኵሉ ነሐምም ወኢንትመነደብ ንትሜነንሂ ወኢነኀሥር ንሰደድሂ ወኢንትገደፍ ንዌዓርሂ ወኢንትሐጐል ወዘልፈ ንጸውር ሞቶ ለክርስቶስ በሥጋነ ከመ ይትዓወቅ ሕይወቱ ለክርቶስ በላዕለ ዝንቱ ነፍስትነ መዋቲ ወለእምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኮነ ላቲ ከማሁ ወእምዝ ካዕበ አፅዓና ውእቱ ሐራዊ ዲበ ውእቱ በቅል ወአብጽሓ ሀገረ ዢበይ ወወሀበ ኪያሃ ለሻንቅላ ወነገሮ ኵሎ ትእዛዘ ንጉሥ ወይቤሎ ዕቀብ እስከ አመ ይኤዝዝ ንጉሥ እመኒ ለሞት ወእመኒ ለሕይወት ::

፫ ወሀለወት ይእቲ ባሕቲታ ወሶበ ሰምዓት እማ ክርስቶስ ዕበያ ከመ ሖረት ባሕቲታ ኀዘነት ፈድፋደ ወድኅረ ፈነወት ላቲ ኢላርያሃ አመታ ከመ ትንበር ምስሌሃ ወትትለአካ ወተመጠዋ ውእቱ ሻንቅላ ወገብረ በከመ አዘዘ ንጉሥ ወወደያ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ወነበረት ፫ ዕለተ እንዘ ኢትበልዕ ወኢትሰቲ እስመ አረሚ ወርኵስ ውእቱ ሻንቅላ ወአልቦቱ ኀብረት ምስሌሃ እመሂ በምግባር ወእመሂ በሃይማኖት ወኢትሰምዕ ቃሎ ሶበ ይትናገር ምስሌሃ እመሂ ሠናየ ወእመሂ እኩየ ሚመጠን ግርምት ዛቲ ዕለት ወዕፅብት ዛቲ ሰዓት እንተ ባቲ ኮነ መከራ ወስደት ላእለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወፈድፋደ የአኪ ወየዓፅብ እምኵሉ መከራ ወስደት ዘረከቦሙ ለክርስቲያን በእሉን ዓመታት::





## ምዕራፍ ፱ የሐሙስ

፩ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ግን ያን ጊዜ መልአክ ተቀበላትና ወስዶ ከለመለመ ሣር ላይ አስቀመጣት ምንም ሣትሆን ፈጥና ተነሣች መጽሐፍ ሦስቱን ስሞች ይዤ እመረኮዛለሁ ብወድቅም እነሣለሁ እንደአለ ዳዊትም የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው እግዚአብሔር ከሁሉ ያድናቸዋል አጥንቶቻቸውንም ይጠብቃል ከውስጣቸው አንዱም አይጐዳም ዳግመኛም ስለአንተ መላእክትን ያዝልሃል በመንገድ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ በእጃቸውም ያነሱ ዘንድ እንደ አለ::

፪ ጳውሎስም ከእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ኃይል እንዲሆነን በማሠሮ እቃ ሳጥን አለ በሁሉ ዘንድ ስንታመም አንቸገርም ስንናቅ አንዋረድም ስንሰደድ አንጣልም እንጨነቃለን እንጅ አንጠፋም ዘወትር በሥጋችን የክርስቶስ መከራ ሞቱን እንሸከማለን የክርስቶስ መከራ ሟች በሆነ ሰውነታችን ይገለጥ ዘንድ እንደ አለ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮሽ እንደዚሁ ለመከራ ታድላለች ዳግመኛ ያ ወታደር በበቅሎ ላይ ጭኗት ወደ ዢበይ ሀገር አደረሳት እና ለሻንቅላ አስረከባት ንጉሡ ለሞትም ቢሆን ለሕይወት እስከ አዘዘ ድረስ ጠብቃት አለውና የንጉሡን ትእዛዝ ነገረው::

፫ እሷም ብቻዋን እዚያው ተቀመጠች እናቷ ክርስቶስ እበያ ብቻዋን እንደሄደች በሰማች ጊዜ በጣም አዝና አገልጋይዋ ኢላርያን ከሷ ጋር ሆና ታገለግላት ዘንድ ላከችላት ያም ሻንቅላ ተቀበላትና ንጉሡ እንዳዘዘው እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ከእስር ቤት አስገባት ሦስት ቀን ሳትበላ ሳትጠጣ ሰነበተች ያም ሻንቅላ በሃይማኖትም ሆነ በምግባር ከሷ ጋራ ሕብረት የሌለው የረከሰ ጨካኝ አረመኔ ነውና በሚናገራት ጊዜ ቋንቋቸው ስለተለያየ ክፉም ሆነ ደጉን አታውቅም ነበር በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ላይ ስደት የደረሰባት ይህች ቀን ምን ያህል የምታስፈራ ምን ያህል የምታስጨንቅ ናት በዚያን ዘመን መከራ ካገኛቸው ክርስቲያን ይልቅ የእሷ መከራ እጅግ የከፋ የሚያስጨንቅ ነበር::

፬ አይ ይእቲ እምአንስት ዘትመስል ኪያሃ ወትትዔገሥ ዘንተ ኵሎ ከማሃ ኀድጉሰ ለብእሲት ድክምት ለእደውኒ እለ ቦሙ ኃይል እምኢተክህሎሙ ይትዓገሡ ከማሃ ዳዕሙ ኃይለ እግዚአብሔር ዘላዕሌሃ ያስተዔግሣ ወያጸንዓ በከመ ይቤ ጴጥሮስ ሐዋርያ ወኀዳጠ ሐሚመክሙ ውእቱ ይፌጽም ለክሙ ወያጸንዓክሙ ወያሌበወክሙ እመሰ አንበርዋ በሀገረ ክርስቲያን ዘትሰምዕ ነገሮሙ ወተአምር ግዕዞሙ ወትሳተፍ በበሊዕ:ወሰትይ ምስሌሆሙ እምኢኮነ መንክረ ወዕፁብ አላ እምኮነ ቀሊለ።

ምዕራፍ ፲፩

፩ ወሶበ ርእያ ውእቱ ፃንቅላ ይቤላ በልሳነ ዚአሁ ምንትኑ አንቲ ወምንትኑ ግዕዝኪ ዘኢትበልዒ ወኢትሰትዪ ወእፎ ይከውን ንብረትኪ ወአልቦ ዘይተረጉም ማዕከሌሆሙ ወሶቤሃ ከሠተ እግዚአብሔር እዝና ወሰምዓት ልሳኖ በከመ ይቤ መጽሐፍ ወዓቀመ ስምዓ ለዮሴፍ አመ የሐውር ብሔረ ግብፅ ወሰምዓ ልሳነ ዘኢየአምር ወኮነ ላቲ ከማሁ ወአውሥአቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎ እፎ እበልዕ አነ ክርስትያናዊት መብልዓ ዘአንተ ገበርከ ወእፎ እሰቲ ማየ ዘአንተ ትሰቲ በጽዋዕ እንዘ አንተ አረሚ ርኩስ ወኢተኃብር ምስሌየ በሃይማኖት ወአልብከ ኀርመት ወትበልዕ አንጺዋ ወከይሴ ወኵሎ አራዊተ ርኩሳነ ዘከልአት ሕግ ከመ ኢይኅሥሥዎሙ ወኢይብልዕዎሙ ።

፪ ወባሕቱ አምጽእ ሊተ እክለ ጥራየ ወመቅፁተ ሐዲሰ ለአብስሎ ወኃምኃመ ሐዲሰ ለቀዲሐ ማይ ውእቱኒ ሰምዓ ልሳና ወገብረ ከማሁ ወአምጽአ ላቲ በከመ ትቤሎ ወእምዝ አብሰለት ኢላርያ ውእተ እክለ ወአቅረበት ላቲ ወጥዕመት እምኔሁ ንስቲተ:ወኃደገቶ:ወበከየት:ፈድፋደ:ኢላርያ:በእንተ:ዘኃደገቶ:ለመብ ልዕ:እምነ:ቅድስት:ወቡርክት:ወለተጴጥሮስ:ወበዝንቱ:ግብር:ነበራ: ፪ኤሆን:ባሕቲቶን:፩ደ:ወርኃ:ወበውእቱ:መዋዕል:ቦአ:ሰይጣን:ውስ ተ:ልበ:ፃንቅላ:ወወደየ:አዕይንቲሁ:ኀቤሃ:ወአኃዘ:ያመክራ:በከመ:ያ መክርዎን:ዕደው ለአንስት።

፫ ወሶበ ዓበየቶ አሰራ ድኅሪተ በሐብል ምስለ ሰርዌ ቤት ወዓቀማ ወአስተጋብአ ዕፀወ ወአምጽአ እሳተ ከመ ያንድድ መትሕቴሃ ወያመነድባ በጢስ ወጠፍአ ውእቱ እሳት ኢነደ ወኢጤሰ ወሶበ ስእነ ኃደጋ ወፈትሐ እማዕሰራ ወባሕቱ ኢኃደገ





፬ ከሴቶች እሷን የሚመስል ይህን ሁሉ መከራ የምትታገስ ማናት ማን አለች እንኳን ሴት ቀርታ ኃይል ያላቸው ወንዶችም ቢሆኑ እንደሷ መከራውን መታገስ አይቻላቸውም ነበር እሷን ግን በእሷ ላይ ያለ የእግዚአብሔር ኀይል ያስታግሳትና ያጸናት ነበር ሐዋርያው ጴጥሮስ ጥቂት መከራ ብትቀበሉ እሱ ያስፈጽማችኋል ያጸናችኋል አስተዋይ ያደርጋችኋል እንዳለ ነገር ግን ቋንቋቸውን በምትሰማ ፀባያቸውን በምታውቅ በመብልና በመጠጥ ከነሱ ጋራ አንድ በምትሆን በክርስቲያን አገር ቢያሳድጿት ኖሮ የሚያስጨንቅና የሚያስደንቅ ባልሆነ ቀላልም በሆነ ነበር።

ምዕራፍ ፲፩

፩ ያም ፃንቅላ በእሱ ቋንቋ አንቺ ምንድን ነሽ ፀባይሽስ ምንድነው አትበይምን አትጠጭምን ኑሮሽስ እንደምንድነው አላት በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ቋንቋውን ገለጠላትና ፃንቅላው የሚናገውን እንድትሰማ አደረጋት መጽሐፍ ወደ ምድረ ግብፅ በሄደ ጊዜ ለዮሴፍ ምስክርን አቆመ የማያውቀውን ቋንቋ ሰማ እንዳለ ለሷም እንደዚሁ አደረገላት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም መልሳ እኔ ክርስቲያናዊት ስሆን አንተ የሠራሀውን መብል እንዴት እበላለሁ አንተ ያልተጠመቅህ አረመኔ ስትሆን አንተ የጠጣህበትን ጽዋ እንዴት እጠጣበታለሁ አንተ በሃይማኖት ከእኔ ጋር አንድ ያልሆንክ አይጥንና እባብን ሕግ የምትከለክላቸው እርኩሳን አራዊትን ሁሉ የምትበላ ነህና አለችው።

፪ ነገር ግን ጥሬና ንፍሮ የምቀቅልበት አዲስ ማሠሮ ውሀ የምቀዳበት አዲስ ቅል አምጣልኝ አለችው እሱም ንግግሯን ሰምቶ ያለችውን አመጣላት ከዚህ በኋላ ኢላርያ ያን እህል አብስላ አቀረበችላት እሷም ትንሽ ቀምሣ ተወችው እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ያንን እህል አልበላም ስላለች ኢላርያ እጅግ አለቀሰች እንደዚህ ሆነው ሁለቱም አንድ ወር እዚያ ተቀመጡ በዚያን ጊዜ ሰይጣን በፃንቅላው ልቡና አድሮ ሻንቅላው ዓይኑን በእሷ ላይ አተኩሮ ወንዶች ሴቶችን እንደሚፈትኑ ይፈታተናት ጀመር።

፫ እሷም አይሆንም ባለችው ጊዜ በገመድ ከምሰሶ ጋራ እጇን ወደኋላ አስሮ አቆማትና እንጨቶችን ሰብስቦ ከበታቿ እሳት አንዶ በጢስ ያስጨንቃት ጀመር ያም እሳት ሳይነድና ሣይጤስ ጠፋ በደከመው ጊዜ ከማሠሪያዋ ፈታት ነገር ግን

አመክሮታ ወአሐተ ዕለተ ሖረ ኀቤሃ በምክረ ሰይጣን ሐልዮ ከመ ይፈጽም ፈቃዶ ወሶበ ቦአ ውስተ ቤት ዘሀለወት ውስቴቱ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ርእያ እንዘ ትቀውም ለጸሎት ወይበርህ ገጻ ከመ ፀሐይ ወምስሌሃ ይቀውም መልአከ እግዚአብሔር መንገለ ገቦሃ ወሰይፍ ምሉሕ ውስተ እዴሁ በጥቃ እዝና ወሶቤሃ ደንገፀ ወፈርሃ ወገብአ ድኅሬሁ ወወድቀ ድኅሪተ።

፬ ወተገሥጸ እምይእቲ ዕለተ ወኢደገመ አመክሮታ አላ ኮነ ያከብራ ወይፈርሃ ወሰይጣንኒ ተኃፍረ ወተመውአ እፎ ሀለየ ኀበ ሀለየ ዘኢኮነ ግብር ለመልክዓ ክርስቶስ ቦኑ ተሐዘበ ከመ ይከውን ሎቱ እንዘ ገብር ፅዩዕ ውእቱ ዝንቱሰ ሕሊና ዚአሁ ኢኮነ ዘዚአሁ አላ ዘሰይጣን ውእቱ እስመ ውእቱ ኀሠሠ ከዊነ አምላከ በትዕቢቱ ወእኀተ ክርስቶስኒ እምአመ ተፈልጠት እምኔሃ ነበረት እንዘ ትበኪ ወታስቆቁ መዓልተ ወሌሊተ በእንተ ዘተርፈት ባሕቲታ ወኃደገታ እማ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወኮነት ከመ ሕፃን ዘአኅደግዎ ጥበ እሙ ወሖረት ኀበ እኅተ አመተ ክርስቶስ ወቆመት ቅድሜሃ ወበከየት ፈድፋደ ወዓንብአት ወተስእለታ አመተ ክርስቶስ እንዘ ትብል ምንት ያበክየኪ ኦ ብእሲቶ ።

፭ አውሥአታ እኀተ ክርስቶስ ወትቤላ አንሰ እበኪ እስመ ፈለጡኒ እምእምየ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወአትረፉኒ ባሕቲትየ ወይእዜኒ እስእለኪ ኦ እግዝእትየ እመ፡ረከብኪ ሞገሰ፡በቅድሜኪ ተሣሃልኒ ወነጽሪ ኃዘንየ ወሰአሊዮ በእንቲአየ ለመልክዓ፡ክርስቶስ፡ከመ፡ይፈንወኒ፡እሑር፡ኀበ፡እምየ፡ወይእተ፡ጊዜ፡ተራ ኅርኃት፡ላዕሌሃ፡ወጸውዓቶ፡ለመልክዓ ክርስቶስ ወሰአለቶ በከመ ትቤላ ወአብሀለቶ ኦሆ ወውእቱኒ ቦአ ኀበ ንጉሥ ወቆመ ቅድሜሁ ወይቤሎ ሕየው ኦ እግዚእየ ንጉሥ ዕፁበ ርኢኩ ወመንክረ ሰማዕኩ ዘኮነ ዮም በመንግሥትከ።

፮ ወይቤሎ ንጉሥ ምንተ ርኢከ ወምንተ ሰማዕከ ወተሠጥዎ ወይቤሎ ኵሉ ሰብእ ሶበ ገፍዕዎ ወሰደድዎ ወፈለጥዎ እምአዝማዲሁ ይበኪ ወየኃዝን ይእቲሰ ብእሲት እንተ ነበረት ምስለ ወለተ ጴጥሮስ ሶበ ንቤላ ምስለ አዝማድኪ በሀገርኪ ንበሪ ትበኪ ወትላሁ ወይቤሎ ንጉሥ አንተሰኬ ምንተ ትፈቅድ ንግበር ላቲ ወይቤሎ አንሰ እፈቅድ ንፈንዋ ኀበ ውእቱ ሀገር ከመ ይቅትላ ሕማመ ማቄ ከመ ኢታስርሐኒ ወኢታንጥየኒ ዘልፈ





መፈታተኑን አልተዋትም ከዕለታት በአንድ ቀን በሰይጣን ምክር ፈቃዱን ይፈጽም ዘንድ እሷ ካለችበት ቤት በገባ ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ቆማ ስትጸልይ ፊቷ እንደ ፀሐይ ሲያበራ የእግዚአብሔር መልአክ በጐኗ ቆሞ የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ ይዞ አየና ያን ጊዜ ደንግጦ ወደ ኋላ ተመልሶ የኋሊት ወደቀ።

፬ ከዚያች ቀን ጀምሮ ሊፈትናትም አልሞከረም ተገስጿልና ይፈራትና ያከብራታል እንጅ ሰይጣንም ተሸንፎ አፈረ ለመልክዓ ክርስቶስ አስቦ ያልሆነለት ይህ እንደምን አሰበ የከፋ ባሪያ ሲሆን ይህን እንደምን አሰበ ይህስ የሱ አሳብ ሆኖ አይደለም የሰይጣን አሳብ ነው እንጂ እሱ አምላክ መሆንን በትዕቢቱ አስቦ ነበርና እኅተ ክርስቶስም ከሷ ከተለየች ጀምሮ ቀንና ሌሊት ብቻዋን ስለቀረችና እናቷ ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከሷ ስለተለየች የእናቱን ጡት እንደከለከሉት ሕፃን እጅግ ታለቅስና ታነባ ነበር ወደ ዓመተ ክርስቶስ እኅት ሄዳ ከፊቷ ቆማ እጅግ አለቀሰች ዓመተ ክርስቶስም አንቺ ሴት ምን ያስለቅስሻል አለቻት።

፭ እኅተ ክርስቶስም መልሳ ከእናቴ ከቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለይተውኝ ብቻየን እዚህ አስቀርተውኛልና እጅግ አለቅሳለሁ አለቻት አሁንም እመቤቴ ሆይ በአንቺ ዘንድ ባለሟልነትን ካገኘሁ ዘንድ ራርተሽ ኃዘኔን አይተሽ ወደ እናቴ ይሸኙኝ ዘንድ መልክዓ ክርስቶስን ለምኚልኝ አለቻት ያን ጊዜ አዝና መልክዓ ክርስቶስን ጠርታ እንዳለቻት ለመነችውና እሽ አሠኘችው እሱም ወደ ንጉሡ ሄዶ ከንጉሡ ፊት ቆሞ ጌታየ ንጉሥ ሆይ ለዘላለም ኑር ዛሬ በመንግሥትህ ዘመን የተደረገውን ያየሁትን ልንገርህ አለው።

፮ ንጉሡም መልሶ ምን አየህ ምንስ ሰማህ አለው መልሶ ሰው ሁሉ ግፍ ሲያደርሱበት ሲያሳድዱት ከዘመዶቹ ሲለዩት ያለቅሣል ያዝናል ይቺ ከወለተ ጴጥሮስ ጋራ የነበረችው ሴት ግን ከዘመዶችሽ ጋራ በሀገርሽ ተቀመጭ ብንላት ፈጽማ ታለቅሣለች ንጉሡም መልሶ አንተስ ምን እናደርግላት ዘንድ ትፈልጋለህ አለው እኔስ በሽታ ይገላት ዘንድ ዘወትር እንዳታስጨንቀኝና እንዳትጨቀጭቀኝ ወደዚያ ሀገር እንልካት

ወተየውሀ ንጉሥ በዝንቱ ነገር ወይቤሎ ይኩን በከመ ትቤ ወወፅአ ወነገራ ወይቤላ ኀበ ኀለይኪ ሑሪ ወሰሚዓ ዘንተ ወድቀት ወሰዓመት እገሪሁ ወተፈሥሐት ወተሐሥየት ፈድፋደ ወአእኰተቶ ለእግዚአብሔር።

፯ ወእምዝ ተንሥአት ወሖረት ወበጽሐት ኀበ ውእቱ ሀገር ዘሀለወት ውስቴቱ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወተራከበት ምስሌሃ ወተአምኃታ ወሶበ ርእየት ከመ ጸልመ አርአያሃ ወደግደገ ሥጋሃ ሐቀፈት ክሣዳ ወበከየት ላዕሌሃ ወትቤላ እምነ ቅድ ስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ትናዝዛ ምንትኑ ያበክየኪ ይእዜ ሶበ ረከብኪ ኪያየ አኮኑ አነ ዘተኃሥሥኒ እምይእዚሰ ይደልወነ ንትፈሣሕ ወናእኩቶ ለእግዚአብሔር ዘረሰየነ ንንበር ኅቡረ አሐተኔ ወኢኃደገነ ዝርዋነ ሊተኒ ወለኪኒ ወዘንተ ብሂላ አኀደገታ ብከያ ወእምድኅሬሁ ነበራ እኀተ ክርስቶስ ወኢላርያ እንዘ ይትለአካሃ ወይትጌበራ ለሲሳያ ዘትበልዕ ወዘትሰቲ።

፰ ወእምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ነበረት እንዘ ትጸመድ ወትትቀነይ ለእግዚአብሔር ወእምድኅሬሁኒ መጽኡ ፪ቱ አርድእቲሃ ተክለ ማርያም ወዓፅቀ ሐዋርያት ወኮኑ የሐውሩ ኀበ እማ ወአዝማዲሃ ወአኃዊኃ ወይነሥኡ ንዋየ ዘዚአሃ ወአልባሳተ ሠናያተ ዘዘዚአሁ ወያበጽሑ ኀቤሃ ወአሐተ ዕለተ ሖረ ተክለ ማር ያም ኀበ እማ ነሥአ ንዋየ ብዙኃ ወፀዓነ አድገ ወገብአ ወእንዘ የሐውር ፍኖተ በድው መስየ ላዕሌሁ ብሔር ወአልቦ ቤት ዘይትአንገድ ቦቱ ወአጽለለ ታሕተ:ዖም:ዘበቈለ:ላዕለ:ተመን:ወአውረደ:ፆረ:እምላዕለ:አድግ:ወአሰ ሮ:ለአድግ:በውእቱ:ዖም:ዘመልዕልተ:ተመን ውእቱሂ ሰከበ ህየ ወኢርእዮ ለውእቱ ተመን ወኖመ።

፱ ወሶበ ኮነ አፈ ጽባሕ ነቀወ ውእቱ ተመን ወአንሰሐሰሐ ወአንቀልቀሎ ለውእቱ ዖም ወሶበ ርእዮ ውእቱ ረድእ ደንገፀ ወፈርሃ ወፍጡነ ፈትሐ አድገ ወአጸሮ ንዋየ ወሖረ እንዘ ይረውጽ ወመሰሎ ዘይተልዎ ድኅሬሁ እመሰ ፈቀደ ይትልዎ ውእቱ ተመን ለውእቱ ረድእ እምውሕጦ ሌሊተ እንዘ ይነውም ወለአድግኒ እምኢኃደጎ ወባሕቱ ሶበ ፈቀደ እግዚአብሔር ከመ ይክስት ኀይለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አዘዞ ለተመን ከመ ይንቀ ወያንሰሐስሕ እመሰ አርመመ ተመን እምኢርእዮ ውእቱ ረድእ መኑ እምነገረነ ለነ ወእፎ እምጸሐፍነ ዘንተ ተአምረ።





ዘንድ እወዳለሁ አለው ንጉሡም በዚህ ነገር ተታሎ አንተ እንዳልክ ይሁን አለው ከዚያ ወጥቶ አሠናብተንሻልና ሂጅ አላት እሷም ይህን ሰምታ ወድቃ እግሩን ስማ እጅግ ተደስታ እግዚአብሔርን አመሰገነችው።

፯ ከዚህ በኋላ ተነሥታ ሄዳ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ካለችበት አገር ደርሳ ከሷ ጋር ተገናኝታ እጅ ነሣቻት መልኳ እንደጠቆረ ሰውነቷ እንደከሳ አይታ አንገቷን አቅፋ አለቀሠች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም እያረጋጋቻት ዛሬ ምን ያስለቅስሻል ትፈልጊኝ የነበረ እኔን አግኝተሻልና ከዛሬ ወዲህ በአንድነት እንድንኖር የፈቀደልን እንለያይ ዘንድ ያልተወን እግዚአብሔርን እናመስግነው ዘንድ ይገባል አለቻት ይህን ብላ ለቅሶውን አስተወቻት ከዚህ በኋላ እኅተ:ክርስቶስና:ኢላርያ:ይላላኳትና:የምትበላውንና:የምትጠጣውን ያዘጋጁላት ጀመር።

፰ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ጽሙድ እንደ በሬ ቅኑት እንደገበሬ ሆና ለእግዚአብሔር ታገለግል ጀመር ከዚህ በኋላ ሁለቱ አገልጋዮቿ ተክለ ማርያምና አፅቀ ሐዋርያት ወደሷ መጡ እነሱም ወደናቷና ወደ ዘመዶቿ ወደ ወንድሞቿ እየተላኩ ገንዘብና ልብስ ያመጡላት ነበር ከዕለታት በአንድ ቀን ተክለ ማርያም ወደ እናቷ ሄዶ ብዙ ገንዘብ ብዙ እቃ በአህያ ጭኖ ሲሄድ በረሃ ሲደርስ መሸበት የሚያድርበት ቤት በዚያ ስለአልነበረ በዘንዶ ላይ የበቀለ እንጨት ሥር ተጠግቶ ሸክሙን ከአህያ ላይ አውርዶ በዘንዶ ላይ በበቀለው እንጨት አህያውን አሠረና እሱም እዚያው ተኛ ያንን ዘንዶ አላየም ነበርና።

፱ ሊነጋጋ አካባቢ ያ ዘንዶ እየጮኸ ሲንቀሣቀስ ያንን እንጨት አንቀሣቀሠው ያም ረድዕ ይህን አይቶ ደነገጠና ፈርቶ አህያውን ፈቶ እቃውን ጭኖ እየሮጠ ሄደ ከኋላ የተከተለው መስሎታልና ይህ ዘንዶ መከተል ቢፈልግ ኖሮ ሌሊት ተኝቶ ሳለ በዋጠው ነበር አህያዋንም በዋጣት ነበር ነገር ግን እግዚአብሔር የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የጸሎቷን ኃይል ይገልጥ ዘንድ በወደደ ጊዜ ያ ዘንዶ እንዲጮህ እንዲንቀሣቀስ አደረገው ያ ዘንዶ ባይንቀሳቀስ ኖሮ ረዱም ባላየውም ነበር ለኛ ም ባልነገረን ነበር ይህን ተአምር እኛም ባልጻፍን ነበር።

፲ ወሖረ እንዘ ያነክር ውእቱ ረድእ ወበጽሐ ውእተ ሀገረ ወአውረደ ጾረ እምላዕለ አድግ ወቦአ ኀበ እምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ ወአንበረ ቅድሜሃ ውእተ ንዋየ ዘአምጽአ ወነገራ መልእክተ ዘእማ ወዘአኃዊሃ ወዜነዋ ሰላመ ወአምኃ ወቆመ ቅድሜሃ ወርእየቶ ላዕለ ወታሕተ እስመ አእመረት ድንጋፄ ዘረከቦ በበድው እምቅድመ ይክሥት ላቲ ወትቤሎ አይቴ ኃደርከ ዮም ወምንትኑ ድንጋፄ ዘረከበከ ወአውሥአቶ ወተስእለቶ ከመ ዘኢተአምር ወነገራ ውእቱኒ ኵሎ ዘኮነ ወትቤሎ ለምንት ፈራህከ ወለምንትኑ ደንገፅከ አኮኑ እግዚአብሔር ሀሎ ምስሌከ ኢይቤኑ መጽሐፍ እስመ እግዚአብሔር አምላክነ ምስሌነ አልቦ ዘይክለነ ወካዕበ ይቤ ጽድቅ በወልታ የዓውደከ ወኢትፈርህ እምግርማ ሌሊት ላዕለ ተኵላ ወከይሲ ትጼዓን ወበአንተዝ ኢትፍራህ ምንትኒ:አልቦ ዘይነክየከ::

፲፩ ወእምዝ ነሥአት ውእተ ንዋየ አልባሰ ወወርቀ ወወሀበቶ ለውእቱ ሻንቅላ ወከመዝ ትሁቦ ኵሎ አሚረ ወእምዝ ሶበ ርእየ ስነ ኂሩታ ወዕበየ ጸጋ ወሞገስ ዘላዕሌሃ አክበራ ፈድፋደ ወአፍቀራ ወሰመያ በልሳነ ብሔሩ ስቲ ዘበትርጓሜሁ እግዝእት እስመ እግዚአብሔር ሀለወ ምስለ እምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ በከመ ትቤ አሪት ወደይዎ ለዮሴፍ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ኀበ ይነበሩ ሙቁሓን ወነበረ ህየ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ወሀለወ ረድኤተ እግዚአብሔር ምስለ ዮሴፍ ወከዓወ ምሕረተ ላዕሌሁ ወፍቅረ ወወሀበ ሞገስ ወወደየ ውስተ ልበ ሊቀ ዓቀብተ ሞቅሕ ሎቱ ሣህለ ወርኅራኄ ወሤሞ ሊቀ አቀብተ ቤተ ሞቅሕ ለዮሴፍ ላዕለ ኵሎሙ ሙቁሓን እስመ እግዚአብሔር ሀለወ ምስሌሁ ወበኵሉ ዘገብረ ይሤርሖ እግዚአብሔር ::

፲፪ ወዳዊትኒ ይቤ ሀሎኩ ምስሌሁ አመ ምንዳቤሁ ወእግዚእነሂ ይቤ እነ እሄሉ ምስሌክሙ በኵሉ መዋዕል እስከ ኅልቀተ ዓለም ወከማሁ ሀለወ እግዚአብሔር ምስለ እምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ ወወሀባ ሞገስ በቅድመ አረሚ ሻንቅላ ወአሜሃ ይቤላ ለሊሁ በፈቃዱ እንዘ አልቦ ዘያጌብሮ ኵሉ ዘፈቀደ ይንበር ኀቤኪ ወይምጻእ እመኒ በዝኀ ወኮኑ ፻ተ ኢየኃዝን ወኢይከልአሙ እምቅድመ አሜሃ ሶበ ርእየ ሰብአ ፪ አው ፫ ይዴግኖሙ ወይፈቅድ ይቅትሎሙ ወይሴውሮሙ እግዚአብሔር እምአዕይንቲሁ ወሶበ የኃሥሥሙ የኃጥአሙ ወባሕቱ ይእዜ ሶበ ርእየ ስነኂሩታ ወዕበየ ግርማ ወሞገስ ዘላዕሌሃ ተመይጠ እምእከይ ኀበ ኂርውና ወአብሆሙ ይንበሩ ::





፲ ረዱም እያደነቀ ሄዶ እዚያ አገር ደረሠና ከአህያው ላይ ሸክሙን አወረደ ከዚህ በኋላ ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ገብቶ ያንን እቃ በፊቷ አደረገ የእናቷንና የወንድሞቿን ሰላምታ ነገራት ወደ ላይ እና ወደ ታች አየችው በበረሃ ያገኘውን ድንጋጤ ገና ሳይነግራት አውቃለችና ዛሬ ወዴት አደርክ አለችው ያገኘህም ድንጋጤ ምንድነው አለችው እንደማታውቅ መልሳ ጠየቀችው እሱም የሆነውን ሁሉ ነገራት ለምንስ ፈራህ ለምንስ ደነገጥህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋራ አይደለምን እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ከሆነ ማን ይችለናል ብሎ መጽሐፍ ተናግሮ የለምን ዳግመኛም እውነት እንደጋሻ ይከበሃል ከሌሊት ግርማ የተነሣ አትፈራም በተኵላና በእባብ በዘንዶ ላይ ትጫናለህ ብሎ የለምን ስለዚህ ምንም ቢያጋጥምህ አትፍራ አለችው::

፲፩ ከዚህ በኋላ ያንን ወርቅና ልብስ ወስዳ ለዚያ ሻንቅላ ሰጠችው እንደዚሁ ዘወትር ትሰጠው ነበርና ከዚህ በኋላ በእሷ ላይ ያለውን ጸጋና ደግነቷን በአየ ጊዜ እጅግ ወደዳትና አከበራት በሀገሩ ቋንቋ ስቲ ብሎ ጠራት ይህም ማለት ትርጓሜው እመቤት ማለት ነው እግዚአብሔር ከእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጋር አለና ኦሪት ዮሴፍን እስረኞች ከአሉበት ከእስር ቤት አስገቡትና በእስር ቤት ሳለ የእግዚአብሔር ረድኤት ከዮሴፍ ጋር ነበር ይቅርታንና መወደድን ለእሱ ሰጠው የእስር ቤት በሚጠብቀው
ዘበኛ ልቡና ውስጥ ርኅራኄንና ይቅርታን አሳድሮ በእስረኞች ላይ አለቃን እንዲሾም አደረገውና ያም ዘበኛ ዮሴፍን በእስረኞች ላይ አለቃ አደረገው እግዚአብሔር ከእሱ ጋር ስለነበረ የሚሠራውን ሁሉ እግዚአብሔር ያስተካክልለት ነበር::

፲፪ ዳዊትም በመከራ ጊዜ ከእሱ ጋር አለሁ አለ ጌታችንም እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ እንደአለ እንደዚሁ እግዚአብሔር ከእታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጋር ሁኖ በሻንቅላው ዘንድ ባለሟልነትን ሰጣት ያን ጊዜ ማንም ሳያስገድደው በፈቃዱ ከአንች ጋር መቀመጥ የሚፈልግ ሰው ሁሉ መጥቶ ይቀመጥ ከዛሬ ወዲህ በዝተው መቶም ቢሆኑ ምንም አልአዝንም አለ ቀድሞ ሁለትና ሦስት ሰው በአየ ጊዜ ተከትሎ ይገላቸው ዘንድ ይፈልግ ነበር እግዚአብሔር ግን ከዓይኑ ፊት ይሰውርበት ነበር በፈለጋቸው ጊዜ ያጣቸዋል ነገር ግን ቸርነቷንና ታላቅነቷን ክብሯን በእሷ ላይ ያለውን ጸጋ በአየ ጊዜ ከክፋት ወደ ደግነት ተመልሶ ይቀመጡ ዘንድ ፈቀደላቸው::

## ምዕራፍ ፲፪

፩ ወመጽአ ብዙኃን ስዱዳን እምለፌ ወእምለፌ ወተጋብኡ ኀቤሃ ወዐገትዋ ከመ ይትጋብኡ አንህብት ኀበ ንጋሢሆሙ ወየዓግትዎሙ በዝጐ እድ ወአንስት ወአማኅበሩ ምስሌሃ ዝ ውእቱ ቀዳማይ ማኅበር ወነበረት ህየ ፫ ዓመተ እንዘ ትሜግቦሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሀሎ ህየ ፩ዱ ሙቁሕ ዘስሙ በኃይለ ማርያም ወመነኮስ ውእቱ ዘተሞቅሐ እገሪሁ ሙቃሔ ጽኑዓ በእንተ ሃይማኖት ርትዕት ወውእቱ መነኩስ ጻድቅ ወቀደመ ነቢረ እምኔሃ ኀበ ውእቱ መካን ወአልቦ ዘይሬእዮ መኑሂ::

፪ ወሶበ ርእየቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኃዘነት ፈድፋደ ወነበረት እንዘ ትትራድኦ ወትሴስዮ ወተነበየ ላቲ ወይቤላ አንቲ ትወፅኢ እምዝንቱ ሀገር ወእመውት አነ በዝየ ወባሕቱ ለእመ ሞትኩ አነ እንዘ ሀሎኪ አንቲ ወቀበርክኒ አአምር ከመ ይምሕረኒ እግዚአብሔር በደኃሪት ዕለት አመ ይመጽእ ይኰንን ዓለመ ወእመ አኮሰ አልቦ ወኢይምሕረኒ ወእምድኅረ ነበረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በውእቱ ሀገር ፫ ዓመተ ቦአ እኁሃ ዮሐንስ ኀበ ፋሲል ወልደ ንጉሥ ወሰአሎ ከመ ይትናገሮ ለንጉሥ ከመ ያውፅኣ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እምቤተ ሞቅሕ ወይቤሎ ሠናይኑ ለእመ ሞተት በምድረ አረሚ እምቅድመ ዝኒ ሐመት ወህቀ ከመ ተርፈት እመዊት ከመዝሰ ኢይኩን ወኢይባእ ኃዘን ማዕከሌነ ወማዕከሌክሙ ወቦአ ውእቱኒ ኀበ ንጉሥ ወነገሮ ወይቤሎ አዝዝ ከመ ያውፅእዋ ለወለተ ጴጥሮስ እምነ ዝርበይ ከመ ኢትሙት በህየ ወኢይኅዝኑ ላዕሌከ አኃዊሃ እስመ እሙንቱ ያፈቅሩከ ወይቀንዑ ለመንግሥትከ ወተሠጥዎ ንጉሥ ወይቤሎ እሆ ለቃልከ ወይኩን በከመ ትቤ ወሶቤሃ ፈነወ ንጉሥ ሐራሁ ኀበ ውእቱ ሻንቅላ ወይቤሎ ፈንዋ ለወለተ ጴጥሮስ እንተ አዘዝኩከ ትዕቀባ ወበጺሖ ላእከ ነገሮ:መልእክተ:ንጉሥ:ለውእቱ:ሻንቅላ:ለዛቲኒ ነገራ ዘከመ ይቤላ ፃዒ::

፫ ወሶበ ሰምዐ ውእቱ ሙቁሕ ዘዘከርናሁ ቅድመ ኃዘነ ፈድፋደ ወቀብጸ ተስፋሁ ወይቤ እምይእዜሰ አእመርኩ ከመ ኢይምሕረኒ እግዚአብሔር ወባሕቱ ተሣሃለ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ወአርአየ አድኅኖቶ ወበቅድመ አሕዛብ ከሠተ ኪዳኖ ወበጊዜሃ ሐመ ውእቱ ሙቁሕ ወይቤላ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እፎ ተሐውሪ እንበለ ትቅብሪ ኪያየ ወትቤሎ ኢየሐውር እንበለ እቅብርከ:ወተፈሥሐ:ወሰዓመ እዴሃ ወእምዝ ሰአለቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለውእቱ ሻንቅላ ከመ ያመክኒ ወይበል ኢበጽሐኒ ትእምርተ ንጉሥ ወሐሰውከ አንተ አንሰ ኢይፌንዋ::





## ምዕራፍ ፲፪

፩ ብዙ በሃይማኖት የተሰደዱ ከየአሉበት መጥተው ንህብ ወደ አውራው እንዲሰበሰብ ወደ እሷ ተሰብስበው ብዙ ወንዶችና ሴቶች ከእሷ ጋር ማኅበር መሠረቱ የመጀመሪያ ማኅበር ይህ ነበር በዚያ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እነሱን እያስተዳደረች ሦስት ዓመት ቆየች በዚያ ስሙ በኃይለ ማርያም የሚባል ስለ ሃይማኖት በጽና የታሰረ አንድ መነኩሴ ነበር ያም የበቃ መነኩሴ ከእሷ አስቀድሞ በዚያ ቦታ ታስሮ ይኖር ነበር የሚጠይቀውም አልነበረም::

፪ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በአየችው ጊዜ እጅግ አዝና ትረዳውና ትመግበው ጀመር እሱም አንች ከዚህ አገር ትወጫለሽ እኔ ግን እዚሁ እሞታለሁ ነገር ግን አንች ሳለሽ ከሞትኩ እግዚአብሔር መጨረሻ ዘመን ይቅር እንደሚለኝ በዚህ እረዳለሁ ካልሆነ ግን እንጃ እንደ ቸርነቱ አላት ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሦስት ዓመት ከተቀመጠች በኋላ ወንድሟ ዮሐንስ ወደ ንጉሡ ልጅ ወደ ፋሲል ሄዶ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ከእስር ቤት ያስወጣለት ዘንድ ለመሆኑ በአረመኔ አገር ብትሞት መልካም ነውን ከዚህ በፊት ታማ ለሞት ደርሳ በግድ ከሞት ዳነች አሁንም በእኛና በእናንተ መካከል ቅሬታ አይግባ ለንጉሡ ንገርልኝ አለው ልጁም ወደንጉሡ ገብቶ ወለተ ጴጥሮስን ከዝርበይ እንዲያወጧት እዘዝ እዚያ እንዳትሞትና ወንድሞቿ እንዳያዝኑብህ እነሱ አንተን ይወዱሃል ስለመንግሥትህ ይቀኑልሃልና አለው ንጉሡም አንተ እንደአልክ ይሁን አለውና ያን ጊዜ ንጉሡ ወደዚያ ሻንቅላ ጠብቅ ብየ ወደ አንተ የላኳትን ወለተ ጴጥሮስን ላክልኝ ትምጣ ብሎ ወታደር ላከ ሻንቅላውም ንጉሡ ትምጣ እንደ አለ ለእሷ ነገራት::

፫ ያ የታሰረው መነኩሴ ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ አዝኖ ተስፋ ቆርጦ እግዚአብሔር ይቅር እንዳልአለኝ በዚህ አወቅሁ አለ ነገር ግን እግዚአብሔር ይቅር ብሎት ማዳኑን አሳየውና በአሕዛብ መካከል:ቃል:ኪዳኑን:ስጠውና:ያን:ጊዜ:ያ:የታሰረ:መነኩሴ ታመመና ወለተ ጴጥሮስ እንዴት እኔን ሳትቀብሪ ትሄጃለሽ አላት እሷም አይዞህ አንተን ሳልቀብር አልሄድም አለችው እሱም ደስ ብሎት እጇን ሳመ ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ያን ሻንቅላ የንጉሡ ደብዳቤ ምልክት አልደረሰኝም አንተ ውሸትህን ነውና እኔ አልካትም በለው አለችው::

፬ ወውእቱኒ ይቤላ እሆ ወገብረ በከመ ትቤሎ ወሖረ ውእቱ ላእክ ወተመይጠ ኀበ ንጉሥ ወነገሮ ከመዝ ወሶቤሃ ተምዓ ንጉሥ ወጸሐፈ ትእምርተ ዘማዕከሌሆሙ ወፈነዎ ዳግመ ለውእቱ ላእክ ወውእቱኒ ሙቁሕ አዕረፈ እምዘደወየ በሳብዕት ዕለት ወረከበ ዘተመነየ ወቀበርዎ በዝማሬ ወበጸሎት ወወደይዎ ውስተ መቃብር ምስለ መዋቅሕቲሁ እስመ ጽኑዕ ውእቱ ወኢይትፈታሕ ወፈጸመ ገድሎ ሠናየ ወአዕረፈ በሰላም ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስለ ፍቁሩ ለዓለመ ዓለም አሜን::

፭ ወእምድኅሬሁ በጽሐ ላእከ ንጉሥ ወወሀቦ መጽሐፈ መልእክት ዘንጉሥ ለውእቱ ሻንቅላ ወተመጠወ ወይቤ ሠናይ ቃለ ንጉሥ ርኢክሙኑ ፍቁራንየ ከመ አልቦቱ ሥልጣን ወመባሕት ለንጉሥ ምድራዊ ከመ ይቅትል መነሂ ዘእንበለ ፈቃደ እግዚአብሔር ወውእቱ ንጉሥ ሰማያዊ ንጉሠ ሥጋ ወመንፈስ ወብዙኃ ጊዜያተ ፈቀደ ንጉሥ ሱስንዮስ ከመ ይቅትላ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ቦ ጊዜ በሰይፍ እመ ቆመት ቅድሜሁ ወጸረፈት ላዕሌሁ ወእኀደግዎ መማክርቲሁ እንዘ ይብሉ ለእመ ቀተልካ ለይእቲ ይከውኑከ አጽራረ ኵሎሙ አዝማዲሃ ደዋሮ ወፈጠጋር ወዓዲ ተጥበበ ጥበበ ሰይጣናዊ ከመ ይሰውር እከየ ዚአሁ እመ ፈነዋ ብሔረ ዝርበይ ይቤሎ ለውእቱ ሻንቅላ ግበር ላቲ ልገተ ለምንባሪሃ ማዕከለ ሣዕር ዘገዳም ወፈኑ እሳተ መትሕቴሁ ጊዜ ንፍሐተ ነፋስ ከመ ያውዕያ ወትሙት ወለእመ ገበርከ ዘንተ አነ አከብረከ ክብረ ዐቢየ::

፮ ወገብረ ውእቱ ሻንቅላ በከመ አዘዞ ንጉሥ ወአንበራ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ውስተ ልገት ዘማዕከለ ሣዕር ወውእቱ ሣዕር ነዊኅ ጥቀ ወፈነወ እሳተ እምርኁቅ ወዓውዓዮ ለውእቱ:ሣዕር:ወይሰማዕ:ድምፀ:ነጐድጓዱ:እምርኁቅ:ወበጽሐ:ኀበ:ውእቱ:ልገት:እንዘ:ያንጐደጕድ:ከመ:ነጐድጓደ:ክረምት:ወዓገታ:ለ እምነ:ቅድስት:ወቡርክት:ወለተ:ጴጥሮስ:ከመ ሐፁር እምለፌ ወእምለፌ::

፯ ወይእተ ጊዜ ጸለየት ጸሎተ ፫ቱ ደቂቅ እንዘ ትብል ይባርክዎ እሳት ወላህብ ለእግዚአብሔር ሰቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም እምጥንቱ እስከ ተፍጻሜቱ ኢትፈርህ ወኢትደነግፅ ምንተኒ እላ ትጋጉዕ ከመ ትፈጽም መዊተ ወትንሣእ አክሊለ ስምዕ ወሶቤሃ ጠፍአ ውእቱ እሳት ወኮነ ከመ ዘወረደ ላዕሌሁ ዝናም ወአርአየ እግዚአብሔር ኃይሎ ላዕሌሃ ወአድኃና ከመ አድኃኖሙ ለ፫ ደቂቅ ይእቲሰ ኢተፈሥሐት በድኅነታ እላ ኮነት ኀዘንተ እስመ ታፈቅር ሞተ እምሕይወት::





፬ እሱም እሽ ኣላትና እሷ እንደ አለችው አደረገ ያም መልክተኛ ተመልሶ ሄዶ ይህን ለንጉሡ ነገረው ንጉሡም ተቆጥቶ በመካከላቸው የነበረውን ምልክት በደብዳቤ ጽፎ ለዚያው መልእክተኛ ዳግመኛ ላከ ያም የታሰረ መነኩሴ ታሞ በሳምንቱ አረፈና በእሷ እጅ መቀበር ተመኝቶ ነበርና፣የተመኘውን፣አገኘ በጸሎተ ፍታትና በዝማሬ አጀቡና አግሮቹ አስተጋመው እንደታሰሩ ወደ መቃብር አውርደው ቀበሩት እንደማይፈታ አድርገው በፅና አሰረውታልና እሱም መልካም ተጋድሎውን ፈጽሞ በሰላም አረፈ ጸሎቱና በረከቱም ከእኛ ጋር ይሁን ለዘላለሙ ይደረግልን፡፡

፭ ከዚያ በኋላ ያ መልክተኛ ተመልሶ መጥቶ የንጉሡን ደብዳቤ ለዚያ ሻንቅላ ሰጠ እሱም ተቀብሎ የንጉሥ መልዕክት ትክክል ነው አለ ወዳጆቼ ሆይ ያለ ፈቃደ እግዚአብሔር ምድራዊ ንጉሥ ማንንም መግደል እንደማይችል አያችሁን የሥጋና የነፍስ ንጉሥ መግደል ማዳን የሚችል እሱ እግዚአብሔር ነው ንጉሡ ሱስንዮስ ብዙ ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በፊቱ ቁማ በሰደበችው ጊዜ ይገላት ዘንድ አስቦ ነበር ነገር ግን አማካሪዎቹ እሷን ከገደልካት በፈጠጋርና በደዋሮ ያሉ ዘመዶቿ ሁሉ ጠላት ይሆኑሃል ብለው በምክንያት አስተዉት እንደገና የሰይጣን ምክር መክሮ የራሱን ክፋት የሰወረ መስሎት ወደ ዝርበይ በላከ ጊዜ ያንን ሻንቅላ በበረሃ ሣር መካከል አስረህ ጐጆ ሰርተህላት አስቀምጣትና ነፋስ በተነሳ ጊዜ ከታች እሳት አያይዝባት እና አቃጥላት ፈጥና እንድትሞት አንተ ይህን ከአደረክ እኔ ታላቅ ክብርን አከብርሃለሁ አለው፡፡

፮ ያም ሻንቅላ ንጉሡ እንደ አዘዘው አደረገና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ከፍ ከአለ መቀመጫ ላይ አስቀምጦ ከበታቿም እሷ የተቀመጠችበት ብዙ ሣር ነበርና ያን ሣር በእሳት ለኰሶ ከሩቅ ቁሞ ይመለከት ጀመር የሣሩ ክምር ትልቅ ስለ ነበር የእሳቱ ድምፅ ከሩቅ ይሰማ ነበር እሳቱም ሣሩን እያቃጠለ ሄዶ እሷ ከተቀመጠችበት መቀመጫ ዘንድ ደርሶ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን እንደ አጥር ከወዲያና ከወዲህ ከበባት፣ድምፁም እንደ ክረምት ነጐድጓድ ይሰማ ነበር፣

፯፣በዚህም፣ጊዜ፣እናታችን የሠለስቱ ደቂቅን ጸሎት እሳትና ሙቀት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል እሱ፣የተመሰገነ ነው፣ለዘለዓለም እሱ ምስጉን ነው እያለች ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ጸለየች እሷ ምንም አትፈራም አትደነግጥም ሰማዕትነትን ተቀብላ ሙታ የዘለዓለም አክሊልን ታገኝ ዘንድ ትጣደፍ ነበር እንጂ ያን ጊዜ ያ እሳት ታላቅ ዝናም እንደወረደበት ፈጥኖ ጠፋ እግዚአብሔርም በእሷ ላይ ኃይሉን ገልጦ ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት፣እንደአዳናቸው፣እሷንም፣አዳናት፣እሷም፣ከመኖር፣መሞትን፣ስለ ምትወድ፣በመዳኗ፣አልተደሰተችም ነበር፡፡

፰ በከመ ይቤ ጳውሎስ እፈቱ እፍልስ ወእትፈለጥ እምዓለም ከመ እሀሉ ምስለ ክርስቶስ ወፈደፋደ ይኄይስ ወይደሉ ሊተ ዝንቱ ወባሕቱ ኢፈቀደ ላቲ እግዚአብሔር ከመ ትሙት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አላ ትንበር ወትዕቀብ መራዕይሁ ወሶበ ስዕነ ቀቲሎታ ውእቱ ንጉሥ አዘዘ ያውፅእዋ ወእምዝ ይቤላ ውእቱ ሻንቅላ ንጊ ወሑሪ በከመ አዘዘኒ ንጉሥ ወወፅአት ወሖረት እንዘ ትትፌሣሕ በእግዚአብሔር አቡሃ ለምሕረት ወአምላካ ለኲሉ ትፍሥሕት።

፱ በከመ ይቤሉ ትሩፋን በባቢሎን አመ ሜጠ እግዚአብሔር ፄዋ ጽዮን ወኮነ ፍሡሓነ አሜሃ መልአ ፍሥሓ አፉነ ወተኀሥየ ልሳንነ ወሀለዉ ምስሌሃ እኀተ ክርስቶስ ወኢላርያ ወእርድእትሂ ተክለ ማርያም ወአፅቀ ሐዋርያት ወካልአንሂ ስዱዳን መነኮሳት ወመነኮሳይያት ወፅሉ ኀቡረ ምስሌሃ ወእንዘ ተሐውር እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በጽሐት ጫንቋ እምአህጉረ ደምብያ ወነበረት ህየ ኀዳጠ መዋዕለ እስመ አብሐ ንጉሥ ኀበ ዘፈቀደት ትንበር።

፲ ወተጋብኡ ኀቤሃ ብዙኃን ስዱዳን እድ ወአንስት እለ አውረዱ ቆብያሙ ወተመሰሉ ከመ ሰብአ ዓለም እለ ተዘርዉ ውስተ ኲሉ በሐውርት ወኮንዋ ውሉደ ወአዋልደ ከመ ይትፈጸም ቃለ መዝሙር ዘይቤ ህየንተ አበውኪ ተወልዱ ለኪ ደቂቅ ወትሰምዩዮሙ መላእክተ ለኲሉ ምድር ወይዘክሩ ስመኪ በኲሉ ትውልደ ትውልድ ወእንተ ጸብሐት ይትዌሰኩ ወኮኑ ፩ ማኅበረ። ዝ ውእቱ ዳግማይ ማኅበር።

፲፩ ወእንዘ ሀለወት ህየ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተንሥአ ደዌ ጽኑዕ ወሐሙ ብዙኃን እምኔሆሙ እንዘ ወበእንተዝ ፈርሁ ሰብአ ሀገር ወአንጐርጐሩ ላዕሌሆሙ እንዘ ይብሉ እሉ ፈላስያን አምጽኡ ብነ ደዌ ጽኑዓ ወተከልኡ እምቀሪቦቶሙ
ወርኅቁ፡እምኔሆሙ፡ወእምዝ፡ትቤ፡እምነ፡ቅድስት፡ወቡርክት፡ወለተ፡ጴጥሮስ፡ለእመ፡ነበርነ፡በዝየ፡አልቦ፡ዘይቀብሮ፡ለዘሞተ፡ወዝዕብኒ፡ይት ማሰጠነ ይኄይሰነ ንእቱ ደሴተ እንገራ ወቅርብት ይእቲ ደሴት እምሀገር ዘሀለዉ ቦቱ።

፲፪ ወሶቤሃ ተንሥኡ ወጸሩ ድውያኒሆሙ ወአተዉ ውስተ ይእቲ ደሴት ወነበሩ ወሀለወት አሐቲ ድንግል ሕፃን





፰ ቅዱስ ጳውሎስ እሱ ስለሚሻል ከክርስቶስ ጋር እኖር ዘንድ ከዚህ ዓለም ተለይቼ እሄድ ዘንድ እወዳለሁ እንደአለ ነገር ግን እግዚአብሔር እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በሰማዕትነት ትሞት ዘንድ አልፈቀደም በሕይወት ኑራ በጐቹ ምዕመናንን ትጠብቅ ዘንድ መርጧታልና ይህ ንጉሥ መግደል ስለአልቻለ እንድትወጣ አዘዘ ሻንቅላውም ንጉሡ ውጪ እንደአለ ውጪ አላትና የደስታ ባለቤት በሚሆን በእግዚአብሔር ማዳንና ድንቅ ሥራ እየተደሰተች ወጥታ ሄደች ።

፱ ከፋርስ ከባቢሎን የተመለሱ ትሩፋን እግዚአብሔር የጽዮንን ምርኮ በመለሰ ጊዜ ደስተኞች ሆን ያንጊዜ ደስታ አፋችንን መላ አንደበታችንም ተደሰተ እንደ አለ እኅተክርስቶስና ኢላርያ ደቀ
መዛሙርቶቿ ተክለ ማርያምና አፅቀ ሐዋርያት ሌሎችም በሃይማኖት፥ምክንያት፥የተሰደዱ፥ወንዶች፥መነኮሳትና፥ሴቶች፥መነኮሳይያት፥በአንድነት፥ከእሷ፥ጋር፥መጡ፥እናታችን፥ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ከደንብያ አውራጃ ጫንቋ ደርሳ እዚያ ጥቂት ወራት ተቀመጠች ንጉሡ ወደፈለገችበት እንድትቀመጥ ፈቅዶላታልና።

፲ ከመከራው ጽናት የተነሣ ፈርተው ቆባቸውን ጥለው ዓለማዊ የመሰሉ ብዙ ወንዶች መነኮሳትና ሴቶች መነኮሳይያት ወደ እሷ እየመጡ ንስሐ እየገቡ የሷ ልጆች ሆኑ መዝሙር ስለ አባቶችሽ ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ ለዓለም ሁሉ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት ካህናት ዲያቆናት አድርገሽ ትሾሚያቸዋለሽ ለልጅ ልጅ ዘመን ስምሽን ይጠራሉ እንደአለ ዕለት ዕለት እየተጨመሩ በዝተው አንድ ማኅበር ሆኑ ሁለተኛ ማኅበር ይህ ነው።

፲፩ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እዚያ ሳለች ከባድ በሽታ ተነሥቶ ከእነሱም ብዙዎች ታመሙ ስለዚህ የአገሩ ሰዎች እነዚህ ስደተኞች ከባድ በሽታ አመጡብን ብለው ወደ እነሱ መቅረብ ትተው ከእነሱ ሸሹ ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በዚህ ብንኖር የሞተውን የሚቀብርልን የለም ጅብ ይበላናል ወደ እንጋራ ደሴት ብንሄድ ይሻለናል አለች ካሉበት አገር ያቺ ደሴት ቅርብ ናትና።

፲፪ በዚያን ጊዜ ተነሥተው የታመሙትን ተሸክመው ወደዚያ ደ ሴት ገቡ የለባሲተ ክርስቶስ ልጅ አንዲት ደግ ለሁሉ የምትታዘዝ ፈጽማ አይሆንም የማትል ለትልቁም ለትንሹም የማታንጐራጕር

ዘለባሲተ ክርስቶስ ወሠናይት ይእቲ ወትትለአክ ለኵሉ ወኢትትሀከይ ግሙራ ወኢታንጐረጕር ምንተኒ ኢላዕለ ንዑስ ወኢላዕለ ዐቢይ አላ ትትለአክ ለኵሉ በዕሩይ ዘእንበለ አድልዎ ወእሐተ ዕለተ እንዘ ትጼሊ ውዳሴ እግዝእትነ ማርያም ዘዕለተ ሐሙስ ጸውዓታ እኅተ ክርስቶስ ለሕፃን ወለሊከታ ወሖረት ኀበ ግብር ዘአዘዘታ ወፈጸመት መልእክታ ወገብአት ወሀለወ ጸሎት ውስተ አፉሃ ወኢፈጸመት ወካዕበ ለአከታ ኀበ ካልዕ መልእክት ወካዕበ ሖረት ይእቲኒ እንዘ ትእኅዝ ጸሎተ ውስተ አፉሃ ወእምዝ መጽአት ኀቤሃ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወትቤላ ምንትኑ ታጸምወኪ ወምንትኑ ታሠርሐኪ ፍጡነ ፈጽሚ ዛተ ጸሎተ ዘውስተ አፉኪ ወአነ አዓርፈኪ እምዝንቱ ጻማ ወሥራሕ ወእነሥአኪ ውስተ ዕረፍት ዘለዓለም::

፲፫ ወሶበ ፈጸመት ጸሎታ ሐመት ንስቲተ ከመ እንተ ድካም ወተናገረት ዘከመ ትቤላ ወአዕረፈት ፍጡነ በጊዜሃ ካልእትኒ ወለት አዕረፈት ምስሌሃ እምእሉ ሕሙማን አልቦ አሜሃ ብእሲ ዘይከሪ መቃብረ ዘእንበለ አባ ዝክረ ማርያም ወሶቤሃ ተከዘት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎ ሎቱ በቃለ ትሕትና አ እኁየ እፎ ንገብር ወመኑ ይከሪ ለነ መቃብረ::

፲፬ ውእቱሰ አውሥአ በቃለ ቍጥዓ እንዘ ይብል ምንተ ተኃሥሢ እምኔየ ወምንተ ትብልኒ ሊተ ቦኑ ትትሐዘቢ ከመ አነ እከሪ አንሰ ኢየአምር ወኢይክል ተንሥኢ አንቲ ወቅንቲ ሐቌኪ ወክረዩ:እኮኑ:አንቲ:አስተጋባእኪ:ወመላእኪ:ኵሎ:ሰብአ:ወአምጻእ ኪ:ዘንተ:ሕማመ:ወይእዜኒ:መኑ:ይበውእ:ውስተ:ፃማ:ዚአኪ:አላ:አ ንቲ:ፈጽሚ:በከመ:ወጠንኪ:ወሰአለቶ:ዳግመ:በቃለ:ትሕትና::

፲፭ ወሶቤሃ ተንሥአ እንዘ ይትመዓዕ ወያንጐረጕር ወአመረቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መካነ ዘይከሪ ወአኃዘ መክርየ ወዘበጣ ለምድር አሐተ ዝብጠተ ወሶቤሃ ተከሥተ ወተርኅወ አፈ ዓዘቅት ዕሙቅ ወርኊብ ዘያገምር መጠነ ብዙኃ ሰብአ ወአልቦ ዘያአምሮ ለውእቱ ዓዘቅት እምቅድመ ዝንቱ ዳዕሙ ተከሥተ በጸሎተ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አሜሃ ወወደይዎን ውስቴቱ ኀቡረ ለእማንቱ ደናግል እለ አዕረፉ ወእምድኅሬሆንኒ አዕረፉ ብዙኃት አኃት ወተወድያ ውስተ ውእቱ ዓዘቅት ወቦአ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ጸሎቶን ወበረከቶን የሀ ሉ ምስለ ፍቁርን ለዓለመ ዓለም አሜን::





ያለ ማድላት ለሁሉም የምትላላክ አንዲት ሴት ልጅ ነበረች ከ ዕለታት በአንዲት ቀን የእመቤታችንን የሐሙስ ውዳሴ ማርያም ስትደግም እኅተ ክርስቶስ ያችን ሕፃን ጠርታ ላከቻት መልዕክቷን ፈጽማ ተመለሰች የጀመረችውን ጸሎት አልፈጸመችም ነበርና እንደ ገና እየጸለየች ሳለ ዳግመኛ ወደሌላ ቦታ ላከቻት ያች ልጅ በአፏ እየጸለየች ስትሄድ ከሁለት ወገን ድንግል የምትሆን የአምላክ እናት እመቤታችን ወደ'ሷ መጥታ ምን ታደክምሻለች ምን ታመላልስሻለች አሁኑ ፈጥነሽ ይህን ጸሎት ፈጽሚ እኔ ከዚህ ድካምና ሥቃይ አሳርፍሻለሁ ወደዘለዓለም እረፍት እወስድሻለሁ አለቻት ::

፲፫ ያችም ልጅ ጸሎቷን በፈጸመች ጊዜ ጥቂት የድካም ያህል ታመመች እመቤታችን የነገረቻትንም ተናግራ ወዲያውኑ ፈጥና አረፈች ከታመሙትም መካከል ሌላ ሴት ልጅ ከእሷ ጋር አረፈች ያን ጊዜ ያለ አባ ዝክረ ማርያም በቀር መቃብር የሚቆፍር አልነበረም ያን ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በትሕትና ቃል ወንድሜ ሆይ እንዴት እናደርጋለን መቃብርን ማን ይቆፍርልናል አለችው::

፲፬ እሱም በቁጣ ቃል መልሶ ከእኔ ምን ፈለግሽ ምንድነው የምትይኝ በውኑ እኔ እንድቆፍር አሰብሽን እኔ አላውቅም አልችልም አንቺ ተነሥተሽ ወገብሽን ታጥቀሽ ቆፍሪ ሰውን ሁሉ በብዛት ሰብስበሽ ይህን በሽታ ያመጣሽው አንቺ ነሽና አንቺ እንደ ጀመርሽ ፈጽሚ እንጂ ያንችን መከራ ሥቃይ ማን ይሸከማል አላት ዳግመኛም በትሕትና ቃል መልሳ ለመነችው::

፲፭ ያን ጊዜ እየተቆጣና እያንጐራጐረ ተነሣ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የሚቆፍርበት ቦታ አመለከተችውና ዶማ ይዞ አንድ ጊዜ መሬቱን ቢወጋ ያን ጊዜ ብዙ ሰውን የሚችል ጥልቅና ሰፊ የሆነ የታላቅ ጉድጓድ አፍ ተከፈተ ያን ጉድጓድ ከዚያ በፊት የሚያውቀው ሰው አልነበረም በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎት ያን ጊዜ ተከፈተ እንጂ ያረፉትን እነዚያን ደናግል እዚያ ውስጥ አስገብተው ቀበሩዋቸው ከእነሱ በ ኋላ ብዙ እኅቶች ሙተው እዚያ ጉድጓድ ውስጥ ተቀብረው ገነት መንግሥተ ሰማያትን ወረሱ ጸሎታቸውና በረከታቸው ከሕዝበ ክርስቲያን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ በውነት ያለ ሐሰት ይደረግልን ::

## ምዕራፍ ፲፫

፩ ወእንዘ ሀለወት ህየ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለአከ ኀቤሃ እኁሃ ዘድንግል ወይቤላ ንበሪ ውስተ ምድርየ ዘሀለወት መንገለ እንፍራዝ እስመ ሠናይት ይእቲ ወባቲ ዕፅ ወ ማይ ወይኄይሰኪ ሀልዎ በህየ ወሰሚዓ ትቤ ፈቃደ እግዚአብሔር ለይኩን ወእምዝ ሐተተት አህጉረ ብዙኃነ እምገዳማት ወእምደሰያት እመሂ ዳጋ ወእመሂ ፃና ዘይኄይስ ላቲ ለነቢር ወሶቤሃ ወሀበት መስቀላተ ለታቦት ወጸለየት በዐቢይ ቀኖና መጠነ ፫ቱ ሱባዔያት ከመ ይክሥት ላቲ እግዚአብሔር መካነ ዘውእቱ ፈቀደ ወገብረት ዕፃ ወወፃእ ዕፃ በፈቃደ እግዚአብሔር መንገለ ምድረ ደራ ፫ ጊዜ በበሱባዔሁ::

፪ ወእምድኅሬሁ ለአከት ኀበ መልክዓ ክርስቶስ እንዘ ትብል አይቴ ይፈቅድ ንጉሥ እምነ ደሰያት ከመ እንበር አነ ውስቴቶን ወ የአዝዝ ንጉሥ ከመ ኢይትበዓሱኒ ሰብእ በእንተ ሃይማኖት ወበእንተ ቍርባን ወቦአ መልክዓ ክርስቶስ ኀበ ንጉሥ ወነገሮ ከመዝ ወይቤሎ ንጉሥ አባሕክዋ ትንበር ፃና ወኢይስኃጣ መኑሂ ወእምዝ!ወፅአት እምዛቲ ደሴት ወግዕዘት ወበጽሐት ደሴተ ፃና ወቦአት ውስተቤተ፩ዱ መነኮስ ወነበረት ውስቴቱ ወአሜሃ ርእየቶ ለመቅደሰ ፃና እስመ:ኮነት ትበውእ ብእሲት በዘመነ አፍርንጅ::

፫ ወአርአይዋ ካዕበ ሥዕለ እግዝእት ማርያም ወላዲተ አምላክ እንተ ይእቲ ስዕለ ግብጻውያን ዘሥዕልት በቀለመ ወርቅ ወኢኮነት ቀይሕተ በህቁ ወኢጸሊመ አላ ማዕከላዊት ይእቲ ከመ ሰብአ ኢትዮጵያ ወትቤ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በአማን ትመስላ ዛቲ ሥዕል ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወይቤላሃ እለ ሀለዋ ምስሌሃ ማእዜ ርኢኪያ አንቲ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወሶቤሃ ሜጠት ቃላ ወሠወረቶን ወትቤሎን አንስ ኢርኢክዋ አላ እቤ ትመስላኑ ዛቲ ሥዕል ለእግዝእት ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወኢይቤ ርኢክዋ::

፬ ወጸመት በህየ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ፫ተ አጽዋማተ ዘውእቶን ጾመ ቍስቋም ወጾመ ስብከት ወጾመ ፵ ቅድስት ወአምስለቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለፃና ከመ መዲና በእንተ ብዝኃሙ ለሰብእ ወኢፈቀደት ትንበር





## ምዕራፍ ፲፫

፩ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እዚያ እያለች ወንድሟ ዘድንግል በእንፍራዝ በኩል በአለችው መሬቴ ላይ ተቀመጭ ጥሩ መሬት ናትና እንጨትና ውሀም አላት በዚያ መኖር ይሻልሻል ብሎ ወደ እሷ ላከ እሷም የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን አለችው ከዚህ በኋላ ትቀመጥበት ዘንድ የሚመቻትን ገዳማትና አገሮች ከደሰያት ዳጋም ሆነ ጣና ከሌሎችም ገዳማት ዘንድ ለታቦታት መስቀላትን እየሰጠች እግዚአብሔር ይገልጥላት ዘንድ ሦስት ሱባኤ ታላቅ ቀኖና አድርጋ ዕጣ ብትጥል ዕጣው በሱባኤው ልክ ሦስት ጊዜ ደራ ወጣ::

፪ ከዚህ በኋላ ስለሃይማኖትና ስለ ቍርባን እንዳይጣሉኝ ንጉሡ ያዝ ዘንድ እኔ ምቀመጥበት ከደስያት የትኛውን ይፈቅዳል ብላ ወደመልክዓ ክርስቶስ ላከች መልክዓ ክርስቶስም ወደንጉሡ ገብቶ ለንጉሡ ነገረው ንጉሡም ጣና እንድትቀመጥ ፈቅጄላታለሁ ማንም እንዳይነካት አለ ከዚህ በኋላ ከዚህች ደሴት ወጥታ ወደጣና ሄዳ ከአንድ መነኩሴ ቤት አረፈችና በካቶሊክ ዘመን ሴቶች ይገቡ ስለ ነበር የጣናን ቤተ መቅደስ አየች

፫ ዳግመኛ በወርቅ ቀለም የተሳለች የግብፃውያን ሥዕል የሆነች አምላክን የወለደች የእመቤታችን ሥዕልን አሳይዋት ያች ሥዕል እጅግም ቀይ እጅግም ጠይም ሳትሆን እንደ ኢትዮጵያ ሰዎች ነበረች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ይህች ሥዕል በውነት አምላክን የወለደች ድንግል እመቤታችንን ትመስላለች አለች ከእሷ ጋር ያሉትም አንቺ እመቤታችንን መች አየሻት አሏት መልሳ ቃሏን ሠወረችና እኔስ አልአየኋትም አምላክን የወለደች እመቤታችንን ትመስላለች አልኩ እንጂ መች አየኋት አልኩ አለቻቸው::

፬ እናታችን ቅድቅስና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሦስቱን አጽዋማት ጾመ ቍስቋምና ጾመ ስብከት ዓቢይ ጾምን ከዚያ ጾመች ጣናንም ሰው ስለሚበዛበት እንደመነኃሪያ አደረገችው ከዚህ በኋላ ብቻዋን በፀጥታ የምትኖርበት ቦታ ይገልጥላት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለየች የእግዚአብሔር መልአክም ተገልጸ

ወበእንተዝ ጸለየት ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይክሥት ላቲ መካነ ኀበ ትነብር በጽማዌ ወአስተርአያ መልአከ እግዚአብሔር ወይቤላ ሑሪ ምጽሌ እስመ ይእቲ ክፍልኪ ወሶቤሃ ለአከት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኀበ መልክዓ ክርስቶስ እንዘ ትብልአስተምህር ሊተ ኀበ ንጉሥ ከመ ያብሐኒ እንበር ምጽሌ እስመ ይእቲ መካነ ጽሙና ወይኄይስኒ እንበር ውስቴታ።

፮ ወመልክዓ ክርስቶስኒ ነገሮ ከመዝ ለንጉሥ ወንጉሥኒ ይቤ አባሕክዋ ትንበር ወእምዝ ሖረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወቦአት ምጽሌ ወሶበ ርእየታ ለይእቲ ደሴት አፍቀረታ ፈድፋደ ወኃረዩ ላቲ ቤተ ኀበ ትነበር ውስቴቱ ወረከቡ ላቲ ቤተ ዘኃደጎ እግዚኡ ወተሰደ ወቦአት ወነበረት ህየ ወእምዝ መጽአ ኀቤሃ መምህረ ደብር ወምስሌሁ መነኮሳት እለ ሀለዉ በሃይማኖተ አፍርንጅ ወይቤልዋ መኑ አብአኪ ውስተ ደብርነ አንቲ ዘዓለ ውኪዮ ለንጉሥ ወለእመ ሰምዓ ንጉሥ ይትመዓዕ ላዕሌነ ወይትቤቀለነ ሑሪ እምኔነ በሰላም ወእመ አኮ ንሕነ ንትበአስ ምስሌኪ ወአውሥአቶሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በቃለ ትሕትና ወትቤሎሙ ንጉሥሰ ይቤለኒ ኀበ ፈቀድኪ ንበሪ ወለእመ ጸላእክሙኒ አሐውር እምኔክሙ ወአኃድግ ለክሙ ደብረክሙ እመኒ ነበርኩ ዝየ ኢያነክየክሙ ምንተኒ።

፯ ወኃደግዋ ሶቤሃ ወሖሩ እስመ ሞአቶሙ በቃለ ትሕትና በከመ ይቤ መጽሐፍ ኢትማዖ ለእኩይ በእኩይ አላ ማዖ ለእኩይ በገቢረ ሠናይ ወጴጥሮስኒ ሐዋርያ ይቤ እስመ ከመዝ ውእቱ ፈቃዱ ለእግዚአብሔር ከመ በሠናይ ምግባሪክሙ ትዕስሩ አፉሆሙ ለአብዳን ሰብእ እለ ኢየአምርዎ ለእግዚአብሔር ወእምዝ ነበረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በኀድአት ወበጽሙና ወተጋብኡ ኀቤሃ ብዙኃን ሰብእ እድ ወአንስት ወነበሩ ምስሌሃ ወጸጋ ክርስቶስኒ ዘአምባ ማርያም ሀሎ ህየ ወኮኑ ፩ደ ማኅበረ ዝውእቱ ሣልሳይ ማኅበር።

፰ ወበውእቱ መዋዕል ሰምዓ ሥዕለ ክርስቶስ ዘሞተ በሃይማኖተ አፍርንጅ ከመ ሀለወት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ምጽሌ ምስለ ብዙኅ ሰብእ ወዘከመ ዓበየት ቍርባነ ተምዓ ጥቀ ወጥህረ ከመ አንበሳ ወተዓየረ ላዕሌሃ ወይቤ ቦኑ ትመውዓኒ ብእሲት አንስ አሐውር ኀቤሃ ወእቀሥፋ በአሥዋጥ ወእጸፍዕ መላትሒሃ። ወእሬስያ ትእመን ሃይማኖተ አፍርንጅ ወትቀውረብ ቍርባነ። ወሶበ ሰምዓት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወፅአት በሌሊት እምነ ምጽሌ ወጕየት ወበጽሐት ገዳመ ቈራጻ ኀበ ሀለውነ ቦቱ ይእዜ ወተኃብአት።





ወደምጽሌ ሂጂ እሷ ክፍልሽ ናትና አላት ያን ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ምጽሌ እኖር ዘንድ ከንጉሡ አስፈቅድልኝ እሷ የቀኖና ቦታ ናትና እሷ ትሻለኛለች ብላ ወደ መልክዓ ክርስቶስ ላከች ።

፮ መልክአ ክርስቶስም ለንጉሡ ነገረላት ንጉሡም ትኑር ፈቅጄላታለሁ አለ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ወደ ምጽሌ ሂዳ በአየች ጊዜ እጅግ ወደደቻት የምትኖርበት ቤት መረጡላት ባለቤቱ ትቶ የተሰደደውን ቤት አገኙላት ገብታ እዚያ ተቀመጠች ከዚያ በኋላ የደብሩ አስተዳዳሪ በካቶሊክ እምነት ያመኑ መነኮሳትን አስከትሎ መጣ እነሱም ንጉሡን የምትሳደቢ አንቺ እዚህ ትኖሪ ዘንድ ማንፈቀደልሽ ንጉሥ እዚህ መቀመጥሽን ቢሰማ ተበቅሎ ያጠፋናልና ከቦታችን በሰላም ሂጂልን ካልሆነ እኛ እንጣላሻለን አሉዋት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም በትሕትና ቃል ንጉሡስ ከፈለግሽበት ኑሪ ብሎኛል እናንተ ከጠላችሁኝ ግን እሄድላችኋለሁ ደብራችሁንም እተውላችኋለሁ እዚህ ብኖር ግን አላስነካችሁም አለቻቸው ።

፯ እነሱም ያን ጊዜ ትተዋት ሄዱ በትሕትና ቃል ድል አደርጋቸዋለችና መጽሐፍ ክፉን በክፉ አታሸንፍ ክፉን በመልካም አሸንፈው እንጂ እንደአለ ቅዱስ ጴጥሮስም የእግዚአብሔር ፈቃዱ እግዚአብሔርን የማያውቁትን ሰነፎች ሰዎች በመልካም ምግባር አፋቸውን ታስሯቸው ዘንድ ነው እንደአለ ከዚህ በኋላ እናታች ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም በፀጥታና በፅሙና ሳለች ብዙ ወንዶችና ሴቶች ወደ እሷ ተሰበሰቡና ከእሷ ጋር ሲቀመጡ የአምባ ማርያም ጸጋ ክርስቶም እዚያ ነበረ በዚያ አንድ ማኅበር ሆኑ ሦስተኛ ማኅበር ይህ ነው።

፰ በዚያን ወራት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከብዙ ሰዎች ጋር ምጽሌ እንደ አለች በካቶሊክ እምነት የሞተ ሥዕለ ክርስቶስ ሰምቶ የካቶሊክ ቍርባንንም አልቀበልም ማለቷን ተረድቶ እንደ አንበሳ እየደነፋ ተሳድቦ በውኑ ሴት እንዴት ታሸንፈኛለች ሄጄ በብረት አለንጋ እገርፋታለሁ በጥፊ እመታታለሁ በካቶሊክ ሃይማኖት አምና የኛ የካቶሊክ ቍርባን እንድትቀበል አደርጋታለሁ አለ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ይህን በሰማች ጊዜ ከምጽሌ ወጥታ ወደ ቆራጣ ገዳም ሄደችና ከዚያ ተደበቀች።

፰ ወእምህየኒ ሖረት ድቡተ ኀበ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሚካኤል ወተሰወረት በቤተ መዛግብት ወነበረት ህየ ኀዳጠ መዋዕለ ወሥዕለ ክርስቶስኒ ሖረ ወኃለፈ በታንኳ እስመ ኢያብሖ እግዚአብሔር ያኀስም ላዕሌሃ ወምክሩሂ ኮነት ከንቶ እስመ ከመዝ ይቤ መጽሐፈ መዝሙር ወያረስዮሙ ምክሮሙ ለመላእክት አኮ በፍርሃተ ቅሥፈት ወሞት ዘገሞየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አላ በእንተ ጽሑፍ ዘይብል ኢታምክሮ ለእግዚአብሔር አምላክከወስደትሰ ጽድቅ ውእቱ ብሂላ፡፡

፱ ወእምድኅሬሁ ተመይጠት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወቦአት ምጽሌ ወካዕበ ሶበ ይቤልዋ መጽአ መዝራዕተ ክርስቶስ ነሢአ መጽሐፈ መባሕት እምኀበ ንጉሥ ከመ ይሞቅሕ ክርስቲያነ እለ ኢቦኡ ውስተ ሃይማኖተ አፍርንጅ ውስተ ኵሉ ምድረ ደራ ወለኪ፣ የኃሥሥኪ ወናሁ በጽሐ ወሰሚዓ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወፅአት ሰደጭላ ወኮነ ዳኅነ ወተመይጠት ካዕበ ምጽሌ ወካዕበ ይቤሉ ፈንውዋ በታንኳ እንተ ባሕቲታ እንበለ ሐዳፍ ወኢሰብእ እንዘ ይነፍሕ ነፋስ ኃያል ከመ ይገፍትዓ ወያስጥማ ማዕበል ወትሙት፡፡

፲ ወሶቤሃ ተልዕለ ውእቱ ታንኳ እምነ ባሕር ወሰረረ ከመ ዘይሰርር ሐፅ ወሖረ ወአብጽሖ ኀበ መርሶ ወካዕበ ሰረረ ወተመይጠ ወአብጽሓ ኀበ መካን ዘቀዳሚ ለዝንቱሰ ተአምራት ስምዓ ኮኑ ብዙኃን እምነ አኃት ወአኃው ወኃብረ ቃሎሙ፡፡

፲፩ ወእምድኅሬሁ ነበረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ውስተ ምጽሌ በሰላም ወሀለዉ ምስሌሃ ሰብእ ወየአክል ጕልቆሙ ፶ ወይ ነብሩ በ፩ ቤት ወኅቡረ ይባርኩ ማዕደ ወይሴሰዩ ሲሳዩሙ በትፍሥሕት ወኢይትፈለጡ እድ ወአንስት ዘእንበለ ምስካብ እስመ አልቦ ውስተ ልቦሙ ኃልዮ ኃጢአት ወኵሎሙ ንጹሐን እሙንቱ በከመ ኮነት ስምዓ ለሊሃ እንዘ ትብል ለሰይጣነ ዝሙት ወለሰይጣነ ስስዕት አልቦሙ መባሕት ውስተ ቤትየ ወለ፩ሰ እምኔሆሙ ዘስሙ መርቆሬዎስ ዘይብልዎ ነበረ እንዘ ይሰርር በክንፍ ወየሐውር ዘጌ፡፡

፲፪ ወእንዘ ሀለወት ህየ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተንሢኦ መስተዋድይ ዘስሙ መልክዓ ክርስቶስ ወአንገሠ ርእሶ በላስታ ወመጽአ ቢኾና ምስለ ሠራዊቱ ወአገቶ ለንጉሥ ወፈቀደ ይቅትሎ ወይንሣእ መንግሥቶ፡፡





፰ ከዚያ ተደብቃ ማንም ሳያያት ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሂዳ ከእቃ ቤት ተሠወረችና እዚያ ጥቂት ወራት ቆየች እንዳያያትና እንዳይጣላት እግዚአብሔር ከእሱ ደብቋታልና ሥዕለ ክርስቶስም በታንኳ አልፎ ሄደ የሱም ምክር ከንቱ ሆነችበት መዝሙር የአለቆችን ምክር ያስረሳቸዋል እንደ አለ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የሸሸችው መገረፍንና መከራን ፈርታ አይደለም አምላክህ እግዚአብሔርን አትፈታተን የሚል ጽሑፍ አለና መሰደድም ዋጋ ነው ብላ ነው እንጂ፡፡

፱ ከዚህ በኋላ እናታችን ተመልሳ ምጽሌ ገባች ዳግመኛ መዝራዕተ ክርስቶስ ከንጉሥ ዘንድ የፈቃድ ደብዳቤ ይዞ በካቶሊክ እምነት ያላመኑትን ክርስቲያን ያሥርና ይገድል ዘንድ ከደራ ምድር ደርሶ አንቺንም ይፈልግሻል ብለው በነገሯት ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከምጽሌ ወጥታ ወደ ሰደጭላ ሄደች እንደገና ሲረጋጋ ወደ ምጽሌ ተመለሰች ዳግመኛም ሌላ ጊዜ ዋና የሚችልና ሌላም ሰው ማንም ሳይኖር ብቻዋን ኃይለኛ ማዕበል ሲነሳ ሂጂ ብላችሁ ሸኟት ማዕበል ገፍቷት ተሰጥማ ትሙት በማለት ሸኟት ፡፡

፲ በዚያን ጊዜ ያ ታንኳ ባሕሩን ለቆ እንደተወረወረ ጦር ሰማይ ለሰማይ እየበረረ ከወደቡ አደረሳት ዳግመኛ በሌላ ጊዜ እንደዚያው ተመልሶ ቀድሞ ከነበረችበት ቦታ አድርሷታል ይህንን ተአምራት ከወንድሞችና ከእኅቶች ብዙዎች ምስክር ሁነዋል፡፡

፲፩ ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በሰላም ምጽሌ ተቀምጣ ሳለች ሃምሣ የሚሆኑ ሰዎች ከእሷ ጋር በአንድ ቤት በአንድነት ማዕድ እየባረኩ በደስታ ይመገቡ ነበር ሴቶችና ወንዶች ያለመኝታ ጊዜ አይለያዩም ነበር የኃጢአት ሐሳብ በልባቸው ውስጥ አልነበረምና ሁላቸውም ንጹሐን ነበሩ የስስትና የዝሙት አጋንንት በቤቴ መሠልጠን አይችሉም ብላ እሷ እራሷ ምስክር እንደሆነች ከእነዚያ ማኅበርተኞች መካከል አንዱ በክንፍ እየበረረ ወደ ዘጌ የሚሄድ ስሙ መርቆሬዎስ የሚባል ነበረ፡፡

፲፪ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከእዚያ ሳለች በጉልበቱ እራሱን በላስታ ያነገሠ ስሙ መልክዓ ክርስቶስ የሚባል አንድ ሽፍታ ተነሣ ገድሎ መንግሥቱን ይቀማ ዘንድ ቢኾና ደርሶ ከሠራዊቱ ጋር ንጉሡን ከበበ፡፡

፲፫ ወሶቤሃ ደንገፀ ወፈርሃ ወበፅዐ ብፅዓተ እንዘ ይብል ለእመ ወሀበኒ እግዚአብሔር ኃይለ ወመዊዓ ወለእመ አግብኦ ውስተ እዴየ ለዝንቱ ዓላዊ አነ አእምን በሃይማኖተ ዲዮስቆሮስ ቅዱስ ወእክሀድ ሃይማኖተ ልዮን ርኩስ ወኮነ ሎቱ በከመ ይቤ ወሞኦ ወቀተሎ ወገብአ በሰላም ወእምዝ አአደ አዋዴ እንዘ ይብል ኩሉ ዘየአምን በሃይማኖተ አፍርንጅ እምድኅረ ሰምዐ ቃልየ ወተዓደወ ትእዛዝየ ይትበርበር ቤቱ ወትትኳነን ነፍሱ መዊተ ወይግብኡ ክርስቲያን እለ ተሰዱ በበሀገሮሙ ወበበርስቶሙ ወኮነ ሎሙ ፍሥሓ ዐቢይ ለክርስቲያን ወአተዉ አብያቲሆሙ እንዘ ይሴብሕዎ ወየአኩትዎ ለእግዚአብሔር።

ምዕራፍ ፲፬

፩ ወእምዝ ፈነወ ንጉሥ መልእክተ ብሥራት ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ይብል ናሁ አመንኩ ሃይማኖተ ክርስቲያን ወሠዓርኩ ሃይማኖተ አፍርንጅ ተፈሥሒ ወተሐሠዪ እምይእዜሰ ይኩን ሰላም ማዕከሌየ ወማዕከሌኪ ወበጺሖ ላእከ ንጉሥ ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወወሀባ መጽሐፈ መልእክት እንተ ትብል ከመዝ ወተመጠወት ወአንበበት ወተፈሥሐት ወየበበት በዐቢይ ቃል በከመ ይቤ መጽሐፈ መዝሙር ኩልክሙ፡አሕዛብ፡ጥፍሑ፡እደዊክሙ፡ወየበቡ፡ለእግዚአብሔር፡በቃለ፡ትፍሥሕት፡ወካህናትኒ፡እለ፡ሀለዉ፡ምስሌሃ፡ኃለዩ፡እንዘ፡ይብሉ፡ንሴብሖ፡ለእግዚአብሔር፡ስቡሐ፡ዘተሰብሐ፡ወኮነ፡ውእቱ፡ዕለት፡አመ፡፫ለ ወርኃ፡ሐምሌ።

፪ ወበሳኒታ ይቤላ ውእቱ ላእከ ንጉሥ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ፈነውኒ እሑር ጣና እስመ ሀየኒ አዘዘኒ ንጉሥ ከመ አብጽሕ ዘንተ ብሥራተ ወትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለአባ ዘሥላሴ አብጽሖ ለዝንቱ ላእክ ኀበ ጣና ወበሀየኒ አሥግር ሊተ ዓሣ ከመ ይኩንኒ ጸብሐ ለበዓለ ጴጥሮስ ወጳውሎስ።

፫ ወይቤላ እሆ ወባረከቶ ወፈነወቶ ወሖረ ምስለ ውእቱ ላእከ ንጉሥ ወአብጽሖ ጣና ወሶቤሃ አውረደ መሣግሪሁ ወወረወ ውስተ ባሕር ወተእኅዘ ሎቱ ዓሣ ወወዓለ እንዘ ያሠግር ወተመይጠ ምጽሌ ወአተወ እንዘ ይጸውር ፲ወ፫ ዓሣተ ወአቅረበ ቅድመ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወይቤላ ናሁ እምጻእኩ ዘወሀበኒ እግዚአብሔር በበረከተ ዚአኪ ወትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እሉ ፲ወ፪ ዓሣት ከመ ሐዋርያት እሙንቱ ወ፩ ከመ ሊቆሙ ክርስቶስ ውእቱ በረከተ ሐዋርያት፡ወበረከተ ሊቆሙ ክርስቶስ ይኅድር ላዕሌክ ወይቤ አሜን በአማን መንክር ውእቱ ዝንቱ ዘኮነ እንዘ ኢይትዌሰክ ወኢይንተግ እምዝንቱ ኍልቍ።





፲፫ ንጉሡም ያን ጊዜ ፈርቶ እጅግ ደንግጦ እግዚአብሔር ኃይልንና ማቸነፍን ቢሰጠኝና ይህን ወንጀለኛ በእጄ አሳልፎ ቢሰጥ እኔ ቅዱስ በሆነ በዲዮስቆሮስ ሃይማኖት አምኜ ርኩስ የሆነ የልዮንን ሃይማኖት እክዳለሁ ብሎ ተሳለ እንደተሳለውም ሆነለትና ድል አድርጎ ገድሎ ተመለሰ ከዚህ በኋላ ቃሌን ሰምቶ አልቀበልም ብሎ በካቶሊክ እምነት ያመነ ቢኖር ሀብቱ ይወረስ ቤቱ ይተኮስ ሰውነቱ በሞት ይቀጣ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ጸንተው የተሰደዱ ክርስቲያን ወደ አገራቸውና ወደ ርስታቸው ይመለሱ ብሎ አዋጅ ነጋሪ ላከ ለክርስቲያን ታላቅ ደስታ ሆኖ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደ አገራቸው ተመለሱ።

ምዕራፍ ፲፬

፩ ዳግመኛም ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የካቶሊክ ሃይማኖት ክጄ በተዋህዶ ሃይማኖት አምኛለሁና እጅግ ደስ ይበልሽ ከእንግዲህ ወዲህ በእኔና በአንቺም መካከል ሰላም ይሁን ብሎ መልእክተኛ ላከ የንጉሡ መልክተኛም ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ደርሶ የንጉሡን ደብዳቤ ሰጣት እሷም ተቀብላ አንብባ መዝሙር አሕዛብ ሁላችሁ እጃችሁን እያጨበጨባችሁ በደስታ ቃል ለእግዚአብሔር እልል በሉ እንደ አለ ከደስታዋ የተነሣ ቃሏን ከፍ አድርጋ እልል አለች ከሷ ጋራ ያሉትም ካህናት የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን እያሉ አመሰገኑ ይህም ዕለት ሐምሌ ሦስት ቀን ነው።

፪ በማግስቱም የንጉሥ መልዕክተኛ እናታችንን ጣና ሄጄ የንጉሥ የምሥራች አደርስ ዘንድ ስደጅኝ አላት እናታችን ቅድስትና፡ቡርክት፡ወለተ፡ጴጥሮስም፡ለአባ፡ዘሥላሴ፡ይህንን፡መልክተኛ፡ወደ፡ጣና፡አድርስህ፡በዚያው፡ለጴጥሮስና፡ለጳውሎስ፡በዓል፡ለወጥ፡ይሆነኝ ዘንድ አሣ አጥምደህ ይዘህልኝ ና አለችውና ባርካው ላከችው።

፫ እሱም እሺ ብሎ ከንጉሥ መልክተኛ ጋራ ወደ ጣና ሄደ በዚያን ጊዜ መረቡን ወደ ባሕር ጥሎ ዓሣ ሲይዝ ዋለና አሥራ ሦስት ዓሣ ተሸክሞ ወደ ምጽሌ ሄዶ ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በአንቺ በረከት እግዚአብሔር የሰጠኝ ዓሣ ይህ ብሎ ሰጣት እናታችንም ተቀብላ እነዚህ አሥራ ሁለቱ ዓሣዎች የሐዋርያት ምሳሌ ናቸው አንዱ እንደአለቃቸው ክርስቶስ ምሳሌ ነው የሐዋርያትና የክርስቶስ በረከት በአንተ ላይ ይደር አለችው ይሁን ይደረግልኝ በእውነት ያለ ሐሰት አለ ከዚህ ቁጥር ሳይጐል ሳይጨምር በዚህ ልክ መሆኑ ድንቅ ነው።

፩ ወበሳኒታ ኮነ በዓለ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ወአግበረቶ ጸብሐ ለውእቱ ዓሣ ወአምስሐት ኵሎ ማኅበረ ወኵሎ ሰብአ ደብር ወእምድኅረ ኮነ ዝንቱ በወርኃ ሐምሌ ሞተ ንጉሥ ሱስንዮስ አመ ፲ ለወርኃ መስከረም በበዓለ ጼዴንያ ወነግሠ ህየንቴሁ ወልዱ ፋሲለደስ ወአርትዐ ሃይማኖተ ወበውእቱ መዋዕል መጽአ አባ አጽፌ ክርስቶስ ዘምጽሌ መምህር ዘነበረ ሙቁሐ በሀገረ ቴራ ወካልአንሂ መነኰሳት እለ ተሰዱ ወጉዩ እምሃይማኖተ አፍርንጅ አተዉ።

፪ ወእምድኅሬሁ ነበረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዓመተ ፍጽምተ እስመ በፅዓት ብፅዓተ ለቅዱስ ፋሲለደስ እንዘ ትብል ለእመ ተመይጠት ሃይማኖት እነብር ዓመተ ወእትመጦ ቍርባነ በዛቲ መቅደስከ ወነበረት እንዘ ትትሜጦ በእደዊሆሙ ለስዱዳን ካህናት ወአመ ይብል ቀሲስ ፈኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ትኔጽር ገሃደ ርደተ መንፈስ ቅዱስ።

፫ ወሶበ ይከውን ምሴተ ትበውእ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወትቀውም ቅድመ ሥዕላ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ከመ ዓምድ ትኩል ወኢታሰምክ ኀበ ዓረፍት ወኢኀበ ዓምድ ወትጼሊ ወታስተበቍዕ በእንተ መድኃኒተ ነፍሳ ወበእንተ ድኅነተ ሕዝብ ወትበይት ኵላ ሌሊተ እንዘ ትጼሊ እንበለ ዕረፍት ወሶበ ይከውን ጽባሐ ወይሠርቅ ፀሐይ ወይትነበብ ስንክሳር ወይትፌጸም ጸሎተ ሕትመት ትወፅእ፡እምቤተ፡ክርስቲያን፡ወተአቱ፡ቤታ፡ወታነብብ፡ወንጌለ፡ዘዮሐ ንስ፡ወኵሎ፡አሚረ፡ትገብር፡ከመዝ፡ወኮነት፡ከመ፡አባ፡አርሳንዮስ።

፬ ወጕልቈ ዓመታቲሃ በውእቱ ዓመት ፴ወ፱ ወኮነ ያሜክራ ውኂዘተ ደም ብዙኅ ወተሐምም ፈድፋደ ወጊዜ ቀዊሞታ ትስእል ኀበ ሥዕለ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወትቤላ እስእለኪ ኦ እግዝእትየ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ከመ ይንጽፍ ሊተ ዝንቱ ደም በስእለትኪ እስመ ተመንደብኩ ፈድፋደ ወተናገረታ ዛቲ ሥዕል ወትቤላ ምንትኑ ታነጥዪኒ ዘልፈ ወናሁ ሰማዕኩ ጸሎተኪ ወርኢኩ ሕማመኪ ወአይበስኩ ለኪ ትክቶ ደምኪ እምይእዜ ዳግመ ኢያስተርኢ ደም ግሙራ እምኔኪ ወሶቤሃ የብሰ ትክቶ ደማ እንዘ ውርዝውት ይእቲ ወኢበጽሐ ዕድሜሃ ለኃዲገ ትክቶ።





፩ በማግስቱ በጴጥሮስና በጳውሎስ በዓል ያንን ዓሣ ወጥ ሠርታ የማኅበሩን ሰዎችና የደብሩን ሰዎች መገበቻቸው ይህ በሐምሌ ወር ተደርጐ ንጉሡ ሱስንዮስ በጼዴንያ በዓል መስከረም አሥር ቀን ሙቶ ስለ እሱ ፈንታ ልጁ ፋሲለደስ ነገሠና ተዋህዶ ሃይማኖትን አቀና አስፋፋ በዚያን ዘመን በቴራ አገር ታስሮ የነበረ የምጽሌ መምህር አባ አጽፌ ክርስቶስ መጣ ሌሎችም የካቶሊክ ሃይማኖት አንቀበልም ብለው የተሰደዱ መነኩሳት ተመልሰው ወደአገራቸው ገቡ ::

፪ ከዚህ በኋላ እናታችን ዓመት ምጽሌ ተቀመጠች ለቅዱስ ፋሲለደስ የተዋህዶ ሃይማኖት ብትስፋፋ በምጽሌ ዓመት ተቀምጬ በአንተ ቤተ መቅደስ ቍርባን እቀበላለሁ ብላ ብፅአት ገብታ ነበርና በተሰደዱት ካህናት እጅ ሥጋ ወደሙን ስትቀበል ቆየች ቆማ በ ምታስቀድስበት ጊዜ ቄሱ ፈኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሲል የመንፈስ ቅዱስን መውረድ በገሐድ ትመለከት ነበር ::

፫ በመሸ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብታ አምላክን ከወለደች ከመቤታችን ከቅድስት ድንግል ሥዕል ፊት እንደተተከለ ምሰሶ ወዲያና ወዲህ ሳትል ቁማ ስለነፍሷ ድኅነትና ስለ ሕዝብ ድኅነት ያለ እረፍት ሌሊቱን ሁሉ በጸሎት ታድር ነበር ነግቶ ጥዋት በሆነና ስንክሳር ተነቦ ኑዛዜ በተደረገ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ወጥታ ወደቤቷ ገብታ የዮሐንስን ወንጌል ታነብ ነበር ሁልጊዜ፡እንደዚህ፡ታደርጋለች፡ሥራዋ እንደ አባ አርሳንዮስ ነበር።

፬ በዚያን ጊዜ እድሜዋ ሠላሳ ዘጠኝ ነበርና የሴቶች ደም እጅግ ያስቸግራት ነበር ቁማ በምትጸልይ ጊዜ ወደመቤታችን ሥዕል ቀርባ ይህንን አጥፊልኝ እመቤቴ ሆይ ባንቺ ልመናና አማላጅነት ይህ ደም ይድረቅልኝ አለች ያችም ሥዕል ዘወትር ለምን ትጨቀጭቂኛለሽ ጸሎትሽን ሰምቼ መቸገርሽን አይቼ የመርገም ደምሽን አደረቅሁልሽ ከእንግዲ ወዲህ ሁለተኛ የመርገም ደም አያገኝሽም አለቻት በዚያን ጊዜ እድሜዋ ያነሰ ወጣት ስትሆን የመርገም ደም ጨርሶ ተዋት።

፳ ወተመሰለት ከመ ብእሲት እንተ ለከፈት ጽንፈ ልብሱ ለእግዚእ ኢየሱስ በከመ ይቤላ ሃይማኖትኪ አሕየወተኪ ወእምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ቆመት በሃይማኖት ቅድመ ሥዕላ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወተፈወሰት እምዝንቱ ሕማም ወእሉሰ ስዱዳን ነበሩ ኵሎ ዕለተ እንዘ ይሔውጽዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወይዜያነዉ ምስሌሃ ኵሎ መከራ ወምንዳቤ ዘረከቦሙ በስደት ለለ፩፩ ወዓዲ ይትፌሥሑ በተመይጦቶሙ ወይትበሃሉ በበይናቲሆሙ በከመ ይቤ ጳውሎስ ወይእዜሰ አልፀቀት ሕይወትነ እንተ ተሰፈውናሃ ወኃለፈት ሌሊት ወመጽአ መዓልት ወዓዲ ይብሉ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክነ ዘኢያግብአነ ውስተ መሥገርተ ማዕገቶሙ ለአፍርንጅ ነፍስነሰ አምሰጠት ከመ ዖፍ እመሥገርት ነዓዊት መሥገርትሰ ተቀጥቀጠት ወንሕነሰ ድኅነ::

## ምዕራፍ፲፫ የዓርብ

፩ ወበውእቱ መዋዕል ገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተዝካረ አቡነ አባ ዘርአ ዮሐንስ እስመ ውእቱ ሞተ በአምባ ማርያም እምኀበ ተሰደ ወወሀበት ብዙኃ መባልዕተ ወስቴያተ ለሰብአ ውእቱ ደብር ወኵሉ ማኅበር ወፈጸመት ኵሎ ዘባቲ ወኢያትረፈት ለጌሰም በከመ ይቤ ወንጌል ኢትበሉ ለጌሠም እስመ ጌሠምሰ ትሄሊ ለሊሃ ለርእሳ ወርእዮ ፩ዱ መነኮስ እንጐርጐረ ወይቤ ምንትኑ ዝንቱ ውሂብ ዘእንበለ ዓቅም እንዘ አልብነ ሲሳየ ዕለት አኮኑ በእንተ ውዳሴ ከንቱ ውእቱ ወንሕነሰ ምንት ንበልዕ ጌሠመ ወገሠጾቶ እኅተ ክርስቶስ ወትቤሎ፡አ፡ነዳየ፡አእምሮ፡ወኀጡአ፡ተስፋ፡ከማከኑ፡ነዳየ፡ረሰይኮ፡ለእግዚአብሔር፡አኮኑውእቱ፡ባዕል፡ወየአክል፡ለኵሉ፡ለዘጸውዖ፡ዮምኒ፡ውእቱ፡ወጌሠምኒ ውእቱ::

፪ ወይእተ ጊዜ መጽኡ ልዑካን እኂዞሙ እክለ ዘኢሐለዩ ወዘኢያእመሩ ቀዲሙ እምለፌ ፱ ጫን ወእምለፌ ፬ ወእለ ርእዩ ዘንተ አንከሩ ወሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ወእምድኅረ ኃለፈ መዋዕለ ስደት በተፍጻሜተ ፩ዱ ዓመት ጸለየት ካዕበ ፫ ሱባዔ በዐቢይ ቀኖና እንዘ ትቀውም ቅድመ ዛቲ ሥዕል ዘተናገረታ ቀዲሙ ወትቤላ እስእለኪ ኦ እግዝእትየ ከመ ትክሥቲ ሊተ መካነ ዘአኀድር ቦቱ ወትሠርሕኒ ኀበ ኮነ ፈቃድኪ ወፈቃደ ወልድኪ::





፳ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልብሱን ጫፍ የዳሰሰች ሴትን ሃይማኖትሽ አዳነሽ እንዳላት በሃይማኖት እሷን መስለቻትና አምላክን የወለደች የመቤታችን ሥዕል ፊት ቁማ ለምና ከዚህ በሽታ ዳነች ከስደት የተመለሱ ሰዎች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ይጐበኟትና ከሷ ጋር በስደት ጊዜ የደረሰባቸውን መከራ እያንዳንዳቸው እያነሱ ይጨዋወቱ በመመለሳቸውም ተደስተው ቅዱስ ጳውሎስ ጨለማ አልፎ ቀን ሆነ እንድናለን ብለን ተስፋ እንዳደረግነ ዛሬ ሕይወታችን ለመዳን ደርሰች እንዳለ እነሱም እንደዚህ ይሉ ነበር በካቶሊክ ክሕደት ወጥመድ ያልጣለን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ከተጠመደ ወጥመድ እንደምታመልጥ ወፍ ነፍሳችንም አመለጠች ተባባሉ

## ምዕራፍ፲፫ የዓርብ

፩ በዚያን ወራት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የአባ ዘርዓ ዮሐንስን መታሰቢያ ተዝካር ደገሰች እሱ በተሰደደበት በአምባ ማርያም ሞቶአልና በዚያ ደብር ላሉ ሰዎችና ለማኅበሩ ብዙ መብልንና መጠጥን ለነገ ሳታስቀር ሰጠች ወንጌል ለነገ አትበሉ ነገ ለራሷ ታስባለች እንዳለ አንድ መነኵሴ እኛ የዕለት ምግብ ሣይኖረን ያለአቅም ይህን ሁሉ መስጠት ምንድነው ውዳሴ ከንቱ ፍለጋ ነውን ብሎ አንጐራጐረ በዚህን ጊዜ እኅተ ክርስቶስ ተሥፋ ያጣህ የአዕምሮ ድሀ የሆንክ አንተ እንደአንተ እግዚአብሔርን ድሀ አደረግኸውን እሱ በእምነት ለለመነው ዛሬም ነገም ዘወትርም የሚሠጥ የማያልቅበት ባለጸጋ ነውና አለችው::

፪ በዚህም ጊዜ ቀድሞ ያላወቁትና ያላሰቡት ባንድ በኩል ዘጠኝ ጭነት ባንድ በኩል አራት ጭነት የያዙ መልዕክተኞች በወዲያና በወዲህ በኩል መጡ ይዘው የመጡትን ያዩ ሰዎችም እጅግ አድንቀው እግዚአብሔርን አመሰገኑ የስደት ወራት አልፎ የዓመት መጨረሻ ሲሆን እናታችን በታላቅ ሱባኤና ቀኖና አስቀድሞ ከአናገረቻት ሥዕል ፊት ቁማ እመቤቴ ሆይ አንቺ የምትወጂውና ልጅሽ የሚፈቅደው የምኖርበትን ቦታ ትገልጭልኝ ዘንድ ብላ በሦስት ሱባኤ ጠየቀቻት ::

፫ ወተናገረታ ካዕበ ይእቲ ሥዕል ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤላ ሑሪ ዘጌ እስመ ኮነ ሥምረትየ ወሥምረተ ፍቁር ወልድየ ወሶበ ሰምዓት ዘንተ ቃለ እምሥዕለ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አስተጋብአቶሙ ለአባ ዓጽፈ ክርስቶስ መምህር ዘምጽሌ ወለመነኮሳት ወተሰነአለቶሙ ወነገረቶሙ ዘከመ ተሐውር ዘጌ ወካዕበ ሰአለቶሙ ወአስተብቍዓቶሙ ከመ ኢያብኡ አንስተ ውስተ ምጽሌ እስመ ረከበት ግዘተ እምገድለ አቡነ አፍቅረነ እግዚእ ከመ ኢይባእ ፍጥረተ አንስት ውስተ ይእቲ ደሴት ወይቤልዋ ኦሆ ወይእተ ዕለተ አውፅእዎን ለአንስት እምህየ ወዳግመኒ ከመ ኢያብእዎን አውገዘ አባ ዓጽፈ ክርስቶስ ወእምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እምድኅረ አቀመት ዘንተ ሥርዓተ ተሰነአለቶሙ ወወፅአት በይእቲ ዕለት ወቤተት በዖፍ ኀገር።

፬ ወፈለሰት እምህየኒ ወሖረት ወቦአት ገዳመ ዘጌ ወነበረት ውስቴቱ ወተጋብኡ ኀቤሃ ብዙኃን ሰብእ እድ ወአንስት አዕሩግ ወሕፃናት ወራዙት ወደናግል ወይመጽኡ እምሥራቅ ወእምዕራብ ወእንተ ጸብሐት ይትዌሰኩ ዝ ውእቱ ራብዐይ ማኅበር።

፭ ወእምዝ ቦአ ሰይጣን ውስተ ልቦሙ ለሰብአ ክብራን፡አስተናሥአሙ ላዕሌሃ ወሖሩ ኀቤሃ ምስለ መምህሮሙ ወይቤልዋ መኑ አብአኪ ዝየ ወመኑ ወሀበኪ ዘንተ ገዳመ አኮኑ ዘዚአነ ውእቱ ወይእዜኒ ንብለኪ ፃኢ በሰላም ወእመ አኮ ንትበዓስ ምስሌኪ ወናውዒ ቤተኪ ወእምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተወክፈቶሙ በፍቅር ወበትሕትና ወአቅረበት ሎሙ መብልዓ ወመስቴ ወበልዑ ወጸግቡ ወአሠነዩ ልቦሙ ወተመይጡ ኀበ ኂሮሙ ወኃደግዋ ወሖሩ እስመ ከመዝ ይቤ መጽሐፍ ለእመ ርኅበ ጸላኢከ አብልዖ ወለእመ ጸምዓ አስትዮ ወዘንተ ለእመ ገበርከ አፍሐመ እሳት ታስተጋብእ ዲበ ርእሱ።

፮ ወአሜሃ መጽኡ ሰሚዖሙ ዘንተ ነገረ አባ ጸዋሬ መስቀል ዘፃና መምህር ወአባ መንክር ዘወንጬጥ ከመ የሐውጽዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወነገረቶሙ ዘከመ ይቤልዋ ሰብአ ክብራን ወሰሚያ አባ ጸዋሬ መስቀል ይቤላ ኢትኅዝኒ ለእመ ፈቀድኪ ትንበሪ ዝየ አልቦ ዘይከልአኪ ንልአክ ኀበ ንጉሥ ወውእቱ ይዌስን ለኪ ዘንተ ገዳመ ወእመ አኮንበሪ ገዳመ ቈራጻ ወእሁበኪ አነ ወባሕቱ ኦሆ በልነ ንንግርኪ አሐተ ነገረ ንዒ ቤተ መንዞ ወንንበር ንሕነኒ ምስሌኪ ከመ ይተርጕም ለነ ጸጋ ክርስቶስ መጽሐፈ ሐዊ ወእምዕፁብ ኦሆ አበልዋ ዝኒ ጥበበ እግዚአብሔር ውእቱ እስመ ፈቀደ ከመ ይሰውራ እምሕማመ ብድብድ።





፫ ያችም ሥዕል ዳግመኛ እናታችንን ወደ ዘጌ ሂጂ የኔ ፈቃድና የልጄ ወዳጄ ፈቃድ ሆኖአልና አለቻት ከመቤታችን ሥዕል ይህን በሰማች ጊዜ የምጽሌ መምህር አባ አፅፈ ክርስቶስንና መነኮሳትን ሰብስባ ዘጌ እንደምትሄድ ነገረቻቸውና ተሰናበተቻቸው ዳግመኛም ሴቶችን ወደ ምጽሌ እንዳያስገቡ አደራ አለቻቸው ሴቶች እንዳ ይገቡ ግዝት እንደሆነ ከአቡነ አፍቅረነ እግዚእ ገድል አግኝታለችና እነሱም እሽ አሏትና ሴቶችን በዚያች ዕለት ከምጽሌ አስወጡ ዳግመኛም አባ አጽፈ ክርስቶስ እንዳያስገቧቸው አወገዘ እናታችን፡ቅድስት፡ወለተ፡ጴጥሮስ፡ይህን፡ሥርዓት፡ከሠራችና፡ከነገረቻቸው በኋላ ተሰናብታ በዚያች ዕለት ወጥታ በዖፍ ኀገር አደረች ።

፬ ከዚያ ተነስታ ወደ ዘጌ ገብታ እዚያ ተቀመጠች ብዙ ወንዶችና፡ሴቶች፡ሕፃናትና፡ወጣቶች፡ወንዶች፡ደናግል፡ሴቶች፡ከምሥራቅና፡ከምዕራብ፡ከሰሜንና፡ከደቡብ እየመጡ እሷ ካለችበት ተሰበሰቡ ብዛታቸውም፡ዕለትዕለት፡እየጨመረ ሄደ አራተኛ ማኅበር ይህ ነው።

፭ ከዚህ በኋላ ሰይጣን በክብራን ሰዎች ልብ አድሮ አነሣሣቸውና ከነአርድዕቶቻቸው እሷ ከአለችበት ሂደው እዚህ ቦታ እንድትኖሪ ማን አሰለጠነሽ ይህን ገዳም ለአንቺ ማን ሰጠሽ አሁንም የኛ ቦታ ነው በሰላም ወጥተሽ ሂጅ ከአልሆነ ተጣልተን ቤትሽን እናቃጥላለን አሏት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በፍቅርና በትሕትና ተቀበለቻቸውና የሚበሉት የሚጠጡትን ሰጠቻቸው በልተው ጠግበው ልባቸውን ደስ አሰኝተው ወደ ደግነት ተመልሰው ትተዋት ሄዱ መጽሐፍ ጠላትህ ቢራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍህም ትከምራለህና እንደአለ።

፮ ያን ጊዜ የጣና መምህር አባ ጸዋሬ መስቀልና የወንጬጥ አባ መንክር ይህን ነገር ሰምተው እናታችንን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ይጉበኟት ዘንድ መጡ የክብራን ሰዎች እንዳሏት ሰምቶ አባ ጸዋሬ መስቀል አትዘኝ እዚህ መኖር ከፈለግሽ ይሁን ብሎ ይወስናልና ካልሆነም በቆራጣ ገዳም ኑሪ አላት እኔ እሰጥሽ አለሁና እነሆ አንድ ነገር እነግርሽ ዘንድ ወደ ቤተ መንዞ ነይ እኛ ከአንቺ ጋራ ተቀምጠን ጸጋ ክርስቶስ መጽሐፈ ሐዊን እንዲተረጕምልን አላትና ከብዙ ሀተታ በኋላ እሽ አሰኛት ይህም የእግዚአብሔር ጥበብ ነው ከተላላፊ በሽታ ይሰውራት ዘንድ ወዶአልና ።

፯ ወካልአንሂ ቅዱሳን እለ አቅደሙ አእምሮ ዜነውዋ ወይቤልዋ ናሁ ይመጽእ ሕማመ ብድብድ ወይቀትል ብዙኃነ እምደቂቅኪ ወባሕቱ አንቲ ፃኢ ከመ ትትርፊ ወትኩኒ አርአያ ለኩሉ ወቦ እለ ይቤሉ አስተርአየ ላቲ እንዘ ይዌስቅ ቀሥቶ ብድብድ ወይቤላ ፃዒ ወእምዝ ሖረት ምስሌሆሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወበጽሐት ቤተ መንዞ ወነበረት ህየ ወእምድኅሬሁ መጽአ ፩ዱ ብእሲ አቡሃ ለክርስቶስ ስና ወቦአ ዘጌ ኀበ ሀለዉ ማኅበር ወተወከፍዎ ወሐመ በይእቲ ዕለት ሕማመ ብድብድ ወሞተ በሣልስት ዕለት ወበውእቱ መዋዕል ሐሙ ብዙኃን መነኮሳት ወመነኮሳይያት እምውእቱ ሕማመ ብድብድ ወሶበ ሰምዓት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትቤ አነኒ አሐውር እሙት ምስለ ደቂቅየ ወእሳተፍ ምስሌሆሙ ሕማመ ወኵሎ መከራ ዘይበጽሕ ላዕሌሆሙ::

፰ ወአውገዝዋ ወአምሐልዋ ከመ ኢትሑር ወይቤልዋ ለእመ ሖርኪ አንቲ ወሞትኪ ምስሌሆሙ አልቦ ዘይበቍዖሙ ለሕሙማን ወዘይቀብርዎሙ አላ ንፌኑ ሰብአ ዘይጸውርዎሙ ለሕሙማን ወዘይቀብርዎሙ ለሙታን:: ወእምዕፁብ አኅደግዋ ሐዊረ ወፈነዉ ሰብአ በከመ ይቤሉ ወሞቱ አሜሃ በውእቱ ብድብድ ፶ወ፮ ሰብአ ወፈጸሙ ገድሎሙ ወቦኡ ውስተ መንግሥተ ሰማያት በከመ ተካየዶ እግዚአብሔር ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ወይቤሎ ለእለ ሞቱ ደቂቅከ በሕማመ ብድብድ እኌልቆሙ ምስለ ሰማዕታት ወአወፍዮሙ ለከ በመንግሥተ ሰማያት ጸሎቶሙ ወበረከቶሙ የሃሉ ምስለ ፍቁሮሙ ለዓለመ ዓለም አሜን::

፱ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ነበረት ቤተ መንዞ ወወጠነት ሐድሶ ሕንፃሃ ለቤተ ክርስቲያን ዘተመዝበረት ወይእተ አሚረ መጽአት እማ ክርስቶስ ዕበያ ከመ ተሐውጻ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወበህየ ሐመት በፈቃደ እግዚአብሔር ወሶበ አኃዛ ጽንዓ ሕማም ወአልፀቀት ለመዊት ፈነወታ ሬማ ወእንዘ ሀለወት በታንኳ እንበለ ትብጻሕ ደሴተ ሬማ ሞተት ወተቀብረት በሬማ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ነበረት ቤተ መንዞ ወሰምዓት በህየ ወበከየታ ለእማ::





፯ አስቀድመው ያወቁ ሌሎችም ቅዱሳን ተላላፊ በሽታ መጥቶ ከልጆችሽ ብዙዎችን ይገድላቸዋል ነገር ግን አንቺ ለሁሉ አርአያ ትሆኚ ዘንድ ከዚህ ገዳም ውጪ ብለው ነግረዋታልና ተላላፊ በሽታ ጦሩን እየወረወረ ውጪ ሲላት ታይቷታል የሚሉም አሉ ከዚህ በ ኋላ እናታችን ከነሱ ጋራ ቤተ መንዞ ሄዳ እዚያ ተቀምጣ ሳለች የክርስቶስ ስና አባት የሚሆን አንድ ሰው መጥቶ ማኅበሩ ካለበት ከዘጌ ገባ እነሱም ተቀበሉትና አስተናገዱት በዚያች ዕለት ያ ሰው በተላላፊ በሽታ ታሞ በሦስተኛ ቀን አረፈ በዚያን ወራት ብዙ ወንዶችና ሴቶች መነኮሳት በተላላፊ በሽታ ተይዘው ታመሙ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም እኔም ሄጄ ከልጆቼ ጋራ የሚደርስባቸውን መከራና ሕማምን ተሣትፌ ልሙት አለች

፰ አንቺ ሄደሽ ከነሱ ጋር ከሞትሽ የሚጠቅማቸው የለም ካልሆነ የታመሙትን የሚሸከማቸውንና የሞቱትን የሚቀብራአቸው ሌላ ሰው እንልካለን ብለው እንዳትሄድ አማልዋትና ገዘትዋት ከብዙ ሐተታ በኋላ ከመሄድ አስቀሯት እንደአሉም ሰው ሰደዱ በዚያን ጊዜ በዚህ በተላለፊ በሽታ ሙተው ተጋድሎአቸውን ፈጽመው መንግሥተ:ሰማያት:ገቡ እግዚአብሔር ለአባታችን ለተክለሃይማኖት ልጆችህ በተላላፊ በሽታ ቢሞቱ ከሰማዕታት ጋራ ቆጥሬአቸው በመንግሥተሰማያት ታላቅ ዋጋን ስለአንተ ብዬ እሰጣቸዋለሁ እንደአለ ጸሎታቸውና በረከታቸው ከሁላችን ጋራ ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን::

፱ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም በቤተ መንዞ ተቀምጣ ፈርሳ የነበረችውን የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ማደስ ጀመረች በዚያን ጊዜ እናቷ ክርስቶስ ዕበያ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ትጐበኛት ዘንድ መጥታ በእግዚአብሔር ፈቃድ በዚያው ታመመች እናታችንም ለሞት የሚያደርስ ታላቅ በሽታ መሆኑን አውቃ በታንኳ ወደ ሬማ ላከቻት:ታንኳላይ:ሳለች:ሬማ:ሳትደርስ:አርፋ:በሬማ:ተቀበረች:እና ታችን:ቅድስትና:ቡርክት:ወለተጴጥሮስ ግን በቤተ መንዞ ሳለች ሰምታ በዚያው ለእናቷ አለቀሰች::

፲ ወቤተ ክርስቲያንኒ ተሐንፀት በፈቃደ እግዚአብሔር እንዘ ይእቲ ተቀድሕ ማየ ወትጸውር አዕባነ ወእምዝ ፈነወት ሰብአ በታንኳ ከመ ያምጽእዎሙ ለእለ ተርፉ ሐሙማን ወአምጽእዎሙ ወአንበርዎሙ ውስተ ንዕስት ደሴት እንተ ሀለወት ቀሩበ ጓንጕት እስከ ይጥዕዩ ፍጹመ ወእምዝ ቦአት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሬማ ከመ ትግበር ተዝካረ እማ ወፈጸመት በህየ ፴ወ፶ ወእምድኅሬሁ ኮነ ወርኃ ክረምት ወከረመት በሬማ።

፲፩ ወበውስቴታ ገብረት ተአምረ ወአንሥአቶ ለሥዕለ ክርስቶስ እምድኅረ ሞተ በከመ ስምዓ ኮነ ለሊሁ ወአሐተ ዕለተ ሶበ ተኃጥአ ዘይቄድስ ዲያቆን ቅድመ ምፅአተ ጳጳስ እስመ አርኰሶሙ አፍርንጅ ለዲያቆናት አዘዘቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለሥዕለ ክርስቶስ ከመ ይቀድስ ወይቤላ እንብየ ወይእቲኒ ካዕበ አዘዘቶ ውእቱኒ ካዕበ ይቤላ ወይቤላ እንብየ ወይእቲኒ ካዕበ አዘዘቶ ውእቱኒ ካዕበ ይቤላ ወአኮ እንብየ ወአኀዘና ወካዕበ መነና ወአስተሐቀራ ወይቤ በልቡ ወአኮ በአፉሁ ምንት ዛቲ ብእሲት፡ዘትኤዝዘኒ፡ከዊና ሊቀተ ወመምህርተ አኮኑ ይቤላ መጽሐፍ፡ብእሲትሰ፡ትምሐር ኢናበውሐ ወኢትመብል ላዕለ ብእሲ።

፲፪ ወእምነስ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አእመረት ህቡእቲሁ ወኢከሠተት ሎቱ ምንተኒ ወበውእቱ ወርኀ ኮነ በዓለ ቅዱስ ፋሲለደስ አመ ፲ወ፩ ለመስከረም ወሖረ ሥዕለ ክርስቶስ ምጽሌ ወሶበ ፈቀደ እግዚአብሔር ከመ ይክሥት ኃይላ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አምጽአ ላዕሌሁ ደዌ ጽኑዓ ወሐመ በይእቲ ዕለት እንተ ባቲ ሖረወሶበ ጸንዓ ላዕሌሁ ይቤ ሰዱኒ ሬማ ወአምጽእዎ ሶቤሃ ወአብጽሕዎ ወአስከብዎ ውስተ ቤቱ ለታቦተ ክርስቶስ ወኮነ ከመ በድን ወነበረ እንዘ ኢይበልዕ ወኢይሰቲ ከወኢያንሰሐስሕ ወኢይትናገር አላ ይብል ኵሎ ዕለተ ኤሎሄ ኤሎሄ ወኃብጠ ኵለንታሁ ወኮነ ቅብወ።

፲፫ ወበ፳ ዕለት እምዝ ደወየ ሞተ በበዓለ አቡነ አባ ኤዎስጣቴዎስ አመ ፲ወ፰ ለመስከረም ወአሞቁ ማየ ለማኅፀብ ወአምጽኡ ልብሰ ግንዘት ወአንበሩ ዲቤሁ ወአሠነዩ ፈትለ ለግንዘት ወአስተዳለዉ ኵሎ ዘይትገበር ላዕለ አብድንት ወሖሩ ይንግርዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወረከብዋ እንዘ ታነብብ መጽሐፈ ተአምሪሃ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወነገርዋ ከመ ሞተ ወሶቤሃ ቦአት ቤተ ክርስቲያን እንዘ ትእኀዝ ይእተ መጽሐፈ ወቆመት ቅድመ ሥዕላ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወሰአለታ እንዘ ትብል ኦ እግዝእትየ ቅድስት ድንግል ማርያም ኢይኩን ከመዝሰ ኢሰአልኩኪ ከመ ተቅትሊዮ አላ ከመ ትገሥጺዮ ተአክሎ ተግሣጽ እንተ ረከበቶ በሕማሙ መሐሪ ሊተ ኦ መሐሪት።





፲ ቤተ ክርስቲያንም እሷ ድንጊያ እየተሸከመችና ውሀ እየቀዳች በእግዚአብሔር ፈቃድ ተሠራች ከዚህ በኋላ ከሞት የተረፉትን ታማሚዎች ያመጡላት ዘንድ በታንኳ ሰው ላከች አምጥተው ወደ ጓንጉት የቅርብ ወደሆነች ትንሽ ደሴት ፈጽመው እስከሚድኑ ድረስ አስቀመጡዋቸው ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ፡የእናቷን፡መታሰቢያ፡ቊርባን፡ታደርግ፡ዘንድ፡ወደ፡ሬማ፡ሂዳ፡፴ ውን፡፶ውን፡እዚያ፡ፈጸመች፡ወራቱ፡የክረምት፡ወራት፡ነበርና፡እዚያው፡ሬ ማ፡ከረመች፡

፲፩ በዚያ ድንቅ ተአምራትን በማድረግ ሥዕለ ክርስቶስንም ከሞተ በኋላ አስነሣች እሱ እራሱ ምስክር እንደሆነ ካቶሊኮች ዲያቆናትን ስለአረከሱ ጳጳሱ ከመምጣቱ አስቀድሞ ቅዳሴ የሚቀድስ ዲያቆን በጠፋ ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ይቀድስ ዘንድ ሥዕለ ክርስቶስን አዘዘችው እሱም እምቢ አላት ዳግመኛም ተው ሲቻልህ ቅዳሴው እንዳይታጐል ቀድስ አለችው እሱም አይሆንም አላትና አሳዘናት ዳግመኛም በልቡናው በመናቅና በማቃለል በአፉ ሳይናገር መምህርና አለቃ ሁና የምታዘኝ ይህች ሴት ምንድናት መጽሐፍ ሴት ታስተምር ዘንድ አናሰናብታትም በወንድ ላይም አትናገር ይል የለምን አለ።

፲፪ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም በልቡ ያለውን አውቃ ለእሱ ሳትነግረው ዝም አለች በዚያን ወራት የቅዱስ ፋሲለ ደስ በዓል መስከረም፲፩ ቀን ነበርና ሥዕለ ክርስቶስ ወደ ምጽሌ ሄደ እግዚአብሔርም የእናታችን ቅድስትና ቡረክት ወለተ ጴጥሮስን የታምራቷን ኃይል መግለጥ ፈልጎ የጸና ታላቅ ደዌ አመጣበትና በዚያች እምቢ ብሎ በሄደበት ቀን ታመመ በሽታው በጸናበት ጊዜ ወደ ሬማ ውሰዱኝ ብሎ ያንጊዜ አምጥተው ከታቦተ ክርስቶስ ቤት አስተኙት ሳይበላ ሳይጠጣ ሳይናገር ሳይንቀሳቀስ ሁለንተናው ሰውነቱ መግል እንደቋጠረ መስሎ አበጠ እሱ ግን በልቦናው ይቅርበለኝ ይቅርበለኝ ይልነበር።

፲፫ በታመመ በሳምንቱ መስከረም ፲፰ በአቡነ ኤዎስጣቴዎስ በዓል ቀን ሞተ አስከሬኑን ለማጠብ ውሀ አሙቀው የሚገነዝበትንም ልብስ አምጥተው ሬሳው ላይ አስቀምጠው ለመገነዣ ክር እያዘጋጁ ሳለህ ግማሾቹ ወደእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ይነግሯት ዘንድ በሄዱ ጊዜ አምላክን የወለደች የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ተአምር እያነበበች አገኟትና እንደ ሞተ ነገሯት እናታችንም ያን ጊዜ የያዘችውን መጽሐፍ ይዛ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዳ አምላክን ከወለደች ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ሥዕል ፊት ቁማ እመቤቴ ቅድስት ድንግል ሆይ እኔ የለመንኩሽ እንዲሞት ሳይሆን ትገስጭው ዘንድ ነበር በመታመሙ የደረሰችበት መከራ ትበቃዋለችና ይቅር ባይ እመቤቱ ሆይ ይቅር በይልኝ ብላ ለመነች።

፲፬ ወሶቤሃ ወፅአ አፅባዕተ እድ እምኑ ተአምር ወደጕጸ አፉሃ ወካዕበ ወፅአ ቃል እምውስተ ሥዕል ወይቤላ አንቲ ፪ኤ ልሳን ሐሪ መሐርኩ ለኪ ወሶቤሃ ወፅአት እምኑ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እምቤተ ክርስቲያን ወአተወት ቤታ ወጸውዓታ ለእኅተ ክርስቶስ ወትቤላ ቦኑ ሞተ ሥዕለ ክርስቶስ እንበለ ይመንኵስ እስኩ ሑሪ ኀቤሁ ወጸውዒ ስሞ ፫ ጊዜ ወበሊዮ ሥዕለ ክርስቶስ መንኵስ ወይእተ ጊዜ ሖረት እኅተ ክርስቶስ ወጸውዓት ስሞ ፫ ጊዜ ወትቤሎ ሥዕለ ክርስቶስ መንኵስ ወሶቤሃ ነቅሃ ወከሠተ አዕይንቲሁ ወነጸራ ወሰምዓ ቃለ ዘትቤሎ ወቀፀባ በአዕይንቲሁ ከመ ዘይቤ እሆ ወሶቤሃ አምጽኡ ቆብዓ ወባረኩ ሎቱ ወአንበሩ ዲበ ርእሱ ወተንሥአ በጊዜሃ ወኮነ ሕያወ ከመ ቀዳሚ ወሶቤሃ አምጽኡ ሎቱ መብልዓ ወበልዐ።

፲፭ ወካዕበ ስምዑ ንነግረክሙ ዘርእየ ራእየ ውእቱ ሥዕለ ክርስቶስ በይእቲ ዕለት አመ ተፈልጠት ነፍሱ እምሥጋሁ ወይቤ መጽአ ኀቤየ ብእሲ ብርሃናዊ በአምሳለ መነኰስ ወይመስለኒ ከመ ውእቱ አባ ኤዎስጣቴዎስ ወዕለቱሂ ዕለተ በዓሉ ይእቲ ወነሥአኒ ምስሌሁ ወአዕረገኒ ላዕለ ወአርአየኒ ሀገረ ብርሀተ ወፅዕዱተ ዘኢይትዐወቅ ኀበሪሃ ወዘኢይተረጐም አምሳሊሃ በዲበ ምድር።

፲፮ ወካዕበ አርአየኒ በማዕዶተ ይእቲ ሀገር ካልእተ ሀገረ እንተ ትሰመይ ገነተ ወሀለዉ ውስቴታ አዕዋም ዐቢያን እለ አልቦሙ ፍሬ ወካዕበ ሀለዉ ዕፀዋት ንኡሳን እለቦሙ ፍሬ ወተስእልክዎ ለውእቱ ብእሲ ወእቤሎ ምንትኑ እሉ አዕዋም ዐቢያን እለ አልቦሙ ፍሬ አውሥአኒ ወይቤለኒ መነኮሳት እሙንቱ እለ ያሌዕሉ ርእሶሙ ወይሰመዩ መነኮሳተ በስም ወይለብሱ አልባሰ መነኮሳት ወይፈቅዱ ይበልዎሙ አባ ወአባ ወኢይገብሩ ግብረ መነኮሳት ወአኅለፉ መዋዕሊሆሙ በሀኬት ወበጽርዓት ወበአንሶስዎ ዘወትር እምሀገር ለሀገር ወበእንተዝ ኢፈረዩ ፍሬ ምግባራት።

፲፯ ወካዕበ ተስእልክዎ ወእቤሎ እሉሰ ዕፀዋት ንኡሳን እለቦሙ ፍሬ ምንትኑ አውሥአኒ ካዕበ ወይቤለኒ መነኮሳት እሙንቱ እለ አኅሠሩ ርእሶሙ ወእለ ኢይትዓወቅ ስሞሙ





፲፬ ያን ጊዜ ከተአምረ ማርያም የእጅ ጣቶች ወጥተው ነካ አደረጓት ዳግመኛም ከሥዕል ቃል ወጥቶ አንቺ ሁለት ምላስ የምትናገሪ ምሬልሻለሁና ሂጂ አላት ያን ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ከቤተ ክርስቲያን ወጥታ ወደ ቤቷ ሄደችና በውኑ ሥዕለ ክርስቶስ ሳይመነኩስ ሞተን እስኪ ወደ እሱ ሂደሽ ሦስት ጊዜ ጠርጠሽ ሥዕለ ክርስቶስ መንኵስ በይው አለቻት ያን ጊዜ እኅተ ክርስቶስ ወደ እሱ ሄዳ ሦስት ጊዜ ሥዕለ ክርስቶስ ብላ ጠርታ መንኵስ አለችው ያን ጊዜ ነቅቶ ተነሥቶ ዓይኖቹን ገልጦ አያት የምትለውንም ቃል ሰምቶ እሺ እንደሚል በዓይኖቹ ጠቀሳት ያን ጊዜ ቆብ አምጥተው ባረኩለትና በእራሱ ላይ ጫኑለት ያን ጊዜውኑ እንደቀድሞ ድኖ ተነሣ ምግቡንም አመጡለትና በላ።

፲፭ ዳግመኛም ይህ ሥዕለ ክርስቶስ በዚያች ቀን ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ ያየውን እንነግራችኋለን ስሙ በምነኩሴ አምሳል የብርሃን ልብስ የለበሰ ሰው ወደ እኔ መጣ አባ ኤዎስጣቴዎስ ይመስለኛል ቀኑም የኤዎስጣቴዎስ ቀን ነውና ከእሱ ጋር ወሰደኝና ወደላይ አሳርጐኝ ኀብሯ የማይታወቅና ምሳሌዋ በምድር የማይተረጐም ነጭና ብርሀት የሆነች አገር አሳየኝ ዳግመኛም በዚያች አገር ማዶ ሌላ ገነት የምትባለዋን አገር አሳየኝ በውስጧም ፍሬ የሌላቸው ብዙ እንጨቶች ነበሩ።

፲፮ ዳግመኛም ፍሬ ያላቸው ጥቂቶች እንጨቶች ነበሩ እኔም እነዚህ ፍሬ የሌላቸው ብዙ እንጨቶች ምንድናቸው ብየ ያን አባት ጠየቅሁ እሱም መልሶ እነዚህ በስም መነኮሳት የሆኑ እራሳቸውን ከፍ ከፍ የሚያደርጉ የመነኮሳት ልብስ ለብሰው አባ አባ ሲሏቸው የሚወዱ የመነኮሳትን ሥራ ያልሰሩ ዘመናቸውን በክፋትና ጸሎትን በማስታጐል ዘወትር ከአንዱ አገር ወደ አንዱ አገር በመዞር ዘመናቸውን ያሳለፉ ስለዚህ የምግባር ፍሬ የሌላቸው ናቸው አለኝ።

፲፯ ዳግመኛም እነዚህ ፍሬ ያላቸው መጠነኞች እንጨቶች ምንድን ናቸው ብየ ጠየቅሁ እሱም መልሶ እራሳቸውን ያዋረዱ ስማቸውን ከውዳሴ ከንቱ ያራቁ በቀንና በሌሊት በጸሎትና በስግደት በጾም ተጠምደው ያለ እግዚአብሔር

ወአልቦ ዘየአምሮሙ ዘእንበለ እግዚአብሔር ባሕቲቱ እለ ይተግሁ መዓልተ ወሌሊተ በጾም ወበጸሎት ወበሰጊድ ወያንሶስዉ ውስተ ተልእኮ ለአዕርፎ ካልአን ወበእንተዝ ፈረዩ ፍሬ ብዙኃ በከመ ይቤ ወንጌል ውስተ ምሳሌ ዘርእ ቦ ዘወድቀ ውስተ ሦክ ወሐነቆ ሦክ ወጠበቆ ወኢፈረየ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ምድር ሠናይ ወወሀበ ፍሬ ቦ ዘ፻ ወበ ዘ፷ ወቦ ዘ፴::

፲፰ ወዘንተ ኲሎ ነገረነ ሥዕለ ክርስቶስ ከመሂ ቀተለቶ ወከመሂ አንሥአቶ ወከመሂ ርእየ ዘንተ ወውእቱ ሀሎ እስከ ይእዜ በሕይወቱ ወስምዑሂ እሙን ውእቱ ወኢይሔሱ ርኢክሙኑ ዕበየ ኃይላ ለእምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘከመ አድወየቶ ወቀተለቶ ለዘሐመያ ወለዘጸአላ በኅቡዕ ይእቲኒ ቀተለቶ በኅቡዕ ወአንሥአቶ በኅቡዕ ወኢትቤሎ ተንሥእ አላ ትቤሎ መንኵስ እስመ ፈርሃት ውዳሴ ከንቱ ብሂለ መንኰስሰ ብሂለ ተንሥእ ውእቱ::

፲፱ ዘንተኒ ነገረቶ ለሊሃ ወትቤሎ አነ ቀተልኩከ ወአንሣእኩከ በኃይለ አምላኪየ እስመ አስተሐቀርከኒ ወጸአልከኒ ለእለ ወበእንተዝ ኢይደሉ ይሕምይዎሙ ወይጽአልዎሙ ለእለ አልሐቆሙ ወሴሞሙ እግዚአብሔር በከመ ይቤ መጽሐፍ ኢትሕሚ መኰንነ ሕዝብከ እምቅድመ ዝኒ ሶበ ሐመይዎ ወጸአልዎ ለሙሴ በኅቡዕ ማርያም ወአሮን ወፅአ ላዕሌሃ ለምጽ ወተአተተት እምትዕይንት ሰቡዓ መዋዕለ እስከ አምኑ በአፉሆሙ ወነገሩ ኃጣውኢሆሙ::

፳ ወይቤሎ አሮን አበስነ እስመ ሐመይናሁ ለእግዚአብሔር ወለከኒ ጸሊ በእንቲአነ ከመ ይእትት እምኔሃ ዝንቱ ለምጽ ወጸለየ በእንቲአሃ ወተፈወሰት ዝኒ ይመስል ከማሁ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር ሖረት እምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ ወቦአት ደሴተ ደምበዛ ወነበረት ውስቴታ ኅዳጠ መዋዕለ ወበህየኒ ተንሥአ ደዌ ጽኑዕ ወሐሙ ኲሉ ማኅበር ወሞቱ እምኔሆሙ ፲ወ፪ ሰብእ ወፈጸሙ ገድሎሙ ወአዕረፉ በሰላም ወወረሱ ሕይወተ ዘለዓለም ጸሎቶሙ ወበረከቶሙ የሃሉ ምስለ ፍቁሮሙ ለዓለመ ዓለም አሜን::





በቀር ሰው ያላወቃቸው የደከመውን ለማሳረፍ ለተልዕኮ የሚፋጠኑ መነኮሳት ናቸው ስለዚህ ብዙ ፍሬን አፈሩ አለኝ ወንጌል በምሳሌው በእሾህ ውስጥ የወደቀ ዘር አለ እንዳያፈራ እሾሁ አጣብቆ አስቀረው በመልካም መሬት ላይ የወደቀ ፍሬ አለ መልካም ፍሬ አፈራ መቶ ፍሬ ስልሳ ፍሬ ሠላሳ ፍሬ ያፈራም አለ እንደ አለ::

፲፰ ሥዕለ ክርስቶስም እሷን አሳዝኖ እንደ ሞተ ኋላም እንደ አስነሣችው ይህን ያየውንም ሁሉ ነገረን እሱም ይህ መጽሐፍ እስከ ተጻፈ ድረስ በሕይወቱ ነበረ ምስክርነቱም እውነት እንጂ ሐሰት አልነበረም የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን የተአምራቷን ታላቅነት በስውር ያማትንና የሰደባትን እንደአሳመመችውና እሷም በስውር እንደገደለችው በሥውር፡እንደ፡አስነሳችው፡አያችውን፡ውዳሴ፡ከንቱ፡እንዳይሆንባት፡ ተነሥ አላለችውም መንኩስ አለችው እንጂ መንኩስ ማለቷ ተነሥ ማለቷ ነበርና::

፲፱ ኋላ ለሱ አንተ ስለ አቃለልከኝና ስለ ሰደብከኝ በፈጣሪየ ኃይል አስቀድሜ ገደልኩህ ኋላ አሥነሣሁህ ብላ ነገረችው ስለዚህ እግዚአብሔር የሾማቸውንና ከፍ ከፍ ያደረጋቸውን መሳደብ አይገባም መጽሐፍ የሕዝብህን አለቃ አትማ እንደአለ ከዚህም በፊት ማርያም እኅተ ሙሴና አሮን ነቢዩ ሙሴን በአሙና በሥውር በሰደቡ ጊዜ የሙሴ እኅት ማርያም ለምፅ ወጣባትና ማማታቸውን በአፋቸው እስኪያምኑ ድረስ ከከተማ ወጥታ ከበርሃ ሁና ሰባት ቀን አልቅሳለች::

፳ አሮንም ሙሴን እግዚአብሔርንና አንተን አምተናልና ለምፅና በሽታ እንዲወገድልን ስለኛ ጸልይልን ብሎ ለመነውና ሙሴ በጸለየ ጊዜ ተፈወሰች ይህም ያንን ይመስላል ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ
ከዚያ ተነሥታ ወደ ደምበዛ ደሴት ሄዳ ጥቂት ተቀመጠች ከዛ ሳለች የጽና ደዌ ተነስቶ ማኅበር ሁሉ ታመመ ከእነሱም ፲፪ ሰዎች ሞቱ ተጋድሏቸውን ፈጽመው በሰላም አረፉ ጸሎታቸውና በረከታቸው ከሁላችን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይሁን ይደረግልን::

## ምዕራፍ ፲፮

፩ ወእለሂ ተርፉ ሕሙማን ተመንደቡ ዐቢየ ምንዳቤ እስከ ስንከ ሥጋሆሙ ወተወለጠ አርአያሆሙ እምጽንዓ ደዌ ወእምጽንዓ ረኃብ ወበውእቱ መዋዕል መጽአ ጳጳስ አቡነ ማርቆስ ወበጽሐ ሀገረ ዋልዋጅ ወለአኩ ኀቤሃ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን ወአይድዕዋ ምጽአተ ጳጳስ ወይቤልዋ ንዒ ንሑር ኀበ ጳጳስ ከመ ንትቀበሎ ወንትባረክ እምኔሁ ወንንሣእ በረከቶ ወሶበ ሰምዓት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተከዘት ፈድፋደ:ወትቤ:ለእመ:ሖርኩ:ባሕቲትየ:ወአኃድግምሙ:ለእሉ:ድውያን:ይመውቱ:በረኃብ:ሊተሂ:አልቦ:ዘይተልወኒ:ወለእመ:አትለውክዎሙ:ኢይክሉ:ሐዊረ:ወካዕበ:ለእመኃደጉ:ሐዊረ:አሐጕል:እምበረከተ:ጳጳስ:ወኃጥአት:ዘከመእፎ:ትገብር:ዝሰ:ዘኮነ:በወርኃ:ጥር:ውእቱ:ወእንዘ:ሀለወት:እምነ:ቅድስት:ወቡርክት:ወለተጴጥሮስ:ማዕከለ:፪ኤ:ሕሊና:ጸለየት:ኀበእግዚአብሔር:ከመ:ይክሥት:ላቲ:እም፪ኤ:ግብር:ዘውእቱ:ፈቀደ:ወሠምረ ::

፪ ወሶቤሃ መጽአ ቃል እምሰማይ ወይቤላ አዝዚዮሙ ለኵሎሙ ሕሙማን ከመ ይረዱ ውስተ ባሕር በዕለተ ጥምቀት ወይወርድ ላዕሌሆሙ መንፈስ ቅዱስ ወይትፌወሱ እምደዌሆሙ ወሶበ ኮነ ዕለተ ጥምቀት አውረደቶሙ ውስተ ባሕር ወተጠምቁ ኵሎሙ ወወረደ ላዕሌሆሙ መንፈስ ቅዱስ ከመ ወረደ ቀዲሙ በጽርሐ ጽዮን በአምሳለ እሳት ወተፈወሱ ኵሎሙ ሕሙማን በውእቱ ዕለት ወኮኑ ከመ ዘኢለከፎሙ ሕማም ግሙራ ወኵሎሙ እለ ሀለዉ ውስተ ምጥማቅ ርእዩ ወአንከሩ::

፫ ወሶቤሃ ተንሥአት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሖረት በፍሥሓ ኀበ ጳጳስ ወለጳጳስኒ አይድዕዎ ኵሎ ዜናሃ ወዘከመ ተፈልጠት እምነ ብእሲሃ መልክዓ ክርስቶስ በእንተ ልብስ ዘአቡነ ስምዖን እምቅድመ ትብጻሕ ኀቤሁ ወእምዝ በጽሐት ኀቤሁ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወተአምኃቶ ወሶበ ርእያ ተስእለ በእንቲአሃ ወይቤ ዛቲኑ ዘይሰማዕ ዜናሃ ውስተ ብሔርነ ብሔረ ግብጽ ወይቤልዎ እወ ይእቲ::





## ምዕራፍ ፲፮

፩ የተረፉ ታማሚዎች እጅግ ተጐዱ ከደዌ ጽናትና ከረሃብ ጽናት የተነሣ ሰውነታቸው ሻክሮ መልካቸው እስኪለወጥ ድርስ በዚያን ወራት ጳጳሱ አቡነ ማርቆስ መጥቶ ከዋልዋጅ አገር ደረሰ የቤተ ክርስቲያን አለቆችም የጳጳሱን መምጣት ለእናታች ያስረዷት ዘንድ መልእክተኛ ላኩና መጥተሽ ጳጳሱን ተቀብለን ከእሱም ቡራኬ እንቀበል አሏት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ይህን መልእክት በሰማች ጊዜ እነዚህን የታመሙትን ትቻቸው ብሄድ በረሀብ ይሞቱብኛል እኔንም የሚከተለኝ የለም ብቻየን ነኝ ባስከትላቸው ከእኔ ጋር መሄድ አይችሉም:ብላ:እጅግ:አዘነች:ዳግመኛም:ከመሄድ:ብቀር:የጳጳስ:በረከትን:አጣለሁ:ብላ የምታደርገው ነገር ግራ ገባት ይህም የተደረገ በጥር ወር ነበር እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በሁለት ሐሳብ ስትቸገር እግዚአብሔር የወደደውን ይገልጥላት ዘንድ ወደ እሱ ጸለየች::

፪ በዚህን ጊዜ እነዚህን የታመሙትን በሙሉ በጥምቀት ቀን መንፈስ ቅዱስ በእነሱ ላይ ወርዶ ይፈውሳቸዋልና ወደውሀ ወርደው እንዲጠመቁ እዘዢያቸው የሚል ቃል ከሰማይ ወደ እሷ መጣ ጥምቀት በደረሰ ጊዜ ወደ ባሕር አወረደቻቸውና ሲጠመቁ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በጽርሐ ጽዮን በእሳት አምሳል እንደ ወረደ በእነዚህም ላይ በገሐድ ወርዶ በጥምቀት ያሉ ሰዎች አይተው እስኪያደንቁ ድረስ ሁላቸውንም ፈወሳቸው::

፫ ከዚህ በኋላ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ተነሥታ ወደ ጳጳሱ በደስታ ሄደች ለጳጳሱም እሷ ከመሄዷ አስቀድመው ስለ አቡነ ስምዖን ልብስ ምክንያት ከባለቤቷ መልክዓ ክርስቶስ እንደተለየችና ዝናዋን ሁሉ አሁንም ወደ እሱ ለመምጣት መንገድ ላይ እንደአለች ነገሩት ጳጳሱም እስክትመጣ በጉጉት ይጠብቅ ነበርና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መጥታ:እጅ:በነሣችው:ጊዜ:እስከ:ግብፅ:ድረስ:ዝናዋ:የሚሰማ:ይህች:ናትን:ብሎ:ጠየቀ:አዎን:እሷ:ናት:አሉት::

፬ ወውእተ ጊዜ ባረካ በቡራኬ ዘይደሉ ላቲ ወአፍቀራ ፈድፋደ ወሶቤሃ ነገረቶ ኵሎ ሕሊናሃ ወትቤሎ ምንተ እግበር ናሁ ይትጋብኡ ኀቤየ ሰብእ እንዘ አነ ኢይፈቅድ ይደልወኒኑ ዝንቱ ወሚመ አልቦ አውሥአ ወይቤላ ኢትፍርሂ ምንተኒ አልቦ ዘይከውን ዘእንበለ ፈቃደ እግዚአብሔር ወይእዜኒ ውእቱ ያጽንዕኪ ወያኀድር መንፈሶ ላዕሌኪ።

፭ ወእምዝ ወሀቦሙ ክህነተ ለእለ ሀለዉ ምስሌሃ ወተሰነአሉ በበይናቲሆሙ ጳጳስኒ ሖረ ኀበ ንጉሥ ወይእቲኒ ተመይጠት ፍኖታ ወይእተ ጊዜ ተለውዋ ብዙኃን ሰብእ እድ ወአንስት ምስለ ደቂቆሙ ወአዋልዲሆሙ ወበዝኅ ፈድፋደ ሰብእ ወሶቤሃ በጽሐት ደምበዛ ወሶበ ርእየት ከመ በዝኅ ሰብእ ወአእመረት ከመ ኢያገምሮሙ መካን ዘእንበለ ዘጌ ወፈቀደት ትንበር ዘጌ ወእምዝ ሖረት ቤተ መንዞ ወወጠነት በህየ ጾመ ወነበረት እስከ ደብረ ዘይት ወፈጸመት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ዘወጠነት ቀዳሚ።

፮ ወእምድኅሬሁ ሖረት ወቦአት ዘጌ ወበጽሐ በዓለ ፋሲካ በዓለ ትንሣኤሁ ለእግዚእነ ወበይእቲ ሌሊት እንዘ ትነብር እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትጼሊ እምድኅረ ኖሙ ሰብእ እንዘ ክሡታት አዕይንቲሃ መጽአ ድቃስ ላዕሌሃ ከመ ዘራዕይ ወሰምዓት ሶቤሃ ቃለ ዘይቤላ አድኅንኒ እምድም እግዚአብሔር አምላከ መድኃኒትየ በሊ ወይእቲሰ አምሰለቶ ሕልመ ወገብአት ኀበ ጸሎታ ዘቀደሚ ወመጽአ ላዕሌሃ ድቃስ ዳግመ ከመ ቀዳሚ ዘይቤላ ቃል ከማሁ ወከመዝ ይቤላ ሥልሰ ጊዜ አድኅንኒ እምድም እግዚአብሔር አምላከ መድኃኒትየ በሊ።

፯ ወሐለየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤ ምንትኑ ዛቲ ራዕይ ወሶቤሃ ርእየት ጽላሎተ ነምር እንዘ ይትሐወስ በአፍአ በብርሃነ ወርኅ ቦ ጊዜ እንዘ ይቀውም ወይፈቅድ ይባእ ወቦ ጊዜ እንዘ ያስምክ ዲበ ምድር ወይፀንሕ ወይደቢ ወኢያእመረት ከመ ነምር ውእቱ ወእምዝ እንዘ ታነክር እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ቦአ ውእተ ራእየ ነምር ወመሰጠ ለ፩ዱ ሕፃን ዘኖመ ወርእየቶ ሶቤሃ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሖረ ወኢያእመሮ መኑሂ አሜሃ እምአኃት ዘእንበሌሃ።





፬ በዚህ ጊዜ ለሷ እንደሚገባ ቡራኬ ሰጣት እጅግም ወደዳት እሷም በልቧ ያለውን እኔ ምን ላድርግ እኔ ከአለሁበት መጥተው ሰዎች ይሰበሰባሉ እኔ አልፈልግም ይህ ነገር ለኔ ይገባኛል አይገባኝም አለችው
ጳጳሱም መልሶ ያለ ፈቃደ እግዚአብሔር የሚሆን ነገር የለምና አይዞሽ አትፍሪ እሱ ያጸናሻል መንፈሱንም በአንች ላይ ያሳድራልና አላት።

፭ ከዚህም በኋላ ከሷ ጋር ለአሉት ሥልጣነ ክህነትን ሰጥቶ ከእሷ ጋር ተሰነባብተው ጳጳሱም ወደ ንጉሡ ሄደ እሷም ተመልሳ ወደመጣችበት ጐዳናዋ ሄደች በዚህን ጊዜ ብዙ ሰዎች ወንዶችና ሴቶች ከነልጆቻቸው ከነቤተሰቦቻቸው ተከተሏትና ደምበዛ ደረሰች ሰዎች በዝተው ያለ ዘጌ በቀር ይህ ቦታ እንደማይበቃ በተረዳች ጊዜ ዘጌ ለመሄድ ፈለገችና ወደ ቤተ መንዞ ሄዳ በዚያ ጾም እየጾመች ጀምራ የነበረውን የቤተ መቅደስ ሕንፃንም ሠርታ እስከ ደብረ ዘይት ጨረሰች።

፮ ከዚህ በኋላ ወደ ዘጌ ሄደች የጌታችን ትንሣኤ የፋሲካ በዓል በደረሰ ጊዜ በዚያች ሌሊት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሰው ከተኛ በኋላ ቍጭ ብላ ስትጸልይ ዓይኖቿ ተገልጠው ራዕይን ለማየት ያክል እንደሰመመን ያለ እንቅልፍ ወሰዳት በዚያን ጊዜ የድኅነቴ ፈጣሪ እግዚአብሔር ሆይ ከደም አድነኝ ብለሽ ጸልዩ የሚል ቃል ሰማች እሷም እንደተራ ህልም አድርጋው ወደቀደመ ጸሎቷ ተመለሰች እንደ ቀድሞ እንቅልፍ ወሰዳትና የቀድሞውን ቃል ሁለተኛ ሰማች እንደገናም ሦስተኛ እንቅልፍ ወስዷት የድኅነቴ ፈጣሪ እግዚአብሔር ሆይ ከደም አድነኝ በዪ ሲል ቃል ሰማች።

፯ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ይህ ራዕይ ምን ይሆን አለችው በዚያን ጊዜ የነብር ጥላ በሌሊት ጨረቃ አንድ ጊዜ ሲተኛ አንድ ጊዜ ወደ ውስጥ ለመግባት ሲነሳና ሲያድን አየች ግን ነብር እንደሆነ አላወቀችም ነበር እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ያን ህልም እያደነቀች ሳለ ያ ነብር ገብቶ አንድ የተኛ ሕፃን ነጥቆ ይዞ ወጣ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ይዞ ሲወጣ አየች ያለ እሷ ከሌሎች እኅቶች ያየ አልነበረም።

፰ ወወሰዶ ወኃብኦ ወካዕበ መጽአ ወመሰጣ ለአሐቲ ሕፃን እንዘ ትነውም ወአኀዘ ስኰናሃ ወሰሐባ ወአውፅአ አፍአ ወከልሐት ይእቲ ሕፃን እንዘ ይስሕባ ነምር ወሶቤሃ ነቅሃ ኵሎን አኃት እለ ኖማ ወርእያሁ ለነምር እንዘ ይስሕባ ለሕፃን ወያንገረግራ ዲበ ምድር ወይትለሐይ ባቲ ወፈርሃ ወደንገጻ ወተግኅሣ ኵሎን መንገለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወወድቃ ላዕሌሃ ወአፅዓቃሃ እስከ አልፀቀት ለመዊት ወጐንደየ ውእቱ ነምር እንዘ ይትለሐይ ባቲ ወትኬልሕ ሕፃንኒ በአፍአ እስመ እዙዝ ውእቱ ከመ ያፍርሆን ወያደንግፆን።

፱ ወእምድኅሬሁ ሖረ ወለሕፃንሰ ተባዕታይ ዘመሰጠ ቀዳሚ በልዐ ንስቲተ እምሥጋሁ ወደፈኖ ውስተ ምድር ወኃደጎ ወሖረ ወእማንቱሰ አኃት ቤታ ኵላ ሌሊተ እንዘ ይትሀወካ ወይደነግፃ ወሶበ ጸብሐ ተዘከርዎ ለውእቱ ሕፃን ኃሠሥዎ ወኢረከብዎ ወአእመሩ ይእተ ጊዜ ከመ ነምር መሰጠ ሌሊተ ወሶቤሃ፡ተጋብኡ፡ኵሎሙ፡መነኮሳት፡ወኃሠሡ፡አብድንቲሆሙ፡ለእለ ፡ሕፃናትወእምዕፁብ፡ረከብዎ፡ለተባዕታይ፡ሕፃን፡ወቀበርዎ፡ወለአንስ ቲያዊትሰ፡ተኃጥአት።

፲ ወኮነ በይእቲ ዕለት ዐቢይ ድንጋፄ ወሁከት ላዕለ ኵሉ ማኅበር ወይቤልዋ ኵሎሙ ኅቡረ በ፩ ቃል ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ንፃእ ወንሑር እስመ አኃዘነ ፍርሃት ወድንጋፄ እምግርማ ውእቱ ነምር ወኢይትከሃለነ ንንበር ውስተዝ ገዳም ወካልእንሂ ይቤልዋ ፃኢ ኢትትቃወሚዮ ለእግዚአብሔር ወከመ ዘይትበአስ ምስሌሁ ኢትኩኒ ወይእቲኒ ሠምረት ወኃብረት ምስሌሆሙ በዝንቱ ምክር ወአብሐቶሙ ይሑሩ ጥዑያን በእግር ወድውያን በታንኳ።

፲፩ ወወፅኡ በይእቲ ዕለት ወሖሩ ፋሬ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወፅአት እምድኅሬሆሙ ወእምዝ ኃለፉ ጥዑያን እንተ እግር ወይእቲኒ ሖረት በታንኳ ምስለ ሕሙማን ወድኩማን ወተራከቡ ኵሎሙ በደምበዛ ኢይምሰልክሙ ኦ ፍቁራንየ ዘጐየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እምፍርሃተ ነምር ወድንጋፄ መዊት አላ በእንተ ፍርሃተ አኃት አዋልዲሃ ወፈቃደ እግዚአብሔር በከመ ይቤ መጽሐፍ እስመ ለእመ ፩ዱ አባል ሐመ የሐምም ምስሌሁ ኵሉ ነፍስትነ።





፰ ነብሩም ያን ሕፃን ወስዶ ደበቀና ዳግመኛ መጥቶ አንዲት ሕፃን ልጅ እግሯን ይዞ እየጐተተ ከውጪ አወጣት ያችም ሕፃን ነብር ሲጐትታት ጮኸች ያን ጊዜ ያ ነብር ሕፃኗን ከመሬት ላይ እያንከባለለ ሲጫወትባት የተኙት እኅቶች ከእንቅልፋቸው ተነሥተው አዩና ደንግጠውና ፈርተው ሁላቸውም ወደ እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ተሰብስበው ከእሷ ላይ ወድቀው እየተንጫጩ በጣም አስጨነቋት ሕፃኒቷ ከውጪ እያለቀሰች ያ ነብር እያንከባለለ ሲጫወትባት ቆየ ያስፈራቸውና ያስደነግጣቸው ዘንድ ታዞዋልና።

፱ ከዚህ በኋላ ነብሩ አስቀድሞ የወሰደውን ሕፃን ግን ከሥጋው ትንሽ በልቶ የተረፈ ሰውነቱን መሬት ቆፍሮ ቀብሮ ትቶ ሄደ እነዚየ እኅቶችም ሌሊቱን በሙሉ ሲታወኩና ሲደነግጡ አደሩ በነጋ ጊዜ ያን ሕፃን አስበው ቢፈልጉ አላገኙ ትም ያን ጊዜ ነብር ሌሊት ነጥቆ እንደወሰደ ተረዱ ከዚህ በኋላ መነኮሳት በሙሉ ተሰብስበው የነዚያን ሕፃናት ሬሳቸውን ፈልገው በጭንቅ የወንዱን ሬሳ አግኝተው ቀበሩ የሴቷ አስከሬን ግን ጠፋ።

፲ በዚያች ዕለት በማኅበሩ ሁሉ ላይ ታላቅ ሁከትና ድንጋጤ ሆነ ሁላቸውም በአንድነተ ተሰብስበው ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከዚህ ከነብር ፍርሃት የተነሣ እዚህ መኖር አልቻልንምና ከዚህ ገዳም ወጥተን እንሂድ አሏት ግማሾችም እግዚአብሔርን አትቃወሚ ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚጣላ ሰው አትሁኚ እሱ በፈቀደው ቦታ መሄድ ነው እንጂ አሏት እሷም በዚህ ምክር ፈቃደኛ ሆና ከእነሱ ጋር ተባበረችና ጤነኞቹ በእግር ታማሚዎቹ በታንኳ እንዲሄዱ አሰናበተቻቸው።

፲፩ በዚያች ቀን ወጥተው ፋሬ ሄዱ ጤነኞቹ በእግር ከሄዱ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክ ት ወለተ ጴጥሮስ ወደ ኋላ ቀርታ ከታመሙት ጋር በታንኳ ሄደች ሁላቸውም በደምበዛ ተገናኙ ወዳጆቼ ሆይ እናታችን ነብርን ፈርታ የሸሸች አይምሰላችሁ ልጆቿ ስለፈሩና የእግዚአብሔርም ፈቃድ ስለአልነበር ወጥታ ሂዳለች እንጂ መጽሐፍ ከሰውነታችን አንዱ አካል ከታመመ መላ ሰውነታችን የታመመ ይሆናል እንደአለ።

፲፱ ይእቲሰ ተአምር ከመ ኢትክል አምስጦ እምትእዛዘ እግዚአብሔር በጕይይ በከመ ይቤ ዳዊት አይቴኑ አሐውር እመንፈስከ ወአይቴ እጕይይ እምቅድመ ገጽከ እመኒ ዓረጉ ውስተ ሰማይ ህየኒ አንተ ወእመኒ ወረድኩ ውስተ ቀላይ ህየኒ ሀሎከ ወእመኒ ነሣእኩ ክንፈ ከመ ንስር ወሰረርኩ እስከ ማኅለቀተ ባሕር ህየኒ እዴከ ትመርሐኒ ወታነብረኒ የማንከ ወለእሉኒ ሕፃናት ዘመሰጦሙ ነምር እስመ ውእቱ ተሠልጠ ወተበውሐ እም እግዚአብሔር በከመ ይቤ ነቢይ ወሥጋሆሙኒ ለጻድቃኒከ ለአራዊተ ገዳም፡፡

፳ ወእምድኅሬሁ አግበረት እምነ ቅድስተ ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ውስተ ደምበዛ ዐቢየ ሰቀላ ወነበረት ምስለ አዋልዲሃ መነኮሳይያት ወመነኮሳትሰ ነበሩ ፃና ወበህየኒ ተጋብኡ ኀቤሃ ብዙኃን ሰብእ እድ ወአንስት ከመ ይትጋብኡ አንስርት ኀበ ሀሎ ገደላ ወአኃዙ ይብዝኁ ወእንተ ጸብሐት ይትዌሰኩ በከመ ይቤ ግብረ ሐዋርያት ወይእተ ጊዜ መጽኡ አባ ዘሐዋርያት ወአባ እደ ክርስቶስ ዝ ውእቱ ኃምስ ማኅበር ወእምዝ ተንሥአ ደዌ ጽኑዕ ወሐሙ ብዙኃን መነኮሳት ወመነኮሳይያት ወሞቱ አሜሃ ፹ ወ፯ ሰብእ ወፈጸሙ ገድሎሙ ወአዕረፉ በሰላም ወወረሱ ሕይወተ ዘለዓለም ጸሎቶሙ ወበረከቶሙ የሃሉ ምስለ ዘጸሐፉ ወአጻሐፉ ዘሰምዑ ወዘአንበቡ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

ምዕራፍ ፲፯

፩ ወቦ እለ ሐይዉ እምውእቱ ሕማም ወሀለዉ እስከ ይእዜ ወይከውኑ ስምዓ በእንቲሃ እንዘ ይብሉ ሶበ ትቤለነ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እምፈቀድኩ ይእዜ ይንድፉክሙ በነፍጥ ወእመ አኮ ይርግዙክሙ በኲናት ሶቤሃ ሐመምነ ወአልፀቅነ ለመዊት ወካዕበ ሶበ ትሔውጸነ ወትልእክ ኀቤነ እንዘ ትብል እግዚአብሔር ይምሐርክሙ ወይፈውስክሙ ንሕነኒ ንቤላ እመሰ ምሕርከነ አንቲ እግዚአብሔርኒ እምፈቀደ ምሒሮተነ ወይእቲኒ ትቤለነ ትፈቅዱኑ ትሕየዉ አንትሙ ወንቤላ እወ ንፈቅድ ንሕየው ወትቤለነ ኢትፍርሁ ኢትመውቱ ወትምሕል በመሐላ ዘልማድ ወንሕነኒ ንትፌሣሕ እመ አይድዓተነ ጥዩቀ፡፡





፲፱ እሷስ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ማምለጥ እንደማይቻል ታውቃለች ዳዊት ከአንተ ፈቃድ ወዴት እሄዳለሁ ከአንተ ፊትስ ወዴት እሸሻለሁ ወደ ሰማይም ብወጣ እዚያም አንተ ነህ ወደ ጥልቅ ባሕርም ብወርድ እዚያም አንተ አለህ እንደንሥር ክንፍ አግኝቼ እስከ ባሕር ዳርቻ ብበር በዚያም ሥልጣንህ ትመራኛለች ቀኝ እጅህ ታስቀምጠኛለች እንደአለ እነዚህን ሕፃናት ነብር የወሰዳቸው እሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዞ ነውና ዳዊት የወደጆችህ የቅዱሳን ሥጋ ለምድር አራዊት ሆነ እንደአለ፡፡

፳ ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በደምበዛ ታላቅ አዳራሽ አሠርታ ከሴቶች መነኮሳት ጋር ተቀመጠች ወንዶች መነኮሳት ግን በጣና ተቀመጡ አሞራዎች የወደቀ ሥጋ ከአለበት እንዲሰበሰቡ እንደዚያው እናታችን ከአለችበት ብዙ ወንዶችና ሴቶች ተሰበሰቡ ዕለት ዕለት እየመጡ እጅግ በዙ እንዳአለ የሐዋርያት ሥራ እነዚህም ዕለት ዕለት እየመጡ እጅግ በዙ በዚያን ጊዜ አባ ዘሐዋርያትና አባ እደክርስቶስ መጡ አምስተኛ ማኅበር ይህ ነው እንደገና የጸና በሽታ ተነሥቶ ብዙ ወንዶች መነኮሳትና ሴቶች መነኮሳይያት ታመው ሰማንያ ሰባት ሰዎች ሞቱ ተጋድሎዋቸውንም በሰላም ፈጽመው የዘለዓለም ሕይወትን ወረሱ ጸሎታቸውና በረከታቸው ይህን መጽሐፍ ከሰሙና ከአነበቡ ከጻፉ ከአጻፉ ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለም ይሁን ይደረግልን፡፡

ምዕራብ ፲፯

፩ ከዚያ በሽታ ድነው ይህ መጽሐፍ እስከተጻፈ ድረስ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እኔ የምፈቅድላችሁ በጦር ቢወጓችሁ ይሻላል ወይም በቀስት ቢወጓችሁ ይሻላል በአለችን ጊዜ ታመምንና ለሞት ደረስን ዳግመኛም በጐበኘችንና ወደ እኛ መልእክተኛ ልካ እግዚአብሔር ይማራችሁ ይፈውሳችሁ በአለችን ጊዜ እኛም መልሰን አንቺ ይቅር ከአልሽን እግዚአብሔርም ይምረናል እንላታለን እሷም እናንተ በሥጋ መዳን ትወዳላችሁን ትለናለች እኛም አዎን እንወዳለን እንላታለን እሷም አይዟችሁ አትሞቱም ብላ በተለመደ መሐላ እውነት ብላ ትምልልናለች ይህን በአስረዳችን ጊዜ እኛም እንደሰታለን ፡፡

፪ ወሶቤሃ ሐየውነ ወተንሣእነ ወዘንቱ ስምዕ እሙን ውእቱ ወኢኮነ ሐሰተ በከመ ይቤ ያዕቆብ ሐዋርያ ብዙኃ ትረድእ ጸሎቱ ለጻድቅ ትክል ወታሠልጥ ኤልያስ ዘከማነ ሰብእ ውእቱ ወዘከመ ነሐምም የሐምም ወጸሎተ ጸለየ ከመ ኢይዝንም ዝናም ወኢዘንመ ውስተ ምድር ፫ ዓመተ ወ፮ አውራኀ ወካዕበ ጸለየ ከመ ይዝንም ዝናም ወወሀበ ሰማይ ዝናሞ ወምድርኒ አብቊለት ፍሬሃ ወከመዝ ይትኤዘዝ ሎሙ እግዚአብሔር ለቅዱሳኒሁ ወይሰምዖሙ ጸሎቶሙ ወይገብር ሎሙ ኵሎ ፈቃዶሙ።

፫ ወሶበ አእመረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሕሊናሆሙ ወዘይረክቦሙ በደኃሪ መዋዕል ትጼሊ ወትስእል ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይሙቱ ፍጡነ በሥጋሆሙ ወይሕየዉ በነፍሶሙ ሕይወተ ዘለዓለም ወዘኢየሐልቅ ለትውልደ ትውልድ በከመ ይቤ ዳዊት እስመ ይኄይስ እምሐይው ሣህልከ ወጳውሎስኒ ይቤ አንገሊገክሙ በስሙ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ መጥውዎ ለሰይጣን ከመ ይሥርዎ ሥጋሁ ወትድኃን መንፈሱ በዕለተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወበእንተዝ እምነኒ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኢትምሕክ መነኒ እሞተ ሥጋ እስመ ክሡት በኀቤሃ ኅቡአተ ኵሉ ሰብእ።

፬ ወተአምር ግዕዞሙ ለለ፩፩ በከመ ይቤ ጳውሎስ ወዘሰ ቦ መንፈስ ቅዱስ ኵሎ ይትኃሠሥ ወሎቱሰ አልቦ ዘይት ኃሥሦ አማንከ ህልው ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወተአምር ዘይከውን እምቅድመ ይኩን እመኒ ሠናየ ወእመኒ እኩየ ወትፈትን ልበ ወኵልያተ ወትከሥት ሕሊናሆሙ ለሰብእ ወትነግሮሙ ለሊሃ እምቅድመ ይንግርዋ ወኢይበውእ መኑሂ ኀቤሃ ዘእንበለ ይፍትን ወያመክርእሶ።

፭ ወከመ ይትርአይ ዘተሰውጠ ውስተ ጽዋዕ ማኅው እመሂ ኅፁፅ ወእመሂ ምሉእ ከማሁ ይትርአይ ላቲ ሕሊና ዘሀሎ ውስተ ልበ ሰብእ ወበእንተዝ ኢትፈቅድ ይትሐጐል መኑሂ አላ ትስእል ኀበ እግዚአብሔር ወይገብር ላቲ ኵሎ ዘፈቀደት ወያመጽእ ሕማመ ወይቀትል በከመ ትቤሎ እስመ ለሊሁ አቅደመ ወተካየዳ በዋልድባ።





፪ በዚያን ጊዜ ድነን እንነሳለን ሐዋርያው ያዕቆብ የጻድቅ ሰው ጸሎት እጅግ ኃይልን ታደርጋለች ኤልያስ እንደእኛ ሰው ነበር እኛ እንደምንታመም ይታመማል ዝናም እንዳይዘንብ ጸሎት ጸለየ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር በምድር ላይ ዝናም አልዘነበም ዳግመኛም እንዲዘንብ ጸለየ ዝናብም ዘነበ ምድርም የዘሩባትንና የተከሉባትን አበቀለች እግዚአብሔር ለወዳጆቹ እንደዚህ ታዞ ጸሎታቸውን ሰምቶ የፈለጉትን ያደርግላቸዋል።

፫ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ሐሳባቸውንና ወደ ኋላ የሚደርስባቸውን ውድቀት በአወቀች ጊዜም በሥጋቸው ፈጥነው ሞተው በነፍሳቸው እንዲድኑና የዘለዓለምን ሕይወት እንዲወርሡ ወደ እግዚአብሔር ትለምንላቸኋለች ዳዊት በሥጋ ከመኖር ይልቅ ሞተው በአንተ ቸርነት በነፍስ መዳን ይሻላል እንደአለ ቅዱስ ጳውሎስም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሥጋውን ያባዝተው ዘንድ ለጠላት ስጡት ነፍስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ቀን ትድናለችና አለ ስለዚህ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የሥጋን ሞት ሞተ ብላ ለማንም አታዝንም ከሰው ሁሉ የተሰወረ በእሷ ዘንድ ግልጥ ነውና ረቂቁን ምሥጢር ትመለከት ነበር እንጂ ።

፬ የሰውንም ባሕርይ እያንዳንዳቸውንም ገና ስታያቸው ታውቃለች ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ያለበትን ሁሉ ይፈልጋል እሱ ግን ማንንም አይፈልግም እንደአለ በእውነት በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ላይም መንፈስ ቅዱስ አድሮ ከመደረጉ አስቀድሞ ወደፊት የሚደረገውን ክፉም ሆነ ደግ ገልጠላት ታውቃለች የሰው ልቡና ያመላለሰውን ኩላሊት ያጤሰውን አውቃ እከሌ እንዲህ አስቧል ብላ ለሌላ ትነግረው ነበር እነሱም ገና ሳይናገሩ የልባቸውን አውቃ ትነግራቸው ነበር እራሱን ሳይመረምርና ሳይፈትን ወደ እሷ የሚገባ አልነበረም።

፭ በብርሌ የተቀዳ ነገር ሙሉም ሆነ ጐደሎ እንደሚታይና እንደሚታወቅ በሰው ልቡና ውስጥ ያለው ሀሳብ ለእሷ እንደዚሁ ይታያታል ስለዚህ የማንንም ጥፋት የማትወድ ስለሆነ ወደ እግዚአብሔር ለምና የፈለገችውን ሁሉ ያደርግላት ነበር እንደ አለችውም ሕማምን አምጥቶ በሞት ይወስዳቸዋል እሱ እራሱ አስቀድሞ በዋልድባ ቃልኪዳን ሰጥቷታልና።

፮ ወከመዝ ትገብር ዘልፈ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሶበ ትሬእዮሙ ለሰብእ እንዘ ይበዝኑ ወያፈደፈዱ ፍሬ ምግባራት ትስእል ሞተ ኀበ እግዚአብሔር ወትፌንዎሙ አምኃ ለእግዚአብሔር በከመ ሐረሳዊ ይኄጽር ወይሬኢ ኀበ ገራህቱ ከመ ፃዕደወ ወበጽሐ ለማዕረር ያስተጋብእ ዓፃድያነ ወይፌንዎሙ ወየዓፅዱ ሎቱ ወያስተጋብእ እክሎ ውስተ መዛግብቲሁ::

፯ ወዓዲ ሶበ በዝኁ መነኮሳት ወመነኮሳይያት አንበረት ሥርዓተ ቀኖና ማዕከሌሆሙ ከመ ኢይዛውዑ በበይናቲሆሙ እመሂ በሐዊር ወእመሂ በቀዊም ወእመሂ በነቢር ከመኢይፅብዖሙ ሰይጣን ወኢይዝራዕ ውስተ ልቦሙ ሕንጽዋለ ወክርዳደ ወኢያማስን ኀጠተ ጽድቅ እንተ ዘርእት ውስተ ልቦሙ በከመ ይቤ ወንጌል በምሳሌ ዘርእ ኢይምሰልክሙ አ ፍቁራንየ አኮ ዘሠርዓት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሥርዓተ ነኪረ አላ አቅደሙ ወሠርዑ ዘንተ ሥርዓተ ፫፻፲ወ፰ ኤጲስቆጶሳት እንዘ ይብሉ መቅድመ ኩሉ ይርኃቁ ጻድቃን ወመነኮሳት እምአንስት ወኢያውሥእዎን ወኢይትናገርዎን ምንተኒ::

፰ ወበእንተዝ ለነኒ ርቱዕ ይደልወነ ንትሉ ዘንተ ሥርዓተ ወናንብሮ ከመ ኀልቀት ውስተ ልብነ ወከመ ማዕተብ በመዝራዕትነ በከመ ይቤ ጳውሎስ ሀለዉ አበዊነ እለ ወለዱነ በሥጋ ወይጌሥጹነ ወነኃፍሮሙ እፎ እንከ ፈድፋደ ንግነይ ወንትአዘዝ ለአበ መንፈስነ ይደልወነ ወንሕየው ወእሙንቱሰ ለሥላጤ ኀዳጥ መዋዕል ይጌሥጹነ በከመ ፈቀዱ ወውእቱሰ ለእንተ ትኄይስ ለነ ከመ ንርከብ ቅድሳቲሁ ኩሉ ተግሣጽ ኢይመስል ትፍሥሕተ ለጊዜሁ ዳዕሙ ኃዘን ውእቱ ወድኅረሰ ሰላመ ትፈሪ ለእለ ተገሠጹ ወተዓሥዮሙ ጽድቀ::

፱ ወእንበይነዝ ትብል እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እመ ርኢኩ በዓይንየ መነኮሰ ወመነኮሳይያተ እንዘ ይዛውዑ በበይናቲሆሙ እምፈቀድኩ ረጊዞቶሙ በረምኅ ኀቡረ ለክልኤሆሙ ወኢይትሐዘብ ከመ ይከውነኒ ጌጋየ ከመ ፊንሐስ ካህን ቀተሎሙ ለዘንበሪ ወለብእሲት መዲናዊት ወከመ ሳሙኤል ቀተሎ ለአጋግ እንዘ ካህናት እሙንቱ ወኢተበውሐ ለቀቲል እስመ ቀንዑ ቅንዓተ ለእግዚአብሔር ወኢኮኖሙ ጌጋየ አላ ይቤሎሙ እግዚአብሔር አስተንፈስክምዎ ለልብየ::





፮ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ሰዎች መልካም ሥራ እየሠሩ የትሩፋት ፍሬን ሲያበዙ ወደ ኃጢአት ከመመለሳቸው አስቀድሞ በመልካም ትሩፋት ሳሉ በሞት እንዲጠሩ ወደ እግዚአብሔር ትለምንላቸው ነበር የእርሻው ባለቤት እህሉ ለመታጨድ እንደደረሰ አይቶ የሚያጭዱትን ሰብስቦ እንደሚልካቸውና አጭደውለት እህሉን ወደ ጐተራው እንደሚሰበስብ እሷም ለእግዚአብሔር እጅ መንሻ አድርጋ ትልካቸዋለች::

፯ ዳግመኛም ወንዶች መነኮሳትና ሴቶች መነኮሳይያት በበዙ ጊዜ ሰይጣን እንዳይጣላቸውና በልባቸው ውስጥ እንክርዳድ እንዳይዘራ በልባቸው ውስጥ አሜከላና ቅንጣትን እንዳያጠፋባቸው ሴቶችና ወንዶች በሚቀመጡም በሚቆሙም በሚሄዱም ጊዜ እርስ በርሳቸው እንዳይጫዋወቱ በመካከላቸው ሥርዓት ሠራች ወንጌል በዘር ምሳሌ እንደተናገረ ወዳጆቼ ሆይ እናታችን አዲስ ሥርዓት የሰራች አይምሰላችሁ አስቀድመው ፫፻፲፰ቱ ኤጴስቆጶሳት ከሁሉ አስቀድመው እውነተኞች መነኮሳት ከሴቶች ይራቁ ምንም መልስ አይመልሱላቸው አያነጋግሯቸው ብለው ሥርዓትን ሠርተዋል እንጂ::

፰ ስለዚህ እኛም ይህን ሥርዓት እንከተል ዘንድና እንደቀለበት በአንገታችን እንደ ክትባት በክንዳችን እንይዝ ዘንድ ይገባናል ሐዋርያ ጳውሎስ በሥጋ የወለዱን አባቶቻችን አሉን ይቆጡናል እኛም እንፈራቸዋለን ከነሱ ይልቅ ለመንፈስ አባታችን ተገዝተንና ታዘን በሕይወት እንኖር ዘንድ ይገባናል በሥጋ የወለዱን ግን ለጥቂት ጊዜ ሲያሰለጥኑን እንደፈለጉ ይገስፁናል :የመንፈስ አባታችን ግን የተቀደሰችቱን ጸጋ እናገኝ ዘንድ ለምትሻል እንድንዘጋጅ ይገስፀናል ተግሣፅ ሁሉ ለጊዜው ለመልካም አይመስለንም ያሳዝነናል እንጂ ኋላ ግን ለተገሰፁት ሰላም ያፈራላቸዋል ጽድቅንም ይሰጣቸዋል::

፱ ስለዚህ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወንድ መነኩሴንና ሴት መነኩሲት እርስ በርሳቸው ሲጫዋወቱ ባይ ሁለቱን አንድ ላይ በጦር ብወጋቸው እወዳለሁ በደል ይሆንብኛል ብዩ አላስብም ካህኑ ፊናስ ዘንበሪንና መዲናዊትን ሴት እንደገደላቸው ሳሙኤል አጋግን እንደገደለ መግደል ያልተገባቸው ካህናት ሲሆኑ ቅናትን ለእግዚአብሔር ስለ ቀኑ በደል ሁኖ አለተቆጠረባቸውም እግዚአብሔር ልቡናየን ደስ አሰኛችሁት አላቸው እንጂ::

፲ ወካዕበ ለእመ አይድዕዋ ወነገርዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ተዓደዉ ዘንተ መነኮስ ወመነኮይያት ተሐምም ፈድፋደ ወትግዕር ወታንገረግር ዲበ ምድር እስከ ትቀይዕ ወትሰይን ደመ ወመግለ ወነበረት እንዘ ትሳቀይ ኵሎ ጊዜ በረቂቅ ስቃይ ለዓይነ ሰብእ ዘኢይትረአይ ወበዝንቱ ግብር ትትኌለቍ ከመ ሰማዕታት በከመ ኮነት ስምዓ ለሊሃ ሶበ ተስእላሃ አኃት እንዘ ይብላ ኦ እምነ ኵሉ ነገር ዘነበቡ ነቢያት ወሐዋርያት ወቅዱሳን በበጊዜሁ ተፈጸመ ወካዕበ ቦኑ ተሐሰወ ቃለ ቅዱሳን ዘነበቡ በእንቲአኪ ወንሕነ ሰማዕነ ከመ ሀለወኪ ትኩኒ ሰማዕተ አውሥአቶን እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎን እንዳዒ ኢየአምር ለእመ ይኌልቈ ሊተ እግዚአብሔር ለዝንቱ ሥቃይ ዘይረክበኒ እምኔክን በኀቡእ ለለዕለቱ ከመ ሥቃየ ሰማዕታት።

፲፩ ወበእንተዝ ነበረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ትሣቀይ ብዙኃ መዋዕለ በዝንቱ ሥቃይ ወበዘይመስሎ እመኒ ርእየት ወእመኒ ሰምዓት ከመ ተዓደዉ ሕገ ቀኖና ዘአንበረት ላዕሌሆሙ ወኢተኃድጎሙ ይትመከሩ በዘአምጽኡ መከራ ለሊሆሙ አላ ተሐምም በእንቲአሆሙ ወትሜጡ ነፍሳ ቤዛ ነፍሶሙ በከመ ይቤ ጳውሎስ መኑ ዘይደዊ ወኢየሐምም አነ ወመኑ ዘይስሕት ወኢይደነግጽ አነ።

፲፪ ወካዕበ ይቤ አማን እብለክሙ በእንተ ክርስቶስ ወኢይሔሱ ወስምዕየ መንፈስ ቅዱስ ዘውስተ ልብየ ከመ እቴክዝ ወእሐምም በልብየ ፈድፋደ በኵሉ ጊዜ ወእፈቱ ከመ አነ እትማህለል እምክርስቶስ በእንተ አኃውየ ወአዝማድየ ወእምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትትሜሰል ከማሁ ወትፈርህ ከመ ኢይትኃሠሡ ነፍሶሙ እምኔሃ በከመ ይቤ ወንጌል እስመ ለብዙኅ አመገብዎ ብዙኃ ይትኃሠሥዎ ወለዘሂ ፈድፋደ አማኀፀንዎ ፈድፋደ የሐትትዎ።

፲፫ እመሰ ከመዝ ተሐምም ወትሣቀይ በእንቲአነ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ንሕነኒ ይደልወነ ንዕቀብ ሥርዓታቲሃ በተጠናቅቆ ወንግበር ትእዛዛቲሃ በአስተሐምሞ ወፃኅቅ፡ወኢንብላዕ ዕፀ ከመ አቡነ አዳም ወእምነ ሔዋን ከመ ኢንሰደድ እምገነት ወኢንስርቅ ኀሩመ ከመ አካን ከመ ኢናመጽእ ላዕሌነ ሞተ አኮ ሞተ ሥጋ አላ ሞተ ነፍስ።





፲ ዳግመኛም ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወንድ መነኩሴና ሴት መነኩሲት ይህን ሥርዓት አፈረሱ ብለው በነገሯትና በአስረዷት ጊዜ ወዲያውኑ በሰው ዓይን ለማይታይ ረቂቅ በሆነ በሽታ ተይዛ ሁልጊዜ ስትሰቃይ ትኖራለች ኋላ ግን በጌታችን ዘንድ እንደሰማዕትነት ይቆጠርላታል እኅቶችም እናታችን ሆይ ነቢያትና ሐዋርያት ቅዱሳንም የተናገሩት ሁሉ በጊዜው ተፈጸመ በአሏት ጊዜ እሷ እራሷ ምስክር እንደሆነች እንደገናም በውኑ ሰማዕትነትን እንደምትቀበዪ ቅዱሳን የተናገሩት ቃል ሐሰት ይሆናልን አሏት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም መልሳ ከእናንተ የተነሣ በረቂቅ የሚያገኘኝን ይህን ስቃይ እግዚአብሔር እንደ ሰማዕታት ሥቃይ ይቆጥርልኝ እንደሆነ እንጃ ምን አውቃለሁ አለቻቸው።

፲፩ ስለዚህ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ብዙ ዘመን በዚህና ይህን በመሰለው ሥቃይ ስትሰቃይ ኖረች የሠራችላቸውን ሥርዓት ሲያፈርሱ በሰማችና በአየች ጊዜ በራሳቸው ላይ በአመጡት መከራ እንዲጐዱ ዝም አትላቸውም ስለ እነሱ ድኅነት ሰውነቷን ለመከራ አሳልፋ ትሰጣለች እንጂ ጳውሎስ ማን ታሞ እኔ አልታመምም ማንስ ስቶ እኔ አልደነግጥም እንደአለ።

፲፪ ዳግመኛም ስለክርስቶስ ሳልዋሽ እውነት እነግራቸዋለሁ ስለ ዘመዶቼና ስለ ወንድሞቼ በልቡናየ አዝኜና ተጨንቄ ሁልጊዜ ከክርስቶስ እለምን ዘንድ እወዳለሁ እንደአለ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም እንደእሱ ስለሆነች ነፍሳቸውን ከእሷ እንደሚፈልግ አስባ ትፈራለች ወንጌል ብዙ ለሰጡት ብዙ ጥቂት ለሰጡት ጥቂት ይፈልጉበታል እንደአለ ።

፲፫ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ስለእኛ እንደዚህ የምትጨነቅና የምትሰቃይ ከሆነ እኛም ሥርዓቷንና ሕጓን በጥንቃቄ መጠበቅ ይገባናል እንደ አባታችን እንደአዳምና እንደ እናታችን እንደሔዋን ሕግ የማፍረስ ዕፀ በለስን በልተን ከገነት እንዳንሰደድ እንደ አካን የተከለከለውን ሰርቀን ሞትን በራሳችን ላይ እንዳናመጣ ያውም ሞተ ሥጋ ሳይሆን ሞተ ነፍስን።

፲፬ ንግባእኬ ኀበ ዘቀዳሚ ነገርነ ወነበረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ውስተ ደምበዛ በዘከመዝ ግብር በውእቱ ሰቀላ ዘአግበረት ቅሩበ ቤተ ክርስቲያን ዘታቦተ ቍስቋም እንዘ ታሌሊ ወትገይስ ኀቤሃ ኵሎ አሚረ ወእንዘ ትስእል ወታስተበቍዕ ኀበ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወለዲተ አምላክ ወኀበ ፍቁር ወልዳ በእንተ መድኃኒተ ነፍሳ ወፈድፋደሰ በእንተነፍሰ ኵሎሙ ማኅበራኒሃ ወእምድኅሬሁ መጽአ አባ ዘማርያም መምህር ዘደሴተ ሬማ ቅድስት ምስለ ብዙኃን መነኮሳት ወሰአልዋ ከመ ትሕንፅ ሎሙ ቤተ ክርስቲያኖሙ ዘውእቱ መድኃኔ ዓለም እንተ ውስቴቱ ተቀብሩ አቡሃ ወእማ።

፲፭ አው፡ሥአቶሙ ወትቤሎሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እፎ ይትከሃለኒ ሊተ እግበር ዘንተ ዓቢየ ግብረ ወባሕቱ ንጸሊ ኀበ እግዚአብሔር አነሂ ወአንትሙ ወዘፈቀደ እግዚአብሔር ለይኩን ወዘንተ ብሂላ ፈነወቶሙ ወገብኡ እሙንቱ ወአተዉ ደብሮሙ ወእምዝ ጸለየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በዓቢይ ቀኖና ሰቡዓ ዕለተ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ዘደምበዛ ወከሠተ ላቲ እግዚአብሔር ወይቤላ ሑሪ ሕንፂ ወአነ እሄሉ ምስሌኪ ወእትራድአኪ ወእፌጽም ለኪ።

፲፮ ወእምድኅረዝ ወፅአት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እምደምበዛ ወቦአት ሬማ ወምስሌሃ ኵሎሙ መነኮሳት ወመነኮሳይያት ወነሠተት ጠፈረ ሰቀላ ዘቀዳሚ ወወጠነት ሠናየ ሕንፃ እንዘ ይእቲ ትቀድሕ ማየ እምነ ባሕር ወትጸውር በዘባና ወሀለዋ ምስሌሃ ክቡራት አንስት እምአዋልደ ዌዛዝር ወእምዕቅብታተ ንጉሥ ወእም አንስቲያ መኳንንት ወኮና ይትጌበራ ምስሌሃ ወይተልዋ ኪያሃ ቦ ጊዜ ኀበ ቀዲሐ ማይ ወቦ ጊዜ ኀበ ጸዊረ ዕቡር ወዕብን ወመነኮሳትሂ ብዙኃን ሀለዉ ቦ እለ ኃደጉ አበዊሆሙ ወእሞሙ አንስቲያሆሙ ወውሉዶሙ ወኵሎ ጥሪቶሙ ወገራውሂሆሙ ወቦ እለ ኃደጉ ውርዙቶሙ ወኵሎ ፍትወታቲሆሙ ሥጋዊያተ ቦን አንስትኒ እለ ኃደጋ አምታቲሆን ወቦን ደናግልኒ እለ ዓቀባ ድንግልናሆን ወተፍሕራ ለመርዓዊሆን ክርስቶስ ወአፍቀራሁ ወተለዋሁ በኵሉ መዋዕለ ሕይወቶን።





፲፬ ወደቀደመ ነገራችን እንመለስና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በደምበዛ በአለችው ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በተሠራች አዳራሽ ውስጥ እየተቀመጠች ዘወትር ማልዳ ወደቍስቋም እየገሠገሰች አምላክን ወደወለደች ወደ እመቤታችን ቅድስት ድንግልና ወደ ልጇ ወዳጇ ስለ እራሷ ድኅነትና ይልቁንም በአንድነት ስለአሉ ልጆቿ ድነትን ስትለምንና ስትማፀን ቆየች ከዚህ በኋላ አባ ዘማርያም የሚባል የቅድስት ሬማ ደሴት መምህር ከብዙ መነኮሳት ጋር ወደእሷ መጥቶ እናቷና አባቷ በውስጡ የተቀበሩበት የመድኃኔዓለምን ቤተ ክርስቲያን ትሠራላቸው ዘንድ ለመኗት ።

፲፭ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም መልሳ ይህ ታላቅ ሥራ ለኔ እንደምን ይቻለኛል ነገር ግን እኔም እናንተም ወደ እግዚአብሔር እናመልክትና እሱ የፈቀደው ይሁን አለች ይህን ብላ ሸኘቻቸውና ተመልሰው ወደ ደብራቸው ገቡ ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም በደምበዛ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሰባት ቀን ታላቅ ቀኖናና ሱባኤ አድርጋ እግዚአብሔር እኔ ከአንቺ ጋር ሆኘ እረዳሽና እፈጽምልሻለሁ ሄደሽ ሥሪ አላት ።

፲፮ ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከደምበዛ ወጥታ ሬማ ገባች ብዙ መነኮሳትና መነኮሳይያትም ከእሷ ጋር ነበሩ አስቀድሞ የነበረውን የቤተክርስቲያኑን ጣሪያ አፍርሳ ከባሕር ውሀን ቀድታ በጀርባዋ እየተሸከመች መልካም ሕንፃን ጀመረች ብዙ የንጉሥ ሚስቶችና የመኳንንት ሚስቶች የሴት ወይዘሮች ልጆች የሚሆኑ የከበሩ ሴቶች ከእሷ ጋር ሆነው እሷን ተከትለው ውሀን የሚቀዱ ጭቃንና ድንጋይን የሚሸከሙ አሉ ከወንዶች መነኮሳትም እናት አባቶቻቸውንና ሚስቶቻቸውን ልጆቻቸውን ንብረታቸውን ሥጋዊት የሆነች ሐሳባቸውን ትተው እሷን ተከትለው የሚሠሩ ወንዶች ወጣቶችና ባሎቻቸውን የተው ሴቶችና መላ ዘመናቸውን ለክርስቶስ ሙሽራ ለመሆን ድንግልናቸውን ጠብቀው የሚኖሩ ደናግል ከእሷ ጋራ አሉ።

፲፯ በከመ ይቤ ሰሎሞን ደናግል አፍቀራከ ወተለዋ ድኅሬከ ቦ ሕፃናት እድ ወአንስት እለ ተለዉ አበዊሆሙ ወእማቲሆሙ ወቦ አግብርት ወአዕማት እለ ተለዉ አጋእዝቲሆሙ ወግዕዙ እምግብርናት ወአምሠጡ እምቅንየት ወተዓረዩ ምስለ አጋእዝቲሆሙ ወአዕረፉ እምፆማ ወእምሥራኅ በከመ ይቤ ወንጌል ንዑ ኀቤየ ሥሩሐን ወክቡዳነ ፆር ወአነ አዓርፈክሙ ወቦ ኃጥአንሂ ንዑ ኀቤየ ሥሩሐን ወክቡዳነ ፆር ወአነ አዓርፈክሙ ወቦ ኃጥአንሂ ወዘማውያን እለ ተመይጡ ውስተ ንስሓ ወኃደጉ ግብሮሙ ዘቀዳሚ ወኮኑ ደናግለ ለክርስቶስ ወቦ ህየ ነዳያን ወምስኪናን ዕውራን ወሐንካሳን ተማኅፀኑ ወተፀወኑ ባቲ ወአርኃወት ኆኅተ ቤታ ለኩሉ ዘይበውእ በከመ ይቤ ወንጌል ለዘመጽአ ኀቤየ ኢይሰድዶ ወኢያወፅኦ አፍአ።

፲፰ በከመ ይቤ ጳውሎስ አልቦ አይሁዳዊ ወአልቦ አረማዊ አልቦ ነባሪ ወአልቦ አግአዚ ወኮነ በመዋዕሊሃ ሰላም ወፍቅር አልቦ ዘያደሉ ለርእሱ ዘእንበለ ለቢጹ አልቦ ባዕድ ወአልቦ ዘመድ አላ ኵሎሙ ዕሩያን እሙንቱ በ፩ ልብ ወበ፩ ነፍስ እንዘ ማዕከሌሆሙ ክርስቶስ ዝ ውእቱ ሳድስ ማኅበር።

ምዕራፍ ፲፰ ዘቀዳሚት

፩ ወሶበ በዝኀ ፈድፋደ ጸበበቶሙ ሬማ ወኢክህለት አግምሮቶሙ እስመ ኮኑ ይትዌሰኩ ለለጽባሑ ወወሀብዋ መካነ በጽንፈ ባሕር ዘስሙ አፈር ፈረስ ወገብረት ላቲ ማኅደረ ምስለ አኃት ወአኃውሰ ነበሩ ውስተ ዓፀደ ቤተ ክርስቲያን ዘቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ወይእቲሰ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ነበረት እንዘ ታስተባሪ ቦ ጊዜ ሬማ ወቦ ጊዜ አፈርፈረስ ወለለጽባሑ ተአቱ ሬማ ወታስተጌብር ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ወምሴተ ትወፅእ ወተሐውር አፈርፈረስ ወትበይት ምስለ አኃት።

፪ ወአሐተ ዕለተ እንዘ ሀለወት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መልዕልተ ታንኳ ከመ ትፃእ ወትሑር አፈርፈረስ ተንሥአ ሶቤሃ ነፋስ ኃያል ዘስሙ ላጕኒ ወነድኦ ለታንኳ ወወሰዶ ወአብጽሖ በቅጽበት ኀበ ማኅደረ ስብሐት ወቀብፁ ተስፋ ድኂን እለ ሀለዉ ምስሌሃ ውስተ ሐመር እለኒ ሀለዉ ምስሌሃ ውስተ የብስ ወእለኒ ይቀውሙ ውስተ ደሴት አውየዉ ኵሎሙ ኅቡረ እስመ መሰለቶሙ ዘተሐጕለት ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኢትፈርህ ወኢትደነግፅ እስመ ትትዌከል በእግዚአብሔር አምላከ አድኅኖ ዘይክል ኵሎ ወአልቦ ዘይስእኖ ዳእሙ ትጼሊ በልባ ሰላመ መልአክ ወዓዲ ትጌሥጾሙ ለእለ ሀለዉ ምስሌሃ ከመ ኢይፍርሁ።





፲፯ ሰሎሞን ደናግል አንተን ወደዱህ ፍለጋህን ተከተሉ እንደ አለ አባቶቻቸውንና እናቶቻቸውን ተከትለው ወደእሷ የመጡ ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች አሉ ከጌቶቻቸው ጋር ተመርጠው ከባርነትና ከመገዛት ነፃ ወጥተው ጌቶቻቸውን ተከትለው ወደእሷ የመጡ ወንዶች ባሮችና ሴቶች ገረዶች አሉ ወንጌል እናንተ ሸክም የከበዳችሁ ወደእኔ ኑ እኔ አሳርፋችኋለሁ እንደአለ ዘማውያንና የተለያየ ኃጢአት የሚሠሩ ኃጥአን የቀደመ መጥፎ ሥራቸውን ትተው ንስሐ ገብተው ለክርስቶስ ሙሽራ ሆነው ከእሷ ጋር ይሠሩ ነበር ነዳያንና ምስኪናን ዓይነ ሥውሮችና አንካሶች እሷን ተማፅነው ወደ እሷ ተጠግተው የተቀመጡ አሉ ወደ እሷ ለሚገባ ሁሉ የቤቷን ደጃፍ ከፈተችላቸው ወንጌል ወደ እኔ የሚመጣውን አላባርረውም ከቤቴም ወደውጪ አላወጣውም እንደአለ።

፲፰ ጳውሎስም ይህ አይሁዳዊ ነው ይህ አረማዊ ነው ይህ ጌታ ነው ይህ ባሪያ ነው ማለት የለም እንደአለ በዘመኗ ሰላምና ፍቅር ሆነ ለጓደኛው እንጂ ለራሱ የሚያደላ አልነበረም ይህ ባዕድ ነው ይህ ዘመድ ነው አይባልም ክርስቶስ በመካከላቸው ስለሆነ ተስተካክለው አንድ ልብ አንድ አካል ናቸው እንጂ ስድስተኛ ማኅበር ይህ ነው።

ምዕራፍ ፲፰ የቀዳሜ

፩ እጅግ በበዙ ጊዜ ሬማ ጠበበቻቸው እነሱ ዕለት ዕለት እየበዙ ይሄዳሉና ስሙ አፈር ፈረስ የሚባል ቦታንም ሰጧት ለራሷ ከእኅቶች ጋር ቤት ሠራች ወንድሞች ግን ከዮሐንስ ወንጌላዊ ቤተክርስቲያን አካባቢ ተቀመጡ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እያፈራረቀች አንድ ጊዜ ሬማ አንድ ጊዜ አፈር ፈረስ ተቀምጣ በየቀኑ ወደሬማ እየተመላለሰች የቤተ ክርስቲያኑን ሕንፃ ታሠራ ነበር ማታ ከሬማ ወጥታ ወደ አፈር ፈረስ ሄዳ ከእኅቶች ጋር ታድራለች ።

፪ ከዕለታት በአንድ ቀን እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወደ አፈር ፈረስ ለመሄድ በታንኳ ላይ ሳለች እንደ አውሎ ነፋስ ያለ ታላቅ ነፋስ ተነሥቶ እሷ ያለችበትን ታንኳ እየነዳ በፍጥነት እሷ ወደ አልፈለገችበት ወሰደው ከእሷ ጋር በታንኳ ውስጥ ያሉና በደረቅ ቦታ ደሴት ላይ የቆሙ ሁሉ በአንድነት ጮኹ የምትሰጥም መስሏቸዋልና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ግን ፈጽማ አልፈራችም የሚሳነው ነገር በሌለው ሁሉን በሚችል የማዳን ፈጣሪ በሆነ በእግዚአብሔር አምናለችና በልቡናዋም የመልአኩን ሰላምታ እየጸለየች ከእሷ ጋር ያሉት እንዳይፈሩ አትፍሩ እያለች ትቆጣቸውም ነበር።

፫ ወይእተ ጊዜ ተገሠጸ ነፋስ ወአርመመ ማዕበል ወኮነ ዛኅነ ወተመይጠት በዳኅና ወበሰላም ወአተወት ቤታ ወነበረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ትፃሙ ኵሎ አሚረ እስከ ይትፌጸም ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ወበ፩ዱ እመዋዕል ሖረት ከመ ታምጽእ ጸርበ እምነ ወንድጌ ወኮነ ላቲ በከመ ሐለየት ወገብአት በሰላም ወእሉስ ማኅበር በዝኅ ፈድፋደ ወኮኑ መጠነ ፰፻ ወእምዝ ሠርዓት ሎሙ ሥርዓተ ማኅበር እንዘ ታስተዋፅእ እምነ መጻሕፍት ቅዱሳት ወእምዜና አበው ክቡራን ወእምሥርዓተ ሐዋርያት በከመ ይቤ መጽሐፈ አብርክሲስ ወኵሎሙ እለ አምኑ ኅቡረ ይነብሩ ወድሙር ኵሉ ንዋዮሙ ወጥሪቶሙ ይሠይጡ ወይሁቡ ለነዳይ::

፬ ወኵሎ ዕለተ ይጸመዱ ለቤተ መቅደስ በ፩ ነፍስ ወኅቡረ ይባርኩ ማዕደ ውስተ ቤት ወይሴሰዩ ሲሳዮሙ በትፍሥሕት ወበየውሀተ ልብ ወየአኵቱ እግዚአብሔርሃ ወአልቦ በውስቴቶሙ ዘ ይብል ዝሰ ዘዚአየ ንዋይ አላ ዘኵሎሙ ወአልቦ በውስቴቶሙ ዘ ይብል ዝሰ ዘዚአየ ንዋይ አላ ዘኵሎሙ ኅቡረ ወከማሁ ኮነ በመዋዕሊሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወዐቢይ ሞገስ ባቲ በኀበ ኵሎሙ ወይፈርህዋ ወያከብርዋ ወአልቦ ዘይትዓደው እምዝንቱ ሥርዓት ወኮኑ ይትፋቀሩ በበይናቲሆሙ ከመ ነፍስ ወሥጋ እኁ ምስለ እኁሁ ወእኅት ምስለ እኅት::

፭ ወአልቦ ዘይብል እምኔሆሙ ባሕቲትየ እበልዕ ወባሕቲትየ እሰቲ ወባሕቲትየ እለብስ አላ ኮኑ ይትካፈሉ እመኒ ኮነት እሐተ ፍሬ ኢይበልዕ ባሐቲቱ ወሶበ ይረፍቁ ውስተ ምስታይ ለእመ ወሀብዎ ጽዋዓ ይሁቦ ለካልኡ እንዘ ይብል አንተ ትጸምእ እምኔየ ወአነ እጌይስ እምኔከ ወእንዘ ይሜጡ ካልእ ለካልኡ የዓውድ ጽዋዕ ወይገብእ ኀበ ቀደማዊ እኁ ወሶበኒ ወፅኡ ኀበ ተልእኮ ወኀበ ምስያጥ እመኒ አኃው ወእመኒ አኃት ያስተፋንውዎሙ ነግሀ እንዘ ይበክዩ ወይትቄበልዎሙ ሰርከ እንዘ ይስሕቁ ወይትፌሥሑ::

፮ ወዓዲ ሠርዓት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ላዕለ አኃው ወላዕለ አኃት ከመ ኢይሑሩ ፩ወ፩ እንተ ባሕቲቶሙ አላ በበ፪ እመኒ ኮነ ቅሩበ ወእመኒ ርሑቀ እመኒ ኀበ ቤተ ክርስቲያን አው ኀበ ሰብአ ሀገር ወለ እመኒ ፈለሱ ኀበ ካልእ ሀገር ወሠርዓት





፫ በዚያን ጊዜ ወዲያው ነፋሱ ተወገደና ማዕበሉ ፀጥ ብሎ ፀጥታ ሆነ እሷም ተመልሳ ወደቤቷ ገባች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ እስኪፈጸም በጣም ትደክም ነበር ከዕለታት በአንድ ቀን ከወንድጌ የተጠረበ እንጨት ታመጣ ዘንድ ሄዳ እንደአሰበችው ሆነላትና በሰላም ይዛ መጣች እነዚያ ከሷ ጋር ያሉ ማኅበርተኞች እጅግ በዝተው እስከ ስምንት መቶ ሆኑ ከዚህ በኋላ ከቅዱሳን መጻሕፍትና ከከበሩ ከአባቶች ዜና ከሐዋርያት ሥርዓትም እያወጣጣች ሥርዓት ሠራችላቸው የሐዋርያት ሥራ ያመኑ ሁሉ በአንድነት ይኖሩ ነበር ገንዘባቸውም በአንድነት ነው ሽጠው ለውጠው ለነዳያን ይሠጣሉ እንደአለ::

፬ ዘወትር ለቤተ መቅደስ ጽሙድ እንደ በሬ ቅኑት እንደ ገበሬ ሆነው በአንድነት ያገለግሉ ነበር በቤታቸውም እግዚአብሔርን አመስግነው ማዕዳቸውን ባርከው በአንድነት ይመገቡ ነበር ከመካከላቸውም ይህ የእኔ ገንዘብ ነው የሚል የለም በአንድነት የሁላቸውም ገንዘብ ነው እንጂ በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘመን እንደዚህ ነበር በሁሉ ዘንድ ታላቅ ሞገስ ነበራትና ሁሉ ይፈሯትና ያከብሯት ነበር ከዚህ ሥርዓትና ከትዕዛዟ የሚተላለፍ አልነበረም ወንድም ከወንድም እኅት ከእኅት ጋራ እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ ተስማምተውና ተፋቅረው ይኖራሉ::

፭ ከእነሱ መካከል ብቻየን ልብላ ልጠጣ ልልበስ የሚል የለም ይካፈሉ ነበረ እንጂ አንዲት ፍሬም ብትሆን ብቻውን የሚበላ የለም ቁጭ ብለው በሚጠጡበት ጊዜ ለአንዱ ጽዋ ቢሰጡት ከኔ ይልቅ አንተን ጠምቶዋል እኔ ከአንተ እሻላለሁ ብሎ ለሌላ ይሰጣል ያም እንደዚሁ ለሌላ ሲሰጥ ያ ጽዋ ዞሮ ለመጀመሪያው ይደርስ ነበር ወንድሞችም ሆኑ እኅቶች ወደ ተልዕኮም ሆነ ወደገበያ ሲሄዱ ጡዋት እያለቀሱ ተሸኛኝተው ይለያያሉ ማታ ፈገግ እያሉ በደስታ ይቀባበላሉ ::

፮ እንደገና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለየብቻቸው አንድ አንድ ሆነው እንዳይሄዱ ሁለት ሁለት እየሆኑ ቅርብም ሆነ እሩቅ ወደ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ወደአካባቢ ሰዎች ወደ ሌላም አገር እንዲሄዱ ሥርዓት ሠራች ወንድ መነኵሴም ከሴቶች ጋር በአንድ ማዕድ ተቀምጦ እንዳይበላ ሴቶች መነኮሳትም ከወንዶች ጋር ተቀምጠው በአንድ

ከመ ኢይብላዕ መነኮስ ምስለ አንስት በአሐቲ ማዕድ ወመነኮሳይያትኒ ምስለ ዕደው ወኢይኅድር መነኮስ ውስተ ቤት ዘባቲ ብእሲት ወኢትኅድር መነኮሳይት ውስተ ቤት ዘቦቱ ብእሲ ወትቤሎሙ ይኄይሰክሙ ይብልዑ ሥጋክሙ አራዊት እም ይብልዑ ነፍስክሙ ወሥጋክሙ ሰይጣናት ።

፲ ወእለሂ ተርፉ እምትእዛዛት ከመ ኢይትናገሩ ቃለ በክላህ አላ በልኆሳስ ወከመ ኢይሑሩ በፈቃዶሙ ዘእንበለ ይሰነዓሉ እመኒ ኅበ ቍርባን ወእመኒ ኅበ ማኅፀብ ዘልብስ ወኢይስትዩ ፈውሰ ዘዘዚአሁ ወእመኒ ሖሩ ኅበ ሀገር ኢይብልዑ ለእመ ኢኃደሩ ወለእመ የሐውሩ ኅበ ቍርባን ኢይትናገሩ ክንቶ ምስለ ሰብእ በሐረቶሙ ወበግብአቶሙ ወኢይቅረብ ጥዑይ በሰሙን ዘእንበለ በዓላት ወኢይትላጸዩ ርእሶሙ ወከመ ይትጋብኡ በጸሎተ ማዕድ ወበጸሎተ ንዋም ወበኵሉ ሰዓት ጊዜ ይነቁ ደወል፡ ወለእመ ተዓደዉ ዘንተ ሥርዓተ እመሂ ንዑስ አው ዐቢይ አንበረት ላዕሌሆሙ ሕገ ተግሣጽ በበ፸ ጥብጣቤ ወኮነት እምተሕቴሃ ሊቅተ እኀተ ክርስቶስ ወባቲ ሥልጣን ላእለ ኵሉ ግብር ወእሉሰ ማኅበር መነኮሳት ወመነኮሳይያት ኮኑጽሙዳነ ለእግዚአብሔር ዘእንበሌሁ፡ሰ፡ባዕድ ትካዝ አልቦሙ ወአግረሩ ርእሶሙ ታሕተ እግራ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ።

፲፩ ወይእቲኒ ነበረት እንዘ ተዓቅቦሙ ከመ ብንተ ዓይን ወከመ ታስተሐይፅ ስገኖ አንቆቅሆሃ ወከማሁ ታስተሐይፅ ኅበ ነፍሳቲሆሙ መዓልተ ወሌሊተ ወኵሎ አሚረ ትሴሰይ ሐመደ ወኮሶ በእንተዚአሆሙ በከመ ሰትየ እግዚእነ ሐሞተ ወከርቤ ሶበ ጥዕመ ሞተ ለቤዛ ዓለም ስምዑኬ አ ፈቁራንየ እምነ ኵሉ ፃር ይከብድ አረር ወእምኔሁኒ ይከብድ ፀዊረ ግዕዘ ፩ዱ ሰብእ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትቤ ለእመ ኮነ ይበዝኅ እምነ ማኅበር ዘአሜሃ ወእመ ተወሰከ ዲቤሁ ምክዕቢተ እምፃረ ወእምአግመረ ልብየ በኃይለ እግዚአብሔር አምላኪየ።

፲፪ እስመ ሀብተ ትዕግሥት ተውህበ ላቲ ወትዕግሥትኒ ርእሰ ምግባራት ይእቲ ወባቲ ይትረከብ መንግሥተ ሰማያት በከመ ይቤ ወንጌል ወበትዕግሥትክሙ ታጠርይዋ ለነፍስክሙ ሚ ይሴኒ ወይጥዕም ዜናሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ይደልወነ ለመዓርኒ ወለሦከርኒ አልቦሙ ጣዕም ዘከማሃ ወበእንተዝ ይደልወነ ናፍቅራ ለዛቲ ቅድስተ ክርስቶስ ምንንት በኀበ ሰብእ ወትሕት በኀበ ኵሉን አኃት እስመ ይእቲ አገበረተኒ ሊተ ለጽሒፈ ዝንቱ ዜና ወለከሚተ ዝንቱ መድፍን ዘኅቡእ ውስተ ገራኅተ ልቦሙ ለአዕሩግ ሶበ ነደት በፋቅረ ዚአሃ ።





ማዕድ እንዳይበሉ ወንድ መነኩሴ ሴት ካለችበት ቤት እንዳያድር ሴት መነኩሲትም ወንድ ካለበት ቤት እንዳታድር ሥርዓት ሠራች ሰይጣናት ሥጋቸሁንና ነፍሳቸሁን ከሚበሉ አራዊት ሥጋቸሁን ቢበሉ ይሻላቸኋል ትላቸዋለች።

፲ ከትእዛዛትም የቀሩትን ጮኸው እንዳይናገሩ ወደቍርባንም ሆነ ወደ ልብስ ማጠብ ሳይሰናበቱ እንዳይሄዱ መጠጣታቸውን ሳይናገሩ ኮሶ እንዳይጠጡ ወደ ሌላ ቦታ ሄደው ካላደሩ በስተቀር እንዳይበሉ ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ሲሄዱና ተቀብለው ሲመለሱ ከሰው ጋር ዋዛ ፈዛዛን እንዳይጫወቱ ጤነኛ በበዓላት ካልሆነ እንዳይቀርብ አራሳቸውን እንዳይላጩ በጸሎተ ማዕድና በጸሎተ ንዋም ጸሎትን ለመጸለይ ደወል በሚመታ ሰዓት ሁሉ ይሰበሰቡ ዘንድ ሥርዓትን ሠራች ይህን ሥርዓት ያጓደለ ሰው ቢኖር ዓርባ ዓርባ ጅራፍ እንዲገረፍ ደነገገች ከእሷ በታች እኅተ ክርስቶስ አለቃ ሆነች በሚሠራ ሥራ ሁሉ ላይም ሥልጣን ተሰጣት እነዚህ የወንዶች መነኮስትና የሴቶች መነኮሳይያት ማኅበር ለእግዚአብሔር ጽሙድ እንደ በሬ ቀኑት እንደ ገበሬ ሁነው ያገለግሉት ነበርያለእሱም ሌላ የሚያስቡት ነገር አልነበረም ከእናታችን ቅድስትናቡርክት ወለተጴጥሮስ ሥልጣን በታች እራሳቸውን ዝቅ አድርገው ተገዙ።

፲፩ እሷም እንደዓይን ብሌን ትጠብቃቸው ስጕን እንቁላሏን ትክ ብላ እንደምትመለከት በቀንና በሌት ነፍሳቸውን ትመለከት ነበር ስለ እነሱ ዘወትር አመድንና ኮሶን ትመገብ ነበር ዓለምን ለማዳን ጌታችን በሚሞት ጊዜ ከርቤንና ሐሞትን እንደጠጣ ወዳጆቼ ሆይ የምነግራችሁን ስሙኝ ከሸክም ሁሉ ባልጩት ይከብዳል ከእሱም ይልቅ የአንድ ሰው ጸባይ መቻል መታገሥ ይከብዳል እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ግን አሁን ካሉት ማኅበር ይልቅ ሁለት እጅ ቢጨመር በፈጣሪየ እግዚአብሔር ኀይል ልቡናዬ በቻለ ነበር ትላለች ።

፲፪ ሀብተ ትእግሥት ተሰጥቷታልና ትግሥትም የምግባራት ሁሉ አለቃ ናት መንግሥተ ሰማያትም በሷ ይገኛል ወንጌል በትዕግሥታችሁ ነፍሳችሁን ታድናላችሁ እንደ አለ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዜና ገድሏ ምን ያህል ይጥማል ስኳርም እንደ እሷ ዜና አይጣፍጥም ስለዚህ ለክርስቶስ የተመረጠች እቃ የሆነችውን አርዓያ ለመሆን እራሷን ዝቅ ያደረገች ይህችን እናታችንን እጅግ እናፈቅራትና እናከብራት ዘንድ ይገባናል ልቡናየ በእሷ ፍቅር በነደደ ጊዜ በአባቶች ልቡና እርሻ የተሰወረ ረቂቅ የሚሆን ዜና ገድሏን ለመጻፍና ለመግለጥ እሷ ፈቃዷ ሆኖ አስገደደችኝ።

፲ መፍትው ለነኒ ንዘከራ ወናነብብ ዜናሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል በእንተ ብእሲት እንተ ቀብዓቶ ዕፍረተ አማን እብለክሙ ኀበ ሰበክዋ ለዛቲ ወንጌል ውስተ ኵሉ ዓለም ያንብብዋ ዘገብረት ዛቲ ብእሲት ወይዝክርዋ አ ዕሙቅ ብዕለ ጥበቡ ለእግዚአብሔር ዘሰውር እምኔነ እንዘ ብዙኃን አዕሩግ ሀለዉ እምውሉዳ አስተናሥአ ኪያሃ ለቅድስተ ክርስቶስ እንተ ትንዕስ እምኵሉ ወአስተዳለወ ስብሐቲሁ ውስተ አፉሃ በከመ ይቤ መጽሐፍ እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሐተ ወይእዜኒ ይደልወነ ንዘከር ኂሩታቲሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጣዕመ ቃላ ወሣዕሣዓ አፉሃ እስመ ይእቲ ትናዝዝ ወትየውሕ ወኢትቀኒ በኵርህ።

፲፩ በከመ ይቤ ጴጥሮስ ወእንዘ ተዓቅብዎሙ ወኢትቅንይዎሙ በኵርህ አላ በጽድቅ በእንተ እግዚአብሔር እንዘ ኢትትሄየሉ ሕዝቦ ወለእመ መጽአ እኁ ኀቤሃ እንዘ ይትመዓዕ በትዕቢት ሶበ አንበረት እዴሃ ዲበ መታክፍቲሁ ወገሰሰቶ ይወርድ እምላዕሌሁ ሰይጣነ መዓት ወትዕቢት ወይከውን ሶቤሃ የዋሃ ወትሑተ ወይወድቅ ታሕተ እገሪሃ እንዘ ይብል አበስኩ ስረዪ ሊተ ወዓዲ ለእመ ቦቱ ሰይጣነ ዝሙት ወስስዕት ሶበ ይከሥት ላቲ ለእመ መዓደቶ ወናዘዘቶ ይትዓተት ሎቱ ሶቤሃ ወኢይትቃተሎ ዳግመ።

፲፪ ወካዕበ ለእመ መጽኡ ኀቤሃ ክቡራን እለ መነኑ ክብሮሙ እመኒ ብእሲ ወእመኒ ብእሲት ኢታጸውሮሙ ጾረ ክቡደ ዘኢይክሉ ጸዊሮተ ኢበመብልዕ ወኢበመስቴ አላ ትሁቦሙ መፍቅዶሙ ከመ ኢይጕየዩ ወኢይግብኡ ድኅሬሆሙ እስመ ሕፃናተ ልብ እሙንቱ በከመ ይቤ ጳውሎስ ከመ ዘለሕፃናት በሃይማኖተ ክርስቶስ ሀሊበ ወጋዕኩክሙ ወአኮ መብልዓ ጽኑዓ ዘአብላዕኩክሙ እስመ ዓዲክሙ ኢጸናዕክሙ ፡ በሕገ ሥጋ ወደም ሀለውክሙ ወከማሁ ትገብር እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወኢትክልአሙ ምንተኒ አላ ለሊሆሙ በፈቃዶሙ የኃድጉ ፋጡነ ወይሳተፉ በከመ ልማደ ማኅበር።

፲፫ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ትረፍቅ ምስለ አኃት ውስተ ማዕድ ሶበ ያቄርቡ መባልዕተ ቅሱማተ ዘዘዚአሁ ትእኅዝ አዕናፊሃ ከመ ኢይባእ ጼናሁ ወታስተማስሎ ከመ ፂና ኵስሕ ወእምታሕተ ማዕድ ያነብሩ ላቲ መብልዓ ዘግቡር ምስለ ሐመድ ወትበልዕ ከመ ዘትበልዕ ሠናየ መብልዓ ምስሌሆን ወካዕበ የደልወነ ንዘከር ነገረ ራዕይ ዘከሠተ ላቲ እግዚአብሔር





፲ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዜና ገድሏን አስበን እናነብ ዘንድ ይገባል ጌታችን በወንጌል ጌታችንን ሽቱ ስለቀባች ስለዚያች ሴት እውነት እውነት እላችኋለሁ ይህች ሴት ያደረገችው ወንጌሌ በተሰበከበት ይነገራል እንደ አለ የእግዚአብሔር ጥበቡ ረቂቅ ስለሆነና ከእኛ ስለተሰወረ ብዙ አረጋውያን ከልጆቿ ጋር ሲኖሩ ከሁሉ በእድሜ ያነሰች ቅድስተ ክርስቶስን አስነስቶ ምስጋናውን በአንደበቷ አዘጋጀ መጽሐፍ በሕፃናት አንደበት ምስጋናን አዘጋጀ እንደ አለ ከዛሬ ወዲህ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ቸርነቷንና የቃሏን የአንደበቷን የመንቀሳቀስ ቃል አስበን እንሰማ ዘንድ ይገባል እሷ የምታረጋጋና በየዋህነት የምትገዛ ናት እንጂ በትዕቢት የምትገዛ አይደለችምና።

፲፩ ጴጥሮስ ስትገዙዋቸው በትዕቢት አትግዙዋቸው ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ በውነትና በየዋህነት ግዟቸው እንጂ እንደ አለ አንድ አገልጋይ ሰው ተናዶ ተበሳጭቶ ወደ እሷ በመጣ ጊዜ እጇን በትከሻው ላይ አድርጋ በባረከችው ጊዜ የብስጭትና የቁጣ ሰይጣን ከእሱ ላይ ወርዶ ወዲያውኑ የዋህና ትሁት ሆኖ እናቴ ሆይ አጥፍቻለሁና ይቅር በይኝ ብሎ እግሯ ላይ ይወድቅ ነበር ዳግመኛም የዝሙትና የስስት ጋኔን ኑሮበት አስቸገረኝ ብሎ በገለጠላት ጊዜ ብትመክረውና ብታረጋጋው ያን ጊዜ ፈጥኖ ይጠፋለታል ዳግመኛም በዚህ አይዋጋውም።

፲፪ ዳግመኛም ክብራቸውን ንቀው መንነው የነበሩ ሰዎች ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በመብልም ሆነ በመጠጥ የማይችሉትን አድርጉ ብላ ከባድ ሸክም አታሸክማቸውም ሕፃናተ አእምሮ ስለሆኑ እንዳይሸሹና ወደ ኋላ እንዳይመለሱ የሚፈልጉትን ታደርግላቸው ነበር ጳውሎስ ለሕፃናት እንደሚገባ ወተት ጋትኋችሁ እንጂ የጸና ምግብ አላበላኋችሁም ገና በሃይማኖት ያልፀናችሁ በሕገ ሥጋ ያላችሁ ናችሁና እንደአለ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም እንደዚሁ ታደርግላቸው ነበር እንጂ ምንም አትከለክላቸውም ነበር እነሱ በፈቃዳቸው ሁሉንም ፈጥነው ትተው በማኅበሩ ልማድ ይሳተፋሉ እንጂ

፲፫ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከእኅቶች ጋር በማዕድ ተቀምጣ ሳለች የተለያዩ የጣሙና የላሙ ምግቦችን በአቀረቡ ጊዜ ሽታው ወደ አፍንጫዋ እንዳይገባ አፍንጫዋን ትይዝ ነበር ከምግብ በኋላ እንደሚለወጥ ቆሻሻ ይመስላት ነበር እሷ፡ግን፡ከአመድ፡ጋር፡ቀላቅላ፡ከእነሱ፡ጋር፡ተቀምጣ፡መልካም፡ምግብ፡እንደሚመገብ፡ሰው፡ትመገብ፡ነበር፡ዳግመም፡እግዚአብሔር፡ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የገለጠላትን እንናገር ዘንድ ይገባል

ለእምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ሀለወት በአፈር ፈረስ ወትጼሊ ቀዊማ ጸሎተ መንፈቀ ሌሊት ወእሜሃ መጽአ መልአከ እግዚአብሔር ለአቡነ አባ አብሳዲ እምነ መጉና ወወሰዶ እንዘ ይመርሖ ወአዕረጎ ወአብጽሖ እስከ አንቀጸ ሰማይ ሳብዓይ ወቆመ በህየ መልአከ እግዚአብሔር ወይቤሎ ለአባ አብሳዲ ኅልፍ አንተ ባሕቲትከ ወእምነ መንበሮ ለእግዚአከ ወቁም ቅድሜሁ ወሰግድ እምኔሁ ቃለ ዘይቤለከ ::

፲፬ እስመ አብሐከ ለከ ሊተሰ ኢያብሐኒ ወኢይደልወኒ እኅልፍ እምዝንቱ አንቀጽ ወእምዝ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ ተመሥጠት አሜሃ ወርእየት ወሰምዓት፡ዘንተ፡ምሥጢረ እምቃለመልአክ ከመየዐቢ መዓርገ አባ አብሳዲ እመዓርገ መልአክ አብሳዲ ቦአ ውስተ ውሣጤ መንጦላዕት ወመልአክ ቆመ በአፍአ እንከረት ወትቤ ትፌእዩኑ ወለተ ማርያም ዘንተ ዐቢየ ወመድምመ ዘይቤሎ መልአክ ለአባ አብሳዲ ኅልፍ አንተ ባሕቲትከ አንተ አንሰ ኢይደልወኒ እኅልፍ እምዝንቱ አንቀጽ ወዘንተ ትቤ እምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ እንተ ባሕቲታ ወይመስላ ከመ ዘትትናገር ዘልፈ ምስሌሃ ወሀለወት አሐቲ ወለት እንተ ትቀውም በጥቃሃ እስመ ሠወራ ጽልመተ ሌሊት ወሰምዓት ዘንተ ነገረ እምቃለ እምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ ወነገረተነ ለነ ወጸሐፍናሁ ::

፲፭ ወሶበ ፈቀደ እግዚአብሔር ይክሥቶ ለዝንቱ ራእይ አንቀሃ ለዛቲ ወለት ከመ ትስማዕ ዘንተ ራእየ ወይመስል ዝንቱ ራእይ ዘጽሑፍ ውስተ መጽሐፈ ጳውሎስ ሐዋርያ ዘይብል አአምር ብእሴ ምእመነ በክርስቶስ እምቅድመ ፲ወ፬ ዓመት ወመሠጥዎ እስከ ሣልስ ሰማይ ለውእቱ ብእሲ እመሰ በሥጋሁ ወእመኒ ዘእንበለ ሥጋሁ እንዳዒ እግዚአብሔር የአምር ወመሠጥዎ ውስተ ገነት ወሰምዐ በህየ ነገረ ዘኢይተረጎም ወዘኢይከውና ለእጓለ እመሕያው ይንብብ ርእክሙት ዐቢየ ለእምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ተውህበ ላቲ ዝንቱ ሀብት እንዘ ይእቲ ሀለወት በሥጋ ትስማዕ ምሥጢረ ሰማይ ወይእዜኒ ንዜንወክሙ ዐቢየ ግርማሃ ለእምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘከመ ፈርሁ ሰይጣናት ወጐዩ እምኔሃ።





በአፈር ፈረስ ሳለች መንፈቀ ሌሊት ቁማ ጸሎት ስትጸልይ ያን ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ከመጉና አባ አቡነ አብሳዲን ወስዶ እስከ ሰባተኛ ሰማይ ሲያሳርገውና የእግዚአብሔር መልአክ እዚያ ቆሞ አባ አብሳዲን አንተ ብቻህን አልፈህ የፈጣሪህን ዙፋን እጅ ንሳና ከፈጣሪህ ፊት ቆመህ የሚልህን ስማ አለው::

፲፬ ለአንተ ተፈቅዶልሀል ለኔ ግን ከዚህ በር ማለፍ አልተፈቀደልኝም ሲል እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም በዚያን ጊዜ ተመስጣ ስለነበር መልአኩ የሚናገረውን ቃል ሰምታ ከመልአኩ ማዕረግ የአባ አብሳዲ ማዕረግ እንደሚበልጥ ተረዳች አባ አብሳዲ ግን ከመጋረጃው ውስጥ ገባ መልአኩ ከደጅ ቆመ እሷም ይህን አይታ መልአኩ ለአባ አብሳዲ አንተ ብቻህን እለፍ እኔ ከዚህ በር አልአልፍም ሲል ይህን ድንቅ ነገር ወለተ ማርያም ሆይ እያየሽ ነውን አለቻት እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ይህን ያለችውና ያየችው ብቻዋን ሁና ነበር ዘወትር ከእሷ ጋር እንደምትነጋገር መስሏት ተናገረች አንዲት የሌሊት ጨለማ የሰወራት በጐኗ ቁማ የነበረች ልጅ ይህን ቃል ከእናታችን ቅድስትና ቡር ክት ወለተ ጴጥሮስ ሰምታ ስለነበረች ይህን ቃል ነገረችንና ጻፍን ::

፲፭ እግዚአብሔር ይህን ራዕይ መግለጥ ስለፈለገ ይህን ራዕይ እንድትሰማ አነቃት ይህ ራዕይ በሐዋርያው ጳውሎስ መጽሐፍ ውስጥ እንደተጻፈ ከአስራ አራት ዓመት በፊት አንድ የማውቀው በክርስቶስ ያመነ ሰው በሥጋው ይሆን ወይም ያለ ሥጋው ይሆን እንጃ እግዚአብሔር ያውቃል ያ ሰው ወደገነት ተነጥቆ ለሰው ልጅ መናገር የማይቻል ድንቅ ነገርን ሰማ እንደአለ ያለ ራዕይ ነው ወዳጆቼ ሆይ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ታላቅነት አያችሁን በሥጋ ሳለች የሰማይን ምሥጢር ታይ ዘንድ ይህ ሀብት እንደ ተሰጣት አያችሁን ከዛሬ ወዲህ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን አጋንንት ፈርተው ከእሷ እንደሚሸሹ መፈራቷን እንነግራችኋለን::

## ምዕራፍ ፲፱

፩ ወመጽአት ኀቤሃ አሐቲ ብእሲት ዐባይ እምነ ዌዛዝር ከመ ተሐውጻ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወተራከበት ምስሌሃ ወነበረት ቅድሜሃ ወከና ይዜያነዋ ፪ ሆን ወአንሥአት አዕይንቲሃ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወርእየቶሙ ለሰይጣናት እንዘ ይትለሐዩ ባቲ ወየዓግትዋ ኵለንታሃ ከመ ጸናጺት ወትንንያ በአምሳለ ገደላ ምውት ወጽዩዕ ወሶበ ትኔጽሮሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ይጐይዩ ወይደነግፁ ወካዕበ ሶበ ትደንን ውስተ ምድር ይትጋብኡ ፍጡነ ወየዓግትዋ ከመ ቀዳሚ ወካዕበ ሶበ ትኔጽሮሙ ይጐይዩ ወእምድኅረ ሖረት ይእቲ ብእሲት ተስእለታ ግርማና ዘንተ ነገረ እስመ ነበረት ምስሌሆን ወትቤላ እስኩ ንግርኒ ምንተ ርኢኪ በላዕለ ዛቲ ብእሲት እስመ አነ ርኢኩኪ ፩ ጊዜ እንዘ ታነሥኢ አዕይንተኪ ወትኔጽሪ መንገሌሃ ወ፩ እንዘ ትደንኒ ውስተ ምድር በኃፍረት አንሰ ተሐዘብኩ ከመ ሀለወኪ ነገር ::

፪ አውሥአታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በመዓት ምንትኑ ሕሊና የዓርግ ውስተ ልብኪ ኢርኢኩ አንሰ ላዕሌሃ ምንተኒ ወዳግመ አምሐለታ ወተስእለታ ወሶቤሃ ነገረታ ዘከመ ርእየቶሙ ለሰይጣናት በከመ አቅደምነ ወንቤ ርኢክሙ ፍቁራንየ ዘከመ ይፈርህዋ ሰይጣናት ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወይጐይዩ እምኔሃ ዝኒ ይመስል ነገረ አረጋዊ መንፈሳዊ ዘይቤ በከመ ይፈርሁ ቈናፅል ወይትጋብኡ እምጣኅረ አንበሳ ከማሁ ቃሉ ለጠቢብ ያፈርሆሙ ለአጋንንት ወያጐይዮሙ

፫ ወመትልወ ዝንቱ ነገር ንከስት ለክሙ ጸጋ አሦት ዘተውህበ ላቲ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሀለወት አሐቲ ድንግል እምነ ደናግል እንተ ትሰመይ አመተ ክርስቶስ ዘአዳም ስና ወመንክር ላህያ ወአልቦ ዘይትማሰላ በውስተ ዓለም ወአሐተ ዕለተ ርእየታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ትዜኃር ወትትላኰይ ምስለ ካልእታ ወጸውዓታ ሶቤሃ ወአቀመታ ቅድሜሃ ወነጽረታ ላዕለ ወታሕተ በዓይነ መዓት ወትቤላ ምንትኑ ዝንቱ ላህይ በበሊዓ ሕፁፅ መብልዕ ወበሰትየ ማይ ቈሪር እምፈቀድኩ አንሰ ረጊዞተኪ በኵናት ወእምቀተልኩኪ ወገሠጸታ ብዙኃ ተግሣጸ::





## ምዕራፍ ፲፱

፩ ከዕለታት በአንድ ቀን አንዲት ታላቅ ሴት ወይዘሮ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ትጐበኛት ዘንድ ወደሷ መጥታ ከፊቷ ተቀምጣ ሁለቱ እርስበርሳቸው ሲጨዋወቱ እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ዓይኗን አንስታ ትንኝ የወደቀውን ጥንብ ሥጋ እንደሚከብ ሰይጣናትም መላ ሰውነቷን ከበው ሲጫወቱባት አየች እናታችን ቅድስት ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዓይኖቿን አንሥታ በምትመለከታቸው ጊዜ እጅግ ደንግጠው ይሸሻሉ ወደምድር ዘንበል ባለች ጊዜ እንደቀድሞ ፈጥነው ይሠባሠቡባታል እንደገና ስትመለከታቸው ፈርተው ይሸሻሉ ያች ሴት ወይዘሮ ከሄደች በኋላ ግርማና ከእነሱ ጋር ስለነበረች በዚች ሴት ላይ ምን አየሽ እስኪንገሪኝ እኔ ዓይኖችሽን አንስተሽ እሷን ስትመለከቺ አንድ ጊዜ በማፈር ወደ መሬት ስትመለከች ያየሽው ነገር እንዳለ ተረድቻለሁ አለቻት

፪ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መልሳ በቁጣ በልቦናሽ ውስጥ የሚመላለስ ሀሣብ ምንድን ነው እኔ በሷ ላይ ምንም አላየሁም አለቻት ዳግመኛም በመሐላ ለመነቻት በዚያን ጊዜ ሰይጣናትን እንዳየች አስቀድመን የተናገርነውን ነገረቻት ወደጆቼ ሆይ እናታችንን ሰይጣናት እንደሚፈሯትና ከሷ እንደሚሸሹ አያችሁን ይህ ነገር አረጋዊ መንፈሳዊ ተኩላዎች ከአንበሳ ጩኸት የተነሳ ፈርተው እንደሚሠበሠቡ እንደዚሁ የጥበበኛ ቃል አጋንንትን አስፈራርቶ ያባርራቸዋል እንደአለ::

፫ ከዚህ ቀጥለን ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የማሠር ጸጋ እንደተሠጣት እንነግራቸዋለን በደናግል መካከል መልከ መልካም የሆነችና በመልኳ የምትታበይ አመተ ክርስቶስ የምትባል አንዲት ድንግል ነበረች በዓለም ካሉት ሴቶች በመልክ ማማር እሷን የሚመስላት የለም ከዕለታት በአንድ ቀን ከሌላ እኅት ጋር በመልኳ ስትታበይና እንደ እኔ የሚያምር የለም እያለች ስትኩራራ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አይታ ጠራቻትና በፊቷ አቁማ በቁጣ ዐይን ከታች እስከ ላይ አየቻትና ይህ መልክ ጥቅም በሌለው መብልና ውሀ የተገኘ አይደለምን እኔ አሁን ከፈለግሁ በጦር ወግቼ በገደልኩሽ ነበር ብላ ብዙ ተግሣፅ ገሠፀቻት ::

፬ ወእምድኅሬሁ ፈነወታ ቤታ ወይእተ ጊዜ ሐመት ሕማመ ውግዓት ወነበረት ጕንዱየ መዋዕለ እንዘ ትደዊ እስከ ተወለጠ አርአያሃ ወጠግዐ ሥጋሃ ዲበ አዕጽምቲሃ ወኮነት መፃጕዕተ ወኢተንሥአት እስከ አመ ሞተት ወካዕበ ሀለወት አሐቲ ድንግል እንተ ከማሃ ዘትሰመይ እኅተ ክርስቶስ ወይእቲኒ ተሀውከት ወሐለየት ከመ ትሑር ሀገራ ከመ ተሐውጽ:አዝማዲሃ ወነገርዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት:ወለተጴጥሮስ:ከመተሀውከት:ወይእተጊዜጸውዓታ ወተስእለታ ወኃብአት እምኔሃ ወሠወረታ ወኢነገረታ ::

፭ ወእምብዝኃ ሁከት ዓበየት በሊዓ ወአዘዘት ያምጽኡ ላቲ ሐመደ ወይደምሩ ምስለ ኅብስት ወያብልዕዋ በአገብሮ ወበልዓት ዘእንበለ ፈቃዳ ወይእቲኒ ደወየት ወኮነት መፃጕዕተ ወነበረት እንዘ ትድሕክ ከመ ሕፃን ጕንዱየ መዋዕለ በኃይለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወኢሖረት በእገሪሃ እስከ አመ ሞተት::

፮ ወዓዲ በዝንቱ አንቀጽ ረከብነ ፍኖተ እንተ ትመርሐነ ወታበጽሐነ ኀበ ዜናሃ ለቅድስት ኢላርያ ወይእቲኬ ዘወረደት ዝበይ ምስለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወበህየኒ ነበረት እንዘ ትትለአክ ላቲ ወትትጌበር ግብረ ጸብሕ ወኮነት ታፈቅሮ ለቅዱስ ፋሲለደስ ሰማዕት እስመ ነበረት ውስተ ምጽሌ ምስለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወእም አሜሃ ተሠውጠ ፍቅረ ዚአሁ ውስተ ልባ ወዝክረ ስሙ ተጽሕፈ ውስተ ልሳና ወትብል ኵሎ ጊዜ ፋሲለደስ ወውእቱኒ ኢይትፈለጥ እምኔሃ ወያሤኒ ላቲ ተግባራ ወይምዕዝ ወይጥዕም ወነበረት ኵሎ ዕለተ እንዘ ትቀውም አንጻረ ምጽሌ ወታጽሕስ በእገሪሃ ወትዜምር በቃላ እንዘ ትብል ቅዱስ ፋሲለደስ ሰማዕት ፋሲለደስ ኃያል ፋሲለደስ ተራድአኒ ነዓ ለጽኑስ::

፯ ወይእተ ጊዜ ይበጽሕ ኀቤሃ ወሶቤሃ ትሬእዮ ትትፌሣሕ ወታንፈርዕፅ ከመ ሕፃን ፍሡሕ ዘርእየ ገጸ አቡሁ ወእሙ ወትስሕቅ እንተ ባሕቲታ ከመ ሀለወት ምስለ ሰብእ ወትገብር ከመዝ ኵሎ አሚረ ወምቅዋማኒ እሙር ውእቱ በገቦ ጸድፍ እምጽንፈ ባሕር ዘአፈር ፈረስ ወሶበ ኃሠሣሃ አኃት ይረክብዋ በዘከመዝ ግብር ወያንክርዋ ወይቤልዋ ምንተ ትብሊ ወምስለ መኑ ትትናገሪ ወይእቲኒ ትዌልጥ ካልአ ነገረ ወትትናገሮን ወትየውሓቶን ሒጠተ ጥበብ ወልባዌ ::





፬ ከዚህ:በኋላ ወደ ቤቷ ላከቻትና ያን ጊዜ በውጋት በሽታ ታመመች እንደዚያው እንደታመመች ሰውነቷ እስኪለወጥ እና እስኪሻክር ሥጋዋ ከአጥንቶቿ እስኪጣበቅ በሽተኛ ሆና ብዙ ዘመን ኖረች እስከ ምትሞትም አልተነሣችም ዳግመኛ እንደዚያች እኅተ ክርስቶስ የምትባል አንዲት ድንግል ነበረች እሷም ዘመዶቿን ትጠይቅ ዘንድ ወደ ሀገር ለመሄድ አሠበች ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ልሄድ ልሂድ እንደሚያሠኛትና እንደምትታወክ ነገሯት በዚያን ጊዜ ጠርታ ጠየቀቻት ያችም ልጅ ከእሷ ሰወረቻት እንጂ አልነገረቻትም::

፭ ብዙ ከተነጋገሩ በኋላ እህል መብላትን እምቢ አለች እናታችን አመድን ከእንጀራ ጋር ቀላቅለው እንዲያመጡና በግድ እንዲያበሏት አዘዘች አመጡላትና ያለ ፈቃዷ በግድ በላች የችም ልጅ ታማ በሽተኛ ሆና ብዙ ዘመን እንደ ሕፃን እየዳኸች በእናታችን ጸሎት ኃይል በእግሯ ሳትሄድና ወደ ዓለም ገብታ ሳትበላሽ ሳትሳሳት እስከምትሞ ት ቆየች ::

፮ እንደገና በዚህ አንቀፅ ወደ ቅድስት ኢላርያ ዜና ገድል የሚያደርሰን አገኘን እሷም ከእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጋር ወደ ዝበይ ተሰዳ ብዙ መከራ እየተቀበለች ለእናታችን ወለተ ጴጥሮስ ትላላክና ወጥ ታፈላላት የነበረች ናት እሷም ሰማዕቱ ቅዱስ ፋሲለደስን እጅግ ትወደው ነበር ከእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጋር በምጽሌ ስለነበረች በዚያን ጊዜ ጀምራ የእሱ ፍቅር በልቡናዋ አድሮ ስሙን መጥራት ባንደበቷ ተጽፏልና ሁልጊዜ ፋሲለደስ ትል ነበር እሱም ከሷ ሳይለይ የምትሠራውን ሁሉ ያስተካክልላት ነበር ሁልጊዜ ፊቷን ወደ ምጽሌ መልሣ በእግሯ እያሸበሸበች ቅዱስ ፋሲለደስ ሰማዕት ፋሲለደስ ኃያል ፋሲለደስ ሆይ ችግረኛ ልጅህን መጥተህ እርዳኝ እያለች ትዘምርና ትለምን ነበር::

፯ እሱም ፈጥኖ ወደ እሷ ይመጣል ያን ጊዜ አይታ የአባቱንና የእናቱን ፊት አይቶ ፈገግ እንደሚል ሕፃን እሱን እያየች እጅግ ትደሰትና ከሰው ጋር እንዳለች ትስቅ ነበር ሁልጊዜ ዘወትር እንደዚህ ታደርጋለች የምትቆምበትም በአፈር ፈረስ ገደል ጫፍ ላይ ከባሕር አጠገብ ነበር እኅቶች በፈለጓት ጊዜ እንዲህ ስታደርግ ያገኟትና እያደነቁ ምን እያልሽ ነው ከማንስ ጋር ትነጋገሪያለሽ ይሏታል እሷም መልሳ በማታለልና በጥበብ ሌላ ነገር ትነግራቸው ነበር::

፰ ወዘልፈ ሶበ ትትጌበር ግብረ ጸብሕ ትቤላ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለኢላርያ ተሰአሊያ ለወለተ ማርያም ዘትፈቱ ጸብሐ ወዘአዘዘተኪ ይእቲ ግብረ ላቲ ወነበረት ኵሎ ዕለተ እንዘ ትፌጽም ፈቃደ ዚአሃ ወአሐተ ዕለተ እምነ ዕለታት ተበውሐት እምኔሃ በከመ ልማዳ ወገብረት ጸብሐ በአዘዛታ ወሶበ ኮነ ጊዜ ሰርክ አቅረበት ዘንተ ጸብሐ ወአውረደት ቅድመ ወለተ ማርያም ወሶበ ፈቀደ እግዚአብሔር ከመ ይክሥት ኃይለ ዕበየ ለቅድስት ኢላርያ ወደየ ቀቢጸ ተስፉ ውስተ ልበ ወለተ ማርያም ወአስቈረረቶ ለውእቱ ጸብሕ ወኀደገት በሊዓ ወሶበ ርእየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ኃደገት በሊዓ ትቤላ ለኢላርያ፡ለምንት፡ኢገበርኪ የም ፈቃደ ዚአሃ ወናሁ ኃደገት በሊዓ።

፱ ወትቤ ኢላርያ አንሰ አሐውር ዮጊ ወአበጽሕ ፍጡነ ወይእተ ጊዜ ወፅአት ወሖረት ቤታ ወትቤሎን ለእለ ሀለዋ ምስሌሃ ውስተ ቤተ ጸብሕ ፍጡነ አስተዳልዋ አንትን ወአሠንያ ዒወ ወኵሎ አቃቂረ ዘይሜኔ ለዓሣ ወአንሰ አሐውር ኀበ መሠግር ወአሣየጥ ዓሣ ወይእተ ጊዜ ነሥአት እክለ ወወፅአት ወአትለወታ ለአሐቲ ሕፃን ወሖረት እንዘ ትጔጕዕ ወርእየታ ለፀሐይ ከመ ተቈልቈለት ወቀርበት ለዓረብ ወትቤላ አንቲ ፀሐይ አምሐልኩኪ በአምላከ ቅዱስ ፋሲለደስ ከመ ትቁሚ ወትጽንሒኒ እስከ እገብእ ወእፌጽም ፈቃድየ ወትቤላ ይእቲ ሕፃን ምንተ ትብሊ የምሰ ምስለ ፀሐይኑ ትትናበቢ ወይእቲሰ ኢተአምር ዘይከውን እስመ ሕፃን ይእቲ አሜሃ ።

፲ ወበጽሐት ኀበ መሠግር ወተሣየጠት እምኔሁ ዓሣ ወገብአት እንዘ ትጔጕዕ ወፀሐይሰ ሀለወት ወቆመት በከመ አዘዘታ ወበጺሓ ውስተ ቤት አብሰለት ወአሠነየት ውእተ ዓሣ ወአቅረበት ውስተ ማዕድ ወአንበረት ቅድመ ወለተ ማርያም ወተፈሥሐት ወበልዓት ወኢላርያሰ ረስዓታ ለፀሐይ ወኢተዘከረታ ወጕንደየት ነዋኃ እንዘ ትቀውም ወአኃትኒ ያነክራ ወይትበሃላ በበይናቲሆን ምንተ ኮነት የም ዛቲ ፀሐይ ወእምዝ ተዘከረታ ኢላርያ ወወጽአት አፍአ ወርእየታ እንዘ ትቀውም ወትቤላ ሶቤሃ ቡርክት ኩኒ አንቲ ፀሐይ እስመ ፀናሕክኒ እም ይእዜሰ አከለኪ ሖሪ ፍኖተኪ ወይእተ ጊዜ ዐረበት ወኮነ ፍጹመ ጽልመተ ወዘንተኒ ሰምዓት ይእቲ ሕፃን ወአኃትኒ እለ ሀለዋ ምስሌሃ ወባሕቱ ኢያእመራ ዘኮነ አሜሃ ዘእንበለ እምድኅረ ሞታ እስመ ይእቲ ነገረቶ ለዕቀሲስ ወውእቱኒ ነገረ ለኵሉ ሰብእ።





፰ ዘወትር ወጥ ስታፈላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኢላርያን ወለተ ማርያምን ጠይቀሽ እሷ የምትፈልገውን ወጥ ሥሪላት እያለች ዘወትር ትነግራትና እሷም ትዕዛዟን ትፈጽም ነበር ከዕለታት አንድ ቀን ከሷ ታዝዛ እንደ ልማዷ ወጥ ሠርታ ማታ ያን ወስዳ አቀረበችላት እግዚአብሔር የቅድስት ኢላርያን የታምራቷን ኃይል ስመግለጥ በአሰበ ጊዜ በወለተ ማርያም ልቡና ያን ወጥ እንድትፀየፍ አደረገ ያን ወጥ ተፀይፋ መብላትን እምቢ አለች እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ እንዳልበላች በአየች ጊዜ ዛሬ እሷ የፈለገችውን ለምን አላደረግሽላትም አልበላም ብላ እምቢ አለች አለቻት ።

፱ ኢላርያም መልሳ እኔ ሄጀ የምትፈልገውን ፈጥኜ አደርስላታለሁ ብላ ያን ጊዜ ፈጥና ወጥታ ወደ ወጥ ቤት ሄዳ ከእሷ ጋር ወጥ ቤት ያሉትን ፈጥናችሁ ለአሳ የሚገባውን ቅመማ ቅመምና ጨው ጨምራችሁ እያበሰላችሁ ቆዩኝ እኔ ሄጀ ዓሣ ከሚያጠምዱት ዓሣ ገዝቼ ልምጣ አለችና እህል ዘግና ይዛ አንዲት ልጅ አስከትላ በፍጥነት ስትሄድ ፀሐይ ልትጠልቅ አቈልቊላ አየቻትና አንቺ ፀሐይ እኔ ፈቃዴን እስክፈጽም ድረስ ከአለሽበት እንዳትነቃነቂ ቁሚ በፋሲለደስ አምላክ ይገዝሻለሁ አለቻት ያችም ሕፃን ዛሬስ ከፀሐይ ጋር ትናገር ጀመረች አለች ሕፃን ስለሆነችም የሚደረገውን አታውቅም ነበርና ።

፲ እሷም ወደ አሣ አጥማጆች ዘንድ ደርሳ አሣ ገዝታ ፈጥና ገብታ ያን አሣ አብስላ በገበታ አድርጋ ወስዳ ከወለተ ማርያም ፊት አቀረበች እሷም ደስ ብሏት በላች ኢላርያ ግን ፀሐይን እንደአቆመች ረስታ ፀሐይ ብዙ ጊዜ ቁማ ቀረች እኅቶች ፀሐይን እያዩ ይህች ፀሐይ ምን ሁና ቆመች እያሉ አደነቁ ከዚህ በኋላ ኢላርያ ትዝ አላትና ወደውጪ ወጥታ ቁማ አይታ አንቺ ፀሐይ የተባረክሽ ሁኚ እስከአሁን ቆይተሽኛልና ጉዳናሽን ሂጂ አለቻት ያን ጊዜ ጠለቀችና ፈጽሞ ጨለማ ሆነ ያች ሕፃን ይህን ሰማች ከሷ ጋር የነበሩ እኅቶች እሷ በሞት ከዚህ ዓለም እስከ ተለየች ድረስ አላወቁም ከመሞቷ አስቀድማ እሷ ለአንድ ቄስ ስለነገረችው እሱ ኋላ ለሰው ሁሉ ነገረ።

፲፩ ወይእዜኒ ይደልወነ ንክሥት ለክሙ ዜናሃ ለእምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ እስመ ይእቲ ነበረት ኵሎ መዋዕለ ሕይወታ እንዘ ትገብር ቀሚሰ አነዳ ዘእጉለ አልህምት ንዑሳን ዘተሰፍየ በአምትንት ወትነጽፍ ሰሌነ በምድር ወ፩ ማዕሰ በግዕ ወትሰክብ ዘልፈ ወኢትሰክብ ግሙራ በዓራት ወኢትገብር ዓሣዕነ ለእገሪሃ ወእግበረት ካዕበ ሐፃውንተ በሊሐተ እሳ ቦን አስዋክ ወአስናን ከመ መዋስርት በአምሳለ አውቃፋት ወትጌብሮን ውስተ እደዊሃ ወእገሪሃ ወትቀንት ሠቀ ውስተ ሐቌሃ ወትከስትር ዘልፈ ሐመደ እቶን ወትሰክብ ላዕለ ሐመድ ወካዕበ ይደልወነ ንዘከር ዜናሃ ለእምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥ ሮስ ዘኮነ በአምባ ማርያም ወበ፩ ዓመት እምእሉን ዓመታት ሖረት እምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ አምባ ማርያም ምስለ ኀዳጣን ማኅበር።

፲፪ ወመንፈቀ ማኅበር ሖሩ ቢዛባ ምስለ እኀተ ክርስቶስ ወከረሙ ህየ ወመንፈቆሙ ሀለዉ በአፈር ፈረስ ወለእሉ ረከቦሙ ዐቢይ ምንዳቤ ወኃዘን እስመ ኮኑ እጓለ ማውታ ወእምነሂ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ ከረመት ህየ በፈቃደ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ በከመ ዜነውነ ማእምራን እንዘ ይብሉ ወሶበ ፈቀደት እምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ትግባእ አፈር ፈረስ ሖረት ኀበ ቤተ ክርስቲያን ወቆመት ቅድመ ሥዕላ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወጸለየት እንዘ ትብል ኦ እግዝእትየ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ እስነአለኪ አንሰ ከመ ታብሕኒ እግባእ ወእሑር ኀበ ደቂቅየ አፈር ፈረስ ወእውዕአት እዴሃ ይእቲ ሥዕል ወአኃዘት ልብሳ ወተናገረታ ወትቤላ ኢየበውሐኪ ትሑሪ ኃዲገኪ ኪያየ አንሰ እፈቅድ ትክርሚ ምስሌየ በዝየ ወበዝንቱ ምክንያት ከረመት በአምባ ማርያም

፲፫ ወሰብእሰ እለ ሀለዉ ምስሌሃ ኢሐወዞሙ ዳዕሙ አንጐርጐሩ እስመ ኢያእመሩ ዘትቤላ ሥዕለ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወካዕበ ጸለየት እምነ ቅድስት ወብርክት ወለተ ጴጥሮስ ኀበ ይእቲ ሥዕል ከመ ትክሥት መካነ ዘትነብር ቦቱ እንዘ ትብል ኦ እግዝእትየ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ እስእለኪ ከመ ትክሥቲ ሊተ መካነ ለምዕራፍየ ኀበ ኮነ ሥምረተ ዚአኪ ወሥምረተ ፍቁር ወልድኪ አውሥእታ ካዕበ ይእቲ ሥዕል እንዘ ትእኀዝ እዴሃ ወትቤላ እምሐልኩኪ ከመ ኢትትሀወኪ ለዓለም ወኢታንቀልቅሊ እመካንኪ ወኢትበሊ ለፌ ወለፌ ኢየማነ ወኢፀጋመ እስመ ይእቲ ክፍልኪ አፈር ፈረስ ።



፲፩ እነሆ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ዜና ገድሏን እንነግራችሁ ዘንድ ይገባል እሷ መላ ዘመኗን ሁሉ አነስተኛ የከብት ቆዳ አሰፍታ እሱን በመልበስና የአንድ በግ ቆዳ በመሬት ላይ አንጥፋ ትተኛ ነበር እንጂ ፈጽማ በአልጋ ላይ አትተኛም ለእግሮቿም ጫማ አታደርግም ዳግመኛም እንደ እሾህና እንደ መጋዝ ጥርስ ያላቸው ብረቶችን አሠርታ በእግሮቿና በእጆቿ ታደርግ በወገቧም ትታጠቅ ዘወትር የምድጃ አመድ እየጫረች አመድ ላይ ትተኛ ነበር እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በአምባ ማርያም እንደነበረች እንነግራችሁ ዘንድ ይገባል ከእነዚህ ዓመታት በአንደኛው ዓመት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከጥቂቶች ማኅበር ጋራ ወደ አምባ ማርያም ሄደች ።

፲፪ እኩሌታው ማኅበር ከእኅተ ክርስቶስ ቢዛባ ሂደው እዚያ ከረሙ እኩሌቶቹ በአፈር ፈረስ ቀሩ እነሱን ትልቅ ችግር አግኝቷቸዋል እናት ያጡ ሁነዋልና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አምላክን በወለደች በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ፈቃድ እዚያ ከረመች ብለው ያወቁት እንደነገሩን እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወደ አፈር ፈረስ ትመለስ ዘንድ በፈለገች ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዳ አምላክን የወለደች በእመቤታችን ሥዕል ፊት ቁማ ልጆቼ ወደአሉበት ወደአፈር ፈረስ እሄድ ዘንድ እመቤቴ አሰናብችኝ አለቻት ያችም የእመቤታችን ሥዕል እጅዋን አውጥታ ልብሷን ይዛ እኔን ትተሽ ትሄጅ ዘንድ አልፈቅድም ፈቃዴስ ከኔ ጋር ትከርሚ ዘንድ ነው አለቻት በዚህ ምክንያት በአምባ ማርያም ከረመች።

፲፫ ከሷ ጋራ ያሉ ሰዎች ግን እዚያ መሆን ደስ ስለአላላቸው አንጐራጐሩ አምላክን የወለደች የእመቤታችን ሥዕል ከኔ ጋራ ክረሚ እንዳለቻት አላወቁምና ዳግመኛ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወደዚያች ሥዕል የምትኖርበትን ቦታ ትገልጽላት ዘንድ አምላክን የወለድሽ እመቤቴ ቅድስት ድንግል ሆይ የልጅሽ ፈቃድና የአንች ፈቃድ ወደሆነ የማረፊያየ ቦታ አመልክችኝ ብላ ጸለየች ያችም ሥዕል ዳግመኛ እጅዋን ይዛ ለዘለዓለሙ እንዳትታወኪ እና ከቦታሽ እንዳትናወጭ ወደግራም ሆነ ወደ ቀኝ ወዲያና ወዲህ እንዳትዪ አምዬሻለሁ ያንቺ ክፍልሽ እና ቦታሽ አፈር ፈረስ ነውና አለቻት ::

፲፬ ወሰሚዓ ዘንተ እምቃለ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አርመመት ወኃደገት ተሀውኮ ወበውእቱ መዋዕል ሀለወ ምስሌሃ ፩ እኁ ወውእቱ ተሰአላ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ይብል መንፈቀ ማኅበር ሖሩ ቢዛባ ወንሕነ ሀለውነ በዝየ ለምንት ኢነሐውር ንሕነ ኀቤሆሙ ወትቤሎ ንሕነ ኢነሐውር አላ፡እሙንቱ ይመጽኡ ኀቤነ ወይቤለኒ ፩ ብእሲ ኢትሖሪ

፲፭ ወተሰአላ ካዕበ ወይቤላ መኑ ውእቱ ብእሲ ዘይቤለኪ ዘንተ ወትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮሰ አንሰ ኢይነግረከ ስሞ ለእመ ከሠትከ ዘንተ ወነገርከ ለካልእ የኃዝን ኢይነግረከ ስሞ ለእመ ከሠትከ ዘንተ ወነገርከ ለካልእ የኃዝን ላዕሌየ ውእቱ ብእሲ ወይቤላ አንሰ ኢይነግር ለመኑሂ ወአምሐለቶ ሶቤሃ ከመ ኢይክሥት ዘንተ ነገረ ዘእንበለ እምድኅረ ሞታ ወነገረቶ ከመ እግዝእትነ ማርያም ይእቲ ዘትቤላ ወዘአምሐለታ በከመ አቅደምነ ወንቤ ወውእቱሂ ሀሎ ሕያወ እስከ ይእዜ ወነገረነ ወጸሐፍናሁ ወእንዘ ሀለወት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በውእቱ ደብር አእመረት ሞቶ ለዮሐንስ እምቅድመ ይንግርዋ በይእቲ ዕለት እንተ ባቲ ሞተ በትግሬ ወትቤ አሀ ምንተ ኮነ ዮም ዮሐንስ ወእምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል አይድዕዋ ከመ ሞተ ወበከየቶ ወለሐወቶ ዐቢየ ላሀ ወእሙነ ኮነ ራዕይ ዘርእየቶ፡፡

ምዕራፍ ፭

፩ ወእኅተ ክርስቶስሰ ነበረት በቢዛባ እንዘ ትበኪ ወታስቆቁ ኵሎ አሚረ እምአመ ተፈልጠት እምኔሃ እስከ ሐመት በቀቢፀ ተስፋ ወእምድኅረ ሰምዓት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሞቶ ለዮሐንስ ወረደት እምደብር በወርኃ መስከረም እስመ ኮነ ዕለተ ሞቱ እምአሚሩ ለውእቱ ወርኅ ወመጽአት አፈር ፈረስ ወተራከበት ምስለ ማኅበር እለ ሀለዉ ህየ ወተላቀሰት ምስሌሆሙ ወገብረት ተዝካሮ በውስተ ሬማ ወእምድኅሬሁ ነበረት አፈር ፈረስ ወእምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል መጽአት እኅተ ክርስቶስኒ ምስለ ማኅበር እለ ሀለዉ ምስሌሃ ወተራከበት ምስለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወበከየታ በእንተ እኁሃ ዮሐንስ ፡፡

፪ ወነበሩ ኵሉ ማኅበር በአፈር ፈረስ ኅቡረ አሐተኒ ወበውእቱ መዋዕል ፈነዋ ንጉሥ ፋሲለደስ ለወለተ ጊዮርጊስ ወለተ ኢቴ አመተ ክርስቶስ ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ትሚጣ እምሃይማኖተ አፍርንጅ ወትመሀራ ሃይማኖተ ርቱዓ እስመ ስእኑ መይጦታ ኵሎሙ መምህራን ወሠረፀ ውስተ ልባ ሃይማኖተ አፍርንጅ ወሶበ በጽሐት ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተመጠወታ ወአንበረታ ኀቤሃ ወመሀረታ ሃይማኖተ፡፡





፲፬ አምላክን ከወለደች ከእመቤታችን ሥዕል ይህን ቃል ሰምታ ማሰቡን ተወች በዚያን ወራት ከሷ ጋራ የነበረው አንድ ወንድም እናታችን ቅድስት እና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን እኩሌቶቹ ማኅበር ወደ ቢዛን ሄደዋል እኛ ግን እዚህ ቀርተናል እኛም ከነሱ ጋራ ለምን አንሄድም አላት እሷም መልሳ እነሱ ወደኛ ይመጣሉ እንጅ እኛ አንሄድም አንድ ሰው አትሂጂ ብሎኛልና አለችው ፡፡

፲፭ ዳግመኛም መልሶ ይህን ያለሽ ሰው ማነው አላት እናታችንም መልሳ ስሙን አልነግርህም ለሌላ ሰው ብትነግርበት ያ ሰው በኔ ያዝናልና እርሱም ለማንም አልነግርም አላት ያንጊዜ በሕይወተ ሥጋ ሳለች ለማንም እንዳይናገር አማለችው እና እመቤታችን እንደነገረቻትና አስቀድመን እንደተናገርን እንደአማለቻት ነገረችው ያም ሰው ይህ መጽሐፍ እስከሚጻፍ ድረስ በሕይወቱ ስለነበር እርሱ ነግሮን ጻፍን እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በዚያ ደብር ሳለች በትግሬ ሞቶ የነበረው የዮሐንስን ሞት አውቃ አይ ዮሐንስ ዛሬ ምን ሆነ አለች ከጥቂት ወራት በኋላ እንደ ሞተ አስረዷት ታላቅ ልቅሶን አለቀሰችለት ያየችውም ራዕይ እውነት ሆነ፡፡

ምዕራፍ ፭

፩ እኅተ ክርስቶስም ተስፋ በመቁረጥ እስክትታመም ድረስ ከሷ ከተለየች ጀምራ ሁልጊዜ እያለቀሰች ትኖር ነበር እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ የዮሐንስን ሞት ከሰማች በኋላ በመስከረም ወር ከዚያ ደብር ወረደች የሱ ሞት ይህ ወር በገባ በአንድ ነውና ወደ አፈር ፈረስ መጥታ እዚያ ከነበሩት ማኅበር ጋራ ተገናኝታ ከነሱ ጋራ አለቀሰች በሬማም ተዝካሩን አደረገችለት ከዚህ በኋላ ተመልሳ በአፈር ፈረስ ተቀመጠች ከጥቂት ወራት በኋላ እኅተ ክርስቶስ ከሷ ጋራ ካሉ ማኅበር ጋር መጥታ ከእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጋር ተገናኝታ ስለእናታችን ወንድም ዮሐንስ ሞት አለቀሰች፡፡

፪ ማኅበሩ ሁሉ ባንድነት በአፈር ፈረስ ተቀመጡ በዚያን ወራት ንጉሡ ፋሲለደስ የአመተ ክርስቶስን እኅት ወለተ ጊዮርጊስን ከካቶሊክ እምነት መልሳ የቀና የተዋህዶ ሃይማኖትን ታስተምራት ዘንድ ወደእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ላካት የካቶሊክ እምነት በልቧ ስለሰረጸ መምህራን ሁሉ እሷን አስተምረው መመለስ አቅቷቸዋልና ወደ እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ በደረሰች ጊዜ እናታችን ተቀብላ ከእሷ ጋራ አስቀምጣ ተዋህዶ ሃይማኖትን አስተማረቻት፡፡

፲፫ ወይእቲኒ ስእነት መይጦታ ወዓዲ በውእቱ መዋዕል ተሀውከት እሐቲ እኅት እንተ ትሰመይ ፍሕርተ ክርስቶስ ወፈቀደት ትሑር ሀገራ ወትቤላ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አብሕኒ እሑር ሀገርየ ወሰአለታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤላ ጽንሕኒ ዛተ ሰሙነ ወእምድኅሬሁ እፌንወኪ ወትቤላ ኦሆ ኃደገት ሐዊረ ወሶበ ወበየት ወለተ ጊዮርጊስ ተመይጦተ እምሃይማኖተ አፍርንጅ ተንሥኡ ላዕሌሃ ኲሉሙ ማኅበር ወፈቀዱ ይውግርዋ።

፲፬ ወእምዝ ነሥኣታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወጕየት ምስሌሃ ወሖረት ወበጽሐት ሰደጭላ ወቦአት ኀበ ቤተ አሐቲ መነኮሳይት ወነበረት ወበይእቲ ዕለት ሐመት ይእቲ እኅት እንተ ትሰመይ ፍሕርተ ክርስቶስ ወሞተት በይእቲ ሰሙን ወሖራ አኃት ሰደጭላ ከመ ይንግራሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወበጺሖን ሀየ ቆማ በዴዴ እንቀጽ ወወፅአት አሐቲ እኅት እንተ ሀለወት ሀየ ወተአምኃቶን ወተስእለቶን ምክንያተ ምጽአቶን ወነገራሃ ከመ ሞተት ወሰሚዓ ቦአት ኀበ ቤት ወነገረታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ መጽአ እማንቱ አኃት።

፲፭ ወትቤላ ጸውዒዮን ወሶበ አተዋ ኀቤሃ ትቤሎን ማእዜ ሞተት ፍሕርተ ክርስቶስ ወይቤላሃ ዳኅን ይእቲ ወኢሞተት ወትቤሎን አንስ አእመርኩ ከመ ሞተት ትማልም ወይቤላሃ እወ ሞተት ወሶቤሃ አእኰተቶ ለእግዚአብሔር ወአንከራ እማንቱ አኃት እስመ አእመረት እምቅድመ ይንግራሃ ወእመድኅሬሁ ቦአት ወለተ ማርያም እስመ ነበረት አፍአ ወትቤላ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሰማዕኪኑ ከመ ሞተት ፍኅርተ ክርስቶስ ።

፲፮ ወደንገፀት ሶቤሃ ወትቤ ማእዜ ሐመት ወማእዜ ሞተት ወትቤላ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኢትኅዝኒ እስ ቀተልክዋ በኃይለ እግዚአብሔር አምላኪየ ርኢክሙኑ ኃይላ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘከመ ትቀትል በጊዜ ፈቀደት ወዘከመ ተአምር እምቅድመ ይንግርዋ ወእምዝ አሐተ ዕለተ እንዘ ሀለዋ ፪ ሆን እንተ ባሕቲቶን ውስተ ይእቲ ቤት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወለተ ጊዮርጊስ ወሀለወት እኅት እንተ ታበስል ሐምለ በይእቲ ቤት ቅድሜሆን እስመ ታፈቅር ወለተ ጊዮርጊስ በሊዓ ጸብሐ ዘሐምል ወአንበረት መቅፁተ ላዕለ እቶን ወአንደደት እሳተ ወኃደገት ወወፅአት አፍአ።





፲፫ ለእሷም አልመለስም አለቻት እንደገና በዚያን ወራት ፍህርተ ክርስቶስ የምትባል እኅት ወደሀገሯ ለመሄድ ፈልጋ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ወደሀገሬ እሄድ ዘንድ አስናብቺኝ አለቻት እናታችንም ይህችን ሰሞን ሰንብቺ ከዚያ በኋላ እሸኝሻለሁ አለቻት ያቺም እሺ ብላ መሄዱን ተወች ወለተ ጊዮርጊስም ከካቶሊክ እምነት መመለስ እምቢ ባለች ጊዜ ማኅበሩ ሁሉ ይወግሯት ዘንድ በእሷ ላይ ተነሱ ::

፲፬ እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስም ይዛ ሸሽታ ወደ ሰደጭላ ሄዳ ወደ አንዲት መነኩሲት ቤት ተቀምጣ ሳለች በዚያች ዕለት አሰናብቺኝ ያለቻት ፍህርተ ክርስቶስ ታማ በዚያን ሰሞን ሞተች ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ይነግሯት ዘንድ እኅቶች ወደ ሰደጭላ ሂደው እዚያ ደርሰው ከደጅ ቆመው በተጣሩ ጊዜ እዚያ የነበረች አንዲት እኅት ወጥታ እጅ ነሳቻቸውና የመጡበትን ምክንያት ጠየቀቻቸው እነሱም እንደሞተች ነገሯት ያችም ልጅ ሰምታ ወደቤት ገብታ ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እነዚያ እኅቶች መጥተዋል አለቻት::

፲፭ እሷም ጥሪያቸው አለች ወደእሷ በገቡ ጊዜ ፍህርተ ክርስቶስ መቼ ሞተች አለቻቸው እረ ደኅና ናት አልሞተችም አሏት እሷም መልሳ ትናንት እንዳረፈች ተረድቼ አለሁ አለቻቸው እነሱም አዎ አርፋለች አሏት ያን ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገነች ሳይነግሯት ስላወቀች እነዚያ እኅቶች እጅግ አደነቁ ከዚህ በኋላ ወለተ ማርያም ከደጅ ስለነበረች ወደቤት ስትገባ እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ፍህርተ ክርስቶስ እንደሞተች ሰማሽ አለቻት ::

፲፮ እሷም ደንግጣ መቼ ታማ መቼ ሞተች አለቻት እናታችን መልሳ በፈጣሪየ በእግዚአብሔር ኃይል ወደ ዓለም ሂዳ እንዳትሳሳት ገድያታለሁኝና አትዘኝ አለቻት ወዳጆቼ ሆይ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የታምሯን ኃይል በፈለገች ጊዜ እንደምትገድል ሳይነግሯትም እንደምታውቅ አያችሁን ከዚህ በኋላ ከዕለታት በአንድ ቀን እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እና ወለተ ጊዮርጊስ ብቻቸውን ተቀምጠው ሳሉ ጐመን የምታበስልላቸው አንድ እኅት ከነሱ ጋራ ነበረች ወለተ ጊዮርጊስ ጐመን ስለምትወድ ያች ልጅ ከእሳት ላይ ድስቱን ጥዳ እሳት እንደአነደደች ትታ ወደ ደጅ ወጣች ::

፯ ወሶቤሃ ፈልኃ ማይ ውስተ መቅፁት ዘሐምል ወተክዕወ ወሶቤሃ ተንሥአት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወአኰሰቶ ለውእቱ ሐምል ወአንደደት እሳተ ዘጠፍአ ወሶበ ርእየት ትሕትናሃ ወለተ ጊዮርጊስ ትቤላ አኮኑ በእንቲአየ ገበርኪ ዘንተ ወአነሂ ተመየጥኩ በእንተ ትሕትናኪ እምሃይማኖተ አፍርንጅ ርኩስ ወቦእኩ ውስተ ሃይማኖትኪ ቅዱስ ተፈሥሒ ወተኃሠዪ ወሶበ ሰምዐት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘንተ ብስራተ
ወድቀት ውስተ ምድር ወሰዐመት እገሪሃ ወተንሥአት ወየበበት በዓቢይ ቃል ወአኃትኒ ኲሎን እለ ሀለዋ ህየ የበባ ምስሌሃ ወኮነ ዐቢይ ፍሥሐ በይእቲ ዕለት ወሶቤሃ ፈነወት መልእክተ ብስራት ውስተ ኲሎን ደሰያት ወተፈሥሑ ኲሎሙ ወዘበጡ ሶቤሃ ነጋሪተ ወኃለዩ እንዘ ይብሉ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ::

፰ ወንጉሥኒ ሰሚኦ ምስለ ሠራዊቱ ተፈሥሐ በከመ ይቤ ወንጌል እመኒ ብእሲት እመባ ፲ እግሙስ ወእመ ተገድፈታ አሐቲ እም ውስቴቶን አኮኑ ተኃቱ ማኅቶተ ወትፈነቅል ኲሎ ዘውስተ ቤታ ወተኃሥሥ አስተሐሚማ እስከ ትረክባ ወእምከመ ረከበት ትጼውዕ አዕርክቲሃ ወአግዋሪሃ ወትቤሎን ተፈሥሓ ሊተ እስመ ረከብኩ ገመስየ እንተ ተገድፈተኒ እብለክሙ ከማሁ ይከውን ፍሥሐ በቅድመ መላእክተ እግዚአብሔር በእንተ ፩ ኃጥእ ዘይኔስሕ ርእዩኬ ፍሬሃ ለትሕትና እንተ ሠረፀት እምእግዚእነ ወተውህበት ለነ::

፱ በከመ ይቤ ለሊሁ ተመሀሩ እምኔየ እስመ የዋህ አነ ወትሑት ልብየ ወትረክቡ እረፍተ ለነፍስክሙ ወብዙኃን መምህራን እለ ይፌክሩ መጻሕፍተ ብሉያተ ወሐዲሳተ ጻመዉ ወደክሙ ብዙኀ ዓመታተ ወስእኑ መይጦታ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተትሕተት ወኮነት ምኩስታረ ለዕዳወ ክህደት ወሜጠታ በቅፅበት ወአብአታ ውስተ ሃይማኖት ርትዕት በከመ፡ተትሕተ፡እግዚእነ፡ወነሥአ፡አርአያ፡ገብር፡ወአግብኦ፡ለአዳም፡ ኀበ ፡ዘቀዳሚ ርስቱ::





፯ በዚህን ጊዜ በድስት ውስጥ ያለው የጕመን ውሃ ፈልቶ ፈሰሰ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ያን ጊዜ ተነስታ ጕመኑን አማሰለችና የጠፋውን እሳት አነደደች ወለተ ጊዮርጊስም ትሕትናዋን ባየች ጊዜ ይህንን ስለኔ አድርገሻልና እኔም ስለትሕትናሽ እርኩስ ከሆነ ከካቶሊክ እምነት ተመልሼ ቅዱስ በሆነ በተዋህዶ ሃይማኖት አምኛለሁ ፈጽመሽ ደስ ይበልሽ አለቻት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ይህን ምሥራች በሰማች ጊዜ በመሬት ላይ ወድቃ እግሯን ሳመችና ተነሥታ በታላቅ ቃል እግዚአብሔርን አመሰገነች ከእሷ ጋራ እዚያ የነበሩ እኅቶችም እልል አሉ በዚያች ዕለት ታላቅ ደስታ ሆነ በዚያን ጊዜ በደሴያት ወደአሉ ገዳማት መልዕክት ላከች ሁሉም ተደስተው ነጋሪት እየመቱ የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን አሉ::

፰ ንጉሡም ከሠራዊቱ ጋር ሰምቶ እጅግ ተደሰተ ወንጌል ድሪም ያላት ሴት ከነዚያ ውስጥ አንዲቷ ብትጠፋባት መብራት አብርታ በቤቷ ውስጥ ያለውን እያነሳች እስከምታገኝ ድረስ በጣም ተጨንቃ ትፈልጋለች በአገኘችም ጊዜ ወዳጆቿንና ጐረቤቶቿን ጠርታ የጠፋችብኝ የእኔን ድሪም አግኝቻለሁና ደስ ይበላችሁ ትላቸዋለች እኔም እንደዚሁ አንድ ኃጢአተኛ ንስሐ ሲገባ ደስ ይለኛል ከጌታችን ተገኝታ ለኛ የተሰጠች የትሕትና ፍሬ አያችሁን::

፱ እሱ እራሱ ለነፍሳችሁ እረፍትን ታገኙ ዘንድ እኔ የዋህ ልቡናየ ትሁት ነውና ከእኔ ተማሩ እንደአለ የብሉያትንና የሐዲሳትን መጻሕፍት የሚተረጕሙ ብዙ መምህራን ብዙ ዓመት ደክመው ከክህደት መመለስ ያቃታቸውን እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ግን ዝቅ ብላ እራሷን አዋርዳ ለክህደት ቆሻሻ መጥረጊያ ሆነችና ፈጥና ከክህደት መልሳ ወደ ቀናች ተዋህዶ ሃይማኖት አስገባቻት ጌታችን እራሱን ዝቅ አድርጐ የባሪያው አርአያ ይዞ አዳምን ወደ ቀደመ ርስቱ እንደመለሰ::

፲ ወእምዝ ተመይጠት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አፈር ፈረስ ወነበረት ኅቡረ አሐተኔ ምስለ ኵሉ ማኅበር ወቦ እለ ተንሥኡ እምነ መምህራን መንጐራጕራን ወአንጐርጐሩ ላዕለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በቅንዓት ሰይጣናዊ ሶበ ርእዩ ከመ ኵሉ ዓለም ተለወ ድኅሬሃ ወከመ ዐበየት ወተለዓለት እምኔሆሙ ወኮኑ እሙንቱ መትሕቴሃ ወይቤልዋ ቦኑ ዘሀለወ ጽሑፍ በውስተ መጻሕፍት ከመ ትኩን ሊቀተ ወመምህርተ እንዘ ብእሲት ይእቲ ዘከልአ መጽሐፍ ወይቤላ ብእሲትሰ ትምህር ኢናበውሓ ወኢትመብል ላዕለ ብእሲ በበዝንቱ ምክንያተ ፈቀዱ ያኅድግዋ ወባሕቱ ኢክህሉ አኅድጎታ ወይቤሎሙ ሶቤሃ አባ ፈትለ ሥላሴ መምህረ ኵሉ ዓለም እኮኑ እግዚአብሔር አንሥአ ኪያሃ ለዘለፋ ዚአነ እስመ ኮነ ንሕነ መደልዋነ ወሤመ ኪያሃ ወወሀባ ልህቅና ዚአነ ወሠዐረ ኪያነ።

፲፩ ወበእንተዝ ኢትክሉ አኅድጎታ:በከመ ይቤ ገማልያል በመጽሐፈ አብርክሲስ ኅድግዎሙ ለእሉ ሰብእ ወኢትስሐጥዎሙ ለእመሁ ዘእምኀበ ሰብእ ዝ ምክሮሙ ወግብሮሙ የኃልፍ ወይሠዓር
ወለእመ እምኀበ እግዚአብሔር ኮነ ኢትክሉ አኅድጎቶሙ ወከመ ዘምስለ እግዚአብሔር ይትበአስ ኢትኩኑ ወከማሁ እሉሂ መምህራን ዘአንጐርጐሩ ኢክህሉ አኅድጎታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እስመ ተበውሐት እምኀበ እግዚአብሔር ወለእመሰ ኢኮነ እምኀበ እግዚአብሔር እምኢሀለወ እስከ ይእዜ ውእቱ ማኅበር አላ እምጠፍአ ወእምኃለፈ ፍጡነ ስማ

፲፪ ወበዝንቱ ይትዓወቅ ከመ ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ወእምድኅሬሁ ነበረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ምስለ እሉ ማኅበር በፍቅር ወበሰላም እንዘ ምንዱባን ወርኁባን እሙንቱ ኢይሔልዩ ሲሳየ ሥጋ ወኢይብሉ ምንተ ንበልዕ ወምንተ ንሰቲ አላ ይኄልዩ ሲሳየ መንፈሳዌ ዘውእቱ ጾም ወጸሎት ፍቅር ወትሕትና ወዘይመስሎ ለዝንቱ ።

፲፫ ወበአሐቲ ዕለት እምነ ዕለታት እንተ ይእቲ ዕለተ ዓርብ ኃልቀ ሲሳይ ወአልቦ ምንትኒ ግሙራ ወለእመ ኃሠሡ ልቃሐ ኢይትረከብ ወእንበይነዝ ቀብፀት ተስፋ እኅተ ክርስቶስ እስመ ይእቲ ርኅርኅት ወመስተሣህልት ለኵሉ ሖረት ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክተ ወለተ ጴጥሮስ ወቆመት ቅድሜሃ እንዘ ተቴክዝ ወተቤላ እፎ እገብር በእሉን ሰንበታት ይመውቱ ድውያኒነ በረኀብ ወአልቦ ምንትኒ ግሙራ እክል ውስተ ቤት ወኃሠሥኩ ልቃሐ ወየድኩ ሀገረ ወኃጣእኩ ወለእመ መጽአ እክል ጌሠመ በሰንበትኑ ይትሐረፅ ወሚመ ይመውቱኑ ድውያኒነ በረኃብ





፲ ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወደ አፈር ፈረስ ተመልሳ ከማኅበር ሁሉ ጋር በአንድነት ተቀመጠች ከሚያንጐራጕሩ መምህራንም መካከል ከእነሱ ስለበለጠችና ሁሉ እሷን ተከትለው ስለአዩ በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ላይ በሰይጣናዊ ቅናት የተነሡ አሉ እነሱም በውኑ ሴት መምህርት ሁና ታስተምር ዘንድ መጽሐፍ ከልክሎ የለምን በወንድ ላይ ሥልጣን ይኖራት ዘንድ አናሰናብታትም ብለው በዚህ ምክንያት ያስተውዋት ዘንድ ሞከሩ ነገር ግን ሊያስቱ ዊት አልቻሉም ያን ጊዜም የዓለም ሁሉ መምህር የነበረ አባ ፈትለ ሥላሴ እኛ ሰነፎች ስለሆን እግዚአብሔር እሷን አንሥቶ እኛን ሽሮ ለኛ ዘለፋ እሷን ሹሟታልና።

፲፩ ስለዚህ እሷ እንዳታስተምር ማስተው አትችሉም አላቸው የግብረ ሐዋርያት መጽሐፍ ገማልያል እነዚህን ሰዎች ተውዋቸው ይህ ምክራቸውና ሥራቸው ከሰው ከሆነ ይጠፋሉ ከእግዚአበሐር ጋር እንደሚጣላ ሰው አትሁኑ እንደ አለ እንደዚሁ ነገር ይሠሩ የነበሩ መምህራን እናታችንን ያስተውዋት ዘንድ አልቻሉም ከእግዚአብሔር ባይሆን ኖሮ ይህ ማኅበር እስከ ዛሬ ባልኖረም ነበር ስሟም እስከ ዛሬ ባልተጠራም ነበር።

፲፪ ስለዚህ ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑ ይታወቃል ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከእነዚያ ማኅበር ጋር በፍቅርና በሰላም ኖረች እነሱም ተርበው ተቸግረው ሳሉ የሥጋ ምግብ አስበው ምን እንበላለን ምንስ እንጠጣለን አይሉም መንፈሳዊ ምግብ የሚሆን ጾምንና ጸሎትን ፍቅርንና ትሕትናን ሌላም የመሳሰለውን ያስባሉ እንጂ ።

፲፫ ከዕለታት በአንዲት ቀን ይችውም ዕለተ ዓርብ ነበረች ምግብ አልቆባቸው ብድር ስንኳን ቢፈልጉ ምንም አጥተው ስለዚህ እኅተ ክርስቶስ ለሁሉ የምትራራና ለሁሉ የምታዝን ስለ ነበረች አዝና ተስፋ ቆርጣ ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሄዳ እያዘነች ከፊቷ ቆመችና በእነዚህ ሰንበታት ምን አደርጋለሁ እነዚህ በሽተኞች በረሀብ ይሞታሉ በቤታችን ውስጥ ምንም እህል ጨርሶ የለም ብድር ፍለጋ ሄድኩ ብዞር አጣሁ ነገ በሰንበት እህል ቢመጣ ይፈጫል ካልሆነ በሽተኞቹ በርሀብ ይሞታሉ አለቻት ።

፲፬ ወትቤላ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኦ ኅፅፀተ ሃይማኖት አኮኑ አንቲ ሐለይኪ ዘንተ በከመ ፅበተ ክርሥኪ ጌሠመሰ ትርእዪ ኃይለ እግዚአብሔር ወሶቤሃ ናዘዘት ወተመሊአ ሃይማኖተ ወሖረት ኀበ ቤተ ተግባር ወአዘዞቶ ከመ ያስተዳልዋ ተግባራተ በበፆታሆን ወያነክራ እማንቱሂ ወይትበሃላ በበይናቲሆን እምአይቴ ረከበት እክለ ዘትኤዝዘነ ከመ ናስተዳሉ ወኀበ መነኮሳትሂ ለአከት ከመዝ::

፲፭ ወበሳኒታ መጽኡ ሰብእ እምርኁቅ እንዘ ይፅዕኑ ሐሪፀ እክል ዘዘዚአሁ በ፱ አዕዱግ ወአወፈይዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወጸውዓታ ለእኅተ ክርስቶስ ወትቤላ ንስኢ ዘንተ ዘወሀበነ እግዚአብሔር ተፈሥሒ ዮም እስመ ኃዘንኪ ትማልም ወሶቤሃ አእኰተቶ ለእግዚአብሔር ወነሥአት ሐሪፀ ወወሀበቶን ለእለ ይትጌበራ ወለመነኮሳትሂ ከማሁ ወኮኖሙ ሲሳየ በእማንቱ ሰንበታት::

፲፮ ወካዕበ በአሐቲ ዕለት ከማሁ ተኃጥአ ሲሳይ ወትቤላ ለእኅተ ክርስቶስ አንተ ትትለአክ ውስተ ቤተ ተግባር ዮምሰ ምንትኑ ንዴረር እስመ ኀልቀ እክል ወትቤላ ኢሀሎኑ ግሙራ ሐሪፅ ወይእቲኒ ትቤላ ሀሎ መጠነ ኢፍ ሐሪፅ ወአዘዘታ ከመ ታብሕዕ ወትደዮ ውስተ ዝቅ ወትቤላ በዝቅሰ ኢይወድዮ አላ እወድዮ ውስተ ንስቲት ልሕኵት ወትቤላ እኅተ ክርስቶስ ኢትሕዝኒ ደዪዮ ውስተ ዝቅ ዘዘልፍ ወብሂላ አሆ አብሕአቶ ወወደየቶ ውስተ ዝቅ ወሶበ በጽሐ ጊዜ ለሐቢዝ ሐለየት ከመ ትሕብዝ እምኔሁ ለኀዳጣን ድውያን ወአርኃወቶ ለዝቅ ወረከበቶ ምሉአ ወሐበዘቶ ወአከለ ከመ ዘልፍ ወኮነ ድራረ ለኵሉ ማኅበር::

፲፯ ወሶበ ተፈጸመ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ዘሬማ ፈነወት ብስራተ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኀበ ንጉሥ ፋሲለደስ ፈነወ ላቲ መጋዝእተ አልህምት ወመዓረ ወአልባሳተ ወመንጠዋልዓተ ወዘርቤታተ ወካልእተ ዘይትሐሠሥ ወገብረት በከመ ሕግ ወአግብአት ታቦተ ወአስተፍሥሐቶሙ ለሰብእ ውእቱ ደብር ወለካልኣንሂ ሰብእ እለ መጽኡ እምኵሉ አብያተ ክርስቲያናት ወኮነ ውእቱ አመ ፳ ለወርኃ ሐምሌ::

፲፰ ወእምድኅሬሁ ፈነወት ብሔረ ትግሬ ሰብአ ከመ ያፍልሱ ሥጋ ዮሐንስ እኁሃ ወያምጽኡ ላቲ ወገብሩ በከመ አዘዞቶሙ ወአምጽኡ ላቲ ወይእቲኒ ተቀበለቶ ወበከየቶ ወአብአቶ መቅደሰ ሬማ ወአንበረቶ በሣፁን ወእምዝ ትቤ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መጽአ ኀቤየ እኁየ ዮሐንስ ዮም በዛቲ ሌሊት ወይቤለኒ ኢትብክዪ ዘልፈ በእንቲአየ ወኢታንጥዪኒ ንዒ ከመ ትርአዪ ማኅደርየ ዘበሰማያት እስመ ኮነ ክፍልየ ምስለ ሰማዕታት ወወሰደኒ ወአርአየኒ ወተናዘዘ ልብየ ወተፈሣሕኩ:





፲፬ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም አንቺ ሃይማኖት የጐደለሽ ሆድሽ እንደሚጐድል ይህን አሰብሽን ነገ የእግዚአብሔርን ኃይል ታያለሽ አለቻት በዚህን ጊዜ ሃይማኖትን ተሞልታ ተረጋግታ ወደ ተግባር ቤት ሂዳ በእየወገናቸው የሚዘጋጁትን እንዲያዘጋጁ አዘዘቻቸው እነዚያ የታዘዙት እኅቶች እናዘጋጅ ዘንድ ያዘዘችን እህል ከወዴት አገኘች እየተባባሉ ያደንቁ ጀመር ወደ ወንዶች መነኮሳትም እንደዚሁ ብላ ላከች::

፲፭ በማግስቱ ሰዎች እየራሳቸው በዘጠኝ አህዮች ጭነው ከሩቅ አገር መጡና ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እጅ መንሻ ሰጡ እናታችንም እኅተ ክርስቶስን ጠርታ ትናንት ስለ አዘንሽ ዛሬ እግዚአብሔር የሰጠንን ይህን ስጦታ ተቀበዪ አለቻት በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን አመስግና ያን ዱቄት ወስዳ ለሚያዘጋጁት አዘጋጁ ብላ ሰጠች ለወንዶች መነኮሳትም እንደዚሁ ላከችላቸውና በእነዚያ ሰንበታት ተመገቡ::

፲፮ ዳግመኛም አንዲት ቀን የሚበላ ምግብ ጠፋ በተግባር ቤት ውስጥ የምትላላክ ልጅ እኅተ ክርስቶስን እህል አልቆዋልና ምን እንመገባለን ምንም ዱቄት የለምን አለቻት እሷም መልሳ በትልቁ መስፈሪያ ሙሉ ዱቄት አለ አለቻትና ዘወትር በሚያቦኩበት በትልቁ ዋዲያት ታቦካ ዘንድ አዘዘቻት እሷም መልሳ በትንሹ ላቡካ አለቻት እኅተ ክርስቶስም ያልቃል ብለሽ አትሰስች ዘወትር በሚቦካበት ቡሆ እቃ አቡኪ አለቻት እሺ ብላ አቦካችው እንጀራ የሚጋገርበት ጊዜ ሲደርስ ለታመሙት ትጋግር ዘንድ እቃውን በከፈተች ጊዜ ሞልቶ አገኘችውና ወስዳ ጋገረችው ከዚህ በኋላ ጋግራ ያም ምግብ ለማኅበርተኞች እራት:ሆነ ::

፲፯ የሬማ ቤተክርስቲያን ሕንፃ በተፈጸመ ጊዜ እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ወደ ንጉሡ ፋሲለደስ የምሥራች ላከች እሱም ለበዓሉ የሚታረዱ የፍሪዳ በሬዎችንና መዓር የቤተ ክርስቲያን አልባሳት መጋረጃዎችንና ምንጣፎችን ሌላም የሚያስፈልገውን ላከላት እሷም እንደ ሕጉና እንደ ሥርዓቱ ታቦቱን አስገባች የአገሩንም ሰዎችና ከእየአብያተ ክርስቲያናቱ የመጡትን:ሰዎች:ሁሉ:አስደሰተች:ይህም:የተደረገ:ሐምሌ:፳ቀን:ነው

፲፰ ከዚህ በኋላ የወንድሟ የዮሐንስን ሥጋ አፍልሰው ያመጡላት ዘንድ ወደ ትግራይ ሰው ላከች እንደ አዘዘቻቸው አፍልሰው አመጡላት እሷም ተቀብላ ጥቂት አልቅሳ ከሬማ ቤተ ክርስቲያን አስገብታ በሳጥን አድርጋ አስቀመጠች ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በዚህች ሌሊት ወንድሜ ዮሐንስ ወደ እኔ መጥቶ ዘወትር ስለ እኔ አትዘኚ ክፍሌ ከሰማዕታት ጋር ሆኖልኛልና በሰማይ ያለ ቤቴን ታዪ ዘንድ ነዪ ብሎ ወስዶ ቤቱን አሳይቶኛልና ልቡናየ ተረጋግቶልኛል አለች ::

## ምዕራፍ ፳፩ ዘእሑድ

፩ ወበውእቱ መዋዕል ሖረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዝንፈቀራ ኀበ ወለተ ክርስቶስ ምስለ ኀዳጣን ማኅበር ከመ ትርአይ ገዳመ ዘይሤኒ ላቲ ለነቢር ወእኅተ ክርስቶስ ኒ ተርፈት በአፈር ፈረስ ወእንዘ ተሐውር በጽሐት ኀበ ውእቱ ሀገር ወቦአት ቤተ ዌዘሮ ወለተ ክርስቶስ ወነበረት ምስሌሃ ወጾመት በህየ ጾመ ፶ መዋዕል ወበውእቱ መዋዕል ሐመት መቅደሰ ማርያም ወሖረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ተሐውጻ ውስተ ቤት ዘሰከበት ቦቱ ወእንዘ ሀለወት ምስሌሃ በጽሐ ሶቤሃ ጊዜ ፫ ሰዓት ወተገልበበት ገጻ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥርስ ወወጠነት ጸሎተ ፫ቱ ሰዓት ወመቅደሰ ማርያምኒ ሜጠት ገጻ መንገለ ዐረብ ወይእተ ጊዜ መጽአ ላእከ መስቀል ወቦአ ግብተ ውስተ ውእቱ ቤት እንበለ ያስምዕ ድምፀ እስመ ውእቱ ይትለአክ በውእቱ ወርኀ ።

፪ ወሶቤሃ መልሐ ሰይፎ መልአከ እግዚአብሔር ዘሀሎ ምስለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወፈቀደ ይዝብጦ እስመ ቦአ ውእቱ ግብተ ወአደንገፃ ወሶበ ርእየት ይእቲ ሕምምት ደንገፀት ወሜጠት ገጻ መንገሌሁ ወገሠጸቶ ወትቤሎ እፎ ተህበልከ ወቦእከ ዘእንበለ ጊዜ ሶበ አኮ ወለተ ጴጥሮስ ዘአድኃነተከ እም ረከበከ ዐቢይ መከራ ወኀቀ ክመ ተረፍከ እመዊት ።

፫ ወሶቤሃ ቀልዓት ግልባቤ ገጻ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወተስእለታ ወትቤላ ምንተ ትብሊ ወምንተ አደንገፅኪ ይእዜ ወኃብአት እምኔሃ ወትቤላ አንሰ ኢይብል ምንተኒ ወትቤላ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እሙነ ንግርኒ ወኢትሠውርኒ ወሶቤሃ ነገረታ እንዘ ትብል አንሰ ርኢክዎ ለመልአክ እንዘ ይመልሕ ሰይፎ ወይፈቅድ ይዝብጦ ወባሕቱ ኃድጎ በእንቲአኪ ወተሰምዓ ዝንቱ ነገር ውስተ ኵሉ ማኅበር፡ወበውእቱ፡ሕማም፡ሞተት፡ይእቲ፡ድውይት፡ወተቀብረት፡ህየ

፬ ወካዕበ ሐመት ወለተ ክርስቶስ ዘፋሬ በውእቱ ወርኀ ወትቤላ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አምጽኢ ሊተ ግብነተ መጺጸ እስመ ውእቱ ያፈትወኒ ከመእብላዕ ወኮነ ሰሙነ





## ምዕራፍ ፳፩ የእሑድ ገድል

፩ በዚያን ወራት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከጥቂቶች ማኅበር ጋር ለመቀመጥ የሚስማማትን ገዳም ታይ ዘንድ ወደ ወለተ ክርስቶስ ሄደች እኅተ ክርስቶስም በአፈር ፈረስ ቀረች ሂዳ ወደዚያች አገር ደርሳ ከወይዘሮ ወለተ ክርስቶስ ቤት ገብታ እዚያ ተቀመጠችና በዚያ ዓቢይ ጾምን ጾመች በዚያን ወራት መቅደሰ ማርያም ታማ ስለነበር እናታችን ቅድስት ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትጠይቃት ዘንድ ከተኛችበት ቤት ሄደች ከእሷ ጋር ሳለች የሦስት ሰዓት ጸሎት ሲደርስ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ፊቷን ተሸፍና ጸሎት ጀመረች መቅደሰ ማርያም ፊቷን ወደ መዕራብ መለሰች በዚያን ጊዜ ላእከ መስቀል የሚባል፡በዚያን ጊዜ ይላላክ የነበረ ድምፅ ሳያሰማ ድንገት ዘው ብሎ ገባ።

፪ በዚያን ጊዜ ከእናታችን ከቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ጋር የነበረ መልአከ እግዚአብሔር ሰይፉን መዞ ይቀስፈው ዘንድ ፈለገ እሱ ድንገት ዘው ብሎ ገብቶ እናታችንን አስደንግጧልና ያቺ ታማ የነበረች ልጅ አይታ ደንግጣ ፊቷን ወደ ልጁ መልሳ ያለ ሰዓት ለምን መጣህ አሁን ወለተ ጴጥሮስ ባታድንህ ኖሮ ልትቀሠፍ፡ጥቂት፡ቀርቶህ፡ነበር፡ለጥቂት፡ከሞት፡ተረፍክ አለችው ።

፫ በዚያን ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከፊቷ ላይ ልብሷን ገልጣ ምን እያልሽ ነው ለምንድነው የምታስደነግጪው አለቻትና ያችም ልጅ ምንም አላልኩም ብላ ነገርን ደበቀቻት እናታችን ወለተ ጴጥሮስም መልሳ እውነት ንገሪኝ አትደብቂኝ አለቻት ያችም ልጅ መልአኩ ሊቀሥፈው ሰይፉን መዞ አየሁት ነገር ግን ስለ አንቺ ብሎ ሳይቀሥፈው ተወው አለቻት ይህም ነገር በማኅበሩ ሁሉ ዘንድተሰማ ያችም ታማ የነበረች ልጅ በዚያው በሽታ ሙታ እዚያው ተቀበረች።

፬ ዳግመኛም በዚያን ወር የፋሬ ወለተ ክርስቶስ ታመመችና ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የቆየ አይብ ወይም መጣጣ አምሮኛልና እበላ ዘንድ ፈልገሽ አምጪልኝ አለቻት በዚያ ሳምንት ሰሙነ ሕማማት ነበር እናታችንም አይቡን ይልኩላት ዘንድ በከተማ ወደአሉት መኳንንቶች መልእክተኛ ላከች ሁሉም መጣጣ የሆነውን አይብ

ሕማማት በውእቱ ጊዜ ወፈነወት ሶቤሃ ልዑካነ ኀበ ዌዛዝር ወመኳንንት ዘከተማ ከመ ይፈንዉ ላቲ ግብነተ ወኃሠሡ ኰሎሙ ወኃጥኡ ወተመይጡ ልኡካን ወነገርዋ ለወለተ ክርስቶስኒ ኃሠሠት ወኢረከበት ወተከዘት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እስመ ኢረከበት ላቲ ዘፈተወት ሕምምት::

፫ ሀለወ ቅብዕ ዘኢተበስለ ወኢተፀርየ በዐቢይ ቀሱት ዘተፈነወ እምዌዘሮ ክርስቶሳዊት ወበዕለተ መኃትወ ፋሲካ ነሥአት አሐቲ እኅት እምነ ቅብዕ ፩ መቅፀተ ወአፅረየት ወሀለወት ምስሌሃ ካልእት እኅት ወትሬኢ ወካዕበ ነሥአት እምኔሁ ወአፅረየት ወበሣልስ ተረክበ ከዊኖ ግብነተ ወነሥአት እምኔሁ ይእቲ እኅት ወርእየቶ ወአፄነወቶ ወኮነ ፄናሁ አዳመ ዘይሤኒ እምፄና ግብነት ወትቤላ ለካልእታ ስምዒ ዝንቱሰ ቅብዕ ኮነ ግብነተ አውሥእታ ይእቲኒ ካልእት ሶቤሃ ወትቤላ ለምንት ተሐስዊ ወትትናገሪ ዘኢይከውን ነገረ ወትቤላ ይእቲ እኅት አንሰ ኢሐሰውኩ ዳእሙ እሙነ እብል ወለእመ ኢአመንክኒ ኪያየ ንሥኢ አንቲ ነጽሪዮ በአዕይንትኪ ወአፄንዊዮ በአዕናፍኪ::

፬ ወሶቤሃ ነሥአት እምኔሁ ንስቲተ ይእቲኒ ርእየቶ ወአፄነወቶ ወኮነ እሙነ በከመ ትቤ ወአንከራ ፪ሆን ወኃደጋሁ እስከ ይበጽሕ ጊዜ ወሶበ ተፈትሐ ጾም ወኮነ ጊዜ ቍርባን አስተዳለዋ መብልዓ ዘይትፈቀድ በውእቱ ዕለት ወአቅረባ ላቲ እምውእቱ ግብነት ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሶበ:ርእየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትቤላ ለይእቲ እኅት እምአይቴ መጽአ ዝ ግብነት ዘኃሠሥናሁ ብዙኃ ዕለተ: ወኃጣእናሁ ወቀርበት ኀቤሃ ወአልኆሰሰት በእዝና ወትቤላ ውእቱ ቅብዕ ዘሀሎ:ውስተቀሡት:ወኮነ መንፈቁ ቅብዓ ወመንፈቁ ግብነተ::

፭ ወሶቤሃ አንሥአት አዕይንቲሃ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ውስተ ሰማይ አንከረት ወተደመት ወጕንደየት ነዋኃ ወአእኰተቶ ለእግዚአብሔር ወእምዝ ትቤላ ለይእቲ ሕምምት ተንሥኢ ብልዒ ተረክበ ለኪ ዘፈተውኪ ወትቤላ እምአይቴ ረከብኪ አውሥእታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤላ አምጽአ ሊተ እግዚአብሔር እስመ ርእየ ሐዘንየ ወትካዝየ ወተንሥአት ወበልዓት ወእምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በልዓት ወአንከረት እምጣዕሙ ወእመዓዛሁ ::





ፈልገው አጡ መልእክተኞችም ተመለሰው መጥተው ጠፋ ብለው ነገሯት ወይዘሮ ወለተ ክርስቶስም ፈልጋ አጣች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ያቺ የታመመች ልጅ የፈለገችውን ስለአላገኘችላት አዘነች::

፫ ከወይዘሮ ክርስቶሳዊት የተላከ ያልተነጠረ ቅቤ በትልቅ እንስራ ነበር የፋሲካ ዋዜማ ዕለት አንዲት እኅት ያን ቅቤ ወስዳ ስታነጥር ሌላ እኅት ከእሷ ጋር ሁና ትመለከት ነበር ሁለት ጊዜ ወስዳ አነጠረች በሶስተኛ ስታነጥር ያ ቅቤ በተአምራት የቆየ አይብ መጣጣ ሆኖ ተገኘ ያችም እኅት አንስታ አየችና ብታሸተው መልካም መዓዛ ወይም ያማረ አይብ ሆኖ አገኘችው መለስ ብላ ለጓደኛዋ ይህ ቅቤ መጣጣ አይብ ሆነ አለቻት ያችም መልሳ ለምን ትዋሻለሽ የማይሆንም ነገር ለምን ትናገሪያለሽ አለቻት እሷም መልሳ ኸረ እኔ አልዋሸሁም በአይንሽ ተመልከች በአፍንጫሽ አሺች አለቻት::

፬ ያችም ጥቂት አንስታ በዓይኗ አየች በአፍንጫዋም አሸተተችው ጓደኛዋም እንደአለችው እውነት ሆነ ሁለቱም አድንቀው ጊዜው እስኪደርስ ዝም አሉ ጾም ተፈቶ ቅዳሴ ሲገቡ በዚያች ቀን የሚያስፈልገውን ምግብ አዘጋጅተው ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አቀረቡላት እናታችንም ባየች ጊዜ ብዙ ቀን ፈልጌ ያጣሁ አይብ ከየት መጣ ብላ ያችን እኅት ጠየቀቻት ያችም እኅት ወደሷ ቀርባ ቀስ ብላ በጆሮዋ ያ በእንስራ ውስጥ ያለው ቅቤ ግማሹ አይብ ግማሹ ቅቤ ሆነ ብላ ነገረቻት::

፭ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥበሮስም ይህን በሰማች ጊዜ ዓይኖቿን ወደ ሰማይ ቀና አድርጋ እጅግ እያደነቀች እግዚአብሔርን አመሰገነች ከዚህ በኋላ ለዚያች ታማሚ የፈለግሽው ተገኝቶልሻልና ተነሥተሽ ብዪ አለቻት ታማሚዋም መልሳ ከወዴት አገኘሽ አለቻት እናታችንም መልሳ እግዚአብሔር ሐዘኔንና ጭንቀቴን አይቶ አመጣልኝ አለቻት ያችም ተነስታ በላች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ጥቂት በላችና ከመዓዛውና ከጣዕሙ የተነሣ እጅግ አደነቀች ::

፰ ወአሜሃ ሀለዉ ህየ በውእቱ ሀገር አዕሩግ መነኮሳት እምነ ማኅበር ወመነኮሳትሂ ካልአን እለ እምታሕቴሆሙ ሀለዉ ወፈነወት ሎሙ እምውእቱ ግብነት በ፫ አጽሕልት ለአረጋውያን እንተ ባሕቲቶሙ ወለሕፃናትሂ እንተ ባሕቲቶሙ በበምር ፋቃቲሆሙ ወካዕበ ሖረት ከመ ታምጽእ እምውእቱ ግብነት ወረከበቶ ከዊኖ ቅብዓ ከመ ቀዳሚ ወገብአ ኅበ ህላዌሁ ዘትካት ወሶበ ርእየት ዘንተ ይእቲ እኅት አንከረት ወተደመት ወነገረታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘንተ ተአምረ ከመ ኮነ ቅብዓ ወገብአ ኅበ ፍጥረቱ ዘቀዳሚ ወሰሚዓ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘንተ ተአምረ አንከረት እምዕበያቲሁ ለእግዚአብሔር ወአዘዘታ ለይእቲ እኅት ከመ ትሑር፡ኅበ፡ቤተ መነኮሳት ወታምጽእ ውእተ ግብነተ ዘፈነወት ሎሙ ለሕፃናት መነኮሳት ከመ ይኩን ለይእቲ ሕምምት ለጌሠም ወለሣልስት።

፱ ወሶቤሃ ሖረት ይእቲ እኅት እንዘ ትጓጕዕ ወትረውፅ ወበጽሐት ኅበ ቤተ መነኮሳት ወአርኃወት ለሊሃ በእዴሃ ኖኅተ ቤቶሙ ወቦአት ወረከበት አጽሕልተ ክዱናተ ወአሰሰለት ክዳናተ አጽሕልት ወርእየት ወረከበት ምሉአ በከመ ፈነወት ወነሥአት ፱ አጽሕልተ ወወፅአት ወሖረት እንዘ ትጊጕዕ ከመ ቀዳሚ ወኢተናገረት ምንተኒ በበአታሂ ወበፀአታሂ ወርእዮሙ፡ መነኮሳት አንከሩ ወተበሃሉ በበይናቲሆሙ ምንትኑ ምሥጢሩ ለዝንቱ ነገር ወኢያእመሩ ዘኮነ መንክረ ኢዘቀዳሚ ወኢዘድኅሪ።

፲ ወአዕሩግሰ በልዑ ውእተ ግብነተ ዘኃደገት ሎሙ ወአንከሩ እምጣዕሙ ወእመዓዛሁ ወለሕፃናትኒ ወለጠት ከልአ ጸብሐ ወፈነወት ሎሙ ወእምድኅሬሁ ተሰምዐ፡ዝንቱ ተአምር ወኮነ ክሡተ፡ውስተ፡ኵሉ፡ማኅበር፡ወእለሂ፡በልዕዎ፡ለውእቱ፡ግብነት፡ሀለዉ፡ እስከ፡ይእዜ፡ወኮኑ ስምዓ ወስምዐሙኒ እሙን ውእቱ ወኢኮነ ሐሰት

፲፩ ሚይበዝኅ ወሚ ይፈድፍድ ዜና ተአምራቲሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ናሁ ከደነ ሰማያተ ወመልአ ምድረ ወአልቦ መኑሂ ዘይክል ከቢቶቶ ቦኑ የትከበት ጢስ ለእመ ዓፀውዎ ውስተ ቤት ወኃብእዎ አኮኑ ይወፅዕ ወይትረአይ ውስተ ኵሉ መካን ወቦኑ ይትኃባእ ቅብዓ ዘይት ኅዳጥ ለእመ ወደይዎ ታሕተ ውስተ ቀሱት ወለእመ መልእዎ ላዕሌሁ ማየ ብዙኃ ወፈቀዱ ይሠውርዎ አኮኑ የዓርግ ላዕለ ወያንፀበርቅ





፰ በዚህን ጊዜ ከመነኮሳት ማኅበርተኞች በዚያ አገር ስለ ነበሩ ከነሱ በታች ላሉት መነኮሳት ለአረጋውያን ለብቻ ለልጆች ለብቻ በመቀመጫቸው ላከችላቸው ዳግመኛም ያንን አይብ ታመጣ ዘንድ አንዲት እኅት በሄደች ጊዜ ወደ ቀደመ ቅቤነት ተመልሶ ቅቤ ሆኖ አገኘች ያችም እኅት አድንቃ ሄዳ ወደቀድሞው ቅቤነት እንደተመለሰ ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ነገረቻት እናታችንም ይህን በሰማች ጊዜ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን አድንቃ ያችን እኅት ለልጆች መነኮሳት የላከችውን አይብ መልሳ ታመጣና ለታመመችው እኅት ለማግሥቱና ለሦስተኛ ቀን ይሆናት ዘንድ ሂደሽ አምጪ ብላ አዘዘቻት

፱ እሺ ብላ ፈጥና እየሮጠች ሂዳ ከመነኮሳት ቤት ደርሳ ቀስ ብላ እራሷ በሩን በእጇ ገፍታ ስትገባ እነዚያ ሰሃኖች ተከድነው አገኘች መክደኛውን ከፍታ በአየች ጊዜ አስቀድማ እንደላከችው በሳሃኖቹ ሙሉ አግኝታ በሁለት ሰሃን ያለውን ይዛ እንደቀድሞ ፈጥና እየሮጠች ሄደች ስትገባም ስትወጣም ሳትናገር ስለሄደች መነኮሳትም ይህን ነገር አይተው እርስበርሳቸው የዚህን ነገር ምሥጢሩ ምን ይሆን ተባባሉ የመጀመሪያውንም የመጨረሻውንም ተአምር አላወቁም ነበርና።

፲ አረጋውያን መነኮሳት የተወችላቸውን አይብ በልተው ከመዓዛውና ከጣዕሙ የተነሣ እጅግ አደነቁ ለልጆች ግን ሌላ ወጥ ለውጣ ላከችላቸው ኋላ ግን ይህ ነገር በማኅበርተኞች ዘንድ ተሰማ ያንን አይብ የበሉ ሰዎችም ይህ መጽሐፍ እስከ ተጻፈበት ድረስ ነበሩ እነሱም ምስክር ሆኑ ምስክርነታቸውም እውነት እንጂ ሐሰት አይደለም ።

፲፩ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የታምራቷ ዜና ምን ይበዛ ምን ይደንቅ እነሆ በሰማይ በመላእክት ዘንድ በምድር በደቂቀ አዳም ዘንድ ታወቀ ተረዳ ማንም ሊሠውረው አይችልም ጢስ ቤት ቢዘጉበትና ቢሸሽጉት ይሸሸጋልን ወጥቶ በየቦታው ሲበተን ይታያል እንጂ አይሸሸግም ጥቂት ዘይትን ከእንስራ ውስጥ ጨምረው ለመሸሸግ ብዙ ውሀ ከላይ ቢሞሉትና ለመሠወር ቢፈልጉ ይሸሸጋልን ወጥቶ ከላየ ተንሳፎ ይታያል እንጂ እንደዚሁ እኛም የእናታችን የወለተ ጴጥሮስን ዜና መሠወር አንችልም በየአገሩ ሁሉ የታወቀ ነውና

መልዕልተ ማይ ወከማሁ ንሕነኒ ኢንክል ከቢቶተ ዜናሃ ለእምነ ቅድስተ ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እስመ ኮነ ስጡሐ ውስተ ስፍሐ ኵሉ በሐውርት ወእምዝ ሶበ ሰምዓ ንጉሥ ፋሲለደስ ከመ ሖረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወከመ ወሰደታ ወለተ ክርስቶስ ተምዓ ጥቀ ወሐዘነ ፈድፋደ ወይቤ ቦኑ ትኄይስ እምኔየ ዘተሐይደኒ ማኅበርየ::

፲፪ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኢሖረት በፈቃዳ ለኃሢሠ መካን አላ ሶበ አገበርዋ ማኅበር ወይቤልዋ ንሑር ኀበ ካልእ መካን ዘንትጌበር ቦቱ ገራኅት ወንረብሕ እክለ ለሲሳይነ እስመ ዐፀቦሙ ሲሳይ በአፈር ፈረስ ይእቲሰ ኢትፈቅድ ትንበር በ፩ መካን አላ ታፈቅር ተፋልሶ በበዓመት እመካን ኀበ መካን ከመ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ እለ ነበሩ በሃይመታት ወከማሁ እምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ነበረት እንዘ ትትፋለስ እመካን ኀበ መካን ::

፲፫ ሶበኒ ተስእልዋ ወይቤልዋ ምንትኑ አንቲ ዘኢታፈቅሪ ነቢረ በ፩ዱ መካን ኵሎሙ ቅዱሳን ያፈቅሩ አጽንዖ መካን ወይቤሉ ዘይትፋለስ እመካን ኀበ መካን ኢኮነ መነኮሰ ወኢይፈሪ ፍሬ ምግባራት ወይመስል ዕፀ ዘያፈልስዎ እመካን ኀበ መካን ዘኢይልህቅ ወኢይፈሪ ወታወሥአሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎሙ አንሰ አአምር ከመ ይኄይስ አጽንዖ መካን እምነ ተፋልሶ አላ እገብረ ዘንተ በእንተ፩ዱ ነገር ለእመ አንበርክዎሙ ለደቂቅየ ወአዋልድየ ኀበ ፩ መካን የሐንፁ ቤተ ክርስቲያን ወአብያተ ለርእሶሙ ወየአርፉ እምጻማ ወስራሕ::

፲፬ ወበዕረፍት ይለመልም ሥጋ ወእምልምላሜ ሥጋ ይሠርፅ ፍትወት ጠባይዓዊ ወይፀብዖሙ ሶቤሃ ሰይጣን ወእመሰ አፍለስክዎሙ እመካን ኀበ መካን ወይጻምው ወይደክሙ ወይመጽሉ ሥጋሆሙ በፃማ ወበሥራሕ ወበሐልዮ ተግባር ወኢይዜክርዎ ግሙራ ለኃጢአት ወሶበ መስየ ይብሉ ማእዜ ይጸብሕ ወሶበ ጸብሐ ይፌትዉ ከመ ይትመከዓብ ሎሙ ኑኃ መዓልት እስከ ይፌጽሙ ተግባሮሙ ወበእንተዝ ኢያፈቅር አነሂ ነቢረ በ፩ መካን ::





ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንደሄደች ወለተ ክርስቶስ እንደወሰደችው ንጉሡ ፋሲለደስ በሰማ ጊዜ እጅግ አዝኖ እሷ ከኔ ተሽላ ነውን በውኑ ማኅበርተኞቼን የምትቀማኝ አለ::

፲፪ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ቦታን በመምረጥ በፈቃዷ አልሄደችም ማኅበር ሠርተን ደክመን ለምግባችን እህል ይምናመርትበት ወደሌላ ቦታ እንሂድ ስለ አሏት ነው እንጂ በአፈር ፈረስ ምግብ ቸግሯቸዋልና እሷም አንድ ቦታ መቀመጥን አትወድም በድንኳን እንደነበሩ እንደ አብርሃምና እንደ ይስሐቅ እንደያዕቆብ በእየዓመቱ ከአንድ በታ ወደ አንድ ቦታ መዘዋወር ትወዳለች::

፲፫ አንቺ አንድ ቦታ መቀመጥን ለምን አትወጂም ቅዱሳን ሁሉ አፅንኦ በአትን ይወዳሉ ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ የሚዘዋወር መነኩሴ አይደለም መልካም ፍሬን ማፍራት አይችልም በየዓመቱ ከአንድ ቦታ ነቅለው ወደ ሌላ ቦታ በተከሉ ጊዜ ፍሬ እንደማያፈራና እንደሚደርቅ እንጨት ይመስላል ይላሉ አንቺ በአንድ ቦታ መጽናትን ለምን አትፈልጊም ብለው ቢጠይቋት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም መልሳ ከመዘዋወር አጽንኦ በአት እንደሚሻል አውቃለሁ ነገር ግን ይህን የማደርገው ስለ አንድ ነገር ነው ልጆቼን አንድ ቦታ ባስቀምጣአቸው ቤተ ክርስቲያን ከሠሩ በኋላ ቤታቸውን አሳምረው ሠርተው ከድካም ያርፋሉ ::

፲፬ በእረፍት ሥጋ ይለመልማል ሥጋ ከለመለመ በኋላ የሥጋን ፈቃድ መፈጸም ይመጣል በዚህን ጊዜ ሰይጣን ይዋጋቸዋል ነገር ግን ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ ባዘዋውራቸው ይደክማሉ የሚሠሩት የዕለት ሥራን በማሰብ ሥጋቸውን እረፍት ያሳጧታል ፈጽመው ኃጢአትን አያስቡም ሲመሽ መቼ ይነጋልናል ሲነጋ መቼ ይመሽልናል እያሉ የሚሠሩት ሥራቸውን ለመጨረስ ያስባሉ ስለዚህ አንድ ቦታ መቀመጥን እኔ አልፈልግም አለች::

## ምዕራፍ ፳፪

፩ ወእምዝ ተመይጠት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እምዝንፈቀራ ወአተወት ጎንደር ወነበረት ኅዳጠ መዋዕለ ወረከበት ሞገሰ በኀበ ንጉሥ ፋሲለደስ ወኮነ የሐውጽ ኵሎ ዕለተ ወያፈቅራ ፈድፋደ ወይፈርሃ ከመ እግዝእት ወሶበ ይበውእ ኀቤሃ የአጥቅ ልብሶ ከመ ፩ እምነ ሐራሁ ወዌዛዝርሂ ወመኳንንት ይገንዩ ላቲ እንዘ ይርዕዱ ወእንዘ ከመዝ ሀለወት በጎንደር እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሐመት ሕማመ ጽኑዓ እስከ አልፀቀት ለመዊት ወሶቤሃ ደንገፁ ንጉሥኒ ወኵሎንሂ ዌዛዝር ወሶበ አስተይዋ ማየ ኀፃበ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሐይወት ወተፈወሰት ፍጡነ በይእቲ ዕለት።

፪ ወእምድኅሬሁኒ ነበረት ጉንዱየ ዕለተ እስከ አንጕርጕሩ ባቲ ማኅበር ወይቤልዋ ለወለተ ማርያም አኮኑ አንቲ መከርኪ ዘንተ ምክረ ወታፈቅሪ ነቢረ በከተማ ወበዝንቱ ቃል አምረርዋ ወሐለየት ከመ ትትፈለጥ ወትሑር ሀገራ ወእምዝ ሶበ በጽሐ ፈቃደ እግዚአብሔር ተሰነአለት እምንጉሥ ወይእተ ጊዜ ወሀባ ምድረ ለግ ወአስተፋነዋ በዐቢይ ሞገስ ወሶቤሃ ወፅአት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እምከተማ ወሖረት ወበጽሐት ፍንጥሮ ወበጺሓ ህየ ተሰነዐለታ ወለተ ማርያም ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤላ አንሰ ኢየሐውር ምስሌኪ እስመ አንጕርጕሩ ላዕሌየ ማኅበር ወአሕዘንክዎሙ እፎ ንጸድቅ አነሂ ወእሙንቱሂ በዘከመዝ ግብር ወበእንተዝ ይኄይሰኒ እንበር በሀገርየ።

፫ አውሥአታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤላ እፎ ተኃድግኒ በዝንቱ ሀገር ወትትፈለጢ እምኔየ ወበጺሐነ ቅርኛንስነዓል አነኒ አሐውር ወአንቲኒ ትገብኢ ወትቤላ ወለተ ማርያም ኦሆ ወሖረት ምስሌሃ በታንኳ ወበጽሐት ቅርኛ ወቤተት ምስሌሃ ወእምዝ ሰአለታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዳግመ ከመ ትሑር ምስሌሃ ወታብጽሓ ፎገራ ወአበለታ ኦሆ ወበጽሐት ፎገራ ምስሌሃ ወበህየ ተሰነዓላ ፪ሆን እንዘ ይበክያ።





## ምዕራፍ ፳፪

፩ ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እምዝንፈቃራ ተመልሳ ጎንደር ገብታ እዚያ ጥቂት ተቀመጠች በንጉሡ በፋሲለደስ ዘንድም ባለሟልነትን አገኘች ዘወትርም ይጐበኛት እጅግም ይወዳትና እንደ እመቤትም ይፈራት ያከብራት ነበር ወደ እሷም በሚገባ ጊዜ ከወታደሮቹ እንደ አንዱ ልብሱን በአጭር ታጥቆ ከፊቷ ይቆማል ሴት ወይዛዝሮች መኳንንትም እየፈሩ ይገዙላት ነበር በእንደዚህ ሳለች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በጐንደር የጸና ሕማም ታመመች በዚያን ጊዜ ንጉሡና ሴቶች ወይዛዝሮች ደነገጡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀሉን እጣቢ አጥበው በአጠጧት ጊዜ ወዲያውኑ ፈጥና ዳነች ።

፪ በዚህ ማኅበሩ እስኪ አንጐራጒሩባት ድረስ ብዙ ቀን ተቀመጠች ወለተ ማርያምን በከተማ መኖር ስለምትወጅ ይህንን ምክር አንች መከርሽ ብለው በዚህ ቃል አማረሯት እሷም ተለይታ ወደ አገሯ ለመሄድ ፈለገች የእግዚአብሔር ፈቃድ በደረሰ ጊዜ ከንጉሡ ተሰናበተች ንጉሡም ምድረ ለግን ሰጣትና በታላቅ ክብር አሰናበታት በዚያን ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከከተማ ወጥታ ሂዳ ፍንጥሮ ደረሰች እዚያ ስትደርስ ወለተ ማርያም ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እኔ ከአንቺ ጋር አልሄድም ማኅበሩ በኔ ላይ አንጐራጒሮዋልና እኔ ስለ አሳዘንኳቸው እኔና እነሱ እንደዚህ ሁነን እንዴት እንጸድቃለን ስለዚህ በአገሬ ብቀመጥ ይሻለኛል አለች።

፫ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም መልሳ በዚህ አገር ብቻየን እንዴት ትተሽኝ ትሄጃለሽ ቅርኛ ደርሰን እንሰነባበታለን እኔም እሄዳለሁ አንቺም ትመለሻለሽ አለቻት ወለተ ጴጥሮስም እሺ ብላ ከእሷ ጋር በታንኳ ሂዳ ቅርኛ ደርሳ ከእሷ ጋር አደረች እንደገና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ከእሷ ጋር ሂዳ ፎገራ እንድታደርሳት ለመነቻትና እሺ አሰኘቻት ፎገራ ደርሳ በዚያ ሁለቱም እያለቀሱ ተሰነባበቱ።

፩ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተአምር ከመ ትትመያየጥ ወትገብእ በይእቲ ዕለት ወእምዝ ተአምኃ በበይናቲሆን ወተፈልጣ ወዓርጋ በበታንኳሆን ወተገልበበት ገጸ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወተመይጠት መነገለ ፍኖታወይእቲኒ ሜጠት ገጻ መንገለ ፍኖታ ወአኃዘት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትጸሊ ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይሚጣ ለወለተ ማርያም ::

፪ ወእምድኅረ ርኅቀት ንስቲተ ወለተ ማርያም በአ ውስተ ልባ ሶቤሃ ፍርሃት ወድንጋፄ ወሁከት ወቀቢፀ ተስፋ ጦባሕርኒ ተሀወከ ወይእተ ጊዜ ትቤሎሙ ለኖትያት አግብኡኒ ሊተ ወተአዘዙ እምኔሃ ኖትያት ሜጡ ገጾሙ ወሐደፉ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አተወት ደምበዛ ወቤተት ህየ ወወለተ ማርያምኒ ኃለፈት ወኢያእመረት ከመ አተወት ደምበዛ ወሖረት ወበጽሐት አፈር ፈረስ ወእምነሂ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በጽሐት በሳኒታ ወሶበ ርእየታ ለወለተ ማርያም ሰሐቀት ወተፈሥሐት ፈድፋደ::

፫ ወእምድኅሬሁ ነበረት ወለተ ማርያም ምስለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወኢተፈልጠት እምኔሃ እስከ አመ ሞተት ወዝንቱ ኩሉ ኮነ በጸሎተ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እስመ ይእቲ ኢትፈቅድ ይትፈለጥ እምኔሃ መኑሂ ለዓለም ወዓዲ ይደልወነ በዝንቱ ንዘከር ትሕትናሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እስመ ነበረት እንዘ ትትለአክ ለማኅበር በዕብሬታ ከመ አሐቲ እምኔሆን እንዘ ትቀድሕ ማየ ለኀፅበተ እድ ወበጊዜ ማዕድ ታረፍቆን ለአሐት ወትቀውም ይእቲ ወትትለአኮን ወኢትነብር ዘእንበለ ፍጻሜ ጸሎተ አኰቴት::

፬ ወካዕበ ትበውእ ውስተ ቤተ ተግባር ወተሐብዝ ኅብስተ ወትኰስትር ሐመደ ወጕድፈ ወትጸውር በርእሳ ወትገድፍ አፍአ ወካዕበ ተአጽር ሴዋ ወትጸውር ኃሳረ ወትክዑ ኀበ ምክዓወ ዘትካት ወአልቦ አንቀጸ ትሕትና ዘኢቦአት ውስቴቱ እምነ ቅድስት ወቡርክትወለተ ጴጥሮስ ወኮነት ትትረከብ በውስተ ኵሉእንዘ አግአዚት ይእቲ ትከውን አመተ በከመ ይቤ ጳወሎስ እንዘ እግዚእ አነ እምዝንቱ ኵሉ አቅነይኩ ርእስየ ለኵሉ::





፩ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ግን በዚያች ቀን ተመልሳ እንደምትመጣ ታውቃለች ከዚህ በኋላ እርስ በእርሳቸው እጅ ተነሳስተውና ተለያይተው በእየታንኳቸው ገቡ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ልብሷን ተከናንባ ጕዳናዋን ቀጠለች እሷም ፊቷን ወደመንገዷ መልሳ ሄደች እናታችንም ወለተ ማርያምን ይመልሳት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ትጸልይ ጀመረች ::

፪ ወለተ ማርያም ጥቂት ከራቀች በኋላ በልቧ ውስጥ ፍርሃትና ድንጋጤ መታወክ ተስፋ መቁረጥ መጣባት ባሕርም እጅግ ተናወጠች በዚህን ጊዜ ታንኳ የሚነዱትን ወደኋላ መልሱኝ አለቻቸው እነሱም ታዝዘው እሺ ብለው ወደኋላ መለሷት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ደምበዛ ገብታ እዚያ አደረች ወለተ ማርያም ደምበዛ እንደሄደች ስለ አላወቀች አልፋ አፈር ፈረስ ሄደች እናታችን ወለተ ጴጥሮስ በማግስቱ ስትሄድ ወለተ ማርያምን እዚያ አገኘቻትና ደስ ብሏት ሳቀች ::

፫ ከዚህ በኋላ ወለተ ማርያም በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎት ፀናች እሷ ማንም ከእሷ እንዲለይ አትፈልግምና ዳግመኛ የእናታችን የቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ትሕትና እናስብ ዘንድ ይገባናል ከማኅበር ልጆቿ ጋር ተራ ገብታ ተራዋ ሲደርስ ከእነሱ መካከል እንደ አንዲት አገልጋይ በማዕድ ዕንቶችን ታስቀምጥና ውሀ ቀድታ እጃቸውን ታስታጥባቸው ማዕዱ ተፈጽሞ ስብሐት እስኪባል ድርስ ቁማ ታገለግላቸው ነበር::

፬ እንደገናም ተግባር ቤት እየገባች እንጀራ ትጋግር አመድ እየጠረገች በእራሷ ተሸክማ አውጥታ ደጅ ታፈስ ጠላም እየጠመቀች ከተጠጣ በኋላ አተላውን እራሷ ወደ ውጪ አውጥታ ታፈስ ነበር እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ያልገባችበት የትሕትና በር አልነበረም በሥራ ሁሉ ትገኛለች እንጂ እመቤት ስትሆን በፈቃዷ አገልጋይ ሆነች ቅዱስ ጳውሎስ እኔ ገዥ ስሆን እራሴን ለሁሉ አስገዛሁ እንዳለ::

፰ ወአሐተ ዕለተ ሶበ ኮነ በዓለ ፍልሰታ ለእግዝእትነ ቅድስት ወቡርክት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ገብረት ዐቢየ ምስሐ ወአስተዳለወት ማዕዳተ ብዙኃ መባልዕተ ወስቴያተ ዘዘዚአሁ ወአስተጋብአቶን ለኵሎን አኃት ለልሒቃት ወለንዑሳት ወአርፈቀቶን በበምርፋቃቲሆን ወቆመት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወተልእከቶን ወወደየት ማየ ለእደዊሆን ወአስተፍሥሐቶን ወእምድኅረ በልዓ ወጸግባ አቅረበት ስቴያተ ወመጠወቶን ለልሒቃት ወለንኡሳት በበአምጣኒሆን ወፈጸመት በይእቲ ዕለት ኵሎ ግብረ ትሕትና።

፱ በከመ ፈጸመ እግዚእነ በጸሎተ ሐሙስ አመ ሐፀበ እግረ አርዳኢሁ ወይቤሎሙ አእመርክሙኑ ዘገበርኩ ለክሙ አነ እንትሙሰ ትብሉኒ ሊቅነ ወእግዚእነ ሠናየ ትቤሉ እስመ ከማሁ አነ ውእቱ ሊቅክሙ ወእግዚእክሙ ሐፀብኩክሙ እገሪክሙ ወከማሁ አንትሙኒ ርቱዕ ይደልወክሙ ትሕፀቡ እግረ ቢጽክሙ እስመ አርአያየ ወሀብኩክሙ ከመ ትግበሩ አንትሙኒ በከመ ገበርኩ ለክሙ አነ ወከማሁ ገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወመርሐቶን ፍኖተ ትሕትና ለእሊአሃ።

፲ ወእማንቱኒ ኮና ይተልዋ ኪያሃ ወይትማሰላ ከማሃ እመኒ ተአደዋ እምሥርዓት ዘአዘዘቶን አው በገቢር አው በሐልዮ ይትከሠት ወይትርአይ ላቲ ከመ ይትረአይ ንዑስ ሀሠር ዘወድቀ እምውስተ ሀሊብ ጽሩይ ከማሁ ይትረአይ ሊተ ኅሊና ኵሉ ማኅበር ትቤ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወብዙኃን እምነ አኃት ሀላዋ እስከ ይእዜ ወንህነ ነአምሮን ወተነበየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በእንቲአሆን ከመ ይረክቦን መከራ ወድቀት በደኃሪ መዋዕል ለለአሐቲ አሐቲ ተፈፅመ ላዕሌሆን ወኮነ በከመ ትቤሎን ፡፡

፲፩ ወእማንቱኒ ስምዓ ይከውና ከመዝ ወቦ እምነ አኃው ወአኃት ዘተነበየት በእንቲአሆሙ ዘከመ ይወፅኡ ወይትፈለጡ እምነ ማኅበር ወተፈጸመ ወኮነ በከመ ትቤ ወእንዘ ሀለወት በዘከመዝ ግብር እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ውስተ አፈር ፈረስ መጽአ ላዕሌሃ ሕሊና ሁከት ዘይብል ንበሪ ባሕቲተኪ በተባሕትዎ ከመ ነበርኪ ቅድመ በዋልድባ እንዘ ሀሎኪ በተባሕትዎ ፡፡





፰ ከዕለታት በአንድ ቀን ይኸውም አምላክን በወለደች ቅድስትና ቡርክት በሁለት ወገን ድንግል በምትሆን በእመቤታችን በፍልሰቷ በዓል ታላቅ ድግስ ደግሳ ብዙ ማዕድንና በየወገኑ የሚበሉትንና የሚጠጡትን አዘጋጅታ እኅቶችን ሁሉ ትልቆችንም ትንንሾችንም በየማዕረጋቸው አስቀምጣ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በመካከላቸው ቁማ እስኪደሰቱ ድረስ መገበቻቸው በልተው ከጠገቡ በኋላ የሚጠጡትን አቀረበችላቸውና ለታላላቆችም ለታናናሾችም እንደየአቅማቸው ሰጠቻቸው በዚያች እለት የትሕትናን ሥራ ሁሉ ፈጸመች።

፱ ጌታችን በጸሎተ ሐሙስ የደቀ መዛሙርቱን እግር በአጠበ ጊዜ ትሕትናን እንደፈጸመና እኔ ያደረኩላችሁን ታውቃላችሁን መምህራችሁ ስሆን እግራችሁን እንደአጠብኩ እናንተም የወንድማችሁን እግር ታጥቡ ዘንድ ይገባችኋል እኔ እንደአደረኩላችሁ ታደርጉ ዘንድ አርአያ ሁኛችኋለሁና እንደዚሁ እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ እነዚያን እኅቶች የትሕትናን ጐዳና መራቻቸው።

፲ እነሱም እሷን ተከትለው እንደ እሷ ሆኑ እሷን በሥራ መሰሏት ከአዘዘቻቸው ሥርዓት በምግባርም ሆነ በሐሳብ ፈቀቅ ያሉ እንደሆነ በጠራ ወተት ውስጥ ጥቂት ጉድፍ ሲገባ እንዲታይ እንደዚሁ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ማኅበር ሁሉ በልቡናቸውና በኅሊናቸው የሚያስቡት ሐሳብ ይታየኛል አለች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለየአንድ አንዳቸው በኋላ ዘመን መከራና ድቀት እንደሚያገኛቸው የነገረቻቸው ነገር ተፈጸመ እኛም የምናውቃቸው ይህ መጽሐፍ እስከተጻፈበት ጊዜ ድረስ ብዙ እህቶች ነበሩ ፡፡

፲፩ እነሱም እንደዚሁ ይመሰክራሉ ከወንዶችም ከሴቶችም ኋላ ከማኅበሩ እንደሚወጡ የተናገረቻቸው እንደ አለቻቸውም የወጡ አሉ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በዚህ መልካም ትሩፋት በአፈር ፈረስ ሳለች አስቀድመሽ በዋልድባ በተባሕትዎ እንደ አለሽ አሁንም ከሰው ተለይተሽ በዋልድባ በተባሕትዎ ኑሪ እያለ የሚያስቸግራትና የሚያውካት ሐሳብ መጣባት ፡፡

፲፪ ወሐለየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ትሑር ደሴተ ናርጋ ወትንበር ባሕቲታ ወእንበይዝ አምጽአት ምክንያተ ነገር ወትቤ ናሁ ተጋብኡ ኀቤየ ብዙኃን ሰብእ ወአልቦ ምንትኒ ውስተ እዴየ እመኒ ልብስ ወእመኒ ሲሳይ ካዕበኒ ኢይትከሃለኒ ሊተ እጹር ሁከተ ብዙኅ ሰብእ አንሰ አሐውር ናርጋ እስመ ብየ ፈቃድ ለነቢር አስተዳልዉ ሊተ ታንኳ ዝየሰ ትንበር እኅተ ክርስቶስ እስመ ይእቲ ትክል ጸዊረ ሁከተ ብዙኅ ሰብእ ወነቢረ በከመዝ ግብር ወሶበ ትቤ ከመዝ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አውሥአ ሥዕለ ክርስቶስ ወይቤላ እስኩ ኢትጕጕዒ ናቅድም ጸሎተ ወንጸሊ አሐተ ሡባዔ ወትቤ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኦሆ ወጸለዩ ክልኤሆሙ አሐተ ሰባዔ ::

፲፫ ወእምዝ ይቤላ ሥዕለ ክርስቶስ እስኩ ንግርኒ ምንተ ረከብኪ ወትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አንሰ ኢረከብኩ ምንተኒ ወይቤላ ዳግመ ንጸሊ ሰባኤ ወትቤሎ ኦሆ ወጸለዩ ዳግመ ከመ ቀዳሚ ወተስእላ ዳግመ ወይቤላ እስኩ ንግርኒ ዘርኢኪ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኃብአቶ ወሠወረቶ ወትቤሎ አንሰ ኢርኢኩ ግሙራ ወይቤላ ሥዕለ ክርስቶስ ለእመ አንቲ ኃባእክኒ ወሠወርክኒ አነ እነግረኪ::

፲፬ ወትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በል እስኩ ንግረኒ ወሶቤሃ ከሠተ ላቲ ኅቡአቲሃ በከመ አለበዎ ግብተ መንፈስ ቅዱስ ከሣቴ ኅቡአት ወይቤላ ዘይትወሀብ ጸጋ በዘመነ ብሕታዌ ካልእ ውእቱ እምነ ጸጋ ዘይትወሀብ በማኅበር ለባሕታዊሰ ያርእይዎ ጸጋተ ዘዘዚአሁ ከመ ይትናዘዝ ቦሙ ወኢያንቀልቅል እመካኑ ማኅበርሰ በከመ ጕላቄሁ ወበከመ መልክዑ ወአካለ ቆሙ ከማሁ ግዕዙ ወለእመ ጸርኪ ወተዓገሥኪ ግዕዘ ኵሉ ማኅበር ዘዘዚአሁ ጸጋ ውእቱ::

፲፭ ትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እሙነ ትቤ ወእንበይነዝ ተሀወኩ ወባሕቱ ይእዜሰ መጽአ እግዚእነ ወይቤለኒ ሥልሰ ጊዜ ረዓዪ አባግዕየ ወአባግዕትየ ወኢትትሀወኪ ግሙራ አኮኑ አነ ብህልክዎ ለጴጥሮስኒ ቀዲሙ





፲፪ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወደ ናርጋ ደሴት ሂዳ ብቻዋን ትኖር ዘንድ አሠበችና ስለዚህ ምክንያት ፈጥራ እነሆ ብዙ ሰዎች ወደ እኔ ተሰብስበዋል በእጀ ልብስም ቢሆን ምግብ የለኝም ዳግመኛም የብዙ ሰዎችን ፀባይ አልችልም እኔ ወደ ናርጋ እሄዳለሁ እዚያ መሄድ እፈልጋለሁና ታንኳ አዘጋጁልኝ እዚህ ግን እኅተ ክርስቶስ ትቀመጥ እሷ የብዙ ሰዎችን ባህርይ ችላ እንደዚህ መኖር ትችላለችና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንደዚህ ባለች ጊዜ ሥዕለ ክርስቶስ መልሶ እስኪ አትቸኩይ መጀመሪያ አንድ ሱባዔ ጸልየን እንጠይቅ አላት እናታችን እሺ ብላ ሁለቱም አንድ ሱባዔ ጸለዩ::

፲፫ ከሱባዔ በኋላ ሥዕለ ክርስቶስ ምን መልስ አገኘሽ ንገሪኝ አላት እናታችንም እኔ ምንም መልስ አላገኘሁም አለችው ዳግመኛ አንድ ሱባዔ እንጨምር አላት እሽ አለችው እንደ ቀድሞ ሁለተኛውን ሱባዔ ያዙ ሱባዔውን ከፈጸሙ በኋላ እስኪ ያገኘሽውን መልስ ንገሪኝ አላት እናታችንም አውቃ ደብቃ ኧረ እኔ ምንም አላየሁም አለችው ሥዕለ ክርስቶስም መልሶ አንች ብትደብቂኝ እኔ እነግርሻለሁ አላት::

፲፬ እናታችን ቅድስት ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በል እስኪ ንገረኝ አለችው በዚህን ጊዜ የተሠወረውን የሚገልጥ መንፈስ ቅዱስ ድንገት እንደገለጸለት ሠውራው የነበረችውን ገለጠ በብህትውና ዘመን የሚሠጥ ጸጋ ከማኅበር ጋራ በአንድነት ሁነው ከሚሰጥ ጸጋ ይለያልና ከፈተና ፅናት የተነሣ ለባህታዊ ከበዓቱ እንዳይወጣ እና ተስፋ እንዳይቆርጥ የተለያዩ ምሥጢሮች ይታዩታል የአነድነት ማኅበር ግን እንደማኅበሩ ቁጥር ብዛት እንደየ መልኩ እንደየ አቋቋሙ ፀባዩ የተለየ ስለሆነ የእነዚህን የአንድነት ማኅበር ፀባይ ችለሽ ታግሠሽ ብትኖሪ በእያንዳንዳቸው ቁጥር ልክ ጸጋ አለሽ አላት::

፲፭ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም እውነት ብለሃል ስለዚህ ስጦታ ተፈተንኩ ነገር ግን ጌታችን ዛሬ ወደኔ መጥቶ ሦስት ጊዜ በጐቼን ዝምብለሽ ጠብቂ ፈጽመሽ አትታወኪ አስቀድሞ ለጴጥሮስ በጐችን ጠብቅ ያልኩት እኔነኝ ዛሬም አንቺን በጐችን ጠብቂ አልኩሽ ስለዚህ ከዛሬ ጀምሬ

ወለኪኒ እብለኪ ይእዜ ከማሁ ወበእንተዝ አነሂ ኢይትሀወክ እምይእዜ ወዘንተ ትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥርስ ለሥዕለ ክርስቶስ ወውእቱሂ ነገረነ ወጸሐፍናሁ ወዓዲ ሶበ ይቤላ አባ ዘሥላሴ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ባርኪ ሊተ ልብስየ ወባረከት ሎቱ እንዘ ትብል እግዚአብሔር ይባርክ ለከ ወይረሲ ለከ አነዳ::

፲፮ ወተባረከ ሎቱ ወነበረ ብዙኃ ዓመታተ ወአመ ኮነ ረኃብ ዓቢይ በዘመነ አንበጣ ወሀበ አባለ ክርስቶስ እክለ ብዙኃ እምነ ጕና ወአሜሃ ፈነወቶሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለመንፈቀ ማኅበር ከመ ይሴሰዩ በህየ በወርኃ ክረምት ወመንፈቀ ማኅበር ተርፉ በአፈር ፈረስ ምስለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወእምድኅሬሁ ካዕበ ፈነወት ኅዳጣነ ሰብአ እምእለ ሀለዉ ምስሌሃ ከመ ይንበሩ ዘንቦል ወይሴሰዩ እክለ እምነ ለግ ወነበረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ታስተባሪ ቦ ጊዜ አፈር ፈረስ ወቦ ጊዜ ዘምቦል ወአሐተ ዕለተ እንዘ ትመጽእ በታንኳ እምነ ዘምቦል ወሶበ ቀርበት ለበጺሕ ኀበ ዘጌ ተገፍትዓ ታንኳ ወወድቀት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወተሰጥመት ውስተ ቀላይ ወሰከበት በህየ እንዘ ትትገለበብ አጽፋ ወጕንደየት እንዘ ትጼሊ ሰላመ መልአክ ወ፩ አቡነ ዘበሰማያት ወእለ ወድቁ ምስሌሃ ፍጡነ ወፅኡ::

፲፯ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተኃጥአት ወደንገፁ ኵሎሙ ወመሰሎሙ ዘሞተት ወሶበ ፈጸመት ጸሎታ አንሳሕስሐት ውስተ ቀላይ ወይእተ ጊዜ ጾራ ማየ ባሕር ወገደፋ ውስተ ሐይቅ ወወፅአት ዳኅና ወመጻሕፍትሂ ኢጠፍአ አላ ወፅአ ዳኅነ ወሶቤሃ ተኃፍረ ሰይጣን ዘፈቀደ ያመንድባ ወያመክራ በከመ ይቤ ጳውሎስ ተመንደብኩ በባሕር ወእምዝ ዓርገት ዳግመ በውእቱ ታንኳ ወመጽአት አፈር ፈረስ ወነበረት ህየ እስከ ይበጽሕ ፈቃደ እግዚአብሔር ወእምድኅሬሁ ሖረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሖሩ ምስሌሃ በምልአሙ ኵሉ ማኅበር እለ ሀለዉ በአፈር ፈረስ ወእሉኒ እለ ሖሩ ጕና መጽኡ ወተጋብኡ ኵሎሙ ውስተ ዘምቦል ወነበሩ ኅቡረ አሐተኔ አሐውኒ ወአኃትኒ በበማኅደሪሆሙ ወበበአብያቲሆሙ ወበበሥርዓቶሙ ዝ ውእቱ ሳብዕ ማኅበር::





አልታወክም አለችው እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለሥእለ ሥላሴ ይህን ብላው ኋላ እሱ ነግሮን ጻፍን እንደገናም አባ ዘሥላሴ ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ልብሴን ባርኪልኝ አላትና እግዚአብሔር ይባርክልህ ዳባ ያድርግልህ አለችው::

፲፮ ያም ልብስ ተባረከለትና ብዙ ዓመት ለብሶት ኖረ አንበጣ በተነሣበት ዘመን ታላቅ ረሃብ ሆነና ሥዕለ ክርስቶስ ከጉና ሀገር ብዙ እህል ሠጣት በዚያን ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ግማሹን ማኅበር በዚያ ያንን እህል እየበሉ እንዲከርሙ ላከቻቸው ግማሹ ማኅበር ከእናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ጋር በአፈር ፈረስ ቀርተው ነበርና ከሷ ጋራ የነበሩትን ዳግመኛ ዘምቦል ተቀምጠው በዚያ የተገኘውን እህል እንዲበሉ ላከቻቸው እናታችንም አንድ ጊዜ አፈር ፈረስ አንድ ጊዜ ዘምቦል እየሄደች በፈረቃ ትቀመጥ ነበር ከዕለታት በአንድ ቀን ከዘምቦል በታንኳ መጥታ ዘጌ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራት ታንኳ ከማዕበል ጽናት የተነሣ ተገልብጦ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በባሕሩ ወስጥ ሠጥማ አፅፏን ለብሳ የመላኩን ሰላምታ እና አንድ አቡነ ዘበሰማያት እየጸለየች ከባሕሩ ውስጥ ቆየች ከሷ ጋር የተገለበጡት ፈጥነው ወጡ::

፲፯ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ግን ከባሕሩ ውስጥ ቆየች ሁላቸውም ባሕር ውስጥ ሠጥማ የሞተች መስሏቸው ደነገጡ እናታችን ጸሎቷን በፈጸመች ጊዜ ከውሃው ውስጥ ሆና ተንቀሣቀሠች በዚህን ጊዜ ውሃው ተሸከማትና ወስዶ ወደ ወደቡ በደኅና አወጣት መጻሕፍቱም ሣይበሰብሱ ደኅና ሆነው ወጡ ያን ጊዜ ያስጨንቃትና ይፈትናት የነበረ ሰይጣን አፍሮ ጠፋ ጳውሎስ በባሕር ተቸገርሁ እንዳለ ከዚህ በኋላ ዳግመኛ በዚያ ታንኳ ተጭና ወደ አፈር ፈረስ ሄዳ የእግዚአብሔር ፈቃድ እስኪደርስ ድረስ እዚያ ተቀመጠች ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድሰትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ስትሄድ ከሷ ጋራ በአፈር ፈረስ ያሉ ማኅበር ተከትለዋት ሄዱ እነዚያ ወደ ጉና የሄዱትም መጥተው ሁላቸውም ተሠብስበው በዘምቦል ወንዶችም ሴቶችም በእየሥርዓታቸው እና በእየቤታቸው ተቀመጡ ሰባተኛ ማኅበር ይህ ነው :

## ምዕራፍ ፳፫

፩ ወእምዝ ሐደሰት ሥርዓተ ወአስተጋብአቶሙ ለመነኮሳት ከመ ኢይርፍቁ ወኢይኑሙ ውስተ ፩ ቤት እመኒ ንኡስ አው ዐቢይ ወይትፈለጡ በምንትኒ ዘእንበለ ኅዳጣን አዕሩግ ወኃረየቶ እምኔሆሙ በፈቃደ እግዚአብሔር ለአባ ዘሐዋርያት ወረሰየቶ አበ ለኲሉ ወፈለጠት እለ ይትጌበሩ ሰብአ በበአብያቲሆሙ ወአዘዘቶሙ ከመ ኢይባኡ ፩ዱ ውስተ ቤተ ፩ዱ በምንትኒ ምክንያት ወእመኒ ቦሙ ትካዝ ዘይወስድ ይቁሙ አፍአ ወይትናገሩ ትካዞሙ ወለአኃትሰ ሠርዓቶን በበ፶ ወበበኍላቋሆን አሐቲ ርእስ ለለአብያቲሆን ወነበሩ አኃውኒ ወአኃትኒ በዘከመዝ ሥርዓት በፍቅር ወበሰላም ።

፪ ወበውእቱ መዋዕል ወፅአት ሌሊተ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በዕለተ እሑድ ምስለ አሐቲ እኅት ወቦአት ውስተ ቤተ ክርስቲያን ዘፋሬ እስመ ነበረት አሜሃ በውእቱ ምኔት ወሰበ ፈቀደት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ታንብብ ወንጌለ ዮሐንስ በይእቲ ሌሊት እንዘ ዓዲሁ ጽልመት ወፈነወታ ለይእቲ ወለት ከመ ታምጽእ ላቲ ማኅቶተ ወሖረት ይእቲ ወለት ከመ ታምጽእ ወጐንደየት እንዘ ተኃሥሥ እሳተ እስመ ጠፍአ ወለእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወረደ ላቲ እምሰማይ ማኅቶተ ሰምዕ ፀዓዳ ወወጠነት ታንብብ ሶቤሃ ወእመድኅረ ጕንዱይ መጽአት ይእቲኒ እኅት እንዘ ትእኀዝ ማኅቶተ፡፡

፫ ወረከበታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ተኃቱ ማኅቶተ ወታነብብ ወንጌለ ወተስእለታ ይእቲ ወለት ለእምነ ቅድስተ ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤላ አንሰ ጐንደይኩ እንዘ አአውድ አብያተ ወአኃሥሥ እሳተ መኑ አምጽአ ለኪ ዘንተ ማኅቶተ ወነጸረታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በዓይነ መዓት ወሶቤሃ አርመመት ይእቲ ወለት ወኢደገመት ተስእሎታ እስመ አእመረት ከመ ወረደ ላቲ እምሰማይ ወእምዝ እንዘ ሀለወት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ውስተ ዘምቦል ምስለ እሉ ማኅበር ዘተዳሚ ወተወሰኩ በህየኒ ወኮኑ ፻፹ ወሶቤሃ ተንሥአ ደዌ ጽኑዕ ላዕለ አኃት ወአሕመሞን ወቀተለ እምኔሆን ብዙኃተ አኃተ ወኮና ይትቀበራ ውስተ መቃብር ፩ ለለዕለቱ በበ፫ አው ይበዝኅ፡፡





## ምዕራፍ ፳፫

፩ ከዚህ በኋላ መነኮሳትን ሰብስባ በአንድ ቤት፡እንዳይተኙ ትልቅም ሆነ ትንሽ ያለ አረጋውያን በስተቀር አንድ ላይ አይሁኑ ብላ አዲስ ሥርዓት ሠራች ከነሱም መካከል በእግዚአብሔር ፈቃድ አባ ዘሐዋርያትን መምህር አድርጋ ሾመች በእየቤታቸው የሚሠሩትን አንዱ ወደ አንዱ ቤት እንዳይሄድ እና ከውጭ ቆሞ ችግሩን ሣይናገር ዘው ብሎ እንዳይገባ ሥርዓት ሠራች ለእኅቶችም እንደዚሁ ሃምሳ ሃምሳ አድርጋ ከነሱ መካከል አንድ አለቃ በየቁጥራቸውና በየነገዳቸው ሾመች ወንዶችና እኅቶች በዚህ ሥርዓት በፍቅርና በሰላም ተስማምተው ኖሩ፡፡

፪ በዚያች ሰሞን እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እሁድ ሌሊት ከአንዲት እኅት ጋር ፋሬ ወደአለችው ቤተክርስቲያን ሄደች በዚያን ጊዜ የነበረችው በዚያ ገዳም ነበርና እናታችን ገና ጨለማ ስለነበር በዚያች ሌሊት የዮሐንስን ወንጌል ለማንበብ ፈልጋ መብራት ታመጣላት ዘንድ ያችን ልጅ ላከቻት ያችም ልጅ እሳቱ ስለጠፋ እሳት ስትፈግ ቆይታ ስትመጣ ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በረድ የሚመስል ነጭ ጧፍ ከሰማይ ወረደላት ያን እያበራች ጸሎት እየጸለየች ሳለ ያች እኅት ቆይታ መብራት ይዛ መጣች ፡፡

፫ እናታችን ቅድስት ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መብራት አብርታ ጸሎት ስትጸልይ አግኝታ እናታችን እኔ እሳት አጥቼ እሳት ስፈልግ መንደር ለመንደር ስዞር ቆየሁ ይህን መብራት ማን አመጣልሽ አለቻት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ዝም በይ ብላ በዓይነ መዓት አየቻት ያችም ልጅ ዝም አለች ሁለተኛ አልደገመችም ከሰማይ እንደወረደላት አውቃለችና ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ቀድሞ ከነበሩት ማኅበር ጋር በዘምቦል ሳለች ብዙ ሰው ተጨምሮ ዘጠኝ መቶ ማኅበር ሆኑ በዚያን ጊዜ ጽኑ በሽታ እኅቶችን ያዛቸውና ፀንቶባቸው ብዙ እኅቶችን ገደላቸው በእየቀኑ ሦስት ሦስት ከዚያም የሚበዙ በአንድ መቃብር ይቀበሩ ነበር፡፡

፬ ወእምድኅሬሁኒ ቦአ ኀበ መነኮሳት ውእቱ ደዌ ወአኀዘ ይቅትል ወሀለወ እምውስተ አኃው ፩ ወልድ ወሪዛ ዘስሙ ቤዛ መስቀል ወልደ እምነ አመተ ድንግል ወሠናየ ላህይ ውእቱ ወልድ ወዘልፈ ሶበ ትሬእዮ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትትሜነይ ሞተ ዚአሁ ወኮነት ትስእሎ ለእግዚአብሔር ከመ ይትወከፎ ፍጡነ ወእሙኒ ነበረት እንዘ ትጼሊ ከመዝ በእንቲአሁ ወሶበ ኮኖ፺ ዕለት እምአመ መንኰስ ወወዓለ በዕለተ እሑድ እንዘ ይቀውም ወይቀንት ሐቌሁ ወይትለአኮሙ ለማኅበር በጊዜ ምሳሕ እስመ ዕብሬቱ ይእቲ ዕለት ወእምድኅረ ፈጸመ ተልእኮ ሐመ በይእቲ ዕለት ወሞተ በሣልስት ዕለት ወደንገፀ ኲሉ ማኅበር ወለአኩ ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወነገርዋ ዘከመ ሞተ።

፭ እምቅድመ ትስማዕ ደዌሁ ሰምዓት ሞቶ ወሶበ ሰምዐት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተፈሥሐት ፈድፋደ ወሰብሐቶ ለእግዚአብሔር ወይእተ ጊዜ ለአከት ኀበ እሙ ይጸውዕዋ ይእቲሰ ኢተአምር ዘኮነ ወመጽአት ወቦአት ኀቤሃ ወተናገረታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በነገረ ምሳሌ እንዘ ትብል ኲሉ ሰብእ ሶበ ረከበ ዘተመነየ ወተሰፈወ ይደልዎኑ ይትፌሣሕ ወሚመ ይኅዝን ወትቤ እሙ ይደልዎ ይትፌሣሕ ወትቤላ ሠናየ አውሥአታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መርዓዊ ፈታሕኪ አንቲኒ ተፈሥሒ ወተኃሠዪ ናሁ ወልድኪ ዘአዕረፈ ሰማያዊ አዕረፈ ወትቤ እሙ መኑ ውእቱ ወልድየ ወትቤላ አውሥአታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወልድኪ ቤዛ መስቀል አዕረፈ ወትቤ እሙ ማእዜ ሐመ ወማእዜ ሞተ ወሶቤሃ ወድቀት በድንጋፄ እንዘ ኢተአምር ወበከየት ንስቲተ።

፮ ወገሠጸታ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወአኅደገታ ብካየ ወትቤላ እኮኑ ነበርኪ እንዘ ትትሜነዪ ትርአዪ ሞቶ እፎ ተኃዝኒ ይእዜ ወትዌልጢ ቃለኪ ወተኃሥዪዮ ለእግዚአብሔር እመሰ ትፈቅዲ እምእንሣእኩ ለኪ ወትቤ እሙ ዘኮነሰ ኮነ አብሕኒ እሑር እርአዮ ምዕረ ወትቤላ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አንሰ ኢይፌንወኪ ወለእመ ሖርኪ ትበክዪ በህየ ወትቤ አንሰ ኢይበኪ ግሙራ ዳዕሙ ፈንውኒ ንስቲተ እርአይ ገጾ እምቅድመ ይቅብርዎ ወትቤላ አባሕኩኪ ሑሪ ዳዕሙ ኢትብክዪ።





፬ ከዚህም በኋላ ያበሽታ ወደ ወንዶች መነኮሳትም ተላልፎ ይገላቸው ጀመር ከወንድሞች መካከል ስሙ ቤዛ መስቀል የሚባል የእናታችን የአመተ ድንግል ልጅ ነበረ እሱም መልከ መልካም ስለነበረ እናተችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እሱን በአየችው ቁጥር የእሱን ሞት ትመኝ ነበርና እግዚአብሔር ፈጥኖ እንዲወስደው ትለምናለች የልጁም እናት እንደዚሁ እያለች ትጸልይ ነበር መንኩሶ ዓርባ ቀን በሆነው ጊዜ ቀኑ እሁድ ስለነበረ ወገቡን ታጥቆ ምሳ ሲያቀርብላቸው ዋለ ያቺ ዕለት የእሱ ተራ ነበረችና ተልዕኮውን ፈጽሞ በዚያች ዕለት ማታ ታሞ በሦስተኛው ቀን አረፈ ማኅበርተኞችም በጣም ደንግጠው ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሞተ ብለው ላኩ ::

፭ መታመሙን ሳትሰማ ሞቱን በሰማች ጊዜ እጅግ ተደስታ እግዚአብሔርን አመሰገነች በዚህን ጊዜ ይጠሯት ዘንድ ወደ እናቱ ላከች እሷ የሆነውን አታውቅም ነበርና መጥታ ወደ እሷ ገባች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሰው ሁሉ የተመኘውንና ተስፋ ያደረገውን ያገኘ እንደሆነ ይደሰታል ወይም ያዝናል አለቻት እናቱም መልሳ ይደሰታል አለቻት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም መልሳ መልካም መልሰሻል እነሆ ሰማያዊ ሙሽራ ልጅሽ አርፏልና ደስ ይበልሽ አለቻት እናቱም ያረፈ ልጄ የትኛው ነው አለችው እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ልጅሽ ቤዛ መስቀል አረፈ አለቻት እናቱም መቸ ታሞ መቼ ሞተ አለቻትና በድንጋጤ ወድቃ ጥቂት አለቀሰች::

፮ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ተቆጣቻትና ለቅሶውን አስተወቻት የሱን ሞት ትመኚለት አልነበረምን ቃልሽን ለውጠሽ እግዚአብሔርን ዋሽተሽ ዛሬ ለምን አዘንሽ ከፈለግሽ ባስነሳሁልሽ ነበር አለቻት እናቱም የሆነስ ሆኗልና ሂጀ ልጄን አይ ዘንድ አሰናብችኝ አለቻት እናታችንም እኔ አላሰናብትሽም ከሄድሽ ታለቅሻለሽ አለቻት እሷም እኔስ ምንም አላለቅስም ሳይቀብሩት ፊቱን አይ ዘንድ አሰናብችኝ አለቻት እሷም አታልቅሽ እንጅ አሰናብቸሻለሁ ሂጅ አለቻት ::

፯ ወሶቤሃ ወፅአት ወተለዋሃ አብያጺሃ አኃት እንዘ ይበክያ እስከ አንቀጸ ቅጽር ወሶበ ሰምዓት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ድምፀ ብካዮን ለአኃት ተምዓት ጥቀ ወአዘዘት ያግብእዋ ወይእቲኒ ተአዘዘት ወገብአት ወትቤ አንስ ኢበከይኩ ነዋ ነጽሪ እመቦ አንብዕ ውስተ አዕይንትየ ወይእተ ጊዜ ፈነወታ ወአትለወት ላቲ ፲ተ ልሂቃተ እምነ አብያጺሃ አኃት ወሶቤሃ ሖረት ወበጽሐት ኀበ በድኑ ወነጸረቶ ወሐቀፈቶ ወሰዓመቶ ወሶበ ነጸርዋ አኃው በከዩ ወእምድኅሬሁ ወሰድዎ ኀበ ቤተ ክርስቲያን በዝማሬ ወበማኅሌት ወአንበቡ ላዕሌሁ መጽሐፈ ሙታን ወቀበርዎ ።

፰ ወእሴአለክሙ አ ፍቁራንየ እመሰ ከመዝ አዘዘት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኢይብክይዎሙ ለሙታን ከመ አንትሙ ትከውኑ ስምዓ እምአይቴ መጽአ ለነ ዝንቱ ብካይ ወላህ ወሰቆቃው ቦኑ ንከውን ዓላውያኒሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ንከውን ዓላውያኒሁ ለክርስቶስ በከመ ይቤሎሙ ላሊሁ ለሐዋርያት ዘለክሙ ዓበየ ሊተ ዓበየ ወዘሊተ ዓበዮ ለዘፈነወኒ ወአንሰ ዕቤ ይደልወኒ ንዕቀብ ትእዛዘ እምነ እስመ እንበሌሁ አልብነ ድኂን፡፡

፱ ወጳውሎስኒ ይብል ወንፈቅድ ታእምሩ በእንተ እለ ኖሙ ከመ ኢይደሉ ትተክዙ ላዕሌሆሙ ከመ ካልአን ሰብእ እለ ቅቡፃን ተስፋሆሙ ወበይእቲ ዕለት እምድኅረ ቀበርዎ ሖረ አባ ዘሐዋርያት ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወይቤላ እፎ ናረምም በእንተ ዝንቱ መቅሠፍተ ሞት ዘይቀትል ግብተ ወያስተፋጥን ለለዕለት ሊተሰ ይመስለኒ ይኄይሰነ ንግበር ጸሎተ ወምህላ በስብሐተ ፍቁር ከመ ያእትት እምኔነ እግዚአብሔር ዘንተ መቅሠፍተ ወይፈኑ ላዕሌነ ሣህለ ወምሕረተ ።

፲ አውሥአቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎ ለአባ ዘሐዋርያት ኅድግ ዝንቱ ሞት ኢኮነ መቅሠፍተ፡አላ ምሕረተ እግዚአብሔር ውእቱ ወይቤላ አንስ ኢየአምር ዘከመዝ ምሕረተ እግዚአብሔር አላ መቅሠፈት ውእቱ አውሥአቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ





፯ እሷም ያን ጊዜ ወጥታ ስትሄድ ጓደኞቿ እኅቶች እስከ አጥር ደጅ ድረስ እያለቀሱ ተከተሏት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የእኅቶች የለቅሶ ድምጽን ሲያለቅሱ በሰማች ጊዜ እጅግ ተቆጥታ ይመልሷት ዘንድ አዘዘች እሷም ታዛ ተመለሰችና እኔ አላላቀስኩም እንባ በአይኖቼ ላይ ካለ ተመልከች አለቻት ከጓደኞቿ አሥር እኅቶችን አስከተለችላትና ላከቻት ያን ጊዜ ሄዳ አስከሬኑ ከአለበት ደርሳ አይታ እቅፍ አድርጋ ሳመችው ወንድሞችም እሷን በአዩ ጊዜ አለቀሱ ከዚህ በኋላ በዝማሬና በማኅሌት ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደው በአስከሬኑ ላይ መጽሐፈ ግንዘትን አነበቡ ጸሎተ ፍትሐት ከተፈጸመ በኋላ ወደ መቃብር ወስደው ቀበሩት ።

፰ ወዳጆቼ ምዕመናን እስኪ ልጠይቃችሁ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለሞቱት አታልቅሱ ብላ ከአዘዘች ለእኛስ ይህን ያህል ልቅሶና ጩኸት ለምን አስፈለገ በውኑ እናታችንን እየወነጀልን ነው ያለነው የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ቃል አለመቀበል የክርስቶስን ቃል አለመቀበልና ክርስቶስን መወንጀል ነው እሱ እራሱ ለሐዋርያት እናንተን ያልተቀበለ እኔን አይቀበለኝም እኔን ያልተቀበለ የላከኝን አልተቀበለም እንደአለ እኔስ የናታችንን ትእዛዝ ብንቀበል ይሻለናል እላለሁ ያለሱ ድህነት የለንምና፡፡

፱ ጳውሎስም ስለ ሞቱ ሰዎች ተስፋ ትንሣኤ እንደሌላቸው አሕዛብ ታዝኑላቸው ዘንድ እንደማይገባ እንድታውቁ እፈልጋለሁ እንደአለ በዚያች እለት ከቀበሩ በኋላ አባ ዘሐዋርያት ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መጥቶ ስለዚህ ድንገት የሚገል መቅሠፍት መጥቶ እንዴት ዝም እንላለን እለቱን ለሞት የሚያደርስ ነውና እግዚአብሔር ይህን መቅሠፍት ከኛ አስወግዶ ይቅርታውንና ቸርነቱን እንዲልክልን እኔስ በስብሐተ ፍቁር ምህላና ጸሎትን ብናደርግ ይሻል ይመስለኛል አላት፡፡

፲ እናታችንም መልሳ ለአባ ዘሐዋርያት ተው ይህ ሞት መቅሠፍት አይደለም የእግዚአብሔር ምሕረት ነው አለችው እሱም መልሶ እንደዚህ ያለውን የእግዚአብሔር ምሕረት አላውቅም አላት ይህስ መቅሠፍት ነው እንጅ አለ ።

ዳግመ ወትቤሎ አንሰ እብለከ ምሕረተ እግዚአብሔር ውእቱ ወኢኮነ መቅሠፈተ እፎ አንተ ትትቃወመኒ ይእዜ ወትብል መቅሠፍት ውእቱ ወይቤላ አባ ዘሐዋርያት እስኩ ንግርኒ ወአይድዕኒ ዘንተ ምሥጢረ ከመ እእመን ቃለኪ ወትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አንሰ ኢይነግረከ ዳዕሙ አእምር ወእመን በልብከ ከመ ምሕረተ እግዚአብሔር ውእቱ ወይቤላ ውእቱኒ አንሰ ኢየአምን ለእመ ኢያይዳዕክኒ ጥዩቀ አምሕልከ በእግዚአብሔር ከመ ትንግርኒ ወእምዝ ከሠተት ሎቱ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎ እመሰ አገበርከኒ ስማዕ እንግርከ ወኮነ ጊዜ ምሴት እንዘ እነብር ውስተ ቤት አንጻረ ኖኅት ርኢክዎን አነ ለደናግል እንዘ ይትጋፍዓ ወይትማርዓ በበይናቲሆን አሐቲ ምስለ አሐቲ ወሶቤሃ ነደ ልብየ ወአኃዝኩ እትዋቀስ ምስለ እግዚአብሔር ወእቤሎ ቦኑ አንበርከኒ ሊተ ከመ ታርእየኒ ዘንተ ወይእዜኒ እስእለከ ወአስተበቍዓከ ከመ ትንሣእ እምኔየ ዘወሀብከኒ አንተ ማኅፀተከ ወእመአኮ ንሥአ ለነፍስየ ይኄይሰኒ እትሐጐል አነ እምእርአይ እንዘ ይትሐጐላ እማንቱ አዋልድየ።

፲፩ ወሶቤሃ መጽአ ኀቤየ ወናዘዘኒ ወይቤለኒ ኢትፍርሂ አንሰ ሰማዕኩ ጸሎተኪ ወእገብር ፈቃደኪ ወሀለዋ ምስሌሁ ፯ አእማት ጸሊማት ወ፯ ውርዝዋት ወገዚፋት ወአሐቲ አረጊት ወይቤለኒ ንሥኢ እላንቱ አእማት ይፈጽማ ፈቃደኪ ወሥርዒዮን ለ፯ በበአብያቲሆን ለአኃት ለለአሐቲ አሐቲ ወአረጊትሰ ትንበር ኀቤኪ ወኮነ በከመ ይቤለኒ ወበእንተዝ እብለከ ምሕረተ እግዚአብሔር ውእቱ ኢትበልኑ አንተ ከመዝ ወይቤላ ውእቱኒ ዝንቱሰ ምሕረተ እግዚአብሔር ውእቱ ወበውእቱ መዋዕል ሞቱ ፻ወ፴ወ፯ እምነአኃው ወአኃት ወፈለሱ እምፃማ ውስተ ዕረፍት ወእምሐዘን ውስተ ትፍሥሕት ጸሎቶሙ ወበረከቶሙ የሃሉ ምስለ ፍቁሮሙ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

፲፪ ተስእሎ ዘከመ ተስእልዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በእንተ እሉ አኃው ወአኃት እለ ሞቱ ዘከመ ይድኅኑ ወይትሐጐሉ ወይቤልዋ እስኩ ንግርነ ከመ ይትናዘዝ ልብነ ወኢይናፍቅ እሉ ኵሎሙ እለ ሞቱ ይጸድቁኑ ኅቡረ





እናታችን መልሳ እኔ መቅሠፍት አይደለም የእግዚአብሔር ምሕረት ነው ስልህ ዛሬ አንተ እኔን ተቃውመህ መቅሠፍት ነው ለምን ትለኛለህ አለችው አባ ዘሐዋርያትም እስቲ ንገሪኝ ይህንንም ምሥጢር አምኘ ቃልሽን እቀበል ዘንድ አስረጅኝ አላት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም የእግዚአብሔር ምሕረት እንደሆን በልቦናህ መርምረህ አውቀህ እራስህ ተረዳ እንጅ እኔ አልነግርህም አለችው እሱም አንች ፈጽመሽ ካላስረዳሽኝ እኔ አላምንም ትነግሪኝ ዘንድ በእግዚአብሔር አምየሻለሁ አላት እናታችንም ግድ ካልከኝስ ልንገርህ ስማ ከዕለታት በአንድ ቀን ማታ ሲመሽ ከቤቴ ደጃፍ ተቀምጬ ደናግል ልጆቼን አንዷን ከአንዷ ጋራ ተያይዛ እርስበርሳቸው ሲጋፉና ሲላፉ አይቼ በጣም አዝኜ ከእግዚአብሔር ጋር እኔን ያስቀመጥከኝ ይህን ልታሣየኝ ነውን ከዛሬ ወዲህ የሰጠህኝን አደራ ትቀበል ዘንድ እለምንሀለሁ ካልሆነ እነዚህ ልጆቼ ሲጠፉ ከማይ እኔ ብሞት ይሻለኛልና ነፍሴን በሞት ውሠዳት ብየ ከእግዚአብሔር ጋር እዋቀስ ጀመር ።

፲፩ በዚህን ጊዜ ወደ እኔ መጥቶ አይዞሽ አትፍሪ ጸሎትሽን ሰምቼ ፈቃድሽን ላደርግልሽ ላረጋጋሽ መጥቻለሁ አለኝ ከእሱ ጋራም ሰባት የጠቋቆሩ ገረዶችና ፯ የደነደኑ ወጣቶች ባሮች ናቸው አንዲቷ አሮጊት ናት እሱም መልሶ እነዚህ ባሮች ፈቃድሽን ይፈጽሙ ዘንድ እያንዳንዳቸውን ሰባቱን በሴቶች መነኮሳይያት ቤት ይሂዱ ዘንድ እዘዥያቸው አንዲቷ አሮጊት ግን ካንች ዘንድ ትቀመጥ አለኝ እሱ እንዳለኝ ተደረገ ስለዚህ የእግዚአብሔር ምሕረት ነው አልኩህ አንተስ እንደዚህ አትልም አለችው እሱም ይህ ከሆነ የእግዚአብሔር ምሕረት ነው አላት በዚያን ዓመት ከወንድሞችና ከእኅቶች ማኅበር መነኮሳት መቶ ሠላሳ ሰባት ሰዎች ሙተው ከዚህ ዓለም ሥቃይ ወደ እረፍት ከሐዘን ወደ ደስታ ሄዱ ጸሎታቸው እና በረከታቸው ከሁላችን ጋራ ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ ይደረግ።

፲፪ እናታችን ወለተ ጴጥሮስ እነዚያ የሞቱ እኅቶችና ወንድሞች ይድናሉ ይኰነናሉ እስኪ ንገሪን ልባችን እንዲረጋጋ እንዳይጠራጠር እነዚህ የሞቱ ሁሉ ይጸድቃሉን

ወሚመ መንፈቆሙ ይጸድቁ ወመንፈቆሙ የትሐጐሉ አውሥአቶሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎሙ አልቦ ዘይትኴነን እምኔሆሙ መኑሂ ኢእምቅድሜሆሙ ወኢእምድኅሬሆሙ ኅድጉሰ እሉ ማኅበር እለ ውስተ ሕጽንየ እለኒ ሀለዉ በ፬ መዓዝነ ዓለም እለ ይጼውዑ ስምየ ይድኅኑ ወኢይትሐጐሉ ዘኒ ዘእብለክሙ አኮ በእንተ ጽድቅየ አላ በእንተ ምሕረቱ ለእግዚአብሔር ::

፲፫ ወበውእቱ መዋዕል ተሀውከት አሐቲ እኅት እንተ ትሰመይ ፍቅርተ ክርስቶስ ብእሲቱ ለክፍለ ማርያም ወሐለየት ከመ ትሑር ኀበ ሀገራ ወስዕነ መይጦተ ልባ በምክር ወበምዕዳን ወዘፈለሰ ብእሲሃ ነገራ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ተሀውከት እስመ ውእቱ የኃዝን ወይበኪ በእንቲአሃ ወናዘዘቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎ ኢትፍራህ ወኢትኅዝን ወኢይምሰልከ ዘተሐውር ወሰሚዖ ዘንተ ወፅአ እንዘ ይትፌሣሕ ወይእተ ጊዜ ሐመት ይእቲ እኅት በጸሎተ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወአእረፈት::

## ምዕራፍ ፳፬

፩ ወእምድኅሬሁ አመ ፳ ወ ፬ ለነሐሴ ሐመት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሕማመ ጽኑዓ ወሶበ ጽንዓ ላዕሌሃ ሕማም አግሐሥዋ ኀበ ማኅደሪሆሙ ለመነኮሳት ወእንዘ ትሰክብ ህየ መጽኡ ኀቤሃ መላእክት ከመ የሐውፅዋ ነሢኦሙ አፈዋተ ጽጌ እምገነት ወሦጡ ውስተ አዕናፊሃ ወሶበ ሐወጻ ሥዕለ ክርስቶስ ረከባ እንዘ ትትፌሣሕ በመዓዛሁ ወተስእላ ወይቤላ ምንትኑ ዘያስተፌሥሐኪ ወይእቲኒ ነገረቶ በከመ አቅደምነ ወንቤ ወእምዝ ካዕበ አግኃሥዋ ወወሰድዋ ኀበ ቤተ ክርስቲያን ዘፉሬ ወአስከብዋ ውስተ ቤተ አሐቲ መንኮሳይት ወእንዘ ሀለወት ህየ ጸንዓ ላዕሌሃ ሕማም ወአልፀቀት ለመዊት::

፪ ወአኃዙ ይትመሃለሉ ስብሐተ ፍቁር በ፯ ጊዜያተ መዓልት ወአውየዉ ኵሉ ማኅበር አኃው ወአኃት ወአንገርገሩ ዲበ ምድር ወይቤ ፩ዱ እምአዕሩግ እንዘ ንትመሃለል በጊዜ ፯ ሰዓት ርኢክዋ ለሥዕለ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም





ወይስ እኩሌቶች ጻድቀው እኩሌቶቹ ይኮነናሉ ብለው እንደጠየቋት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም መልሳ እነዚህ በእኔ ስር ያሉት ማኅበር ልጆቼ ቀርቶ ከእነሱም በፊት ከእነሱም በኋላ ያሉትና ያረፉት ከመካከላቸው ማንም የሚኰነን የለም እነዚህ ብቻ ሣይሆኑ በአራቱ ማዕዘነ ዓለም ሁነው ስሜን የሚጠሩ ዝክሬን የሚዘክሩ ይድናሉ እንጅ አይጠፉም ይህንንም ያልኳችሁ ስለ ጽድቄ አይደለም የተሠጠኝ በእግዚአብሔር ቸርነት ነው እንጂ አለቻቸው::

፲፫ በዚያን ወራት የክፍለ ማርያም ባለቤት የነበረች ፍቅርተ ክርስቶስ የምትባል አንዲት መበለት ታውካ ወደ ሀገሯ ልሂድ ልሂድ የሚያሠኝ ፈተና ተነስቶባት በምክር ልቧን መመለስ ስለ አልተቻለ ከሷ ጋር መንኖ የነበረው ባለቤቷ ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንደተፈተነች ነገራት እሱ ስለ እሷ እጅግ አዝኖ ያለቅሳልና እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም የምትሄድ መስሎህ አትዘን ብላ አረጋጋችው ይህን ሰምቶ እየተደሰተ ወጥቶ ሄደ ያችም እኅት በዚያን ጊዜ በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎት ታማ አረፈች ::

## ምዕራፍ ፳፬

፩ ከዚህ በኋላ ነሐሴ ሃያ አራት ቀን እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በጣም ታመመች ሕማምም እጅግ በጸናባት ጊዜ ወደ መነኮሳት ቤት ወሰዷት እዚያ ተኝታ ሳለች መላእክት ይጉበኟት ዘንድ መዓዛው ከሽቱ ይልቅ የሚያስደስት የገነት አበባ ይዘው ወደ እሷ መጥተው በአፍንጫዋ አደረጉላት ሥዕለ ክርስቶስም ለመጠየቅ ሲመጣ በመዓዛው ተደስታ አያትና ደስ ብሎሻልና ያስደሰተሽ ምንድን ነው አላት እሷም የተደረገላትን ሳትሰውረው ነገረችው ከዚህ በኋላ ወደ ፉሬ ቤተ ክርስቲያን ወሰዷትና ወደአንዲት መነኩሲት ቤት አስገቧት እዚያ ሳለች በጣም ሕማም ጸናባት ::

፪ በስብሐተ ፍቁርና በሰባቱ ጊዜያት ጸሎት ወንዶች መነኮሳትና ሴቶች መነኮሳይያት ከመሬት ላይ እየተንከባለሉና እየጮኹ ጸሎተ ምህላ ጀመሩ ከአረጋውያን መካከል አንዱ በሰባቱ ጊዜያት ጸሎት ስናደርስ እምላክን የወለደች የቅድስት

ወለዲተ አምላክ በአምሳለ ብእሲት ኀዝንት ወሶበ ተፈጸመ ምህላ ሖርኩ ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ረከብክዋ በብሩህ ገጽ እንዘ ትትፌሣሕ ወትትኃሠይ።

፫ ወሥዕለ ክርስቶስኒ ይቤ እምድኅረ ሀለፈ ፫ ሰዓት ሐወጽክዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወእንዘ ንትናገር ክልኤነ እንተ ባሕቲትነ ትቤለኒ መጽአ ኀቤየ ዮም መልአክ አነኒ ተስእልክዋ ወዕቤ በምንት ግብር መጽአ ኀቤኪ አውሥአተኒ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤለኒ መጽአ ኀቤየ በአምሳለ ብእሲ ብሩህ ወወረደ ስጢቆ ጠፈረ ቤት ውስተ እዴሁ ማዕጠንት ወመስቀል ወእምውእቱ ማዕጠንት ወፅአ ጢሰ ዕጣን ፀዓዳ በአምሳለ በረድ ወመልአ በአፉየ ወተሰውጠ ውስተ ከርሥየ ወጼና ውእቱ ዕጣን ይሰልብ አልባበ።

፬ ወእምድኅሬሁ መጽአ ሕፃን ንኡስ ወብሩህ ገጹ ከመ ፀሐይ ወውስተ እዴሁ ያጸንዕ መስቀለ ብርሃን ወቀርበ ኀቤየ ከመ ይባርከኒ ወከላዕክዎ ገጽየ ወሰገድኩ ውስተ ምድር ወበህየኒ ረከብክዎ ወካዕበ ተመየጥኩ ድኅሬየ ወረከብክዎ በህየኒ ወተመየጥኩ ይምነ ወጽግመ ወኮነ ርኩበ በውስተ ኵሉ ወሶቤሃ ባረከኒ በኃይል አነሂ ተስእልክዎ ወእቤሎ መኑ አንተ ዘትባርከኒ እንዘ ኢይፈቅድ አነ አውሥአኒ ወይቤለኒ አነ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ወውእቱኒ ዘይእኅዝ ማዕጠንተ መልአክ ውእቱ።

፭ ወካዕበ ይቤሉ ካልአን ትቤ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መጽአት ኀቤየ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወትቤለኒ እምፈቀድኩ አንሰ አዕርፍኪ እምፃማ ዝንቱ ዓለም ባሕቱ አኅዘነኒ ብካዮሙ ዘዮም ለደቂቅኪ ወለአዋልድኪ ወበእንተዝ ኃደጉኪ ትንበሪ ሎሙ ኀዳጠ ወእምዝ ሶበ አእመረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ቀርበ ጊዜ ዕረፍታ ሐለየት ትባእ ደሴተ ሬማ ቅድስት ከመ ትትቀበር ውስቴታ ወትቤሎሙ ለአኃው አስተዳልዉ ሊተ ታንኳ ዘእበውእ ቦቱ ደሴተ ሬማ ቅድስት ውእቶሙኒ ገብሩ በከመ አዘዘቶሙ ወአመ ፳ወ፫ ለወርኃ መስከረም ተሰነዓለቶሙ ወትቤሎሙ ለአኃው ወለአኃት ናሁ ጸንዓ ላዕሌየ ሕማም ንበሩ ዝየ አንትሙ ወአነ አሐውር ሬማ እስከ ንትራከብ በፈቃደ





ድንግል እመቤታችን ሥዕል በታላቅ ሴት ተመስላ አዝና ምህላ ሲያበቃ ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በሄድኩ ጊዜ ፊቷ እንደ ፀሐይ እያበራ በጣም ስትደሰት አየኋት አለ።

፫ ሥዕለ ክርስቶስም ሶስት ሰዓት ከአለፈ በኋላ ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሄጄ ሁለታችን ብቻችንን ስንጨዋወት ዛሬ መልአክ ወደ እኔ መጣ አለችኝ እኔም መልሼ በምን መልክ ወደአንቺ መጣ ብየ ጠየኳት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም መልሳ በእጁ ማዕጣንትንና መስቀል ይዞ ፊቱ እንደ ፀሐይ እያበራ በሰው አምሳል የቤቱን ጣሪያ ሰንጥቆ ወደ እኔ መጣ ከዚያ ማዕጠንትም እንደ በረድ ነጭ የሆነ የዕጣን ጢስ ወደ እኔ መጥቶ በአፌ ሞልቶ በሆዴም ተጨመረ የዚያም እጣን መዓዛው ልቡናን ይመስጣል ።

፬ ከዚህ በኋላ ፊቱ ከጸሐይ ይልቅ የሚያበራ ትንሽ ልጅ በእጁ የብርሃን መስቀል ይዞ መጣና ይባርከኝ ዘንድ ቀረበ እኔም ወደ መሬት ተደፍቸ ፊቴን ከለከልሁት እዚያም ከተደፋሁበት መሬትም ያን ሕፃን አገኘሁትና ተነሥቸ ወደኋላ ብመለስ እሱን አገኘሁት ወደ ግራም ወደቀኝም ብመለስ በሁሉም እሱ ስለአለ በግድ ባረከኝ እኔ ሳልፈልግ በግድ የምትባርከኝ አንተ ማነህ አልኩት እሱም መልሶ እኔ የእግዝአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ ወልድ ነኝ ይህ ማእጠንት የያዘውም መልአክ ነው አለኝ ብላ ነገረችኝ አለ።

፭ ዳግመኛም ሌሎች ሰዎች እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ አምላክን የወለደች ቅድስት ድንግል እመቤታችን ወደ እኔ መጥታ ከዚህ አለም መከራና ስቃይ ባሳርፍሽ በወደድኩ ነበር ነገር ግን የወንዶች እና የሴቶች የልጆችሽ ዛሬ ያለቀሱት ለቅሶ አሳዘነኝ እንጂ ስለዚህ ጥቂት ትቆይላቸው ዘንድ ልተውሽ አለችኝ ብላ ነገረችን ያሉም አሉ ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እረፍቷ መድረሱን በተረዳች ጊዜ በውስጧ ትቀበር ዘንድ ቅድስት ወደሆነች ወደ ሬማ ደሴት የምሄድበት ታንኳ አዘጋጁልኝ አለቻቸው እነሱም

እግዚአብሔር ወበይእቲ ሰዓት ይቤላ አባ ዘሥላሴ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ናሁ ደክማ ዓብራኪየ በቀዊም ወስህከ ጕርዔየ በክላህ ወለክዋ አዕይንትየ እምጢስ ዕጣን ዘሌሊት ወዘመዓልት እምአመ ተወጥነ እስከ ይእዜ ወኃጣእኩ ዕረፍተ ወእለሂ ይሬእዩ ወይሰምዑ አስቆረሩኒ እምይእዜሰ ኮነ ጥእከለ ወይእትት እምኔነ ዝንቱ ሞት።

፮ አውሥአቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎ ቦኑ ትፈቅድ አንተ ከመ ይቁም ወይቤላ እወ እፈቅድ ወትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እመሰ ፈቀድከ ይኩን በከመ ትቤ ወሶቤሃ ቆመ በከመ አዘዘቶ ወእምዝ አዕረግዋ በታንኳ ወአብእዋ ሬማ እስመ ይእቲ ሠምረት ከመ ትሙት ህየ ወትትቀበር ውስተ መቃብረ አቡሃ ወእማ በከመ ይቤሎሙ ያዕቆብ ለደቂቁ አመ ሀሎ በብሔረ ግብጽ ቅብሩኒ ኀበ መቃብረ አበውየ ወዮሴፍኒ ይቤሎሙ ከማሁ አመ ሕዋጼ ይሔውጸክሙ እግዚአብሔር ንሥኡኒ አዕፅምትየ ምስሌክሙ ወእንበይነዝ ትቤ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሰዱኒ ሬማ ወሶበ አብጽሕዋ ህየ አብእዋ ውስተ ቤተ፩ዱ እምነ መንኮሳት።

፯ ወእምዝ ከልአቶሙ ለሰብእ ከመ ኢይባእ ኀቤሃ መኑሂ ዘእንበለ ቀሳውስት አባ ዘሚካኤል ወአባ ሥዕለ ክርስቶስ ወሀለወት ምስሌሃ ፈላሲተ ክርስቶስ ወኮነት ታነብብ በሌሊት መዝሙረ ዳዊት ወበመዓልት ወንጌለ ወእምድኅረ ኀልፈተ ፫ቱ ሰዓት ይሔውጻ ዘልፈ አባ ሥዕለ ክርስቶስ ወይናዝዛ ወበዕለተ ሐሙስ እምቅድመ ዕረፍታ በ፩ዱ ዕለት አመ ፲ወ፬ ለወርኃ ኅዳር ሐወጻ አባ ሥዕለ ክርስቶስ በከመ ልማዱ እምድኅረ ኃለፈ ፫ቱ ሰዓት ወቦአ ኀቤሃ ወነበረ ቅድሜሃ ወትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አእመርከኑ መኑ ውእቱ ዘነበረ ምስሌየ ይእዜ።





እንደአዘዘቻቸው አደረጉ መስከረም ሃያ ሦስት ቀን ለወንድሞችና ለኀቶቾ መነኩሳት እነሆ ሕመም ጸንቶብኛልና በእግዚአብሔር ፈቃድ እስክንገናኝ እኔ ወደ ሬማ ስለምሄድ እናንተ እዚሁ ተቀመጡ ብላ ተሰናበተቻቸው በዚህን ሰዓት አባ ዘሥላሴ ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እነሆ ጉልበቶቼ በመቆም ደከሙ ጉሮሮየ በመጮኽ ሻከረ፡ል ዓይኖቼ በቀንና በሌሊት በማጥነው እጣን ጢስ ፈዘዙ ከተጀመረ ጀምሮ እኔም እረፍት አጣሁ የሚያዩንና የሚሰሙን ሰዎች ተፀየፉን እራቁን ከእንግዲህ ወዲህ ይበቃናል ይህ ሞት ከኛ ይወገድ አላት።

፮ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለመሆኑ አንተ ይህ ሞት እንዲቆም ትፈልጋለህ አለችው አወ እንዲቀር እፈልጋለሁ አላት እናታችንም አንተ እንዳልክ ይሁንልህ አለችው እሷም እንዳለችው ቀረ ከዚህ በኋላ ከታንኳ ላይ አስቀምጠው ወደሬማ ወሠዷት እሷም በዚያ አርፋ በአባቷና በእናቷ መቃብር ትቀበር ዘንድ ፈልጋለች እና ያዕቆብ በግብፅ ሳለ ለልጆቹ በአባቶቼ መቃብር ቅበሩኝ እንዳለ ዮሴፍም እንደዚሁ እግዚአብሔር በምሕረት በጐበኛችሁ ጊዜ አጥንቶቼን ከእናንተ ጋር ወስዳችሁ በአባቶቼ መቃብር ቅበሩኝ እንዳለ ስለዚህ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወደ ሬማ ውሰዱኝ አለች እዚያ አድርሠው ከመነኮሳት ቤት መርጠው በአንድ መነኩሴ ቤት አስቀመጧት ።

፯ ከዚህ በኋላ ያለ ሁለት ቄሶች አባ ዘሚካኤል እና ሥዕለ ክርስቶስ በስተቀር ማንም ሰው ወደ እሷ እንዳይገባ ከለከለቻቸው ፈላሲተ ክርስቶስም ከሷ ጋራ ሁና ቀን ወንጌልን ሌሊት መዝሙረ ዳዊትን ታነብ ነበር ሦስት ሰዓት ካለፈ በኋላ አባ ሥዕለ ክርስቶስ ዘወትር እየመጣ ይጠይቃት እና ያረጋጋት ነበር ከማረፏ አስቀድሞ ከዕለታት በአንድ ቀን ዕለቱ ሐሙስ ቀኑ አሥራ አራት ወሩ ኅዳር በሆነ ጊዜ አባ ሥዕለ ክርስቶስ እንደልማዱ ሦስት ሰዓት ካለፈ በኋላ ይጠይቃት ዘንድ ወደሷ ገብቶ ከፊቷ ተቀምጦ ሳለ እናታችን ዛሬ ከእኔ ጋራ ያሉት እነማን ናቸው አውቀሀል አለችው ።

፰ አውሥአ ወይቤላ በአይቴ አአምር አነ ዳዕሙ አንቲ ንግርኒ ዘኮነ ወአውሥአቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎ መጽኡ ኀቤየ በዛቲ ሰዓት ፲ወ፬ ፼ወ፵፻ ሕፃናት ዘቤተ ልሔም እለ ቀተሎሙ ሄሮድስ ወነበሩ ምስሌየ እንዘ ይትለሃዩ ወይትዋነዩ ቅድሜየ ወሶበ መጻእከ አንተ ይእዜ ተፈልጡ እምኔየ ወሖሩ ወካዕበ በይእቲ ዕለት አስተጋብአቶሙ ለመምህር ዘሬማ አባ ዘማርያም ወለአባ ክፍለ ሰማዕት ዘጎንድ ወለኵሎሙ አኃው ወአኃት እለ ሀለው ሀየ ወአዘዘቶሙ ሶቤሃ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ያምጽኡ መጽሐፈ ሐዊ ወሕንፃ መነኮሳት ወካልአነሂ መጻሕፍተ ወትቤሎሙ አንብቡ::

፱ ወአንበቡ ኵሎ መጻሕፍተ በበአንቀፁ ኀበ ሀሎ ጽሑፍ ትእዛዝ ዘመነኮሳት ወእምድኅረ ተፈጸመ አንብቦተ መጻሕፍት ትቤሎሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ንጽሕት አነ እምደመ ኵሉ ሰብእ ወናሁ አነ አሐውር ኀበ አምላኪየ ኵሉ ዘፈቀደ ይሑር በትእዛዘ እሉ መጻሕፍት ወዘኒ ዐበየ ይዑቅ ርእሶ ወኃጢአቱ ዲበ ርእሱ ወአልቦቱ ትኅላፍ እምኔየ ወዘንተ ብሂላ አስተፋነወቶሙ ወሖሩ በበአብያቲሆሙ::

፲ ወአመ ሳኒታ ካዕበ በዕለተ ዓርብ ሐወጻ አባ ሥዕለ ክርስቶስ በከመ ልማዱ ወቦአ ኀቤሃ ወነበረ ቅድሜሃ ወትቤሎ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ስማዕ እንግርከ ዮምኒ መጽአ ኀቤየ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ይለብስ ልብሰ መንዲል ወይሜዓን ዓሣዕነ ዘወርቅ ወመጽአት ምስሌሁ እሙ ድንግል ወይእቲኒ ነበረት ቅድሜየ እንተ አንጻርየ ወውእቱኒ ነበረ እንዘ ያሰምክ ዲበ ምስካብየ ወይቤለኒ ፫ ጊዜ ዘጸመወ በዓለም የሐዩ ለዝሉፉ እስመ ኢይሬኢ ሙስና ወካዕበ ነፍሐ ውስተ ገጽየ ወባረከኒ ወእቤሎ ምንትኑ ዝ ንፍሐት ወዝ ቡራኬ አውሥአኒ ወይቤለኒ ሤምኩኪ ሊቀ ዲያቆናዊት::

፲፩ ወዘንተ ሰማዕኩ እምኔሃ ይቤ ሥዕለ ክርስቶስ ወበዕለተ ቀዳሚ ሶበ ጸንዓ ሕማም ላዕለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተጋብኡ ኵሉ ሰብእ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወገብሩ ጸሎተ ወምህላ ወኮነ በይእቲ ዕለት ዐቢይ ኃዘን ወካዕበ በይእቲ ዕለት ጊዜ ፱ቱ ሰዓት ተጋብኡ ኀቤሃ አባ ዘማርያም ወአባ ክፍለ ሰማዕት ወአባ ዘሚካኤል ወአባ ሥዕለ ክርስቶስ ወይቤልዋ እመ አዕረፈ ሙሴ ኃደጎ ህየንቴሁ ለኢያሱ ወአቀቦሙ ለእስራኤል ወኤልያስኒ ኃደጎ ለኤልሳዕ ወኵሎሙ በበዘመኖሙ ከማሆሙ ገብሩ ወአንቲኒ ንግርነ ይእዜ ዘትከውን እመ ህየንቴኪ ወተዓቅቦሙ ለማኅበርኪ::





፰ እሱም መልሶ እኔ በምን አውቃለሁ የሆነውን አንች ንገሪኝ እንጅ አላት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም አሥራ ዐራት እልፍ ከዐራት ሺ የሚሆኑ ሄሮድስ ያስገደላቸው የቤተልሔም ሕፃናት ወደ እኔ መጥተው በፊቴ ሆነው እያመሰገኑ ከእኔ ጋራ ሲጫዋወቱ ነበር አንተ ስትመጣ አሁን ከእኔ ተለይተው ሄዱ ዳግመኛ በዚያች ዕለት የሬማ መምህር አባ ዘማርያምን እና አባ ክፍለ ሰማዕት ዘጎንድን እና እዚያ ያሉትን ወንዶች እና ሴቶች መነኮሳትን ሰበሰበቻቸው እና ያን ጊዜ ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መጽሐፍ ሐዊንና ሕንፃ መነኮሳትን ሌሎችንም መጻሕፍት አንብቡ አለቻቸው ::

፱ እነሱም ስለመነኮሳት የሚናገረውን መጻሕፍት ሁሉ በየምዕራፉ በእየ አንቀጹ እያወጡ አነበቡ አንብበው ከጨረሱ በኋላ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እኔ ከነዚህ ሁሉ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ እነሆ እኔ ወደ ፈጣሪየ እሄዳለሁ የፈለገ በመጽሐፍ ትእዛዝ ይሂድ እምቢ ያለው ኃጢአቱ በራሱ ላይ እንደሆነ እኔ ስለ እነሱ መተሳሰፍ እንደሌለብኝ ይወቅ አለች ይህን ብላ ሸኘቻቸው እና በየቤታቸው ሄዱ ::

፲ በማግስቱ አባ ሥዕለ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ እንደልማዱ ወደ እሷ ገብቶ ከፊቷ ተቀምጦ ሳለ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ስማ ልንገርህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የወርቅ ጫማ አጥልቆ የአመረ ሐር ልብስ ለብሶ ወደኔ መጣ እናቱ ድንግልም ከሱ ጋራ መጥታ ከፊት ለፊት ቁጭ አለች እሱ ግን ከመቀመጫየ ጠጋ ብሎ ተቀምጦ ሦስት ጊዜ በዓለም መከራ የተቀበለና የደከመ ለዘለዓለም በሕይወት ይኖራል ጥፋትንም አያይም አለኝ ዳግመኛም በፊቴ ላይ እፍ ብሎ ባረከኝ እኔም መልሸ ይህ እስትንፋስና ይህ ቡራኬ ምንድነው ብየ ጠየቅሁት መልሶ ሊቀ ዲያቆናዊት ሾምኩሽ ሲለኝ ይህን ከሱ ሰማሁ አለች::

፲፩ ይህንን ስትል ሥዕለ ክርስቶስ ከሷ ሰማሁ አለ ቅዳሜ ዕለት በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ላይ ሕማም በጸና ጊዜ ሰው ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን ተሰብስበው ጸሎትና ምህላን ያዙ በዚያች ዕለት ታላቅ ሐዘን ሆነ ዳግመኛ በዚያች ዕለት በዘጠኝ ሰዓት አባ ዘማርያምና አባ ክፋለ ሰማዕትአባ ዘሚካኤል አባ ሥዕለ ክርስቶስ በአንድነት ወደ እሷ መጥተው ሙሴ ባረፈ ጊዜ ስለ እሱ ፋንታ እስራኤልን እንዲጠብቃቸው ኢያሱን ተክቷል ኤልያስም ባረገ ጊዜ ኤልሳዕን ተክቷል ሌሎችም ሁላቸው እንደዚሁ በየዘመናቸው ተክተዋ ል አንችም ዛሬ ስለአንች ፋንታ እናት ሁና ማኅበርሽ ልጆችሽን የምትጠብቃቸውን ንገሪን አሏት::

፲፪ አውሥአቶሙ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትቤሎሙ አንሰ ቀነይክሞሙ ብዙኃ ዓመታተ ዳግመኑ እቤሎሙ ተቀነዩ እምይእዜሰ ግዑዛነ ይኩኑ ወይንበሩ በፈቃዶሙ ወይዕቀቡ ርእሶሙ መኑ ውእቱ እኑ ወመኑ ይእቲ እኅት ዘኢመዓድክምሙ ወዘኢመሀርክምሙ አነ ወኩሎሙ ምሁራን እሙንቱ ወየአክሉ ለርእሶሙ ወባሕቱ እብለክሙ ወአማኃፅነክሙ ለኩልክሙ እኅተ ክርስቶስሃ እስመ አነ አኃድጋ ወአሐውር ወይእቲ ትትረፍ ባሕቲታ ወትከውን እንብዝተ ወአልባቲ ተስፋ ዘእንበሌየ ወትቤሎሙ ከመዝ ፫፡ጊዜ፡ወዘንተ፡ብሂላ፡ፈነወቶሙ፡ወአመረቶሙ፡በምሥጢር፡ይሚምዋ፡፡

፲፫ ወእምድኅሬሁ ፈድፈደ ጽንዓ ሕማም ላዕለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወስዕነት ተናግሮ ወዓፀወት ሞኅተ ወከልኡ ከመ ኢይባእ መኑሂ ወኮነ ኩሉ ሰብእ ይትጋብኡ ውስተ ቤተ ክርስቲያን በጊዜ ሰርክ ወበጊዜ ንዋም ወይትመሃለሉ ወይገብሩ ጸሎተ ወሶበ ኮነ መንፈቀ ሌሊት ለጸቢሐ እሑድ አመ ፲ወ፯ ለወርኃ ኅዳር ወፅአት ነፍሳ እምሥጋሃ ወአዕረፈት በሰላም እንዘ መዋዕሊሃ ፶ ዓመት እምቅድመ ምናኔ ፳ወ፬ ዓመት ወእምድኅረ ምናኔ ፳ወ፮ዓመት፡፡

፲፬ ወበይእቲ ዕለት ተተክለ ዓምደ ብርሃን ወአስተርአየ ውስተ ኩሉ ዓለም ወተጋብኡ ኩሎሙ ሰብእ እምነ ደስያት ወእምነ ኩሉ በሐውርት እስመ ይእቲ ኮነቶሙ እመ በብዙኅ ፆታ ለዘይፈቅድ ትምህርተ ትሁቦ ሲሳየ ወልብሰ ወትዴምሮ ኀበ መምህር ወበከይዋ ዐቢየ ብካየ ወለሀውዋ ዐቢየ ላሃ በከመ በከይዎ ወለሀውዎ፡ደቂቁ፡ለያዕቆብ፡ኦ፡ዘአሜሃ፡ብካይ፡ወላሀ፡ኦ፡ዘአሜሃ፡አውያት ወከላህ፡ወኢይኔጽሮ ፩ዱ ለካልኡ ወኩሉ የኃዝን ወአልቦ ዘይናዝዝ፡፡

፲፭ ወኢይትአመሩ በይእቲ ዕለት መነኮሳት ወመሃይምናን እለ ይበክዩ ብካየ እስከ ተገድፈ ቆብዖሙ እምዲበ ርእሶሙ ወእምድኅሬሁ ገነዝዋ በዓፅፍ ከመ ሥርዓተ ምንኩስና በዝማሬ ወበማኅሌት ወቀበርዋ ውስተ ዴዴ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ዘሬማ ወአንበርዋ በምድር እንበለ ሣፁን ትንብልናሃ ወሀብተ ረድኤታ የሃሉ ምስለ ፍቁራ አግናጥዮስ ወምስለ ገብራ ሐዋርያ መስቀል ወምስለ ኩሎሙ ውሉዳ ወአዋልዲሃ እለ ጽሕቁ ወአስተሐመሙ ለጽሒፈ ዝንቱ ገድል ለዓለመ ዓለም አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን ፡፡





፲፪ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም መልሳ እኔ ብዙ ዓመት ገዛኋቸው ዳግመኛ ተገዙ ትሏቸዋላችሁ ከእንግዲህ ወዲህ ከመገዛት ነፃ የወጡ ሁነው በፋቃዳቸው ተቀምጠው እራሣቸውን ይጠብቁ እኔ ያላስተማርኋቸውና ያልመከርኋቸው ከሴትም ሆነ ከወንድም ማን አለ ሁሉም እራሣቸውን የቻሉ ምሁራን ናቸው ነገር ግን እኅተ ክርስቶስን አደራ እልኳችሁ እኔ እሷን ትቸ ስለምሄድ እሷ ብቸኛ ናትና አለች እንደዚህም ብላ ሦስት ጊዜ ነገረቻቸውና በምሥጢር እሷን ይሾሚት ዘንድ አመለከተቻቸውና ሸኘቻቸው ፡፡

፲፫ ከዚህ በኋላ በሽታው በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ላይ ጸንቶ መናገር ተሳናትና የደጃፏን በር አዘጋች ማንም ሰው እንዳይገባ ከለከሉ ሰው ሁሉ በሰርክና በንዋም ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን ተሰብስበው እጅግ እየተማፀኑ ጸሎት ያደርጉ ነበር ለእሑድ አጥቢያ መንፈቀ ሌሊት በሆነ ጊዜ ኅዳር አሥራ ሰባት ቀን የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ነፍስ ከሥጋዋ ተለየች በሃምሣ ዓመቷ በሰላም አረፈች ነፍሷንም ጌታችን ተቀብሎ ወደሰማይ ዐሳረጋት ከመመነኗ አስቀድሞ ሃያ ዓራት ዓመት በዓለም ከመነነች በኋላ ሃያ ስድስት ዓመት ኖራለች መላ ዘመኗ ፶ የተባለ ይህ ነው፡፡

፲፬ እናታችን በአረፈችበት ዕለት የብርሃን ምሰሶ ከምድር እስከ ሰማይ ተተክሎ በዓለሙ ሁሉ አበራ የብርሃን ምሶሰን እያዩ በደስያት ገዳማት ያሉ ሰዎች ሁሉና በየአገሩ ያሉ ሰዎች ሁሉ ተሰብስበው መጡ እናታችን የብዙ ወገን እናት ሁናቸዋለችና ትምህርት መማር ለሚፈልግ ስንቅንና ልብስን ሰጥታ ደህና መምህር ካለበት ትምህርት ቤት አስገብታ ታስተምር ነበርና እጅግ ታላቅ ለቅሶንም አለቀሱላት የያዕቆብ ልጆች ለያዕቆብ እንደአለቀሱለት በዚያን ጊዜ ያለ ለቅሶ እንደምን ያለ ለቅሶ ነው ዐዚያን ጊዜ የነበረ ጩኸት እንደምን ያለ ጩኸት ነበረ አንዱ አንዱን አይመለከትም ሁሉ ለየራሳቸው ያለቅሳሉ እንጂ የሚያረጋጋቸውም አልነበረም ሁሉ ያዝን ነበርና፡፡

፲፭ በዚያች ዕለት መነኮሳትና ምዕመናን አይለዩም ቆባቸው ከራሳቸው እስኪወርድ ድረስ ያለቅሱ ነበርና ከዚህ በኋላ እንደምንኩስና ሥርዓት በክብር ገነዟት በዝማሬና በማኅሌት እያሸበሸቡ ቅድስት በሆነች በሬማ ቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ያለ ሳጥን በሰሌን ቀበሯት አማላጅነቷና ልመናዋ ከአባ ወልደ ሥላሴና ከተክለ ማርያም ከአካለ ወልድ ከሕዝበ ክርስቲያን ይህንንም ገድል ለመጻፍ ለማጻፍ ከተባበሩት ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይሁን ይደረግልን ይሁን ይሁን የእናታችን የቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ገድል እዚህ ተፈጸመ፡፡

## ፩ኛ ተአምር

፩ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ ዓዲ ንዌጥን ጽሒፈ ተአምር ዘገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ፦ንብልናሃ የሃሉ ምስለ ፍቁራ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፪ ስምዑ ንንግርክሙ ኃይለ ተአምር ዘኮነ እምድኅረ ዕረፍታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘርኢነ ዘይትገበር በዕለተ ተዝካራ ለለጊዜሁ እም፴ ዕለት እስከ ፍጻሜ ዓመት ከመ ወረደ በረከተ እግዚአብሔር ላዕለ ኵሉ ዘኮነ ግብረ ተዝካር ዘይትገበር ወአሜሃ ተጋብኡ ብዙኃን ሰብእ እለ አልቦሙ ትልቍ እምደሰያት፡ወእምአድባራት፡ወእመካት ወእምገዳማት ወእምኵሉ አህጉር፡፡

፫ ቦ እምኔሆሙ መምህራን ወቀሳውስት ወዲያቆናት ወመነኮሳት ምስለ ማዕጠንት ወመስቀላት ወቦ እምኔሆሙ ነዳያን ወምስኪናን ዕውራን ወሐንካሳን እስመ ስሙዕ ዜናሃ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም ወወሀብዎሙ ብዙኃ መብልዓ ወመስቴ፡በበመዓርጊሆሙ፡ወበበመጠኖሙ እስከ ጸግቡ ወአትረፉ ፡፡

፬ ወሀለወ ኀዳጥ ብትእ መጠነ ፩ዱ ኀብስት በዐቢይ ጋን ዘተርፈ እምነ ተዝካር ወተረክበ እንዘ ይፈልሕ ወይመልእ እስከ ላዕሉ ወይትከዓው ወሶበ ቀድሕዎ ኢይነትግ ወኢየሐፅፅ አላ ይፈደፍድ ለለዕለቱ ወይትረከብ ምሉዓ ወአኃትኒ እለ የአምራ ምሥጢሮ ያረምማ ወኢይትናገራ አላ ያነክራ ወይደመማ እምዕበየ ኃይላ ለእምነ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ፡፡

፭ ወእምድኅረዝ መጽአት አሐቲ እምነ አኃት እንተ ትጊጉዕ ለነቢብ ወነጸረቶ እንዘ ይፈልሕ ወከልሐት ወትቤ ነዋ ይፈልሕ ዝንቱ ብትእ ወበጊዜሃ አርመመ ወኢፈልሐ ወሶበ ቀድሐቶ እንተ ተሐብዝ አኃዘ ይኅፅፅ ወይንትግ እምነ ምልአቱ ወሐሪፅኒ ንስቲተ ፈድፈደ ከማሁ እስከ አግሐሠ እምኔሁ መሥፈርተ ብዙኃ ከመ ገብረ ኤልያስ ነቢይ በሰራጵታ ወሶበ ተናገረት ካልእት እኅት ውእቱኒ ነትገ ከማሁ ፡፡





## ፩ኛ ተአምር

፩ አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ተአምር መጽሐፍ እጀምራለሁ አማላጅነቷ ከሕዝበ ክርስቲያን ጋር ይህን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይሁን ይደረግልን ፡፡

፪ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከአረፈች በኋላ የተደረገውን የታምራቷን ኃይል ስሙ እንንገራችሁ ከሠላሳ እስከ ዓመት ፍጻሜ ያየነውን የእግዚአብሔር በረከት ለተዝካሯ በሚዘጋጅና በሚደገስ ድግስ ሁሉ ላይ እንደወረደ እንንገራችሁ ስሙ በዚያን ጊዜ መታሰቢያዋ ሲደርስ ከደስያትና ከአድባራት ከገዳማት ከአገሩ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ሰዎች ተሰበሰቡ ፡፡

፫ ከእነሱም መካከል መምህራንና መነኮሳት ቀሳውስት ዲያቆናት ከነማዕጠንታቸውና ከነ መስቀላቸው አሉ ከእነሱም መካከል የዕለት ጉርስ የሌላቸው ነዳያን የዕለት ጉርስ ያላቸው ምስኪናን እውራንና አንካሳን ነበሩ ዜና ገድሏ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ተሰምቷልና በየማዕረጋቸውና በየደረጃቸው አስቀምጠዋቸው ብዙ መብልን ብዙ መጠጥን በልተው ጠግበው እስኪያተርፉ ድረስ ሰጡዋቸው፡፡

፬ ለመታሰቢያ ከሚጋገር እንጀራ የተረፈ አንድ እንጀራ የሚሆን ሊጥ በትልቅ ጋን ውስጥ ነበርና ወደ ላይ እየፈላ እስኪፈስ ድረስ ሞልቶ እየፈሰሰ ተገኘ በሚቀዱ ጊዜ አይጐልም በየቀኑ እየጨመረና እየበዛ ሞልቶ ይገኝ ነበር እንጂ ምሥጢሩን የሚያውቁ እኅቶችም ፈጽመው አልተናገሩም ከእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የታምራቷ ኃይል የተነሳ እጅግ ያደንቃሉ እንጂ ፡፡

፭ ከዚህ በኋላ አንዲት ለመናገር የምትቸኩል እኅት ይህ ሊጥ ይፈላል ብላ ጮኻ ተናገረች በዚያን ጊዜ መፍላቱን አቆመ ጋጋሪዋ በምትቀዳ ጊዜ እያደር እየጐደለ ሄደ እንደዚሁ ጥቂት ዱቄት ነበረች በብዙ እንቅብ እየወሰዱ ሌላ ቦታ እስኪያስቀምጡ ድረስ እጅግ በዛ ኤልያስ በሰራጵታ እንደ አደረገ ሌላም እኅት በተናገረች ጊዜ እንደዚያ ቆመ፡፡

፮ እስመ ዘይጊጉዕ ለነቢብ ይሰድድ በረከተ እግዚአብሔር እምኔሁ በእንተ ዝንቱ ይቤ ሐዋርያ ወይኩን ኩሉ ብእሲ ፍጡነ ለሰሚዕ ወጒንዱየ ለነቢብ ወአረጋዊ መንፈሳዊ ይቤ ወዘይጊጉዕ ለነቢብ ይርኅቆ ፈጣሪሁ ወዓዲ ይቤሉ ጸረ ዕፅ ንስቲት ፈድፈደት ወአከለት ለሐቢዘ ኅብስት ብዙኅ እምሴት እስከ ጽባሕ ወካልእሰ በረከት ዘኮነ ላዕለ ኅብስት ወፀብሐ ወስቴ ሰዋ ኢይትአመር ኍላቌሁ እንዳዒ እግዚአብሔር የአምር ወዝንቱ ኩሉ ኮነ በኃይለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎታ ወበረከታ የሀሉ ምስሌ ገበራ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፪ኛ ተአምር

፩ ተአምር ዘገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎታ ወበረከታ የሃሉ ምስለ ፍቁራ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፪ ወሀሎ ፩ዱ መነኮስ በሀገረ ወይብና ዘስሙ ዓፅቀ ማርያም ዐቃቤ መዛግብት ዘእምዕራፈ እግዝትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወውእቱ መነኮስ ሐመ ሕማመ ጽኑዓ ወደወየ ዐቢየ ደዌ እስከ ኮነ መፃጉዓ ወኢይክል ይቁም በእገሪሁ አላ ይሰክብ ከመ መፃጉዕ ወስዕነ ዐቃብያነ ሥራይ ፈውሶቶ ወእምዝ ሐለየ በልቡ ወይቤ ለእመ ሖርኩ ፃና እምተፈወስኩ ወእምረከብኩ ጥዒና እምዝንቱ ሕማም ጽኑዕ በረድኤተ ቅዱስ ቂርቆስ ሰማዕት ወሶቤሃ ሰአሎሙ ለሰብኡ ወይቤሎሙ ሰዱኒ ፃና ለእመ እረክብ ፈውሰ ወጥዒና ወለእመ ሞትኩ እትቀበር በህየ ወይቤልዎ ኦሆ ይኩን ፈቃድከ።

፫ ወእምዝ ነሥእዎ ወወሰድዎ ወአብእዎ ፃና ወነበረ ጕንዱየ መዋዕለ ወኢረከበ ምንተኒ ፈውሰ ወጥዒና አላ ይፈደፍድ ላዕሌሁ ሕማም እምዕለት ለዕለት ወአልፀቀ ለመዊት ወቀብፀ ተስፋ ሐይው ወእምህየኒ ካዕበ ተሀውከ ወይቤ ሰዱኒ ቤትየ አንሰ አእመርኩ እምይእዜሰ ኢይትፌወስ ለእመ ሞትኩ በዝየ ወተቀበርኩ የዓፅበክሙ ለገቢረ ተዝካር እመሰ ሞትኩ ወተቀበርኩ በምዕራፈ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ይቀልል ለክሙ ኩሉ ግብር ።

፬ ወሰሚያሙ ቃሎ ይቤልዎ ኦሆ ወጾርዎ ወአውረድዎ ወአብጽሕዎ ውስተ ባሕር ወፀዓንዎ በታንኳ ወሀለዉ ምስሌሁ ፪ቱ ሰብእ እለ ይሔድፉ ወበጺሆሙ አንጸረ ደሴተ ሬማ ተዘከረ





፮ ለመናገር የሚቸኩል ሰው የእግዚአብሔር በረከት ያሳጣል ሐዋርያው ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገር የዘገየ ይሁን እንደአለ አረጋዊ መንፈሳዊ ለመናገር የሚቸኩል ሰውን ፈጣሪው ይርቀዋል እንደ አለ እንደገናም ጥቂት እንጨት በርከታ ብዙ ሆና ከማታ እስከ ጥዋት ብዙ እንጀራ ጋገረች ሌላም በእንጀራ ቡወጥ በጠላ ላይ ያለው ተነግሮ አይዘለቅም የታምራቷንም ብዛት እግዚአብሐር ያውቃል እንጂ በሰው ዘንድ ቁጥሩም አይታወቅም ይህ ሁሉ የተደረገ በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የታምራቷ ኀይል ነው ጸሎቷና በረከቷ ከህዝበ ክርስቲያን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን።

፪ኛ ተአምር

፩ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ያደረገችው ተአምር ይህ ነው ጸሎቷና በረከቷ ከሁላችን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይሁን ይደረግልን።

፪ ወይብና በሚባል አገር ስሙ አፅቀ ማርያም የሚባል አምላክን የወለደች የእመቤታችን ማረፊያ በምትባል ቤተ ክርስቲያን እቃ ጠባቂ የሆነ አንድ መነኩሴ ነበር ያም መነኩሴ በእግሮቹ መቆም አቅቶት እንደ ሽባ እስኪተኛ ድረስ በፀና በሽታ ታመመ ባለ መድኃኒቶችም ማዳን አቃታቸው በልቡ ወደ ጣና ብሄድ በቅዱስ ቂርቆስ ረዳትነት ከዚህ ከከፋ በሽታ እድናለሁ ከሞትኩም ከዚያው ልቀበር በማለት ወደ ጣና ውሰዱኝ አለ።

፫ ከዚህ በኋላ ተሸክመው ወስደው ጣና አስቀመጡት ጤና ሳያገኝብዙ ጊዜ እዚያ ተቀመጠ ዕለት ዕለትም ሕማሙ እየበዛበትና እየፀናበት ስለ ሄደ የመዳን ተስፋ ቆረጠ ለሞትም የሚያደርስ ጽኑ ደዌ ሆነበት በዚያም ዳግመኛ ተጨናንቀና እኔ እንዳልድን አውቄያለ ሁና በዚህ ሙቼ እዚሁ ብቀበር ተዝካሬን ለማውጣት ያስቸግራቸዋልና አምላክን በወለደች በእመቤታችን ማረፊያ ሙቼ ብቀር እዚያ ይቀላቸኋልና ወደ ቤቴ ውሰዱኝ አላቸው።

፬ እነሱም ቃሉን ተቀብለው እሺ ብለው ተሸክመው ወስደው ከባሕር አድርሰው በታንኳ ጭነውት ሄደው ከሬማ አንፃር ሲደርሱ ታንኳዋን የሚነዱ ሁለት ሰዎች ነበሩ ያ ታማሚ ሰው የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ

ውእቱ መነኮስ ድውይ ከመቦ ህየ መቃብሪሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወመጽአ ላዕሌሁ ሕሊና ዘይብል ለእመ ሖርከ ወተማኅፀንከ በመቃብሪሃ ለወለተ ጴጥሮስ ተሐዩ ምደዌከ ወትትፌወስ እምሕማምከ ወእንበይነዝ ሰአሎሙ ለኖትያት ወይቤሎሙ እስእለክሙ ብቁዑኒ ወአብጽሑኒ ሬማ ከመ እስዓም መቃብሪሃ ለእምየ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ::

፫ ወይቤልዎ ኦሆ ወእምዝ አርሰዩ ታንኳሆሙ ኀበ ጽንፈ ደሴት ወነሥእዎ ሎቱ እሉ ኖትያት ወጾርዎ በመታክፍቲሆሙ ወአብጽሕዎ ኀበ መቃብሪሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወአውረድዎ ወተግሕሡ እምኔሁ ወተርፈ ባሕቲቱ ውእቱ ድውይ ወሰዓመ መቃብሪሃ ወአንገርገረ ዲቤሃ ወአኃዘ ይስአላ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በጥቡዕ ልብ ወበጽኑዕ ሃይማኖት እንዘ ይብል ኦ እምየ ርድእኒ ወተሣሃልኒ አንሰ አአምን ወእትአመን ለእመ ኮንኪ አንቲ ጻድቅተ ትክሊ ፈውሶትየ ወይሰምዕ:እግዚአብሔር:ስእለተኪ ዘሰአልኪዮ በእንቲአየ በከመ ይቤ ሐዋርያ ጸሎተ ጻድቅ ትክል ወታሠልጥ ወእንዘ ከመዝ ይብል ጐንደየ ህየ ነዋኃ ሰዓተ::

፬ ወሶቤሃ ተወክፈት ጸሎቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወፈወሰቶ ፍጡነ ወኮነ ከመ ዘኢለከፎ ሕማም ግሙራ ተንሥአ ወቆመ በእገሪሁ ወመጽኡ እሉ ኖትያት ከመ ይጹርዎ እስመ ኢያእመሩ ከመ ጥዕየ ወተፈወሰ እምሕማሙ ወለሊሁሰ ይቤሎሙ ኢትጹሩኒ እምይእዜሰ አንሰ አሐውር በእገርየ እስመ ፈወሰተኒ እምየ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሰሚያሙ ቃሎ አንከሩ ወይእተ ጊዜ ወረደ ውስተ ባሕር እንዘ የሐውር በእገሪሁ ወተፅዕነ ላዕለ ታንኳ ወበጽሐ ማዕዶተ ባሕር ወእምህየ ሖረ ፍኖቶ እንዘይጸውር ጽፍነተ ዘምሉዕ ውስቴቱ እኽለ ከመ ብእሲ መፃጉዕ ዘፆረ ዓራቶ::

፭ ወአተወ ቤቶ እንዘ ይሴብሖ ለእግዚአብሔር ዘገብረ መንክረ በእንተ ስማ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወውእቱ ሀሎ ሕያው እስከ ይእዜ ወይከውን ላቲ ስምዓ ወይዜኑ ለኵሉ ሰብእ ተአምራቲሃ ወመንክራቲሃ እምጥንቱ እስከ ተፍጻሜቱ እስመ ይእቲ ትሰምያ ለዘሰአላ ወታድኅኖ ለዘይትዌከላ ትንብልናሃ ጣዐብተ ረድኤታ የሃሉ ምስለ ፍቁራ ለዓለመ ዓለም አሜን::





መቃብር እዚያ እንደ አለ አሰበና በልቡናው ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሄደህ ብትሳልም ከበሽታህ ትድናለህ የሚል ሐሳብ መጣበት ስለዚህ እነዚያን ቀዛፊዎች እለምናችኋለሁ አዝናችሁልኝ የእናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ መቃብር እሳለም ዘንድ እለምናችኋለሁ አላቸው::

፫ እነሱም እሽ ብለው ታንኳቸውን ወደ ደሴት አስጠግተው እነዚያ ቀዛፊዎች በትከሻቸው ተሸከመውት ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተጴጥሮስ መቃብር አድርሰው አወረዱትና ጸሎት እስኪያደርስ ድረስ ዘወር አሉ ያም ታማሚ ብቻውን በመቃብር ላይ ወድቆ እናታችንን በጣም በጸና ሃይማኖት ሁኖ እናቴ ሆይ ራርተሽ ይቅር በይኝ እኔን ማዳን እንደሚቻልሽና ስለ እኔ የለመንሽውን እግዚአብሐር እንደ ሚሰማሽ ጻድቅም እንደሆንሽ እኔ አምናለሁ አለ ሐዋርያው የጻድቅ ጸሎት እጂግ ኀይልን ታደርጋለች እንዳለ እንደዚህ እየጸለየ ብዙ ሰዓት ዘገየ::

፬ በዚያን ጊዜ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎቱን ተቀብላው ፈጥና ፈወሰችውና ምንም እንዳልታመመ ሆኖ ተነሥቶ በግሮቹ ቆመ እነዛ ቀዛፊዎች ከበሽታ እንደተፈወሰ ስለ አልአዩ ይሸከሙት ዘንድ መጡ እሱም አትሸከሙኝ ከእንግዲህ ወዲህ እኔ እራሴ በግሬ እሄዳለሁ እናቴ ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አድናኘአለችና አለ እነሱም አይተው አደነቁ በዚያን ጊዜ በእግሮቹ እየሄደ ከባሕር ደርሶ በታንኳ ላይ ተጫነና ከባሕር ማዶ ደርሶ ወርዶ በእግሩ እሕል የሞላበት አኩፋዳ ተሸክሞ ሄደ መፃጉዕ አልጋውን ተሸክሞ እንደሄደ::

፭ ስለ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ስም ብሎ ድንቅ ሥራ የሠራለት እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ ቤቱ በደህና ገባ እሱም ይህ መጽሐፍ እስኪጻፍ ድረስ ነበር ለእርሷም እየመሰከረና ታምራቷን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ለሰው ሁሉ ሲመሠክር ኖረ እሷ የለመኗትን ትሰማለች የአመነባትን ታድነዋለች የረዳተንቷ ሃብትና አማላጅነቷ ከሁላችን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ ይሁን ይደረግልን ::

## ፫ኛ ተአምር

፩ ተአምር ዘገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትንብልናሃ የሃሉ ምስለ ፍቁራ ለዓለመ ዓለም::

፪ ወሀሎ ፩ ብእሲ ውስተ አሐቲ ሀገር እምአህጉረ ትግሬ እንተ ስማ ጸለምት ወኮነ ውእቱ ብእሲ ይሁቦሙ አሥራተ እክል ለመነኮሳት ዘዋልድባ ወእሙንቱሂ ይሔውጽዎ ወትረ በመዋዕለ ሕዋጼ ከመ ሥርዓተ ገዳም ወእንዘ ሀለዉ በዘከመዝ ግብር ውእቱሂ ወእሙንቱሂ መጽአ አንበጣ ውስተ ኵሉ ብሔር ወበልዓ ኵሎ እክለ ዘውስተ ገራህት ወኢያትረፈ ምንተኒ ኢእክለ ወኢሣዕረ::

፫ ወበውእቱ መዋዕል ኮነ ረኃብ ዓቢይ ውስተ ኵሉ ብሔር ወሞቱ ብዙኃን ሰብእ በረኃብ ወእለ ተርፉ ተሰዱ ወይእተ አሚረ ሶበ ሐወጽዎ እሉ መነኮሳት ከመ ልማዶሙ ረከብዎ እንዘ ይቴክዝ ወየሐዝን በእንተ እክሉ ዘገራህት እስመ ዓገቶ አንበጣ እምለፌ ወእምለፌ ወናዘዝዎ እሉ መነኮሳት ወይቤልዎ ኢትኅዝን ለእመሰማዕከ ምክረነ ወተወከፍከ ቃለነ ይትዓቀብ ለከ ገራኅተ እክልከ ወይድኅን እምአንበጣ::

፬ አውሥእሙ ወይቤሎሙ እስኩ ንግሩኒ ኦ አበውየ መነኮሳት አንሰ እገብር ኵሎ ግብረ ዘትኤዝዙኒ ወኢይትዓደው እምቃልክሙ አምክርዎ ወይቤልዎ ሀብ ብፅዓተ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ገራኅተ እክልከ ወግበር ተዝከራ ወተአመን በጸሎታ ወግድፍ ሕሊናከ ላዕሌሃ ወይእቲ ተዐቅብ ለከ ገራኅተከ ወትከልእ ለአንበጣ ከመ ኢይቅረብ ወኢይብላዕ ምንተኒ እምእክልከ ወይቤሎሙ ውእቱ ብእሲ ኦሆ እገብር ኵሎ ዘትኤዝዙኒ እስመ ዓደመኒ ቃልክሙ ወይእተ ጊዜ በጽዓ ብፅዓተ በቅድሜሆሙ ከመ ይግበር ተዝካራ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወፈለጠ ላቲ ፩ደ ገራኅተ እምገራኅቱ ወሰመዮ ገራተ ወለተ ጴጥሮስ::

፭ ወእምድኅሬሁ ሖሩ እሉ መነኮሳት ውስተ ገዳሞሙ ወነበረ ውእቱ ብእሲ እንዘ ይትአመን በጸሎታ ወይትዌከል በረድኤታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወኢይናፍቅ ወኢምንተኒ ወለእመ መጽአ አንበጣ ኢይወፅእ እምቤቱ ወኢየሐውር ኀበ ገራኅቱ ወእምይእቲ ዕለት እንተ በፅዓ ባቲ ብፅዓተ ኢቀርበ አንበጣ ውስተ ገራኅቱ አላ ይሰርር ወየኃልፍ እንተ ላዕሉ እስመ ሰወሮ መንጦላዕተ ረድኤታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት





## ፫ኛ ተአምር

፩ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የአደረገችው ታምር ይህ ነው ጸሎቷና በረከቷ ከሁላችን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ ይሁን ይደረግልን

፪ ከትግራይ ክፍለ ሀገር ውስጥ ልዩ ስሟ ጸለምት ከምትባል ቦታ የሚኖር አንድ ሰው ነበር ያም ሰው ለዋልድባ መነኮሳት በየጊዜው አስራት ይሰጥ ነበር እነሱም እንደ ገዳሙ ሥርዓትና ደንብ ዘወትር እየሄዱ ይጐበኙት ነበር እሱና እነሱ በዚህ ተፋቅረው ሳሉ በአገሩ ሁሉ አንበጣ መጣና በእርሻ ያለውን እህል ምንም ሳያስቀር ሳርም ጨምሮ በላ::

፫ በዚያን ዘመን በአገሩ ታላቅ ረሀብ ሆኖ ብዙ ሰው በረሀብ ሞተ ከሞት የተረፉትም ተሰደዱ በዚያን ጊዜ በጉበኙት ጊዜ በእርሻው ውስጥ ስላለው እህል በጣም ሲያዝን አገኙትና አንበጣ በግራም በቀኝም እህሉን ስለከበበው እነዚያም መነኮሳት ምንም አትዘን የእኛንም ምክር ከተቀበልክና ከሰማህ የአንተ እርሻ ተጠብቆልህ ከአንበጣ ይድንልሀል አሉት::

፬ እሱም መልሶ አባቶቼ መነኮሳት እስኪ ንገሩኝ ምክራችሁን እፈጽማለሁ ከቃላችሁም አልተላለፍም አላቸው እነሱም ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በእርሻህ ከአለ እህል ብፅአት ስጣት ሀሳብህን በእሷ ላይ ጥለህ በጸሎቷ ተማምነህ ዝክሯን ዘክር እሷ እርሻህን ትጠብቅልሃለችና አንበጣም ቀርቦ እንዳይበላብህ ትከለክልላሃለችና አሉት ያም ሰው ቃላችሁ ተስማምቶኛልና ያላችሁኝን ሁሉ አደርጋለሁ ብሎ በዚያን ጊዜውኑ በእርሱ ፊት የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ዝክሯን ይዘክር ዘንድ ለእሷም ለብቻ ከእርሻዎቹ መካከል አንዱን እርሻ ለይቶ የቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ነው ብሎ ብፅአት ገባ::

፭ ከዚህ በኋላ እነዚያ መነኮሳት ወደ ገዳማቸው ሄዱ ከዚህ በኋላ ያ ሰው በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ረድኤቷ ታምኖ ምንም ሳይጠራጠር አንበጣ ቢመጣ ከቤቱ ወጥቶ ወደ እርሻ ሳይሄድ ቀረ እሱ ብፅአት ከገባበት ቀን ጀምሮ አንበጣ ወደ እርሻው ፈጽሞ አልቀረበም በእህሉ በላይ ከፍ ብሎ እየበረረ ያልፍ ነበር እንጂ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የረዳትነቷ መጋረጃ ጋርዶታልና አንበጣውም በአጠገቡና በአገር በአሉት ሰዎች እርሻ ላይ እየወረደ

ወሎተ ጴጥሮስ ወይወርድ ውስተ ገራኅቶሙ ለሰብአ ሀገር እለ ሀለው ጥቃሁ ለውእቱ ብእሲ ወይበልዕ እክሎሙ እስከ ወድአ ወፈጸመ ወእሙንቱሂ ይጸምዉ ወያንሶስዉ ማዕከለ ገራኅቶሙ ወይኬልሑ ወይመስሎሙ ዘየዐቅቡ እክሎሙ ወይከልእዎ ለአንበጣ ወኢተክህሎሙ::

፯ ወአልቦ ዘአረረ መኑሂ እክለ እምኵሉ ሰብአ ሀገር በውእቱ ዘመን ዘእንበለ ዝኩ ብእሲ ዘተአመነ በጸሎታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወውእቱ ዓረረ ባሕቲቱ እክሎ ወወጠነ ይግበር ተዝካራ ለእምነ ቅደስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለለወርኀ ወበዕለትሰ ዘአዕረፈት ቦቱ አመ ፲ወ፯ ለወርኃ ኅዳር ያስተጋብኦሙ ለነዳያን ወለምስኪናን ወያረፍቆሙ ውስተ ቤቱ ወይጠብሕ ሎሙ በግዓ ወይሁቦሙ መብልዓ ወመስቴ ወያጸግቦሙ ወያስተፌሥሖሙ:: ወእም አሜሃ ኮነ ውእቱ ብእሲ ያፈቅራ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወይገብር ተዝካራ ኵሎ አሚረ ወኢያጸርዕ እምአፉሁ ተዘክሮ ስማ ትንብልናሃ የሃሉ ምስለ ገብራ ለዓለመ ዓለም አሜን::

፴ ኛ ተአምር

፩ ተአምር ዘገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎታ ወበረከታ የሃሉ ምስለ ፍቁራ ለዓለመ ዓለ::

፪ ወሀለወት አሐቲ ብእሲት ውስተ ብሔረ ደቅ እንተ ታፈቅራ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትገብር ተዝካራ ወይእቲ ብእሲት ሶበ ሐመ ወልዳ ሕፃን ንዑስ ሕማመ ጽኑዓ እስከ አልፀቀ ለመዊት ተከዘት ፈድፋደ ወኃጥአት ዘትገብር ወእምዝ አስተጋብአት ሕሊናሃ ወሰአለት ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በጥቡዕ ልብ ወበጽኑዕ ሃይማኖት ወበፅዓት ብፅዓተ እንዘ ትብል ኦ እምየ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለእመ ናዘዝክኒ እምኃዘንየ ወለእመ ፈወስኪዮ ለዝንቱ ወልድየ እምሕማሙ ወአድኃንኪዮ እሞት አነ እከውነኪ አመተ ወእገብር ተዝከረኪ ለለዓመት አምጣነ ክሂሎትየ::

፫ ወእምዝ ሶበ ርእየት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጽንዓ ሃይማኖታ ለይእቲ ብእሲት ወብዝኃ ኃዘና ወትካዘ ልባ ተራኅርኃት ላዕሌሃ ወተወክፈት ጸሎታ ወፈወሰቶ ለወልዳ እምሕማሙ ወይእቲ አኃዘት ትግበር ተዝካረ በዓላ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በዐቢይ ፍሥሐ እንዘ ተአኵት ስነ





እህላቸውን እስኪፈጽም ድረስ በላባቸው እህሎቻቸውን የሚያዱኑት እየመሰላቸው በየእርሻቸው ውስጥ እየተሯሯጡና እየጮኹ ቢያባርሩለማስወገድ አልቻላቸውም::

፯ በዚያን ዘመን በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎት ከአመነ ከዚህ ሰው በስተቀር ከአገር ሰዎች አዝመራ ያገኘ ሰው አልነበረም እሱም ብቻውን አዝመራውን ሰብስቦ የእናታችን ዝክር በየወሩ መዘከር ጀመረ ያረፈችበት ህዳር ፲፯ ቀን ግን ደግሶ ነዳያን ምስኪናንን ጠርቶ ከቤቱ አስቀምጦ በግ እያረደላቸው የሚበሉትንና የሚጠጡትን እየሰጣቸው እያጠገባቸው ያስደስታቸው ነበር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያሰው እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስን እጅግ ወዶ ዝክሯን እየዘከረና በአፉም ስሟን መጥራት ሳያቋርጥ ኖረ የእናታችን ልመናዋ ከሁላችን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ ይሁን ይደረግልን::

፴ኛ ተአምር

፩ የእናታችን ቅጽስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተአምር ይህን ነው ጸሎቷና በረከቷ ከሁላችን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይሁንልን::

፪ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን የምትወድና ዝክሯን የምትዘክር በደቅ ሀገር የምትኖር አንዲት ሴት ነበረች ያችም ሴት ትንሽ ልጇ በጸና ታሞ እስከ ሞት በደረሰ ጊዜ እጅግ አዝና የምታደርገው ግራ ገባት ከዚህ በኋላ ህሊናዋን ሰብስባ በፍጹም እምነትና በጸና ልቡና ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ለምና ከሐዘኔ ከአረጋጋሽኝ ይህን ልጄን ከበሽታ አድነሽ እንዳይሞት ብታደርጊ አገልጋይሽ ሆኜ በየዓመቱ ዝክርሽን እዘክራለሁ ብላ ብፅአት አደረገች ::

፫ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም የዚያችን ሴት የሃይማኖቷን ጽናትና ከልብ የምታዝነውን የሀዘኗን ብዛት በአየች ጊዜ ራርታላት ጸሎቷን ተቀብላ ልጁን ከሕማም ፈወሰችላት እሷም የእናታችን ዝክር በደስታ ከምስጋና ጋር ስትዘክር ኖረች ታላቅ ተአምር አድርጋ ልጇን ከሞት አድናላታለችና እንደዚህ እያደረገች ስትኖር የቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በዓል በደረሰ ጊዜ ከዓመታት መካከል በአንደኛው ዓመት ለበዓሏ አንድ እንሥራ ጠላ

ጊሩታ ለእምነ እስመ ገብረት ላቲ ዐቢየ ተአምረ ወአሐየወቶ ለወልዳ እሞት ወእንዘ ከመዝ ትገብር ይእቲ ብእሲት ሶበ ዐልፀቀ ወቀርበ ዕለተ በዓላ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በ፩ዱ ዓመት እምዓመታት አንበረት በውሣጤ ቤታ ፩ደ ቀሱተ ባሕቲቶ ዘምሉእ ውስቴቱ ሰዋ ወአልቦ ካልእ ዘእንበሌሁ ወሐለየት ተሀብ ኪያሁ ለነዳያን በእንተ ስማ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወበይእቲ ዕለት።

፬ ካዕበ መጽአ መምህር ዘዳጋ እምከተማ እምድኅረ ጕንዱይ መዋዕል ወተዓንገደ ቅሩበ መንገሌሃ ወቦአ ውስተ ኀረቤታ እስመ መለኪሃ ውእቱ ለይእቲ ሀገር ወሖረት ይእቲ ብእሲት ወተአምኅቶ ወእምድኅረዝ ተመይጠት ውስተ ቤታ ወአኃዘት ትተክዝ በዐቢይ አስተሐምሞ እስመ አልባቲ ሰዋ ዘታቄርብ ሎቱ ዘእንበለ ፩ዱ ቀሱት ዘአንበረት ለተዝካረ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወጐንደየት ነዋኃ ሰአተ እንዘ ታስተዋፅዕ ምክረ እምሕሊናሃ ዘይረትዕ ላቲ ለገቢር እም፪ቱ ነገር እምውሂብ ለመምህር ወእምውሂብ ለነዳያን በእንተ ስማ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ።

፭ ወእምዝ ሐለየት እንዘ ትብል ለእመ ወሀብኩ ዘንተ ለነዳያን ወከላእክዎ ለመምህር የሐዝን ላዕሌየ መምህር ወከላእክዎሙ ለነዳያን ተኃዝን ላዕሌየ እምየ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እስመ አፅራዕኩ ተዝካራ ወሰዓርኩ ብፅዓተ ዘበፃዕኩ ላቲ ወኃጥአት ዘተኃሪ እምእሉ ፪ቱ ግብር ወሶበ ተፃብዑ ወተቃተሉ ፪ ሕሊናት በውስተ ልባ ኀየለ ዝኩ ሕሊና ዘይብል ሀቢ ለመምህር በእንተ ፪ ግብር ፩ በእንተ እግዚእናሁ ወ፩ በእንተ ከዊኖቱ ነግደ።

፮ ወእምዝ ጸውዓታ ለአመታ ወአዘዘታ ከመ ታምጽእ ወታውፅኦ ለውእቱ ሰዋ እምውሣጤ ቤታ ወትሰድ ለመምህር ወሶበ ቦአት ይእቲ አመት ረከበት ፪ ቀሰታተ ዘምሉእ ውስቴቶን ሰዋ ወወፅአት ይእቲ አመት ወተመይጠት ኀበ እግዝእታ ወትቤላ አየኑ ቀሱተ አምጽእ አዘዝክኒ እም፪ቱ ቀሱታት ወትቤላ እግዝእታ እምአይቴ መጽአ ካልእ አኮኑ አንበርኩ ፩ደ ቀሱተ ዘእምልብኪኑ ትብሊ ዘንተ ወሚመ ትሣለቅኒኑ አንቲ ወትቤላ ይእቲ አመት አማንየ እብል አንሰ ወኢይሣለቀኪ። አዝዝኒ አምጽእ ፩ደ ቀሱተ እም፪ሆን ዘትፈቅዲ አንቲ ወተንሥአት ሶቤሃ ይእቲ በዓልተ ቤት እንዘ ትትመዓዕ ወቦአት ውሣጤ ቤታ ወረከበት ፪ ቀሱታተ በከመ ትቤ ይእቲ አመት ወሶቤሃ አንከረት ወተደመት እምዕበየ ኃይላ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በእንተ ዘገብረት ላቲ ዓቢየ ተአምረ ወናዘዘታ እምኃዘን።





አስቀምጣ ሳለች ያለሱ ሌላ ስለአልነበረ በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ስም ለነዳያን ትሰጥ ዘንድ አዘጋጅታለችና ።

፬ ዳግመኛም በዚያች እለት የዳጋ መምህር ከተማ ስለቆየ ከከተማ መጥቶ ከቤቷ አጠገብ በነበረ ጐረቤቷ አረፈ ለዚያች አገር ገዥ ነውና ያችም ሴት ሂዳ እጅ ነሳችውና ወደ ቤቷ ተመልሳ ያለ አንድ እንስራ ሌላ ጠላ ስለሌላት እጅግ አዘነች ይህንን ለእናታችን ዝክር ያዘጋጀችውን ለመምህሩ ልስጠው ወይስ በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ስም ለነዳያን ልስጥ ምን ይሻለኛል እያለች በልቡናዋ ስታመነታ እረጅም ሰዓት ቆየች።

፭ ከዚህ በኋላ ይህንን ጠላ ለነዳያን ሰጥቼ ለመምህር ብከለክለው መምህሩ በእኔ ያዝናል ለመምህሩ ሰጥቼ ነዳያንን ብከለክላቸው እናቴ ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ታዝንብኛለች ይህ ብፃት የገባሁላት ዝክሯን ቃሌን ሽሬ አስታጉየባታለሁና እያለች ከነዚህ ከሁለቱ የምታደርገውን አጥታ በልቧ ውስጥ ካሉት ከሁለቱ ሐሳቦች ስለ ሁለት ነገር ለመምህር ስጭኝ አንዱ ስለገዥነቱ አንዱ ስለ እንግድነቱ የሚል ሐሳብ አሸነፈ።

፮ ከዚህ በኋላ ያን ጠላ ከቤቷ አስወጥታ ለመምህሩ ትሰድ ዘንድ ገረዷን ጠርታ አዘዘቻት ሠራተኛዋም ወደ ቤት በገባች ጊዜ ጠላ የያዙ ሁለት እንስራዎች አግኝታ ተመልሳ ወጥታ እመቤቷን ከሁለቱ እንስራዎች የትኛውን እንዳመጣ አዘዝሽኝ አለቻት እመቤቷም ሁለተኛው እንስራ ከወዴት መጣ ያኖርኩት አንድ ነው ይህ የምትናገሪው ነገር ከልብሽ ነው ወይስ ትሳለቂብኛለሽ አለቻት ያችም ሠራተኛ እውነት እኔ አልሳለቅብሽም ከሁለቱ የምትፈልጊውን አንዱን አመጣልሽ ዘንድ እዘዥኝ አለቻት ባለቤቷም ያን ጊዜ እየተቆጣች ተነስታ ወደ ቤቷ ገብታ ያች ሠራተኛ እንደነገረቻት ሙሉ ሙሉ ጠላ ያዙ ሁለት እንሥራዎች አገኘች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከአደረገችላት ታላቅ ታምር የተነሣ እጅግ አድንቃ ከሐዘኗ ተረጋጋች።

፯ ወነሥአት ፩ደ ቀሱተ ሰዋ ወወሀበት ለመምህር ወ፩ደ ወሀበት ለነዳያን በእንተ ስማ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ርኢክሙኑ ዕበየ ኃይላ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘገብረት ዘንተ ተአምረ ዘኢኮነ እምቅድመዝ ኢይከውን እምድኅረዝ አውለደት እምነ ቀሱት ዘምስለ ሰዋ በከመ፡ወልደት ሔዋን እምገቦሁ ለአዳም ዘምስለ ነፍስ ወሥጋ እስፍንተ ንዜኑ ተአምራቲሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎታ ወበረከታ የሃሉ ምዕለ ፍቁራ ለዓለመ ዓለም አሜን::

፹ ተአምር

፩ ተአምር ዘገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትንብልናሃ የሃሉ ምስለ ገብራ ለዓለመ:ዓለምአሜን::

፪:ወመጽአት:አሐቲ:ብእሲት እምርኁቅ ብሔር እንዘ ትጸውር ማኅቶተ ስምዕ ከመ ተሀብ አምኃ ለቤተ ክርስቲያን በእንተ ስማ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በዕለተ በዓላ አመ ፲ወ፯ ለወርኃ ኅዳር እንዘ ተሐውር ውስተ ፍኖት አዕረፈት ታሕተ ጽላሎተ ዕፅ እምድካመ ፍኖት ወእምዋዕየ መዓልት::

፫ ወረስዓት ውእተ ማኅቶተ ኀበ ውእቱ ዕፅ ዘአዕረፈት ቦቱ ተንሥአት እምህየ ወሖረት ፍኖታ ወበማዕከለ ፍኖት ሶበ ገብአ ሕሊናሃ ወተአተተ እምኔሃ ዝንጋዔ ተዘከረቶ ለውእቱ ማኅቶት::

፬ ወገብአት ይእቲ ብእሲት እንዘ ትቴክዝ ወተሐዝን ወበጽሐት ኀበ ውእቱ ዕፅ ዘአዕረፈት ቦቱ ቀዳሚ ኃሠሠቶ ለውእቱ ማኅቶት ወኢረከበቶ ወሶቤሃ አኃዘት ትትዋቀስ ምስለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ትብል ለምንት ከመዝ ረሰይክኒ ወአስተኃፈርክኒ ሊተ ወለምንት አግባእኪ ትፍሥሕትየ ውስተ ኃዘን ውትካዝ ቦኑ ትብሊ ቅብዓ ኃጥአንሰ ኢይትቀባዕ ርእስየ ወኢይትዌከፍ መባአ እምእደ ብእሲት ኃጥእት አኮኑ ይቤ አምላክኪ ኢመጻእኩ እጸውዕ ጻድቃነ አላ ኃጥአነ::

፭ ወዘንተ ብሂላ ተመይጠት መንገለ ፍኖታ ወአኃዘት ትሑር በ፪ ልብ ወካዕበ አዕረፈት ኀበ አሐቲ ዕፅ ሶበ ስእነት ሐዊረ ፍኖት በቀቢፀ ተስፋ ወእምነሰ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አዘዘታ ለአሐቲ ጠሊት ከመ ትንሣእ ውእተ ማኅቶተ ዘተኃጥአ ወትሑር ወተሀባ ለይእቲ ብእሲት ኀዘንት ወመጽአት ኀበ ይእቲ ጠሊት እንዘ ትጸውር በአፉሃ ማኅቶተ ወበጽሐት ኀቤሃ ወመጠወታ ከመ ዘይሜጡ ካልእ ለካልኡ::





፯ አንደኛውንም እንስራ ወስዳ ለመምህሩ ሰጠች ሁለተኛውንም በእናታችን ስም ለነዳያን መጸወተች ወዳጆቼ ሆይ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ያደረገችውን ከዚህም በፊት ያልተደረገውን ወደፊትም የማይደረገውን እንሥራን ከእንሥራ ከነጠላው እንዳስገኘች ይህን ተአምር አያችሁን ሔዋንም ከሥጋው ሥጋ ከነፍሱ ነፍስ ነስታ ከአዳም እንደተገኘች የናታችን ቅድስት ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ታምራቷን ስንቱን እንናገራለን ጸሎቷና በረከቷ ከሁላችን ጋራ ይሁን ዛሬም ዘወትር ለዘለዓለሙ ይደረግልን::

፹ ኛ ተአምር

፩ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ታምር ይህ ነው አማላጅነቷ ከሁላችን ጋራ ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለአለሙ ይደረግልን

፪ አንዲት ሴት ጧፍ ተሸክማ በእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ስም ለተሠራች ቤተ ክርስቲያን ለመስጠት ከሩቅ አገር መጥታ በበአሏ ቀን ኅዳር አሥራ ሰባት በጐዳና ስትሄድ ከድካምና ከፀሐይ ሐሩር የተነሣ ከእንጨት ጥላ ሥር አረፈች::

፫ ያን ጧፍ ረስታ ከዚያ ተነሥታ ጐዳናዋን ሂዳ ከመንገድ መካከል ስትደርስ ልቡናዋ ተመልሶ ዝንጋኤዋ ከሷ ተወግዶ ያን ጧፍ መርሳቷን አስታወሰች::

፬ በዚያን ጊዜ እያዘነች ወደኋላዋ ተመልሳ ቀድሞ ካረፈችበት እንጨት፡ጥላ ስር፡ደረሰች እና ፈልጋ ያንን መብራት አጣች በዚህን ጊዜ ከእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጋራ እንደዚህ ለምን አደረግሽኝ ለምንስ አሳፈርሽኝ ደስታዬንስ ወደ ሐዘን ለምን መለስሽ በውኑ እራሴ የኃጥአንን ቅቤ አይቀባም ከኃጢአተኛ ሴት እጅ መባ አልቀበልም ለምን አልሽ ፈጣሪሽ ኃጥአንን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም ብሎ አልነበረም እያለች ትከራከር ትዋቀስ ጀመር::

፭ ይህን ብላ ወደ መንገዷ መለስ ብላ ልቧን እያመነታች ሂዳ ሳገመኛ ተስፋ ከመቁረጥና ከድካም የተነሣ ከአንዲት እንጨት ስር አረፈች እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ጠፍቷት የነበረውን ያንን መብራት ትወስድላት ዘንድ አንዲቷን ፍየል አዘዘቻት ያችም ፍየል መብራቱን በአፏ ይዛ አያንጠለጠለች ፈጥና ሩጣ እሷ ከአለችበት ደርሳ አንዱ ሰው ለአንዱ እንደሚሰጥ ሰጠቻት::

፮ ወሶቤሃ ተመይጠት ይእቲ ጠሊት በውእቱ ፍኖት ዘመጽአት ቦቱ ወኢተግሕሠት እምኔሁ ኢለየማን ወኢለፀጋም ወይእቲኒ ብእሲት ተፈሥሐት ዐቢየ ፍሥሐ ወሰብሐቶ ለእግዚአብሔር ወአእኰተታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ገባሪተ ተአምር ወተንሥአት ወሖረት ወበጽሐት ኀበ ቤተ ክርስቲያን ዘማኅበር ወአብአት ውእተ ማኅቶተ ወዜነወት ዘንተ ተአምረ ለኵሉ ሰብእ በከመ ይቤ በመዝሙር ዜኖኩ ጽድቀከ ለማኅበር ዐቢይ።

፯ ወበእንተዝ ንዑ ኵልክሙ ጉቡአን ናስተብፅዓ ወንወድሳ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወብፅዕት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ትተንብል በእንቲአነ ኀበ መፍቀሬ ሰብእ ኢየሱስ ክርስቶስ ይጸግወነ ሣህሎ ወምሕረቶ በብዝኃ ምሕረቱ ወንትአቀብ በጸሎታ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲቱ ትንብልናሃ ወሀብተ ረድኤታ የሃሉ ምስለ ፍቁራ ለዓለመ ዓለም።

## ፳ ተአምር

፩ ተአምር ዘገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትንብልናሃ የሃሉ ምስለ ፍቁራ ለዓለመ ዓለም።

፪ ወመጽአ ፩ ብእሲ መነኮስ እምነ ግራርያ ሶበ ዐዕረፈ የማነ ክርስቶስ መምህር ከመይዜኑ ሞቶ ለማኅበር ወበጺሖ ኀበ ማኅበር ዘእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዜነዎሙ ወበከይዎ ወለሀውም ወእምዝ ሀለፈ ወሖረ ጋዝጌ ወአደ ውስተ ኵሉ ገዳም ወዜነዎሙ ሞቶ ወገብአ ወእንዘ ይገብእ በጽሐ ፋሬ ወቦአ ውስተ ባሕር በንዑስ ታንኳ።

፫ ወምስሌሁ ሀለወ ፩ ብእሲ ዘይሔድፍ ሎቱ እንዘ ይነብር መንገለ ፍጽም ወውእቱሰ መነኮስ ኢለመደ ባሕረ ወኢየአምር ግብሮ ለታንኳ ወኮነ ይፈርህ ወይርዕድ ወይመስሎ ከመ ዘይሰጠም እምብዝኃ ናዕሱ ለታንኳ ወውእቱ ብእሲ ዘይሔድፍ ያጸንዖ ወይቤሎ ኢትፍራህ ወምስለ ዝኒ ኢሀሎ ካልእ ትርክዛ ዘእንበለ ፩ ዘይሔድፍ ቦቱ ወእንዘ የሐውሩ ከመዝ በውእቱ ታንኳ ኃለፉ ንስቲተ እምነ ዘጌ ወእምዝ ተንሥአ ላዕሌሆሙ ዐቢይ ነፋስ ዘይነፍሕ መንገለ አባቢት ወሜጠ ገጸ ለታንኳ ኀበ ካልእ ገጽ ወሶቤሃ ፈርሃ ወርዕደ ውእቱ ብእሲ ወቀርበት ነፍሱ ለወፂእ ወተሰፈወ ተስፋ ሞት ውስተ ቅላየ ባሕር ወአኃዞ ለታንኳ በ፪ሆን እደዊሁ ወውእቱሰ ነፋስ ኃያል መሰጦ ለትርክዛ እምነ እዴሁ ለውእቱ ብእሲ ዘይሔድፍ ወይቤሎ ውእቱ ብእሲ ለመነኮስ እምይእዜ ተሐጉልነ ናሁ መሰጦ ነፋስ ለትርክዛ ወአልብየ ካልእ ዘእንብሌሁ ዘእሔድፍ ቦቱ ወአውየወ ሶቤሃ ውእቱ መነኮስ ወከልሐ እንዘ ይብል ኦ አምላከ ወለተ ጴጥሮስ ርድአኒ ወተሣሃለኒ።





፮ ከዚህ በኋላ ያች ፍየል የመጣችበትን ጐዳና ይዛ ወደ ግራም ወደ ቀኝም ሳትል ሄደች ያችም አዝና የነበረችው ሴት እግዚአብሔርን እና እናታችንን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስን እያመሰገነች ድንቅ ሥራንም የምትሠሪ እናት እያለቻት እየተደሰተች ተነስታ ሄዳ ወደ አንድነት ገዳሟ ቤተ ክርስቲያን ደርሳ ይህንንም ተአምር ለሰው ሁሉ ተናግራ ያንን መብራት አስገባች መዝሙር በታላቅ ጉባዔ ቸርነትህን ተናገርኩ እንዳለ

፯ ስለዚህ ከዚህ የተሰበሰባችሁ ሁላችሁም እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስንም እናድንቃት እና እናመስግናት ዘንድ ኑ በይቅርታውና በቸርነቱ ብዛት ቸርነቱንና ይቅርታውን ይሰጠን ዘንድ ሰውን ወደሚወድ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኛ እንድትለምንልን አምላክን በወለደች በእመቤታችን ጸሎት እንድንጠበቅ ልመናዋና የረዳትነቷ ሀብት ከእኛ ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ በውነት ያለ ሐሰት ይደረግልን ::

## ፳ኛ ተአምር

፩ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተአምር ይህ ነው አማላጅነቷ ከሁላችን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን።

፪ መምህር የማነ ክርስቶስ ባረፈ ጊዜ መሞቱን ለማኅበሩ ይናገር ዘንድ አንድ መነኩሴ ከግራሪያ ሀገር መጣ እዚያ ከማኅበሩ ዘንድ ደርሶ ለእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አንድነት ማኅበር ነገራቸው እነሱም አለቀሱለት ከዚህ በኋላ አልፎ ወደ ጋዝጌ ሄደ እንደገና በየገዳማቱ ዞሮ ሞቱን ነግሮ ሲመለስ ፋሬ ደርሶ በትንሽ ታንኳ ወደ ባሕር ገባ ከፊቱ ተቀምጦ የሚቀዝፍለት አንድ ሰው ከሱ ጋር ነበር ያም መነኩሴ ባሕሩን መዋኘት አያውቅም ታንኳ ላይም መቀመጥ አለመደምና የሚሰጥም እየመሰለው ከታንኳ ማነስ የተነሣ ፈርቶ ይንቀጠቀጥ ነበር የሚቀዝፍለት ሰውየም አይዞህ እያለ ያጽናናው ነበር ::

፫ ከሱ ጋር ያለ አንድ መቅዘፊያ ሌላ መቅዘፊያ አልነበረም በአንድ መቅዘፊያ እየቀዘፈ በዚያች ታንኳ ሄደው ጥቂት ከዘጌ እንዳለፉ ወደ አባቢት የሚነፍስ ታላቅ ነፋስ ተነስቶባቸው ያንን ታንኳ ወደ ሌላ ቦታ መለሰው በዚያን ጊዜ ከማዕበሉ የተነሣ ያ ሰው እጅግ ፈርቶ ነፍሱ ልትወጣ የተቃረበች እየመሰለው በዚህ በባሕር ተሰጥሞ መሞቱን ተስፋ ቆርጦ በሁለት እጆቹ ታንኳውን ያዘ ያም ኃይለኛ ነፋስ ከቀዛፊ ሰውየ እጅ የሚቀዝፍበት መቅዘፊያውን ቀምቶ ወሰደበት በዚህን ጊዜ ያ ሰው ለዚያ መነኩሴ ከእንግዲህ ወዲህ መስጠማችን ነው መቅዘፊያየን ነፋስ ወስዶብኛል ያለ እርሱ ሌላ የምቀዝፍበት የለኝም አለው ያም መነኩሴ ይህን በሰማ ጊዜ አምላከ ወለተ ጴጥሮስ አድነኝ እርዳኝ አለ

፩ ወካዕበ ኃለየ ማኅሌተ ዚአሃ በልዑል ቃል እንዘ ይብል ሰላም ለኪ ወለተ ጴጥሮስ ገነት ክልልተ መዓዛ ጥዑም እስከ ተፍጻሜቱ ወዘእንበለ ይፈጽም ጸሎቶ አርመመ ነፋስ ወሐድአ ማዕበለ ባሕር እስመ ገሠጾቶ እምነ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ በጊዜሃ አመጸለየ ውእቱ መነኮስ በማኅሌተ ዚአሃ እንዘ የኃሊ በዓቢይ ዜማ ወታንኳኒ ተመይጠ ለሊሁ በፈቃዱ እንዘ አልቦ ዘይሔድፎ ወይመይጦ ወአርትዓ ሐዊረ ዘይጔይስ እምነ ሑረቱ ዘቀዳሚ ወሶቤሃ ጸበተ መልዕልተ ማይ ዘእንበለ ሐዳፍ ወአብጽሖሙ ፍጡነ በቅጽበት ውስተ መርሶ ኀበ ፈቀዱ።

፪ ወወፂኦሙ ውስተ ሐይቅ ሰብሖ ለእግዚአብሐር ውእቱ መነኮስ ወአእኰታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘአድኃነቶ እምተሰጥሞ ወባልሐቶ እሞት ወእምድኅረሁ ውእቱ ይቤ በልቡ ናሁ ውስተ አናቅጸ ሲኦል ኃደገ ዘተርፈ ዓመትየ ወኢይሬኢ ሰብአ እምአዝማድየ ወእምድኅረ ፀአቱ እምባሕር አተወ ውእቱ መነኮስ ውስተ ማኅበር ዘእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወነገሮሙ ዘንተ ተአምረ እምጥንቱ እስከ ተፍጻሜቱ ወሰሚዖሙ እሙንቱሂ አስተብፅዕዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወይቤልዋ ዐቢይ ውእቱ ክብር ዘተውህበ ለኪ ኦ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እስመ አንቲ በባሕር ወአንቲ በየብስ ዘትክሊ አድኅኖታ ለዘትጼውዓኪ ነፍስ።

፫ ወእምድኅረዝ ተመይጡ ኀበ ዝኩ መነኮስ ወይቤልዎ እስኩ ንግረነ ዘከመ እፎ ድኅንከ ወአምሠጥከ እምተሰጥሞ አውሥአሙ ውእቱ መነኮስ ወይቤሎሙ እንዘ ሀለውኩ አነ በዓቢይ ድንጋፄ ተዘከርክዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወኃለይኩ ማኅሌተ ዚአሃ በዐቢይ ዜማ ወይእተ ጊዜ ሀድአ ነፋስ ወአርመመ ባሕር ወይቤልዎ እስኩ ኃሊ ለነ በዜማ በከመ ኃለይከ ውስተ ባሕር ወይቤሎሙ እሆ ወኃለየ በዐቢይ ዜማ ወእምዝ ሖረ ውእቱ መነኮስ እምኀቤሆሙ እንዘ ያነክሩ ኃይለ ዕበያ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎታ ወበረከታ የሃሉ ምስለ ገበራ ለዓለመ ዓለም አሜን ።





፩ ዳግመኛም በጣፈጠ መዓዛ የታጠርሽ ገነት ወለተ ጴጥሮስ ሰላምታ ይገባሻል እያለ በታላቅ ድምፅ እየጮኸ የሷን የማኅሌት ወረብ እስከ መጨረሻው ወረበ ይህንን እየዘመረ እያለ ነፋሱ ፀጥ ብሎ ማዕበሉ ቆመ ያም መነኩሴ በታላቅ ዜማ የእሷን የማኅሌት ወረብ ስለወረበ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ማዕበሉን ገስፃ ፀጥ አሰኘችው ታንኳውንም የሚቀዝፈውና የሚመልሰው ወደ ሚሻለውም ጐዳና የሚወስደው ሳይኖር እራሱ በሚሻለው ጐዳና አቅንቶ ሄደ ያለ ቀዛፊ እራሱ እየበረረ ወደ ፈለጉበት ወደብ ፈጥኖ አደረሳቸው።

፪ ከባሕር ውስጥ ከወጡ በኋላ እግዚአብሔርን አመሰገኑ ከሞትና በባሕር ከመስጠም ያዳነችውን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን እያደነቀ አመሰገናት እሱ በልቦናው የተረፈውን ዘመኔን በመቃብር ሆድ አደረግሁት ከወገኖቼም፡ጋር ከእንግዲህ አልገናኝ ብሎ ነበርና ያ መነኩሴም ከባሕር እንደወጣ ወደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ አንድነት ገዳም ሄዶ ይህን ተአምር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ነገራቸው እነሱም ሰምተው እናታችንን አደነቋት እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሆይ ለአንች የተሰጠሽ ክብር ትልቅ ነው አንች በባሕርም በየብስም ሆና ተጨንቃ ለምትጠራሽ ሰውነት ፈጥነሽ ደርሰሽ ከስቃይ ታድኛታለሽና ።

፫ ከዚህ በኋላ ወደ መነኩሴው ተመልሰው እንዴት እንደዳንክና ከመስጠም እንዴት እንዳመለጥህ ንገረን አሉት እሱም በታላቅ ድንጋጤ ሳለሁ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን አስቤ በታላቅ ዜማ የማኅሌቷን ወረብ በወረብኩ ጊዜ ነፋሱ ተወገደ ማዕበሉም ፀጥ አለልን አላቸው እነሱም መልሰው በባሕር ውስጥ እንደወረብክ ወረብን ወርብልን አሉት እሽ ብሎ ወረበላቸው የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የታምራቷን ኃይል እያደነቁ ያም መነኩሴ ከነሱ ተለይቶ ሄደ ጸሎቷና በረከቷ ከሁላችን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን ።

## ፮ ተአምር

፩ ተአምር ዘገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትንብልናሃ ያድኅነነ። ለዓለመ ዓለም

፪ ወሀለወት አሐቲ እኅት እምነ አኃት በውስተ ማኅበር ወባቲ መጽሐፈ መልክዐ ዘእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ዘጽሑፍ ምስለ ጎልጎታ ወትጸውሮ ውስተ ክሳዳ ወትጼሊ ቦቱ ኵሎ አሚረ ዘእንበለ ዕርዓት ወአሐተ ዕለተ ወረደት ውስተ ባሕር ከመ ትኅፅብ አልባሲሃ ይእቲ እኅት ወውእቱኒ መጽሐፈ መልክዐ ዘእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሀሎ ውስተ ክሳዳ ዕኑቅ ወሶበ በጽሐት ኀበ ባሕር እምኀባበ አልባስ አውረደቶ እምክሳዳ ለውእቱ መጽሐፍ ወአንበረቶ በጥቃሃ መልዕልተ ዕብን እስከ ተኃፅብ አልባሲሃ ወሶበ ፈጸመት ኃጺበ አልባስ ወፅአት እምኀባብ ወሖረት ቤታ ወመጽሐፍሰ ተረስዓ ወተኃድገ በዝየ ኀበ አንበረቶ ቀዲሙ ::

፫ ወእምዝ ግብተ መጽአ ብእሲ መሠግረ ዓሣ ኀበ ውእቱ መካን ወረከቦ ለውእቱ መጽሐፍ ንቡረ መልዕልተ ዕብን ወአንሥአ ወወሰዶ እንበለ ያእምሮ መኑሂ ወእምድኅረዝ ሶበ ተዘከረቶ ይእቲ እኅት ለውእቱ መጽሐፍ ደንገፀት ዐቢየ ድንጋፄ ወወረደት ውስተ ባሕር እንዘ ትጔጕዕ ከመ ትኅሥሥ ኀበ መካን ዘአንበረቶ ቀደሙ ወበጺሓ ኃሠሠቶ ወኢረከበቶ ወኃዘነት ዐቢየ ኃዘነ ወእምዝ ተመይጠት ወአተወት ቤታ እንዘ ተኃዝን ወትበኪ ወነበረት እንዘ ትጼሊ ወትስእል ኀበ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ትክሥት ላቲ ኀበ ሀሎ መጽሐፍ ወአማፀነቶሙ ለኵሉ ማኅበር ለአኃው ወለአኃት ከመ ኢይርስዕዋ በጊዜ ጸሎት ወይእቲኒ ትወድቅ ታሕተ እገሪሆሙ ኵሎ ዕለተ በጸሎተ ማዕድ ወበስብሐተ ፍቁር ወኢታፀርዕ አሐተ ሰዓተ::

፬ ወውእቱሰ ብእሲ መሠግረ ዓሣ ዘነሥአ ለውእቱ መጽሐፈ መልክዐ ዘእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኮነ የዓውድ ውስተ አህጉር ወውስተ አብያት እንዘ ኪያሁ ከመ ይሢጦ ወርእዮሙ ሰብአ ሀገር ውእተ መጽሐፈ ይቤልዎ ለውእቱ ብእሲ እምአይቴ ረከብከ ዘንተ መጽሐፈ አኮኑ ዘማኅበር ውእቱ ቦኑ አንተ ሠረቀ ወአምጻእከ ወሚመ ወሀበከ ባዕድ ሠራቂ ንሕነሰ ኢንሣየጥ እምኔከ መጽሐፈ ዘተሠርቀ ዘቦቱ ትእምርት ወኢንሳተፍ በኃጢአተ ባዕድ ዘተሳተፈ ምስለ ሠራቂ ሠራቂ ውእቱ ወሶበ ኃጥአ ዘይሤየጥ እምኔሁ አግብኦ ለውእቱ መጽሐፍ ወአንበሮ ውስተ ቤቱ::





## ፮ ተአምር

፩ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ተአምር ይህ ነው አማላጅነቷ ከሁላችን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን ::

፪ በአንድነት ማኅበር ካሉት እኅቶች መካከል አንዲት እኅት ነበረች ያችም እኅት የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከጐልጐታ ጋር በአንድነት የተጻፈ መልኳን በአንገቷ ታደርግ ነበር ሳታስታጉል ዘወትር ትጸልይበታለች ከእለታት በአንድ ቀን ያች እኅት ልብሷን ታጥብ ዘንድ ወደ ባሕር ወረደች የእናታችን ወለተ ጴጥሮስ መልክ በአንገቷ ተንጠልጥሎ ስለነበር ልብስ ከምታጥብበት ባሕር ደርሳ ያንን መጽሐፍ ከአንገቷ አውልቃ ልብሷን አጥባ እስከምትጨርስ ድረስ ከአጠገቧ ባለው ድንጋይ ላይ አስቀመጠች ልብስ አጥባ ስትጨርስ ወደ ቤቷ ሄደች መጽሐፉ ግን ተረስቶ መጀመሪያ ወደ አስቀመጠችበት ቦታቀረ::

፫ ከዚህ በኋላ ዓሣ የሚያጠምድ አንድ ሰው ወደ እዚያ ቦታ ድንገት መጥቶ በድንጋይ ላይ የተቀመጠውን መጽሐፍ አግኝቶ ማንም ሳያውቅበት አንስቶ ወሰደ ከዚህ በኋላ ያች ልጅ ያንን መጽሐፍ ባሰበች ጊዜ ትዝ አላትና በጣም ደንግጣ እየሮጠች ወደ ባሕር ሄዳ ወደ አስቀመጠችበት ቦታ ደርሳ በፈለገች ጊዜ አጥታ በጣም አዘነች እያለቀሰች እና እያዘነች ወደ ቤቷ ተመለሰች ያም መጽሐፍ ከአለበት ቦታ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትገልጥላት ዘንድ ትጸልይ ጀመር ወንድሞችንና እኅቶችን መነኩሳት በጸሎት ጊዜ ያስቡላት ዘንድ ተማጸነቻቸው በጸሎተ ማዕድና በስብሐተ ፍቁር አንድ ቀን ሳታስታጉል በእግራቸው ላይ ትወድቅ ነበር::

፬ ዓሣ አጥማጅ የነበረ የእናታችን ወለተ ጴጥሮስ መልክዐ መጽሐፍ የወሰደ ሰው ይሸጠው ዘንድ በየቤቱና በየአገሩ እየተዘዋወረ ለመሸጥ ያስማማ ጀመር የአገሩ ሰዎች መጽሐፉን እያዩ ይህን መጽሐፍ ከወዴት አገኘህ ይህ የአንድነት ገዳም ማኅበር መጽሐፍ ነው አንተ ሰርቀህ አምጥተህ ወይም ሌላ ሌባ ሰርቆ ሸጥ ብሎ ሰጥቶህ ነው እኛ ግን ምልክት ያለበትን የተሰረቀውን መጽሐፍ አንገዛም ከሌባ ጋራ ተባባሪ ሆነን በሌላ ሐጢአት አንገባም ከሌባ ጋራ የተባበረ ሌባ ነውና እያሉ እንቢ አሉ ከእሱ የሚገዛው ባጣ ጊዜ መልሶ ከቤቱ አስቀመጠው::

፳ ወካዕበ ሐለየ ከመ ይሑር ካልአ ሀገረ ወይሚጦ ለውእቱ መጽሐፍ ወይቤላ ለብእሲቱ በዝየሰ ኃጣእኩ ዘይሣየጥ እምኔየ ዘንተ መጽሐፈ ወይቤሉኒ ሠራቂ አንተ ወባሕቱ አስተዳልዊ ሊተ ስንቀ አንስ እፈቅድ እሑር ርኁቀ ብሔረ ከመ እሚጥ ውእተ መጽሐፈ ወትቤሎ ብእሲቱ ኦሆ ወእንዘ ሀሎ ውእቱ ብእሲ በዝንቱ ሕሊና አስተርአየቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በሕልም እንዘ ይነውም ሌሊተ ወትቤሎ ኢትግበር ዘሐለ ይከ ወኢትሚጥ መጽሐፈ መልክዕየ ወነቂሆ ውእቱ ብእሲ እምንዋሙ ኢአምነ ነገረ ሕልም ወአምሰሎ ሕልመ ሐሰት።

፳፩ ወካዕበ ኖመ ከመ ቀዳሚ ወይእቲኒ ካዕበ አስተርአየቶ ከመ ቀዳሚ ወትቤሎ ዑቅ ኢትግበር ዘሐለይከ ወአምሰሎ ሕልመ ወኖመ ከመ ቀዳሚ ወበሣልስ አስተርአየቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በዐቢይ ግርማ እንዘ ትትመዓዕ ላዕሌሁ ወናሁ አስተርአይኩከ ሥልሰ ጊዜ ወእቤለከ ዑቅ ኢትግበር ዘሐለይከ ወኢትሚጥ ውእተ መጽሐፈ አንተ ኢሰማዕከ ቃልየ ወረሰይከ ከመ ወኢምንት ለነገርየ ወይእዜኒ እብለከ አግብእ ውእተ መጽሐፈ ውስተ ማኅበር ወሀብ ለእመ ማኅበር እገሊት ወንግር ዘከመ አነ አስተርአይኩከ ወዘከመ እቤለከ ወለእመ ትፈርህ አንተ ንግሮ ለእገሌ ይሑር ምስሌከ ወይትናገር በእንቲአከ ወየሀብ ውእተ መጽሐፈ ወይግበር ለከ ሰላመ ወዕርቀ ወእመሰ አበይከ ሰሚዖተ ቃልየ ወተዓደውከ ነገርየ አነ እትቤቀለከ በቀለ ዐቢየ ወአመጽእ ላዕሌከ መቅሠፍተ እኩየ ወዘንተ ብሂላ ተሠወረቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ።

፳፪ ወእምድኅሬሁ ነቅሀ ውእቱ ብእሲ እንዘ ይፈርህ ወይርዕድ እምቃለ ግርማሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሶበ ጸብሐ ሖረ ኀበ ውእቱ ብእሲ ዘአመረቶ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዘ ይእኅዝ ውእተ መጽሐፈ ወበጺሖ ኀቤሁ አይድዖ ዘንተ ኲሎ ነገረ እምጥንቱ እስከ ተፍጻሜቱ ዘከመ አስተርአየቶ ወዘከመ አዘዘቶ ከመ ይሑር ምስሌሁ ወየሀብ ለእመ ማኅበር ውእተ መጽሐፈ ወሰሚዖ ውእቱ ብእሲ ዘንተ ነገረ መጽአ ኀበ ማኅበር እንዘ ምስሌሁ ውእቱ መሠግር ወቦአ ኀበእመ ማኅበር ወይቤላ ኦ እምየ እመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜኪ መሀሪ ሊተ ብእሴ ዘቦቱ አበሳ።





፳ ዳግመኛ ወደ ሌላ አገር ሂዶ ያንን መጽሐፍ ይሸጠው ዘንድ አስቦ ሚስቱን አንተ ሰርቀህ አምጥተህ ነው ከአንተ አንገዛም በማለት እንቢ ስለአሉኝ ወደ ሌላ አገር ርቄ ሂጄ ይህን መጽሐፍ እሸጥ ዘንድ እፈልጋለሁ እና ስንቅ አዘጋጅልኝ አላት ሚስቱም እሽ አለችው ያ ሰው በዚህ ሐሳብ ላይ ሳለ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሌሊት በሕልም ተገልፃለት ያሰብከውን አታድርግ የመልኬንም መጽሐፍ አትሽጥ አለችው ያም ሰው ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ ሕልሙን አላመነም እንደ ሐሰት አደረገው ።

፳፩ ዳግመኛ እንደቀድሞው ተመልሶ ተኛ እሷም ዳግመኛ ተገልጣለት ያሰብከውን እንዳታደርግ ተጠንቀቅ አለችው አሁንም እንደ ተራ ሕልም አድርጎ እንደ ቀድሞው ተመልሶ ተኛ በሦስተኛው እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እሱን እየተቆጣች በታላቅ መፈራት ታይታው እነሆ ሦስት ጊዜ ተገልጬልህ ያሰብከውን አታድርግ ይህን መጽሐፍ አትሸጥ ብዬ ነግሬህ አለሁ ከእንግዲህ ተጠንቀቅ አለችው አንተ ቃሌን ሰምተህ ነገሬን እንደ ኢምንት አድርገሃል ከእንግዲህ ወዲህ ይህን መጽሐፍ ለማኅበር መልስ ለእመምኔቲቱ እገሊት እኔ ተገልጬ እንደነገርኩህ ንገራት አንተ ከፈራህ እገሌ ዘንድ ሂድና እሱ ከአንተ ጋራ ሂዶ ይንገርልህና ይህን መጽሐፍ ሰጥቶ ያስታርቅሃል ነገሬን ተደፋፍረህ ቃሌን አልቀበልም ብትል እኔ አንተን ተበቅየ በአንተ ላይ ታላቅ መቅሠፍት አመጣብሃለሁ ይህን ብላው ከእሱ ተሰወረች ።

፳፪ ከዚህ በኋላ ያ ሰው እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ግርማና ከሚያስፈራ ቃል የተነሣ ፈርቶ እየተንቀጠቀጠ እናታችን ወደ አመለከተችው ሰው በጥዋት ሂዶ እንደታየችውና እንደ አዘዘችው እሱም ከእሱ ጋር ሂዶ ይህን መጽሐፍ ለማኅበሩ እንዲሰጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለውን ሁሉ ነገረው ያም ሰው ይህን ሰምቶ አሣ አጥማጁን አስከትሎ ወደ ማኅበሩ ሂዶ እመምኔቲቱን እናቴ ሆይ ባንቺ ዘንድ ባለሟልነትን ካአገኘሁ አንድ በደለኛ ሰው ይቅር በይልኝ አላት ።

፰ አውሥአቶ ወትቤሎ መኑ ውእቱ ዘአበሰ አንሰ ኢያአምር ብእሴ ዘቦቱ አበሳ አውሥአ ወይቤላ ሀሎ ብእሲ ዘነሥአ መጽሐፈ በኢያምሮ እምኀበ ተገድፈ ወናሁ ይቀውም በአፍአ ወትቤሎ እስኩ ጸውዖ ይምጻእ ለሊሁ ወይንግረኒ ዘከመ ገብረ ወእምዝ ጸውዖ ወቦአ ወተናገረ እንዘ ይፈርህ ወይርዕድ ኲሎ ነገረ ዘአቅደምነ ወወሀበ ውእተ መጽሐፈ፡፡

፱ ወተስእለቶ እመ ማኅበር ለውእቱ መሠግር ወትቤሎ በአይ አምሳል ርኢካ ወምንተ ትመስል ወአይድዓ ዘከመ ርእየ አምሳሊሃ ወእምዝ ሰረየት ሎቱ ወሖረ ቤቶ ወውእቱኒ መጽሐፍ ገብአ ኀበ ይእቲ እኅት ዘአጥረየቶ ቀዲሙ ወይእቲኒ ተፈሥሐት ወአአኰተታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትንብልናሃ ወሃብተ ረድኤታ የሃሉ ምስለ ገበራ ለዓለመ ዓለም፡፡

፰ ኛ ተአምር

፩ ተአምር ዘገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎታ ወበረከታ የሃሉ ምስለ ፍቁራ ለዓለመ ዓለም ፡፡

፪፡ወካዕበ፡ሀለወት፡አሐቲ፡ብእሲት፡በውስተ፡ሀገር፡እንተትሰመይ፡ዛራ፡ወለይእቲ ብእሲት አብአታ ክርስትና አሐቲ አረጊት እምነ ማኅበር ወበእንተዝ፡ትመጽእ፡ኲሎ፡አሚረ፡ኀበ፡ይእቲ፡አረጊት፡እማ፡እንተ፡ተወከፈታ በጥምቀት ወሰአለታ ይእቲ እማ አረጊት ከመ ትንበር፡ ምስሌሃ ውስተ ማኅበር ወትትመሀር መጽሐፈ ወትፍትል ወትስፊ ወአበየት ወኢተወክፈት ነገረ እማ ወነበረት ውስተ ሀገር፡፡

፫ ወእምዝ ዘመወት ወፀንሠት በዐመፃ ወወለደት ወበውእቱ መዋዕል ሐወጸት ወመጽአት ኀበ ማኅበር እንዘ ተሐዝል ሕፃና ወቦአት ኀበ ቤተ አረጊት በከመ ልማዳ ወሀለወት ውስተ ይእቲ ቤት አሐቲ እኅት እንተባ መጽሐፈ መልክዐ ዘእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሠረቀት ይእቲ ብእሲት እንግዳ ውእተ መጽሐፈ ወኃብአቶ ወወፅአት እምይእቲ ቤት ከመ ትሑር ሀገራ እንዘ ትነሥእ ውእተ መጽሐፈ ወይእቲሰ እኅት በዓልተ መጽሐፍ ኃሠሠቶ ወኢረከበቶ ወሐተተት ኀበ አኃቲሃ ኲሎን ከመ ይንግራሃ ለእመ ነሥእሁ ውእቶን ወይቤላሃ ንሕነሰ ኢነሣእነ ወኢነአምር ዘነሥኦ ወባሕቱ የቤላሃ እስኩ ሑሪ ኀበ ይእቲ ብእሲት ወተሰአሊያ ለእመነሥእቶ ወይክስት ለኪ ኃይለ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ፡፡





፰ እሷም ኧረ እኔ በደል ያለበትንም ሰው አላውቅም አለችው እሱም መልሶ በወደቀበት መጽሐፍ አንስቶ ባለማወቅ የወሰደው ሰው አለ እነሆ ከደጅ ቆሟል አላት እሷም እስኪ ጥራውና እንዴት አድርጎ እንደወሰደ ይንገረኝ አለች ከዚህ በኋላ ጠራውና ገብቶ እየፈራና እየተንቀጠቀጠ አስቀድመን የተናገርነውን ነገር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ተናግሮ መጽሐፉን ለእሷ አስረከበ፡፡

፱ እመምኔቱም በምን መልክ አያት ምንስ ትመስላለች አለችው እሱም በምን አምሳል እንደአያት ነገራት ከዚህ በኋላ ይቅር ብያለሁ አለችውና ተመልሶ ወደ ቤቱ ሄደ ያም መጽሐፍ ገዝታ ወደ ነበረችው እኅት ተመለሰ ያችም እጅግ ተደስታ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስንም አመሰገነቻት አማላጅነቷና የረዳትነቷ ሀብት ከሁላችን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን፡፡

፰ ተአምር

፩ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ታምር ይህ ነው አማላጅነቷና በረከቷ ከሁላችን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን፡፡

፪ ዳግመኛም ዛራ በምትባል አገር የምትኖር አንዲት ሴት ነበረች ያችንም ሴት በማኅበር ውስጥ የነበረች አንዲት አሮጊት ክርስትና ስለአነሣቻት ስለዚህ ወደ ጥምቀት እናቷ አሮጊት ከእሷ ጋራ ባንድነት ገዳም ተቀምጣ እየፈተለችና እየሰፋች መጽሐፍ እየተማረች እንድትኖር ለመነቻት እሷ ግን የክርስትና እናቷን ምክር እምቢ ብላ በአገር ትኖራለች፡፡

፫ ከዚህ በኋላ በዝሙት ፀንሳ በዓመፅ ወለደች በዚያን ወራት ትጠይቅ ዘንድ ያንን ሕፃን አዝላ ወደ ማኅበሩ መጥታ እንደልማዷ ወደ አሩጊቷ ቤት ገባች በዚያች ቤት የእናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ መልክ መጽሐፍ ያላት እኅት ነበረች ያች እንግዳ ሴት ያንን መጽሐፍ ሠርቃ ደብቃ ይዛ ከዚያ ቤት ወጥታ ሄደች ባለመጽሐፏ የነበረች እኅት ፈልጋ ባጣችው ጊዜ ወደ እኅቶቿ ሁሉ ሂዳ እነሱም አንስተው እንደሆነ መረመረቻቸው እኛ አላነሣንም ያነሣውንም አናውቅም አሏት ነገር ግን አንሥታ እንደሆነ ወደ እዚያች ሴት ሄደሽ ጠይቂ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ኃይል ያስገኝልሽ አሏት፡፡

፩ ወእምዝ ተንሥአት ይእቲ ወዴገነታ ወበጽሐት ኀበ ምሥያጥ ዘይሰመይ ቸር ተከል ወረከበታ በህየ ወሰአለታ በትሕትና እንዘ ትብል እስኩ ንግርኒ ለእመ አንቲ ነሣእኪዮ ለዝንቱ መጽሐፍ አ እኅትየ ወፍቅርትየ ወአውሥአታ ይእቲ ብእሲት ወትቤላ አ እኅትየ ሐሰ ሊተ ኢገበርኩ ዘንተ ዘትብሊ ወመሐለት እንዘ ትብል አምላክ ዘወለተ ጴጥሮስ ያርኢ ተአምራቲሁ በላዕሌየ ወየሀብ ሥጋየ ለአዕዋፈ ሰማይ ወሶበ ሰምዓት ይእቲ እኅት ዘመሐለት መሐላ ዐቢየ ተግሕሠት ወሖረት እምኀቤሃ ወእምድኅረ ህቅ ተመይጠት ካዕበ ወሰአለታ ከመ ቀዳሚ እስመ አእመረት ከመ መሐለት በሐሰት ወመሐለት ዳግመ ለንዘትብል አምላከ ወለተ ጴጥሮስ ይክሥት ተአምራቲሁ በላዕሌየ ወየሀብ ሥጋየ ለአዝዕብት::

፪ ወእምድኅረ ዝንቱ ትቤ ይእቲ እኅት ምንተ እብል ወምንተ እገብር እምይእዜ ዳእሙ እገድፍ ሕሊናየ ላዕለ እምየ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እስመ ይእቲ ታገብእ ሊተ መጽሐፍየ ወለእመሰ ኢያግብአት ሊተ ኢይጼውዕ ስማ ለዓለም ወኢይነብር ውስተ ማኅበር አላ አሐውር ውስተ ካልእ ሀገር ወመሐለት በቅድመ ኵሉ እንዘ ትብል ከመዝ::

፫ ወእምዝ ተመይጠት ወአተወት ወስተ ማኅበር ከመ ታእምር ዘይከውን ወትርአይ ማኅለቅቶ ለነገር ወነበረት እንዘ ተኃዝን ወትቴክዝ ኵሎ ዕለተ ወይእቲሰ ብእሲት ሠራቂት ቦአት ውስተ ሀገር ወሤጠቶ በ፩ አሞሌ ለውእቱ መጽሐፍ ወሶበ አንበቦ ዘተሣየጦ ብእሲ ረከበ ጽሑፈ ውስቴቱ ስመ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሶቤሃ አእመረ ከመ ውእቱ መጽሐፈ ማኅበር ወበእንተዝ ፈርሃ ወይቤላ ለይእቲ ብእሲት አግብኢ ሊተ ንዋይየ ወንሥኢ መጽሐፊኪ አንሰ እፈርህ ወኢይሣየጥ እምኔኪ ከመ ኢያምጽእ ላዕሌየ ዕዳ እስመ ቦ ጽሑፍ ውስቴቱ ስመ ወለተ ጴጥሮስ ::

፬ ወእምዝ ነሥአት እምኔሁ ውእተ መጽሐፈ ወሖረት ይእቲ ብእሲት ወቦአት ደሴተ ጓንጉት ከመ ትሢጦ ለውእቱ መጽሐፍ ወካዕበ አንበብም ወረከቡ ውስቴቱ ጽሑፈ ስመ ወለተ ጴጥሮስ ወፈርሁ እሙንቱሂ ወይቤልዋ ኢንሣየጥ እምኔኪ እስመ ውእቱ መጽሐፈ ማኅበር ወሶበ ኃጥአት ዘይሣየጥ ላቲ ወፅአት እምውእቱ ደሴት ወአደት ውስተ አህጉር ብዙኃ ወኢረከበት ዘይሣየጥ እምኔሃ ወእምዝ ሐለየት ከመ ታግብእ ውእተ መጽሐፈ ለይእቲ እኅት ወፈነወት ላቲ እንዘ ትብል ንሥኢ መጽሐፊኪ ኢትኀዝኒ ላዕሌየ እስመ አነ ነሣእክዎ በኢያእምሮ ወፈቀድኩ እሢጦ ምዕረ ወካዕበ ወባሕቱ ኃይለ ወለተ ጴጥሮስ ከልአኒ ወአዕቀፈኒ::





፩ ከዚህ በኋላ ተነሥታ ተከትላ ቸርተከል ወደምትባል ገበያ ደርሳ በዚያ አገኘቻትና በትሕትና ቃል እኅቴ ወዳጄ መጽሐፉን አንቺ አንሥተሽው እንደሆነ ንገሪኝ አላቻት ያችም ሴት መልሳ እኅቴ አንች የምትይውን ነገር አላደርገውም ዋሽተሻል በማለት አምላከ ወለተ ጴጥሮስ አንስቼ እንደሆነ ታምራቱን በኔ ላይ ይግለጥ ሥጋዬንም ለሰማይ አይዋፍ ምግብ ያድርግ ብላ ማለች ያችም እኅት ይህንን መሐላ ((ሰማች ጊዜ ከሷ ተለይታ ተመልሳ ሄደች ቆይታ መለስ ብላ ዳግመኛም ብትጠይቃት የወለተ ጴጥሮስ አምላክ በኔ ላይ ታምራቱን ይግለጥ ሥጋየንም ለጅቦች አሳልፎ ይስጥ አለቻት::

፪ ከዚህ በኋላ ያች እኅት ምንስ እላለሁ ከንግዲህ ወዲህ ምንስ አደርጋለሁ ሐሳቤን ለእናቴ ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እሰጣለሁ እንጅ እሷ መጽሐፌን ትመልስልኛለችና እሷ ከአልመለሰችልኝ ለዘለዓለም ስሟን አልጠራም ከአንድነት ማኅበርም ጋራ አልኖርም ወደ ሌላ ቦታ እሄዳለሁ እንጅ እያለች በሰው ሁሉ ፊት ማለች::

፫ ከዚህ በኋላ የነገሩን መጨረሻ የሚሆነውን ታይ ዘንድ ወደ ማኅበሩ ተመልሳ ገባችና በየቀኑ እያዘነችና እየተከዘች ኖረች ያችም ሠርቃ የነበረች ሴት ወደ አገሯ ገብታ ያንን መጽሐፍ ለሁለት አሞሌ ጨው ሸጠች የገዛው ሰውዬ በአነበበው ጊዜ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ስም በውስጡ ተጽፎ አግኝቶ የገዳሙ መጽሐፍ እንደሆነ አወቀና ስለዚህ ፈርቶ በኔ ላይ እዳ እንዳይመጣብኝ ፈርቻለሁና መጽሐፍሽን ወስደሽ ገንዘቤን መልሽልኝ የወለተ ጴጥሮስ ስም በውስጡ ተጽፎአልና አላት::

፬ ከዚህ በኋላ ያንን መጽሐፍ ከሱ ተቀብላ ወደ ጓንጉት ደሴት ያንን መጽሐፍ ትሸጠው ዘንድ ሄደች ዳግመኛም እነሱ አንብበው የወለተ ጴጥሮስን ስም በውስጡ አግኝተው ፈርተው የወለተ ጴጥሮስ ስም በውስጡ ተጽፎበታልና የማኅበሩ መጽሐፍ ስለሆነ አንገዛም አሏት ከዚያ ደሴት ወጥታ አገሩን ሁሉ ብትዞር ከሷ የሚገዛ አላገኘችም ከዚህ በኋላ ይህን መጽሐፍ ለዚያች እኅት ትመልስ ዘንድ አስባ መጽሐፍሽን ውሰጅ እኔ ሳላውቅ ወስጄ ለመሸጥ ብፈልግ የወለተ ጴጥሮስ ኃይል አደናቅፎ ከለከለኝ ብላ ላከችላት::

፰ ወተመጠወት ውእተ መጽሐፈ ወተፈሥሐት ፈድፋደ ወአእኰተታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወእምድኅሬሁ መጽአ ዝዕብ ኀበ ትነውም ይእቲ ብእሲት ወነሰካ ወገመደ ስኩና እገሪሃ እስመ ይእቲ መሐለት በድፍረት ወአርአየት ኃይላ በላዕሌሃ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮሰ ትንብልናሃ ውኩፍ ወ ኃይለ ረድኤታ ትሩፍ የሃሉ ምስለ ፍቁራ ለዓለመ ዓለም አሜን ::

፱ ተአምር

፩ ተአምር ዘገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትንብልናሃ የሃሉ ምስለ ፍቁራ ለዓለመ ዓለም አ::

፪ ወበሳድስ ወርኀ እምዘ አዕረፈት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሀለዋ አኃት አንስት ውስተ መካነ መቃብሪሃ ሬማ ከመ ይግበራ ተዝከረ ዚአሃ ወሀለወት ህየ አሐቲ እኅት እምኔሆን እንተ ትትጌበር ተግባረ ሰዋ ወመልአት ሰዋ በዐቢይ ጋን ወአንበረት ወእምዝ ንቅዓ ወተሰብረ ውእቱ ጋን ወተከፍለ መንገለ ፪ እስከ ያስተርኢ ዘውስቴቱ ሰዋ ወአሜሃ አኃዘቶ በእዴሃ አሐቲ እኅት እምነ አኃት እለ ሀለዋ ህየ ይትለአካ እንዘ ትብል ኦ እምየ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮሰ ርድእኒ::

፫ ወቆመ ውእቱ ሰዋ ማዕከለ ጋን ወሮጸት ይእቲ እኅት እንተ ትትጌበር ግብረ ሰዋ ወሖረት ኀበ ካልእ ቤት ወአምጸአት: ቀሱታተ ወቀድሐቶ ወኢነጠበ እምኔሁ ፩ ንጥበተ ወኢርኅሰ ሐመድ ዘመትሕቴሁ ወእምድኅሬሁ አውፅአሁ ለውእቱ ጋን ከዊኖ ፪ ክፍለ ገልዓ ወገደፋሁ አፈኣ ወኮነ ዝንቱ በኃይለ እምነ ቅድስት ወቡር ክት ወለተ ጴጥሮስ ::

፬ ወበይእቲ ዕለት መጽአት አሐቲ ብእሲት እንዘ ትጸውር ሕፃነ ዕውረ ወመፅጕዓ ወፈቀደት ትባእ ሬማ ከመ ታመኀፅኖ ለወልዳ ኀበ መቃብሪሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወኃጥአት ታንኳ ወኃሠሠት መሬተ ዝኅር ዘእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ትቅብዖ ለወልዳ ወኢረከበት ::

፭ ወነበረት በአፍአ ምስለ ነዳያን ወወሀብዋ ኅብስተ ወስቴ ሰዋ ወበልአት ወሰትየት ወቀብዓቶ እምውእቱ ስቴ ሰዋ ለውእቱ ወልዳ ዕውር ወመፃጕዕ ዓይኖ ወዘባኖ እንዘ ትትአመን ኃይለ ረድኤታ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሶቤሃ ተከሥተ ዓይኑ ወረትዓ ዘባኑ ወኵሎሙ እለ ርእዩ ዘንተ ተአምረ አንከሩ ወአእኰትዋ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎታ ወበረከታ የሃሉ ምስለ ገብራ ለዓለመ ዓለም::





፰ እሷም ያንን መጽሐፍ ተቀብላ እጅግ ተደስታ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን አመሰገነቻት ከዚህ በኋላ ያች ሴት ተኝታ ሳለች ጅብ መጥቶ ነከሣትና እግሯን ቆርጦ ወሰደ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በሷ ላይ ኃይሏን ገለጠች ተቀባይነት ያለው የአማላጅነቷ ኃይል ከሕዝበ ክርስቲያን ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን::

፱ኛ ተአምር

፩ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ያደረገችው ታምር ይህ ነው ጸሎቷና አማላጅነቷ ይህን መጽሐፍ ከጻፉትና ከጻፉት ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን::

፪ እናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከአረፈች መንፈቅ በሆናት ጊዜ በመቃብሯ ቦታ በሬማ የመንፈቋን መታሰቢያ ለማድረግ እዚያ ተቀምጠው ሳሉ ከነሱ መካከል ጠላን ትጠምቅ የነበረች አንዲት እኅት በትልቅ ጋን ሞልታ አሥራ አስቀምጣ ሳለች ጋኑ ተሰንጥቆ በውስጡ ያለ ጠላ ከሩቅ እስኪታይ ድረስ ከሁለት ተከፈለ ከእኅቶች መካከል እዚያ ትላላክ የነበረች አንዲት እኅት እናቴ ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሆይ ይህ ጠላ እንዳይፈስ ርጅኝ ብላ በእጇ ያዘችው::

፫ ያም ጠላ በተሰበረው ጋን ውስጥ እየታየ ሳይፈስ ቆመ ጠላ ትጠምቅ የነበረችው እኅት ሩጣ ወደሌላ ቤት ሄዳ እንስራዎችን አምጥታ ቀዳች ያም ጠላ የዕንባባን ጠብታ ያህል ጠብ አላለም ከጋኑ በታች ያለውም አመድ አልራሰም ከዚህ በኋላ ሁለት ቦታ ተሰብሮ የነበረውን የጋኑን ገል አውጥተው ከደጅ ጣሉት ይህም የተደረገው በእናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ኃይል ነው::

፬ በዚያች በመታሰቢያዋ ዕለት አንዲት ሴት አይነስውርና ሽባ የነበረውን ሕፃን ተሸክማ ወደሬማ ገብታ ከእናታችን ወለተ ጴጥሮስ መቃብር ታማፅነው ዘንድ መጣች የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የመቃብር አፈር ለልጇ ትቀባ ዘንድ አላገኘችም ታንኳ አጥታለችና::

፭ ከነዳያን ጋራ በባሕሩ ዳር ተቀምጣ የመታሰቢያዋን እንጀራና ጠላ ሰጧት እና በልታ ጠጥታ ከዚያ ከጠላው እውርና ሽባ የሆነውን ልጇን ዓይኑንና ጀርባውን መላ ሰውነቱን በእናታችን ቅድስት ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ረዳትነቷ ኃይል ተማምና ቀባችው በዚያን ጊዜ ዓይኑ በራለት ወገቡም ቀናለትና መላ አካሉ ደህና ሆነለት ያዩትም ሰዎች ሁሉ እጅግ አድንቀው እናታችንን ቅድስት ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን አመሰገኗት ጸሎቷና በረከቷ ይህን መጽሐፍ ከጻፉትና ከአጻፉት ጋራ ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን::

## ፲ ተአምር

፩ ተአምር ዘገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ በረከታ የሃሉ ምስለ ፍቁራ ለዓለም ዓለም ::

፪ ወሀሎ ፩ መነኮስ ቀሲስ ዘስሙ መዝገበ ሃይማኖት ዘተሐፅነ ወልሀቀ ውስተ ማኅበር ዘእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እስመ ውእቱ ቦአ ምስለ እሙ እንዘ ውእቱ ሕፃን ወይጠቡ አጠባቲሃ ወበህየ ተምህረ መጻሕፍተ ወኮነ ትሑተ ወየዋህ ወኄረ ወመፍቀሬ እግዚአብሔር ወመንኰሰ በድንግልና ወውእቱ ደወየ ደዌ ጽኑዓ ወሐመ ሕማመ ዐቢየ ወስሕከ ሥጋሁ ወዘልፈ ይሄሉ ስኩበ ውስተ ዓራት መጠነ ብዙኅ ዓመታት ወበአሐቲ ሌሊት እንዘ ይነውም ርእየ ራእየ ዘይትፌጸም ወይከውን በዕድሜሁ ወነቂሆ እምንዋሙ ጸውዓኒ ሊተ ለጸሐፌ ዝንቱ መጽሐፍ ወሖርኩ ኀቤሁ ወተስእልክዎ ወእቤሎ በአይ ምክንያት ጸዋዕከኒ ::

፫ አውሥአኒ ወይቤለኒ ስማዕ እንግርከ ዘርኢኩ ዮም በሕልምየ በዛቲ ሌሊት እስመ አዘዙከ ለከ ከመ ትጽሐፍ ገድላቲሃ ወተአምራቲሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወካዕበ ርኢኩ በቅፅበት ጽሒፈከ ወፈጺመከ መጽሐፈ ዐቢየ ዘአዳም ቃሉ ወሠናይ ፊደሉ ወሰማዕኩ እንዘ ይትነበብ ማእከለ ጉባኤ ብዙኅ ምንትኑ ይመስለከ ዝንቱ ኅልም እሙንኑ አው ሐሰት ቦኑ ይትወሀብ ለከ ዝንቱ ሀብት እምኀበ እግዚአብሐር ዘእምኀቤሁ ኵሉ ሀብት ሠናይ ወኵሉ ፍት ፈጹም:ወዓዲ:ይቤለኒ:ለእመ ኮነ ከመዝ እምክህልከኑ ትጸሐፍ አንተ

፬ አውሣእክዎ እፎ እክል እግበር ዘንተ ባሕቱ አልቦ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር ይኩን ፈቃደ ዚአሁ ወውእቱኒ ይቤለኒ እምፈቀድኩ አንሰ ከመ ትጽሐፍ ለእመ ኮነ ፈቃደ እግዚአበሐር አውሣእክዎ አነሂ ካዕበ ወእቤሎ እፎ እዝበር ዘንተ ወእጽሕፍ በፈቃድየ ዘኢአዘዙኒ አበውየ ወበአይቴ አአምር ገድለ እምነ ቅድስት:ወቡርክት:ወለተ:ጴጥሮስ:አኮኑ:ሐዲስ ተክል አነ ወኢነበርኩ አሜሃ እመሰ ነገሩኒ እለ ቀደሙኒ በተጋድሎ አዕሩግ እምጸሐፍኩ ውእቱኒ አውሥአኒ ወይቤለኒለእመ ኢጸሐፍከ ይእዜ ሀለወከ ትጽሐፍ ድኅረ ኢይምሰልከ ዝንቱ ሕልም ሐሰት ዕቀቦ በልብከ ::





## ፲ኛ ተአምር

፩ የእናታችን ቅድስትና ብርክት ወለተ ጴጥሮስ ያደረገችው ተአምር ይህ ነው በረከቷ ከወዳጇ አግናጥዮስ ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደግልን::

፪ ስሙ መዝገበ ሃይማኖት የሚባል በእናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ገዳም አንድነት ያደገ አንድ ቄስ መነኩሴ ነበር እሱ ሕፃን ሳለ ከእናቱ ጋራ ጡቶቿን እየጠባ በገዳም አድጓልና በዚያም መጽሐፍትን ተምሮ የዋህ ቸር እግዚአብሔርን የሚወድ ስለሆነ በድንግልና መነኮሰ እሱም ታላቅ በሽታ ታሞ ሰውነቱ ሻክሮ ዘወትር ካልጋ ሣይነሣ በበሽታ ታስሮ ይኖር ነበር ከዕለታት በአንድ ቀን ሌሊት ተኝቶ በህልሙ በእድሜው የሚደረገውንና የሚፈጸመውን አይቶ ይህን መጽሐፍ የጻፍሁ እኔን ጠራኝ እኔም በምን ምክንያት ጠራኝ ብየ ጠየቅሁት::

፫ እሱም መልሶ ዛሬ በዚች ሌሊት ያየሁትን ራዕይ ስማ ልንገርህ የእናታችን ቅድስና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ገድሏን እና ታምሯን ትጽፍ ዘንድ አንተን አዘዋል እና ዳግመኛም ፊደሉ መልካም የሆነ ቃሉ ደስ የሚያሰኝ ትልቅ መጽሐፍ በፍጥነት ጽፈህ ፈጽመህ ብዙ ሕዝብ በተሠበሰበበት ጉባኤ መካከል ሲነበብ:አየሁ:አለ:ይህ:ህልም:ምን:ይመስልሀል:እውነት:ነው:ሐሰት: በውኑ:ይህ:የሚሰጥ:የፀጋ ስጦታ:
ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው ፍጹም ፍርድ እና መልካም ስጦታ ከሱ ዘንድ ይገኛል እና አለኝ::

፬ እኔም መልሼ ይህን አደርግ ዘንድ እንደምን ይቻለኛል ነገር ግን ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም እና የሱ ፈቃድ ይሁን አልሁት እሱም የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን አንተ ብትጽፍ በወደድኩ ነበር አለኝ እኔም መልሼ ይህን ነገር በእኔ ፈቃድ አባቶቼ ሳያዙኝ የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን ገድል እኔ በወዴት አውቄ እጽፋለሁ እኔ ያንጊዜ ያልነበርኩ አዲስ ተክል ነኝና በተጋድሎ እና በብቃት የቀደሙኝ:አባቶች:ቢነግሩኝ:በጻፍኩ:ነበር:አልሁት:እሱም:መልሶ:ዛሬ:ባትጽፍ:ኋላ:የምትጽፍበት:ጊዜ:አለ:ይህ:ራዕይ:ሐሰት:አይምሰልህ: በልብህ:ያዝ አለኝ::

## ፻፳፪ ተአምር ዘቅድስት ወለተ ጴጥሮስ

፳ ወእምድኅረ አይድዓኒ ዘንተ ነገረ ነበረ በዝንቱ ደዌ መጠነ ፱ዓመት በ፳ አዕረፈ በሰላም እግዚአብሔር ያዕርፍ ነፍሰ በመንግሥተ ሰማያት አሜን ወዝንቱሰ ነገር ተረስዓ ወአልቦ ዘነገሮ ወእምድኅረ አዕረፈ መዝገበ ሃይማኖት በ፫ ዓመት ካዕበ አስተናሥአ ሥምረተ እግዚአብሔር ለአሐቲ እኅት: ወአገበረተኒ ሊተ ከመ እጽሐፍ ዘንተሰ ነገረ አቅደመ ዘርዕየ መዝገበ ሃይማኖት ነገረኒ ሊተ ወባሕቱ ኃደጉ እስመ ኢአዘዙኒ አበውየ ወይእቲኒ ነገረቶሙ ለአበው ወለእመ ማኅበር ወሠርዑ ቀኖና ጸሎት መጠነ ሱባዔ ዕለታት ጠየቅዎ ተአዘዝኩ ወጸሐፍክዎ በሥምረተ እግዚአብሔር ወበረድኤተ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትንብልናሃ ወኃይለ ረድኤታ የዕቀቦ ለገበራ ለዓለመ አለም አሜን::

### ፲፩ ተአምር

፩ ተአምር ዘገብረት እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትንብልናሃ የሃሉ ምስለ ፍቁራ አግናጥዮስ ለዓለመ ዓለም::

፪ ወሀለወት አሐቲ ብእሲት በማዕዶተ ፈለገ ርብ እንተ ታፈቅራ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወትገብር ተዝካራ ወእንዘ ተሐውር ይእቲ ብእሲት ውስተ ፍኖት አሐተ ዕለተ እስመ ነበረት ውስተ ቤተ ክርስቲያን እንዘ ሀለወት ርኁቀ እምነ ቤታ መስየ ላዕሌሃ ብሔር ወተቈልቈለ ፀሐይ ወአልፀቀ ይዕርብ ወእምዝ ትቤሎ ይእቲ ብእሲት ለፀሐይ አምሕለከ በስማ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ከመ ትቁም ሊተ ኀበሀሎከ ወለእመኒ ዐረብከ ከመ ትሥርቅ ዳግመ

፫ ወእምዝ ተልዕለ ፀሐይ ወቆመ እስከ ተአቱ ይእቲ ብእሲት ውስተ ቤታ ወእምድኅረዝ ትቤሎ እምይእዜሰ አከለከ ሑር ኀበ ተአዘዝከ ወይእተ ጊዜ ዐረበ ፀሐይ ወካዕበ እንዘ ሀለወት ይእቲ ብእሲት ውስተ ፈኖት ምስለ ብዙኅ ሰብእ መጽአ ዐቢይ ዝናም ወበረድ ወንጕድጓድ ወመብረቅ ወፀዓዕ ግሩም ወእምዝ ትቤሎሙ ይእቲ ብእሲት ለእለ ሀለዉ ምስሌሃ ሰብእ ለእመ ድኅንክሙ ዮም እምዝንቱ መዐት ግሩም ትገብሩኑ ተዝካራ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ::



## የቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ተአምር



፳ ይህን ካስረዳኝ በኋላ አራት ዓመት ተቀምጦ በአምስተኛው ዓመት በሰላም አረፈ እግዚአብሔር በመግሥተ ሰማይት ያሰርፈው በውነት ይደረግለት ይህም ነገር ተረሣ እሱም ለማንም አልተናገረም መዝገበ ሃይማኖት ካረፈ ሦስት ዓመት በሆነ ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ አነሣስቷት አንዲት እኅት እጽፍ ዘንድ አስገደደችኝ እኔ ይህን ነገር መዝገበ ሃይማኖት አስቀድሞ ነግሮኛል ነገር ግን አባቶቼ ስላላዘዙኝ እግዚአብሔር የፈቀደው ጊዜ ስላልደረሰ ሳልጽፍ ቆየሁ እሷም ለአባቶች እና ለማኅበሩ እመምኔቲቱ ነገረቻቸው እና ሱባኤ እና ቀኖና ይዘው ጠይቀው እንድጽፍ:ታዘዝሁ:ከዚህ:በኋላ :በእግዚአብሔር:ፈቃድ እና በእናታችን ቅድስት ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ረዳትነት ጻፍኩ አማላጅነቷ ከሁላችን ጋራ ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን::

### ፲፩ኛ ተአምር

፩ የእናታችን ቅድስት እና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ያደረገችው ተአምር ይህ ነው አማላጅነቷ ከሁላችን ጋራ ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይደረግልን::

፪ እናታችን ቅድስትና እና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስን የምትወድና ዝክሯን የምትዘክር ርብ የሚባል ወንዝ ማዶ የነበረች አንዲት ሴት ነበረች ከዕለታት በአንድ ቀን በጐዳና ስትሄድ ከቤተ ክርስቲያን ቆይታ ቤቷ ለመድረስ ረጅም ጐደና ሲቀራት ቀኑ መሸባትና:ፀሐዩ:ሊጠልቅ:ደረሰ:ያችም:ሴት አንተ ፀሐይ በእናታችን ቅድስት እና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ስም አማጽኛለሁ ካለህበት ቦታ ወደላይ ከፍ ብለህ ዳግመኛ ወጥተህ ቁምልኝ አለችው::

፫ ከዚህ በኋላ ፀሐይ ወደኋላ ተመልሶ ከፍ ብሎ ያች ሴት ወደ ቤቷ እስክትገባ ድረስ ቆመ:እሷም:ቤቷ:ከደረሠች:በኋላ ከእንግዲህ ወዲህስ ወደታዘዝህበት ሂድ አለችው:ያን:ጊዜ:ፀሐዩ:ጠለቀ:ዳግመኛም:ይህች:ሴት:ከብዙ:ሰዎች:ጋራ:በጐዳና:ሣለች:ታላቅ:ዝናብ:እና:በረዶ:ነጐድጓድ:እጅግ:የሚያስፈራ:የመብረቅ:ብልጭልጭታ:መጣ:ያችም:ሴት:ከሷ:ጋር:የነበሩትን:ሰዎች:ከዚህ:ድንገት:ከመጣብን የሚያስፈራ:መቅሠፍት:ብትድኑ:የእናታችንቅድስት:ቡርክት:ወለ ተጴጥሮስን:ዝክር ትዘክራላችሁን አለቻቸው::

፬ ወይቤልዋ ኦሆ ንገብር ወበፅዑ ኵሎሙ ብፅዓተ ሶቤሃ በ፩ ቃል ወይእተ ጊዜ ኃለፈ ዝናም እምኔሆሙ ወአማዕከሎሙ ወኮነ ይዝንም እንተ ቅድም ወእንተ ድኅር እንተ የማን ወእንተ ፀጋም ወወረደ በረድ ዐቢይ ወእሙንቱሰ ሰብእ ድኅኑ ወአተዉ ውስተ አበያቲሆሙ ወኢዘንመ ላዕሌሆሙ ዝናም ወኢነጠበ ግሙራ።

፭ ወኮነ ዝንቱ በጸሎተ እምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወሣልስ ተአምር ዘኮነ ውስተ ይእቲ ቤት ወበ፩ እምዋዕል ተአንገዳ ኀቤሃ አኃት እለ ውስተ ማኅበር ዘእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ወተወክፈቶን ይእቲ ብእሲት ወአሰበጠቶን ኅብስተ ወሀሎ ፩ሰዋ ውስተ ቤታ ወአልቦ ካልእ ዘእንበሌሁ ወእንዘ ትብል ሐለየት ለጌሠም ለእመ መጽአ ዘየዐቢ እንግዳ ቈቀየቶን ወኢወሀበቶን ወአስተየቶን ማየ ኑግ።

፮ ወበሳኒታ እምድኅረ ሖራ እማንቱ አኃት ዘምስለ እንግዳ አቅረብዎ ከመ ይስተይዎ ወኮነ ምሩገ ወሶበ አርሐ ውዎ በዕፁብ ግበር ተረክበ ዕራቆ ቀሱት ይቡሰ ከመ ዘኢለከፎ ሰዋ ግሙራ ወኢተዓውቀ ኀበ አይቴ ሖረ ውእቱ ሰዋ ወትቤ ይእቲ ብእሲት ዝንቱ ኃይል ዘእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ውእቱ ወሶበ ርእየቶ ለቀሱት እምላዕሉ እስከ ታሕቱ ኢተሰጥቀ ምንተኒ።

፯ ወበእንተዝ አእመረት ከመ ዝንቱ ኃይል ዘእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ውእቱ ወአምነት ለሊሃ በአፉሃ እንዘ ትብል እስመ ገፋዕክዎን ለእማንቱ አኃት አዋልዲሃ ተገብረ ላዕሌየ ዝንቱ ተአምር ኦ ዝ መንክር ወዕፁብ ኃይለ ተአምሪሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ትንብልናሃ ወኃይለ ረድኤታ የሃሉ ምስለ ኵሎሙ ደቂቃ ወአዋልዲሃ ወምስለ እለ ጽሕቁ ወአስተሐመሙ ለጽሒፈ ዝንቱ መጸሐፍ ለዓለመ ዓለም አሜን ለይኩን ለይኩን ። ። ። ። ።

........................................................

ተፈጸመ መጽሐፈ ተአምራቲሃ ለእምነ ቅድስት ወቡርክት ወብፅዕት ወኂሪት ወለተ ጴጥሮስ ።





፬ እነሱም በአንድ ቃል እንዘክራለን ብለው ተሳሉ በዚያን ጊዜ ዝናቡ እነሱ ያሉበትን ትቶ ከፊታቸው እና ከኋላቸው በግራቸው እና በቀኛቸው ታላላቅ በረዶ እየቀላቀለ ይዘንብ ጀመር በረዶው ወርዶ ወርዶ ከመሬት ላይ ተከመረ እነዚያም ሰዎች ምንም:ዝናብ: :ሣይነካቸው:ከዝናብ:ድነው:በሰላም:ወደ:ቤታቸው:ገቡ።

፭ ይህም የተደረገው በእናታችን ቅድስት እና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ጸሎት ነው በዚች ሴትዮ ቤት ሦስት ጊዜ ተአምር እንደተደረገ ይነገራል ከዕለታት በአንድ ቀን የእናታችን ቅድስትና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የአንድነት ማኅበር እኅቶች ወደ እሷ ቤት እንግድነት ሄዱ ያችም ሴት ተቀበለቻቸው እና ምግብን ሠጠቻቸው አነስ ባለ እንስራ በቤቷ ውስጥ ጠላ ነበር ያለሱ ጠላ አልነበረም ከነሱ የሚበልጥ እንግዳ ይመጣብኛል ብላ ነፈገቻቸው እና ሳትሰጣቸው ቀርታ የኑግ ውሀ በጥብጣ አጠጣቻቸው።

፮ በማግስቱ እነዚያ እኅቶች መነኮሳይያት ከሄዱ በኋላ ከእንግዳ ጋር ይጠጡ ዘንድ አቀረቡት የጠላውም ክዳን አልከፈትም አለ በግድ በከፈቱት ጊዜ ምንም ጠላ አልተገኘም ወዴት:እንደሄደም:አልታወቀም:ያችም:ሴት:ይህ:ተአምር:የእናታችን:ቅድስት:ቡርክት:ወለተ:ጴጥሮስ:ተአምር:ነው:ብላ:እንሥራውን:እየገለባበጠች:ከላይ:እስከ:ታች:ብትመለከት:ምንም:የመሠንጠቅ:እና:የመሠበር:ምልክት:አልተገኘበትም።

፯ ስለዚህ ይህ ኃይል የእናታችን ቅድስት እና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ድንቅ ሥራ ነው ብላ እሷ እራሷ በአፏ የእሷን ልጆች እኅቶች መነኮሳትን ስለበደልኳቸው ይህ ተአምር በእኔ ላይ ተደረገ ብላ መሰከረች የእናታችን ቅድስት እና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ የተአምራቷ ኃይል ምን ይደንቅ ምን ይረቅ አ ወዮ እንደምን ያለ ረቂቅ ነው ለዚህ አንክሮ ይገባል አማላጅነቷ እና የረዳትነቷ ኃይል ይህን መጽሐፍ ከጻፉ ከተረጐሙ ካነበቡ ከሰሙ ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይሁን ይደረግልን የእናታችን ቅድስት እና ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ መጽሐፍ እዚህ ላይ ተፈጸመ አነሣሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለቸሩ እግዚአብሔር ምስጋና ይገባል ንጽሕት እና ከሁለት ወገን ድንግል የምትሆን እናታችን ጽዮን ማርያምንም ምስጋና ይገባታል ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙም አሜን።የእናታችን ገድል በእዚህ ተፈጸመ

በስመ እግዚአብሔር ሕያው ዘእምቅድመ ዓለም
መንግሥቱ:: እንዘ በአካላት ሠላስ ወዋሕድ በመለኮቱ።
ለዝ አምላክ ወለተ ጴጥሮስ አመቱ:: አርትዒ ቃለ አፉየ
እስመ ድኩመ ኃይል ውእቱ:: ውዳሴ መልክዕኪ እንብብ
ወእትናገር ቦቱ::

ሰላም ሰላም ለዝክረ ስምኪ ሰላም:: እምአስካለ ወይን
ጥዑም:: ወለተ ጴጥሮስ በጸጋ ወላዲተ ኵሉ ዓለም::
እስመ ይቤሉኪ ካህናተ የማን ወጽግም ለባርኮቶሙ ንዒ
እምልዑል አርያም::
ሰላም ለሥዕርትኪ ወለርእስኪ ዘተቀጸለ ዘትሩፋኑ ገድል
ጻድቃን ወዘሰማዕታት አክሊለ ወለተ ጴጥሮስ ዜናኪ እም
አርእስተ አድባር ተልዕለ ቦ ጊዜ ኀበ መሀርኪ ወንጌለ::
ወቦ ጊዜ ዘጾርኪ መስቀለ ::
ሰላም ለገጽኪ ዘተገልበበ በግርማ:ወለቀራንብትኪ ኪሩብ
ዘመልዕልተ አዕይንት ተሰይማ: ወለተ ጴጥሮስ
እንቶሙ ለመላእክተ ኃይል ዘራማ: ታስተበፅዓኪ በአእጋረ
ኃሤትቀዊማ: መቃብረ ቅዱስ ሥጋኪ ደብረ ፍቅር ሬማ::

ሰላም ለአዕይንትኪ ዘኢነጸራ በፍትወት: መንገለ ኃላፊ
ንብረት ወለተ ጴጥሮስ ፀሐይ ኵናኒተ ዓለም
መዓልት:ተበሀሉ በ ዕረፍትኪ ትጉሃነ ሰማይ ኃይላት ነያ
ሠናይት ነያ ሠናይት: ሰላማዊት ነያ ሠናይት::
ሰላም ለአእዛንኪ ርኅዋተ እለ ኮና ገድለ ቅዱሳን
ያጽምአ ወዘሰማዕታት ዜና: ወለቱ ለጴጥሮስ ጸዋሪተ
ሐዲስ ቀኖና: ክድንኒ በረድኤትኪ ወጸልልኒ ጥዒና:ከመ
ይጼልሎ ፍጹመ ለሰማይ ደመና::
ሰላም ለመላትሕኪ ዘስነ ቂሐቶን ሮማን:ወለአዕናፍኪ
ሰላም አናቅጸ ምዑዝ ዕጣን:ወለተ ጴጥሮስ እሞሙ
ለአእላፈ ተስፋ ጻድቃን: ሀብኒ ልብሰ ሞገስ እንተ
የዓውዶ ብፅዓን:ወነጽሮቶ ጥዩቀ ዘኢይክል ዓይን::
ሰላም ለከናፍርኪ ዘልምላሜሆን መንክር:ወለአፉኪ ሰላም
ነባቤ መለኮት ክቡር:ወለተ ጴጥሮስ ኬፋ ብእሲተ ሰላም
ወፍቅር: ለኢየሩሳሌም ሬማ እግዝእተኵሎን
አህጉር:አናቅጺሃ ዕቀቢ ኢይባእ ነኪር::



ሰላም ለአስናንኪ ጽዕድዋት ከመ ሐሊብ ወለልሳንኪ
ዕፍረት በውሣጤ አፍ ዝጉብ:ወለተ ጴጥሮስ እሌኒ
ንግሥተ አሕዛብ ወሕዝብ:ሕሊናኪ ሶበ ኃሠሠ መስቀለ
ኢየሱስ ዘዓርብ:መንገለ ሀሎ መካን መርሐኪ ጥበብ::
ሰላም ለቃልኪ ነጐድጓደ ስብሐት ዘአንጐድጐደ: ለወላዴ
ዓለም ክርስቶስ እንተ እማርያም ተወልደ: ወለተ ጴጥሮስ
ኃይልኪ ዘኃይለ አጋንንት ሰደደ:ይዝርዎሙ ለአጽራርየ
እለ መከሩ እበደ:ከመ ኃይለ ነፋስ ጽኑዕ ይዘሩ ሐመደ::
ሰላም ለእስትንፋስኪ ዘመዓዛሁ ዕፍረት:ወለጕርዔኪ ሰላም
ሰዋስወ ንጹሕ ጸሎት: ትምክህተ እስራኤል ኵሎሙ
ወለተ ጴጥሮስ ዮዲት ለፀርየ ሆሎፎርኒስ ኀበ ይነውም
በግብት ጕንደ ክሳዱ ምትሪ በስሑል መጥባሕት::

ሰላም ለክሳድኪ ዘአርማስቆስ አምሳሉ: ወለመታክፍትኪ
ዕሩቃት እምልብሰ ትዕቢት ኵሉ: ወለተ ጴጥሮስ ዝክርኪ
ለትውልደ ትውልድ ይሄሉ: አብዳን በጥበብኪ ሰማየ
ልቡና ተልዕሉ: ወበጸሎትኪ ነዳያን ብዕሉ::
ሰላም ለዘባንኪ ሰንዱነ ሃይማኖት ዓጽፉ ወሰላም ካዕበ
ለእንግድዓኪ ሱታፉ: ለሊቀ ካህናት ክርስቶስ ወለተ
ጴጥሮስ ርእሰ መጽሐፉ ብዙኃን በተግሣጽኪ ነገረ ዝንጋዔ
ገደፉ: ወአንቀጸ መስቀል ጸባበ በትፍሥሕት ኃለፉ::

ሰላም ለሕፅንኪ ታቦተ ትእዛዝ ዓስር: ወለአጥባትኪ
ምንትዋት አፍላጋተ ጥበብ ወምክር: ወለተ ጴጥሮስ
ማርታ እኅተ አልዓዛር ፍቁር: ሠናይ ተልእኮትኪ
ለእግዚአ ኵሉ ብሔር:ናሁ ተጽሕፈ በሰማይ ወምድር::

ሰላም ለአእዳውኪ ምስለ መዛርዕ ወኵርናዕ: እለ ስፉሐት
ለጸልዮ በጊዜ ሰዓታት ሳብዕ: ወለተ ጴጥሮስ ማኅፈድ
ምስካየ ብእሲ ግፉዕ: አድኅንኒ በረድኤትኪ እምሰብአ
ምንሳዌ ወፀብእ:እስመ በጻድቅ ይድኅን ኃጥእ::
ሰላም ለእመትኪ ዘተሞቅሐ በኃዒን: በእንተ ኢየሱስ
ክርስቶስ በዓውደ ጲላጦስ ኩኑን: ወለተ ጴጥሮስ ምስካይ

ወለተ ጴጥሮስ ጸወን፡ተሰደ ኃይለ ጽልመት በስነ ጽድቅኪ ብርሃን፡ወዕውራነ ልብ ነጸሩ እምርሑቅ መካን፡፡

ሰላም ለእራኃትኪ ለውኂበ ምጽዋት ዘሰፍሓ፡ወለአፃብዕኪ ዓሥር ለቤተ ክርስቲያን ማኃትዊሃ ለኅዙናነ ልብ ኵሎሙ ወለተ ጴጥሮስ ወይነ ፍሥሓ፡ጸሎትኪ ገባሬ ኃይል ማእሰረ ሕማማት ፈትሐ፡ ወብእሴ ምውተ እሙታን አንቅሀ፡፡

ሰላም ለአጽፋረ እዴኪ ዘጽዕዳዌሆን ኀብረ በረድ፡ ወለገቦኪ ርጉዝ በኵናተ ፍቅሩ ለወልድ፡ርእሰ ዕለታት ሳብዕ ወለተ ጴጥሮስ እሑድ፡ይኩነኒ ጸወነ ነፍስ ረድኤትኪ ማኅፈድ እስመ እም ንእስየ አነ ዘዚአኪ ወልድ፡፡

ሰላም ለከርሥኪ ዘተሴሰየ ሐመደ፡ወለልብኪ ንቁህ ርእሰ ዝንጋዔ ዘኬደ ወለተ ጴጥሮስ ጸጋኪ እምጸጋ ቅዱሳን ፈድፈደ፡ባርኪ ማኅበረነ እንዘ ታነሥኢ እደ፡ እስመ በሕማም እኩይ ደወየ ወውሕደ፡፡

ሰላም ለኵልያትኪ ዘግልባቤሆን ትዕግሥት ወለሕሊናኪ ጽሩዕ እምሐልዮ በቀል ወቅንአት፡ወለተ ጴጥሮስ እኅቶሙ ለጻድቃነ ሐዲስ ወብሊ ት ዕቀቢ እግረ ነፍስየ እመሳግሪሁ ለሞት፡ እስመ ብእሲተ ኃይል አንቲ ወአነ ትሑት፡፡

ሰላም ለአማዑትኪ በእሳተ ፍቅረ ሰብእ ውዑይ፡ ወለንዋየ ውስጥኪ ሥጡም ውስተ ባሕረ ኂሩት ቀላይ፡ ወላዲተ አእላፍ ከዋክብት ወለተ ጴጥሮስ ሰማይ፡ ለፀርየ ብእሴ ዓመፃ መሠረተ ኵሉ እከይ፡ እንዘ ቀትረ መዓልት በቅድሜሁ ኢያብርህ ፀሐይ፡፡

ሰላም ለሕንብርትኪ ማእከለ ሥጋ ግብረቱ ወለሐቌኪ ሰላም ሐብለ መንፈስ ቅዱስ ቅናቱ፡ለዕፀ ገነት አቡኪ ወለተ ጴጥሮስ ጽጌ ትርሲቱ፡ኪያኪ በእንቲአሁ ነገደ መላእክት አእኰቱ፡ ወበስነ ምግባር ዘዚአኪ ወደስዎ ሎቱ፡፡

ሰላም ለአቍያጽኪ ምስለ አእጋር ወአብራክ፡ እለ አርትዓ ቀዊመ ቅድመ ገጸ ዋሕድአምላክ፡ለባሲተ ሞገስ ወጸጋ ወለተ ጴጥሮስ ሐሪክ፡ዕቀብኒ በትንባሌኪ ለለ ጊዜ ጽባሕ ወሠርክ፡እምግዙፈ ክሳድ ፀርየ ዘልቡ ድሩክ፡፡

ሰላም ለሰኳንውኪ እምፍኖተ ጥበብ ዘአድኀፃ ወለመከየድኪ ሰላም ዘኢዓርጋ ደብረ ዓመፃ፡ወለተ ጴጥሮስ ኪያኪ እለ አጥረዩ በዕፃ፡ ፈድፈደ ትፍሥሕቶሙ



እምትልቄ ከዋክብት ውኖፃ፡ወሀገረ ሕይወት ወረሱ ዘአምላክ ሐነጻ፡፡

ሰላም ለአፃብዕኪ ወለአጽፋርኪ ልጹቃት፡ ዘኢያዕቀፎን ምንተ እብነ ኃጢአት፡በአክሊለ መስቀል ዘዓርብ ወለተ ጴጥሮስ ክልልት፡ ይብልያሙ ለአጽራርየ ረድኤትኪ እሳት፡እስመ በልቦሙ ሀለወት እኪት፡፡

ሰላም ለአካለ ቆምኪ ተመሳሌ ዓርዝ ዘሊባኖስ፡ ወለመልክዕኪ ግቡር በአርአያ ሥሉስ ቅዱስ፡ ወለቱ በጸጋ ለሊቀ ካህናት ሐዲስ፡ታንጽሕኒ በትንባሌኪ እምርስሐተ ሥጋ ወነፍስ፡አስተበቍዓኪ ወልድኪ ንኡስ፡፡

ሰላም ለፀአተ ነፍስኪ እምደብተራ ሥጋ ማሳኒ፡ ምስለ ሲኖዳ ተሀሉ ወምስለ አፈ ወርቅ ዮሐኒ፡እመንገለ ኂሩት ወጸጋ ለዘወለድክኒ፡በትረኪ ወመስቀለኪ ወለተ ጴጥሮስ ሁብኒ፡፡ በጊዜ መከራ ረድኤተ እማንቱ ይኩናኒ፡፡

ሰላም ለበድነ ሥጋኪ በማየ ንስሐ ሕጹብ ወለግንዘትኪ ሰላም በእደ ኅሩያን አርጋብ እኅተ ደናግል ኃምስ ወለተ ጴጥሮስ ጠባብ፡ኢይትአፀው በላዕሌኪ ጽርሐ ሰማያዊት ከብካብ፡ እመ መርዓዊ ይመጽእ በስብሐት ዕፁብ፡፡

ሰላም እብል ዘዚአኪ መቃብረ፡ቅድመ ዕረፍትኪ ይብጻሕ ኀበ እዴኪ አመረ፡ለወለተ ጴጥሮስ አስቴር ሃይማኖትኪ ዘከብረ ፡እንዘ ሥርወ ሰግላ ይመልሕ ወእንዘ ያፈልስ ደብረ፡ኵሉ ዘርእየ አንክሮ አንከረ፡፡

ፍዳ አቅረብኩ ሰላመ ለመልክዕኪ ክቡር፡በዘአክሀለኒ ሌተ እግዚአብሔር፡ ወለተ ጴጥሮስ እምየ ዘወለድክኒ በፍቅር፡አግዕዝኒ በጸሎትኪ እምቅኔ ኃጢአት ሙፋር እስመ አግዕዞቶ ትፈቅድ እግዝእት ለገብር፡፡